አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

# ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ

በ

አስቴር ሙሉ

መጋቢት፣ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በአስቴር ሙሉ

አማካሪ፡- ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)



መጋቢት፣ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ** በሚል ርዕስ በ ፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በአስቴር ሙሉ ተወልደ በመጋቢት 2007 ዓ.ም. የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪ፡- **ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)** ፊርማ ________________

የውጪ ፈታኝ፡- **ተስፋዬ ዳኛው (ዶ/ር)** ፊርማ ________________

የውስጥ ፈታኝ፡- **ሙሉ እመቤት ዘነበ ዶ/ር** ፊርማ ________________

# ማረጋገጫ

ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብሁት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምሁባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም____________________________ ፊርማ ________________ቀን________________

# ምስጋና

ጥናቴን በማረም፣ በትጋት እንድሰራ በማበረታታት፣ በወቅቱ ለፈተና እንድቀርብ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ጥናቱ ለፍፃሜ እንዲበቃ ያገዙኝን አማካሪዬን ዶክተር ፈቃደ አዘዘን እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

በዚህ የትምህርት መርሃ ግብር እንድማር የላከኝ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ለትምህርቱ ማካሄጃ ላፕቶፕ ሰጥቶኛል፣ ሙሉ ደሞዜን እየከፈለ አስተምሮኛል፣ መጠነኛ የገንዘብ ድጎማ አድርጎልኛልና ያለኝ ምስጋና ከፍተኛ ነው፡፡ በመርሃ ግብሩ እንድማር ዕድሉን የሰጠኝ እንዲሁም ለጥናቱ ማካሄጃ የሚሆን መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲንም አመሰግናለሁ፡፡

በመስክ ቆይታዬ መረጃ በመስጠት ጥናቱ እንዲሳካ ቀና ትብብር ያደረጋችሁልኝ በአባሪው ክፍል ስማችሁ የተዘረዘረው መረጃ አቀባዮቼ ያለእናንተ ድጋፍ ይህ ጥናት ሊደረግ አይችልም ነበርና እጅግ ባለውለታዎቼ ናችሁ፡፡

መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተንዝሁባቸው ቦታዎች አብራችሁኝ ተጉዛችሁ የመስክ ዕቃዎችን ሸክም በማገዝ፣ በእግር መንገዱ አለመመቸትና ርቀት ተስፋ እንዳልቆርጥ በመምከርና በማበረታታት፣ ባጋጠሙኝ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሁሉ አብራችሁኝ በመሆን እገዛችሁን ያደረጋችሁልኝ መንገድ መሪዎቼና ረዳቶቼ ሰመረ ከበደ፣ ተስፋዬ እሸቴ፣ ሙሐመድ ሁሴን፣ አሸናፊ መኮንን፣ ሙሐመድ ፈንታሁን፣ ወይንሸት አሊ እና ቃልኪዳን ሙሉጌታ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

አቶ አሰፋ ለገሰና አቶ መላኩ መድፉ ከመረጃ መስጠት በተጨማሪ መንገድ መሪ ሆናችሁኝ ነበርና ለድርብ እርዳታችሁ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ ጋሽ አሰፋ ለገሰ በአንተ ዕድሜ ለሚገኝ ሰው እንኳን ሊሞከር ሊታሰብ በማይችለው የደረቅ ወይራ መንገድ አብረኸኝ ተጉዘህ ጠንክሬ እንድሰራ ምሳሌ ሆነኸኛል፡፡ በህይወቴ ሁሉ ሳመሰግንህ እኖራለሁ፡፡

ወሎ ውስጥ የሚገኙ የአዝማሪ መንደሮችን ፍለጋ ባደረግሁት ጥረት ጥቂት መንደሮችን የጠቆሙኝንና ምን ማድረግ እንደሚገባኝ የመከሩኝን ፍራንሲስ ፋልሴቶ በአድካሚው የመንደር ፍለጋ ስራ ውስጥ መከተል ያለብኝን ፈለግ እንዳስብበት ረድተውኛልና አመሰግናለሁ፡፡

በርዕሱ ዙሪያ የተፃፉ ጥቂት የማይባሉ ቀደምት ጥናቶችን የያዙ ‹‹አርቲክሎችን›› እና መፅሃፎችን የሰጡኝ ፕሮፌሰር ዴቪድ ኢቫንስ፣ ላገኛቸው የማልችላቸውን መፅሃፎች እንዳገኝ

ስለረዱኝና ‹‹አርቲክሎችን›› በመፈለግ አጠፋ የነበረውን ጊዜ በእጅጉ ስላተረፉልኝ አመሰግንዎታለሁ፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ የምሄድባቸውን ቦታዎች አስቀድሞ በማመቻቸት፣ የሚረዱኝን ሰዎች በማገናኘት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳገኝ በማገዝና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ አቅማችሁና ሁኔታው በፈቀደው መጠን ያደረጋችሁልኝን አቶ አፈወርቅ ተፈራ፣ አቶ ሃይሉ ታደሰ፣ አቶ በላይነህ ኃይሉ፣ አቶ አሰፋ አበጋዝ፣ አቶ ታደሰ አበጋዝ፣ አቶ አንድነት ሰብስቤ፣ አቶ መለሰ አያሌውና የአምባሰል ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈት ቤት ሰራተኞች በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ይህንን ጥናት በማደርግበት ጊዜ ከጎኔ ሆናችሁ ስታበረታቱኝ የነበራችሁትንና አስፈላጊውን እገዛ አቅማችሁ በፈቀደ መጠን ያደረጋችሁልኝ ቤተሰቦቼ እህቴ ኢትዮጵያ ሙሉ፣ ባለቤቴ ዮናስ ምትኩ፣ ወንድሜ አገሩ ሙሉ፣ ወንድሜ ተስፋ ሙሉና ባለቤቱ ገነት ማሞ በእጅጉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በማህበራዊና ‹‹አካዳሚያዊ›› ህይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለሽ ጓደኛዬ ስንቅነሽ አጣለ ያለምንም መልስ ጥበቃ ስለፍቅር ብቻ ላደረግሽልኝ እገዛ የማመሰግንበት ቃል የለኝም፡፡

ጋሽ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በመምህርነትህ፣ በርትቼ እንድሰራ በመምከርና በማገዝ፣ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ባለህ ሃላፊነት ደግሞ ከትምህርት ክፍሉ የምፈልጋቸውን ድጋፎች ሁሉ በጊዜው እንዳገኝ እያገዘሽኝ ጥናቴን በወቅቱና በጥሩ ሁኔታ እንድሰራ ስለረዳኸኝ በእጅጉ አመሰግንሃለሁ፡፡

የጥናት ፅሁፌን ስፅፍ የምቀመጥበት ቢሮ በመፍቀድ፣ ለፅህፈት የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች በመስጠትና እንድበረታ በመምከር የረዳችሁኝ የቀድሞ መምህሮቼና የአሁን የስራ ባልደረቦቼ ተሾመ ይመር (ረ.ፕሮፌሰር) እና አንተነህ አወቀ (ዶ/ር)፣ ጓደኛዬ ሂሩት አድማሱ ምንጊዜም ሳመሰግናችሁ እኖራለሁ፡፡

## ማውጫ


ምስጋና ........................................ I

ማውጫ ........................................ III

የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ VII

ሙዳዩ ቃላት ........................................ VIII

አጠቃሎ ........................................ XI

1. መግቢያ ........................................ - 1 -

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ - 1 -
1.2. ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች ........................................ - 3 -
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........................................ - 6 -
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................ - 6 -
1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ - 7 -
1.6. የጥናቱ ስነምግባር ........................................ - 7 -
1.7. በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች ........................................ - 8 -
1.8. በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........................................ - 10 -

2. ክለሳ ድርሳናት ........................................ - 11 -

2.1. የፅንሰሃሳብ ማዕቀፎች ........................................ - 11 -
2.1.1. ቡድን [ፎክ] ........................................ - 11 -
2.1.2. ልምድ (Tradition) ........................................ - 12 -
2.1.3. ተከታታይነት (Continuity) ........................................ - 14 -
2.1.4. ለውጥ (Change) ........................................ - 14 -
2.1.5. ሃገረሰባዊ ሙዚቃ (folk music) ........................................ - 16 -
2.1.6. ሙዚቃና የሰው ልጅ ባህርይ ........................................ - 18 -
2.1.7. ሃገረሰባዊ ሙዚቀኞች ........................................ - 21 -
2.1.8. አዝማሪ ምንድን ነው? ........................................ - 25 -
2.1.9. የአዝማሪዎች አመጣጥ ........................................ - 32 -
2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ ........................................ - 39 -

3. የአጠናን ዘዴ ........................................ - 54 -

3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................ - 54 -
3.1.1. ምልከታ ........................................ - 54 -
3.1.2. ቃለመጠይቅ ........................................ - 55 -
3.1.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ........................................ - 59 -
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎችና የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ ........................................ - 60 -
3.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ........................................ - 62 -
3.3.1. ክዋኔያዊ የመረጃ ንድፈ ሃሳብ (Performing theory) ........................................ - 62 -
3.3.2. ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ (Marxist theory) ........................................ - 66 -

3.3.3. “የአስከሳቢ ቡድኖች ጊዜ መራሽ ፍላጎት እና የከሳቢ ቡድን አላባመር ተከተል አካሄድ ውጤት [በስራ ቡድኖች የተከታታይነትና ለውጥ ልምድ” ጥናት]............- 68 -

4. የወሎ አካባቢ መልክዓምድራዊ ገፅታ፣ የማህበረሰብ መልክና የዘፈን ባህል አጠቃላይ ቅኝት ..........................................................................................- 74 -

4.1. አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ ..........................................................- 74 -
4.2. የማህበረሰቡ አጠቃላይ ገፅታ.................................................................- 75 -
4.2.1. የአስተዳደር መልክ .........................................................................- 76 -
4.2.2. መተዳደሪያና ልዩ ባህላዊ መገለጫዎች...................................................- 84 -
4.3. የወሎ ማህበረሰብ የዘፈን ባህል አጠቃላይ መልክ ........................................- 86 -

5. የመስክ ልምድ ...................................................................................- 90 -

5.1.ቅድመ መስክ ዝግጅት ..........................................................................- 90 -
5.2. የመስክ ውሎ .....................................................................................- 91 -

6. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ...................................................................- 112 -

6.1. ተከታታይ የኑሮና የዘፈን ልምዶች በወሎ አዝማሪዎች ህይወት .......................- 112 -
6.1.1. ለአዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች...........................- 113 -
6.1.1.1. አሰፋፈር.......................................................................- 113 -
6.1.1.2. የእርስ በእርስ ዝምድና ......................................................- 119 -
6.1.1.3. የሰርግ ስርዓት ................................................................- 125 -
6.1.1.4. ፆታዊ የስራ ክፍፍል...........................................................- 131 -
6.1.1.5. ሃይማኖት.......................................................................- 136 -
6.1.1.6. የሚስጥር ቋንቋ ................................................................- 138 -
6.1.1.7. ማህበራዊ ደረጃ................................................................- 145 -
6.1.1.7.1.አዝማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ማህበራዊ ...........- 146 -
ግንኙነት ............................................................................- 146 -
6.1.1.7.2. አዝማሪዎች ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት ............................- 149 -
6.1.1.7.3. አዝማሪዎች ለሌላው ሰው ያላቸው አመለካከት..........................- 152 -
6.1.1.7.4. ሌላው ማህበረሰብ ስለአዝማሪዎች ያለው አመለካከት ................- 155 -
6.1.1.7.5. ማህበራዊ ደረጃ በአዝማሪዎች መካከል .................................- 158 -
6.1.2. በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ..................- 162 -
ልምዶች.................................................................................- 162 -
6.1.2.1. የዘፈን ግንዛቤ ................................................................- 162 -
6.1.2.2. የዘፈን ለመዳና ተስተላልፎ ..................................................- 164 -
6.1.2.3. የዘፈን መልክ...................................................................- 172 -
6.1.2.3.1. ቅኝቶች ......................................................................- 173 -
6.1.2.3.2. የቅኝቶች ቅደም ተከተል ...................................................- 179 -
6.1.2.3.3. ግጥሞች.......................................................................- 182 -
6.1.2.3.4. የግጥሞች ደረጃ..............................................................- 186 -
6.1.2.4. የዘፈን መከወኛ አውዶች......................................................- 187 -

6.2. በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ባህል ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች ...........- 213 -
6.2.1. በአዝማሪዎች ኑሮ ውስጥ የተከናወኑ ለውጦች....................................- 213 -
6.2.1.1. ከህዝብ ጋር መቀላቀል..............................................................- 213 -
6.2.1.2. የቡድኑ አሰፋፈር.....................................................................- 219 -
6.2.1.3. የገቢ ምንጭ ለውጥ ...................................................................- 220 -
6.2.1.4. የጋብቻ ልምድ .........................................................................- 222 -
6.2.2. በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ የተከሰቱ......................- 224 -
ለውጦች ........................................................................................- 224 -
6.2.2.1. የዘፈን አከዋወን ደንብ ..............................................................- 225 -
6.2.2.2. የዘፈን መከወኛ አውዶች.............................................................- 227 -
6.2.2.3. የግጥሞች ይዘትና ቅርፅ ..............................................................- 231 -
6.2.2.3.1. የግጥሞች ይዘት ለውጦች .......................................................- 232 -
6.2.2.3.2. የግጥሞች ቅርፅ ለውጦች ........................................................- 246 -
6.3. ለወሎ አዝማሪዎች ኑሮና ዘፈን ልምድ መለወጥ ዋና ዋና..............................- 250 -
ምክንያቶች .........................................................................................- 250 -
6.3.1. የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከት ..........................- 250 -
6.3.2.የመንግስታት ርዕዮተ ዓለም ለውጥ ........................................................- 252 -
6.3.3. የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት............................- 258 -
6.4. የወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ........................................................- 260 -
6.4.1. በዘፋኝነት የሚተዳደሩ ..................................................................- 261 -
6.4.2. በገበሬነትና የመንግስት ሰራተኛነት የሚተዳደሩ....................................- 266 -
7. ማጠቃለያና ይሁንታ ...........................................................................- 269 -
7.1. ማጠቃለያ ..........................................................................................- 269 -
7.2. ይሁንታ ............................................................................................- 271 -
ዋቢዎች ...............................................................................................- 273 -
አባሪዎች ..............................................................................................- 285 -
አባሪ አንድ፡- የመረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ.............................................- 285 -
አባሪ ሁለት፡- የምርምር ጥያቄዎች .........................................................- 289 -
አባሪ ሶስት፡- ቃል ታሪክ (ከአንድ መረጃ አቀባይ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ) ...........- 295 -
አባሪ አራት፡ - ፎቶ ግራፎች ...................................................................- 302 -
አባሪ አምስት፡- ቃልግጥም .....................................................................- 308 -
አባሪ ስድስት፡- የድጋፍ መጠየቂያ ደብዳቤዎች .........................................- 311 -

# የስዕል ማውጫ


ስዕል 1. "እዝራና ዳዊት ለድንግል ማርያም እንደዘመሩ" ................ - 36 -

ስዕል 2. የአማራ ክልል ካርታ ................ - 82 -

ስዕል 3. ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች ................ - 83 -

ስዕል 4.የአዝማሪ ሰርግ፣ክትክታ መንደር ................ - 131 -

ስዕል 5. የመሰንቆ ክፍሎች ................ - 166 -

ስዕል 6. የመሰንቆ አቀማመጥ፣ኢላዳ ................ - 168 -

ስዕል 7. በመሰንቆ ጭራ ላይ ለአራቱ ቅኝቶች የጣቶች አቀማመጥ ................ - 176 -

ስዕል 8. አዝማሪዎች በመጠጥ ቤት፣ ኢላዳ ................ - 204 -

ስዕል 9. አዝማሪዎች በመጠጥ ቤት፣ ማርዬ ................ - 204 -

ስዕል 10. አዝማሪዎች ታቦት ሲመሩ፣ ማርዬ ................ - 206 -

ስዕል 11. ሴትና ወንድ አዝማሪዎች፣ኢላዳ ................ - 211 -

ስዕል 12. አዝማሪው በሰርግ ቤት፣ ኢላዳ ................ - 211 -

ስዕል 13. አኮርዲወን ................ - 216 -

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1. የወሎ አዝማሪዎች ሰፍረው የሚገኙባቸው መንደሮች .............................. - 116 -

ሰንጠረዥ 2. የአዝማሪ ‹‹ቋንቋ››/እንዛትኛ ቃላት ጥቂት ምሳሌዎች................................ - 143 -

ሰንጠረዥ 3. የአዝማሪ ‹‹ቋንቋ››/እንዛትኛ ሃረጋት ጥቂት ምሳሌዎች............................. - 144 -

## ሙዳዬ ቃላት

| ቃሉ (ሐረጉ) | ፍቺ (ትርጉም) |
|---|---|
| ላንቋ | ቋንቋ |
| መደለቅ | መጨፈር፣ መደነስ |
| ሙጫ | በዕድሜ ልጅ የሆነ |
| ማንፈፍ | በብዛትና ከስርዓት ውጪ መመገብ |
| ምርቃት | በቋንቋ የሚገለፅ በጎ ምኞት |
| ሙሀቻ | የእንጀራ ሊጥ ማስቀመጫ |
| ረጋ | አዝማሪ ያልሆነ |
| ርስት | ለአንድ ሰው በመንግስት የተሰጠ፤ ለልጅ የሚተላለፍ ቦታ |
| ርግማን | በቋንቋ የሚገለፅ ክፉ ምኞት |
| ሴት ወይዘሮ | የባላባት ሚስት |
| ሽልንግ | ሃምሳ ሳንቲም |
| ቀሚስ | አዝማሪዎች የሚለብሱት የማዕረግ ልብስ |
| ቅሬ | አዝማሪ |
| ቅራሬ | ዋናው ጠላው ተቀድቶ ከአተላው ላይ ውሃ ሲጨመር የሚገኘው ቀጭን ጠላ |
| ቡዳ | ሰውን የሚያጠቃ ክፉ መንፈስ ያረፈበት ሰው |
| ባላባት | የተወሰነ ቦታ የማስተዳደር ስልጣን ያለው ሰው |
| ባላገር | አራሽ፣ አዝማሪ ያልሆነ |
| ባሪያ | አገልጋይ |
| ተጫዋች | አዝማሪ |
| (አ)ተከሳቢ | አስዘፋኝ |
| ቱፍታ | የተከበሩ ሰዎች በሚመርቁበት ጊዜ በተመራቂው ላይ በስሱ የሚተፉት ምራቅ |
| ትልሚድ | ልምድ |
| ነቀዝ | እህል የሚበላ ተባይ |
| አለቃ | የሁሉም ሹሞች የበላይ |
| አርእስት | ጥልቅ ይዘት |
| አበልጅ | ህፃን ልጅን አደራ በመስጠትና በመቀበል የሚፈጠር ዝምድና |
| አባ ውዴ | ያለመሳሪያ አጀብ በድምፅ ብቻ እያዜሙ በየሃገሩ እየዞሩ የሚኖሩ ቡድኖች ስም |
| አጋፋሪ | ዘበኛ |
| እርዚቅ | ሃብት |

| | |
|---|---|
| ኮረፌ | በቤት ውስጥ የሚሰራ የመጠጥ አይነት |
| ከሳቢ | ዘፋኝ |
| ኮርቻ | ከብረት የተሰራ፣ ከፈረስ ጀርባ ላይ ሆኖ ፈረስ ጋላቢው የሚቀመጥበት ቁስ |
| ከጀለ | ፈለገ |
| ኮንትራት | በሰዎች መካከል የሚደረግ የስራና ክፍያ ስምምነት |
| ኸረጢት | ከጨርቅ የተሰራ የዕቃ መያዣ |
| ወልይ | ነብይ (የሚመጣን ነገር አስቀድሞ) የመተንበይ ስጦታ ያለው ሰው |
| የአዝማሪ ቤት | አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑበት መጠጥ ቤት |
| የእኛ ቤት ሰው | ከአዝማሪ የተወለደ |
| የአባት ስራ | ከቤተሰብ የተወረሰ ስራ |
| የእዝራ ልጆች | አዝማሪዎች |
| ደርግ | ከ1967 ዓ.ምእስከ1982 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ የነበረ ወታደራዊ አስተዳደር |
| ደደሆ | የዛፍ አይነት |
| ደጃች(ደጃዝማች) | ራስ ተብሎ ከሚጠራው ማዕረግ በታች የሚገኝ የጦር ማዕረግ አይነት |
| ደጃፍ | በር |
| ዱብርቲ | መንፈሳዊ ክብር ያላቸው ሴቶች |
| ዱኣ | ፀሎት |
| ዳስ | ድግስ የተጠራ ሰው የሚመገብበት በቅጠላ ቅጠልና እንጨቶች የተሰራ መጠለያ |
| ድግስ | በዓላትን ምክንያት አድርጎ የሚዘጋጅ የምግብ ግብዣ |
| ጅል | የመሰንቆ ችሎታው ጥሩ ያልሆነ |
| ጋንፋር ጨው | ለዕቃ ግብይት ያገለግል የነበረ፣ ጠፍጣፋ ቅርፅ ያለው ጨው |
| ጎተራ | ከጭቃ የሚሰራ የእህል ማስቀመጫ |
| ጎጥ | መንደር |
| ጥሊያን | ኢጣሊያ |
| ጭራ | መሰንቆ |
| ጭፈራ ቤት | በአብዛኛው በማታ የሚሰሩ ሰው ለመጠጣትና ለመዝፈን፣ ዘፈን ለማየት የሚሄድባቸው መጠጥ ቤቶች |
| ፈን | ዕድል |

## የቃላት ትርጉም አጠቃቀም ገለፃ

### ልምድ፡-

በዚህ ጥናት ውስጥ ልምድ የሚለው ቃል ያገለገለው የፎክሎር ምሁራን በእንግሊዝኛ ቋንቋ Tradition የሚሉትን፣ በፎክሎር እሳቤ ውስጥ የአንድ ቡድን ዕውቀትና ዕውቀቱ የሚተላለፍበትን መንገድ (ኢመደበኛነት) የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ለመጥራት ነው።

### ንድፈሃሳብ፡-

በዚህ ጥናት ውስጥ ይህ ቃል ያገለገለው ለመረጃ መተንተኛ ሆነው የገቡ የመተንተኛ ዘዴዎችን ለመጥራት ሲሆን በእንግሊዝኛ ቋንቋ Approache የሚለውን ቃል ይተካል።

### የፅንሰሃሳብ ማዕቀፎች፡-

በዚህ ጥናት ይህ ቃል ለርዕሱ ዳራ የሆኑ ሃሳቦችን ለመጥራት የገባ ሲሆን አገልግሎት ላይ የዋለው theoretical background የሚለውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃል ተክቶ ነው።

### ጥንታዊና ቀድሞ፡-

እነዚህ ቃላት የሚገኙት በትንተናው ክፍል ነው። መረጃ ሰጪዎች በህይወት ያልኖሩበትን ነገር ግን በታሪክ የሚያውቁትን ከአፄ ሃይለስላሴ ዘመን በፊት ያለውን ጊዜ ለመጥቀስ የሚጠቀሙባቸው ናቸው። እኔም ያንን ዘመን ለማሳየት በሞከርኩባቸው ጊዜዎች ሁሉ ቃላቱን እንደመረጃ ሰጪዎቹ አጠቃቀም ተጠቅሜባቸዋለሁ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ለመሰራቱ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ለርዕሰጉዳዩ/ ‹‹ለአዝማሪ የዘፈን ልምድ›› ያለ ጥልቅ ስሜት፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በርዕሰጉዳዩ ላይ የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች ያሉባቸውን በወሎ አካባቢ መንደር መስርተው የሚኖሩ አዝማሪዎችን ያለማጥናት፣ አዝማሪዎችን ከራሳቸው ከአዝማሪዎች አቅጣጫ ሆነው አለመመርመርና ጊዜ በቡድኑ የአኗኗርና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ ግምት አለመክተት ክፍተቶችን የመሙላት አስፈላጊነት ናቸው፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማው የወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ነው፡፡ ይህ ዓላማ ግቡን እንዲመታ በስሩ የኑሮውና የዘፈን ልምዱ ምን ተከታታይ መልክ አለው? በልምዱ የተከሰቱ ለውጦች ምንድን ናቸው? ለለውጦቹ መከሰት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የአዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ምላሽ አግኝተዋል፡፡

ጥያቄዎችን ለመመለስ የረዱ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ የወሎ አዝማሪዎችን ይወክላሉ ተብለው ከተመረጡ፣ በረከት፣ ከድጆ፣ ደረቅ ወይራና ማርዬ ከተባሉ የአዝማሪ መንደሮች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ከስልሳ ስምንት የመረጃ አቀባዮች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መቅረፀ ድምፅ፣ የፎቶና የቪዲዮ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተር ደግሞ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሶች ናቸው፡፡ ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው፣ የጥናቱን መነሻ ሃሳብ የሚያጠናክሩ፣ ለጥሬ መረጃዎች ማነፃፀሪያና ማወዳደሪያ የሚሆኑ፣ ፅሁፎች ተፈትሸዋል፡፡ አስራ ስድስት ቀደምት ጥናቶች እንዲሁም የተለያዩ ፅንሰሃሳቦች ተቃኝተዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተሰበሰቡ ጥናቶች በአግባቡ ከተመረመሩ በኋላ ባስገኙት ተፈጥሯዊ ቅጥ ተመድበው በክዋኔያዊና ማርክሳዊ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

ከትንታኔው ወሎ ውስጥ የሚኖሩ አዝማሪዎች አሰፋፈራቸው፣ የእርስበርስ ዝምድናቸው፣ የሰርግ ደንባቸው፣ ሚስጥራዊ ቋንቋቸው፣ ሃይማኖታቸው፣ ፆታዊ የስራ ክፍፍላቸው፣ በመካከላቸው ያለው ማህበራዊ ደረጃ ከሌላው ቡድን የተለዩ እንዲሆኑ ያደረጓቸው ተከታታይ የኑሮ ልምዶች ናቸው፡፡ በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ልምድ ውስጥ በዘፈን ለመዳና ተስተላለፎ፣ በአከዋወን ስርዓት፣ በመከወኛ ቦታ ውስጥ ለዘመናት ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገሩ የኖሩ ልምዶች አሉ፣ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ በቡድኑ አሰፋፈርና በጋብቻ

ልማድ፣ በገቢ ምንጪ፣ በዘፈን አከዋወን ደንብ፣ በዘፈን መከወኛ አውዶች ላይ ለውጥ ተከስቷል፣ የመንግስት ርዕዮተዓለም ለውጥ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከትና የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሳሪያዎች ወደአካባቢው መግባት ለወሎ አዝማሪዎች ልምድ መቀየር ምክንያት ናቸው፣ አብዛኞቹ የወሎ አዝማሪዎች ከዘፈን የሚያገኙት ገቢ ለኑሮ የማይበቃቸው በመሆኑ ቀስ በቀስ ራሳቸውን ከዘፈን ስራ እያላቀቁ ሌላው የአካባቢው ነዋሪ በተሰማራባቸው ሌሎች ተግባራት ላይ በመሰማራት ላይ ናቸው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ከውጤቶች በመነሳት ለወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ባህላዊነቱን ጠብቆ ለመጓዙም ሆነ ለመለወጥ ዋና ምክንያቱ ቡድኑ በየዘመኑ ከዘፈን ስራው ያገኘው የነበረውና የሚያገኘው የገቢ መጠን ሁኔታ ነው ከሚል መደምደሚያ ተደርሷል፡፡

ከመደምደሚያው በመነሳት የፌዴራልና የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች አዝማሪዎች በክብረ በዓሎችና በፌስቲቫሎች አማካኝነት ገቢ እንዲያገኙ ቢያግዟቸው፣ ባህሉ በትምህርት ቤቶች ቢከወንና ጥናት ቢደረግበት፣ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ ለአካባቢው ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫና የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን ቢሰጥ፣ የሙዚቃ ባለሙያዎች በሙያው ላይ ትኩረታቸውን ቢያሳርፉ፣ የየወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈት ቤቶች ለወጣት አዝማሪዎች የመለማመጃና ስራ የማግኛ መንገዶችን ቢፈጥሩ፣ ቀጣይ አጥኝዎች የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ባህል ጥንታዊ መልኩን ጠብቆ ይኖር ዘንድ ድጋፍ የሚያደርጉ የተግባራዊ ፎክሎር ጥናቶችን ቢያደርጉ የሚሉ ይሁንታዎች ተሰጥተዋል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡- አዝማሪ፣ ዘፈን፣ ልምድ፣ ተከታታይነት፣ ተለዋጪነት**

# 1. መግቢያ

በዚህ ክፍል የጥናቱን መልክ የሚያሳዩ ሃሳቦችን የያዙ ንዑሳን ርዕሶች ቀርበዋል፡፡ ንዑሳን ርዕሶቹ፣ የጥናቱ ዳራ፣ ጥናቱን ለማድረግ ያነሳሱ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ስነምግባር፣ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎችና በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች የሚሉ ናቸው፡፡ ክፍሉ አጠቃላዩን ጥናት የማስተዋወቅ ተግባር ያለው ሲሆን ዝርዝር ሃሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

*"እዚያ ላይ አቃንቶ፣ እታች ሲመልሰው፤*
*እንዴት ባኗኗሩ አላውቅም ይላል ሰው"፡፡*

*(ማስረሻ ፈንታው፣ ማርዬ፣ 12/05/2005 ዓ.ም.)*

የዚህ ቃል ግጥም ከዋኝ ለጥናቱ መረጃ ከሰጡኝ መረጃ አቀባዮቼ አንዱ ናቸው፡፡ በወሎ ስላለው አዝማሪነት ጠቅላላ ታሪክ እንዲነግሩኝ ጠይቄያቸው "ድሮ እንዲህ ነበር፣ ዛሬ ደግሞ እንዲህ ነው" እያሉ የአዝማሪነት ህይወት በጊዜ ውስጥ የተጓዘውን መንገድ ሲገልፁልኝ ቆዩ፡፡ ጭውውታችን ሲያበቃ መሰንቆ እንዲጫወቱልኝ ጠየቅኋቸው፡፡ አምላክን በዜማ አመስግነው ጨረሱና ወደዘፈን ገቡ፡፡ ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም የዘፈን ዜማ መጀመሪያቸው ሆነ፡፡ ቃል ግጥሙ የያዘው ትርጉም በአውዱ ሲተረጎም "ከጥንት እስከዛሬ አዝማሪ ያለፈበትን መንገድ በመኖር አውቀዋለሁ"፡፡ የሚል መልዕክት አለው፡፡ ከቃል ግጥሙ አዝማሪነት በወሎ ረጅም ዘመን መኖሩንና በዚህ የረጅም ዘመን ዕድሜው ደግሞ አንድ ጊዜ ከፍ፣ ሌላ ጊዜ ዝቅ የሚያደርጉት ለውጦች መኖራቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ግጥሙ በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና ዘፈን ውስጥ ተከታታይነትና ለውጥ መሰረታዊ ባህርያት ሆነው መቆየታቸውን ይናገራል፡፡

የፎክሎር ምሁራን እንደሚሉት ተከታታይነት በጊዜ ሂደት ውስጥ የልምድን የማያቋርጥ ጉዞ የሚገልፅ ፅንሰሃሳብ ሲሆን ለውጥ ደግሞ በነበረ ተጨባጭ ሁነት ላይ ጊዜ የፈጠራቸውን ማሻሻያዎች፣ መተኪያዎችና ሁነቶች መፈጠራቸውን የሚያሳይ ፅንሰሃሳብ ነው (Sims and Stephens,2005) ተከታታይነትና ለውጥ በማንኛውም

ባህል ውስጥ የሚከሰቱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ባህል የአንድን ቡድን ማንነት የሚገነባው ረጅም ዘመን ውጤት በመሆኑ ነው፡፡ በረጅም ዘመን ውስጥ ማለፉ ተከታታይነት (ከትውልድ ትውልድ/ ከጊዜ ጊዜ ሽግግር) እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ተከታታይነቱ ግን በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈጠር ለውጥ ውስጥ የሚያልፍ እንጅ ፍፁም አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተከታታይነትና ለውጥ የማይለያዩ የባህል ገፅታዎች ናቸውና፡፡

የዚህ ጥናት ርዕሰጉዳይ በአዝማሪነት ህይወት ውስጥ ያለን ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ነው፡፡ የተለያዩ መረጃዎች እንደገለጡት አዝማሪነት በኢትዮጵያ ረጅም ዕድሜ ያለው ሙያ ነው፡፡ የሙያው ባለቤት የሆኑት አዝማሪዎች ዘፈንን የገቢ ምንጫቸው አድርገው ለዘመናት የኖሩ ‹‹ፎክ›› ቡድኖች ናቸው፡፡ ቡድኖቹ ገቢ ለማግኘት ሲሉ ዘፈንን[1] በተለያዩ አውዶች ሲከውኑ ኖረዋል፡፡ እንደዛሬው የቴክኒዮሎጂ ውጤት የሆኑት ቴፕሪከርደርና ቴሌቭዥን ወደሃገራችን ከመምጣታቸው አስቀድሞ፣ እንዲሁም ዘመናዊ የሙዚቃ ባንድ በሃገራችን ከመቋቋሙ በፊት ሰርግ፣ ክርስትናና የመሳሰሉ ማህበራዊ የደስታ መሰባሰቦች ያለአዝማሪ የዘፈን አጀብ አይታሰቡም፡፡ በዓሉን የማድመቅና ታዳሚውን በዘፈን የማስደሰት ስራ ለአዝማሪ የተተወ ጉዳይ ነበር (Ashenafi, 1971; Mesganaw,2010)፡፡

በአዝማሪ ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚሉት የአዝማሪዎች አገልግሎት በማህበራዊ ህይወት ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ አዝማሪዎች ዘፈንን ከሚከውኑበት ሰውን የማዝናናት ተለምዷዊ ተግባር ባሻገር በኢትዮጵያ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ነበራቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ Kimberlin (1983) እንደሚገልፁት ዘፈን ከኢትዮጵያ ህዝብ አኗኗር፣ ይትብሃልና ህይወት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ እንደ Ashenafi (1971) እና Teclehaimanot (1986) ትንታኔ አዝማሪዎች ዋና ስራቸው ማዝናናት ቢሆንም በተጨማሪ ግን ዜናና ታሪክ ነጋሪዎች፣ ሃያሲዎች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ መዝጋቢዎች፣ አዝማቾች፣ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ይሁንና ማህበረሰቡ የአዝማሪዎችን አገልግሎት ይፈልግ እንጅ እነሱን ንቆ እንደሚመለከታቸው፣ ‹‹አዝማሪ›› የሚለውን ስማቸውን ሳይቀር ለስድብነት

[1]የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበቃላት አለማዊ የሆነ ዘፈን፣ ዜማ፣ እንጉርጉሮ (1993፣ 443) ሲል ይበይነዋል፡፡ ቃሉ በወሎ አካባቢ ለሃገረሰባዊ ሙዚቃ መጠሪያ ያገለግላል፡፡ ማህበረሰቡ የራሱንም ሆነ የአዝማሪ ሙዚቃ ዘፈን ብሎ ይጠራል፡፡ በጥናቱ ውስጥም የአዝማሪዎችን ሙዚቃ ለመግለፅ ይኸው ሃገረኛ ቃል አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በሌሎች አጥኝዎች አጠራር ግን ሙዚቃ የሚል በመሆኑ የሌሎችን ሰዎች ሃሳብ መጥቀስ ሲፈለግ ቃሉ አገልግሎት ላይ የዋለው እነሱ እንዳሉት ነው፡፡

ሲጠቀምበት እንደኖረ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት አዝማሪዎችን በተገለሉ መንደሮች እስከመኖር አድርሷቸው እንደኖረ Kawase (2005)፣ አበበ (2002 ዓ.ም[2].) እና Mesganaw (2010) በጥናቶቻቸው ገልፀዋል፡፡ አጥኝዎች በዚህ ሁኔታ ተመሰረቱ ካሏቸው መንደሮች ውስጥ በጎንደር ዙሪያ ወረዳ የምትገኝ ‹‹ቡርቧክስ›› የተባለችን መንደር አሳይተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አዝማሪዎች በጎንደር ብቻ ሳይሆን በሸዋ፣ በጎጃም፣ በወለጋ፣ በትግራይና በወሎ እንደሚገኙ አጥኝዎች ገልፀዋል (Kawase 2005፣ In Kimberlin (2003)፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያዩ የሃገራችን ቦታዎች በራሳቸው አውድ ሊጠኑ የሚገባቸው የአዝማሪ ቡድኖች መኖራቸው ተገማች ነው፡፡ ወሎ ደግሞ በውዝዋዜና በዘፈን ሃብቱ ገናና ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጥናት ትኩረት ከሚስቡ ቦታዎች ውስጥ ቀዳሚው ይሆናል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በዚሁ አካባቢ የሚኖሩ አዝማሪዎችን ማጥናት ነው፡፡

## 1.2. ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች

ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ለርዕሰጉዳዩ ያለኝ ፍላጎት [አጥኝዋ] ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በርዕሱ ዙሪያ ባደረግሁት የቀደምት ጥናቶች አሰሳ ያየኋቸውን ክፍተቶች የመሙላት አስፈላጊነት ነው፡፡

ለርዕሰጉዳዩ ያለኝን ፍላጎት ልብ ያልሁት በ1999 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ባዘጋጀው ‹‹የበገና ምሽት›› አዝማሪዎች ዘፈንን ሲከውኑ ታዳሚ በመሆን ተገኝቼ ነው፡፡ በጊዜው ክዋኔው በፈጠረብኝ ከፍተኛ የሆነ አዝማሪዎችንና የሙዚቃ መሳሪያቸውን የማወቅ ጉጉትና ፍላጎት በርዕሰጉዳዩ ላይ ጥናት እንዳደርግ አነሳሳኝ፡፡ በተለይ በምኖርበት ባህር ዳር ከተማ ‹‹የአዝማሪ ምሽት ቤቶች›› መኖራቸው[3] ከአዝማሪዎች ጋር ለመገናኘትና የተለያዩ ውይይቶችን ለማድረግ ዕድል በመፈጠሩ በርዕሱ ላይ ጥናት ለመስራት እንድወስን አድርጎኛል፡፡

---

[2]በኢትዮጵያ አቆጣጠር ለተጠቀሱ ጥቅሶች ዓ.ም የሚለው መግለጫ የሚቀርብ ሲሆን ይህ ምህፃረቃል ያልተደረገላቸው ዓመተ ምህረቶች በአውሮፓውያን አቆጣጠር የቀረቡ ናቸው፡፡

[3] በባህር ዳር ከተማ ከአስር በላይ ባህላዊ የምሽት ቤቶች አሉ፡፡ በእነዚህ ባህላዊ ምሽት ቤቶች ሙዚቃ የሚከወነው በአዝማሪዎች ነው፡፡ በከተማው ውስጥ በአጠቃላይ ከሰባ እስከሰማንያ የሚሆኑ አዝማሪዎች ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል (አስቴር፣ 2003፣ 2፤ ሃረገወይን 2004፣ 19)፡፡

ከውሳኔዬ በኋላ በርዕሱ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን ማንበብ በመጀመሬ ጥናት ሊያስደርጉ የሚችሉ ክፍተቶች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ፡፡ በቀደምት ጥናቶች ላይ ካየኋቸው ክፍተቶች ውስጥ ሶስት ያህሉ ለምሳሌነት ቀጥለው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው የራሳቸውን መንደር መስርተው በሚኖሩ የወሎ አዝማሪዎች ላይ ጥናት አለመደረጉ ነው፡፡ ሁለተኛው በመሰረቱ በወሎ አዝማሪዎች ላይ ጥናት እንዲደረግ የሚገፋፉ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከምክንያቶቹ ጥቂቶች ወሎ ሰፊ የባህላዊ ሙዚቃ ሃብት ያለው መሆኑ፣ ለኢትዮጵያ የሙዚቃ ቅኝቶች መጠሪያ የሆኑት ትዝታ (በጥንት አጠራሩ ‹‹ወሎ ቅኝት››)፣ አምባሰል፣ ባቲና አንቺ ሆዬ ከተሰኙት አራቱ ቅኝቶች ውስጥ ከአንቺ ሆዬ በስተቀር ሶስቱ በአካባቢው በሚገኙ ቦታዎች ስም የሚጠሩ መሆናቸው (አለማየሁ፣1992 ዓ.ም)፤ እንዲሁም በ1970 ዓ.ም ተመስርቶ በ1983 ዓ.ም የፈረሰውና በሃገራችን ከሚጠቀሱስኬታማ የባህል ቡድኖች አንዱ የሆነው የ‹‹ላሊበላ የኪነት ቡድን›› ወሎ ውስጥ የተመሰረተና ያደገ መሆኑ (ያሬድ፣1993 ዓ.ም) የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የተዘረዘሩትና ሌሎች ምክንያቶች እንደሚጠቁሙት ወሎ ለኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ ህይወት አስተዋፅኦ ያበረከተ አካባቢ መሆኑን ሊጠቁሙ የሚችሉ ፍንጮች ቢታዩበትም የአጥኝዎች ዐይን የሚገባውን ያህል አላረፈበትም፡፡ አልማዝ (1974 ዓ.ም) እና መንገሻ (1992 ዓ.ም) በተባሉ አጥኝዎች፤ ‹‹አዝማሪና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ›› እና ‹‹የወገል ጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃላዊ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና›› የሚሉ ሁለት ጥናቶች ቢኖሩም ጥናቶቹ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ በመሆናቸው ከአንድ የባህል ጥናት የሚጠበቀውን ያህል ጥልቀት የላቸውም፡፡ አስረጂ ለመጥቀስ ያህል፣ ለጥናቶቹ የዋሉ መረጃዎች በአርቲፊሻል መቼቶች የተሰበሰቡ በመሆናቸው ለአውድ ትኩረት አልሰጡም፣ የግጥሞችን ባለቤት ታሪክ፣ የሙያውን ተከታታይነትና ለውጥ አልተመለከቱም፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን በተደረጉ ጥናቶች በጎንደርና በአካባቢው እንዲሁም ከተለያዩ አካባቢዎች መጥተው ለስራ አዲስ አበባና ባህር ዳር ከተሞች በሚኖሩ አዝማሪዎች ላይ እንጂ በወሎ አዝማሪዎች ላይ ጥናቶች አለመደረጋቸውን ለማወቅ ችያለሁ፡፡

ከቀደምት ጥናቶች አሰሳ የተገኘው ሁለተኛው የመረጃ ክፍተት አስቀድመው በተሰሩ ስራዎች ውስጥ የተገኙ አንዳንድ ዕውቀቶች ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር መጋጨታቸው ነው፡፡ ለምሳሌ Powen (1968, 61) የተባሉ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ያጠኑ የውጭ ሃገር ሰው ‹‹አዝማሪዎች በበጋ ሃብታምና ደስተኛ በክረምት ደግሞ

በጣም ችግረኞች እንደሆኑ ለማሳየት የአዝማሪዎች ህይወት ‹‹በጋውን በሙሉ እንደ ፌንጣ ይዘፍናሉ››[4] ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ በ09/07/2003 ዓ.ም.‹‹የቡርቧክስ አዝማሪዎች ማህበረ ኢኮኖሚያዊ መልክ›› በሚል ርዕስ ‹‹ቃል ታሪክ›› ለተባለው ኮርስ ማሟያ የሚሆን ጥናት ባደረግሁበት ጊዜ አዝማሪዎች በዚህ ሃሳብ የማይስማሙ መሆኑን ለመረዳት መቻሌ ለጥናት አነሳስቶኛል፡፡

ሶስተኛው በቀደምት ጥናቶች ላይ የታየው ክፍተት ሌላው ማህበረሰብ አዝማሪዎችን ከሚያይበት አንፃር ብቻ በማየት የማጥናት አቅጣጫ ነው፡፡ Dorson(1972) እንደሚያስረዱት በትልቅ ማህበረሰብ ውስጥ የራሱን ቡድን መስርቶ በሚኖር ንዑስ ቡድን ላይ ጥናት ሲደረግ አጥኚዎች የ‹‹የኤሚክ፣ ኤቲክ›› (አንድን ማህበረሰብ ከውስጥና ከውጭ አቅጣጫ ማየት) አተያይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይሁንና በአዝማሪ ላይ በተደረጉ ቀደምት ጥናቶች ላይ ይህ ሁኔታ አይታይም፡፡ ለምሳሌ Ashenafi (1971), Kawase(2005), Mesganaw(2010) በጥናቶቻቸው አዝማሪዎች በሌላው ቡድን የተገለሉ ወይም የተናቁ እንደሆኑና ሌላው ማህበረሰብ ከእነሱ መጋባትን ሳይፈልግ ኖሯል ይላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጥናቶች አዝማሪዎች ለሌላው ሰው የሚሰጡትን ግምት ያላሳዩ መሆኑ ክፍተት መኖሩን ስላሳየኝ ለጥናቱ ተነሳስቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ለርዕሰጉዳዩ ጥልቅ ፍላጎት መኖር፣ ይህንን ፍላጎት ተከትሎ በተደረገ የጥናታዊ ፅሁፎች አሰሳ ወሎ ውስጥ የራሳቸውን መንደር መስርተው በሚኖሩ አዝማሪዎች የዘፈንና የኑሮ ልምድ ላይ ጥናት ባለመደረጉ፣ የተደረጉ ጥናቶችም ቢሆኑ ጥልቅ ባለመሆናቸው፣ እንዲሁም ቡድኑን ከራሱ አንፃር ከማጥናት ይልቅ ከሌላ ቡድን አተያይ አንፃር ብቻ የተጠና በመሆኑ እነዚህን ክፍተቶች የሚሞላ ጥናት ማድረግ ለመስኩ አስተዋጽኦ ማበርከት ነው በሚል መነሳሳት ይህንን ጥናት ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የዘፈንና የኑሮ ልምድ›› በሚል ርዕስ ለማድረግ ወስኛለሁ፡፡

---

[4]አንበጣ የሚመስል፣ ሳር የሚበላና ሲሄድ ጡብ ጡብ የሚል የነፍሳት አይነት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት (1993፣601)፡፡
በጆሮንድ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም በአንድ ስለነገ ማሰብ እንደሚገባ ለማስተማር በፃፉት ግጥም ፌንጣንና ጉንዳንን ምሳሌ አድርገዋል፡፡ ፌንጣ በጋውን፣ ለክረምት የሚሆናትን ምግብ ሳታዘጋጅ፣ እንዲሁ ስትዘፍን ኖራ፤ ክረምት ሲመጣ ጉንዳንን እባክሽ ክረምቱን ካንቺ ጋር ልሁን ምግብ አብይኝ ትላታለች፡፡ ጉንዳንም በበጋ እኔ ስራ ስሰራ አንቺ እኮ ትዘፍኝ ነበር፡፡ እንዴት አሁን ትለምኝኛለሽ አትሰሪም ነበርን? የሚል መልስ ትሰጣታለች (ታሪክና ምሳሌ፣ 1961፣ 66-67)፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

- የወሎ አዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች ምንድን ናቸው?
- በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ልምዶች ምን መልክ አላቸው?
- በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች ምንድን ናቸው?
- በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ ለተከሰቱ ለውጦች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?
- የወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ምን ይመስላል?

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት መካሄዱ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ አምናለሁ፡፡

- ባህልን የመጠበቅና የመመርመር ተልዕኮ ላላቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የአዝማሪን ባህል እንዲጠብቁና እንዲመረምሩ ያሳስባል፤ የባህላዊ አርቲስቶችን አድራሻ ይጠቁማል፡፡
- ለትምህርትና ባህል ፖሊሲ አውጪዎች የመረጃ ምንጭና ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡
- በኢትዮጵያ የፎክሎር ጥናት ውስጥ በባህላዊ ‹‹ዘፈን›› ረገድ ያለውን የመረጃ እጥረት ከመቅረፍ አንፃር አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡
- ከአዝማሪዎች ጋር በመተባበር ባህላዊ ፌስቲቫሎችን ለማዘጋጀትና ጥናቶችን ለማካሄድ ለሚፈልግ የባህል ጥናት ባለሙያ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡
- በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገኙ ባህል ነክ ትምህርት ክፍሎች ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡
- ከርዕሱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያያዙ ጥናቶችን ለሚያደርጉ ሰዎች የመነሻ ሃሳብ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት ነው፡፡ ፎክሎር ጠቅለል ተደርጎ እንኳን ሲታይ በስራቸው ሌሎች ብዙ ዘርፎችን የያዙ አራት ሰፋፊ ዘርፎች አሉት Dorson, (1972)፡፡ ዘርፎቹ ካላቸው ብዛትና ስፋት የተነሳ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ማጥናት አይቻልም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ሃገረሰባዊ ሙዚቃ የተባለው ዘርፍ ብቻ ተመርጦ ትኩረት ተደርጎበታል፡፡ ሃገረሰባዊ ሙዚቃም ብዙ አይነቶች አሉት Dorson, (1972)፡፡ የአዝማሪ ዘፈን በባህርያቱ ምክንያት ከሃገረሰባዊ ሙዚቃ አይነቶች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን የአዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ልምድ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገበት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

ጥናቱ እንደ ርዕሰ ጉዳዩ ሁሉ ከቦታና ከጊዜ አንፃርም ተገድቧል፡፡ አዝማሪዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩ ቢሆንም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገበት የቦታ ወሰን ወሎ ነው፡፡ ይሁንና ወሎ በጣም ሰፊ አካባቢ ስለሆነ በዚያ የሚኖሩ አዝማሪዎችን ሁሉ በአንድ ጥናት ማካለል አይቻልም፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በተመረጡና መቄት፣ አምባሰል፣ ደሴ ዙሪያና ለጋምቦ በተባሉ አራት ወረዳዎች ላይ ብቻ የተደረገ ነው፡፡

ጥናቱ ከጊዜ አንፃርም አዝማሪዎች መጣን ብለው ከሚጠቅሱት አፈ-ታሪካዊ ዘመን ጀምሮ አሁን እስካሉበት ወቅት ድረስ ትኩረቱን አድርጓል፡፡

የባቲ ወረዳ ከወሎ አካባቢዎች ውስጥ ኦሮምኛ ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚኖርበት በመሆኑ በጥናቱ ቢካተት ኖሮ በአዝማሪነት ሙያ ተከታታይነትና ለውጥ ላይ የኦሮሞ ባህል ያሳረፈውን አሻራ ማየት ይቻል እንደነበር ይታመናል፡፡ ሆኖም ካለው የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት እጥረት ምክንያት በባቲ ወረዳ የሚኖሩ አዝማሪዎችን አለማካተቱ የጥናቱ ውስንነት ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ስነምግባር

አንድ አጥኝ ጥሩና ትክክለኛ የሆነ ጥናትና ምርምር ለመስራት ተጠኝውን ማህበረሰብና የማህበረሰቡን ባህል ማክበር፣ የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማሳወቅ የመሳሰሉ የምርምር ስነምግባሮች ሊጠብቅ እንደሚገባው Dawson (2007) ይመክራሉ፡፡ በዚህ ጥናትም

ይህንኑ ምክር መሰረት በማድረግ ቀጥለው የቀረቡ ስነምግባራዊ ተግባራትን ከውኛለሁ፡፡

- የመረጃ ስብሰባ ስራ ከመጀመሬ አስቀድሞ በየደረጃው ላሉ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት ፈቃድና ትብብራቸውን ጠይቄያለሁ፡፡
- ወደተጠኚው ማህበረሰብ በገባሁ ጊዜ አላማዬን ማስረዳትና ፈቃድ ማግኘት ከማንኛውም ነገር በፊት አስቀድሜ የከወንኳቸው ተግባራት ናቸው፡፡
- ከተጠኚው ማህበረሰብ ታማኝነትን ለማግኘት ስል ለማህበረሰቡ አጠቃላይ አኗኗር ክብር ሰጥቻለሁ፡፡
- በጥናቱ ወቅት ቪዲዮ፣ ፎቶ ካሜራና መቅረፀድምፅን የመሳሰሉ የቀረፃ መሳሪያዎችን የተጠቀምሁት የመረጃ ሰጪዎችን ፈቃድ ጠይቄ ነው፡፡ ለቀረፃ ፈቃድ ለሰጡት ሰዎች የተቀረፀውን በማሳየት ለመረጃነት ከማገልገሉ በፊት የሚስማሙበት መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡ ስማቸው እንዳይጠቀስና ምስላቸው እንዳይቀረፅ የፈለጉ፣ እንዲሁም ከሰጡኝ መረጃ ውስጥ ‹‹ይህንን በጥናቱ ውስጥ እንዳታካትቺ›› ያሉኝ ሰዎችን ፍላጎት አክብሬያለሁ፡፡
- ጥናቱ በመረጃ አቀባዮች፣ በመንገድ መሪዎችና በሌሎች ሰዎች ድጋፍ ጭምር እንጅ በእኔ ትጋት ብቻ ሊሳካ የማይችል መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ በመሆኑም መረጃ አቀባዮችም ሆኑ የጥናቱን ቦታ በማመቻቸት፣ በማስተርጎም፣ መንገድ በመምራት ወዘተ የተባበሩ ሰዎች ጊዜና ጉልበታቸውን ለጥናቱ ያዋሉ በመሆኑ ተገቢውን ክፍያ እንዲያገኙ አድርጌያለሁ፡፡ አነስተኛ ስጦታዎችን በማበርከትና መጠነኛ ማበረታቻዎችን በማድረግ ትብብራቸው እንዲቀጥል ሰርቻለሁ፡፡
- ለየትኛውም መረጃ ሰጪዬ፣ መረጃዎችን ለማግኘት ስል ከአቅም በላይ የሆኑ ተስፋዎችንና ማድረግ የማይቻሉ ነገሮችን ‹‹አደርጋለሁ›› የሚል ቃል አልገባሁም፡፡

## 1.7. በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች

ለመረጃ ስብሰባ በሄድሁባቸው አካባቢዎች ጥናቱን ለማድረግ የሚያበረታቱና የሚደግፉ ምቹ ሁኔታዎችን አይቻለሁ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ተጠኚው ቡድን፣ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ብዙ ግለሰቦችና የየወረዳዎች የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ፅህፈት ቤቶች በርዕሱ ላይ ጥናት እንዲደረግ ያላቸው ፍላጎት የሚለው ዋናው ነው፡፡

ተጠኚ ከሆነው ቡድን ውስጥ ብዙ ጊዜ ገንዘብ የሚጠይቁ መረጃ ሰጪዎች ያጋጠሙኝ ቢሆንም ብዙዎቹ ግን ርዕሱ ላይ ጥናት በመደረጉ ሙያው የተሻለ ዕድገትና ተቀባይነት ያገኛል የሚል እምነት ያላቸው ናቸው፡፡ ገንዘብ ካልተሰጠን ብለው ያስቸግሩ የነበሩ ሰዎችም የጥናቱን ዓላማ በሚገባ ከገለፅሁላቸው በኋላ በጣም ተባባሪና አጋዥ የመሆን ፀባይ አሳይተውኛል፡፡ መረጃ ለመስጠት የተሻለ ዕውቀትና ልምድ አለው/አላት የሚሏቸውን ሰዎች መርጠው መስጠትና፣ ከእነዚህ ሰዎች መልካም መስተንግዶ እንዳገኝ መረጃ ሰጪዎችን ማግባባት በራሳቸው በተጠኚው ቡድን አባላት ሲከወኑ የነበሩ ተግባራት ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ ተጠኚዎቹ እስከምፈልግበት ጊዜ ድረስ በቤታቸው እንድቆይ በመፍቀድ፣ መልካም መስተንግዶ በማድረግና እንደቤተሰብ ቆጥሮ በመቀበል የጥናት ስራው በመልካም ሁኔታ እንዲካሄድ ከፍተኛ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል፡፡

መረጃ ሰጪዎች እንደዘመድ የተቀበሉኝ ከመሆኑ የተነሳ ለጥምቀትና ለመድሃኒያዓለም በዓላት በእንግድነት ጠርተው ጋብዘውኛል፡፡ ይህንን በማድረጋቸውም ከእነሱ ጋር ለመፍጠር ለምፈልገው የዝምድና ስሜት ተባባሪ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አዝማሪ ያልሆኑ የወሎ ተወላጅ በርካታ ሰዎች ወሎ ውስጥ ጥናት በማድረጌ ከፍተኛ የሆነ የማቅረብና የማክበር ስሜት እንዳላቸው ይገልፁልኝ ብሎም ያሳዩኝ ነበር፡፡ ብዙዎችም ይህንን ስሜታቸውን መረጃ በመስጠት፣ መረጃ ከሚሰጡ ሰዎች ጋር በማገናኘት፣ አብረውኝ መስክ በመውጣት፣ በቤታቸውና በሻይ ቤቶች በመጋበዝ ገልፀውልኛል፡፡ ጥናቴ ቀጣይነት እንዲኖረው አሳስበውኛል፡፡

የየወረዳዎቹ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮዎች ደግሞ በየገጠሩ ለሚደረጉ ጉዞዎች አጋዥና መንገድ መሪ የሚሆኑ ሰዎችን በመመደብ፣ አስፈላጊና አመቺ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ጥናቱ እንዲደረግ ያላቸውን ቀና አመለካከት አሳይተውኛል፡፡

## 1.8. በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመስክ ስራ ወቅት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ባደረግሁት ጥረት በርካታ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ይሁንና ከበርካታዎች ውስጥ በጣም ጎልህ ናቸው ያልኳቸውን ሁለት ችግሮች ገልጫለሁ፡፡ የመጀመሪያው፣ በየትኛውም ጥናቱ በተደረገባቸው ወረዳዎች የሚገኙ የአዝማሪ መንደሮች እስከአምስት ሰዓት የሚፈጅ የእግር ጉዞና ጠንካራ የመጓዝ ብቃት የሚጠይቁ ፈታኝ መሆናቸው ነው፡፡ ጥናቱ የተደረገባቸው ሁሉም መንገዶች ከዋና መንገድ በጣም የራቁና ወደመንደሮቹ የሚያስሄዱ መንገዶች ዳገትና ቁልቁለት የበዛባቸው ናቸው፡፡ እነዚህን መንገዶች ተቋቁሞ መረጃ መሰብሰብ ብዙ ትዕግስትን የሚጠይቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር፡፡ ይሁንና እነዚህን ተስፋ መቁረጦች ወደየመንደሮቹ አብረው በተጓዙ የገጠር መንገድ ጉዞ ልምድ ያላቸው የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ሰራተኞች አጋዥነትና አፅናኝነት አልፌያቸዋለሁ፡፡ ከዕለት ዕለት ብቃቴን እያስተካከልኩ በመጓዝ፣ ከአንድ ጉዞ በኋላ በቂ እረፍት እያደረግሁ፣ ከወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች እና የአስተዳደር ፅህፈት ቤቶች መኪና እንዲሰጡኝ በመጠየቅና ወደ ቦታዎች በመድረስ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡

እንደሁለተኛ ችግር የሚነሳው አንዳንድ አዝማሪዎች መረጃ እንዲሰጡ ሲጠየቁ በምላሹ ከአቅም በላይ ክፍያ የሚጠይቁ መሆናቸው ነው፡፡ ይሁንና በእንደዚህ አይነት ሁኔታ አላማዬን በጥንቃቄ በማስረዳት፣ ያልተጋነኑ ስጦታዎችን በማበርከት፣ በተደጋጋሚ ጉብኝት ወዳጅነትን በመፍጠር፣ አስቀድሞ ወዳጅ በሆኑ ሰዎች አማካኝነት አዲስ ሰዎችን በመተዋወቅ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ በተለይ ደግሞ ተደጋጋሚ ጉብኝት በማድረግ ወዳጅነት የመፍጠር ዘዴው ብዙ ገንዘብ በመክፈል ወይም ምንም አልከፍልም በማለት ምክንያት በመረጃ ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ተፅዕኖ ከመከላከል አንፃር በጣም ጠቃሚ በመሆኑ ከሌሎች መፍትሄዎች በተሻለ ተግብሬዋለሁ፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል ‹‹ፅንሰሃሳቦች›› እና ‹‹የቀደምት ጥናቶች ክለሳ›› የሚሉ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡ ‹‹የፅንሰሃሳብ ማዕቀፎች›› በሚለው ክፍል ከተለያዩ የኢትኖሙዚኮሎጅ፣ የፎክሎርና የሌሎች ተዛማጅ ባለሙያዎች ስራዎች ውስጥ የተወሰዱ ሃሳቦች ተካትተዋል፡፡ እነዚህ ሃሳቦች የጥናቱ ማጠንጠኛ ለሆኑት ዋና ጉዳዮች ምንነት የቀረቡ ዳራዎች ሲሆኑ፤ በትንተናው ወቅት ከመስክ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎችን ለማወዳደርና ለማነፃፀር አገልግለዋል፡፡ የቀደምት ጥናቶች አሰሳ ደግሞ ከዚህ ስራ አስቀድሞ በርዕሱ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ተከልሰው የቀረቡበት ነው፡፡ ክለሳው ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናቶች በምን እንደሚመሳሰልና እንደሚለያይ ለማሳየት፣ የትኛውን ክፍተት ለመሙላት እንደተሰራ ለማስረዳት፣ እንዲሁም የጥናቱን መደረግ አስፈላጊነት ለማረጋገጥ ያገለገለ ነው፡፡

## 2.1. የፅንሰሃሳብ ማዕቀፎች

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ዓላማ ግብ መምቻ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎችን ለማወዳደርና ለማነፃፀር የሚጠቅሙ፣ በጥናቱ በዋናነት የሚነሱ ፅንሰሃሳቦችና ብያኔዎች ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1. ቡድን [ፎክ]

‹‹ፎክሎር፣ ‹‹ፎክ›› እና ‹‹ሎር›› ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ፅንሰሃሳብ ነው፡፡ ‹‹ፎክ›› ህዝብ/የሰዎች ስብስብ ማለት ሲሆን ‹‹ሎር›› ደግሞ ዕውቀት ማለት ነው፡፡ የሁለቱ ቃላት ጥምረት ‹‹የቡድን ዕውቀት›› የሚል ነው›› Dundes (1980, 1)፡፡ ፎክሎር በሰዎች የተፈጠረ፣ ሰዎች የሚኖሩትና የሚኖሩበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ሰዎች የፎክሎር መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በፎክሎር እሳቤ ቡድን ማለት የጋራ ፍላጎትና ልምድ ያላቸው ሰዎች የፈጠሩት ስብስብ ማለት ነው፡፡

ቡድን ወይም ‹‹ፎክ›› የሚለውን ቃል ለማስረዳት Dundes (1980, 6) «የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ፎክ/ ቡድን ይባላል» ይላሉ፡፡ ብያኔው ውስጥ የቡድኑ አባላት ለመሰባሰብ ምክንያት የሆናቸውን የጋራ ባህርይ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቡድኑም ሆነ እያንዳንዱ

የቡድኑ አባል ‹‹ማነህ?›› ተብሎ ሲጠየቅ ማንነቱን የሚገልፅበትና ለምን የቡድኑ አባል እንደሆነ የሚሰጠው ምክንያት አለው ማለት ነው፡፡

Toelken (1996, 56) ቡድን፣ መገለጫቸው ባህልን መሰረት ያደረገ ተግባቦት (Communication) ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው ብለዋል፡፡ የ Toelken ብያኔ ከ Dundes ብዙ ያልራቀ ሲሆን በእሳቸው ብያኔ ውስጥ ግን ለቡድኑ መሰባሰብ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ባህላዊ መሰረት ያለው ነው፡፡ ይህ ባህላዊ መሰረት ደግሞ ኢመደበኛነትን፣ ውስብስብ አለመሆንንና ከመደበኛ ይልቅ ልማዳዊ ገፅታን የሚጠቁም እንደሆነ Sims and Stephens (2005፣ 34) ይገልፃሉ፡፡ በጥቅሉ የፎክሎር ባለሙያዎች ስለፎክ ቡድን ምንነት ሲያስረዱ ዘር፣ ጎሳ፣ ፆታ፣ ስራ፣ መደብ፣ ዕድሜ፣ የጋራ ፍላጎት ወዘተ ለመሰባሰባቸው ምክንያት የሆኗቸው ከመደበኛ ህጎች ይልቅ ልማዳዊ በሆነ መንገድ የተመሰረቱና የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ ፎክ ቡድን ይባላል ይላሉ፡፡ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው አዝማሪዎች ስራን ምክንያት አድርገው የተሰበሰቡ ሰዎች የፈጠረው ቡድን በመሆናቸው ‹‹Occupational Group/ የስራ ቡድን (ትርጉም የእኔ) ናቸው፡፡

## 2.1.2. ልምድ (Tradition)

ልምድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ፅንሰሃሳብ ነው፡፡ ይህንን መሰረታዊ ፅንሰሃሳብ በመተርጎም ሂደት በርካታ የፎክሎር ባለሙያዎች የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ Hield (2007,59) Glassie (1995)ን ጠቅሰው ‹‹Tradition has widely been associated with stability through processes of unchanging transmission and the preservation of authentic practices›› ‹‹የአንድ ቡድን መለያ ሆነ ተጠብቆ በኖረ ተግባራዊ ልምምድ ውስጥ በሚካሄድ የተስተላልፎ ሂደት ካለ ዘላቂነት ጋር የሚያያዝ ፅንሰሃሳብ ነው›› ይላሉ (ትርጉም የእኔ)፡፡

Green (1997, 800)ም እንደዚሁ ‹‹Tradition as something passed down from one generation to the next, generally by informal means, with little or no change in the transmission of that item or in the item that is transmitted››.‹‹ልምድ የአንድ ነገር ከአንድ ትውልድ ወደሌላው በጥቂት ለውጥ አለዚያም ያለምንም ለውጥ ኢመደበኛ በሆነ መንገድ መተላለፍ ነው›› ብለዋል (ትርጉም የእኔ)፡፡ በተጨማሪም Green የሃያኛው ክፍለዘመን የፎክሎር ባለሙያዎች ልምድን

ባለፈውና በአሁኑ ጊዜ መካከል ያለ ግንኙነት ነው። ያለፈው ጉዳይ ለአሁኑ መነሻ ሲሆን፣ የአሁኑ ደግሞ ያለፈው የሚታይበት ነው በማለት ይገልፁታል። ከዚህ በመነሳት ልምድ፣ በፎክሎር ሙያ ውስጥ ዋና ፅንሰ ሃሳብ የሆነ፣ ከጊዜ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሃሳቦችን የሚይዝ፣ በኢመደበኛ ትምህርት የሚገኝና ከተከታታይነትና ለውጥ ጋር የሚያያዝ ፅንሰ ሃሳብ ነው ማለት ይቻላል። ፅንሰሃሳቡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም፣ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኙ የባህል ጉዳዮችን መቀባበል ነው ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። ይሁንና ከዚህ በተሻለ መልኩ ግልፅ ብያኔ ሊያገኝ እንደሚችል የሚጠቁሙት Sims and Stephens (2005, 65) ልምድን ‹‹Both the lore we share and the process by which we share it›› /‹‹ልምድ የምንቀባበለው ዕውቀትና የዕውቀቱን የምንቀባበልበት ሂደት ነው›› እና ‹‹Something that creates and confirms identity››/.‹‹ ማንነትን የሚፈጥርና የሚተክል ነገር ነው›› (ትርጉም የእኔ) ሲሉ ይበይኑታል። ብያኔዎችን ሲያብራሩም ልምድ፣ አንድ ቡድን ያለው ሃገር በቀል ዕውቀትና ዕውቀቱን የሚቀባበልበት ሂደት ነው። ቃሉ የማንኛውም ድግግሞሽን የሚፈጥር ሂደት መገለጫ እስከመሆን ይደርሳል። ለምሳሌ ታሪክ፣ ታሪክ የሚነገርበት እንቅስቃሴ፣ ታሪኩ ወይም ታሪክ ነገራው ትርጉም የሚያገኝበት መንገድ፣ እነዚህ ሁሉ ልምድ ይሆናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ፅንሰሃሳቡ በተወሰነ ቡድን ውስጥ ያሉና የሚቀጥሉ ቁሶችን፣ ልማዶችን፣ ቃላዊ ገለፃዎች መቀባበልንና ተከታታይነትን (continuity) ይመለከታል።

በዚህ ጥቅስ Sims and Stephens (2005) ልምድ፣ አንድ ቡድን ያለውን ሃገር በቀል ዕውቀትና ዕውቀቱን ያገኘበት ኢመደበኛ መንገድ ነው የሚል ሃሳብ የሰጡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ልምድ፣ ቡድኑ ባለው ዕውቀት ማንነቱን ለመገንባትና ለማጠናከር የሚያገለግለው ጉዳይ እንደሆነ ቡድኖች ልምድን የሚተገብሩት መርጠው በመውሰድ ነው። ይህ በመሆኑ ልምዱ የማንነታቸው መለያ ይሆናል። በአንድ በተወሰነ ቡድን ውስጥ አባላቱ መሳተፋቸው የልምዱ አካል የመሆን ስሜት ይፈጥርባቸዋል። በልምዱ አማካይነትም ማንነታቸው የሚፈጠር ብሎም የሚረጋገጥ ይሆናል። በዚህ የተነሳ ይህ ቡድን ከሌሎች ቡድኖች ተለይቶ ይታያል። ሌሎችም በዚህ ልምዱ የተነሳ ይለዩታል ማለት ነው ሲሉ ይገልፃሉ።

Glassie (1995)ም ልምድ፣ ካለፈው ጊዜ መጪውን ጊዜ መፍጠር ነው ሲሉ ከጊዜ ጋር የተያያዘ ሃሳብ እንደሆነ ሲገልፁ Horner በበኩላቸው ልምድ በትውልድ መካከል ያለ የዕውቀትና የአስተሳሰብ ቅብብሎሽ ነው ይላሉ፣ ቅብብሎሹ ግን ካለፈው ዘመን

ወደአሁኑ ብቻ የሚተላለፍ አይደለም። ይልቁንም በተመሳሳይ ወቅት የሚገኙ ቡድኖች ሊጋሩት ይችላሉ በማለት የልምድ ቅብብሎሽ በተጓዳኝም ሆነ በተዋረድ በሚገናኙ ቡድኖች መካከል ሊካሄድ እንደሚችል ያስረዳሉ (1990)።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡ ብያኔዎች ልምድ የአንድ ቡድን ዕውቀትና የዕውቀቱ የሽግግር መንገድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ልምድ በውስጡ ሁለት መሰረታዊ ሃሳቦች አሉ። እነሱም ‹‹ተከታታይነት›› እና ‹‹ለውጥ›› ናቸው። ይህንን ሃሳብ Toelken (1996, 37) ተከታታይነትና ተለዋጭነት የፎክሎር ሂደት መንታ ህጎች ናቸው ሲሉ ገልፀውታል።

### 2.1.3. ተከታታይነት (Continuity)

ተከታታይነት በጊዜ ሂደት ውስጥ የልምድን የማያቋርጥ ጉዞ የሚገልፅ ፅንሰሃሳብ ነው። ፅንሰሃሳቡ በልምድ ውስጥ ያለ ጊዜንና የልምዱን ድግግሞሽ ይመለከታል። ምክንያቱም ልምድ ራሱ በጊዜ ውስጥ የሚደረግ ድግግሞሽ ነው። በእርግጥ ጊዜ የዓመታት ወይም የቅፅበት ጉዳይ ሊሆን ቢችልም የድግግሞሹ መኖር ልምድን ቀጣይ ያደርገዋል። ይህንን ሃሳብ የሚደግፉት Sims and Stephens በየትኛውም የጊዜ ርዝመት የሚደረግ ድግግሞሽ ልምድን ይፈጥራል። የልምድ መደጋገም ደግሞ ተከታታይነትን ይፈጥራል። እዚህ ላይ ግን ተከታታይነት ተመሳሳይነት ወይም የነበረውን መስሎ መቀጠል እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ልምድ በተደገመ ቁጥር ራሱን መስሎ አይወጣም። ይልቅ ተከታታይነት የሚለው ቃል በቡድኑ ውስጥ የልምዱን ትርጉም ወይም ጥቅም ያያዙ ድሮችን የሚመለከት ነው ይላሉ (2005, 65)።

በአጠቃላይ ተከታታይነት የልምድን ድግግሞሽ የሚያሳይ ፅንሰሃሳብ ነው። ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ድግግሞሹ የሚቋረጥበት ብሎም የሚጠፋበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም ለውጥ (ተለዋጭነት) ወደሚለው ሌላው የልምድ ባህርይ የሚወስድ ጉዳይ ይሆናል።

### 2.1.4. ለውጥ (Change)

የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበቃላት (1993፣ 21) ‹‹ለውጥ›› የሚለውን ቃል አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት ሲል ይበይነዋል። የቃሉ ግስ የሆነውን ‹‹ለወጠ››ን ደግሞ የአንድን ነገር ቀድሞ የነበረ ሁኔታ፣ ባህርይ፣

መልክ፣ በሌላ እንዲቀየር፣ እንዲተካ አደረገ። አንድ ነገር ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ፣ ባህርይ፣ መልክ በሌላ ቀየረ። ቀየረ፣ ተበላሸ፣ ቀድሞ ከነበረው አሻሻለ ይለዋል። Oxford Advanced Learner's Dictionary ደግሞ አሮጌውን ስልት/ ‹‹ሲስተም›› በመተው አዲሱን መያዝ ይላል። እነዚህ ትርጉሞች ለውጥ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ‹‹ልዩነት መፈጠር›› የሚል ትርጉም ይይዛል። ይህንንም ወደልማድ በመውሰድ ባለፈውና በመጣው ልማድ መካከል የተፈጠረ ልዩነት በማለት መገንዘብ ይቻላል። ለውጥ የሚለው ቃል በነበረው ተጨባጭ ሁነት ላይ ጊዜ የፈጠራቸውን ማሻሻያዎች፣ መተኪያዎችና ሁነቶች መፈጠራቸውን የሚያሳይ ፅንሰሃሳብ ነው ማለት ይቻላል። ብያኔዎች ለውጥ ማለት በነበረው ሁኔታ ላይ የአዲስ ነገሮች መምጣት መሆኑን ብቻ ሳይሆን የሚፈጠሩት ሁነቶች አወንታዊና አሉታዊ መልክ ያላቸው መሆኑንም ይገልፃሉ።

ከላይ የቀረበው የለውጥ ትርጓሜ በፎክሎር እሳቤ ውስጥ ቦታ ያለው መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። ለምሳሌ Tolken (1996) ለውጥ የፎክሎር አንድ ህግ መሆኑን የሚናገሩ ሲሆን Dorson (1972)ም ለውጥ (ተለዋጭነት) የፎክሎር በተለይም የሃገረሰባዊ ሙዚቃ ዋና ባህርይ መሆኑን ይናገራሉ።

Sims and Stephens (2005) እንደሚሉት በውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች ምክንያት ልምድ ይለወጣል። በፎክሎር እሳቤ መሰረት ልምዶች የሚኖሩት ቡድን ካለ ነው። ቡድኑ በዝምድና፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በቦታ ወዘተ የተሳሰረ በመሆኑ ሁልጊዜም አንድ አድርጎ የሚይዘው ልምድ አለው። ልምዱ ለእያንዳንዱ አባል ቡድኑን የመጠበቅ ሃላፊነት እንዲሰማው የማድረግ ጠንካራ አቅም አለው። ስለዚህም ምንጊዜም ቢሆን ቡድኑ ልምዱ እንዳይጠፋበት የመጠበቅ ተግባር ያከናውናል። ይሁንና ከውጫዊ ሁኔታዎች አንፃር የድንበር ጦርነቶች፣ ሆን ተብለው የሚደረጉ የዘር ማጥፋት ተግባራት፣ በሽታ፣ ቅኝ ገዥዎች ወዘተ ልምድን በፍጥነትና በአደገኛ ሁኔታ ሊለውጡትና ሊያጠፉት ይችላሉ። ከውስጣዊ ሁኔታዎች አንፃር ደግሞ ለውጥ የፎክሎር መሰረታዊ ባህርይ በመሆኑ የተነሳ ልምድ ይለወጣል። ይህ በመሆኑም ማንኛውም ልምድ ለውጥን ያስተናግዳል ማለት ነው። Tolken (1996፣ 45) በማንኛውም ሁኔታ ልምዱ ላይ የሚደረጉ ፈጠራዎች ለውጥ ናቸው። ሲሉ ይህንን አባባል ያረጋግጣሉ። እሳቸው እንደሚሉት ቃላዊ ጥበቦች፣ ግለሰቦች ቃላዊ ጥበቦችን ለመፍጠር የሚያደርጉት ምርጫ፣ አሃዱ እንዴት፣ መቼ፣ እነማን ተሳተፉበት የሚለው ተለዋጭነትን ለሚፈጥሩ ሁኔታዎች ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

Sims and Stephens (2005, 74) እንደሚሉት ደግሞ ለውጥ ለፎክሎር መሰረታዊ ባህርይው ቢሆንም ለውጡ ሁልጊዜም ፎክሎሩን ለሚጋራው ቡድን ጠቃሚ፣ ትርጉም ያለውና ተገቢ መሆን ስለሚገባው ከተፈጥሯዊ ሂደትነቱ ባሻገር ቡድኖች በልምዳቸው ላይ ለውጥን ሆን ብለው ያመጣሉ፡፡ ከዚህ አይነት ተግባራት ውስጥ አንድን ልምድ ፈጥሮና ለተለየ ቦታና ዓላማ ወስዶ መጠቀም አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ ለአዲስ ታዳሚ ሲባል፣ ቀድሞ ለነበረው ታዳሚም ቢሆን ፈጠራ ማከል ሲያስፈልግ ወዘተ ልምድ ሊቀየር ይችላል፡፡ ይህ ቅየራም ወደፊት ልምዱ እንዳይኖር እስከማድረግ ድረስ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ይህ የልምድ መቀየር ሰፊ ከሆነ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አንድምታ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

በአጠቃላይ ልምድ በፎክሎር እሳቤ ውስጥ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ በውስጡ ሌሎች ፎክሎርን ለመረዳት የሚያስችሉ መሰረታዊ ሃሳቦችን ይዟል፡፡ እነዚህ ሃሳቦች ዕውቀት፣ ዕውቀቱ የሚተላለፍበት መንገድ፣ ቡድን፣ ተከታታይነትና ለውጥ የተሰኙት ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ መሰረት ተከታታይነትም ሆነ ለውጥ የሚዳሰሰው በሃገረሰባዊ ሙዚቃ ውስጥ ነው፡፡

### 2.1.5. ሃገረሰባዊ ሙዚቃ (folk music)

ሃገረሰባዊ ሙዚቃ፣ የአንድ ማህበረሰብ ባህላዊ መገለጫ የሆነ በማህበረሰቡ ዕውቀትና ምናባዊ ፈጠራ ላይ የተመሰረተ ቃላዊ ጥበብ ነው፡፡ ይህ ጥበብ በቀዳሚ ተግባሩ የማህበረሰቡን የእለት ከእለት እንቅስቃሴ በመግለፅ ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ ባህላዊ እሴት ነው፡፡ ሙዚቃ የሌለው ማህበረሰብ የለም፡፡ በመሆኑን እያንዳንዱ ማህበረሰብ ራሱ የሚኖርበትን አውድ መሰረት አድርጎ ሙዚቃን ይከውናል፡፡ ይህ መሆኑ ሙዚቃውን በበርካታ አውዶች እንዲገኝ ያደርገዋል፡፡ እያንዳንዱ አውድም የራሱ ባህርይ ስላለው ሃገረሰባዊ ሙዚቃን ለመበየን የሚደረገው ሙከራ ብዙ ምላሾችን ያስገኛል፡፡ ከእነዚህና ከሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ አንድ ነጠላ ብያኔ እንደሌለው የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ Bohlman (1988, xviii) ይህንን አስመልክቶ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> It is difficult to give a single definition to folk music.There are two reasons for this, First, the different contexts of folk music that I investigate here yield very different

definitions. To apply many of the most common definitions of folk music in European and North American society to the Middle East would be a pointless and thankless undertaking. Second, because I regard change as ineluctably bound to folk music tradition, I also assert that the dynamic nature of folk music belies the stasis of definition.

*ለሃገረሰባዊ ሙዚቃ አንድ ነጠላ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ ነው። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ምክንያት ሃገረሰባዊ ሙዚቃ በተለያዩ አውዶች ላይ ሲከወን የሚኖረው ብያኔ የተለያየ መሆኑ ነው። ለምሳሌ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ማህበረሰቦች ዘንድ የተሰጠው ብያኔ ወደመካከለኛው ምስራቅ ቢሄድ ፍሬ ቢስና የማይረባ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ፈጣንና ተለዋጭ ባህርይ ያለው በመሆኑ አሁን የተሰጠው ብያኔ፣ እስከመቼ እንደሚዘልቅ አይታወቅም። የብያኔው የህይወት ዘመን አጭር ነው (ትርጉም የእኔ)።*

ከላይ የቀረበው ሀሳብ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ በባህርይው ፈጣን ለውጥ የሚካሄድበት ስለሆነ በየጊዜው አዳዲስ ብያኔዎችን እያገኘ ያለ ዘርፍ እንደሆነ ይገልፃል። የተለያዩ የመስኩ ሙሁራን ለሃገረሰባዊ ሙዚቃ ብያኔዎችን ሰጥተዋል። ከእነዚህ ውስጥ (Greenway 1953, 8) በ Bohlman (1988) ‹‹This is what a folk song really is the folks composes their own songs about their own life's and there home folks that live around them››/ «ሃገረሰባዊ ሙዚቃ ሰዎች ስለራሳቸው ህይወትና በአካባቢያቸው ስለሚኖሩ ሰዎች አኗኗር የደረሱት ዘፈን ነው» (ትርጉም የእኔ) ሲሉ Merriam (1964, 12) ደግሞ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ በፈጠራም ሆነ በክዋኔ ሂደቱ ከመደበኛ ይልቅ ኢመደበኛ ባህርይው ያመዝናል። የራሱ የሆነ የመከወኛ አውድ ይፈልጋል።

በሁለቱም ብያኔዎች የተንፀባረቀው ሃሳብ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ፣ አንድ ቡድን የራሱን ኑሮና አካባቢ ለመግለፅ የሚደርሰው፣ ባለቤቱ ህዝብ እንጅ ግለሰብ ያልሆነ፣ አፈጣጠሩም ሆነ ተስተላልፎው አፋዊ እንጅ ፁሁፋዊ ያልሆነ፣ የፈጣሪውን ማህበረሰብ ባህል መሰረት አድርጎ የሚፈጠርና የሚከወን ሙዚቃ ነው የሚል ነው። ከላይ ከቀረቡት ምሁራን ሌላ ሃገረሰባዊ ሙዚቃን የበየኑት Dorson (1972, 331)ም ‹‹The term folk music is often loosely applied to cover all traditional or aurally

transmitted music, music that is passed on by ear and performed by memory rather than by the written or printed musical score››/ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ የሚለው ቃል ለሁሉም ልማዳዊ ለሆነ ወይም በቃል ለሚተላለፍ ሙዚቃ መግለጫነት የሚውል ነው››። ከተፃፈው ወይም ከታተመው ይልቅ በመደመጥ የሚተላለፍና በመታወስ የሚከወን ሙዚቃ ነው›› ይላሉ።

ሃገረሰባዊ ሙዚቃ ከኢመደበኛነቱና አካባቢን ከመግለፅ ባህርይው ባሻገር ማህበራዊነቱ መገለጫው ነው። ምክንያቱም ግለሰብ ደራሲ የለውም፤ በግለሰቦች ቢደረስም እንኳን ሃብትነቱ የማህበረሰብ ነው። በሙዚቃው የሚገለፀው የማህበረሰብ ህይወት ነው። ከዚህ የተነሳ ማህበራዊ መልክ አለው። ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ Ball et.al (2010, 9) የጎሳ ጥናት ባለሙያዎች፣ ሃገረሰባዊ ሙዚቃ የሰው ልጅ ተግባራት ቅርፅ ተሰጥቷቸው የሚቀርቡበት፣ በፈጠራው ላይ ግለሰቦችና ማህበረሰብ የሚሳተፉበት፣ ውጤቱ ቅፅበታዊ ያልሆነ፣ ግቡም ቋሚ ያልሆነ (የሚለዋወጥ) ተግባር ነው ብለዋል።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ሃሳቦች ባለሙያዎች ለሃገረሰባዊ ሙዚቃ የሰጧቸውን ብያኔዎች ለማሳየት የተሞከረ ሲሆን ብያኔዎቹ ፅንሰ ሃሳቡ አንድ ወጥ ብያኔ የሌለው መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው። ይሁንና ሁሉም ብያኔዎች የሃገረሰባዊ ሙዚቃን ባህርይ በመግለፅ ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ከልዩነት ይልቅ ብዙ የሚያመሳስሏቸው ነጥቦችን ያነሳሉ። ስለዚህ እነዚህን ተመሳስሎዎች በመውሰድ ‹‹ሃገረሰባዊ ሙዚቃ በቃል ተደርሶ በቃል የሚተላለፍ፣ ቀዳሚ ተግባሩ አካባቢውን መግለፅ የሆነ የቡድን ሃብት ነው›› የሚል ብያኔ መስጠት ይቻላል።

## 2.1.6. ሙዚቃና የሰው ልጅ ባህርይ

ሙዚቃ የሌለው ማህበረሰብ የለም። ሁሉም ማህበረሰብ የራሱን ሙዚቃን ፈጥሮ ይገለገላል። የሙዚቃው ተግባር ማዝናናት፣ ማስተማር፣ ቡድኑን ስርዓት ማስያዝ፣ አምላክን ማመስገኛ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ተግባሩ ምንም ይሁን ምንም የሰው ልጅ ከሙዚቃ ውጪ እየኖረ አይደለም። ይህ መሆኑ በሙዚቃና በሰው ልጅ ባህርይ መካከል ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል። ሙዚቃና የሰው ልጅ ባህርይ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ፀሃፍት ይገልፃሉ። Blacking (1995, 223) ይህንን ሲገልፁ:-

Music is a primary modelling system of human thought and a part of the infrastructure of human life. Music making is a special kind of social action which can have important consequences for other kinds of social action. Music is not only reflexive; it is also a generative, both as cultural system and as human capability

ሙዚቃ፣ የሰውን ልጅ አስተሳሰብ የሚመራ ሁነትና ለሰው ልጅ ህይወት መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች አካል ነው፡፡ ሙዚቃን መፍጠር ውጤቱ ለሌሎች ማህበራዊ ተግባራት የሚጠቅም አንድ ልዩ ማህበራዊ ተግባር ነው፡፡ ሙዚቃ ባህላዊ ሁነቶችንና የሰውን ልጅ አቅም አንፀባራቂ ብቻ አይደለም፤ መፍጠሪያም ነው›› (ትርጉም የእኔ) ብለዋል፡፡

ከብያኔው መገንዘብ እንደሚቻለው ሙዚቃ፤ የሰውን ልጅ ባህርይ ቅርፅ (መልክ) ከሚያሲይዙ ነገሮች ውስጥ ቀዳሚው፣ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ ደግሞ አንዱ ነው፡፡ ሙዚቃን መፍጠር አንድ ልዩ አይነት ማህበራዊ ተግባር ሲሆን፣ ይህ ተግባር ለሌሎች ማህበራዊ ተግባራት የሚጠቅም ውጤት አለው፡፡ ሙዚቃ የማህበራዊ ሁነቶችና የሰው ልጅ ችሎታ መፍጠሪያ ጭምር እንጅ ማንፀባረቂያ ብቻ አይደለም፡፡

ሙዚቃ የግለሰቦችን ባህርይ በመግራት የወጡበትን ማህበረሰብ ግንዛቤ እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ ግለሰቦች በሙዚቃ አማካኝነት በሚያገኙት ግንዛቤ የማህበረሰባቸውን ርዕዮተዓለም፣ ስሜቶችን፣ አመለካከቶችን፣ ማህበራዊ ደንቦችን ይጋራሉ፡፡ ይህ በተራው በሙዚቃ የሚከወን ትልቅ ልምድ ይፈጥራል፡፡ በዚህ ረገድ ሰዎች ለሙዚቃ ፈጠራም ሆነ ክወና የሚሰጡት ምላሽ ደመነፍሳዊ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በሙዚቃ አማካኝነት ራሳቸውንና ማንነታቸውን የሚገነዘቡ ከሆነና የተገነዘቡትን ደግሞ መልሰው ሙዚቃ አድርገው ከፈጠሩትና ከከወኑት ሙዚቃ ታስቦ የሚሰራ፣ ከሰዎች ግንዛቤን የሚፈልግ እንጅ ደመነፍሳዊ ጉዳይ አይደለም ማለት ነው Ter Ellingson, et al. (1987, 470)፡፡

ከላይ የቀረበው ሃሳብ ሙዚቃ ይሁነኝ ተብሎ ታስቦበት የሚፈጠርና የሚከወን ተግባር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይሁንና የሰው ልጅ ስራዬ ብሎ ሙዚቃን የመፍጠሩን ያህል ሙዚቃም ፈጣሪውን (የሰውን ልጅ) መልሶ ስርዓት የሚያስይዘው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ በሙዚቃና በሰው ልጅ መካከል ያለው ግንኙነት የራሱ የሆነ

ስርዓት እንዳለው የሚጠቁም ነው፡፡ ይህ ስርዓትም አንዱ ለሌላው ህልውና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ Lortat-Jacob, (1984, 20) የተባሉ ፀሃፊ ‹‹ሙዚቃ፣ በሰዎች የተፈጠረ ነው፡፡ በሰዎች (በማህበረሰብ) ስርዓት የሚይዝም ነው፡፡ በዚህ የተነሳ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ዘፈንና የዘፈን አይነቶች አሉት፡፡ ይሁንና ሙዚቃ ደግሞ በምላሹ የሰው ልጅ እንዴት መኖር እንዳለበት፣ ምን አይነት ባህርይ ሊኖረው እንደሚገባ ያስተምረዋል›› በማለት ይገልፁታል፡፡

በመሆኑም ‹‹ሙዚቃና የሙዚቃ ተግባር የሰውን አስተሳሰብ መፍጠሪያና ቅርፅ ማስያዣ ነው›› በሚለው ሃሳብ መስማማት ከተቻለ፣ በሌላ በኩል ይህ ሙዚቃ ለሰው ልጅ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ተግባራት መፈጠርና መከወን አነሳሽ ምክንያት ሊሆን ይችላል ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሙዚቃን ፈጠራና ክወና እንዲሁም ከዋኞችን በማጥናት የማህበረሰብን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ማንነትና ማንኛውንም ጉዳይ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች ሲመረመሩ የሰው ልጅና ሙዚቃ የማይነጣጠሉ ጉዳዮች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ከአንዳንድ ፅሁፎች መገንዘብ እንደሚቻለው የሰው ልጅና የሙዚቃ ግንኙነት ከዚህ በላይ ነው፡፡ ለምሳሌ ሙዚቃ በአንዳንድ ማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ሁለንተናዊ ነገር ነው፡፡ ማህበረሰቡ ህይወቱን በሙዚቃ ጥላ ስር አስጠልሎ የሚኖር ይመስላል፡፡ ለምሳሌ Batt-Rawden (2007) Robinson, (1997, 8)ን ጠቅሰው እንዳሉት በብዙ ምዕራባውያን ባልሆኑ ሃገሮች ሙዚቃ በህይወት ውስጥ ዋና ነገር ነው፡፡ የተለያዩ ጠቃሚ የሆኑ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ሚናዎችን ይጫወታል፡፡ በብዙ ሃገሮች ሙዚቃ የጊዜና ቦታ ማመላከቻ ካርታ ነው፣ መድሃኒት ሆኖ ይፈውሳል፣ ያኗኗር ብልሃትን ያስተምራል ወዘተ፡፡

በአጠቃላይ ሙዚቃና የሰው ልጅ ከፍተኛ ትስስር ያላቸው ሲሆን፣ ለአንዱ ህልውና እርግጠኝነት የሌላው መኖር አስፈላጊ እስከመሆን የሚደርስ ይመስላል፡፡ በመሆኑም በተለይ ባህላዊ ሙዚቃን በማጥናት የሰውን ልጅ ማንነት መገንዘብ የሚቻል ስለሆነ አንድን ቡድን በሙዚቃው አማካኝነት ለማጥናት የሚፈልጉ የባህል ሙዚቃ አጥኝዎች ተግባር ሰዎች በተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች ሙዚቃን ሲከውኑ ሙዚቃው የሚፈጥርባቸውን ስሜት መፈለግ፣ ግለሰቦች በሙዚቃ ፈጠራቸው ወቅት የሚጠቀሙትን የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታና ይህንን ፈጠራቸውን የሚገዛውን ባህላዊ ስምምነት መለየት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገበት የአዝማሪ ዘፈንም የተዘረዘሩትን እንደቃላዊነት፣ አካባቢን መግለፅ፣ ቡድናዊነት የሚሉ ባህርያት

የሚያሟላ ሲሆን፣ የተገለፀውን የአጠናን መንገድም የሚፈልግ በመሆኑ ከሃገረሰባዊ ሙዚቃ ይመደባል። ሃገረሰባዊ ሙዚቃ ባለቤቶቹ ሃገረሰባዊ ሙዚቀኞች ናቸው። ምንነታቸውና ማንነታቸው ቀጥሎ ቀርቧል።

### 2.1.7. ሃገረሰባዊ ሙዚቀኞች

በየትኛውም አለም የሚኖር ማህበረሰብ የእኔ የሚለውና በጋራ የሚከውነው ሙዚቃ አለው። በአንፃሩ በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ሙዚቃን ስራቸው አድርገው የሚከውኑ ቡድኖች አሉ። የዚህ አይነት ቡድን እንዴት ሊከሰት እንደቻለ የሚገልፁት Merriam (1964፣ 123) የስራ ክፍፍል የሌለው ማህበረሰብ የለም። ክፍፍሉ፣ በጎሳ፣ በመደብ፣ በዘር፣ በዕድሜ ወዘተ ሁኔታዎች ሊፈጠር ይችላል። የስራ ክፍፍል ለአንድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚ መጠበቅ የሚውለውን ጠቅላላ ሃይል መከፋፈል ነው። በዚህ ሁኔታ እያንዳንዱ ቡድን ለዚያ ሙያ ሊቅ ነው ማለት ነው። ስለዚህም ሸክላ ሰሪው፣ ዛፍ ቆራጩ፣ ጠንቋዩ ወይም ሙዚቀኛው የራሱን ስራ ሲሰራ የአጠቃላዩን ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ፍላጎት ለማሳካት የራሱን ድርሻ እየተወጣ ነው ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ለሙዚቃው ባለቤት የሆነ፣ ለዚህም በመደበኛነት የሚከፈለው ወይም ሽልማት የሚሰጠው፣ ወይም ምስጋናን የሚያገኝ ሙዚቀኛ የተባለ ባለሙያ አለ። ይሁንና አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ባለሙያ ሊባል የሚችለው በሌላው የማህበረሰብ አባል ባለሙያነቱ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው። ግለሰቡ ባለሙያነቱን ቢያምን እንኳን ማኅበረሰቡ ያለውን ሚናና ደረጃ እስካልተቀበለው ድረስ እውነተኛ ባለሙያ አይደለም። ማህበረሰቡ የዘፋኙን ዘፋኝነት የተቀበለው መሆኑ በተለያዩ መንገዶች ይገለፃል። ብዙ ጊዜ የተለመደውም ክፍያ ነው። ክፍያው በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌላ ለኑሮ አስፈላጊ በሆነ ነገር ሊሆን ይችላል። አለዚያ ደግሞ ሽልማት መስጠት ይሆናል ይላሉ።

በዚህ መንገድ በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ሙዚቃን ልማዳዊ በሆነ መንገድ ከቤተሰቦቻቸው በመውረስ በዘፋኝነት ታውቀውና መተዳደሪያቸውን ሙዚቃ አድርገው የሚኖሩ የተለያዩ ቡድኖች መኖራቸውን መዛግብት አስፍረዋል። በእርግጥ እነዚህ ባህላዊ የሙዚቃ ቡድኖች በየሃገሩ የሚጠሩበት ስም የተለያየ ነው።

ለምሳሌ መነሻቸው ህንድ ሆኖ በመላው አለም ተበትነው የሚኖሩ ‹‹ጅፕሲ /Gypsy›› የሚባሉ የሙዚቃ ቡድኖች ሲኖሩ የዚህ አይነት ቡድኖች በፈረንሳይ፣ ‹‹ትራውባዶር›› (troubadour) ፣በእንግሊዝ ‹‹ሚኒስትራል›› (minstrels)፣ በጥንታዊ ግሪክ

‹‹ራፕሶደስ›› (rhapsodes) ፤ በፓኪስታን ‹‹ሚራሲስ›› (Mirasis)፤ በጀርመን ‹‹ሴልቲክ›› (seltic) በተጨማሪ ‹‹ሚኒሲንገርስ›› (minnesingers)፤ በምዕራብ አፍሪካ፣ ‹‹ግሪዮ›› (Griot) ይባላሉ (Cohn, 1973; Oakley, 1983; Sage, 1990; Sheppared, 2004)፡፡

ከእነዚህ ውስጥ ጎላ ያለ ታሪክና በዛ ያሉ መዛግብት ያሏቸውን፣ በአውሮፓና በምዕራብ አፍሪካ የሚኖሩ ‹‹ጅፕሲ/Gypsy›› እና ‹‹ግሪዮ››(Griot) ስለሚባሉ የሙዚቃ ቡድኖች ጥቂት ማለት ከርዕሱ አንፃር ሃሳብን ግልፅ ሊያደርግ ስለሚችል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

Sheppared (2004) እንደሚሉት አውሮፓ ብዙ አይነት ባህላዊ የሙዚቃ ከዋኝ ቡድኖች የሚታዩበት አህጉር ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶች ቢጠቀሱ በደቡብ ፈረንሳይና በሰሜን ጣሊያን ትራውባዶርስ ተብለው የሚታወቁት፣ በጀርመን ሚኒሲንገር የሚባሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በፈረንሳይና ጣሊያን የሚታወቁት ትራውባዶሮች ከአስራ አንደኛው እስከ አስራ ሶስተኛው ክፍለዘመን ገንነው የነበሩ፣ ራሳቸውን በመሳሪያ አጅበው ሙዚቃን የሚጫወቱ ባህላዊ ዘፋኞች ናቸው፡፡ የዘፈን ግጥማቸው ምጣኔው ያማረ ይዘቱም ፍቅር (በተለይም የቤተመንግስት ውስጥ) ነው፡፡ ለንግግር ሙሉ ነፃነት አላቸው፡፡ የሚፈሩት ነገር የለም፡፡ ዘፈናቸው ዛሬም ድረስ የአውሮፓ ዘፋኞች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ችሏል (Gaunt and Kay 1999, 97)፡፡

የፈረንሳይ ትራውባዶሮች ከአስራ አንደኛው እስከ አስራ አራተኛው ክፍለዘመን የታዩ ናቸው፡፡ በመላው ባህርያቸውና ተግባራቸው ከትራውባዶሮች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ በተለይ ስለቤተመንግስት ፍቅር የሚዘፍኑ ሲሆን የዘፈን ግጥማቸው ተራኪ ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ከአገልግሎታቸው የተነሳ ከላይኛው መደብ አባላት ጋር የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ በኋላ ግን ወደታች ወርደው የሰራተኛው መደብ አባል ሆነዋል፡፡

Sheppared (2004) እንደሚሉት የጀርመን ሚኒ ሲንገሮች ከ1150 እስከ1325 የታዩ ናቸው፡፡ ጠቅላላ ባህርያቸው ከትራውባዶሮችና ከትሮውቬሮች ጋር ይመሳሰላል፡፡ የግጥማቸው ይዘት ፖለቲካና ስነምግባር ቢኖረው ብዙው ግን ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር የሚል ትርጓሜ ያለው *Minne* የሚለው ስማቸውም ከግጥሞቻቸው ይዘት የተወሰደ ነው፡፡ እነዚህ ቡድኖች መጀመሪያ ላይ የተከበረ ቦታ ቢኖራቸውም የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ባደረሰችባቸው ጫና ቀስ በቀስ ደረጃቸው እየቀነሰ መጥቶ ወደ አስራ አምስተኛው ክፍለዘመን አካባቢ እየጠፉ መጥተዋል፡፡ በአውሮፓ የባህላዊ ሙዚቃ

ከዋኞች ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸውና ዛሬም ድረስ ሙዚቃቸውን በመከወን ላይ የሚገኙ ህዝቦች የሮማንያ ጅፕሲዎች ናቸው፡፡

በመስኩ ያጠኑ ሰዎች እንደሚሉት ጅፕሲዎች የራሳችን የሚሉት ቦታ (ሃገር) የሌላቸው፤ ነገር ግን ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ጅፕሲዎች ከ14ኛው ክፍለዘመን ጀምረው ከህንድ በመነሳት (ጊዜው ከፀሃፊ ፀሃፊ ይለያያል) በአውሮፓ መታየት ጀመሩ፡፡ ከህንድ ተነስተው ወደኢራን ተሰደዱ፣ ሃንጋሪ፣ ሰርቢያ፤ ወደሌሎች ባልካን ሃገሮች ደረሱ፤ ቀጥሎ ወደፖላንድ፤ ሩሲያ፣ ስዊድን ፣ ስፔን፣ ታላቋ ብሪታኒያ ተበተኑ፡፡ እንደየሚኀዙባቸው ሃገሮች ጥቂት ጅፕሲዎች ወደሙስሊም ወይም ወደኦርቶዶክስ ተቀየሩ፡፡ ብዙዎቹ ግን ካቶሊክ ሆኑ፡፡ ከቅድመ ክርስትና በፊት የነበሩ እምነቶችን የሚያምኑም አሉ፡፡ ‹‹በዘላናዊ›› የአኗኗር ስርዓታቸው የተነሳ ህይወታቸው ፈረሶችን፣ ሌሎች እንስሳትን፣ አልማዝና ወርቅ በመሸጥ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ሙዚቃን መጫወት በተለይ ዋና የመተዳደሪያ መንገዳቸው ነው፡፡ ሙያው በቤተሰብ ከአባት ወደልጅ የሚተላለፍ ነው፡፡ ክዋኔው በቡድን ነው፡፡ በሰርግ፣ በድግሶችና በመሳሰሉ ቦታዎች ይከወናል፡፡ ዕውቀቱ በልምድ የሚገኝ ስለሆነ የኖታ ዕውቀት አይጠይቅም፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ከቡድኑ ውስጥ የተሻለ ችሎታ ያላቸው ጅፕሲዎች ለባላባቶች ይዘፍኑ ነበር (Cohn, 1973; Oakley 1983; Burton, 2000)፡፡

እንደአውሮፓ ሁሉ በአፍሪካም (በተለይ በምዕራብ) ግሪዮ የሚባሉ ታዋቂ የሙዚቃ ቡድኖች አሉ፡፡ መረጃዎች ‹‹ግሪዎ›› የሚለው ቃል አፍሪካዊ ቃል አለመሆኑ እንጅ የት መጣው እንደማይታወቅ ይገልፃሉ፡፡ ጥቂት መረጃዎች ግን ቃሉ ፈረንሳይኛ እንደሆነና ወደ አፍሪካ የመጣው ፈረንሳዮች አፍሪካን ማሰስ ከጀመሩ ጀምሮ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Sage (1990, 3-4) እንደሚሉት በምዕራብ አፍሪካ ስለግሪዮች አመጣጥ የሚያወሩ ቃል ትረካዎች፣ ግሪዎች በሙሉ የስጋ ዝምድና እንዳላቸው የሚተርቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዱ ቃል ታሪክ የሚከተለውን ይላል ይላሉ፡-

> ሁለት ወንድማማቾች ረጅም የእግር መንገድ ሲኀዙ ሰንብተው ስንቃቸው ያልቅባቸዋል፡፡ ረሃብ እየፀናባቸው ስለመጣ ታላቅ ወንድም ጠበንጃ ይዞ ለምግብ የሚሆን ነገር ለማደን ጫካ ይገባል፡፡ ትንሽ ቆይቶ ታናሽ ወንድም የጠበንጃ ተኩስ ድምፅ ይሰማል፡፡ ተኩሱን ተከትሎ ታላቅ ወንድም በአንድ እጁ ጠበንጃውን በሌላ እጁ ደግሞ ሙዳ ስጋ ይዞ እያነከሰ ይመጣና ስጋውን አብስሎ ለታናሽ ወንድሙ ይሰጠዋል፡፡ እሱ ግን የራሱን ድርሻ እዚያው

በልቶ እንደመጣ ገልፆ ሳይበላ ይቀራል። ከዚያም ጉዞ ይጀምራሉ። ከሶስት ቀን ጉዞ በኂላ ታላቅ ወንድም መጓዝ አልቻለም። ምክንያቱም ከሶስት ቀን በፊት ‹‹አድኜ›› አመጣሁልህ ሲል ለወንድሙ የሰጠው ስጋ ከእግሩ የቆረጠው ኑሮ መጓዝ አቃተው። ያም ሆኖ ከብዙ ቀን ድካም በኂላ ከጉዟቸው መጨረሻ ይደርሳሉ። ታናሽ ወንድም ታላቅ ወንድሙ ስለከፈለለት መስዋዕትነት ዘፈን ደርሶ ያበረክትለታል።

ዛሬ ራሳቸውን በዘፈን የሚያስተዳድሩ የምዕራብ አፍሪካ የባህል ሙዚቃ ቡድኖችም የእነዚህ ሰዎች ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው ተብሎ ይታመናል። ይህ ተረት ግሪዎችን ከሌላው ማህበረሰብ የተለዩና ደረጃቸው ያነሰ እንዲሆን አድርጓቸዋል። ምክንያቱም ተረቱ እንደሚገልፀው የግሪወች አባት ተብለው ከሚጠሩት ሰዎች ውስጥ አንዱ በአብዛኛው የሰው ልጆች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ፀያፍ የሚባለውን የሰው ስጋ መብላት ተግባር ፈፅሟልና። ስለዚህ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር መጋባት አይችሉም።

ግሪዮች ምንም እንኳን ማህበራዊ ደረጃቸው ዝቅ ያለ ቢሆን፣ በባህላዊው የምዕራብ አፍሪካ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ሚና አላቸው። በጠለቀ የቋንቋ ችሎታቸው ይታወቃሉ፤ የማህበረሰቡን ታሪክና ዕውቀት በጥልቀት ያውቃሉ። ታዳሚያቸው በክዋኔያቸው ተሳታፊ እንዲሆን የማድረግ ችሎታ አላቸው፤ ለመሪዎች አፈቀላጤ ሆነው ያገለግላሉ፤ የታሪክ ቀናትን ይጠቁማሉ፤ በግጥሞቻቸውና በቀልዶቻቸው ህዝብን ያዝናናሉ፤ ያስተምራሉ፤ የዘር ሃረግን ይቆጥራሉ። ታሪክ አዋቂዎች በመሆናቸው ያለፈውን ጊዜ ከአሁኑ ጋር ያገናኛሉ። ለሁለቱም ዘመን ምስክር ናቸው።

Okpewho (1992, 27) እንደሚሉት ግሪዮች እንደጋብቻ፣ የህፃናት ስም ማውጣት፣ ቀብር የመሳሰሉ በገጠርና በከተማ የሚከወኑ በዓላትንና ክብረበዓላትን በሙዚቃ በማጀብ ለበዓላቱ ድምቀትን ሰጥተው ለራሳቸው ደግሞ መተዳደሪያቸውን የሚያገኙ የሙዚቃ ቡድኖች ናቸው። ዛሬ የግሪዮች ሚና ከመንደር አዝናኝነትና ታሪክ ነጋሪነት ወደሬዲዮና ቴሌቭዥን አዝናኝነት መጥቷል። ብዙዎቹ ታዋቂ የባህል ዘፈን ተጫዋቾች ናቸው።

እንደ Okpewho (1992) ማብራሪያ ‹‹የግሪዮች የሙዚቃ አከዋወንና የሚያገኙት ገቢ ከጊዜ ጊዜ እና ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያያል። በቀድሞው ጊዜ ለመሪዎች የዘፈን አገልግሎታቸውን ይሰጣሉ። መሪዎች በተራቸው ለመኖር የሚያስፈልጓቸው ነገሮች

ይሰጧቸዋል፡፡ የጎሳ አመራር በቅኝግዛት ምክንያት ሲቀር ደግሞ ሙያቸውን ከአዲሱ ዘመን ጋር የሚስማማ እንዲሆን አድርገው አስተካክለውታል፡፡

ከላይ በአውሮፓና አፍሪካ የሚገኙ ገናን ባህላዊ የሙዚቃ ቡድኖችን ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ እነዚህ ቡድኖች ከበቀሉበት ቦታ ጀምሮ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ልዩነት ያላቸው ቢሆኑም በርካታ የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች እንዳሉም ታይቷል፡፡ ባህላዊ የሙዚቃ ቡድኖች ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ሙዚቃን የሚከውኑ ቡድኖች ናቸው፡፡ ሁሉም ቡድኖች የት መጣቸውን የሚገልፁበት ትረካ አላቸው፡፡ ሁሉም ሙዚቃን በልምድ ከቤተሰብ፣ ከአካባቢ የተማሩ ናቸው፡፡ ሙዚቃ መተዳደሪያቸው ነው፡፡ በሚኖሩበት ማህበረሰብ ዘንድ የተናቁ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ አገልግሎታቸው በቤተመንግስት ውስጥ የነበረ፣ አሁን ግን ሙዚቃን ወደስራ ቀይረውት የሰራተኛው መደብ አባል የሆኑ ናቸው፡፡ ሙዚቃቸው ጥልቅ፣ የጥበብ ችሎታቸውም ምጡቅ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ‹‹ፖፕላር››[5] በሚባለው ሙዚቃ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር ችለዋል፡፡ ዛሬ ዛሬ ሙዚቃቸውን በካሴት እያስቀረፁ መሸጥ ጀምረዋል የሚሉት ሊጠቀሱ የሚችሉ መመሳሰሎቻቸው ናቸው፡፡ የተዘረዘሩትን ባህርያት በአመዛኙ የሚጋሩ የሙዚቃ ቡድኖች በኢትዮጵያም አሉ፡፡ እነዚህ የዘፈን ቡድኖች አዝማሪዎች ይባላሉ፡፡ ምንነታቸው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 2.1.8. አዝማሪ ምንድን ነው?

አዝማሪ የሚለውን ቃል/ፅንሰሃሳብ ብያኔ ለመፈለግ የተሰበሰቡ መረጃዎች ሲተነተኑ አዝማሪ ከሶስት አቅጣጫዎች ሊበየን እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ አቅጣጫዎች ከፀሃፍት አንፃር፣ አዝማሪ ካልሆኑ ሰዎች አንፃርና ከራሳቸው ከአዝማሪዎች አንፃር የተሰጡ ናቸው፡፡

አዝማሪን ርዕሰጉዳያቸው አድርገው የፃፉ ሰዎች ፅሁፎቻቸውን በጉዞ ማስታወሻዎች፣ በጋዜጦችና የምርምር ስራዎችን በሚያወጡ መፅሄቶች ላይ አቅርበዋል፡፡ Shelemay and Jeffery (1997) እንደገለፁት አስራ ሰባት ሃገር ጎብኝዎች (ተጓዦች) በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ የተለያዩ ፅሁፎችን ፅፈዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎች አዝማሪን ያነሱ

[5] ፖፕላር ሙዚቃ (ባህል) ፈጣንና ብዙ አይነቶች ያሉት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ቁጥሩና አይነቱ ብዙ ለሆነ ታዳሚ የሚዘጋጅ ሙዚቃ ነው፡፡ ተስተላልፎው እንደ ቴሌቭዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጣና "ኢንተርኔት" ባሉ መገናኛ ብዙሃን ነው፡፡ የሰዎችን ትኩረት ይዞ የሚቆየው በመገናኛ ብዙሃን እየተላለፈ ባለበት ወቅት ብቻ ነው፡፡ መተላለፍ ሲያቆም የሰዎች ትኩረት ይቀንሳል፡፡ ፖፕላር ሙዚቃ ፖፕ ሙዚቃም ተብሎ ይጠራል Sims and Stephens (2005, 4)፡፡

ሲሆን፣ በበርካታዎቹ ማስታወሻዎች ውስጥ የተገለፀው በምርጥ ቋንቋና በጥልቅ የጥበብ ችሎታ ዘፈንን የሚከውኑ የዘፈን ቡድኖች መሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ Powne (1968) እንደገለፁት ጀምስ ብሩስ በአዝማሪዎች ላይ ከፃፉ የውጪ ሃገር ጎብኝዎች አንዱ ሲሆን አዝማሪዎች በ1770 በራስ ሚካኤል ስሁል[6] ላይ በገጠሟቸው ስድብ አዘል ቅኔያዊ ግጥሞች የተነሳ በራስ ሚካኤል ትዕዛዝ ጎንደር ውስጥ በጅምላ ሲጨፈጨፉ ማየቱን ጀምስ ብሩስ ፅፏል ብለዋል፡፡

ቀደምት ጋዜጦች ሌሎች ስለአዝማሪዎች የተፃፈባቸው አውዶች ናቸው፡፡ የተለያዩ ፀሃፍት አዝማሪዎችን አስመልክቶ ስለጥንታዊ ተግባራቸው፣ ስለወቅታዊ ሁኔታቸው፣ ስለሚናቸው መለወጥ ወዘተ ስሜታቸውን ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ ፀጋዬ ደባልቄ[7] የተባሉ ፀሃፊ ዓርብ 20/2/1968 ዓ.ም.አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ባወጡት ‹‹አዝማሪ ምን አለ›› የሚል ፅሁፍ አዝማሪ ላይ ያላቸውን ሃሳብ እንደሚከተለው አስፍረዋል፡-

> የጥንት አዝማሪ እንደዘፋኝ እንደመሰንቆና ክራር ተጫዋች፣ እንደታሪክ ተራኪ፣ እንደፖለቲካዊ አስተያየት ሰጪ፣ እንደፍቅር መላክተኛ፣ እንደታዛቢና እንደ ህብረተሰቡ ቅሬታ ተናጋሪ፣ እንዲሁም እንደ አጫዋች በመሆን ስላገለገለ በጥንት ጊዜ የአዝማሪ ተፈላጊነት በጥቂቱ የተገመተ አልነበረም፡፡ በጥንቱ ጊዜ ድርጅት በብዛት ባለመኖሩ፣ የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ባለመኖራቸው የህዝብ መገናኛ መሳሪያዎችና እንዲሁም የመገናኛው ችግር ስለነበር የጥንቱ አዝማሪ ብዙ ስራ ነበረበት፡፡ ዛሬ ግን በጥንቱ አስተሳሰብ ከላይ የተጠቀሱትን ባያከናውንም በህብረተሰብ ላይ

[6]ራስ ሚካኤል ስሁል 1761 እስከ1845 ድረስ በኢትዮጵያ ታሪክ ‹‹ዘመነ መሳፍንት ተብሎ በሚጠራው ዘመን›› ውስጥ የነበሩና ትግራይን ለረጅም ዘመን የመሩ መስፍን ናቸው፡፡ በምፅዋ በኩል ከቱርኮች ባገኙት የጦር መሣሪያ የተነሳ በግዛቱ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጥረው ኑረዋል፡፡ ስልጣናቸውን እስከጎንደር ድረስ አጠናክረው ነበር፡፡ በተለይም አፄ ኢዮአስ የኦሮሞዎችን መስፋፋት ፈርተው እነሱን እንዲከላከሉላቸው ወደጎንደር ጋበዟቸው፡፡ በጎንደርም የእቴጌ ምንትዋብን ልጆች አንደኛዋን ለልጃቸው አጋብተው፣ አስቴር የምትባለዋን ሌላዋን ደግሞ ለራሳቸው አግብተው ስልጣናቸውን አደላደሉ፡፡ ከዚያም ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ድፍረት የጎንደር ነገስታትን አንዱን ከስልጣን በማውረድ ሌላውን ስልጣን በማስያዝ የአስተዳደር ስርዓቱን ተፅዕኖ ፈጥረውበት ቆዩ፡፡ ወደጎንደር ያመጧቸውን አፄ ኢዮአስን ከስልጣን አውርደው የራሳቸው ምርጫ የሆነውን ዳግማዊ ዮሐንስን አነገሡ፡፡ ዓመት ሳይሞላ ደግሞ ዮሐንስን አውርደው ተክለ ሐይማኖትን አነገሡ፡፡ ጀምስ ብሩስ በ1770 ጎንደር ሲመጣ ራስ ሚካኤል፣ ሚስታቸው አስቴርና አማታቸው እቴጌ ምንትዋብ በአስተዳደሩ ላይ ተፅዕኖ ፈጥረው ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን የአማራና የኦሮሞ ራሶች አንድ ላይ በመሆን ራስ ሚካኤል ስሁልን ስለወጓቸው ወደትግራይ ተመልሰዋል Henze (2000፣ 121)፡፡

[7]የኢትዮጵያ ሬዲዮ ባልደረባ፣ የባህል ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ፣ ሙዚቀኛ፣ በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት መምህር፣ የሙዚቃ አሰልጣኝ፣ የነበሩ፣ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የሙዚቃ ሰው የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር (2007 ፣1) ፡፡

ስለሚያስከትሉት ችግሮች (መጠጥ፣ ዝሙት፣ ሌብነት፣ ቁማር ስለመሳሰሉት) ጉዳታቸውን ሊያመለክት ይችላል፡፡

ሲሉ አዝማሪ ላይ ያላቸውን ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ ፀሃፊው በዚህ ፅሁፋቸው የአዝማሪዎችን ተደራቢ ስራዎች ያነሱ ቢሆንም እነዚህ ሁሉ ስራዎች የሚከወኑት በአዝማሪው የዘፋኝነት ችሎታ ላይ ተመስርተው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ፅሁፉ ‹‹አዝማሪዎች ዘፋኞች ናቸው›› ማለቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንን ግንዛቤ የሚያጠናክረውም በስልሳዎቹ ይፃፉ የነበሩ የአዲስ ዘመን ጋዜጦች ዘፈን የሚዘፍኑ ሰዎችን በሙሉ አዝማሪ ብለው መጥራታቸው ነው፡፡ ለምሳሌ አርቲስት ታምራት ሞላን ቤተሰቦቻቸው ልጃችን አዝማሪ ሆነ በሚል ተጣልተዋቸው እንደኖሩ የገለፁት፣ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በሚወጡ ፅሁፎች ስለብዙነሽ በቀለ፣ አለማየሁ እሸቴ፣ ስራዎች የቀረቡ ፅሁፎች ርዕሶቻቸው፣ ‹‹አዝማሪው ምን አለ?››፣ አምዶቻቸው ደግሞ ‹‹አዝማሪ›› የሚሉ መሆናቸው እንደ ማስረጃ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው (አዲስ ዘመን፣ 1968)፡፡

በሁለተኛነት ለቃሉ ብያኔ የሰጡ ተብለው በዚህ ጥናት የታዩ ወገኖች ርዕሱን ስራዬ ብለው መርምረው ብያኔ የሰጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ Powne (1968, 61) ‹‹The Azmari is the singing gazelle of Ethiopian a remarkable feature of the Musical scene in the traditional highlands›› በማለት አዝማሪዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ አካባቢዎች (በሰሜኑ ክፍል) የሚገኙ ዘፋኞች ናቸው በማለት በይነዋል፡፡ Ashenafi (1971, 168) ደግሞ ቃሉን ከሙያው ባህርይ በመነሳት ግጥምና ዜማውን በሃገረሰባዊ መሳሪያ (መሰንቆ) በማጀብ በታዳሚው ፊት ብቻውን ወይም በጥንድ ሆኖ የሚከውን እና ታዳሚውን የሚያዝናና ዘፋኝ ማለት ነው ብለዋል፡፡ በመጨመር አዝማሪ የሚለው ቃል «ዘመረ» ከተባለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን፣ ትርጉሙ አመስጋኝ ማለት ነው ይላሉ፡፡ በዚሁ ምድብ በማስገባት ለቃሉ ብያኔ የሰጡ መዝገበ ቃላትም ሲታዩ ለምሳሌ ደስታ ተክለ ወልድም (1962 ፣496) አዝማሪን «ያዘመረ፣ የሚያዘምር፣ ዘፋኝ፣ ባለማሲንቆ፣ አርኾ፣ ጧሂ» ሲሉ የማህበረሰብን ግንዛቤና የሙያውን ባህርይ መሰረት አድርገው ይበይኑታል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል መዝገበቃላት ደግሞ እንዲሁ የማህበረሰብን ግንዛቤና የሙያውን ባህርይ መሰረት አድርጎ «በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እየታጀበ በመዝፈን የሚተዳደር ሰው»፣ «ምላሰኛ ተሳዳቢ» ሲል ሁለት ብያኔ ይሰጣል፡፡ Leslau and Ken (2001 ,74) ደግሞ በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ አዝማሪ በመባል የሚታወቁ ከትክሻቸው ማሲንቆ ከክንዳቸው

ክራር[8] (አፅንኦት የእኔ) የማይጠፉ ከቦታ ቦታ ከመሸታ መሸታ ከሰርግ ሰርግ እያሉ ሰውን በማሞገስ፣ የፍቅር ዘፈን በመጫወት ኑሯቸውን የሚመሩ ሰዎች አሉ በማለት ከሚይዙት የሙዚቃ መሳሪያና ስራቸውን ከሚሰሩበት ቦታ አንፃር አዝማሪን ገልፀዋል፡፡

ፀሃፍት ከላይ በቀረበው መልኩ ለቃሉ የየራሳቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን ብያኔዎችን ለመስጠት የሙያው ባህርይ፣ የማህበረሰቡ ግንዛቤ፣ አዝማሪዎች የሚይዙት የሙዚቃ መሳሪያ የሚሉ ሶስት መስፈርቶችን እንደተጠቀሙ ማየት ይቻላል፡፡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የተሰጡት ብያኔዎች ሲታዩ፣ አዝማሪ ማለት መሰንቆ የተባለ የሙዚቃ መሳሪያን በመጠቀም ዘፈን የሚዘፍን፣ ዘፈንን ለሌላ ሰው ደስታ ሲል የሚዘፍን፣ ዘፈንን ከቦታ ቦታ፣ ከመሸታ ቤት መሸታ ቤት፣ ከሰርግ ሰርግ፣ እየዞረ የሚዘፍን፣ ሰውን የሚሳደብ፣ የሚሉ ዋና ሃሳቦች ሊወጡላቸው የሚችሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ አዝማሪዎች ላይ የቀረቡ ፅሁፎችን የተጓዦችና የሃገር ጎብኝዎች የጋዜጣና የተመራማሪዎች ፅሁፎች ብሎ በሶስት መክፈል ይቻላል፡፡ በእነዚህ ፅሁፎች ውስጥ እያንዳንዱ ፀሃፊ አዝማሪዎችን ያየበት የራሱ አተያይና መስፈርት ቢኖረውም በሶስቱም መንገዶች የቀረቡ ፅሁፎች ‹‹አዝማሪ ዘፈንን በመዝፈን በሚያገኘው ገቢ ራሱን የሚያስተዳድር ቡድን ወይም የቡድኑ አባል የሆነ ግለሰብ ስም ነው›› የሚሉ ናቸው፡፡

ይህ ጥናት ከፀሃፍት ሌላ ለአዝማሪዎች ብያኔ የሰጠ ወገን መኖሩንም አመልክቷል፡፡ ይህ ወገንም አዝማሪ ያልሆነው የማህበረሰብ ክፍል ነው፡፡ አዝማሪ ያልሆነው ማህበረሰብ አዝማሪን የሚገልፅበት መንገድ አለው፡፡ ይህ መንገድም አዝማሪ ለሚለው ቃል/ፅንሰ ሃሳብ ብያኔ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ ብያኔ ግን በቀጥታ ‹‹አዝማሪ ምንድን ነው?›› በሚል ጥያቄ የተገኘ ሳይሆን ጥናቱ በተደረገበት ቦታ የተገኙ ሰዎች በተለያዩ አውዶች አዝማሪ የሚለውን ቃል ነገሮችን ሲገልፁበት በመስማት ከቃሉ አጠቃቀም የተገኘ ነው፡፡ ለዚህ ማስረጃ ይሆኑ ዘንድ ሶስት አውዶች ቀርበዋል፡፡

**አውድ አንድ፡-** ቀለባስ ተብሎ ወደሚጠራው የጥናት ቦታ ስጓዝ ከፅድ ዛፍ ሙጫ የተሰራ፣ ለመሰንቆ ማለስለሻ የሚያገለግል ሙጫ ይዤ ነበር (ከአንድ መረጃ ሰጪ

---

[8]አዝማሪ መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልፁት አዝማሪ መሰንቆ እንጂ ክራር አይዝም፡፡ አዝማሪ መሰንቆ የመያዙ ልምድም የመጣው እዝራ ድንግል ማርያም ስትሞት መሰንቆ ከመጫወቱ ጋር ነው አዝማሪዎች ደግሞ የእዝራ ዘሮች ነን ስለሚሉ ለእነሱ መሰንቆ እንጅ ክራር አልተሰጠም፡፡ ታሪኩን ‹‹እዝራ በመሰንቆ ዳዊት በበገና እያጫወታት ሳታውቀው አለፈች ያን መላከ ሞት›› በሚለው ግጥም ያስሩታል (አሰፋ ለገሰ፣ መላኩ መድፉ፣ 16/04/2005 ዓ.ም)፡፡

ነበር የተቀበልሁት)፡፡ በቦታው ደርሼ መረጃ ስሰበሰብ ከቆየሁ በኋላ አንዱን መረጃ ሰጪዬን መሰንቆ ተጫወት አልሁት፡፡ ‹‹ለመሰንቆው ማለስለሻ የሚሆን ሙጫ የለኝም›› አለ፡፡ ‹‹እንካ በዚህ አለስልስ፤ ግን ትመልሳለህ›› ብዬ የያዝሁትን ሙጫ ሰጠሁት፡፡ ሰውዬው በሁኔታው ተገርሞ ሲያበቃ አሁን እኮ ፍለጋ ልሄድ ስል አገኘሁ፡፡ "አልመልስልሽም" አለ፡፡ ይህንን ጊዜ አብረው ያሉ ሰዎች፣ አይ አንተ እንደመስጠት እስዋ ለመማሪያ ከሰው የተቀበለችውን እንዴት ትወስዳለህ በሚል ተግሳፅ እንዲመልስ አደረጉት፡፡ ከመረጃ ስብሰባ በኋላ አብረውኝ ከነበሩት ሁለት የመቄት ወረዳ ተወላጅ የሆኑ የጥናት ረዳቶቼ (አንዱ መምህር፣ አንዱ ‹‹አማተር›› የዳንስ ባለሙያ) ጋር ወደ ከተማ እየተመለስን የነበረውን ሁኔታ ስናወራ ሙጫ እወስዳለሁ ያለውን አዝማሪ ሁኔታ አነሳሁ፡፡ ሁለቱ አጋዥ መረጃ ሰብሳቢዎችም በመቀባበል «ታዲያ ይኸ ምን ይገርምሻል ድሮ አዝማሪ ከልመና በስተቀር ምን ሙያ አለው ልመና ለምዶበት ነው እንጂ እሱ መስጠት የሚገባውን ነገር ስጡኝ ይላል?›› የሚል ምላሽ ሰጡኝ፡፡

**አውድ ሁለት፡-** ለጋምቦ ወረዳ ውስጥ ኢላዳ፣ በረከት ወደሚባለው የአዝማሪ መንደር ሙሐመድ ፈንታሁን ከተባለ መንገድ መሪዬ ጋር እየተጓዝሁ ነው፡፡ ትናንት ከሙሐመድ ጋር ወደዚህ ሰፈር ለመሄድ መንገድ ከጀመርን በኋላ አዝማሪዎች ገበያ ስለሚሄዱ እንደማይኖሩና ነገ እንጂ ዛሬ የማናገኛቸው መሆኑን ባገኘነው መረጃ መሰረት ነው ዛሬ የምንሄደው፡፡ በመሃል ‹‹ሙሐመድ አዝማሪዎችን እንዳናጣቸው እንጂ? አለ፡፡›› እኔ ‹‹ለምን ሰጋህ የቀበሌው ሊቀመንበር ይገኛሉ ብሎ የለም?›› አልሁት፡፡ ‹‹አይ አንቺ አልገባሽም አዝማሪ እኮ አርፎ አንድ ቦታ አይቀመጥም መዞር ነው ስራው›› የሚል መልስ ሰጠ፡፡

**አውድ ሶስት፡-** አንድ ቀን ደሴ ከተማ ውስጥ ሴቶች ተሰብስበው ያወራሉ፡፡ ወሬው መቀላለድ አለበት፡፡ ከመካከላቸው አንደኛዋ ሌላዋን ውፍረቷን መነሻ አድርጋ በነገር ጎሽም አደረገቻት፡፡ ይህቺ ጉሽማ የደረሰባት ሴትም ጎሻሚዋን ‹‹አንቺ አዝማሪ፣ አዝማሪ እኮ ነሽ›› አለቻት፡፡ ምንድን ነው አዝማሪ አለች የመጀመሪያዋ ተናጋሪ፤ ተሳዳቢ ነዋ ስትል መለሰችላት፡፡

እነዚህ ለምሳሌነት የቀረቡ ሶስት አውዶች መረጃ በተቀናበረና ባልተቀናበረ ሁኔታ የተሰበሰበባቸው ናቸው፡፡ በሁሉም አውዶች መረጃ ሰጪዎች አዝማሪዎችን የሚረዱባቸውና የሚገልፁባቸው መንገዶች ይታያሉ፡፡ እያንዳንዱ ሲታይ በመጀመሪያው አውድ አዝማሪው ሙጫውን ለመውሰድ ያሳየውን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የተሰጠው አስተያየትና ሃሳብ ‹‹አዝማሪ ለማኝ ነው መቀበል እንጅ መስጠት

አያውቅም›› የሚል ነው፡፡ ወደሁለተኛው አውድ ሲመጣ ደግሞ ‹‹አዝማሪ ዘዋሪ ነው፡፡ ከአንድ ቦታ ተረጋግቶ አይቀመጥም›› ይላል፡፡ ሶስተኛው አውድ ‹‹አዝማሪ ተሳዳቢ ነው ››ይላል፡፡

**አውድ አራት፡-** ደረቅ ወይራ ውስጥ አዝማሪ ባልሆኑ ሰዎች የተጠኘ ውይይት ወቅት ሽመልስ የተባሉ የዕድሜ ባለፀጋ የመንደሩ ነዋሪ የአዝማሪን ምንነትና ጥቅም ሲገልፁ፡ ‹‹አዝማሪዎች ስራቸው መዝፈን ነው፡፡ እነሱ ካልመጡ ዳሱ ዳስ አይሆንም፤ እንዲያውም ዳስ ሆኖ ካልመጡ እነዚህ ሰዎች ተጣልተዋል እንዴ ምንድን ነው ነገሩ ተብሎ ይሸመገል ነበር! ተጫዋች አልመጣምሳ ይባላል፡፡ ሌላው ሰው ይህንን ይላል›› ብለዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት አውዶች በቅደም ተከተል ለማኝ፣ ዘዋሪ፣ ተሳዳቢና፣ ዘፋኝ የሚሉ ስያሜዎች ለአዝማሪዎች ተሰጥተዋል፡፡

አዝማሪዎች ስያሜዎችን ያገኟቸው ከሚሰሩት ስራ ባህርይና ከሚከውኑት ተግባር አንፃር ነው፡፡ ‹‹ለማኝ›› የሚለው ስያሜ አዝማሪዎች ከሌላው ሰው በሚያገኙት ስጦታ የሚተዳደሩ በመሆናቸው፣ ‹‹ዘዋሪ›› የሚለው ደግሞ አዝማሪዎች ዘፈንን ከቦታ ቦታ እየተዟዟሩ የሚሰሩ በመሆናቸው፣ ‹‹ተሳዳቢ›› የሚለው ጥበብ የሰጠቻቸውን ‹‹የነፃነት መብት››[9] ተጠቅመው ያልተደሰቱበትን ሰው የሚተቹ በመሆናቸው፣ የተሰጧቸው ስሞች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ እስካሁን ከቀረቡት ሃሳቦች በወሎ አካባቢ አዝማሪ ያልሆነው የማህበረሰብ ክፍል አዝማሪ ለሚለው ቃል የሰጠው ብያኔ አዝማሪ ማለት ዋና መተዳደሪያቸው ዘፈን የሆነ፣ ማህበረሰብን ለመተቸት ‹‹ማህበራዊ ፈቃድ›› ያላቸው ሰዎች ስብስብ የሚል ነው፡፡

በዚህ ጥናት አዝማሪ የሚለውን ቃል ለመበየን የተቻለበት ሌላ አቅጣጫ ከራሳቸው ከአዝማሪዎች አንፃር ነው፡፡ አዝማሪዎች አዝማሪ ማለት ‹‹አመስጋኝ ማለት ነው›› ይላሉ፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ‹‹አዝማሪ ምንድን ነው›› የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ሶስት አዝማሪዎች አዝማሪ የሚለው ቃል መነሻው ‹‹ዘመረ›› የሚል የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ‹‹አመሰገነ›› ነው፡፡ እኛ ደግሞ በዘፈን እግዜርን እናመሰግናለን፣ ዳኛውን እናመሰግናለን፣ አለሙን እናመሰግናለን፣ የሰጠንን እናመሰግናለን የሚል

[9]አዝማሪዎች ከጥንት ጀምሮ ይዘውት በኖሩት ልምድ የወደዱትን አሞግሰው የጠሉትን (በግላቸው ምክንያት ወይም ከማህበራዊ ደንብ የወጣን ሰው) ሰድበው፣ ይኖራሉ፡፡ በየትኛውም የስልጣን ደረጃ ያለ ሰው አዝማሪ ሰደበኝ ብሎ አዝማሪን ሊቀጣ አይችልም፡፡ ይህንም ጥበብ ለአዝማሪ የሰጠችው ‹‹የነፃነት መብት›› ሊባል የሚችል ነው፡፡ የጉዳዩ አስፈላጊነት በአካባቢው ሰው ዘንድ የሚታመንበት ቢሆንም ‹‹ተሳዳቢ›› የሚለውን ስም ግን አሰጥቷቸዋል፡፡

መልስ ሰጥተዋል። (ብርሃን ትኩ፣ ማስረሻ ፈንታው የተተኳሪ ቡድን ውይይት 12/05/2005 ዓ.ም እና ደምሴ አበበ፣ 21/04/2005 ዓ.ም።

በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች አዝማሪ ከሚለው ስም በተለዋጭ ራሳቸውን ‹‹ተጫዋች›› ብለው ይጠራሉ። ይህንን ስያሜ የሰጡት ዘፈንን ጨዋታ ብለው ስለሚጠሩ ነው። ለምሳሌ ‹‹አሁን ትዝታን እየተጫወትሁ ነው››፣ ‹‹እስቲ ትዝታን ተጫወት›› ይላሉ። ስለዚህ ዘፈንን ጨዋታ ይሉና ዘፋኙን ተጫዋች ይላሉ። በዕድሜ የገፋ መረጃ ሰጪዎች ይህ ስያሜ ‹‹አዝማሪ›› የሚለው ስም ስድብ የሚመስላቸው አዝማሪዎች ለራሳቸው የሰጡት ነው ይላሉ። ይሁንና ዛሬ ዛሬ በራሳቸው በተጫዋቾችም ሆነ በሌላው ሰው ዘንድ ከአዝማሪ ይልቅ ‹‹ተጫዋች›› የሚለው ስያሜ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ ሲውል ይታያል። የቃል መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ለሁለቱም ስያሜዎች መሰረቱ ዘፋኝነት ነው። አንድ አዝማሪ አዝማሪነትን ከቤተሰቦቹ አለዚያ ደግሞ ከአካባቢው በማየት ሊማረው ይችላል። ይሁን እንጅ ዘፋኝነትን ከቤተሰቦቻቸው የወረሱ አዝማሪዎች ዘፈንን ከአካባቢያቸው ለተማሩ አዝማሪዎች ያላቸው አመለካከት እጅግ ዝቅተኛ ነው። ‹‹አምባገነን››፣ ‹‹ረጋ ሰራሽ››፣ ‹‹ወራሲሞ››[10]በሚሉ ባለሙያዎችን ዝቅ በሚያደርጉ ስሞች ይጠሯቸዋል። ያም ቢሆን ግን ዘፋኝነት ለአዝማሪ የተሰጠ ድርሻ በመሆኑ ማንም ራሱን በዘፈን የሚያስተዳድር ሰው ሁሉ አዝማሪ ነው ብለው ያምናሉ። አቶ አሰፋ ለገሰ የተባሉ አዝማሪ መረጃ ሰጪ የሰጡት ሃሳብ ይህንኑ ጉዳይ የሚያንፀባርቅ ነው። ‹‹አሁን እኮ ቅጅው ነው የበለጠ እኛ ደምወዝ የሌለው ስም አለ፤ ስሙ ተረፈን እንጅ አሁን እየተማሩ ገቡበት። ደሞዝ የሚያገኙበት ቅጅዎች ናቸው። ድሮ እኛን ሲሳደቡ የነበሩት ሁሉ አሁን ገብተውበታል›› (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ ደሴ፣ 14/04/2005)። ሲሉ አዝማሪ የሚባለው ሰው ማን እንደሆነ ገልፀዋል። አቶ ሽመልስ የተባሉ ሌላ አዝማሪ ያልሆኑ መረጃ ሰጪ ‹‹አዝማሪ እኮ ማለት ይኼ ብቻ አይደለም ካሴት የሚሰሩትም ናቸው። እነሱ ደግሞ ረጋ ናቸው። ስለዚህ በአዝማሪም ሌሎች እየገቡበት ነው›› (የተተኳሪ ቡድን ውይይት 16/04/2005፣ ደረቅ ወይራ) ሲሉ የሰጡት መረጃ የአቶ አሰፋን አባባል የሚያጠናክር ነው። መረጃዎች በወሎ አዝማሪዎች ዘንድ

[10]ሶስቱም በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ያሉ ቃላት አዝማሪን ከቤተሰቦቹ ሳይሆን በራሱ ተምሮ አዝማሪ ለሆነ ሰው የሚሰጡ ስያሜዎች ናቸው። አምባገነን፣ ድንገት ገብቶ ወቅት ያገነነው፣ ረጋ ሰራሽ፣ በስርዓት ሳይሆን ከስርዓት ውጪ የሆነ ተብለው የሚተረጎሙ ሲሆን ወራሲሞ ደግሞ በአዝማሪ ቋንቋ ‹‹አዝማሪነት በቤተሰቦቹ ሳይኖር ከሌሎች ተምሮ አዝማሪ የሆነ ማለት ነው የዚህ ቃል ተቃራኒ ደለቅሬ ነው። ትርጉሙ አዝማሪነትን ከቤተሰቡ የተማረ ነው።

‹‹አዝማሪ ማለት ማንኛውም መተዳደሪያው ዘፈን የሆነ ሰው›› መጠሪያ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ትንታኔዎች አዝማሪን ለመበየን ሶስት አቅጣጫዎች የተገኙ መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ብያኔዎቹን ፀሃፍት፣ አዝማሪ ያልሆነው ቡድንና አዝማሪዎች የሰጧቸው ናቸው፡፡ በሶስቱም ብያኔዎች ውስጥ ‹‹አዝማሪ ማለት ዘፋኝ ማለት ነው›› የሚል አንድ የጋራ ሃሳብ አለ፡፡ ይሁን እንጅ የተወሰኑ ፀሃፍትና አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች አዝማሪነትን ዝቅ አድርገው ሲያዩ፤ አዝማሪዎች ራሳቸው ግን አዝማሪ ማለት የተመረጠ ሙያ ባለቤት በማለት ይገልፁታል፡፡ መረጃዎች አዝማሪዎችን ‹‹አዝማሪ ምንድን ነው›› ከሚለው ባሻገር ‹‹ከየት መጡ/ መጣን›› በሚል መንገድም ሊገለፁ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ጉዳይ ለማስረዳት ቀጥሎ የአዝማሪዎችን አመጣጥ የሚገልፁ ሃተታዎች ቀርበዋል፡፡

## 2.1.9. የአዝማሪዎች አመጣጥ

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አዝማሪነት በኢትዮጵያ ጥንታዊ ሙያ ነው፡፡ ይሁንና ሙያው መቼ ተጀመረ የሚለውን ትክክለኛ ሃሳብ የሚገልፅ መረጃ አለመኖሩን ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡ በአንፃሩ እንደ Ashenafi (1971) ያሉ አጥኝዎች ከፊውዳል ስርዓተማህበር መመስረት ጋር አብሮ የመጣ እንደሆነ መላምት ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ለዚህ ጥናት አላማ ሲባል የተመረመሩ የፅሁፍና የቃል መረጃዎች የአዝማሪን አመጣጥ አስመልክቶ የሚነገሩ ትረካዎች እንዳሉ ለመገንዘብ አስችለዋል፡፡ እነዚህ ትረካዎች በጥቅሉ ሲታዩ ከሁለት አቅጣጫ የተሰነዘሩ ናቸው፡፡ አንደኛው አቅጣጫ ፀሃፍት የሰጡት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ራሳቸው አዝማሪዎች የሚተርኩት ነው፡፡ ለአዝማሪዎች የት መጣ ምላሽ ለመስጠት ከሞከሩ ፀሃፍት ውስጥ አንደኛው አለቃ ታዬ ናቸው፡፡ አለቃ ታዬ (1920፤ 34-35) አዝማሪ ከየት መጣ ሲሉ በገለፁበት ትረካ ቀጣዩን ይላሉ፡፡

> አጋዓዝያን የተባሉ ነገደ ዮቅጣን የኢትዮጵያን አገርና መንግስት በያዙ ጊዜ ይህ ጋፋት ከነልጆቹ ያዘዛችሁትን ሰርቼ ለናንተ ተገዝቼ እኖራለሁ፡፡ ወደማላውቀው አገር አልሰደድ፤ በለመድሁት ልኑር ብሎ ወደ ነገደ ዮቅጣን ላከ፡፡ እነርሳቸውም ያዘዝንህን ሰርተህ ለኛ ተገዝተህ ከኖርህ ምረንሃል ግባ አሉት፡፡ እሱም መጥቶ ከነልጆቹ ገባ፡፡ ከነልጆቹም ያዘዙትን እየሰራ

> ለነርሳቸው እየተገዛ የኢትዮጵያ መንግስት ዜጋ ሁኖ ተቀመጠ . . . ነገደ ጋፋት ጥንት አረማውያን ነበሩ፡፡ አሁን ግን ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ ባማራ ህዝብ መሃከል ስለተቀመጡ ቋንቋቸውን አጥፍተው ባማርኛ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ . . . ዛሬ ክርስቲያን ሆነው በክርስትያን መሀከል ሲኖሩ ስራቸው ሸማ፣ ብረት፣ ቆርበት፣ መሰንቆ መምታት፣ አዝማሮች፣ ሀማኖችም፣ ሌላም የእጅ ስራ የሚያውቁ ሰራተኞች ዋኖች በዚሁ በስራቸው የታወቁና የተለዩ ከጋፋትና ከፈላሻ ዘር ናቸው፡፡ እኒህም ምን ክርስቲያን ቢሆኑ እርስ በእርሳቸው ይጋባሉ እንጅ ጨዋ ከሚባል ክርስቲያን እስከዛሬ የሚጋባቸው የለም፡፡

ይህ ጥቅስ አለቃ ታዬ <u>የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ</u> በሚለው መፅሃፋቸው የኢትዮጵያን ህዝብ በነገድ ከፋፍለው የህዝቡን ማንነትና የት መጣ ሲያስረዱ ያሰፈሩት ነው፡፡ እንደፀሃፊው ሃሳብ ይህ አዝማሪዎችንና ሌሎችን የእጅ ስራ ባለሙያዎች የያዘው ነገድ ነገደ ጋፋት ይባላል፡፡ የዚህ ነገድ አባቱ አንድ ጋፋት የተባለ ትልቅ ሰው ነው፡፡ ዘሩም ከካም ልጅ ከኩሳ ነው፡፡ ይህ ነገድ ከመጀመሪያው ኢትዮጵያ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ የሚኖር ቢሆንም በኋላ ግን የነገደ ዮቅጣንን ወደኢትዮጵያ መምጣት ተከትሎ ከቦታ የመፈናቀል አደጋ አንዣቦበት ነበር፡፡ ይሁንና ነገዱ ቀደምት ቦታውን ለቅቆ ከመሄድ ይልቅ ለመጤው አገልጋይ ሆኖ መኖርን በመምረጥ በዚሁ መንገድ አገልጋይ ሆኖ መቅረቱን ጠቁመዋል፡፡ ከአገልግሎቱ አንዱ መሰንቆ መምታት መሆኑን ጥቅሱ ያስረዳል፡፡ አለቃ ታዬ ምንም እንኳን እሳቸው የማይቀበሉት መሆኑን ቢገልፁም ነገደ ጋፋቶች ፅላተሙሴን ተከትለው እንደመጡ የሚገልፅ አፈታሪክ መኖሩን ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ጥናት ይህ ትረካ መኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ ትረካው የአዝማሪዎች ትውልድ ከእስራኤል ጋር የሚገናኝ መሆኑንና ቡድኑ ፅላተ ሙሴን አጅቦ ወደኢትዮጵያ እንደገባ ያብራራል፡፡ ይህ ትረካ ‹‹የምስረታ ሚት›› (Foundational myth) ከሆነው ስለኢትዮጵያዊው ሰሎሞናዊ ስርወ መንግስት አመሰራረት ከሚተርከው ‹‹ሚት›› ጋር የሚነካካ ነው፡፡ <u>ክብረ ነገስት</u> እንደሚለው ንግስት ሳባ የንጉስ ሰለሞንን ዝና ሰምታ ወደ እስራኤል ተጓዘች፡፡ ቀዳማዊ ምኒልክን ከንጉሱ ፀንሳ ተመለሰች፡፡ ልጁ ካደገ በኋላ ወደ አባቱ ሄደ፡፡ ወደ ሃገሩ ሲመለስ ታቦተፅዮንን ይዞ ተመለሰ፡፡ ታቦቷን ይዞ ሲመጣ በየሙያቸው ታቦቷን የሚያገለግሉ በርካታ ሰዎችን አስከትሎ ነበር፡፡ ከእነዚህ ሙያተኞች ውስጥ ሙዚቀኞች አሉበት፡፡ ታቦቷ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ስትመጣ የነበረው የሙዚቃ ድባብ በክብረ ነገስት (1994፣ 55) በሚከተለው ሁኔታ ተገልጧል፡፡

እንዚራንም አነሱ፣ ከበሮዎችና ነጋሪቶች ተመቱ፡፡ መለከቶችም ተነፉ፡፡ በዘፈናቸውና በደስታቸው ቃል የግብፅ አገር ፈፅማ ታወከች፡፡ ከእነሱም ጋር ውካታውና እልልታው አስተጋባ፡፡ . . . ቅድስት ፅዮን ከእሷ ከሆኑትና ከእሷ ጋር ካሉት በመሰንቆና በእንዚራ፣ መዝሙር በተሻገረች ጊዜ፣ ባህር ማዕበሎቿን እያዘለለች፣ ረጃጅም ተራሮች ሲፈነቀሉ፣ እንዲናወጡ እንደሚያገሳ አንበሳና እንደበገና እንዲሁም እንደደማስቆና እንደኢትዮጵያ ክረምት ነጎድጓድ መብረቅ ደመናቱን ሲመታ እንዲያንጎደጉድ እንደዚሁ ታንጎደጉድ ነበር፡፡ ነጎድጓዱም ከእንዚራዎች ጋር ተስማማ፡፡ ባህርም ማዕበሎቿ እንደተራሮች እየታወኩ ሰገደችላት፡፡ ሰረገላዎቻቸውም በሞገዱ ላይ ሶስት ክንድ ያህል ከፍ ከፍ አሉ፡፡

ይህ ጥቅስ ታቦተፅዮን ከግብፅ[11] ወደኢትዮጵያ ስትመጣ የነበረውን የዘፈን አጀብ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ አጀብም በመሰንቆ በበገና፣ በእንዚራ፣ በመዝሙር እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ጥቆማውን መሰረት በማድረግ የአጃቢዎች ማንነት ሲመረመር ከመካከላቸው ባለመሰንቆዎች ይገኛሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ የሚደግፉ ሌሎች ፀሃፍትም አሉ፡፡ ለምሳሌ ኤልያስ አብርሃ (2005፣ 72) የሚከተለውን ይላሉ፡፡ ‹‹ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተፅዮንን ይዞ ወደኢትዮጵያ ሲመጣ ከእርሱ ጋር የመጡት እስራኤላውያን ድንኳን ሰፊዎችና ተካዮች፣ እንደዚሁም የሽመና ስራ ሰራተኞች ገሚሶች ደግሞ አንጥረኞችና ብረት አቅላጮች ገሚሶች የታቦተ ፅዮን ባለወጎች ማለትም ጅራፍን እያስጮሁ፣ መለከት፣ እምቢልታን፣ ቱልቱላንና ዋሽንትን እየነፉ መሰንቆ እየመቱና በገናን እየደረደሩ ታቦተፅዮን ስትንቀሳቀስ በፊት ለፊት የሚሄዱ ነበሩባቸው››፡፡

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ታቦተፅዮን በከፍተኛ አጀብ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣች ተገልጿል፡፡ ከአጃቢዎች ውስጥ ባለመሰንቆዎች አብረው እንዳሉ ተጠቁሟል፡፡ ይህንን ሃሳብ የሚደግፉ አመለካከቶች ከራሳቸው ከአዝማሪዎች ትረካዎች ውስጥም ይገኛሉ፡፡ አዝማሪዎቹ የዘር ሃረጋቸው ከእስራኤል ጋር የሚገናኝ መሆኑን ከአባቶቻችን ሰማነው ብለው ይናገራሉ፡፡

[11]ሮበርት ኮርነክ (1999፣ 223) ፅፈውት ሣህለ ጥላሁን በተረጎሙት ፅላተሙሴ በኢትዮጵያ ናትን? የሚል መፅሃፍ የታቦተፅዮንን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የሚተርከው አፈታሪክ እንዲሁም የፈላሻ የሃይማኖት መሪዎች ታቦቱ ወደኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ለሁለት መቶ ዓመታት ግብፅ ውስጥ መቀመጡን ይናገራሉ ሲል ይገልፃል፡፡


ለምሳሌ አንድ ማንነቱን እንዳይገለጥ የፈለገ አዝማሪ መረጃ ሰጪ ከትልልቆቹ የሰማሁት ነው ሲል የሰጠው መረጃ አዝማሪዎች ከቤተመንግስት ጋር በነበራቸው ንክኪ የተነሳ ብዙ የመንግስትና የህዝብ ምስጢር የሚያውቁ በመሆናቸው አገር ትተው እንዲሄዱ ባለመፈለጉ የተነሳ ከእስራኤላዊነታቸው ይልቅ ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲቀበሉ የተገደዱ በመሆኑ እንጅ ዘራቸው ከእስራኤል አመጣጣቸውም ታቦተፅዮንን በማጀብ ነው ይላል፡፡ የወሎ አዝማሪዎች ስለየት መጣቸው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ ከዚህ ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ እኛ የዕዝራ ዘሮች ነን፡፡ አዝማሪ ከሚለው ስማችን በተጨማሪ የምንታወቅበት ስም ዕዝራ ነው ይላሉ፡፡ ዕዝራ ማን ነው ሲባሉ ዕዝራ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው፡፡ መሰንቆ እየተጫወተ እግዚአብሔርን በምስጋና ያገለግላል፡፡ ዕዝራ መሰንቆን፤ ዳዊት በገናን እየተጫወቱ አምላክን ያመሰግኑ ነበር፡፡ ዳዊት የቂሶች፣ ዕዝራ ደግሞ የእኛ አባት ነው ይላሉ፡፡ ይህንን ለማስረዳት፡-

ዳዊት በበገና፣ ዕዝራ በመሰንቆ፣ እያጫወታት፤
ሳታውቀው አለፈች፣ ያን መላክ ሞት፡፡

የሚሊ ስለድንግል ማርያም ሞት በራሳቸው በአዝማሪዎች የሚባለውን ጥንታዊ ግጥም ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡ ‹‹ይህ ግጥም ከአባቶቻችን ያገኘነው ነው እንጅ ዛሬ እኛ የፈጠርነው አይደለም›› ይላሉ፡፡ መረጃ ሰጪዎች የግጥሙ መነሻ የድንግል ማርያም ሞት ነው ይላሉ፡፡

> ድንግል ማርያም በምድር ላይ ስልሳ አራት ዓመት ከኖረች በኋላ የሞትዋ ጊዜ እንደደረሰ ልጅዋ ይነግራታል፡፡ እስዋ ግን ሞትን ፈርታ ስለነበር ‹‹ይቅርብኝ እኔ የአንተ እናት ሆኜ እንዴት እሞታለሁ›› ብላ ጠየቀችው፡፡ እሱም ስጋ ለባሽ ሁሉ ከሞት እንደማይቀር ነግሯት፣ እሱ በሞቱ ሲኦል የነበሩ ነፍሳትን እንዳወጣ ሁሉ እርስዋም በሞትዋ ከሲኦል ልታወጣቸው የሚገቡ ነፍሳት እንዳሉ ያሳያታል፡፡ እርስዋም ስለእነዚህ ነፍሳት ስትል በሞትዋ ተስማማች፡፡ ይሁንና አሁንም ቢሆን በፍርሃት ውስጥ በመሆኗ ልጅዋ፣ ከዚህ ፍርሃቷ እንድትወጣ ሲል ዕዝራ፣ መሰንቆ፣ ዳዊት ደግሞ በገና እንዲጫወቱላት ያዝላታል፡፡ ሙዚቃውን እየሰማች ተመስጣ እያለ በዚያው ነፍስዋ ከስጋዋ ተለይታለች፡፡ የዚህ ግጥም መነሻውም ይኸው ታሪክ ነው፡፡ እኛም የዚያ የዕዝራ ልጆች ነን፡፡ (ብርሃን ትኩ፣ቃለ መጠይቅ፣ 11/05/2005፣ ማርዬ)

የሚል መረጃ ሰጥተዋል። ሃይማታኖታዊ መፅሃፍት ስለድንግል ማርያም ሞት ይገልፃሉ። ይሁንና በሞትዋ ጊዜ ዳዊት በገና ዕዝራ ደግሞ መሰንቆ መጫወታቸውን አይገልፁም። እንዲያውም በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ በመፅሃፈ ዕዝራ ካልዕ ምዕራፍ. 4. ቁጥር 63 ላይ “ ወጥተው ኢሩሳሌምን ይሰሯት ዘንድ። ስሙ የተጠራባትን ቤተ መቅደስ ይሰሯት ዘንድ። ይቅር ብሎ ዕረፍትን የሰጣቸውን ያባቶቻቸውን ፈጣሪ አመሰገኑ። መሰንቆውን በገናውን እየመቱ ሰባት ቀን ተድላ ደስታ አደረጉ።” የሚል የዕዝራን ስም ከመሰንቆ ጋር የሚያያይዝ ጥቅስ ከመኖሩ ውጪ መፅሃፍት የዕዝራን ፀሃፊነት እንጅ ዘማሪነት አይናገሩም (መፅሃፍ ቅዱስ፤ 1980፣ 379) የመፅሃፍ ቅዱስመዝገበ ቃላት (1992፣ 210)። ጉዳዩን አስመልክቶ ቃለመጠይቅ ያደረግሁላቸው የኦርቶዶክስ እምነት መምህራን ትረካው መኖሩን ቢያውቁም ምንም መፅሃፍት ላይ የሌለ መሆኑንና ‹‹አፈ ታሪክ›› መሆኑን ይገልፃሉ። ይህ ይባል እንጂ በባህር ዳር ከተማ በሚገኘው ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ውስጥ ዕዝራ መሰንቆ፣ ዳዊት ደግሞ በገና ለድንግል ማርያም የተጫወቱላት መሆኑን የሚገልፅ ስዕል መኖሩን ገልፆ ማለፍ ሃሳቡ በቤተክርስቲያን በኩል ተቀባይነት ያለው መሆኑን ለመረዳት የሚጠቅም ማስረጃ ነው።




ስዕል 1. “እዝራና ዳዊት ለድንግል ማርያም እንደዘመሩ”

የሃይማኖት መምህራን ትረካው አልተፃፈም ማለታቸው አዝማሪዎቹ ስለማንነታቸው ለመግለፅ የሚያቀርቡትን ትረካ ውሸት አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ማህበረሰብ የየት መጣ ትረካዎችን የሚያዘጋጀው ራሱ አለምን በተረዳበት ሁኔታ ነውና፡፡ በዚህ መሰረት የወሎ አዝማሪዎች አመጣጣቸውን ሆነ የሙያውን አገልግሎት ከቅድስና ጋር ያያይዛሉ፡፡ ይህንን የሚገልፁባቸው ሌሎች ፎክሎራዊ መረጃዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ሲታዩ ስለመሰንቆ ታሪካዊ የአገልግሎት ሂደት የሚቀርበው ትረካ አንዱ ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት መሰንቆ በመጀመሪያ ያገለግል የነበረው ለአምላክ ምስጋና በቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ ደግሞ ለነገስታትና ለሹማምንት ማጫወቻ የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ ሆነ፣ ነገስታትና ሹማምንት ደግሞ ምንጊዜም በአምላክ የሚመረጡ በመሆናቸው መሰንቆ አሁንም ለተመረጡ ሰዎች ማገልገያ ሆነ፡፡

መሰንቆ ነገስታትን ከማወደሱ ሲወርድ ቀጥሎ ማገልገል የጀመረው በሰርግ ቤት ነው፡፡ ሰርግ ቤት ደግሞ በአምላክ የተወደደ ቅዱስ ቦታ እንደሆነ የአዝማሪውም ሆነ ሌላው የአዝማሪን አገልግሎት የሚፈልገው ማህበረሰብ ያምናል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ (ዮሐ.2፣ 1-12) ላይ እንደተፃፈው ኢየሱስ በቃና ዘገሊላ በሰርግ ቤት ተገኝቶ ተዓምር ማድረጉ ነው፡፡ መፅሃፍ ቅዱስ ኢየሱስ በሰርግ ቤት አደረገ ያለው ተኣምር የሚከተለውን ይላል፡፡

> በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፡፡ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፡፡ ኢየሱስም ደግሞም ደቀመዛሙርቱም ወደሰርጉ ታደሙ፡፡ የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የእየሱስ እናት የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው፡፡ እናቱም ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው፡፡ አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንፃት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር፡፡ እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሶስት እንስራ ይይዙ ነበር፡፡ ኢየሱስም ጋኖችን ውሃ ሙሏቸው አላቸው፡፡ እስከአፋቸውም ሞሏቸው፡፡ አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም፡፡ አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም፡፡ ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን

ያውቁ ነበር፡፡ አሳዳሪውም ሙሽራውን ጠርቶ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፤ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው፡፡ ኢየሱስ ይህንን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፡፡

ጥቅሱ የኢየሱስን በሰርግ ቤት መገኘት፣ ከመገኘትም አልፎ ተኣምር ሠርቶ የሰርግ ቤቱን ችግር እስከመፍታ መድረሱን ይገልፃል፡፡ የክርስቶስ በሰርግ ቤት መገኘት በአንድ በኩል የቦታውን ቅዱስነት ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ቦታው አስቀድሞ እንኳን ቅድስና ባይኖረው ክርስቶስ የተገኘበት በመሆኑ፤ እሱ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ የተባረከ ሆኗል፡፡ ስለዚህ መሰንቆ ከቤተክህነትም ሆነ ከቤተ መንግስት ወጥቶ ወደ ሰርግ በመሄድ ህዝብ የሚገለገልበት የዜማ ዕቃ ሆኗል፡፡

መሰንቆ ከቤተክህነትና ቤተመንግስት ወጥቶ ወደ ህዝብ ከገባ በኋላም ቢሆን ጥንታዊ መንፈሳዊነቱን የሚያመለክቱ ዱካዎች/አሻራዎችን አለቀቀም፡፡ ለዚህ ሶስት ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡ አንደኛው በምንም አይነት ዘመናዊነት ውስጥ እንኳን ቢያንስ ሙሽራ ከቤት ሲወጣ (ሰርግ ቤት ውስጥ) አዝማሪ እንዲኖር መፈለጉ፣ ሁለተኛው አዝማሪዎች ታቦት በሚወጣባቸው የንግስ በዓላት ከታቦቱ ፊት በመጓዝ ለአምላክ ምስጋና ማቅረብ ዛሬም የተለመደ ባህል መሆኑና ሶስተኛው ደግሞ በማንኛውም የዘፈን ክዋኔ ውስጥ መዲናና ዘለሰኛ በሚባሉ አምላክን ለማመስገን በሚያገለግሉ ዜማዎች ዘፈንን መጀመር ግዴታ መሆኑ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አዝማሪዎች ከእስራኤል ጋር የሙያ ንክኪ አለን ሲሉ የሚገልፁትን ጉዳይ የሚደግፍ ሃሳብ ከመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ ማግኘት የሚቻል ይመስላል፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስደፍረው ጉዳይ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ መሰንቆ የሚለው ቃልና የአገልግሎቱ መልክ በብዛት የተጠቀሰ መሆኑ ነው፡፡ እንዳረጋገጥሁት መፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ መሰንቆ ከሃያ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡

እንደሚታየው በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የቀረቡ ታሪኮች የእስራኤልን ባህል አውድ አድርገው የተፃፉ ናቸው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የታቦተ ፅዮንን ወደኢትዮጵያ መምጣት በምርምር ስራ አረጋግጫለሁ የሚሉት Hancock (1992, 254) ‹‹The whole cast of religious expression in Ethiopia as antique and ceremonial and imbued with an undercurrent of Judaic practice›› ሲሉ እንደሚገልፁት ኢትዮጵያ

የተለያዩ የሃይማኖት ስርዓቶችን ከአይሁዳውያን ተቀብላለች፡፡ በመፅሃፍ ቅዱስ ከቀረቡ ታሪኮች መገንዘብ እንደሚቻለው ታቦትን በመስንቆ ማጀብ ከስርዓቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ስርዓት በኢትዮጵያውያን እስከተተገበረ ድረስ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤላውያን ባህሉን ወርሰውታል ማለት የሚያስችል ይመስላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡ ሁለት የፅሁፍና የቃል መረጃዎች ሲታዩ እርስ በእርስ የሚደጋገፉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ድግግፋቸውም የአዝማሪነት ሙያ ምንም እንኳን ረጅም ዘመን በመኖሩ የተነሳ ኢትዮጵያውያን የአሃዘቡት[12] ቢሆንም ጥንተ አመጣጡ አይሁዳዊ ነው የሚል መልስ የሚሰጥ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከመስክ ለተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ማጣቀሻ ሆነው ያገለገሉ ሃሳቦች ከተለያዩ ምንጮች ተለቅመውና ተቀናብረው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ሃሳቦች ከማጣቀሻነት ባሻገር የጥናቱ ሃሳብ ከመደበኛ ዕውቀት ጋር ያለውን ቅርርብ ለማሳየት አገልግለዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ በጠበበ ሁኔታ ግን ጥናቱ ከቀደምት ጥናቶች ጋር ያለውን ቀጥታ ዝምድና ለማሳየት ሲባል በአዝማሪ ላይ በተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ላይ ቀጣዩ ክለሳ ተደርጓል፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

በተለያዩ ቤተመፃህፍትና በሌሎችም ቦታዎች በተደረገ ከርዕሱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው የቀደምት ጥናቶች ፍለጋ አስራ ስድስት በኢትዮጵያ አዝማሪዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ተገኝተው ፍተሻ ተደርጎባቸዋል፡፡ ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ አራቱ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ፣ ሶስቱ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ ሁለቱ ከሶሻል አንትሮፖሎጅ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ ሰባቱ በጆርናሎች ላይ የወጡ ናቸው፡፡ ከመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፎች በመጀመር ጥናቶች በተሰሩበት የጊዜ ቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

አዝማሪ በሚለው ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶች አልማዝ (1974) «አዝማሪና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ»፣ ኑርሁሴን (1986) «በፎገራ አካባቢ የሚሰሙ

[12] የአሃዘቡት የሚለው ቃል ከዶር. ፈቃደ አዘዘ የተወሰደ ሲሆን፣ አንድን ከሌላ ቦታ የመጣ ፅንሰሃሳብ/ቃል በሌላው ማህበረሰብ ውስጥ አስገብቶ የማህበረሰቡ ማድረግን የሚገልፅ ነው፡፡ ቃሉ Popularize ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ ነው ይላሉ፡፡

የአዝማሪ ግጥሞች ይዘት ትንተና» መንገሻ (1992) «የወገል ጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃልግጥም»፣ አንለይ (1995) «የአዝማሪ ታደለ የህይወት ታሪክና ቃላዊ ግጥሞቹ» የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ የአንለይ (1992) ጥናት የአንድን አዝማሪ የህይወት ታሪክ በመጨመሩ የተነሳ ከሌሎች ጥናቶች በከፊል ልዩ ከመሆኑ በስተቀር አራቱም ጥናቶች በዋናነት ትኩረታቸው የአዝማሪ ግጥሞችን ይዘት መተንተን በመሆኑ በጣም ይመሳሰላሉ፡፡ በመካከላቸው ያለው ልዩነት የጥናት ቦታ ብቻ ነው፡፡

አራቱ ጥናቶች የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያዎች እንደመሆናቸው[13] የመረጃ ስብሰባቸው ብዙውን በአርቲፊሻል መቼቶች የተከወኑ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ አፍን ሞልቶ ስነቃሉን ከነሙሉ ተፈጥሮው ቀርሰውታል ለማለት ይከብዳል፡፡ ይሁንና ሊጠና የሚገባውን ርዕሰ ጉዳይ መምረጣቸውና ለሌላው አጥኝ መነሻ መሆን መቻላቸው ጠንካራ ጎናቸው ነው፡፡በዚህ መሰረት የእኔ ጥናት ከላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች የሚያነሷቸውን የአዝማሪዎችን ቃልግጥም እንዲሁም የህይወት ታሪክ የሚያካትት በመሆኑ ከጥናቶች ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ጥናቶች ያላነሷቸውን የተከታታይነትና ለውጥ ሃሳቦችን በመያዝ፣ ጥናቶቹ ያላደረጓቸውን መረጃዎችን በተፈጥሯዊ አውዳቸው መሰብሰብና ተገቢ ትንታኔዎችን ማድረግ ተግባራት በመከወኑ ከጥናቶቹ ይለያል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተዳሰሱት ስልጠና አግኝተው፣ ‹‹እውቀቱ ኖሯቸው›› ጥናቱን ያደረጉ ሰዎች የሰሯቸው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያና ለጆርናሎች የተሰሩ ጥናቶች ናቸው፡፡ በዚህም ቀድሞ የተገኘው ስራ “An Ethiopian Minstrels’ Argot” በሚል ርዕስ በ1952 የተሰራው የWolf Leslau ስራ ነው፡፡

---

[13]የመጀመሪያ ዲግሪ ፅሁፎች ተማሪዎች ፍላጎት ስላላቸው ይሰሯቸዋል እንጅ፣ ለጥናቱ መስሪያ የሚሆን በትምህርት ክፍሎች ታውቆ የተመደበ የጊዜም ሆነ የገንዘብ በጀት የለም፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ተማሪዎች በፊት ከሶስተኛ ዓመት ወደአራተኛ፣ አሁን ደግሞ ከሁለተኛ ወደሶስተኛ ዓመት ከተሻገሩ በኋላ በመካከል ባለው ክረምት የእረፍት ጊዜያቸውን በመጠቀም መረጃ ሰብስበው የሚሰሯቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ፍላጎት እንጂ፣ የጊዜና የገንዘብ በጀት፣ በቂ የመረጃ አሰባሰብ ስልጠና የሌላቸው ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ መረጃዎች በአግባቡ ተሰብስበው ተተንትነዋል ለማለት ይከብዳል፡፡ እንዲያውም ፈቃደ (1975፣ 96) እነዚህን ጥናቶች ሲገልፁ፣ ‹‹የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አፋዊ ኪነተቃል ‹‹ጥናቶች›› እንደቀዳማይ የአውሮፓ ‹‹ምሁራን›› ‹‹ጥናቶች›› ከማህበረሰቡ ጋር ተደባልቆ በመኖርና ሕዝቡን ተረድቶ፣ አካባቢያዊ የሶሻል፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሕይወቱን አድቅቆ በልቶ፤ የተሰሩ ሳይሆኑ የአፋዊ ኪነተ ቃልን ህልውና ዋና መሰረት የሆነውን ክዋኔን ሁሉ የማይጨምሩ ብቻቸውን ፈንጠር ብለው የቆሙ ስራዎች ናቸው፡፡ የአፋዊ ኪነተቃልን ኪነታዊ እሴቱን አንስተው ቃሉን ብቻ ቆዳውን ገፍፈው፣ስጋውን በጭቀው፣ ደሙን አፍስሰው፣ አፅሙን ብቻ ያቀረቡ አይነት›› ይላሉ፡፡

Leslau (1952) ጥናታቸውን ያደረጉት በአዝማሪዎች ቋንቋ ላይ ነው፡፡ አጥኚው መረጃዎችን በደብረ ማርቆስ አካባቢ ከሚኖሩ አዝማሪዎች በቃለመጠይቅ መረጃዎችን ሰብስበው ጥናቱን ያደረጉ ሲሆን በውጤቱም አዝማሪዎች ሙዚቃዎችን በሚከውኑበት ወቅት ከሌሎች ሰዎች ሚስጥር ለመደበቅ ሲሉ ቋንቋውን ይገለገሉበታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ስለቋንቋው አመሰራረት ባደረጉት ምርመራም መደበኛውን አማርኛ ቋንቋ ሆነ ብለው በማጣመም እንደሚፈጥሩትና የአዝማሪ ቋንቋ ቃላት ‹‹ስር››[14] ከተሰኘው የአማርኛ የቃል ክፍል ይመሰረታል ብለዋል፡፡ ቃላቱ የሚከተሏቸው የአመሰራረት ሂደቶች ያሏቸው ሲሆን እነሱም መቁረጥ (metathesis)፣ ፊደል/ድምፅ መጨመር (augementation) ማባዛት (reduplication)፣ ማሳጠር (Substitution of a radical and shortening) ናቸው፡፡ አጥኚው እንደሚሉት የአዝማሪዎች ቋንቋ ከአማርኛ ቋንቋ የሚፈጠር ቢሆንም ከአማርኛው ይልቅ ወጥ የሆነ አጠቃቀም ይከተላል፡፡ በቋንቋው የአማርኛው የስነምዕላድ ባህርይ የሚንፀባረቅ ሲሆን ቋንቋው የተወሰነ ቡድን የሚጠቀምበት የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ ነው ማለት ይቻላል ይላሉ፡፡ Leslau የአዝማሪ ቋንቋ ቃላት ስነልሳናዊ ሁኔታ ከጉራግኛ፣ ከትግርኛ፣ ከአረብኛ፣ ከግዕዝና መሰል ቋንቋዎች ጋር ያለውን ተመሳስሎ ገልፀዋል፡፡

Leslau አዝማሪዎችን ያጠኗቸው ከስነልሳን አንፃር ነው፡፡ የአዝማሪዎችን የሚስጥር ቋንቋ ወስደው የቋንቋውን አፈጣጠር፣ አግልግሎት፣ ስነልሳናዊ ባህርይ፤ ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር ያለውን የስነልሳናዊ ባህርይ ምስስሎሽ መርምረው አሳይተዋል፡፡ ጥናታቸው በአዝማሪዎች ቋንቋ ላይ የተደረገ በመሆኑ አዝማሪዎች የራሳቸው ቋንቋ ያላቸው መሆኑን እንድገነዘብና የወሎ አዝማሪዎችም የራሳቸው የሆነ ቋንቋ ያላቸውና የሌላቸው መሆኑን ትኩረት ሰጥቼ እንዳይ በማድረግ ረገድ ለዚህ ጥናት እገዛ አድርጎልኛል፡፡

አጥኚው ይህንን ጥናት ያደረጉት በደብረማርቆስ ከተማ ያገኟቸውን ጥቂት አዝማሪዎች የመረጃ ምንጭ በማድረግ እንጅ. አዝማሪዎች በትውልድ በሚኖሩባቸው መንደሮችና በተፈጥሯዊ አውዶች በመገኘት አይደለም፡፡ ይህ የጥናቱ ስነልሳናዊ መሆን እንዲሁም

[14] ባዬ (2000፣ 160-161) ስር ምን እንደሆነ እንዲህ ያስረዳሉ፡- በአማርኛ የማናቸውም ግስ እንደዚሁም የተወሰኑ ቅፅሎችና ስሞች መሰረት፣ ተናባቢ ድምፆች ናቸው፡፡ የተናባቢዎቹ ቁጥር ከአንድ እስከስድስት እንደሚደርስ ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ እያንዳንዱ ተናባቢ ድምፅ እግር ይባላል፡፡ ተናባቢዎቹ አንድ ላይ ሆነው የሚፈጥሩት ቅንጅት ስር ይባላል፡፡ ይህ ስር እንደ ተናባቢዎቹ ቁጥር ባለሁለት፣ ባለሶስት፣ ወዘተ እግር እየተባለ ይለያል፡፡ ስሩ ብቻውን አጠቃላይ የሆነ ቅርፅና ትርጉም አለው፡፡

ኢትኖግራፊያዊ አለመሆን የእሳቸው ጥናት ከዚህ ስራ የተለየ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ አዝማሪ ላይ ጥናት አድርገው የተገኙ ሌላው ሰው Ashenafi ናቸው፡፡

Ashenafi (1971) "The 'Azmari', Poet-Musician of Ethiopia" In: The Musical Quarterly በሚለው ስራቸው የአዝማሪዎችን ማንነት፣ መኖሪያ ስፍራ፣ የሙዚቃ መከወኛ ቦታዎችና ማህበራዊ ደረጃ ገልጠዋል፡፡ Ashenafi አዝማሪዎች የመኖሪያ ስፍራቸው የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ከፍተኛ ቦታዎች የሆነ፣ በተለይም በፊውዳሉ ዘመን ህዝብን በማዝናናት የሚኖሩ የሙዚቃ ባለሙያዎች እንደሆኑ ፅፈዋል፡፡ አጥኚው፣አዝማሪዎች እንደጥምቀት፣ ክርስትና፣ ፋሲካ በመሳሰሉ ክብረበዓሎችና ዓመታዊ በዓላት ላይ ዘፈንን ይጫወታሉ፡፡ የገበያ ቀን፣ እንዲሁም እንደደቦና ማህበር ያሉ ሃገር በቀል ማህበራዊ ተቋማት የአዝማሪዎች ሙያ ተፈላጊነት የሚታዩባቸው ቦታዎች ናቸው ብለዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጥኚው አዝማሪዎች መነሻቸው ሙዚቃ ክወና በመሆኑ፤ በሌላው ማህበረሰብ የተገለሉ፣ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህ ጥናት የአዝማሪዎችን ህይወት ሰፊ ዳራ እንዳለው ያሳየ በመሆኑ በርዕሰ ጉዳዩ ለሚደረግ ጥናት አያሌ ገፅታዎችን መመርመር የሚቻል መሆኑን ከመጠቆም አንፃር ለእኔ ጥናት አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

Ashenafi በዚህ ስራቸው አዝማሪዎች ያጠኗቸው ከሙዚቃ ሙያ አንፃር ነው፡፡ ትኩረታቸው አዝማሪዎች ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ የሚያሳይ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን የአዝማሪዎችን የዘፈንና የኑሮ ልምድ ተከታታይነቱና የተከሰቱበት ለውጥ ምንድን ነው? የሚለውን ሃሳብ ከፎክሎር እሳቤ አንፃር የመረመረ በመሆኑ ከ Ashenafi ጥናት ይለያል፡፡ ሌላው አዝማሪ ላይ ጥናት አድርገው የተገኙ ሰው Teclehaimanot ናቸው፡፡

Teclehaimanot (1986) «A Brief Survey Study of the Azmareis in Addis Ababa» በሚል ርዕስ የአዲስ አበባ አዝማሪዎች ላይ ቅኝታዊ ጥናት አድርገዋል፡፡ እኒህ አጥኚ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚኖሩ በዕድሜ የገፉ አዝማሪዎች በቃለመጠይቅ መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥናቱን አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም ጦርነትን የሚገልፁና ፖለቲካን የሚሄሱ ቃልግጥምን ሰብስበዋል፡፡ ጥቂት የአዝማሪ የሚስጥር ቋንቋ ቃላትንም ከነትርጉማቸው ሰብስበዋል፡፡ Teclehaimanot በጥናታቸው የአዝማሪ ባህልን ጥንታዊነት የጠቆሙ በመሆኑ የሙያውን የዕድሜ ዘመን ርቀት ከመጠቆም አንፃር ለዚህ ጥናት አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

የTeclehaimanot ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የተወሰነ ነው። አጥኚው የታሪክ ባለሙያ እንደመሆናቸው የጥናታቸው ትኩረትም ታሪክ ነው። ስለዚህም በአዲስ አበባ በሚገኙ በዕድሜ የገፉ አዛውንት አዝማሪዎችን የጦር ሜዳና የፖለቲካ ሚና በመመርመር ላይ አተኩረው መረጃዎችን ሰብስበዋል። የጥናታቸው ትኩረት የአዝማሪዎችን ፖለቲካዊ ሚና በማሳየት ላይ ያተኮረ ብቻ በመሆኑ ሌላውን ህይወታቸውን አልተመለከቱም። በተጨማሪም ጥናቱ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የተወሰነ ስለሆነ መረጃዎች የተሰበሰቡ ከትውልድ ቦታቸው ለረጅም ጊዜ ርቀው ከቆዩ መረጃ አቀባዮች በአርቲፊሻል መቼት ነው። የእኔ ጥናት ጥቂት መረጃዎችን በአርቲፊሻል መቼቶች የተሰበሰቡ ጥቂት መረጃዎችን የተጠቀመ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን በተፈጥሯዊ መቼቶች የተሰበሰቡ በመሆናቸው አዝማሪነትን ከየት መጣው ጀምሮ እስከወቅታዊ ሁኔታው በማጥናቱ፣ እንዲሁም የአዝማሪዎችን ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገፅታቸውን ጭምር በመመርመሩ ከTeclehaimanot ጥናት ይለያል።

ከዚህ በኋላ የተዳሰሰው ጥናት Bolay (2002) "The Azmari: Voice of Ethiopian Memory" ሲሉ ያቀረቡት ስራ ነው። ፀሃፊዋ ፅሁፋቸውን የሚጀምሩት ስለአዝማሪዎች ማንነትና ምንነት በመግለፅ ነው። አዝማሪዎች ሙዚቀኛነትን ከቤተሰቦቻቸው ወርሰው፣ በትናንሽ መንደሮች፣ በቡና ቤቶች፣ በገበያ፣ በግለሰብ ድግሶች ወዘተ በጥንድ ወይም በነጠላ በመዘዋወር መሰንቆ ተብሎ በሚጠራ የሙዚቃ መሳሪያ ራሳቸውን አጅበው የሚዘፍኑ ሙዚቀኞች ናቸው ይላሉ።

የአዝማሪዎች ዘፈን ግጥሞች ከአዝናኝነት ባሻገር ብዙ የታሪክ መረጃዎችን ይዘዋል የሚሉት የጥናቱ ባለቤት የስራቸውን ዓላማ ይህንን ጉዳይ ማሳየት ነው ይላሉ። ለዚህ ሲባል መረጃዎች በጎንደርና በወሎ እንደተሰበሰቡ ገልፀዋል። አጥኚዋ በዚህ ጥናት ሶስት ጉዳዮችን አይተዋል። እነሱም አንደኛ ግጥሞችን፣ ሁለተኛ በአስራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ ላይ የኖሩ ጥቂት ቁጥር ያላቸው አዝማሪዎች የህይወት ታሪክና ሶስተኛው አዝማሪዎች የተሳተፉባቸው ጥቂት ታሪካዊ ሁነቶች ናቸው።

አጥኚዋ አዝማሪው መረጃዎችን የሚያስተላልፈው በግጥም አማካኝነት ስለሆነ ግጥም ለአዝማሪ ትልቅ ሃብት ነው። የአዝማሪ ግጥሞች የየራሳቸው ምደባ አላቸው፣ አንድ አዝማሪም ብዙ ግጥም ማወቁ ክዋኔውን ያሳምርለታል። በዚህ የተነሳ አዝማሪዎች

የግጥም ችሎታቸውን ለማዳበር ይጥራሉ፡፡ የግጥም መግጠም ችሎታቸውን የሚያገኙበት ትምህርት ግን ኢመደበኛ ነው ይላሉ፡፡

ከዚህ በኋላ አጥኝዋ በጥናቱ አገኘሁ ያሏቸውን ግኝቶች ለማሳየት የሶስት አዝማሪዎችን ታሪክ፣ አዝማሪዎች በጦርነት ላይ የነበራቸውን ሚና አቅርበዋል፡፡ ከዚህ ሌላ ጣፋጭ የተባለውን የአፄ ቴዎድሮስ አዝማሪ (አፅንኦት በእኔ/ የአፅንኦቱ አስፈላጊነት ዝቅ ብሎ የሚታይ ነው) አፄ ቴዎድሮስ በሽፈቱ ጊዜ እሳቸውን አንቋሾ መዝፈኑንና በኋላ እሳቸው ድል አድርገው ለምን ሰደብከኝ ሲሉት በራሱ ላይ በዱላ የመደብደብ ፍርድ የመስጠቱን ታሪክ ዋቢ በማድረግ አዝማሪዎች በፍርድ ሂደት አስተዋፅኦ ነበራቸው ይላሉ፡፡

በማጠቃለያቸው የአዝማሪ ግጥሞች የተገጠሙበት ምክንያትና አውድ ያላቸው ስለሆነ ብዙ የታሪክ መረጃዎችን ይዘዋል፡፡ ስለዚህ ግጥሞችን ብቻ ሳይሆን የተፈጠሩበትን ምክንያትና አውድ በመመርመር ለታሪክ መረጃነት መጠቀም ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ ብቻቸውን እንደመረጃ መጠቀሙም ብዙ የማያስኬድ በመሆኑ ከሌሎች መረጃዎች ጋር ማመሳከር አስፈላጊ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ይህ ስራ አዝማሪዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያላቸውን ሚና እንዲሁም የአዝማሪ ግጥሞች በታሪክ ጥናት ውስጥ ያላቸውን ጥቅም ያሳየ ጥሩ ስራ ነው፡፡ ስራው አዝማሪዎችን ከታሪክ አተያይ አንፃር ለማጥናት ለሚፈልግ ሰው መንገድ ይጠቁማል፡፡ እኔም በአዝማሪ ግጥሞች ላይ ትኩረት መስጠት የሚገባኝ መሆኑን አመላክቶኛል፡፡ ይሁን እንጅ ጥናቱ ድክመቶችም አሉበት፡፡ ከእነዚህ ድክመቶች ውስጥ በዋናነት የሚነሱት የመረጃ ሰጪዎች ውክልና ማነስና ታሪክ ማዛባት ናቸው፡፡ የመረጃ ሰጪዎች ውክልና የሚለው ሲታይ አጥኝዋ ገና ከጅምሩ መረጃዎችን ከወሎና ከጎንደር ሰበሰብኳቸው ብለው ተነስተዋል፡፡ ነገር ግን በጥናቱ የቀረቡት የጎንደር እንጂ የወሎ አዝማሪዎች አይደሉም፡፡ ከጎንደሮችም ቢሆን የሶስት ታዋቂ አዝማሪዎችን ታሪክ ብቻ በማንሳት ማጠቃለያ ላይ መድረሳቸው የጥናቱን ውጤት ተዓማኒነት ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው፡፡

የታሪክ መዛባት ወደሚለው ሲመጣ ደግሞ አጥኝዋ ጣፋጭ የተሰኙትን አዝማሪ የአፄ ቴዎድሮስ አዝማሪ ሲሉ ይጠራሉ፡፡ ዳሩ ግን የታሪክ መፅሃፍት፣ እንደሚሉት ጣፋጭ የደጃች ጎሹ እንጅ የራስ ካሳ (አፄ ቴወድሮስ) አዝማሪ አልነበሩም (አለቃ ተክለ እየሱስ፣ 2002፣ 101)፡፡ በመሆኑም የእኔ ጥናት በ Bolay ጥናት የታዩትን ስህተቶችን ያረመና አጥኝዋ ያልዳሰሷቸውን በመንደር ተወስነው የሚኖሩ የወሎ አዝማሪዎች የኑሮና

የዘፈን ልምድ የመረመረ በመሆኑ ከእሳቸው ጥናት የተለየ ነው፡፡ ሌላው አዝማሪ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰው Kawase ናቸው፡፡

Kawase (2005፣ 2008፣ 2010) እኚህ አጥኝ አዝማሪዎችን በተለያዩ ሶስት ጊዜያት አጥንተዋል፡፡ በ2005 ያደረጉት ጥናት "Musical Performance and Self-Designation of Ethiopian Minstrels: Azmari" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን በዚህ ጥናት የጎንደር አዝማሪዎችን አጥንተዋል፡፡ በጥናቱ የጎንደር አዝማሪዎች በአንድ ቦታ ተቀምጠውና ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሙዚቃን ስራ የሚሰሩ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ፤መጠጥ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ጠላ ቤቶችና ጠጅ ቤቶች የተለመዱ የአዝማሪዎች የሙዚቃ መከወኛ ቦታዎች መሆናቸውን፣ በዚህ የተነሳም በሌላው ማህበረሰብ ዝቅ ተደርገው የሚታዩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህ ቦታዎች ውጭ ግን በህይወት ዑደት ፌስቲቫሎች፣ በዛር ቤቶች፣ በአዲስ አበባና በአውሮፓም እየተስፋፉ ባሉ የአዝማሪ ቤቶች ሙዚቃቸውን እንደሚከውኑ አሳይተዋል፡፡ አጥኚው በዚህ ስራ የአዝማሪ ዘፈን ቴክስቶችን ያሳዩ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ቅኔ፣ ሰምና ወርቅ፣ ፉከራ፣ የመሳሰሉ ይገኙበታል፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪ የአዝማሪ ቃላትን ትርጉም መርምረዋል፡፡ አጥኚው በመጨረሻም አዝማሪዎች እርስ በእርሳቸው እንጅ ከሌላው ጋር ጋብቻ የማይፈፅሙ፣ ለራሳቸው እንዲህ ነን የሚል መልክ የሰጡ፣ ራሳቸውን ‹‹ኢንዛታ›› ሌላውንና አዝማሪ ያልሆነውን ወገን ደግሞ ‹‹ቡጋ›› ብለው ከፍለው የሚኖሩ ቡድኖች እንደሆኑ ገልፀው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን ግንኙነት አሳይተዋል፡፡

ሁለተኛው ስራቸው በ2008 የተሰራውና "The Transformation of Musical Activities and Self-imposed Group Markers of Azmari in Ethiopia". የሚል ርዕስ ያለው ነው፡፡ አጥኚው የዚህን ስራ ወሰን በጎንደር ዙሪያ ወረዳ በምትገኝ ቡርቧክስ በተባለች የአዝማሪዎች መንደር ጀምረው፣ ጎንደርና አዲስ አበባ ድረስ በመዘርጋት ነው የሰሩት፡፡ አጥኚው ጥናቱን ለረጅም ጊዜ ቡርቧክስ በመቀመጥ ያደረጉት እንደሆነ የገለፁ ሲሆን፣ በጥናቱ የቡርቧክስ አዝማሪዎችን የሙዚቃ መከወኛ ቦታዎች፣ የምርቃት ግጥሞቻቸውን፣ የሚስጢር መግባቢያ "ኮዶችን" እና የዘር ሃረጋቸውን፣ የአዲስ አበባ የምሽት ቤት አነሳስና የአዝማሪ ቤት ግጥሞችንና ትርጓሜያቸውን አቅርበዋል፡፡

Kawase በ2010 ባደረጉት ሶስተኛው ስራቸው ደግሞ፣ ላሊበላ በተሰኙ ሙዚቃን በመከወን የሚለምኑ ቡድኖችን ህይወት ተመልክተዋል፡፡ እኚህ አጥኝ "Intercultural Dialogue on the Visualization of Local Knowledge: Films on Hereditary

Singers in Ethiopia. የሚል ርዕስ ባለው ስራቸው፣ ላሊበላዎች ሙዚቃቸውን የሚከውኑባቸውን መንገዶች፣ በላሊበላዎችና በአዝማሪዎች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት፣ ላሊበላዎች ገንዘብ ወይም ምግብ ሲሰጣቸው የሚያቀርቡትን ምርቃት፣ የግል ቋንቋቸውን፣ ስሞቻቸውን አጥንተዋል፡፡

እንደታየው Kawase ጥናቶቻቸውን ያደረጓቸው በተለያዩ ሶስት ጊዜያት ነው፡፡ አጥኚው የቪዡዋል አንትሮፖሎጅ ባለሙያ ሲሆኑ ጥናቶቻቸው ኢትኖግራፊያዊ ናቸው፡፡ በተለይም በ2008 “The Transformation of Musical Activities and Self-imposed Group Markers of Azmari in Ethiopia” በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ለረጅም ጊዜ ቡርቧክስ ውስጥ በመቀመጥ ያደረጉት ነው፡፡ Kawase በጥናቶቻቸው የእኔን ጥናት ጨምሮ ለሌሎችም አጥኝዎች ምሳሌ የሚሆኑ ከተጠኝው ማህበረሰብ ጋር እየኖሩ መረጃዎችን የመሰብሰብ ዘዴን በመከወን ጥናቶቻቸውን ሠርተዋል፤ በባህል ጥናት መስክ ዋጋ ያላቸው ዕውቀቶችን ጨምረዋል፡፡ ለእኔ ጥናትም በማህበረሰቡ ውስጥ በመኖር መረጃ መሰብሰብ ያለውን ጥቅም በማሳየት ረገድ ትምህርት ሰጥተውኛል፡፡

ይሁን እንጅ አጥኝው ‹‹እኛ›› እና ‹‹እነሱ›› የሚሉ ሃሳቦች በጥናታቸው ያነሱ ቢሆንም መረጃዎችን ከአዝማሪዎች ብቻ እንጅ አዝማሪ ካልሆነው ማህበረሰብ አልሰበሰቡም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቪዲዮ ቀረፃ ላይ በማተኮራቸው (ቪዡዋል አንትሮፖሎጅስት ስለሆኑ)፣ ወይም የተጠኝውን ማህበረሰብ ሃይማኖት ጠንቅቀው ካለማወቃቸው የተነሳ በጥናቶቻቸው ውስጥ ስህተቶች ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ የጎንደር አዝማሪዎች የሚከተሉትን የክርስትና ሃይማኖት ካለመገንዘብ የተነሳ የጎንደር አዝማሪዎች ‹‹ቅዱሳን›› የሚሏቸውን [15]እዝራንናና ዳዊትን መላዕክት ብለው ይጠራሉ፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ክፍተቶች የተነሳ የአዝማሪዎችን የኑሮና የዘፈን ልምዶችና ለውጥ ለመመርመር ከአዝማሪዎች በተጨማሪ አዝማሪ ካልሆኑ ሰዎችም በተሰበሰቡ መረጃዎች ከተሰራው ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡

ከ Kawase ቀጥሎ በአዝማሪ ላይ የተደረገው የKefyalew (1998) “Minstrels in Addis Ababa: a Study in the Social Life of Gondarian Inzatas” የሚለው ጥናት ነው፡፡ Kefyalew በዚህ ስራቸው አመጣጣቸው ከጎንደር የሆነና በአዲስ አበባ የሚኖሩ አዝማሪዎችን ህይወት አጥንተዋል፡፡ በጥናቱም የአዝማሪዎችን ማንነት እና

[15]የክርስትናው እምነት እዝራና ዳዊትን ቅዱስ ይላቸዋል እንጅ መላዕክት አይላቸውም፡፡

የየት መጣ ፈጠራቸውን፣ ዝምድናቸውን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ምድባቸውንና ሚናቸውን አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም አዝማሪዎች የራሳቸው ማህበር አላቸው፣ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር እኛና እነሱ (እንዛታና ቡጋ በሚል ስያሜ) የሚል ክፍፍል አበጅተዋል፣ በሙዚቃ ክዋኔያቸው ጊዜ የሚግባቡበት የራሳቸው የሚስጥር ቋንቋ አላቸው ብለዋል፡፡ እንዲሁም የአካባቢ ለመዳቸውን፣ የፍልሰት ሂደታቸውንና ቅደም ተከተላቸውን፣ የከተማ አኗኗራቸውን፣ ቤቶቻቸውን፣ የርስበርስ ግንኙነታቸውንና ትብብራቸውን አጥንተዋል፡፡ አጥኚው አዲስ አበባ የሚኖሩ አዝማሪዎች ሙዚቃን በተለያዩ ቦታዎች እንደሚሰሩና ሙዚቃም ለእነሱ የገቢ ምንጫቸው መሆኑን ይህም በመሆኑ አዝማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ሙዚቃውን ለገንዘብ ማግኛ እንደሚያደርጉት ገልፀዋል፡፡

Kefyalew በአዝማሪዎች ላይ የሰሩት ጥናት በሶሻል አንትሮፖሎጅ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ነው፡፡ የጥናታቸው ትኩረት አዲስ አበባ ውስጥ የሚኖሩና መተዳደሪያቸው ዘፈን የሆነ አዝማሪዎች ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ጥልቅ ሊባል የሚችልና ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ጥናት ነው፡፡ ይህ የጥናቱ ገፅታም እኔ ጥናቴን በምን ያህል ዝርዝር መንገድ ልፅፍ የሚገባኝ መሆኑን እንዳስብበት በማድረግ በኩል ማሳሰቢያ ሰጥቶኛል፡፡

ነገር ግን Kefyalew ጥናታቸውን ያደረጉት ከትውልድ ቦታቸው የራቁ ሰዎች ላይ በመሆኑ የአዝማሪዎችን ታሪካዊ ዳራና መሰረት በሚገባ የፈተሸ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ እንዲያውም በአዝማሪዎች ሙዚቃዊ ህይወት ላይ ብቻ በማተኮራቸው ሌላ ህይወት የሌላቸው እስኪመስል ድረስ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የሚያደርጉትን ጥረት በማሳየት ላይ እጅግ አተኩረዋል፡፡ በዚህም የተነሳ የአዝማሪዎች ሌላው ህይወታቸው በሙዚቃው የህይወት ክፍል ተሸፍኗል፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ ከ Kefyalew ጥናት በሰፋ አተያይ አዝማሪዎችን በትውልድ መንደራቸውና በስራ ቦታቸው ያጠና ሲሆን በይዘት ረገድም የአዝማሪዎችን የዘፈን ህይወት ብቻ ሳይሆን ኑሯቸውንም መርምሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእኔ ጥናት በወሎ አዝማሪዎች ላይ የተደረገ በመሆኑ በጎንደር አዝማሪዎች ላይ ከተደረገው ከ Kefyalew ጥናት ይለያል፡፡ ሌላው አዝማሪ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰው አበበ ማለደ ናቸው፡፡

አበበ (2002 ዓ.ም) ‹‹በጎንደር ዙሪያ ወረዳ በቡርቧክስ ቀበሌ የአዝማሪነት ሙያና የዘፈን ግጥሞች›› በሚል ርዕስ ጥናታቸውን ሰርተዋል፡፡ ይህ ጥናት አዝማሪነት በቡርቧክስ መቼ ተጀመረ? ሙያው አሁን ያለበት ደረጃና አዝማሪው ለሙያው ያለው

አመለካከት የሚሉ ርዕሶች ቀርበውበታል፡፡ የቡርቧክስ አዝማሪዎች ዘፈን ግጥም አደራረስ፣ አከዋወንና ተስተላልፎ፣ የቡርቧክስ አዝማሪዎች ዘፈን ግጥም ይዘት ቀርቧል፡፡ በውጤቱም የቡርቧክስ አዝማሪዎች በሙያቸው የተነሳ በአካባቢው ማህበረሰብ የተናቁ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ከባላገሩ ጋር የጋብቻ ግንኙነት የላቸውም ነበር፡፡ የቡርቧክስ አዝማሪዎች የዘፈን ግጥሞቻቸውን ከህዝቡ ያገኛሉ፡፡ ቃል ግጥሙን እንደሁኔታው በይዘቱም ሆነ በቅርፁ ለውጥ ሳይደረግ፣ የተወሰነ ለውጥ በማድረግና ሙሉ ለውጥ በማድረግ ይከውናሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የራሳቸውን ግጥም ፈጥረው ያቀርባሉ፡፡ ይህን የዘፈን ግጥምና አጠቃላይ የዘፈን ክወናቸውን በተናጠል፣ በጥንድ፣ በማጋነን፣ ግጥም በመቀበልና በመሳሰሉ ስልቶች ይከውናሉ፡፡ የቡርቧክስ አዝማሪዎች የራሳቸው የሚስጥር ቋንቋ አላቸው፡፡ ይህንን የሚስጥር ቋንቋ የፈጠሩት የራሳቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ነው፡፡ በዚህም ዘፈን በሚከውኑበትም ሆነ በሌላ ጊዜ ከጥቃት ይከላከሉበታል፡፡ የቡርቧክስ አዝማሪዎች በዘፈን ግጥሞቻቸው የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን ይዳስሳሉ፡፡ በዚህም ምስጋና፣ ሙገሳ፣ ምክር፣ ትችት፣ ፍቅር፣ ስድብ ይዘት ያላቸውን ግጥሞች በመደርደር ታዳሚን ያሞግሳሉ፣ ይመክራሉ፣ ያስተምራሉ ይተቻሉ ብለዋል፡፡

አጥኚው የአዝማሪዎች ሙያ በዘመናዊ ሙዚቃ ባንድ ተፅዕኖ እየቀዘቀዘ ስለመጣ ሙያው ራሱን ችሎ ከዘመናዊ ሙዚቃ ጎን ለጎን የሚያድግበትና የሚሻሻልበት አጋጣሚ ቢመቻች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ተፅዕኖ ሙያው እየቀዘቀዘ እንዲመጣ ስላደረገው በአካባቢው የባህል ባለሙያዎች ዘንድ አዝማሪዎችን የማበረታታትና የስራቸውን ውጤት ለሌላው ማህበረሰብ የማስረዳትና የማሳወቅ ስራ ቢሰራ፣ ግጥማቸው በሚመለከተው አካል በየወቅቱ እየተሰበሰበና እየተተነተነ በቅርስነት የሚያዝበትና የሚጠበቅበት ሁኔታ ቢመቻች፣ ባህል ነክ ተመራማሪዎች በአዝማሪ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ቢያደርጉ ለአዝማሪው ሙያ መዳበር አስተዋፅኦ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ ሲሉ የመፍትሄ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

አበበ በቡርቧክስ አዝማሪዎች ላይ ያተኮረውን ጥናታቸውን ያደረጉት በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪያቸው ማሟያ እንዲሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ጥናታቸው የቡርቧክስ አዝማሪዎች በሚገጥሟቸው የዘፈን ግጥሞች ላይ ያተኮሩ ሲሆን፣ በጥናቱ ለሌሎች አጥኚዎች መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን በማቅረባቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል፡፡ ለምሳሌ አዝማሪዎች በትውልድ በሚገኙበትና የእኔ በሚሉት አካባቢ ተገኝተው መረጃ መሰብሰባቸው የአዝማሪዎችን ህይወትና የሙዚቃ ለመዳ በቀጥታ ለመመልከት የሚያስችላቸው በመሆኑ ጥሩ መረጃን ለሌሎቻችን

አስተላልፈዋል፤ በሃገራችን ከሚገኙ የአዝማሪ ቦታዎች ውስጥ አንዱን አመላክተዋል (አስተዋውቀዋል)፤ በአዝማሪ ዙሪያ መረጃዎችን ሰብስበዋል። አበበ የጥናታቸው ትኩረት ቃል ግጥም በመሆኑ የእኔ ጥናት ደግሞ በአጠቃላይ በአዝማሪዎች ልምድ ላይ ስለሚያተኩር እንዲሁም የእሳቸው ጥናት በጎንደር አዝማሪዎች ላይ የተደረገ በመሆኑና የእኔ ጥናት ደግሞ በወሎ አዝማሪዎች ላይ የተደረገ በመሆኑ ሁለቱ ጥናቶች ልዩነት አላቸው። ሌላው አዝማሪ ላይ ያጠኑ ሰው Mesganaw ናቸው።

Mesganaw (2010) ‹‹Change and Continuity in the Lives of Birbuax Azmaris›› በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ነው። አጥኚው እንደአበበ ሁሉ ጥናታቸውን በቡርቧክስ አዝማሪዎች ላይ አድርገዋል። አጥኚው ይህ ስራቸው ሙሉ በሙሉ በቡርቧክስ አዝማሪዎች ህይወት ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ጥናቱን በኢትኖግራፊክ ዘዴ እንደከወኑት ገልፀዋል። በስራውም አዝማሪዎች ራሳቸውን የቻሉ ቡድኖች እንደሆኑ አስፍረዋል። የአዝማሪዎች የት መጣ አከራካሪ መሆኑንና በራሳቸው ሚት ግን ከእስራኤል መጣን ሲሉ እንደሚናገሩ፣ የቡድኑ ብቻ የሆነ መግባቢያ ቋንቋ እንዳለ፣ ማህበረባህላዊ ዝምድናቸው እርስ በእርስ ብቻ በሚደረግ ጋብቻ እንደሚመሰረት፣ ሃይማኖታቸው ክርስትና መሆኑንና ሌሎች ባህላዊ እምነቶችም እንዳሏቸው፣ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነት የተወሰነ መሆኑን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና (ሰርግ ያለአዝማሪ የማይታሰብ መሆኑን)፣ ኢኮኖሚያዊ መልካቸውን (በእርሻ ስራና በሙዚቃ ክወና እንደሚተዳደሩ) አሳይተዋል። በመጨረሻ በቡርቧክስ አዝማሪዎችና አዝማሪነት ላይ የተከሰቱ ዋና ዋና ለውጦችንና ተግዳሮቶችን የሆኑ ጉዳዮችን አብራርተዋል።

አጥኚው ጥናታቸውን የሰሩት በሶሻል አንትሮፖሎጅ ትምህርት ክፍል ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያቸው ሲሆን ጥናቱ በቅርፅም ሆነ በይዘት ረገድ ጠንካራ አቀራረብ ያለው ነው። የምስጋናው ጥናት አዝማሪዎች በትውልድ የእኔ በሚሉት ቦታ ላይ የተደረገ መሆኑና ትኩረቱ ደግሞ ጥናቱ ‹‹ተከታታይነት››ና ‹‹ለውጥ›› በሚሉ ፅንሰሃሳቦች ዙሪያ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ያመሳስለዋል።

ይሁንና የ Mesganaw ጥናት ጎንደር ውስጥ መሆኑ የእኔ ጥናት ደግሞ ወሎ ላይ መሆኑ፣ እንዲሁም ምንም እንኳን ሁለቱም ጥናቶች ተከታታይነትና ለውጥ ላይ ቢያተኩሩም Mesganaw የጎንደር አዝማሪዎችን ህይወት በአንትሮፖሎጂ አተያይ ከማኅበረሰቡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መስፈሪያዎች አንፃር ምን ይመስላል የሚሉ ዋና ዓላማዎችን በመያዝ ሲያዩ የእኔ ጥናት ደግሞ የፎክሎር ጥናት

በመሆኑ የቡድኑን ማንነት ቡድኑን የገነቡትን የኑሮና የዘፈን ልምዶች ምንነት ከኢመደበኛነት ተፈጥሮና ክዋኔያቸው አንፃር በመመርመሩ ሁለቱ ጥናቶች በትኩረት አቅጣጫ የተለያዩ ሆነዋል። Mesganaw የጎንደር አዝማሪዎችን ሲያጠኑ ትኩረታቸውን ያደረጉት የአዝማሪዎች ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ህይወት ምን ይመስላል የሚለው ላይ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የወሎ አዝማሪዎች በኑሯቸውና በዘፈናቸው ውስጥ ያሉ ልምዶችን እንዴት አዳበሯቸው? እንዴት ሲያስተላልፏቸው ኖሩ? ልምዶቹ አሁን ምን እየሆኑ ነው? በሚለው ላይ አተኩሯል። ከዚህ ባሻገር አጥኚው መረጃዎችን ለመተንተን ንድፈሃሳቦች ያልተጠቀሙ ሲሆን እኔ ግን የልምዶችን ለውጥ ለመረዳት ማርክሳዊ ተከታታይነታቸውን ለማየት ደግሞ ክዋኔያዊ ንድፈሃሳቦችን ተጠቅሜ መረጃዎችን ተንትኛለሁ። በዚህም በተለይ በፎክሎር ጥናት ውስጥ በፍፁም ሊቀር የማይችለውን ክዋኔ የተባለ ሃሳብ በመተንተኑ ይህ ጥናት ከ Mesganaw ጥናት የተለየ ሁኗል። ቀጥሎ የተዳሰሰው ስራ የሐረገወይን ነው።

ሐረገወይን (2004 ዓ.ም) ‹‹በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን አቅርበዋል። አጥኚዋ በጥናታቸው በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ ባህላዊ የምሽት ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ የሶስት አዝማሪዎችን የህይወት ታሪክ ፅፈዋል። አዝማሪዎች በሚሰሩባቸው የባህል ምሽት ቤቶች የሚከውኗቸውንና በጥምቀት በዓል የከወኗቸውን ቃልግጥም ሰብስበው በይዘታቸው መድበዋል። መረጃዎችን በምልከታና በቃለመጠይቅ የሰበሰቡ ሲሆን ‹‹ተረካዊ›› የተሰኘውን ንድፈሀሳብ በመጠቀም ትንተና አድርጌያለሁ ብለዋል። ከትንተናውም ማህበረሰቡ ለአዝማሪነት ሙያ ያለው አመለካከት በተወሰነ መልኩ እየተቀየረ መጥቷል፣ አዝማሪዎች በመታወቅ ደረጃቸው ሙዚቃን የሚከውኑበት ቦታ ይለያያል፣ አዝማሪዎች በዓመታዊ የሃይማኖት ከበራዎች ላይ ታቦትን ያጅባሉ፣ በአሁን ሰዓት ደግሞ የመንግስት እንግዳዎች የአቀባበል ስነስርዓት ላይ እንዲከውኑ ይጋበዛሉ፣ በጥናቱ የተገኙት ቃልግጥም በሌሎች ጥናቶች ላይ ከታዩት ቃልግጥም አዲስ ፈጠራ የታከለባቸው ናቸው፣ ለዚህ ጥናት ግብዓትነት ከተለያየ አውድ የተሰበሰቡ አብዛኞዎቹ የአዝማሪ ቃልግጥም በቋንቋ መረጣ ዝቅተኛ በመሆናቸው የቃልግጥም እምቅነት፣ ዘይቤያዊነት፣ ስነውበት እና ቅኔያዊነታቸው እየጠፉ መጥቷል፤ ቃልግጥም ጉራማይሌ እየሆኑ ነው፤ ባህል ምሽት ቤቶች ባህላዊ ያልሆኑ መጠጦች እና ቂስ በውስጣቸው አካትተዋል የሚሉ ውጤቶችን አገኘሁ ብለዋል።

ከውጤቶች በመነሳት በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ አዝማሪያን ለታዳሚ፣ ለንግድ ወዘተ የሚለውን ምክንያት ትተው ለቃል ግጥሙ ስነውበት ቅድሚያ ቢሰጡ። ምክንያቱም በዚህ አያያዝ ቃልግጥሙ ለዛው ከጠፋ ታዳሚውንም ለማግኘት ያስቸግራል። የባህል ምሽት ቤቶች የባህል መገለጫ እንደመሆናቸው ባህላዊ ነገርን ብቻ ማሳየት ቢችሉ። ምክንያቱም በዚህ ቦታ ባህላዊውን የሙዚቃ ክዋኔና አጠቃላይ አውዱን ለማየት የሚመጣው ታዳሚና ቱሪስት የሀገራችንን ባህል ብቻ መመልከት ያለበት ይመስለኛል ሲሉ የይሁንታ ሃሳቦችን አቅርበዋል። ሐረገወይን በዚህ ጥናታቸው እስከዛሬ ድረስ በአንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናት ብቻ የተሞከረ እንጅ በሌሎች አጥኝዎች ያልተሰራበትን በአዝማሪዎች የህይወት ታሪክ ላይ ስራቸውን ማቅረባቸው በጣም የሚያስመሰግናቸው ነው። ምክንያቱም በርካታ ጥናቶች አዝማሪዎችን እንደቡድን ያያሉ እንጅ በቡድኑ ውስጥ ግለሰቦችን አያስቡም። ሌላው ጥናቱን ሊያስመሰግነው የሚችለው ጉዳይ ተጨባጭ በሆነ ተፈጥሯዊና ወቅታዊ የሆነ መቼት መደረጉ ነው። በዚህ ረገድ በቡድኑ ላይ ብቻ ማተኮር እንደሌለብኝ እንዲሁም ለተፈጥሯዊ አውድ ትኩረት መስጠት እንዳለብኝ በማስገንዘብ ደረጃ ለእኔ ጥናት አስተዋፅኦ አበርክተውልኛል። ከዚህ በተጨማሪ አጥኝዋ በመስክ ስራቸው ወቅት ያጋጠሟቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች በዝርዝር በማስቀመጣቸው ለመስክ ስራ በምወጣበት ጊዜ ላደርግ ስለሚገባኝ ጥንቃቄ ጥቆማ ሰጥተውኛል።

በጥናቱ ላይ ሊሄሱ የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ። አጥኝዋ የህይወት ታሪካቸው የተጠናው አዝማሪዎች በባህር ዳር ከተማ ታዋቂ ናቸው ይላሉ። ይሁንና እነዚህ ሰዎች ታዋቂ የሚለውን ማዕረግ ለመስጠት ምስክሮች ሆነው የቀረቡት እሳቸውም እንደሚሉት አብረዋቸው የሚሰሩ ‹‹አንዳንድ›› አዝማሪዎች ናቸው። ታዳሚው ማህበረሰቡ አይደለም። ስለዚህ መረጃው ከታዳሚ ሊፈለግ ይገባ ነበር። አጥኝዋ ከተሰበሰቡት ቃልግጥም በመነሳት አብዛኛዎቹ ቃልግጥም በቋንቋ መረጣ ዝቅተኛ ናቸው። የቃልግጥሞች እምቅነት፣ ዘይቤያዊነት፣ ስነውበትና ቅኔያዊነታቸው እየጠፋ መጥቷል ሲሉ የደረሱበትን ውጤት አስፍረዋል። ይሁንና የአዝማሪ ግጥሞች ጥሩነት እየጠፋ መምጣቱን ሲገልፁ አንደኛ ይህንን ለማለት ያስቻላቸውን ንፅፅር አላደረጉም። ሁለተኛ ምናልባት ግጥሞቹ በአብዛኛው የተሰበሰቡት በምሽት ቤቶች ነውና አውዱና ታዳሚው በግጥሞች ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ግምት ውስጥ ያላስገቡ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ሌላው በጥናቱ ላይ የታየው ክፍተት ባህላዊ የአዝማሪ ምሽት ቤቶች ባህላዊ ጉዳዮችን ብቻ ሊከውኑ ይገባል ሲሉ የሰጡት የይሁንታ ሃሳባቸው ነው። አጥኝዋ ይህንን

አስተያየት ሲሰጡ ምንጊዜም ቢሆን ባህል ሊለወጥ የሚችል ጉዳይ መሆኑን የረሱ ይመስላል፡፡ ይህ ደግሞ ሊረሳ የማይገባው ጉዳይ ነው፡፡ የሃረገወይን ጥናት ትኩረቱ ባህርዳር ላይ በመሆኑ፣ በሶስት አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ ላይ በመሰራቱ፣ አዝማሪዎች ለስራ በሚኖሩበት አካባቢ የተደረገ በመሆኑ፣ የእኔ ጥናት ደግሞ ወሎ ላይ በመደረጉ፣ የአዝማሪነትን ህይወት ሁለንተናዊ ተከታታይ ልምድና ለውጥ በማየቱ፣ አዝማሪዎችን ከትውልድ ቦታቸው ጀምሮ በማጥናቱ ሁለቱ ጥናቶች የተለያዩ ሆነዋል፡፡

በመጨረሻ ዳሰሳ የተደረገበት ስራ ‹‹የቃል ግጥም ክዋኔ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ አዝማሪ ቤቶች›› በሚል ርዕስ 2005 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰራው የቤተልሔም አለምሰገድ ጥናት ነው፡፡ አጥኝዋ በጥናታቸው በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ አካባቢዎች የሚገኙ የባህል ምሽት ቤቶችን የቃል ግጥም ክዋኔ በማህበረባህላዊ አውድ ውስጥ በማስገባት መተንተን የሚል ዋና አላማ ይዘው ተነስተዋል፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አዝማሪዎች በብዛት የሚገኙባቸውን ካዛንቺስን፣ ሃያ ሁለትንና ገዳም ሰፈርን በመምረጥ በእነዚህ አካባቢዎች ከሚገኙ አዝማሪ ቤቶች አስር ያህሉን በመምረጥ የአዝማሪ ቤቶችን ቃል ግጥም ክዋኔ ተመልክቻለሁ ብለዋል፡፡

አጥኝዋ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቃለመጠይቅንና ምልከታን፣ መረጃ ለመተንተን ደግሞ የክዋኔ ንድፈሃሳብ እንደተጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ከትንታኔዎች በአዝማሪ ቤቶች የሚደረጉ ክዋኔዎች በሙሉ ባህላዊ ናቸው፣ አዝማሪዎች ታዋቂና ታዋቂ ያልሆኑ ተብለው ይመደባሉ፣ በብዙ አዝማሪ ቤቶች የሚዜሙት ቃልግጥም ይዘታቸው በታዳሚዎች ፍላጎት የተነሳ ወሲብ ነው፣ አዝማሪዎች ታዳሚዎቻቸው ስለማይወዱላቸው ማህበራዊ ሂስነት ያላቸውን ቃልግጥም አይከውኑም፤ አዝማሪዎች ራሳቸውን እንደጥበበኛ የሚቆጥሩ ናቸው፤ አንዳንድ አዝማሪዎች በመሰላቸት ስራ እስከመተው ደርሰዋል የሚሉ ውጤቶችን እንዳገኙ ገልፀዋል፡፡ ከውጤቶች በመነሳት ከእርሳቸው ጥናት በተሻለ ሁሉንም አዝማሪ ቤቶች በማካተት፣ ረዥም ጊዜ በመውሰድና ሰፊ የሆነ ተሳትፏዊ ምልከታ በማካሄድ ቢጠና ከዚህ የተሻለ ውጤት ሊገኝ ይችላል የሚል አስተያየት ሰጥተው ጥናታቸውን አጠናቅቀዋል፡፡

ቤተልሄም በዚህ ጥናታቸው የአዲስ አበባን አዝማሪ ቤቶች የቃል ግጥም ክወና በማሳየት ረገድ ጥሩና ጥልቀት ያለው ስራ ሰርተዋል፡፡ ጥናቱ በከተማ የሚኖሩ አዝማሪ ቤቶችን፣ የአዝማሪዎችን ወቅታዊ ሁኔታ፣ የአዝማሪዎችንና የታዳሚያቸውን ክዋኔያዊ

ተራክቦ በደንብ ያሳያል፡፡ እንዲሁም የክዋኔያቸውን ባህርይ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር እኔም ለክዋኔ መስጠት ያለብኝን ትኩረት አስገንዝበውኛል፡፡

ይሁንና ጥናቱ አዝማሪዎችን በስራ ቦታቸው ብቻ እንጅ፣ ሌላ ማህበራዊ ህይወታቸውን ባለመዳሰሱ፣ ለአዝማሪነት መነሻና ለሙያው ተስተላልፎ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ባለማንሳቱ፣ የሙያውን ታሪካዊና ባህላዊ እድገት ባለማንሳቱ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ብቻ በመሰራቱ፣ ከቦታ አንፃር፣ በወሎ አዝማሪዎች ላይ፣ ከይዘት አንፃር ደግሞ፣ ታሪክ ከክወና ጋር አስተባብሮ ከተጠናው ከዚህ ጥናት በእጅጉ የሚለይ ነው፡፡

ከዚህ በላይ አዝማሪ በሚለው ፅንሰሃሳብ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች አዝማሪን ከተለያዩ አቅጣጫዎች፣ ከተለያዩ ማህበራዊና ተፈጥሯዊ መቼቶች ከተለያየ ጥልቀትና ስፋት አንፃር መርምረዋል፡፡ የተዳሰሱት ጥናቶች ከርዕሰ ጉዳይ፣ ከአጠናን ዘዴ፣ ከመስክ ተሞክሮና ከሌሎችም ጉዳዮች አንፃር ልከናቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በማሳየት ረገድ ለእኔ ጥናት በጎ አስተዋፅኦ አበርክተውልኛል፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ጥናቶቹ በአጠቃላይ በአዝማሪና አዝማሪነት ላይ እውቀት ሊጨምሩ የሚችሉ ወሳኝ ነጥቦችን አንስተዋል፡፡ የዕውቀት መስኩንም ወደፊት ሊያራምዱ የሚችሉ የምርምር ውጤቶችን አቅርበዋል፡፡ ሆኖም ጥናቶቹ ሲመረመሩ አንዳንዶቹ ጥልቅ የሆነ የመስክ ስራ ጉድለት፣ ሌሎቹ በትክክለኛው ማህበራዊና ባህላዊ አውድ መረጃ ያለመሰብሰብ፣ አንዳንዶቹ በጣም ውስን ነገሮች ላይ የማተኮር ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እስካሁን አዝማሪ ላይ በተደረጉ ጥናቶች ውስጥ በአጥኝዎች የሙያ ምንነት፣ በትኩረት እጦት፣ ወይም በጥናት ጉድለት ምክንያት ተጠኚውን ቡድን ከራሱ አተያይ አንፃር ጭምር ያለማጥናት፣ ጊዜና ቦታ በአዝማሪ ባህል ላይ ሊፈጥሩ የሚችሉትን ተፅዕኖ ልብ ያለማለትና ርዕሱን ከዚህ አንፃር ያለመመርመር እንዲሁም ወሎ ውስጥ በመንደር ደረጃ የሚኖሩ አዝማሪዎችን ያለማጥናት ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ በዚህ ጥናት የፎክሎር የአጠናን ዘዴን በመከተል የተዘረዘሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡ ጥናቱም የተከተለው የአጠናን ዘዴ ቀጥሎ ተገልጧል፡፡

# 3. የአጠናን ዘዴ

በዚህ ክፍል ጥናቱ ሲደረግ ምን ምን ተግባራት እንደተከናወኑ፣ ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች አይነት፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶች፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችና አስፈላጊነታቸው ተገልጿል፡፡

## 3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት ዓላማዎቹን ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መፅሃፎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ የተጓዦች ማስታወሻዎች፣ ጋዜጦች፣ ጥናቶች፣ መፅሄቶች፣ ሪፖርቶች፣ በብሔራዊና በክልል ሬዴዮና ቴሌቭዥን ጣቢያዎች የተላለፉ ‹‹ፕሮግራሞች›› ናቸው፡፡ እነዚህ ምንጮች ከቤተመፃህፍት፣ ከፌዴራል ስታስቲስቲክስ መስሪያ ቤቶች፣ ጥናቱ በሚደረግበት አካባቢ በሚገኙ የፌደራል፣ የክልል፣ የዞንና፣ የወረዳ ገንዘብ፣ ኮሚኒኬሽን ወዘተ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የተገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ከመስክ የተገኙ ጥሬ መረጃዎችን ለመተንተን የማመዛዘኛና የማነፃፀሪያ ሃሳቦች ሆነው አገልግለዋል፡፡

ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የመስክ መቼቶች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የመስክ መቼቶች ሆነው ያገለገሉት ስለወሎ አዝማሪዎች ጥሬ መረጃ የተገኘባቸው መቼቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ መቼቶች የተገኙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ምልከታ (Observation)፣ ቃለመጠይቅና (Interview)፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

### 3.1.1. ምልከታ

ምልከታ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የፎክሎር ጥናት በተፈጥሯዊ አውድ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን የሚፈልግ በመሆኑና ምልከታ ለዚህ ተግባር በጣም አመቺ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ በተፈጥሯዊ አውድ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን

ስለሚፈልግ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ውሏል። ዘዴው የወሎ አዝማሪዎችን፣ የኑሮና የዘፈን ልምድ ተከታታይነትና ለውጥ ለመረዳት የሚያስችሉ አውዶች በተገኙበት መስኮች አገልግሏል።

ምልከታው በመኖሪያ ቤቶች፣ በመዝናኛ ቤቶች (በጠጅ ቤቶች፣ በአረቄ ቤቶች፣ በምሽት ክበቦች)፣ በሰርግ ቤቶች፣ በጥምቀት በዓል፣ በዓመታዊ ድግስ፣ በስብሰባ አዳራሽ፣ በሩቅ ተመልካችነትና በቅርብ ተሳታፊነት ተካሂዷል። በሩቅ ተመልካችነት የተሰበሰቡት መረጃዎች መረጃ ሰጪዎቹን በአቅራቢነት፣ ሌላውን ሰው ደግሞ በተመልካችነት ብቻ እንዲሳተፉ በሚጋብዙ አውዶች የተገኙ ናቸው። ከእነዚህ አይነት አውዶች ውስጥ የታቦት ንግስ፣ የስብሰባ ቦታዎች ዋና ዋናዎች ናቸው። በቅርብ ተሳታፊነት መረጃዎች የተሰበሰቡባቸው አውዶች በርካታ ናቸው። ከእነሱ ውስጥ ሰርግ ቤቶች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ መዝናኛ ቤቶች፣ በዓላት ሲሆኑ፣ በእነዚህ ቦታዎች ክዋኔዎች ከታዳሚ የሚጠይቁትን ግጥም ማቀበል፣ ማጨብጨብና መሸለም የመሳሰሉ ተግባራት ላይ በመሳተፍ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎችን በአግባቡ ለመያዝ ሲባል የድምፅ መቅጃ ቴፕሪከርደር፣ የፎቶና የቪዲዮ ካሜራዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል። በምልከታው በርካታ መረጃዎች የተገኙ ሲሆን በተለይ በጥናቱ በአላማ ከተነሱ ጥያቄዎች ውስጥ የወሎ አዝማሪዎች ተከታታይ የኑሮ፣ የዘፈን ልምድ እንዲሁም ወቅታዊ አኗኗር ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ለመመርመር ዘዴው ጥቅም ላይ ውሏል። ይሁንና ለዚህ ጥናት ምልከታ ብቻውን በቂ የመረጃ ማሰባሰቢያ ባለመሆኑ ቃለመጠይቅ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል።

## 3.1.2. ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቅ መረጃ ሰብሳቢው ለመረጃ አቀባዩ ጥያቄ በማቅረብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው። ይህን ዘዴ በተለይም በምልከታ ሊገኙ የማይችሉ ከጊዜ አንፃር ወደኋላ መመለስ የሚጠይቁ እና ከቦታ አንፃር በአጥኝ አይን መታየት የማይችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚያስችልና ይህ ጥናት ደግሞ ‹‹ተከታታይነትንም›› ስለሚያጠና ዘዴው አገልግሎት ላይ ውሏል። ዘዴው በተለይ በአላማው ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የተካተቱት፣ የወሎ አዝማሪዎችን ተከታታይ የኑሮና የዘፈን ልምድን የሚያሳዩ ጉዳዮችን በተፈጥሯዊ አውድ ሊገኝ የማይችለውን ጥንታዊ (ቀደምት) ጎናቸውን

ለመረዳት፣ እንዲሁም የወሎ አዝማሪዎችን ባህላዊ የዘፈን ልምድ ታሪካዊ ዳራና ወቅታዊ ሁኔታ ለመገንዘብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መረጃ ተሰብስቧል፡፡

የቃለመጠይቅ አይነቶች በርካታ ቢሆኑም በዚህ ጥናት ሶስት አይነት የቃለመጠይቅ አይነቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ እነሱም፣ የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ (የተቀናበረና ያልተቀናበረ)፣ የህይወት ታሪክ ቃለመጠይቅ፣ የዘር ሃረግ ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.1.2.1.የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ

ይህ የቃለ መጠይቅ አይነት በአጠቃላይ ስለአዝማሪዎች የህይወትና የስራ ታሪክ ለመረዳት ሲባል የተዘጋጀ ነው፡፡ የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ፤ ውስን ቃለመጠይቅ (structured interview፣ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅና (Semistructured interview) ነፃ ቃለመጠይቅ (Unstructured interview) ተብሎ በሶስት ይከፈላል (ያለው፤ 1998፣ 183)፡፡ በዚህ ጥናትም ሶስቱ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

ውስን የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ አስቀድመው በተዘጋጁ ጥያቄዎች የሚካሄድ የቃለመጠይቅ አይነት ነው፡፡ በዚህ ጥናትም የወሎ አዝማሪዎችን ተከታታይ የኑሮ ልምድ በመረዳት ሂደት የቀረቡ አዝማሪዎች የሚኖሩባቸውን መንደሮች ዝርዝር፣ የዘር ሃረግ ቆጠራን የመሳሰሉ መረጃዎች በዚሁ የቃለመጠይቅ አይነት ተሰብስበዋል፡፡ ይሁንና ውስን ቃለመጠይቅ አስቀድመው በተዘጋጁ ጥያቄዎች እንዲሁም በተመረጡ መረጃ ሰጪዎች ብቻ የሚከናወን በመሆኑ ገደብ አለበትና መረጃ ሰጪዎች በአንፃራዊነት ያለምንም ገደብ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ሲባል በከፊል ነፃና በነፃ የአጠቃላይ የቃለመጠይቅ አይነቶች መረጃ ተሰብስቧል፡፡

ከፊል ነፃ የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ አስቀድሞ የተዘጋጁ ጥቂትና ሁነት የጠራቸውን ጥያቄዎች ለመረጃ ሰጪዎች በማቅረብ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው፡፡ ይህንን የቃለመጠይቅ አይነት በዚህ ጥናት ውስጥ መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት መረጃ ሰጪዎች ለአንዳንድ ትንተናና ገለፃ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች ያለገደብ መረጃ እንዲሰጡ ዕድል ለመስጠትና ለመረጃ ሰብሳቢዋም አስቀድመው የተዘጋጁ ጥያቄዎች የሚያጭሯቸውን ሌሎች ጥያቄዎች የማቅረብ ዕድል ለማግኘት ነው፡፡

ነፃ የአጠቃላይ መረጃዎች ቃለመጠይቅ ለመረጃ ሰብሳቢም ሆነ ለመረጃ ሰጪዎች ሙሉ ነፃነት የሚሰጥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው በዚህ

ጥናትም ከዚህ አላማው አንፃር አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል። መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው የሚሰጠውን ነፃነት በመጠቀም ከመስክ ስራው አስቀድሞም ሆነ በመስክ ስራው ወቅት በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከማንኛውም ቦታና ሰው መረጃ የተሰበሰበበት ነው። በተለይ የመስክ ስራው በተካሄደበት ወቅት ሁኔታው አመቺ በሆነበት አጋጣሚ ሁሉ የአዝማሪዎች ተከታታይ የኑሮ ልምድ ምን ይመስላል? በሚለው የጥናቱ አንድ ጥያቄ ስር የሚታዩ አዝማሪ ምንድን ነው? እና የአዝማሪዎች ማህበራዊ ደረጃ ምንድን ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በርዕሰጉዳዩ ዙሪያ መናገር ከሚችል አዝማሪም ሆነ አዝማሪ ካልሆነ ማንኛውም ሰው ጋር ውይይት በመክፈት መረጃ ተሰብስቧል። ዘዴው መረጃ ሰጪዎች ያለምንም የዕድሜ፣ የፆታ፣ የማንነት ገደብ፣ ‹‹እየተደመጥኩ ነው›› ከሚል ስጋት መረጃ ሳያድበሰብሱና ሳይደብቁ፣ በነፃነት ከሚያደርጉት ንግግር መረጃ የተሰበሰበበት በመሆኑ በርካታና ጠቃሚ መረጃዎች ተገኝተውበታል። ለዚህ ዘዴ የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት ሆነው ያገለገሉት መኖሪያ፣ መዝናኛ፣ መጓጓዣዎችና የመሳሰሉት ቦታዎች ናቸው። የመረጃ ሰጪዎችን ቁጥር የወሰነው አጋጣሚው ነው።

በዚህ ሁኔታ በውስን፣ በከፊል ነፃና በነፃ ቃለመጠይቅ አማካኝነት በወሎ አዝማሪዎች የዘፈንና የኑሮ ልምድ ውስጥ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ የሚገልፁ አጠቃላይ መረጃዎች ብቻ ማግኘት የጥናቱን ጥያቄዎች ስለማይመልስ ለዚህ ሲባል ልዩ ጉዳዮችን በሚያስገኙ በቃል ታሪክ (በህይወት ታሪክ) እና በዘር ሃረግ ቃለመጠይቆች መረጃዎች ተሰብስበዋል።

### 3.1.2.2. ቃልታሪክ (የህይወት ታሪክ ቃለመጠይቅ)

ቃልታሪክ፣ በአንድ ረገድ እንደፎክሎርና አንትሮፖሎጅ ላሉ ወይም ለሌላ የማህበራዊ ሳይንስ ጥናቶች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን በሌላ ረገድ ደግሞ እንደሌሎች ሙያዎች ለምሳሌ እንደታሪክ ራሱን ችሎ የሚጠና መስክ ነው። ዘዴው በዚህ ጥንድ ባህርይውና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ የሌለውና በየጊዜው የተለያዩ ብያኔዎች ሲያገኝ የኖረና እያገኘ ያለ ሙያ ነው።። ይሁንና የተለያዩ ፀሃፍት ለሙያው የሰጧቸውን ብያኔዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቃል ታሪክ የሰዎችን ትዝታና የህይወት ታሪክ ለመረዳት በእነሱም ታሪክ ውስጥ የማህበረሰቡን ጠቅላላ ሁኔታ ለመገንዘብ ሲባል ከግለሰቦች በቃለመጠይቅ መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው Ritchie (1997, 19) ።

በዚህ ጥናት በግለሰቦች የካበተ የህይወት ልምድ አማካይነት የወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ምን ነበር? ምን ለውጥ መጣ? ግለሰቦች በሌላው ማህበረሰብ ውስጥ ምን ሚና አላቸው? የሚሉና ሌሎች ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በአጠቃላይ የጥናቱን ዋና ጥያቄ የወሎ አዝማሪዎች ተከታታይ የኑሮና የዘፈን ልምዶች እና የመጡ ለውጦች ምንድን ናቸው? የሚለውን ማየት የሚያስችሉ መረጃዎች ከተመረጡ አስር ሰዎች በቃል ታሪክ ተሰብስበዋል፡፡ ሰዎች ስለህይወት ታሪካቸው በሚያደርጉት ትረካ ስለተጠኘው ቡድን ቀደምት ባህል መረጃ ተገኝቷል፤ ባለፈውና ባሁን ጊዜያት መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ለመረዳትና የሙያውን ወቅታዊ ሁኔታ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተረፈ ደግሞ ማህበረሰብ የግለሰቦች ስብስብ ነውና በማህበረሰቡ ውስጥ የካበተ ልምድ ያላቸውንና ራሳቸውን በሙያው ውስጥ አስገብተው የኖሩና አሁንም ሙዚቃን በመከወን ላይ የሚገኙ አዝማሪዎችን በመፈለግ የህይወት ታሪካቸው በቃለመጠይቅ ተደምጧል፡፡ ከቃለመጠይቁ የቡድኑን ህይወት፣ እንዲሁም የሙያ ቀጣይነትና ለውጥ ለመረዳት ተሞክሯል፡፡ በዚህም በዓላማው ከቀረቡ ጥያቄዎች ውስጥ በወሎ አዝማሪዎች ህይወት ውስጥ የመጡ ለውጦች ምን ምን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚያስችሉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃ ሰጪዎችን መረጣ በተመለከተ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ይህንኑ የሚያበረታታ በመሆኑ ዕድሜን (በዕድሜ የገፉ) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ከአጠቃላይና ከቃል ታሪክ በተጨማሪ በዘር ሃረግ ቃለመጠይቅም መረጃ ተሰብስቧል፡፡

### 3.1.2.3. የዘር ሃረግ ቃለመጠይቅ፡-

ይህ የቃለመጠይቅ አይነት የወሎ አዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ ተከታታይ ልምዶች ምን ምን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ አንፃር በአዝማሪ ማህበረሰብ መካከል ያለውን የዝምድና ግንኙነት ለማወቅ ሲባል አገልግሎት ላይ የዋለ ዘዴ ነው፡፡ በወረዳዎች ውስጥ ያሉ አዝማሪዎች ዝምድና ምን ይመስላል? በዞኑ ውስጥ በተለያዩ ወረዳዎች የሚኖሩ አዝማሪዎች እርስ በእርስ ምን አይነት ዝምድና አላቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ዘዴው ጥሩ ነው ተብሎ በመታሰቡ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ዝምድና፣ የዝምድና ትስስር ማወቅ ስለቡድኑ አጠቃላይ ማንነትና የትመጣ ለተደረገው ፍለጋ መልስ ሊያስገኙ የሚችሉ መረጃዎችን አስገኝቷል፡፡ ስለዚህም አዝማሪዎች የሚከተሉትን የጋብቻ ስርዓት፣ የዘር ሃረግ ቆጠራ መንገድ፣ አዝማሪ ካልሆኑ ወገኖች ጋር ዝምድና ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን

ለማወቅ፣ በአጠቃላይ በፊት የነበረውና አሁንም ያለው የዝምድና ሁኔታ፣ ወደፊትስ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎች ከሶስት ሴትና ከአምስት ወንዶች በጠቅላላው ከስምንት ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 3.1.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ይህ ዘዴ አገልግሎት ላይ የዋለው በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ያልተገኙ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ተጠኝው ቡድን በአጠቃላይ የእኔ ሲል የተስማማባቸውንና ዋጋ የሰጣቸውን ጉዳዮች ለመገንዘብ፣ እና በጥናቱ ውስጥ ሚዛናዊ መረጃ ለማግኘት ተብሎ ነው፡፡ ለዚህ ሲባል በቡድኑ ውስጥ የታቀፉት ሰዎች አስቀድመው በቃለመጠይቅም ሆነ በምልከታ መረጃ ያልሰጡ እንዲሁም በቃለመጠይቅና በምልከታ መረጃ የሰጡ ናቸው፡፡ በቃለመጠይቅ ያልተካተቱት መረጃ ሰጪዎች ስለተጠኝው ማህበረሰብ በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ያልተገኙ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እንዲሁም ቡድኑ በአጠቃላይ የእኔ ሲል የተስማማባቸውንና ዋጋ የሰጣቸውን ጉዳዮች ለመገንዘብ፣ የቡድኑን ዕውቀት ለመመርመር ሲባል እንዲወያዩ የተደረገ ናቸው፡፡ ቀድመው በቃለመጠይቅ መረጃ የሰጡት ደግሞ አስቀድመው የተገኙ መረጃዎችን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል የተመረጡ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዘዴው ሃሳቦች ለውይይት የሚቀርቡበት በመሆኑ፣ ድንግርግሮች ጠርተውበታል፣ ስህተቶች ታርመውበታል፣ የጎደሉ መረጃዎች ተሟልተውበታል፡፡ በተለይ በውይይቱ ጊዜ ሰዎች እርስ በእርስ ስህተትን የሚተራረሙ በመሆኑ የመረጃዎች እውነትነት አስተማማኝ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በዚህ ዘዴ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ብቻቸውን ሆነው የሰጡትን መረጃ ሌሎች ሰዎች ባሉበት መድገም ሳይፈልጉ፣ እንዲሁም ቀድመው ከሰጡት መረጃ ፍፁም ተቃራኒ የሆነ መረጃ ሲሰጡ የተስተዋሉባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ አይነት ሁኔታዎችን፣ በንቃት በመከታተልና ምክንያታቸውን በመፈለግ ሚዛናዊ መረጃ ለማግኘት ተሞክሯል፡፡ በቡድን ውይይቱ የሚገኙ መረጃዎችን ሚዛናዊ ለማድረግ ሲባል ፆታን፣ ዕድሜንና ስራን መስፈርቶች ያደረጉ ቡድኖች ተደራጅተው መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እያንዳንዱ መንደር ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከድጀ፣ ወንድ አዝማሪዎችን፤ ቀለባስ፣ ሴት አዝማሪዎችን፤ ማርዬ፣ አዛውንት አዝማሪዎችን፣ ደረቅ ወይራ አዝማሪና አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎችን፤ ኢላዳ፣ ወጣት አዝማሪዎችን የያዙ በአጠቃላይ እያንዳንዳቸው ሰባት አባላትን ያላቸው አምስት ቡድኖች ተደራጅተዋል፡፡

በእያንዳንዱ መንደር የተደረገው የፆታ፣ የዕድሜና የስራ ድልድል በየመንደሮቹ ውስጥ ያለውን የመረጃ ሰጪዎች አኗኗርና አዝማሪነት በመንደሮቹ ውስጥ ያለበትን ሁኔታ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከድጆ ሌላ ሰው ሳይቀላቀል አዝማሪዎች ብቻ የሚኖሩበት በመሆኑ፣ ቀለባስ፣ አሁንም በአዝማሪነት ስራ ላይ የሚገኙ ሴቶች የሚኖሩበት በመሆኑ፣ማርዬ ‹‹ጦርነትንና/ ግብር ማብላትን›› ከመሰሉ ቀደምት አውዶች ጀምሮ አሁንም ድረስ በስራ ላይ የሚገኙ አዛውንት አዝማሪዎች የሚኖሩበት ስለሆነ፣ ደረቅ ወይራ፣ አዝማሪዎችና አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች በአንድነት የሚኖሩበት ከመሆናቸው ባሻገር አንዱ ቡድን ከሌላው ጋር በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች የሚገናኙ ስለሆነ፣ ኢላዳ፣ ከሌሎች መንደሮች በተለዬ ሁኔታ ወጣት አዝማሪዎች በዘፈን ስራ ተሰማርተው የሚገኙበት ስለሆነ ድልድሉ ተካሂዷል፡፡ መረጃዎች እንዳሳዩት አንዱ መንደር የተመረጠበት መስፈርት ሌላውን መንደር አይገልፀውም፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎችና የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ

የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎች በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የተመረጡ ናቸው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ከዋናው ጥናት አስቀድሞ ባደረግሁት የአሰሳ ጥናት በወሰድሁት ግንዛቤ በባህርያቸው ወሎን ሊወክሉ የሚችሉ ቦታዎችን መምረጥ እንዳለብኝ በመረዳቴ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አካባቢውን እንደሚወክሉ ያመንኩባቸውን ለጋምቦ፣ ደሴ ዙሪያ፣ አምባሰልና መቄት የተባሉ አራት ወረዳዎችን መርጫለሁ፡፡

አራቱ ወኪል ወረዳዎች እያንዳንዳቸው የመረጥሁባቸው ምክንያቶች አሉ፡፡ ለጋምቦ ወረዳ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ አዝማሪዎች የሚኖሩበት በመሆኑና ወሎ ተብሎ የሚጠራውን ማህበረሰብ ከመግለፅ አንፃር ይህ አንድ ገፅታ በመሆኑ[16]፤ ደሴ ዙሪያ ወሎ ተብሎ ለሚጠራው አካባቢ ዋና ከተማ ከሆነው ከደሴ ከተማ ዙሪያ የሚገኝ ስለሆነ የባህሉን ተከታታይነትና ለውጥ ለማየት ያስችል ይሆናል ብዬ ስለገመትሁ፤ አምባሰል ወረዳ በአሰሳ ጥናቱ ባገኘሁት መረጃ መሰረት በዕድሜ የገፉና በተለያዩ አውዶች ተሳትፎ ያላቸው አዝማሪዎች የሚኖሩበት በመሆኑ እና መቄት ወረዳ ከሌሎች ወረዳዎች በተለየ አዝማሪዎች ብቻ የሚኖሩበት መንደር ያገኘሁበት በመሆኑ ነው፡፡

---

[16] ወሎ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታይ ማህበረሰብ በጥብቅ ማህበራዊ ግንኙነት ተሳስሮ የሚኖርበት አካባቢ ነው፡፡ ዝርዝሩ በአካባቢ ገለፃ ምዕራፍ ውስጥ ይገኛል፡፡

እያንዳንዱ ወረዳ በርካታ ቀበሌዎች ቢኖሩትም በዚህ ጥናት ከለጋምቦ ወረዳ፣ ኢላዳ ቀበሌን፣ ከደሴ ዙሪያ ከድጀና ደረቅ ወይራን፣ ከአምባሰል ማርዬን፣ ከመቄት ቀለባስን መርጫለሁ። ለዚህም ምክንያቱ በየወረዳዎቹ የአዝማሪ መንደሮች የሚገኙት በተጠቀሱት መንደሮች ውስጥ ብቻ በመሆኑ ነው። ደሴ ዙሪያ ወረዳ ውስጥ ሁለት ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት የሙያውን ለውጥ ለመመርመር አመቺ ይሆናል በሚል ምክንያት ነው።

የመረጃ አቀባዮች ናሙና፣ በቡድኑ ውስጥ የማህበረሰቡን ባህልና አጠቃላይ ሁኔታዎች ያውቃሉ ተብለው የተጠቆሙ ሰዎችን በመምረጥ አካሂጃለሁ። ከዚህም በተጨማሪ የፆታና የእድሜ ልዩነት የሚያመጡትን የመረጃ ልዩነት ለማግኘት ስል ከሁለቱም ፆታዎች በተለያየ የእድሜ ክልል ያሉ መረጃ አቀባዮችን በአላማ ተኮር የአመራረጥ ዘዴ መልምያለሁ።

በአጠቃላይ ከስልሳ ስምንት ሰዎች መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን የመረጃ አቀባዮችን ቁጥር የወሰነው የመረጃ ድግግሞሽ መታየቱ ነው። ከአጠቃላይ መረጃ አቀባዮች ውስጥ ሃያ ዘጠኙ ቁልፍ፣ ሰላሳ ዘጠኙ ደግሞ አጋዥ መረጃ አቀባዮች ናቸው። ቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች ለጥናት የተመረጡትን የወሎ አዝማሪዎችን የሚያውቁ፣ አባል በመሆን ወይም አብሮ በመኖር ስለቡድኑ ባህልና አባላት ጥልቅ እውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው። በእድሜ የገፉ ሰዎች፣ በእድሜ ባይገፉም እንኳን የማህበረሰቡ አባላት ስለኛ ያውቃሉ፣ መናገር ይችላሉ ብለው የመሰከሩላቸው ሰዎችም እንዲሁ በጣም ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች ሆነዋል። ቁጥራቸውን የወሰነው በየአካባቢው ጉዳዩን በጥልቀት ያውቃሉ ተብሎ የተሰጠው ምስክርነት ነው። ከእነዚህ ሰዎች ጋር ጥልቅና ተደጋጋሚ ቃለመጠይቅ ስለተደረገ ስለሚጠናው ቡድን ሰፊና ጥልቅ ዕውቀት ተገኝቷል፤ ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮች ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች የተገኙ መረጃዎችን አንዳንድ ክፍተቶችን ለመሙላትና ለማጠናከር መረጃዎችን የሰጡ ናቸው።

ከመረጃ አቀባዮች ውስጥ በፆታ ረገድ አስራ ሰባቱ ሴቶች፣ ሃምሳ አንዱ ደግሞ ወንዶች ናቸው። የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ሊያንስ የቻለው አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በሙያው ላይ በብዛት የሚገኙ ወንዶች ስለሆኑ ነው። ከዕድሜ አንፃር ሃያ አንዱ ከስልሳ በላይ፣ በድጋሚ ሃያ አንዱ በአርባና በስልሳ መካከል እና ሃያ ስድስቱ በሃያና አርባ መካከል የሚገኙ ናቸው። በእነዚህ የእድሜ ክልሎች ከሁለቱም ፆታዎች የሚገኙ መረጃ ሰጪዎች ተካትተዋል። ከሚተዳደሩበት ሙያ አንፃር አዝማሪዎች፣ ገበሬዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች የመንግስት ሰራተኞችና የግል ስራ የሚሰሩ ናቸው።

## 3.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

ምሁራን፣ መረጃን መተንተን ማለት ከመስክ የተሰበሰበው ጥሬ መረጃ በንድፈሃሳቦችና ቀድሞ በተገኙ ውጤቶች እየተገናዘበ ትርጉም እንዲያገኝ ማድረግ ወይም ጥናቱ ውጤት ላይ እንዲደርስ ማድረግ ማለት ነው ሲሉ ይገልፃሉ Maykut and Morehouse (1994, 110)። በዚህ ጥናትም ጥሬ መረጃዎችን ከላይ በቀረበው መንገድ ከመደብሁ በኋላ ከቤተመፃህፍትና ከመረጃ መረብ ከተገኙ ንድፈሃሳብና ፅንሰሃሳቦች ጋር እያገናዘብሁ ተንትኜ ጥናቱ ውጤት ላይ እንዲደርስ ጥረት አድርጌያለሁ።

በጥናቱ ስለወሎ አዝማሪዎች የዘፈንና የኑሮ ልምድ ተከታታይነትና ለውጥ የሚገልፁ መረጃዎችን ለመተንተን የመረጥሁት የትንተና ስልት ገላጭ የምርምር ስልት ሲሆን፣ ጥናቱ ትኩረት ያደረገበትን የአዝማሪዎችን ባህላዊ የሙዚቃ ልምድ ተከታታይነት ለመመርመር ክዋኔያዊ (Performing theory) እና ለውጡን ለመገንዘብ ደግሞ ማርክሳዊ (Marxist theory) ንድፈሃሳቦች የመረጃ መተንተኛ ንድፈሃሳቦችና እነዚህን ንድፈሃሳቦችንና ጥሬ መረጃዎችን መነሻ አድርጌ የፈጠርሁትና "የአስከሳቢ ቡድኖች ጊዜ መራሽ ፍላጎት እና የከሳቢ ቡድን አላባ መርተከተል አካሄድ ውጤት" ብዬ የሰየምሁት ሞዴል የመረጃ መተንተኛ ሆነው አገልግለዋል።

### 3.3.1. ክዋኔያዊ የመረጃ ንድፈ ሃሳብ (Performing theory)

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ፅንሰ ሃሳብ ነው። ምንነቱን አስመልክቶ የዘርፉ ባለሙያዎች የተለያዩ ሀሳቦችን የሰጡ ሲሆን ለምሳሌ Bauman (1975, 95) ክዋኔ የተግባቦት ወይም ያነጋገር ስልት ነው ይላሉ። ከዋኙ ስነቃሉን በሚያቀርብበት ባህል ልምዳዊ ህግ መሰረት የሚጠበቅበትን ጥበብ እያሟላ፣ ታዳሚው ደግሞ ከስነቃሉ የሚጠበቀውን ትውፊታዊ ውበት እያገኘ እርስ በእርስ የሚፈጥሩት ተግባቦት ነው። እንዲሁም ክዋኔ ታዳሚው የከዋኙን ባህላዊ ክህሎት ገምግሞ የሚመዝንበት እና ልምድ የሚቀያየሩበት፣ ለክወናው መፍዘዝም ሆነ መድመቅ የታዳሚው ሚና ወሳኝ የሆነበት፣ ከቃላዊው ባሻገር የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገፅታ መለዋወጥ፣ የቅላፄ መቀያየርን የመሳሰሉ ቃል አልባ ተግባቦቶች የሚገልፁት ድርጊታዊ የተግባቦት ዘዴ ነው ይላሉ።

Kapchan (1995, 479) በበኩላቸው ‹‹ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህሪ፣ የንግግር ዘዴ፣ በአካል የሚከወን፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈፀም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ ነው፡፡ በሌላ በኩል ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰሃሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው፡፡ ይኸውም የፎክሎር ጥበባዊ ድርጊት ከዋኝ፣ ቦታ፣ ተመልካች እና የክዋኔውን ሁኔታ የሚይዝ ነው›› ይላሉ፡፡ የሁለቱ ባለሙያዎች ትርጉሞች በአጠቃላይ ሲታዩ ክዋኔ በከዋኝና ታዳሚ መካከል ያለ ግንኙነትና የፎክሎሩ ባህላዊና አውዳዊ መልክ መገለጫ መሆኑን የሚበይኑ ሲሆን Ben-Amos (1993, 209)ም (Bascom 1954: 334)ን ጠቅሰው ከዚሁ ያልራቀ ብያኔያቸውን በሚከተለው መልክ አስፍረዋል፡፡

> any functional analysis required an adequate description of "the social context of folklore," including the time and place for the telling of specific forms; the identity of the narrators and the composition of the audience, as well as the relationship of the narrator to the text; the use of dramatic and rhetorical devices in performance; audience participation; folk classification of traditional genres and the people's attitudes toward them.

> ማንኛውም ተግባራዊ የፎክሎር ትንታኔ የማህበራዊ አውድን በቂ ገለፃ ይፈልጋል፡፡ ማህበራዊ አውድ ደግሞ ፎክሎሩ የሚነገርበት ጊዜና ቦታ፣ የተራኪውን ማንነት፣ የታዳሚዎችን ስብስብ (አይነት)፣ ተራኪው ከፎክሎሩ ጋር ያለው ግንኙነት፣ በክዋኔው ውስጥ ያሉ ድራማዊና ገለፃዊ ቅንጣቶች፣ የታዳሚዎች ተሣትፎ የፎክሎሩ ማህበራዊ ምደባና ማህበረሰቡ ለምደባው ያለውን አመለካከት ይመለከታል (ትርጉም የእኔ)፡፡

Ben-Amos በዚህ ብያኔያቸው ክዋኔያዊ ንድፈሃሳብ አንድ ፎክሎር ምን እንደሆነ፣ መቼ፣ የት፣ በማን፣ እንዴት እንደሚከወንና ከዋኞችን ምን የጋራ ጉዳይ እንዳሰባሰባቸው፣ በመካከላቸው ያለው ጥበባዊ ተግባቦት ምን እንደሆነ የሚመረምር የፎክሎር ማጥኛ መሆኑን ይተነትናሉ፡፡ አንድ የፎክሎር ባለሙያም በክዋኔያዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ መረጃውን ሊተነትን ሲነሳ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ትኩረት አድርጎ መሆን እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡ Finnegan (1992, 88)ም የክዋኔን ምንነት

አስመልክቶ ክዋኔ ‹‹የተግባቦት ክንውን ነው›› ካሉ በኋላ በክዋኔ ትንተና ወቅት ፎክሎሩ ምንድን ነው? የሚቀርብበት መንገድ ምንድን ነው? የቀረበበት ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ምንድን ነው? ከዋኞች እነማን ናቸው? ምን አይነት ዝግጅት አድርገዋል? ምን አይነት ባህርይ ያሳያሉ? ፎክሎሩን እንዴት እያቀረቡት ነው? ታዳሚው ምን ምላሽ እየሰጠ ነው? በከዋኞች እንዲሁም በከዋኞችና በታዳሚው መካከል ያለው ተግባቦት ምን ይመስላል? ፎክሎሩ የሚቀርብባቸው ቃላዊና ቃል አልባ ተግባቦቶች ምንድን ናቸው? ፎክሎሩ ከዕለት ዕለት ህይወት አንፃር እንዴት ቀረበ? የተለየ ሁኔታ አለ ወይስ ተፈጥሯዊ ባህርይው ቀርቧል? የሚሉት ነጥቦች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ Bauman (1976, 295)ም እንዲሁ የማንኛውም ማህበረሰብ ባህላዊ ክዋኔዎች ማህበራዊ ስምምነት የተደረገበት ቅርፅና የመክፈቻና የመዝጊያ ደንቦች አሏቸው ይላሉ፡፡ (Hymes, 1975) ደግሞ በፎክሎር እሳቤ ውስጥ እያንዳንዱ ክዋኔ የሚከተለው ቅደም ተከተል አለ፡፡ ስለዚህ ክዋኔን በመተንተን ጊዜ ለእነዚህ ቅርፆች ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ሲሉ የFinneganን ሃሳብ ይደግፋሉ፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን በቀረቡት ሃሳቦች ክዋኔ ምንድን ነው? የሚለውን ሃሳብ ለማሳየት ሞክሬያለሁ፡፡ ከቀረቡት ሃሳቦች ውስጥ ክዋኔ አውድ፣ ከዋኝና ታዳሚ የሚባሉ መሰረታዊ ሃሳቦችን የያዘ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ቀጥሎ የመሰረታዊ ሃሳቦች ምንነት ቀርቧል፡፡

**አውድ፡-** አንድ ፎክሎር ሲከወን የሚከወንበት ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን ሃሳብ የሚገልፅ ፅንሰሃሳብ ነው፡፡ (Finnegan1992, 88) ‹‹አውድ፣ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ከክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ክዋኔ ሲመረመር አውድን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ይህም በሰዎች መካከል ያለ ግንኙነትና ባህላዊ ስምምነቶች ለመረዳት ያስችላል››፡፡ በማለት የአውድን ምንነትና አስፈላጊነት ሲገልፁ Dundes (1986, 4) ደግሞ አውድ ‹‹የአንድን ክዋኔ አካላዊ መቼት፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና፣ የድርጊት ቅደም ተከተል፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋትና በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለውን ተግባቦት አጠቃሎ ይይዛል›› ይላሉ፡፡ ይህ በመሆኑ የአውድ ጥናት ሲደረግ ለእነዚህ ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡

**ከዋኝ፡-** ከዋኝ የአንድ ባህል ባለቤት የሆነና ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት ፎክሎሩን የሚከውን ሰው ነው፡፡ ከዋኞች የሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችና የሚከውኗቸው ክዋኔዎች ማንነታቸውን በመግለፅ ረገድ የራሳቸው የሆነ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ (Bronner 1988,

53)። ስለሆነም ከዋኞች ለክዋኔው ያላቸው ስሜትና ተሳትፎ እስከምን ድረስ እንደሆነ የሚጠበቅባቸውን ሚና በተገቢው መልኩ እየተወጡ እንደሆነና ክዋኔውን እየከወኑ ወይም ከመከወናቸው በፊት የፈጠራ ችሎታቸው ምን ያህል እንደነበር መጤን አለበት። ሌላው የክዋኔ መሰረታዊ ሃሳብ ታዳሚ ነው።

***ታዳሚ፡-*** ታዳሚዎች ፎክሎሩ በሚከወንበት አካባቢ ተገኝተው ለከዋኙ ድርጊት አንዳች ምላሽ የሚሰጡ ሰዎች ናቸው። ታዳሚዎች በፎክሎሩ ክዋኔ ውስጥ አንዳች ሚና ይኖራቸዋል። አንድ ክዋኔ በሚከወን ጊዜ ክዋኔው ለሚካሄድበት መቼት የተሳታፊዎቹ ባህሪያትና ምላሽ ትኩረት መስጠት ያሻል። ይህ ደግሞ አዲስ አቅጣጫ ያስጨብጣል። በመቼቱ በተሳታፊው መካከል ያለው ግንኙነት እንደ ተሳታፊዎቹ ዕድሜ፣ ፆታና ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል። ተሳታፊዎች በራሳቸው መንገድ ክዋኔውን ሲረዱት አሉታዊ ወይም አወንታዊ መልስ ይሰጣሉ። ስለዚህ የፎክሎር ተመራማሪ ታዳሚዎቹ በክዋኔው ተሳታፊ መሆናቸውን፣ ተሳትፎአቸው እንዴት እንደነበርና ወደክዋኔው ከመግባታቸው በፊት ከነበራቸው ሁኔታ እንዴት ሊነጠሉና በክዋኔው ሊመሰጡ እንደቻሉ መመርመር አለበት Finnegan (1992, 90-92)። በአጠቃላይ አንድ የፎክሎር አጥኚ ክዋኔን ሲመረምር የክዋኔውን አገላለፅና ጥበባዊ ተግባቦት፣ መቼ ተከወነ?፣ እንዴት ተከወነ? የክዋኔውን ፈፃሚ ማን ነውና ከማን ጋር ከወነው? የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳትና የሚያስገኘውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር የሚያስፈልግ መሆኑን መገንዘብ እንዳለበት የመስኩ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ።

በዚህ ጥናትም የወሎ አዝማሪዎች ተከታታይ የኑሮና የዘፈን ልምድ ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱ መረጃዎችን ለመተንተን ስል ፎክሎሩ በሚገኝበትና በሚከወንበት ቦታ በአካል በመገኘት በምልከታ መረጃዎች ሰብስቤያለሁ። ከዚያም ከላይ የተጠቀሱትን የክዋኔ ንድፈሃሳብ መሰረታዊ ነጥቦች መሰረት አድርጌ የተገኙ መረጃዎችን ተንትኛለሁ። ከዚህ ውጭ ግን የወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ለውጥና የለውጥ ምክንያት ለማስረዳት ከክዋኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ውጪ ሌሎች ፅንሰሃሳቦች ያስፈልጋሉ። ለዚህ ደግሞ ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ (Marxist theory) የቀረበ ሆኖ በመገኘቱ መርጬዋለሁ። ምንነቱ፣ አገልግሎትና በምን መልኩ እንዳገለገለ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 3.3.2. ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ (Marxist theory)

ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ ዋና ማጠንጠኛ ሃሳቡ‹‹mode of production›› /ምርት የሆነ ንድፈሃሳብ መሆኑን Barnard (2004, 88), Ilitskaya (1978, 330) ይገልፃሉ፡፡ ንድፈ ሃሳቡ እንደሚገልፀው ከቀላሉ የአደንና ፍራፍሬ መሰብሰብ ውስብስብ እስከሆነው የኢንዱስትሪ ስራ ድረስ ሰው ከተፈጥሮና ከሰው ጋር የሚያደርገው ግንኙነት፣ ለመኖር የሚያደርገው ጥረት ወይም የምርት ሂደት ነው፡፡ በማንኛውም የምርት ሂደት ሰው ከተፈጥሮ ጋር እንዲሁም ሰው ከሰው ጋር መስተጋብር በመፍጠር ምርትን ያመርታል፡፡ ምርት ከማህበረሰብ ኢኮኖሚና የኢኮኖሚ አቅም ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡

ማርክሳዊ፣ ‹‹ኢኮኖሚ›› ለሁሉም ነገር የጀርባ አጥንት ነው የሚል ንድፈሃሳብ ነው፡፡ Tyson (2006, 54) ይህንን ሲገልፁ ‹‹ለአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርፅ መሰረቱ ኢኮኖሚ ነው የኢኮኖሚው መልክና ቅርፅ የሌሎችን ነገሮች ቅርፅ ይወስነዋል፡፡ የኢኮኖሚው አቅም ትምህርትን፣ ፍልስፍናን፣ ሃይማኖትን፣ መንግስትን፣ ጥበብን፣ ሣይንስን፣ ቴክኖሎጅን የመገናኛ ዘዴዎችን ወዘተ ጨምሮ ለሁሉም ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግባራት አንቀሳቃሽ ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ባህል ለመረዳት የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሁሉም ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግባር ጀርባ የኢኮኖሚ አቅም አለ›› ይላሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ የሚደግፉት Johnson (2005, 126) ለምሳሌ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ወንዶች የበላይ እንዲሆኑና ሴቶች ደግሞ የወንዶች ድጋፍ ሰጪ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምክንያት የማህበረሰቡ የምጣኔ ሃብት ሁኔታ በወንዶች እጅ በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡

በማርክሳዊ ንድፈሃሳብ አራማጆች አባባል የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚጠቅሰው ቁሳዊ ሁኔታን (ምርት የሚባለውን) ሲሆን፣ በቁሳዊ ሁኔታዎች የፈለቀው/የተፈጠረው የማህበራዊና ፖለቲካዊ አመለካከት ደግሞ ታሪካዊ መልክ አለው፡፡ ስለዚህ እንደ ንድፈሃሳቡ አንድን ቁስ ወይም ምርትን ለመረዳት በመጀመሪያ ምርቱ/ቁሱ የተፈጠረበትን ሁኔታ መረዳት ይገባል፡፡ ሁሉም የሰው ልጅ ሁነቶችና ምርቶች የራሳቸው ታሪካዊ ምክንያት አላቸውና፡፡

Tyson (2006) እንደሚገልፁት ደግሞ ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ ታሪክንና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ለመረዳት የሚያስችል ጠቃሚ ንድፈሃሳብ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ የሚደግፉት Ilitskaya (1978, 330) ‹‹ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ በታሪክ ሂደት ውስጥ ዛሬንና ትናንትን ለመግለፅ ብቻ ሳይሆን ነገን ለማየትም ያገለግላል›› ብለዋል፡፡

ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ የተለያዩ የጥበብ ስራዎች (ስነፅሁፍ፣ ፊልም፣ ቲያትር ወዘተ) ሊፈተሹበት የሚችል ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ተጨባጭ የአቅም ግንኙነት በስራዎች ውስጥ እንዴት ተንፀባርቋል የሚለውም ይዳሰስበታል Tyson (2006, 54)፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ Ilitskaya (1978, 469) ሲገልፁ ‹‹ጥበብ የማህበረሰብ ህይወት፣ የማህበራዊ ቅጥና፣ የመደብ ግንኙነት ለውጥ ተፅዕኖ ያርፍበታልና በሆነ ወቅት የተሰራ (የተዘጋጀ) ጥበብ ከዚያ ወቅት የማህበረሰብ ዕድገት ጋር የተያያዘ ነው›› ይላሉ፡፡

Finnegan (1992, 32) ‹‹ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ ከማህበረሰብ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው›› ይላሉ፡፡ ወደፎክሎር ሲመጣም ፎክሎር ከማህበረሰብ ጥበብ ውጤቶች አንዱ እንደመሆኑ በማርክሳዊ ንድፈሀሳብ ሊመረመር ይችላል፡፡ ይህንን ሃሳብ Ilitskaya (1978, 330) ‹‹ፎክሎር ምናባዊ፣ ውበታዊ ትርጓሜና የህይወት መሰረታዊ አመለካከትን ይሰጣል›› ሲሉ ፎክሎር ተፈጥሮ ውበታዊ በሆነ መንገድ የሚገለፅበት ጥበብ መሆኑን በመግለፅ ይደግፋታል፡፡ ከዚህ አንፃር ማርክሳዊ ንድፈሃሳብ በፎክሎር አማካኝነት የተገለፀን ማህበራዊ ህይወት፣ የማህበረሰብ ግንኙነት፣ የማህበረሰብን ለውጥና የለውጥ ምክንያት ለመገንዘብ ጥሩ ንድፈሃሳብ በመሆኑ የወሎ አዝማሪዎችን የዘፈንና ኑሮ ልምድ ለውጥ፣ የለውጥ ምክንያት፣ ቡድኑ ከሌላው ሰው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ በጥበቡ የተንፀባረቁ የማህበረሰብ ህይወት ለመመርመር በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ Finnegan (1992, 32) ‹‹በማርክሳዊ ንድፈሃሳብ የመረጃ ትንተናው አንድ የፎክሎር አይነት/ዣነር እንዴት ተደረሰ? በማህበረሰቡ ውስጥ እንዴት ይዟዟራል? በምን ሁኔታ? በማን አማካይነት? በምን አይነት ፍላጎት? የሚሉ ሃሳቦች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል›› ሲሉ በሚመክሩት መሰረት ለእነዚህ ሃሳቦች ትኩረት ተሰጥቶ የወሎ አዝማሪዎችን የኑሮና የዘፈን ልምድ ተከታታይነትና ለውጥ እንደሚያሳዩ የታመነባቸው ጥሬ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

### 3.3.3. "የአስከሳቢ ቡድኖች ጊዜ መራሽ ፍላጎት እና የከሳቢ ቡድን አላባመር ተከተል አካሄድ ውጤት [በስራ ቡድኖች የተከታታይነትና ለውጥ ልምድ" ጥናት]

"የአስከሳቢ ቡድኖች ጊዜ መራሽ ፍላጎት እና የከሳቢ ቡድን አላባ መር ተከተል አካሄድ ውጤት" ሞዴል ክዋኔያዊና ማርክሳዊ ንድፈሃሳቦች የአንድን በስራ ምክንያት የተመሰረቱ ፎክሎሮችን ለመተንተን በቅንጅት ሲሰራባቸው የያዙትን ባህርይና ከመስክ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎችን መልክ በመመርመር የተፈጠረ ሞዴል ነው፡፡ የሞዴሉን ጠቅላላ ሃሳብ ለማስገንዘብ ስያሜው በውስጡ የያዛቸው ቃላትና የቃላቱ ድምር ትርጉም ቀጥለው ተብራርተዋል፡፡

የወሎ አዝማሪዎች ራሳቸውን አዝማሪ፣ ተጫዋች፣ እንዛታ፣ ቅሬ፣ **ከሳቢ** ብለው ይጠራሉ፡፡ አዝማሪ የሚለው ቃል እነሱም ሌላው የሚጠቀሙበት ስም ነው፡፡ በትልልቅ አዝማሪዎች ዘንድ እንደክብር መጠሪያ ይታያል፡፡ ምክንያቱም አዝማሪ ማለት ዘመረ፣ አመሰገነ ከሚለው ቃል የመጣ በመሆኑ እኛ አመስጋኞች ነን፡፡ አምላክን እናመሰግናለን፡፡ ጥሩ የሰራን ሰው እናመሰግናለን፡፡ ይህ ከአምላክ የተሰጠን ፀጋ ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡

**እንዛታ፣ቅሬ፡-** አዝማሪዎች ሚስጥራቸውን ከሌላው ማህበረሰብ ለመደበቅ በሚገለገሉበት የሚስጥር ቋንቋቸው አዝማሪ የሚለውን ቃል ተክተው ራሳቸውን የሚጠሩባቸው ስሞች ናቸው፡፡

ተጫዋች የሚለው ቃል፣ ዘፈንን የሚጫወት ከሚለው ሃሳብ የተወሰደ ነው፡፡ እነሱም ሌላውም ሰው ይጠቀምበታል ፡፡

**ከሳቢ**፡- በእንዛትኛ (በአዝማሪ የሚስጥር ቋንቋ) ዘፋኝ ማለት ነው፡፡ አዝማሪዎች ዘፈንን ገንዘብ ሊቀበሉበት ሲዘፍኑት ራሳቸውን ከሳቢ ብለው ይጠራሉ፡፡

**አስከሳቢ**፡- ገንዘብ ከፍሎ የሚያስዘፍን ወይም ሲዘፈንለት ገንዘብ የሚከፍል ማለት ነው፡፡ ከሳቢና አስከሳቢ፣ ዘፋኝና አስዘፋኝ ማለት ነው፡፡ የእነዚህ ቃላት ፍቺ ምንጩ ከአዝማሪዎች የተገኘ ማብራሪያ ነው፡፡ በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት ማርዬ ላይ በ12/05/2005 ዓ.ም አዛውንት አዝማሪዎችን ሰብስቤ ባካሄድሁት የተተኳሪ ቡድን ውይይት "በአዝማሪና አዝማሪ ባልሆነው "ሰው" መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት ምንድን

ነው?” የሚል ጥያቄ አቀረብሁ፡፡ ብርሃን ትኩ የተባሉ አንድ ተወያይ “እህ ጌታ እኮ ሁሉንም አንድ አድርጎ አልሰራም፡፡ እኛ ከሳቢ ነን፣ እነሱ ደግሞ” አስከሳቢ ናቸው፡፡ የሚል መልስ ሰጡ፡፡ ከላይ ለከሳቢና አስከሳቢ ምንነት የተሰጡት ብያኔዎች በዚሁ ውይይት ላይ የተገኙ ናቸው፡፡ ይህንን ከሳቢና አስከሳቢ የሚል አካባቢያዊ የቃል ጥመራ ቅጥ ከነትርጉሙ በመያዝ ሠራተኛና አሰሪ፣ አገልግሎት ሰጪና አገልግሎት ተቀባይ ለሚሉ ሃሳቦች መተኪያ መጠቀም ቢቻል፣ አንድም የተተኳሪ ቡድኑን ቃላት መጠቀም የጥናቱን ወሰን ያጎላል በሌላ መንገድ ለቡድኑ ዕውቀት እውቅና መስጠት ነው የሚለውን በማመን ለቲወሪው መግለጫነት ተጠቅሜያለሁ፡፡

**ጊዜ መራሽ ፍላጎት፡-** አገልግሎት ተቀባዩ፣ ለሚቀርብለት አገልግሎት/ ምርት፣ ባለው ፍላጎት ላይ፣ ጊዜ ያለውን አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተፅዕኖ ይገልፃል (የሰዎች ፍላጎት ጊዜን ተከትሎ ባለበት እንዲሄድ ወይም እንዲለወጥ ታሪካዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና፣ ባህላዊ ሁነቶች የሚጫወቱት ሚና አለ)፡፡ በጥናቱ ውስጥ በየዘመኑ አስከሳቢዎች ለአዝማሪ ዘፈን ያላቸው ፍላጎት ምን ሆነ? የሚለውን ይመለከታል፡፡ በጥናቱ ለቃሉ አገልግሎት ላይ መዋል ምክንያቱ በመስክ ላይ የተገኘው ‹‹ ዛሬ ጊዜው ገደለው፤ጊዜው ሲገድለው ጊዜ እኛም ወቅቱን መስለን መኖር ፈለግን›› ከሚለው የመረጃ ሰጪ ንግግር ነው (ማስረሻ ፈንታው፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም.፣ማርዬ)፡፡


**አላባ፡-** እንደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት (1993፣ 303) የስራ ውጤት ወይም ፍሬ ማለት ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ቃሉ አዝማሪዎች ከዘፈን የሚያገኙትን ገንዘብ ይመለከታል፡፡

**መርተከተል ፡-** የ‹‹መሪና ተከታይ›› አካሄድን ለመግለፅ የገባ ቃል ነው፡፡ አንዱ ሲመራ ሌላው ይከተላል፡፡ ተከታዩ የሚያገኘው ውጤት የመሪውን ፍላጐት መሰረት ያደረገነው፡፡ በዚህ ጥናት የአስከሳቢ ቡድኖች ፍላጎት ሲጨምር የከሳቢ ቡድኖች አላባ ይጨምራል፡፡ ምክንያቱም አስከሳቢ ቡድኖች ለከሳቢ ቡድኖች አገልግሎት ፍላጎት ካደረባቸው ገንዘብ ይከፍላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከሳቢ ቡድኖች ስራቸውን እንዲቀጥሉ ይረዳቸዋል፡፡ ያ ካልሆነ ግን የከሳቢ ቡድኖች አላባ ይቀንሳል፡፡

**ውጤት፡-** አንድን ምክንያት ወይም ድርጊት ተከትሎ የመጣ፣ የታየ ሁኔታ ወይም ነገር (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት፣ 419)፡፡ በዚህ

ሁኔታ ለምሳሌ በእንደዚህ አይነት የስራ ቡድኖችን ልምድ ለውጥና ተከታታይነትን በሚያይ ጥናት የአስከሳቢ ቡድኖችን ፍላጎት በመጨመሩ ወይም በመቀነሱ የቡድኑ ልማድ ላይ ያለው ተከታታይነት ወይስ ለውጥ ሚዛን ደፋ? የለውጡ መጠን በቡድኑ ህልውና ላይ ያለው ተፅዕኖ እስከምን ይደርሳል? የሚለው ሊታይበት ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት ውጤት የሚለውን ቃል የአስከሳቢዎችን ፍላጎት ተከትሎ በአዝማሪዎች ገቢ ላይ የተፈጠረው ሁኔታ በዘፈንና የኑሮ ልምዳቸው ላይ ምን መልክ ፈጠረ? የሚለውን ያየሁበት ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ከማርክሳዊና ክዋኔያዊ ንድፈሃሳቦች ጋር አንድ ላይ በማድረግ ሞዴሉን ተጠቅሜ በየዘመኑ የታየው የአዝማሪ ዘፈን ተጠቃሚ ማህበረሰብ ፍላጎት ምንድን ነው? ለፍላጎቱ መነሻ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ይህ ፍላጎትስ አዝማሪዎች ኑሯቸውን በመሰረቱበት የዘፈን ስራ ገቢ በዘፈን ልምድና በአኗኗር ልምዳቸው ተከታታይነት ላይ ምን ተፅዕኖ አመጣ? የሚለውን መርምሬያለሁ፡፡ ሞዴሉን በሚከተለው ሁኔታ በስዕል ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

ሃሳቡን ለመወከል የመረጥሁት ስዕል መሰንቆ ነው፡፡ መሰንቆ አዝማሪዎች ዘፈናቸውን የሚያጅቡበት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ምንነቱን በዝርዝር ለመረዳት በትንታኔ ምዕራፍ ‹‹የዘፈን ለመዳና ተስተላልፎ›› የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)፡፡




በስዕሉ እንደሚታየው መሰንቆ የተለያዩ ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍሎቹ በሞዴሉ ውስጥ የቆሙ ፅንሰሃሳቦች ወክለው እንዲቆሙ ተደርገዋል፡፡ ውክልናቸው የሚከተለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ምሰሶ፡- | ባህልን |
| የምሰሶው ጭራ፡- | ከሳቢ ቡድኑንና የቡድኑን ፎክሎር |
| መቃኛ፡- | ጊዜን |
| ደጋን፡- | አስከሳቢ ቡድኖችን |
| የደጋኑ እንጨት፡- | የአስከሳቢ ቡድኖችን ፍላጎት |
| የደጋኑ ጭራ፡- | የአስከሳቢ ቡድኖችን ገንዘብ |

የምሰሶውና የደጋኑ ጭራ ሲጋጩ የሚፈጠረው ድምፅ፡- የከሳቢ ቡድኑ አላባ (ከሳቢ ቡድኑ ሰርቶ የሚያገኘው ገንዘብ

የመሰንቆ ጨዋታ ቅኝቶች፡- ተከታታይነትና ለውጥን ይወክላሉ፡፡

እያንዳንዱ የመሰንቆ ክፍልና ተግባር በሞዴሉ ውስጥ ላሉ ፅንሰሃሳቦች ወኪል አድርጎ ለመምረጥ በመሰንቆው አካልና በተወካዩ ሃሳብ መካከል ያለውን ተመሳስሎ መሰረት አድርጌያለሁ፡፡ በዚህ መሰረት ምሰሶ ከመሰንቆ አካላት ውስጥ የሁሉም ተሸካሚ በመሆኑ በሞዴሉ ውስጥ ከሚገኙ ሃሳቦች ትልቁ የሆነውን ባህል የሚል ፅንሰሃሳብ ወክሏል፡፡

ከምሰሶው እስከ ድምፅ ሳጥኑ የተዘረጋው ጭራ የመሰንቆ ቀዳሚ ተግባር ለሆነው የድምፅ ማውጣት ስራ ያገለግላል፡፡ ይህ አካልም በሞዴሉ ውስጥ ዋና ጉዳይ ለሆኑት ለከሳቢ ቡድንና ፎክሎሩ ወካይ ሆኖ ተመርጧል፡፡ መቃኛ በመሰንቆ ጨዋታ ውስጥ ቅኝት ለመቀየር፣ ዜማ ለማስተካከል ያገለግላል፡፡ በሞዴሉ ጊዜን ይወክላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ለአስከሳቢ ቡድኑ ፍላጎት መጨመርና መቀነስ ጊዜ ዋና ምክንያት ነው፡፡

ደጋን በመሰንቆ ውስጥ ራሱን የቻለ አካል ነው፡፡ ካለበት ተነስቶ ከምሰሶው እስከ ድምፅ ሳጥኑ በተዘረጋው ጭራ ላይ ሲያርፍ ድምፅ ይፈጠራል፡፡ በሞዴሉ ውስጥ አስከሳቢ ቡድኑ እንደደጋኑ ሁሉ ራሱን የቻለ አካል ነው፡፡ ነገር ግን በፎክሎሩ ምክንያት ከከሳቢ ቡድኑ ጋር ይገናኛል፡፡ ደጋን ከጠማማ (ጎባጣ) እንጨትና ከጭራ የተሰራ ነው፡፡ ጭራው ከእንጨቱ ጫፍና ጫፍ ተወጥሮ ይታሰራል፡፡ ደጋኑ የተሰራበት እንጨት የአስከሳቢ ቡድኖችን ፍላጎት፣ ጭራው ደግሞ አስከሳቢ ቡድኑ ለከሳቢ ቡድኑ የሚከፍለውን ገንዘብ እንዲወክሉ ተደርጓል፡፡ የአስከሳቢውን ፍላጎት በእንጨቱ የተወከለው የቡድኑ ፍላጎት ገንዘብ ለመስጠትና ላለመስጠት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ከጭራው ይልቅ የእንጨቱ ጠንካራነት የፍላጎትን ሚና ይወክላል በማለት ነው፡፡ ጭራው ገንዘብን የወከለው ደጋኑ

ከምሰሶው ላይ ካለው ጭራ ጋር ሲጋጭ ድምፅ እንደሚፈጠረው ሁሉ አስከሳቢው ቡድን ገንዘብ መክፈሉ ፎክሎሩ ቀጣይ እንዲሆን ስለሚያደርግ ነው፡፡

የምሰሶው ጭራና የደጋኑ ጭራ ሲጋጩ የሚፈጠረው ድምፅ ከሳቢው ቡድን ሠርቶ የሚያገኘውን አላባ (ውጤት) ወክሎ ቁሟል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ቡድኑ ህልውናው የሚቀጥለው ገንዘብ ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ ሁሉ መሰንቆውም አገልግሎት መስጠት የሚቀጥለው ድምፅ የሚያወጣ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሞዴሉ የሚያገለግልበት ተከታታይነትና ለውጥ የሚለው ሃሳብ ደግሞ ለመሰንቆ ጨዋታ በሚያገለግሉ ቅኝቶች ተወክሏል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በተከታታይነትና ለውጥ ውስጥ ወጥና የሚለዋወጥ ነገር እንዳለ ሁሉ በቅኝቶችም ቀጥ ብሎ የሚፈስስ ሙዚቃ (ድምፅ) መኖሩ ተከታታይነትን፣ የሚወጣው ድምፅ ፍሰት በተለያዩ የጊዜ ምጣኔዎች የሚቀያየርና የሚለወጥ መሆኑ ተለዋጭነትን ይወክላሉ ብዬ በማሰቤ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሞዴሉ እርስበርስ ተደጋጋፊ በሆኑ ሁለት ቡድኖች መካከል ያለን ተግባቦት ለማሳየት የቆመ ሲሆን ለዚህ እንዲረዳ መሰንቆ ተመርጧል፡፡ መሰንቆ እንደቡድኖቹ ሁለት በአንድ የተግባር ስራ የተሰማሩ ነገር ግን ለየራሳቸው አካል ባላቸው፣ ህልውናቸው አንዱ ከሌላው ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ላይ የሆነ ክፍሎች ያሉት ቁስ በመሆኑ ሞዴሉን ለመግለፅ ጥሩ አቅም ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ቀጥሎ ጥናቱ የተደረገበት አካባቢና ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታ ቀርቧል፡፡

# 4. የወሎ አካባቢ መልክዓምድራዊ ገፅታ፣ የማህበረሰብ መልክና የዘፈን ባህል አጠቃላይ ቅኝት

በዚህ ክፍል ለጥናት የተመረጠው የወሎ አካባቢና የአካባቢው ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታ ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የሙዚቃ ቡድኖች የሚጠኑበት እንደመሆኑ እነዚህ ቡድኖች እንደአንድ ቡድን የሚኖሩበት ትልቁ ማህበረሰብ ስለሙዚቃ ያለውን አመለካከትና ሙዚቃ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ቦታ ለማሳየት የወሎ ማህበረሰብ የዘፈን ባህል በሚል ርዕስ የአካባቢው የሙዚቃ ባህል አጠቃላይ ቅኝት ተደርጓል፡፡

## 4.1. አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

ወሎ በሸዋና በሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛት መካከል የሚገኝ በሰሜን፣ ትግራይ፤ በምዕራብ ጎጃምና ጎንደር፣ በደቡብ ሸዋ፤ በምስራቅ፣ አሰብና ጅቡቲ የሚያዋስኑት ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ የረጅም ዘመን ታሪክ ያለው ቦታ ሲሆን ወሎ የሚለውን መጠሪያውን ከማግኘቱ በፊት ቤተአምሐራ ተብሎ ይጠራ እንደነበር መዛግብት ይገልፃሉ፡፡

ወሎ በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ Hussein (2001, 15) ከደቡብ ወደ መሃል ሃገር ከተንቀሳቀሱ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት አንዱ የነገድ አባት ስም ነው፡፡ ወሎ የኦሮሞ ነገድ መሪ የከረዩ ልጅ፤ የበረይቱማ የልጅ ልጅ ነው፡፡ በዚህ ነገድ መሪ ስር የሚተዳደረው የኦሮሞ ማህበረሰብ ቁጥር ብዛት ከፍተኛ ሆኖ ነባሩን ማህበረሰብ በተጫነው ጊዜ ቀድሞ ቤተአምሐራ ይባል የነበረው ቦታ ስሙ ተቀይሮ በጎሳ መሪው ስም ወሎ ተብሏል ሲሉ ገብረ ኪዳን (1981፣ 31) ተክለፃድቅን ጠቅሰው ፅፈዋል፡፡

በተፈጥሮ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ወሎ የተለያዩ የመሬት ገፅታዎች አሉት፡፡ ማለቂያ የሌለው የተራሮች ሰንሰለት፤ ኮረብታዎች ሸንተረሮች፣ ሜዳዎች፤ ሸለቆዎች ወንዞችና ሐይቆች የወሎ ምድር ጉልህ መልክዓ ምድራዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡ በግምት 8.2 ሚሊዮን ሔክታር ያህሉ የወሎ መሬት በጣም ኮረብታማ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ከኮረብታዎቹ ባሻገር በጣም ትልልቅ ተራሮችና ጥልቀት ያላቸው ሸለቆዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ተራሮችና ሸለቆዎች ከሰሜን ሸዋ ተነስተው ወሎን መሃል ለመሃል በምዕራብና በምስራቅ ሰንጥቀው እስከ ደቡብ ትግራይ ድረስ ይዘልቃሉ፡፡

የምዕራቡ ክፍል ተራራማና ከፍተኛ ስፍራዎች የበዙበት ነው። ተራራማ ክፍሉ በተለይም ደሴ ዙሪያን፣ የወረኢሉ፣ የወረሂመኑ፣ የቦረናና የዋድላ ደላንታ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው። ከእነዚህ ተራሮችና ከፍተኛ ቦታዎች ወንዞች ይነሳሉ። ወንዞች ከበሽሎ ወንዝ ጋር የሚቀላቀሉ ናቸው። የበሽሎ ወንዝ ደግሞ ከአባይ ገባር ወንዞች ትልቁና አንዱ ሲሆን የተጠቀሱትን አውራጃዎች ከሞላ ጎደል የሚያጠቃልል ነው። የምስራቁ ክፍል የአምባሰልን ከፍተኛ ስፍራዎችንና ቃሉን በከፊል የሚያጠቃልል ነው። በዚህም አካባቢ የአዋሽ ገባር ወንዞች ይፈስሳሉ። በምስራቁም ሆነ በምዕራቡ የወሎ ምድር የተለያዩ ሰብሎች ይመረታሉ። በደጋማውና በወይና ደጋው አካባቢ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ባቄላና ምስር ሲመረቱ፣ በምስራቁ ቆላማው ክፍል ደግሞ ጤፍ፣ማሽላ፣በቆሎና ጥጥ ይመረታል ጌታቸው(1984፣ 21)።

## 4.2. የማህበረሰቡ አጠቃላይ ገፅታ

ገብረ ኪዳን (1981፣ 1) እንዳሉት በወሎ ክፍለሃገር ውስጥ የሚኖረው ህዝብ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የአፋር፣ የትግሬ፣ የአርጎባ፣ የአገው ብሔረሰብ አባላትን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ በተለያየ ስም የሚጠሩ የብሔረሰብ አባላት፣ በጋብቻና በአምቻ የተሳሰሩ ሲሆን አብዛኛው የሚያንፀባርቁት የአንድነት ስሜትን ነው። በመሆኑም ማንኛውም የአካባቢው ነዋሪ ማንነቱን ሲጠየቅ የብሔረሰቡን ስም ከመጥራት ይልቅ ወሎዬ ነኝ የሚለው ገለፃው ይሰማል። ለምሳሌ በዋግ አውራጃ የሚኖረው ህዝብ ቢያንስ የሶስት ቋንቋዎች ተናጋሪ ነው። ቋንቋዎቹ፣ አማርኛ፣ ትግርኛና አገውኛ ናቸው። በደሃና ወረዳ በሚገኙት ወረዳዎች አብዛኛዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆኑ በተላጌ ወረዳ የሚገኙት ብቻ ‹‹በአጋውኛ›› ይጠቀማሉ። በሰቆጣ ወረዳ ደግሞ የጀረባና የዝቋላ ወረዳ ሕዝቦች አጋውኛ ብቻ ሲጠቀሙ በቀሩት ወረዳዎች ደግሞ አማርኛና አጋውኛ ይናገራሉ። በወፍላ ወረዳ ያሉት ነዋሪዎች ደግሞ አማርኛ ትግርኛና አገውኛ ይናገራሉ። እነዚህ ሁኔታዎች ወሎ በተባለው ምድር በአንዲት ትንሽ ቀዬ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሰዎች በአንድ ላይ የሚኖሩ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የአንዱ ወረዳ ህዝብ ከሌላው ወረዳ ህዝብ በብዙ ኪሎ ሜትር የሚርቅ ቢሆን እንኳን በዝምድና፣ በአበልጅነት፣ በጋብቻና በመሳሰሉት መንገዶች የተሳሰሩና የሚተዋወቁ ናቸው።

በወሎ የሁለት አበይት ሃይማኖት ተከታይ ሕዝብ ይኖራል። አብዛኛው የወሎ ሕዝብ የእስልምና እምነት ተከታይ ሲሆን አብዛኛዎች እስላሞች የዘር ሃረጋቸው አማራ

እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይሁንና የሁለቱ እምነት ተከታዮች እስከ ጋብቻ በሚደርስ ግንኙነት የተሳሰሩ በመሆናቸው እንደሌሎች አካባቢዎች መጠሪያ ስምን መሰረት በማድረግ ወይም በሌሎች ሳዕላይ ምልክቶች አንድን ወሎዬ የየትኛው እምነት ተከታይ እንደሆነ በቀላሉ ለመገመት አይቻልም፡፡ ከዚህ ሲያልፍ ደግሞ በክርስትና ሃይማኖት እጅግ ጥንታዊና ታሪካዊ ቤተክርስቲያን በወሎ የመገኘቱን ያህል የቁርኣን ጥንታዊ መፅሃፍትና ታሪካዊ መስጊዶችም የመገኘታቸው ሁኔታ ሁለቱ ሃይማኖቶች በአካባቢው ያላቸውን ጥንታዊነት የሚያሳይ ነው ጌታቸው (1984፣ 25)፡፡

### 4.2.1. የአስተዳደር መልክ

ወሎ እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በተለያዩ የግዛት ክልሎች ተከፋፍላ በመሳፍንት፣ በመኳንንትና በባላባት ስትገዛ የኖረች ክፍለ ሃገር ነበረች፡፡ በወሎ በጣም የታወቁት የግዛት ክልሎች ወረሒመኑ፣ የጁ፣ ላስታና ደንከል ወይም አፋር ናቸው፡፡ እንደሚባለው እነዚህ ዋና ዋና የግዛት ክፍሎች ሲሆኑ በውስጣቸው ብዙ ንዑሳን የግዛት ቀበሌዎች በማቀፍ ወይም በማጠቃለል የተመሰረቱ ነበሩ፡፡ የእነዚህ ታላላቅ ግዛቶች ገዥዎች ታናናሽ ባላባት ገዥዎችንና መኳንንቶችን በበላይነት እየተቆጣጠሩ ሲገዙ ነበር፡፡ ከታላላቅ ግዛቶች ለምሳሌ ወረሒመኑን የተመለከትን እንደሆን ከአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በታወቁና ከአንድ ዘር በመነጩ ይማሞች (መሐመዶች) ብዙ ንዑሳን ቀበሌዎችን በቁጥጥር ስር በማድረግ ሰፊ የግዛት ቀበሌዎችን ለመቆጣጠር ችለው እንደነበር ይነገራል፡፡ በሌሎች ቦታዎች እንደዚሁ የተለያዩ አውራጃዎችን ተቆጣጥረው የሚያስተዳድሩ አካላት ነበሩ፡፡ እነሱም በዋግ አውራጃ፣ ዋግ ሹም፣ በየጁ ወረሴኮች፣ በአምባሰል ዣንጥራሮች፤ በቃሉ ወረ ቃሎዎች ናቸው ገብረ ኪዳን (1981፣ 12) ፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ባላባቶችና የገዥ ቤተሰቦች ዋና ዋናዎች ሲሆኑ በየንዑስ ቀበሌው ደግሞ በዋናዎቹ ስር የሚተዳደሩ ንዑሳን ባላባቶች ነበሩ፡፡ እነዚህ ባላባቶች ብዙ ጊዜ በመተባበር ግዛታቸውን የሚያስፋፉ ሲሆን አልፎ አልፎ በመካከላቸው በሚፈጠሩ አለመግባባቶች የተነሳ ሃይል ያለው ባላባት ደካማውን ይደመስሰዋል፡፡ አልፎ አልፎም ንዑሳን ባላባቶች ሃይል ሲያጠናክሩ ከዋና ባላባቶች ጋር ጦርነት የሚገጥሙባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ በዚህ መልኩ አፄ ቴወድሮስ እስከመጡበት ጊዜ ድረስ እንደሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ሁሉ ዘመነ መሳፍንት የወሎም ገፅታው ሆኖ

ቆይቷል። ይሁንና ተክለፃድቅ (1981ዓ.ም፣ 133) እንደሚያስረዱት አፄ ቴወድሮስም ቢሆኑ ከፍተኛ ተቋቁሞና ጦርነት ገጠማቸው እንጅ እንዳሰቡት ዘመነመሳፍንትን ከወሎ ማጥፋት አልቻሉም።

ከአፄ ቴወድሮስ በኋላ በወሎ ውስጥ የነበሩትን ግዛቶች ለመቆጣጠር የቻሉ ዳግማዊ አፄ ሚንሊክ ነበሩ። አፄ ሚኒሊክ ከ1861 እስከ1870 ባለው ጊዜ በወሎ የነበሩትን የተበታተኑ ግዛቶች በማዋሃድና በሸዋ ስር ለማድረግ ዋና ዓላማ ይዘው ነበር። ለዚህም ሲሉ ብዙ ዘመቻዎችን አድርገዋል። በዘመቻዎችም በማሸነፍ ወሎን በሸዋ ስር ማድረግ ችለዋል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በዘመቻዎች እሳቸው ያሸነፉ ቢሆኑ ለግዛት እንዲመች በሚል ስልጣኑን መልሰው ለወሎ ባላባቶች ለአባ ዋጠውና ለይማሙ መሐመድ አሊ ሰጥተዋል። ይህ ጊዜም ለወሎ የማዕከላዊ አመራር መሰረት የተጣለበት ጊዜ ነው።

በአፄ ዮሃንስ ዘመነመንግስት ግን ወሎ ከአዲስ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶች ጋር ተፋጥጣ ነበር። በተለይ አፄ ዮሃንስ በ1870 መጀመሪያ የኢትዮጵያን ሃይማኖት አንድ አደርጋለሁ ብለው መነሳታቸው ከእስልምና እምነት ተከታዮች ጋር በርካታ ጦርነቶችን እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል።

ወሎ ከአስተዳደር አንፃር ስትታይ በተለይም ሳይነሱ የማይታለፉት ንጉስ ሚካኤል ናቸው። ንጉስ ሚካኤል የወረሒመኑ ባላባትና የልጅ እያሱ ወላጅ አባት ናቸው። የመጀመሪያ ስማቸው መሐመድ አሊ የነበረ ሲሆን በአፄ ዮሃንስ አማካኝነት ክርስትናን ተቀብለው ስማቸው ንጉስ ሚካኤል ሆኖ ወሎን ሲያስተዳድሩ ኖረዋል። ንጉስ ሚካኤል በመጀመሪያ ወሎ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ሰፍረው ሃገር ሲያስተዳድሩ የኖሩ ቢሆንም በመጨረሻ ቤተ መንግስታቸውን ወደደሴ አምጥተዋል። ዛሬ በደሴ ከሚገኙ ቅርሶች ውስጥ አንዱ የሆነውን አይጠየፍ አዳራሽን ለግብር[17] ማብያ ይሆናቸው ዘንድ ያሰሩት እሳቸው ናቸው።

ንጉስ ሚካኤል ለሌሎች ሰዎች ግብር የሚያበሉ ቢሆንም ቀደም ሲል በመጣው ልማድ መሰረት ከህዝቡ ግብር ይሰበስቡ ነበር። አምራቹ ማህበረሰብ ከመሬቱ ከሚያገኘው

[17] ማህተመ ስላሴ (1942፣ 34) ዝክረ ነገር በተባለ መፅሃፋቸው ስለግብር ሲያስረዱ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ህዝቡን የሚያስተዳድረው ባገር ግዛት፣ በቀለብ በጉርሻ ብቻ ሳይሆን ሌላ ትልቅ መሳቢያና ማቅረቢያ የጦር ሰራዊት ማደርጃ ግብር የሚባል ማስተዳደሪያ አለው። ግብር የተባለበት ምክንያት ንጉሱ ዘወትር መኳንንቱንና የቤት ልጁን ከልፍኝ ወይም ከልፍኝ አዳራሽ በታላላቅም በዓል ቀን ሠራዊቱን ካዳራሽ ያለማቋረጥና ያለማስታጎል በተለመደው ሰዓት የሚያበላ ነውና ስለዚህ ንጉሰ ነገስቱ ምንም አስገባሪ ቢሆን ራሱም በበኩሉ ለህዝቡ የሚያስበውና የሚደክመው ከግብር ይቆጠራልና በዚሁ ልማድ ግብር ተብሎ ሲጠራ ይኖራል።

ጥቅም ግብር መክፈል ከጥንት ዘመን ጀምሮ የተመሰረተ ወይም የተለመደ ነገር ነበር፡፡ በየዘመናቱ የነበሩት ገዥዎችም ሕዝቡ በተለይም ገበሬው ልዩ ልዩ የግብር አይነት እንዲከፍል ያደርጉት ነበር፡፡ እያንዳንዱ ግብርን የየራሱ ስም ነበረው፡፡ ለምሳሌ በወሎ ከነበሩት የግብር አይነቶች ዋና ዋናዎች የበግ ግብር፣ የሽማኔ ግብር፣ የብር ሰሪ ግብር፣ የቅቤና የማር፣ በጨው በሸማና በእህል የሚከፈል ግብር፣ የቆሎ ግብር (እህል በተወቃ ቁጥር የሚከፈል)፣ የቤተክህነት ልዩ ልዩ ግብር፣ የንጉስ መጠበቂያ ግብር ጥቂቶች ናቸው፡፡ ይህ ስርዓት ትንሽ ለውጥ ቢኖረውም እስከሃይለስላሴ ዘመንም የቀጠለ እንደነበረ መረጃዎች ይገልፃሉ ገብረኪዳን (1981ዓ.ም፣19)፡፡

በአፄ ሃይለስላሴ ዘመን ወሎ የጁ፣ አምባሰል፣ ቃሉ፣ ቦረና፣ ወረኢሉ፣ ዋድላ ደላንታ፣ አውሳ፣ ላስታ፣ ራያና ቆቦ፣ ዋግ፣ ወረሂመኑ፣ ደሴ ዙሪያ የሚባሉ አስራሁለት አውራጃዎች ነበሩት፡፡ በደርግ ዘመን ደግሞ ክፍለ ሃገሩን ሰሜንና ደቡብ ብሎ በሁለት በመክፈል አስተዳደሩ ሌላ መልክ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ በዋናነት የሚነሳው ለውጥ የአስተዳደሩ ለሁለት መከፈል ብቻ ሳይሆን የመሬት ላራሹ አዋጅ ያመጣው ለውጥ ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም በ1967 ዓ.ም በመላ ሃገሪቱ የወጣው የመሬት ላራሹ አዋጅ ወሎንም የነካ በመሆኑ ጭሰኞችና ገባሮች የራሳቸው መሬት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ የባላባትና ጭሰኛ ግንኙነትም ቀርቷል፡፡ ይህ አይነቱ አስተዳደር እስካሁን ድረስ ቀጥሏል፡፡

የሰሜን ወሎ ዞን የመረጃ መፅሃፍ (2003፣ 1) እንደሚገልፀው ዛሬ ወሎ የሚተዳደረው ሰሜንና ደቡብ ወሎ በሚል አከፋፈል ነው፡፡ ሰሜን ወሎ ሶስት የከተማ አስተዳዳርና አስር የገጠር ወረዳዎች በ278 የገጠር፣ በ20 የከተማ ቀበሌዎች በድምሩ 298 ቀበሌዎች የያዘ ነው፡፡ የከተማ አስተዳደሮች ወልዲያ፣ ላሊበላ፣ ቆቦ፣ መርሳ ሲባሉ ወረዳዎች ደግሞ ዳውንት፣ ቡግና፣ ላስታ፣ ሐብሩ፣ ራያ ቆቦ፣ ጉባላፍቶ፣ ግዳን፣ መቄት፣ ዋድላ ይባላሉ፡፡ የዞኑ ቆዳ ስፋት 11,335.69 ስ.ኬ.ሜ ሲሆን በደቡብ፣ ከደቡብ ወሎ፤ በሰሜን፣ ከትግራይና ከዋግኽምራ፤ በምዕራብ፣ ከደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ከአፋር ይዋሰናል፡፡

የዞኑ ከፍታ በሜትር ከ1500 በታች፣ 10.556%፣ ከ1500 እስከ2500 57.493%፣ ከ2500 እስከ 3500፣ 30.443% ከ 3500 ሜትር በላይ ነው፡፡ ዓመታዊ የሙቀት መጠኑ ከ10 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በታች 3.66%፣10 እስከ15 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ 26.01%፣15-20 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ 47.69% ያህል ነው፡፡ ዓመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን ከ600 ሚሊ ሜትር እስከ1300 ሚሊ ሜትር ይደርሳል፡፡ ዞኑ የመኸርና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ነው፡፡ ዞኑ በዝናብ አጠርነት የሚታወቅ ቢሆንም ተከዜ፣ ዥጣ፣

ጎሊና፣ ጎቱ፣ አላውሃ፣ ጨረቲ፣ መሬ የተባሉ ትላልቅ ወንዞች ይገኙበታል። እንዲያውም ዞኑ የኢትዮጵያ ዋነኛና ታላላቅ የአባይ፣ የተከዜን አዋሽ ተፋሰሶች አካል ነው።

Ege and Yegremew (2000) የማዕከላዊ ስታስቲክስን ጠቅሰው እንደገለፁት የሰሜን ወሎ ዞን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ሲታይ ድህነት ጎልቶ የሚንፀባረቅበት ነው። ለምሳሌ አንድ አባወራ በአማካይ 0.70 ሄክታር ብቻ የእርሻ መሬት ያለው ሲሆን ከአጠቃላዩ የዞኑ ማህበረሰብ 43% የሚሆነው የእርሻ በሬ የሌለው ነው። 19% የሚሆነው ህዝብ ብቻ ሁለትና ከዚያ በላይ በሬዎች አሉት። ይህም በአካባቢው ያለው ህዝብ ቁጥር በጣም ከፍተኛ መሆኑን አለዚያ ደግሞ የሃብት ስርጭቱ እኩል አለመሆኑን የሚያሳይ ነው። ወደ ደቡብ ወሎ ሲመጣ ደግሞ በሁለት የከተማ አስተዳደር ዞን በአስራ ስድስት የገጠር ወረዳዎች ተዋቅሮ፣ በስሩ 462 የገጠርና 61 የከተማ በአጠቃላይ 523 ቀበሌዎች የያዘ ዞን ነው። ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች ቃሉ፣ ተንታ፣ ደብረሲና፣ አምባሰል፣ ወረባቦ፣ አልብኮ፣ መቅደላ፣ ኩታበር፣ ደሴ ዙሪያ፣ ተሁለደሬ፣ ጃማ፣ ወረኢሉ፣ ለጋምቦ፣ ከለላ፣ ወግዲ፣ ሣይንት፣ ደሴ ከተማ፣ ኮምቦልቻ ከተማ ናቸው። እንደደቡብ ወሎ ዞን አትላስ ገለፃ ዞኑ በአጠቃላይ1,760,759 ካሬ ኪ.ሜ ስፋት አለው። ዞኑ በሰሜን ምዕራብ ከደቡብ ጎንደር ዞን፣ በደቡብ ከሰሜን ሸዋ ዞን፣ በምስራቅ ከኦሮምያ ዞን፣ በሰሜን ምስራቅ ከአፋር ክልላዊ መንግስት፣ በሰሜን ከሰሜን ወሎ ዞን ጋር ይዋሰናል። ዞኑ ሞለል ያለ ቅርፅ ያለው በመሆኑ በተለይ ከመሃል ወደምዕራብ አቅጣጫ ወደሚገኙት ወረዳዎች ለመጓዝ ያለው የርቀት ልዩነት ከፍተኛ ነው። እንደ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የ1998 ስሌታዊ የህዝብ ግመታ ደቡብ ወሎ ዞን 2,743,065 የህዝብ ብዛት ሲኖረው ይህ ቁጥር የክልሉን 14.76% የሚሆነውን ሕዝብ እንደሚይዝ ይገመታል። ከዚህ የህዝብ ቁጥር ውስጥ 11.90% በከተማው የሚኖር ነው። የዞኑ አማካይ የቤተሰብ መጠኑ 5 ነው። ከዞኑ አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር 1,351,620 ወይም 49.27% ወንድ ሲሆን 1,391,445 ወይም 50.73% ደግሞ ሴት ነው። ዕድሜን በተመለከተ ከ15 ዓመት በታች 41.40%፣ ከ15 እስከ59 መካከል 51.14%፣ ከ60 ዓመት በላይ 7.46% እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ደቡብ ወሎ በአባይ ከሰሜን ወደደቡብ እና በአዋሽ ከምዕራብና ከሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በሚፈሱ ወንዞችና ገባር ወንዞቻቸው የፍሰት ስርዓት ውስጥ የሚገኝ ዞን ነው። ወደደቡብና ምዕራብ አቅጣጫ ከሚፈሱት ዋና ዋና ወንዞች እንደበሽሎ፣ የሹሜ፣ ደጎሎ፣

ዋራንሶ፣ ሶዬ፣ የሚባሉት ወንዞች የዓባይ ወንዝ ይቀላቀላሉ። ቦርከና እና ጨልቃ ወንዞች ወደምስራቅ በመፍሰስ ከአዋሽ ወንዝ ጋር ይቀላቀላሉ። በዞኑ ውስጥ፣ አርጌቦ እና ሃርዲ፣ ሐይቅ የሚባሉ ሃይቆች ሲገኙ ከእነዚህ ውስጥ ሐይቅ የተባለው ሐይቅ በስፋት ትልቅ ነው።

የዞኑ የሙቀት መጠን በ10.0 ዲ.ሴ የአምባፋሪት ተራራ 4242 ሜ. እና በአማካይ በ27.5 ዲ.ሴ. የሙቀት መጠን ምስራቃዊ ወረባቦ ወረዳ መካከል የሚገኝ ነው። ምስራቃዊ የወረባቦ ወረዳ እና ደቡብ ምዕራባዊ የዓባይና ገባር ወንዞቹ ዝቅተኛው ክፍልን ጨምሮ የከላላ፣ የወግዲ፣ የደብረ ሲና እና የመቅደላ ወረዳዎች ከ22.5 -27.5 ዲ.ሴ. አማካይ ዓመታዊ የሙቀት መጠን የሚመዘገብባቸው አካባቢዎች ናቸው።

የከፍተኛ ተራራዎች ዝቅተኛ ክፍሎች (foot of high mountains) እንደሣይንት፣ ወረኢሉ፣ ጃማ፣ መቅደላ፣ እና ኩታበር በመሳሰሉት ከ15.5 እስከ22.5 ዲ.ሴ. የሚደርስ አማካይ ዓመታዊ የሙቀት መጠን የሚመዘገብባቸው አካባቢዎች ናቸው።

ቀዝቃዛው የለጋምቦ፣ የደሴ ዙሪያና የአምባሰል ወረዳ ከፍተኛ ቦታዎች ከ10.0-15.5 ዲ.ሴ. አማካይ ዓመታዊ የሙቀት መጠን ይመዘገብባቸዋል። ከላይ ከተጠቀሱት ቦታዎች ከፍ ብለው የሚገኙ ውርጫማ (ቀዝቃዛማ) ተራራዎች ማለትም በአቀስታ፣ ጨርጨር፣ ውጫሌ ወዘተ አካባቢዎች ዓመታዊ አማካይ የሙቀት መጠናቸው ከ7.5 እስከ10.0 ዲ.ሴ በታች እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።


የዞኑ የዝናብ ስርጭት ከቦታ ቦታ የተለያየ ነው። ለዚህም የመልክዓምድር ከፍታ ከቦታ ቦታ መለያየትና የዝናብ መጠን አንድ ወጥ ያለመሆን እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው። ከፍተኛው የዞኑ ክፍል የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ሲሆን የተወሰነውና ቀሪው የዞኑ ክፍል ደግሞ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ነው። በሰሜን በኩል ሰሜን ወሎ ዞንን አዋስነው የሚገኙ ወረዳዎች እንደተንታና አምባሰል የመሳሰሉት ወረዳዎች ከ500 እስከ700 ሚ.ሜ. የሚገመት አነስተኛ የሆነ ዝናብ መጠን የሚያገኙ አካባቢዎች ናቸው።

በምስራቃዊ ጫፍ የአፋር ብሔራዊ ክልልን የሚያዋስኑ ወረዳዎች እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ዞንን እያዋሰኑ የሚገኙ አካባቢዎች (እንደወረኢሉ ወረዳ የመሳሰሉት) በዓመት በአማካኝ ከ700 እስከ900 ሚ.ሜ. ዝናብ ያገኛሉ። ደቡብ ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚመዘገብበት ዞን ከመሆኑ ባሻገር በስፋትም ቀላል ያልሆነ ድርሻ

አለው፡፡ ለምሳሌ ምዕራባዊ፣ ደቡባዊ፣ ሰሜናዊውና መካከለኛው የዞኑ አካባቢ መጠኑ ከ 900 እስከ1200 ሚ.ሜ የሆነ ዝናብ ያስመዘግባል፡፡

የዞኑ የርጥበት ወቅት በአብዛኛው ከግንቦት መግቢያ ይጀምርና ቀስ በቀስ በመጠን እየጨመረ ሀምሌና ነሃሴ ወሮች ላይ ከፍተኛውን የዝናብ መጠን የሚያስመዘግብበት ወቅት ሲሆን፣ ከዚያም ቀስ በቀስ መጠኑን በመቀነስ እስከመስከረም መጨረሻ የሚዘልቅ ነው፡፡

በአጠቃላይ እንደቀድሞው አጠራር ወሎ ክፍለሃገር በየዘመኑ የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ያስተናገደ ነው፡፡ በተለይም ከአስተዳደር አንፃር ሲታይ ‹‹የክፍለ ሃገሩን›› መልክ በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው እስከአፄ ሃይለ ስላሴ ድረስ የነበረው የዘውድ አገዛዝ ዘመን ሲሆን ሁለተኛው ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም.ድረስ ያለው የደርግ ዘመን፣ ሶስተኛው ደግሞ ከ1984 እስከአሁን ድረስ ያለው የኢህአዴግ ዘመን ነው፡፡ በእነዚህ ሶስት ዘመናት ጉልህ ያስተዳደር ልዩነት ያለ ሲሆን የዘውድ ዘመኑ አካባቢው በብዙ ባላባቶች ተከፍሎ የሚተዳደርበት ማህበረሰቡም ባለባትና ጭሰኛ ተብሎ የተመደበበት በደርግ ዘመን ማዕከላዊ አስተዳደር የነበረበት፣ የባላባትና ጭሰኛ ምደባ ተወግዶ ሁሉም ሰው ባለመሬት የሆነበት የኢህአዴግ ዘመን ደግሞ አካባቢው ሰሜንና ደቡብ ተብሎ የተከፈለበትና ሁሉም ሰው በደርግ ያገኘው የመሬት ባለቤትነት እንዳለ የቀጠለበት ነው፡፡




ስዕል 2. የአማራ ክልል ካርታ

ከላይ በቀረበው ካርታ ወሎ በአማራ ክልል ውስጥ የሚገኝ አካባቢ መሆኑንና ሰሜን ወሎና ደቡብ ወሎ የተባሉ አስተዳደር ዞኖች እንዳሉት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡




ስዕል 3. ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች

**ምንጭ፡- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጂ.አይ. ኤስ. ትምህርት ክፍል**

ከላይ በቀረቡት የሰሜንና የደቡብ ወሎ ካርታዎች ውስጥ የየዞኖቹን ወረዳዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በቀረበው ካርታ ውስጥ በሁለቱም ዞኖች ደማቅ አረንጓዴ ቀለም የተቀቡት ወረዳዎች ጥናቱ የተካሄደባቸው ናቸው፡፡ ቀጥሎ የአካባቢው ማህበረሰብ መተዳደሪያና ልዩ መገለጫዎች ቀርበዋል፡፡

### 4.2.2. መተዳደሪያና ልዩ ባህላዊ መገለጫዎች

የወሎ ማህበረሰብ ከሌላው አካባቢ ህዝብ ጋር የሚጋራቸው አያሌ እሴቶች ቢኖሩትም በተለይ እሱ ብቻ ጎልቶ የሚታይባቸው ባህላዊ መገለጫዎቹ ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች ‹‹ገደብ የለሽ›› ማህበራዊ ግንኙነት፣ ምርቃት፣ ማህበረሰቡ ለሙዚቃና ለግጥም ያለው መስጠት የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

መረጃዎች እንደሚሉት በወሎ በአመዛኙ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሕዝብ ይኖራል፡፡ በአካባቢው የእስልምናም ሆነ የክርስትና እምነት ስር የሰደደ መሰረት ያላቸው እንደሆነ የሚገልፁ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በክርስትናው እምነት በኩል ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደተሰራች የሚነገርላት ተድባበ ማርያምን፣ በአስራአንደኛውና አስራሁለተኛው ክፍለ ዘመን እንደተሰሩ የሚነገርላቸው አስራ አንዱ የላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናትን መጥቀስ ሲቻል በእስልምናው በኩል ደግሞ ጥንታዊውን የደሴ (አረብ ገንዳ) መስጊድ (በወረኢሉ ከሚገኙ መስጊዶች ውስጥ ታላቁ የፈረደ መስጊድን መጥቀስ ይቻላል (የአማራ ክልል ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ 1991፡፡

በወሎ የሚኖሩ የእስልምናና ክርስትና እምነት ተከታዮች የማህበራዊ ግንኙነት ትስስር ጥብቅ ነው፡፡ በሃይማኖት ምክንያት በሚኖሩ በዓላት ድግሶችና ማንኛውም አይነት የመቀራረቢያ ዝግጅቶች እስላም ክርስቲያን ሳይባባሉ ባንድነት ይሳተፋሉ፡፡ ማህበራዊ ቁርኝቱ እስከ ጋብቻ ይደርሳል፡፡

ምርቃት ሌላው የወሎ ህዝብ ባህላዊ መገለጫ ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ለምርቃት ከፍተኛ የሆነ ግምት አለው፡፡ የተመረቀ ሰው ያሰበው ይሆንለታል፤ እድሉ ይሰምርለታል፤ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም የተነሳ በማንኛውም አጋጣሚ ምርቃት መስጠትና መቀበል የተለመደ የእለት ከእለት ክንውን ነው፡፡ ከዚህ ሲያልፍ ደግሞ በምርቃት ሰውን ከችግሩ ማላቀቅ የሚችሉና የምርቃት ተሰጥኦ ያላቸው የተለያዩ ሰዎች መኖራቸውንም ማህበረሰቡ ያምናል፡፡ ጌታቸው (1984፣ 75) ይህንን ሲያስረዱ ‹‹በወሎ በምርቃናቸው፣ በቱፍታቸውና በስማቸው ‹‹አንቱ›› የተሰኙ ያለፈውንና መጪውን ጊዜ እንደጉድ የሚተረትሩ በጭንቅ የተያዘውንና በጣር ላይ የሚገኘውን ሳይቀር የሚፈውሱ ታዋቂ ሼኾችና ቃልቾች በጠቅላላው አዋቂዎች ነበሩ፡፡ አሁንም

አሉ›› ይላሉ። በዚህ መሰረት ማህበረሰቡ ከእነዚህ ሰዎችና ከሌሎችም ትልልቅ ሰዎች ምርቃትን ለማግኘት ቀና የተባሉ ተግባራትን ይከውናል። ምርቃት የሚከናውንባቸውን እንደጫት የመቃም ስርዓት ማዘጋጀት፣ ድግስ መደገስ የመሳሰሉ ተግባራት ያከናውናል።

ማህበረሰቡ ምርቃትን የመፈለጉን ያህል እርግማንን ይፈራል። ምክንያቱም ከምርቃት በተቃራኒ እርግማን የሰውን ብሩህ እድል ይጋርዳል፤ በህይወት ላይም መጥፎ አደጋን ያመጣል ስለሚባል ነው። ስለዚህም ማንኛውም ወሎዬ እርግማንን የሚያመጡ በሰዎች ላይ ክፉ ማድረግ፣ ክህደትና ምቀኝነት የመሳሰሉ ‹‹ክፉ›› ተግባራትን እንዳይፈፅም ይጠነቀቃል።

የወሎ ማህበረሰብ ለሙዚቃና ለግጥም ያለው መሰጠት ሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ባህላዊ መገለጫ ነው። ጌታቸው (1984፣ 43) እንደሚሉት ‹‹የወሎ ሰው ሐዘኑን፣ ደስታውን፣ ብሶቱን ታሪኩን ባህሉ ወዘተ በዜማና በግጥም የመግለፅ ልምድና ባህል አለው››። ሲሉ እንደሚገልፁት ከማንኛውም ተራ ህዝብ አንስቶ ንግግራቸውን በግጥም በመግለፅ ወይም መንዙማን[18] በማዜም እስከመታወቅ የደረሱ እንደነሼህ ሁሴን ጅብሪል፣ የአርሲዋ እመቤት (የጁዬ)፣ የመርሳው አባ ጌትዬ ያሉ በርካታ ሰዎችን ወሎ አፍርታለች።

ከአራቱ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅኝቶች ውስጥ ከአንቺ ሆዬ በቀር ትዝታ (የቀድሞ ስሙ ወሎ ቅኝት ነበር)፣ አምባሰልና ባቲ ወሎ በሚገኙ ቦታዎች ስም የተሰየሙ ናቸው። በርካታ የሙዚቃ ባለሙያዎች የፈለቁባት ምድር ናት። በአካባቢው ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ አዝማሪዎች ይኖራሉ። በአጠቃላይ የሙዚቃ ጥበብ ለወሎ ማህበረሰብ ልዩ መገለጫው ነው ማለት ይቻላል።

በጥቅሉ አብዛኛው የወሎ ማህበረሰብ መተዳደሪያ ግብርና ሲሆን ጥቂቶች ደግሞ በንግድ፣ በመንግስት ስራና በሌሎች የእጅ ስራ ሙያዎች ተሰማርተው የሚኖሩ ናቸው። ይህ ማህረሰብ ከሌላው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጋር የሚጋራቸው አያሌ እሴቶች አሉት። ይሁንና ይህ የጋራው ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ለብቻው ተለይቶ የሚታወቅባቸው እንደእስልምናና እንደክርስትና አማኞች ያለገደብ ተቀላቅሎ መኖር፣ የምርቃት ባህል እና የዘፈን፣ ዜማና ግጥም ተሰጥኦን የመሳሰሉ መገለጫዎች አሉት።

---

[18]መንዙማ የአረብኛ ቃል ሲሆን ውዳሴ ማለት ነው። ጌታቸው (1984፣ 51)

በተለይ የዘፈን ባህሉ ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ትንሽ ሰፋ አድርጎ ማቅረብ ይገባል በሚል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 4.3. የወሎ ማህበረሰብ የዘፈን ባህል አጠቃላይ መልክ

የወሎ ማህበረሰብ ረጅም ዘመን የኖረ የዘፈን ባህል አለው፡፡ ዘፈን ለማህበረሰቡ የህይወቱ አካል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው የህይወት ክንዋኔው ውስጥ አለና፡፡ በሃዘንም ሆነ በደስታ፣ በመንፈሳዊም ሆነ አለማዊ፣ በመወለድም ሆነ በሞት ሂደት ዘፈን ትልቅ ቦታ አለው፡፡ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ህይወት ውስጥ የዘፈን ቦታ ትልቅ ነው፡፡

በአካባቢው የአሰሳ ጥናት በማድረግና የዞኑ የኪነጥበብ ቡድኖች በመድረክ በሚከውኗቸው የኪነጥበብ ስራዎች ታዳሚ በመሆን የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአካባቢው፣ በየተዘዋወረበት ቦታ ሁሉ ከሚያንጎራጉረው ግለሰብ አንስቶ በጠቅላላው ማህበረሰብ ዘንድ ዘፈን ይከወናል፡፡ የግለሰብን ህይወት አስመልክቶ (መወለድ፣ መዳር)፣ በእርሻ ስራ ላይ ፣በአምልኮ ቦታ (ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ ዛር ቤት) ዘፈን አለ፡፡ ሁሉም የህይወት እንቅስቃሴዎች ዘፈንን የሚፈልጉ ይመስላሉ፡፡

ከግንቦት 9 እስከ11/2004 ዓ.ም ድረስ የሰሜን ወሎ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ዘጠነኛውን የሰሜን ወሎ ዞን ባህላዊ የሙዚቃ ፌስቲቫል በወልድያ ከተማ፤ ከሰኔ 15 እስከ17/2005 ዓ.ም ደግሞ የአማራ ክልል የባህል ትርኢቶችና የኪነ ጥበብ ፌስቲቫል በባህር ዳር ከተማ አዘጋጅተው ነበር፡፡ በእነዚህ መድረኮች የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች የየራሳቸውን የዘፈን ባህልና የዘፈኑን የመፈጠሪያ ሰበብ (በአርቲፊሻል አውድ) ይዘው ለውድድር ቀርበው ነበር፡፡ በዚህ አውድ እያንዳንዱ ወረዳ የራሱ የሆነ የአዘፋፈን ስልት በተለይም የውዝዋዜ ስልት ያለው መሆኑን አሳይቷል፡፡ ይህ ሲባል ግን የሁሉም ወረዳዎች ክዋኔ ፍፁም የተለያየ ነው ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም አንድ አይነት እስከመምሰል ድረስ የሚመሳሰል ውዝዋዜ፣ ዜማና ግጥሞች የነበሯቸው ወረዳዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በምልከታ እንደታየውና አቶ ክቡር አባይ (12/9/2004 ዓ.ም.) የተባሉ መረጃ ሰጪ ስለሰሜን ወሎ ወረዳዎች ሙዚቃ እንደገለጡት የየወረዳው የተለየ፣ የተለየ ‹‹አመታት›› (የውዝዋዜ አይነት) አለው፡፡ የጎጥ ባህል አለ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የቆላው አካባቢ ማለትም የቆቦ፣ የጉባላፍቶ፣ የወልድያ አንድ አይነት ውዝዋዜ አላቸው፡፡ ጎንበስ ብሎ በወገብ የሚመታ ነው፡፡ ምታቸውን (Their rhythm)

ፈጠን ያለ ነው፡፡ ወደደጋው ያሉት እነ ዋድላ፣ መቄት ግዳን፣ ዳውንት፣ አንድ አይነት ዓመታት አላቸው ሁለት ሰው ተነስቶ ይዘፍናል ሌላው ተቀምጦ ያጨበጭባል፡፡

በወሎ የሚከወኑ ውዝዋዜዎች በየዋህ እይታ ሲመለከቷቸው አንድ አይነት ይመስላሉ፡፡ ከአንድ ቦታ ቆሞ ከወገብ በላይ ያለ ሰውነትን የሙዚቃውን ምት ተከትሎ እያሽከረከሩ፤ እጅን በተለያየ አቅጣጫ እያወናጨፉ የሚከወን ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንዳሉት መሰረታዊው የውዝዋዜ አይነት አንድ ነው፡፡ ጎንበስ ተብሎ በወገብ የሚመታ (ወገብን ማሽከርከር)፡፡ ይሁንና ይህ አይነቱ ውዝዋዜ በሁሉም ውዝዋዜዎች ላይ የሚታይ ሆኖ ሌሎች ውዝዋዜዎች ደግሞ ሌሎች ጥበቦች እየተጨማመሩባቸው ይከወናሉ፡፡ በዚህ መሰረት በየወረዳው የሚከወኑ ውዝዋዜዎች ብዙና የተለያየ ስም ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ስርጉድ፣ አንድ ትክሻን ወደ ፊት እየወረወሩ የሚመታ፤ ሳውራ፣ በአንገት ብቻ የሚመታ፤ ሶራ/ ሰቆጣ፣ ከወገብ ጀምሮ አንገትን ወደቀኝና ግራ እያሽከረከሩ የሚዘፈን፤ ባውሽ፣ ሁለትን እጅ ከደረት እያጣበቁ መምታት፤ አጀልጅል፣ በጉዞ ላይ የሚመታ፤ ራያ፣ ሁለት እግርን በአንድ ጊዜ እየዘለሉ መምታት፤ ወርና፣ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ለወሎ ማህበረሰብ ሙዚቃ ማህበራዊ ተግባር ነው፡፡ ሰዎች አንድ ላይ ተሰብስበው ይከውኑታል፡፡ ተሰብሳቢው ሰው የየራሱ ድርሻ አለው፡፡ አንዱ በድምፅ ይዘፍናል ሌላው ይወዛወዛል፡፡ ሌላው ደግሞ ያጨበጭባል፣ ዘፈንን ግጥሙን ይቀበላል (ያጅባል)፡፡ በዚህ ሁኔታ አካባቢውንና ማህበረሰቡን የሚገልፁ የሙዚቃ ስራዎች ይከወናሉ፡፡ በሌላው ማህበረሰብ ሳይቀር የወሎነታቸው ከሚታወቁ ዘፈኖች ውስጥ አማሮ፣ መጋሌ ሰመረ፣ ኸረባቲ ባቲ፣ እሪኩም፣ የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ዘፈኖች የአካባቢ ባህል፣ የሴት ልጅ ውበት፣ የወንድ ልጅ ጀግንነት፣ የአምላክ ጠባቂነት ወዘተ የመሳሰሉ ጉዳዮች ይገለፃሉ፡፡ ግጥሞች (Ezra፣ 2009) እንደሚሉት በተለያዩ የሙዚቃ ቅኝቶች ይከወናሉ፡፡ በአካባቢው ትዝታ፣ አምባሰል፣ አንቺ ሆዬና ባቲ ቅኝቶች ተዘውታሪዎች ናቸው (Ezra፣ 2009)፡፡

የወሎ ማህበረሰብ ሙዚቃን ለአለማዊ ማህበራዊ ህይወቱ ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ህይወቱም ይገለገልበታል፡፡ በክርስትና እምነት በኩል በየአብያተክርስቲያናቱ የተለያዩ ጥንታዊና ዘመናዊ መዝሙሮች ይዘመራሉ፡፡ በእስልምና እምነት በኩልም መንዙማ የተሰኘው የዝማሬ አይነት በተከበሩት ሼሆች እንዲሁም በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት ይከወናል፡፡ መንዙማ ነብዩ ሙሐመድንና ነቢያትን

በማወደስ፣ ቅዱስ ተግባራትን በማበረታታት የሚዘመር ነው፡፡ የመዝሙሩ ይዘት መንፈሳዊ ነው (ጌታቸው 1984፣ 43)፡፡

በአካባቢው አራት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሙዚቃን ለማጀብ ያገለግላሉ፡፡ እነሱም ዋሽንት፣ ከበሮ፣ ክራርና መሰንቆ ናቸው፡፡ ዋሽንት ከሸንበቆ የሚሰራ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ሸንበቆ እንደቱቦ ውስጡ ክፍት የሆነ ተክል ነው፡፡ መረጃ አቀባዮች እንዳሉት፣ አለማየሁ (1992)ም እንደገለፁት ለዋሽንት የሚያገለግለው ሸንበቆ በግምት ቁመቱ ከሰላሳ እስከአርባ ሴንቲ ሜትር ይደርስና የመጀመሪያው ቀዳዳ ድምፅ ከሚወጣበት የሸንበቆው ጫፍ በአራት ጣቶች ልዩነት ይበሳል፡፡ ሌሎች ሶስት ቀዳዳዎች ደግሞ በሁለት ጣቶች ልዩነት እየተለኩ ይበሳሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ አራት ቀዳዳዎች ይበሱና ተጫዋቹ እነዚህን በማፈንና በመክፈት የተለያዩ ዜማዎችን ይጫወታል፡፡

ከበሮ ከእንጨትና ከቆዳ የሚሰራ የምት መሳሪያ ነው፡፡ ከላይ ሰፊ ከታች ደግሞ ጠበብ እንዲል ተደርጎ ውስጡ ተቦርቡሮ የተከፈተ ግንድ በሚገባ ከተለሰለሰ በኋላ ጫፍና ጫፉ በከብት ቆዳ ይሸፈናል፡፡ ተጫዋቹ(ቿ) የሙዚቃውን ዜማ ተከትሎ በቆዳ የተሸፈነውን ክፍል በመደብደብ ሙዚቃውን ይጫወታል (ትጫወታለች)፡፡

ክራር፣ በአካባቢው ለዘፈን ማጀቢያነት የሚያገለግል የክር መሳሪያ ነው፡፡ ከእንጨትና ከጅማት ይሰራል፡፡ የ v ቅርፅ እንዲኖረው ተደርጎ የሚሰራ ነው፡፡ የድምፅ ሳጥን አለው፡፡ ከድምፅ ሳጥኑ ተነስተው እንደመከዳ ሆኖ በተሰራው የመሳሪያው ክፍል የሚታሰሩ አምስት ክሮች አሉት፡፡ እነዚህን ክሮች በመነካካትና የተለያዩ ድምፆችን በማውጣት ሙዚቃን መጫወት ይቻላል አለማየሁ (1992 ዓ.ም.)፡፡

ሌላው የሙዚቃ መሳሪያ መሰንቆ ነው፡፡ (ስለምንነቱ የዘፈን ለመዳና ተስተላልፎ በሚለው ክፍል 5.1.2.2. ይመልከቱ)፡፡

እነዚህ አራት የሙዚቃ መሳሪያዎች የወሎ ማህበረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሙዚቃን ሲከውን የሚጠቀምባቸው ናቸው፡፡ ዋሽንትና ክራር በአብዛኛው ወንዶች የሚጫወቷቸው መሳሪያዎች ሲሆኑ ከበሮ ወንድም ሴትም ሊጫወተው ይችላል፡፡ ዋሽንትና ክራር ማንም ፍላጎቱ ያለውና ችሎታውን ያዳበረ ሰው ሊጫወታቸው የሚችሉ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ወደ መሰንቆ ሲመጣ ግን ነገሩ ትንሽ ለየት ይላል፡፡ መሰንቆ ምንም እንኳን በአካባቢው በስፋት የሚገኝ የሙዚቃ መሳሪያ ቢሆንም እሱን የሚጫወቱ ሰዎች መሰንቆ በመጫወታቸው የተነሳ ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ ቡድን ያላቸውና ‹‹አዝማሪ›› የሚል ስም ያላቸው ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ተግባር የእነዚህን ቡድኖች የኑሮና የዘፈን ልማድ ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ነው፡፡

ይህንን ለማድረግ መረጃዎች ከቤተመፃህፍት በተጨማሪ ከመስክ መቼትም ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎች የተሰበሰሰቡበት ሂደት ቀጣዩን ይመስላል፡፡

# 5. የመስክ ልምድ

## 5.1.ቅድመ መስክ ዝግጅት

ለጥናቱ የሚሆን ጥሬ መረጃ ለመሰብሰብ ወደመስክ ከመውጣቴ አስቀድሞ የአንድ ዓመት ጊዜ ዝግጅት አድርጌያለሁ። በዚህ ዝግጅትም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ትውውቅ ለማድረግ የሚረዱ ተግባራትን አከናውኛለሁ። ካከናወንኳቸው ተግባራት ውስጥ በርዕሱ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችን፣ የተፃፉ ፅሁፎችንና መፅሃፍትን ከቤተመፃህፍት፣ ከመረጃ መረብና ከግለሰቦች እጅ በመሰብሰብ ማንበብ፣ የሬዴዮና የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን ማድመጥና መመልከት፣ አዝማሪዎችን እንዲሁም በርዕሱ ማውራት የሚችሉ ሰዎችን ስራዬ ብዬ ፈልጌ በማግኘት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መነጋገርና መወያየት፣ከርዕሱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ወረቀቶችን መፃፍ[19]፣ አዝማሪን ርዕሰ ጉዳያቸው አድርገው በተዘጋጁ ጉባኤዎች መሳተፍ[20]፣ የሚሉት ይገኙበታል። ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ለመተዋወቅ የተጠቀሰውን ያህል ጥረት ካደረግሁ በኋላ ለጥናት የተመረጠውን አካባቢ ማህበረሰብና ባህሉን፣ የመልክዓ ምድሩንና፣ የአየር ሁኔታውን አይነት ለማወቅ ደግሞ የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ። በአጠቃላይ ወሎ ተብሎ ስለሚጠራው አካባቢ የሚገልፁ ፅሁፎችን በማንበብ፣ የአካባቢው ተወላጅ ከሆኑ ሰዎች፣ ከአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ ሰራተኞች መረጃዎችን በመጠየቅ ከአካባቢው ጋር ትውውቅ አድርጌያለሁ። ስለአካባቢው ማህበረሰብና ባህል ያለኝን ዕውቀት ተጨባጭ በማድረግ በአግባቡ ለመዘጋጀት ስል የአካባቢው የዞን ከተሞች ወደሆኑት ደሴና ወልዲያ ከተሞች በመጓዝ ከባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት ሰራተኞች፣ በአካባቢው ከሚኖሩ አንዳንድ የመሰንቆ ተጫዋቾች ጋር ትውውቅና ውይይት አድርጌያለሁ። ዞኖቹ፣ በወረዳዎቻቸው መካከል ባዘጋጁቸው የባህላዊ ሙዚቃ ውድድሮች ላይ በመገኘት ከአካባቢው ባህላዊ ሙዚቃ ጋር ትውውቅ ለማድረግ ሞክሬያለሁ። በዚህ ሁኔታ ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት አካባቢው በሚጠይቀው መልኩ የአካልና የስነልቡና

[19] በርዕሱ ዙሪያ በፎክሎር ትምህርት ክፍል በፒ.ኤች.ዲ መርሃ ግብሩ ለሚሰጠው ‹‹ቃልታሪክ›› የተባለ ኮርስ ማሟያ የሚሆን ‹‹የቡርቧክስ አዝማሪዎች ማህበረ ኢኮኖሚያዊ መልክ የሚልና፤ አንድ ደግሞ ባህል ለልማት ያለው ጠቀሜታ በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ለተዘጋጀ ጉባኤ ‹‹የሴት አዝማሪዎች ሚና›› በሚል ርዕስ አንድ ወረቀት በአጠቃላይ ከርዕሱ ጋር በተያያዘ ሁለት ጥናቶችን አድርጌያለሁ።

[20] በጀርመን ሃገር፣ በሂልድሻየም ዩኒቨርሲቲ፣ በዓለም የሙዚቃ ማዕከል አዘጋጅነት የኢትዮጵያን አዝማሪ ርዕስ አድርጎ በተዘጋጀ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተሳታፊ በመሆን ‹‹የሴት አዝማሪዎች ድርብ ሚና›› በሚል ርዕስ ወረቀት አቅርቤያለሁ።

ዝግጅት አድርጌያለሁ። እንዲሁም ለመስክ ስራ የሚያስፈልጉ አልባሳትን፣ የመቅረጫ መሳሪያዎችን፣ መድሃኒቶችን፣ ደረቅ ምግቦችን በመግዛትና በማዘጋጀት ጭምር ዝግጅቱን ሙሉ ለማድረግ ጥረት አድርጌያለሁ። በዚህ መልኩ ቅድመ መስክ ዝግጅቴን ካጠናቀቅሁ በኋላ ወደ መስክ ወጥቻለሁ።

## 5.2. የመስክ ውሎ

ቅድመ መስክ ዝግጅቱ ከላይ በተገለፀው መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ የመስክ ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልገኝን የድጋፍ ደብዳቤና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ከህዳር ሃያ አምስት እስከህዳር ሰላሳ ባሉት ቀናት ከአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ በማሰባሰብ ታህሳስ አንድ ቀን ወደ ደሴ ከተማ ተጓዝሁ።

በቀጣዩ ቀን ጠዋት ወደ ‹‹ደቡብ ወሎ ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት መምሪያ›› በመሄድ ለፅህፈት ቤቱ ሃላፊ ለአቶ ከድር ሙሐመድ ዓላማዬን አስረድቼና ‹‹የአማራ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ፣ የባህል እሴቶችና ተቋማት ጥናት፣ ልማትና አጠቃቀም የስራ ሂደት መሪ››፣ አቶ ዋጋው ሃይሉ የፃፉልኝን ደብዳቤ በማቅረብ ድጋፍ እንዲያደርግልኝ ጠየቅሁ። ሃላፊው በሁሉም መንገድ ሊረዳኝ ከሚችል አቶ ሰመረ ከበደ ከተባሉ የሙዚቃ ባለሙያ ጋር አላማዬን አስረድተው አስተዋወቁኝ። ከአቶ ሰመረ ጋር ከተዋወቅሁ በኋላ ስልክ ተደዋውለን ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ወደ ደሴ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈት ቤት ሄድሁ።

በደሴ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር ከዚህ በፊት ትውውቅ ያደረግሁ በመሆኑ ‹‹ማግኘት ይገባሻል›› ወደሚሏቸው ሰዎች እንዲወስዱኝ ጠየቅሁ። ቢሮው ለዚሁ ተግባር ሲል አቶ ፀጋው መኮንን የሚባል ወጣት መደበልኝ። እሱም አቶ ጫኔ ወርቅነህ ከሚባሉ የድሮ የላሊበላ ኪነት ቡድን አባል ከነበሩ ሰው ጋር አገናኘኝ። እኒህ ሰው ከሌሎች ሁለት ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የከተማው ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ አንዳንድ ዝግጅቶች ሲኖሩት ጋብዞ ሙዚቃ የሚያሰራቸው ከመሆኑ በስተቀር አሁን በዘበኝነት ሙያ ላይ ተሰማርተው የሚኖሩ ናቸው። በመሆኑም ‹‹ዋይዝ አፐ›› በሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ የጥበቃ ስራቸውን እየሰሩ ባሉበት ሄጀ አገኘኋቸው። አላማዬንም አስረድቻቸው ‹‹ምንም ችግር የለም እኔ የማውቀውን እነግርሻለሁ። ከሌሎች ሰዎች ጋርም አገናኝሻለሁ። ዛሬና ነገ ስራ ስለሆንኩ ከነገ ወዲያ በአራት ሰዓት እንገናኝ›› የሚል ምላሽ ሰጥተውኝ የስልክ ቁጥራቸውን ተቀብዬ ሄድሁ። ቀጥሎ በአቶ ፀጋው መሪነት ‹‹ቃተኛ›› ወደተባለ ምሽት

ቤት ሄድሁ፡፡ አቶ ፀጋው እንደሚለው በከተማው ሶስት ባህላዊ ምሽት ቤቶች የነበሩ ሲሆን አሁን ሁለቱ ተዘግተው ይህ ቤት ብቻ ቀርቷል፡፡ በቤቱ ተገኝቼ ባገኘሁት መረጃ ሁለት አዝማሪዎች ማታ ሰውን ሲያዝናኑ ያመሻሉ፡፡ ቀን ደግሞ ቤቱ የምግብ ቤት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ለምግብ ቤቱ ባለቤት ምን ፈልጌ እንደመጣሁ በመንገር ከአዝማሪዎቹ ጋር እንዲያገናኙኝ ጠየቅሁ፡፡ እንዳልካቸው ከተባለ አዝማሪ ጋር አስተዋወቁኝ፡፡ ከእሱ ጋር ጥቂት ከተወያየን በኋላ በሌላ ቀን ልንገናኝ ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡

በቀጣዩ ቀን ከአቶ ሰመረ ጋር ተገናኘሁ፡፡ አቶ ሰመረ የሙዚቃ ባለሙያ ሲሆን በከተማው የሙዚቃ ስቱዲዮና ትምህርት ቤት ከፍቶ ሙዚቃ ያቀናብራል፤ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ያስተምራል፡፡ አቶ አራጌ ይማም ለተባሉ መሰንቆ ተጫዋች ስልክ ደውሎ አስተዋወቀን፡፡ ከነገ ወዲያ በአራት ሰዓት ‹‹በወሎ ባህል አምባ አዳራሽ›› ከአቶ ጫኔ ወርቅነህ ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ መያዜን በመግለፅ እዚያ ለመገናኘት ጠየቅኋቸው፡፡ ተስማሙ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ከሁለቱም ሰዎች ጋር ተገናኘን፡፡ የመጣሁበትን ምክንያት በሚገባ አስረድቼና ፈቃዳቸውን ጠይቄ አስቀድሜ ባዘጋጀኋቸው ጥቂት ጥያቄዎች መነሻነት ለጥናቴ ዓላማ ግብ መምታት የሚረዱኝን ጥያቄዎች በማቅረብ ከአራት ሰዓት ተኩል እስከሰባት ሰዓት ድረስ ለሁለት ሰዓት ተኩል ያህል መረጃ ሰበሰብሁ፡፡ ለእለቱ ይህ እንደሚበቃ ወስነን በሚቀጥለው ቀን ተገናኝተን ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡ የከሰዓት ውሎዬን የተገኘውን መረጃ ከመቅረፀ ድምፅ ሳዳምጥና የጎደሉ መረጃዎችን በማስታወሻ ስይዝ፣ በአጠቃላይ መረጃዬን የምመረምርበት ጊዜ አድርጌ አሳለፍሁት፡፡

በማግስቱ  ከአቶ ጫኔና አቶ አራጌ ጋር በይደር ያቆየነውን ጉዳይ ለመወያየት ከረፋዱ አራት ሰዓት አቶ ጫኔ የጥበቃ ስራ በሚሰሩበት ‹‹ዋይዝ አፕ›› መስሪያ ቤት ተገናኘን (ቀኑ እሁድ ስለሆነ መስሪያ ቤቱ መደበኛ ስራውን አይሰራምና ቦታውን የመረጥነው ለፀጥታው ሲባል ነበር)፡፡ በእለቱ ከአቶ ጫኔ ይልቅ (አቶ ጫኔ ዋሽንት ተጫዋች ናቸው) የመሰንቆ ተጫዋቹን የአቶ አራጌን የህይወት ታሪክ በመጠየቅና እነዚህ ሰዎች የወሎ ናቸው ብለው በድፍረት የሚመሰክሩላቸውን አራቱን ቅኝቶች ምንነትና፣ የት መጣ ላይ ያተኮሩ መረጃዎችን በመሰብሰብ ላይ ትኩረቴን አድርጌ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዋና ጉዳዮች ይሁኑ እንጅ ሌሎች በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችንም ለአንድ ሰዓት ያህል በቃለመጠይቅና በምልከታ ሰብስቤያለሁ፡፡

በመቀጠል ሁለቱ ሰዎች ‹‹በትውልድም ሆነ በስራ አዝማሪ የሆነ፣ ድሮ የላሊበላ ኪነት አባል ነበረ፣ ዛሬ ግን በደሴ ሙዚየም በዘበኝነት የሚሰራ ተፈራ አያሌው የሚባል ሰው አለልሽ፤ እነሱ ላኩኝ በይና ሂጅ›› ባሉኝ መሰረት ከእነሱ እንደ ተለየሁ ወደ ደሴ ሙዚየም ተጉዤ አቶ ተፈራ አያሌውን አገኘኋቸው፡፡ አላማዬን አስረድቼና እነ አቶ አራጌ እሱን አነጋግሪ እንዳሉኝ ገልጬ መረጃ እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው፡፡ ፈቃደኛ በመሆናቸው ከአምስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ተኩል ለሁለት ሰዓት ተኩል ያህል መረጃዎችን በቃለመጠይቅ ሰበሰብሁ፡፡

ከሰዓት በኋላ አቶ ሰመረ ስልክ ደውለው ከሌላ መረጃ አቀባይ ጋር እንደሚያገናኘኝ ስለገለፀልኝ ወደእሱ ስቱዲዮ ሄድኩኝ፡፡ አቶ አሰፋ ለገሰ ከሚባሉ በዕድሜ የገፉ አዛውንት ሰው ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ ይህ ሰው በቀድሞው የላሊበላ ኪነት ቡድን ውስጥ በመሰንቆ ተጫዋችነት ሲያገለግል የነበረ፣ ዛሬ ደግሞ አኮርዲዎን በተባለው መሳሪያ ከእነ አቶ ጫኔ ጋር አንዳንድ የሙዚቃ ስራዎች ሲገኙ በመስራት የሚኖር ሰው ነው፡፡ ለአቶ አሰፋ ራሴንና አላማዬን አስተዋወቅሁ፡፡ አንዳንድ ነገሮችን ስናወራ ከቆዬን በኋላ ነገ ልንገናኝ ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡ በዚሁ ዕለት ‹‹የአዝማሪ ምሽት ቤት›› ክዋኔ ለማየት አቅጄ ስለነበር ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ወደ‹‹ቃተኛ ባህላዊ ምሽት ቤት›› ሄድሁ፡፡ ሁለት ሰዓት ሲሆን  አዝማሪው መሰንቆውን አለስልሶ ዘፈን ጀመረ፡፡ የዘፈኑን ዜማ በዘለሰኛ ጀምሮ ቀስ በቀስ ታዳሚውን ወደ ሚያሳትፉ ደመቅ ያሉ ዜማዎች በመውሰድ ታዳሚውን ሲያዝናና ቆይቶ ከአርባ ደቂቃ በኋላ ለሌላው አዝማሪ ቦታ ለቀቀ፣ ይኸኛውም እንዲሁ ለአርባ ደቂቃ ያህል ተጫውቶ ለመጀመሪያው ቦታውን ለቀቀ፡፡ በዚህ ሁኔታ የዘፈን ክዋኔው ቀጥሎ አመሸ፡፡ እኔም ዘፈን ሲዘፈን በማጨብጨብና በመቀበል በተሳታፊ ምልከታ መረጃዎችን ስሰበስብ አምሽቼ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት አልጋ ወደ ያዝሁበት ሆቴል ተመለስኩ፡፡

የምሽት ቤቱን ክዋኔ አጠቃላይ ባህርይ ለመረዳት እንዲያስችለኝ በማሰብ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በምሽት ቤቱ እየተገኘሁ ክዋኔውን ስመለከት ሰነበትሁ፡፡ የምሽት ቤቱ የዘፈን ክዋኔ በማታ የሚደረግ በመሆኑ ቀን ከአቶ አሰፋ ለገሰና ከሌሎችም ሰዎች መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በተጠኝ ቡድን ውይይት በመሰብሰብና ወደሌሎች የጥናት ቦታዎች የሚወስዱኝ መንገድ መሪዎች በማፈላለግ እስከ ታህሳስ አስራ አምስት በደሴ ከተማ ቆይቼ አቶ ሰመረ ከበደ፣ አቶ አሰፋ ለገሰና አቶ መላኩ መድፉ የተባለ የደረቅ ወይራ ተወላጅ አዝማሪ መረጃ ሰጪዬ አብረውኝ ለመሄድ ስለተስማሙ በአቶ መላኩ መሪነት ታህሳስ አስራ ስድስት ወደደረቅ ወይራ ጉዞ ጀመርን፡፡

ከአንድ ሰዓት ተኩል ቁልቁለትና ዳገት የእግር መንገድ በኋላ ‹‹አባ ቡላ›› ተብሎ ከሚጠራ የአዝማሪ መንደር ደረስን፡፡ ከዚያም አቶ መላኩን አስቀድሜ ባስገነዘብሁት መሰረት መረጃ ሰጪ የሚሆኑኝን አዝማሪዎች እንዲሁም ስለአዝማሪዎች እውቀት ያላቸውና መረጃ መስጠት የሚችሉ አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎችን ፈልጎ እንዲያገናኘኝ ነገርሁት፡፡ አቶ መላኩ ፈልጎና መርጦ ከአስራ ሁለት ሰዎች ጋር አገናኘኝ፡፡ አምስቱ ሴቶች ሰባቱ ደግሞ ወንዶች ነበሩ፡፡

የመጀመሪያውን መረጃ ስብሰባ በቡድን ውይይት ያካሄድሁ ሲሆን ቡድኑ ሰባት አባላት ያሉትና አዝማሪዎችን፣ የእጅ ስራ ባለሙያዎችንና ገበሬዎችን ያካተተ ነበር፡፡ በዚህ ውይይት በአዝማሪዎችና በሌሎች ባለሙያዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎችን አግኝቻለሁ፡፡ የመጀመሪያው የቡድን ውይይት ካለቀ በኋላ አዝማሪ የሆኑና ያልሆኑ ሰዎችን ለየብቻ በማድረግ የቡድን ውይይቶችን አካሄድሁ፡፡ በእነዚህ ውይይቶች ሁለቱ ቡድኖች እርስ በእርስ ያላቸውን አመለካከት ለማየት የሚያስችሉ መረጃዎችን አገኘሁ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ወ/ሮ ዘሪቱ ከበደ፣ ፈንታዬ ሞላ፣ ትርንጎ መላክ፣ ፀሃይ ሞላልኝ የተባሉ ሴት አዝማሪዎችን ብቻ ያሳተፈ ሌላ ቡድን በመመስረት መረጃዎችን ሰበሰብሁ፡፡ ቀጣዩን መረጃ አዝማሪነትንና ግብርናን አጣምረው ከሚሰሩ ካሳው ተፈራና ደምሴ ቀማው፣ ማለደ አበራ፣ ሰኢድ ዋለ ከተባሉ ወጣቶችን አሰባስቤ አወያየሁ፡፡ በዚሁ ቀን ትናንት ያወያየኋቸውን ሴትና ወንድ አዝማሪዎች አንድ ላይ በማድረግ ውይይት አካሄድን፡፡ ሌላው አቶ መላኩ አብሮን ያደገ ስለሆነ ስለእኛ ብዙ ያውቃል ካላቸው አቶ ሰኢድ ኢብራሂም ከተባሉ ገበሬ ጋር አገናኝቶኝ መረጃ ሰጡኝ፡፡ በመጨረሻም እኒህ መረጃ ሰጪዬ ‹‹ከእስዋ የተሻለ ማን ያውቃል›› ሲሉ በሰጡኝ ጥቆማ መሰረት ወ/ሮ አሰጉ ከተባሉ ዕድሜያቸው ከዘጠና በላይ ከሆኑ የእድሜ ባለፀጋ አዝማሪ በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ሌሎች በዕድሜ የገፉ አዝማሪዎችን ጨምሬ መረጃ ሰበሰብሁ፡፡ በአጠቃላይ በደረቅ ወይራ በምልከታ (አኗኗራቸውን በማየት)፣ በቃለ መጠይቅና በውይይት ለአምስት ቀናት ያህል መረጃዎችን ከሰበሰብሁ በኋላ ታህሳስ ሃያአንድ ወደመንደሩ ካመጡኝ በኋላ ወደደሴ ተመልሰው የነበሩትን መንገድ መሪዎቼን እንዲመጡልኝ ስልክ ደውዬ ጠራሁና ወደደሴ ተመለስሁ፡፡

ቀጥሎ ሁለተኛ የጥናት ቦታዬ ወደሆነው አምባሰል ወረዳ ሄድሁ፡፡ የወረዳው ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈት ቤት በውጫሌ ከተማ ከሚገኙ ወ/ሮ አለም ፀሃይ የማና፣ አቶ ደምሴ አበበ፣ አቶ አበባው ሙሉጌታ፣ አቶ ሞላ ተገኘ ከተባሉ መረጃ ሰጪዎች ጋር እንድገናኝ ስላደረገኝ ከእነዚህና ከፅህፈትቤቱ ሰራተኞች ለአምስት ቀናት ያህል

መረጃዎችን በመሰብሰብ ውጫሌ ቆየሁ፡፡ ከዚያም ፅህፈትቤቱ ከመደበልኝ መንገድ መሪ ጋር፣ የአምባሰል ወረዳ አስተዳደር ፅህፈትቤት ባዘጋጀልኝ መኪና ማርዬ ስላሴ ተብሎ ወደሚጠራው አዝማሪዎች የሚኖሩበት ቀበሌ ሄድሁ፡፡

ማርዬ ስላሴ ደርሰን በየጠጅ ቤቱ አዝማሪዎችን ለማግኘት ብዙ ጥረት ብናደርግም አንድም አዝማሪ ማግኘት አልቻልንም፡፡ በመጨረሻ አባይ ሽመልስ የተባለች የጠጅ ቤት ባለቤት መላኩ ካሳው ለተባለ አዝማሪ መልዕክት ልካበት መጣ፡፡ አላማዬን አስረዳሁት፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ጥቂት ካወራን በኋላ ‹‹አዝማሪዎች ጠጅ ቤት መስራት ስላቆሙ በቀጠሮ ካልሆነ በስተቀር ማግኘት እንደማልችል ነገረኝ፡፡ ለጥምቀት በዓል እንድመጣ እሱም ለሌሎች ነግሮ በዚያ ጊዜ ሊጠብቁኝ ተነጋግረን በዚያው ቀን ወደ ውጫሌ ተመለስሁ፡፡

ይሁን እንጅ ቀጥለው ባሉት ቀናት የገና በዓል በመድረሱ ምክንያት መንገድ መሪዎቼ በበዓል ዝግጅት ላይ ሆኑ፡፡ ያለእነሱ ምንም ማድረግ የማልችል በመሆኑ እኔም ከቤተሰቦቼ ጋር የገና በዓልን ለማክበር ስል በጥር ሃያ ስምንት ቀን ወደባህር ዳር መጣሁ፡፡ የገና በዓልን ካከበርሁ በኋላ እስከ ጥር ስምንት ድረስ ያመጣሁትን መረጃ በመመርመር ቆየሁ፡፡ ከዚህ በኋላም መጪው የጥምቀት በዓል በመሆኑና አስቀድሞ ባገኘሁት መረጃ መሰረት አዝማሪዎች በዚህ በዓል ታቦት ሲያጅቡ የሚውሉ በመሆኑ ይህንኑ ለመመልከትና ከማርዬ ስላሴ አዝማሪዎች ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ ስላለኝ የሁለተኛ ዙር ጉዞዬን ወደ ውጫሌ አደረግሁ፡፡ ወደ አምባሰል ወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት ሄጄ መምጣቴን በመንገር ለጉዞ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ከፅህፈትቤቱ ጋር በማመቻቸት ለነገ ጉዞ ተዘጋጀሁ፡፡

በቀጣዩ ቀን የባህል፤ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት ከሰጠኝ መንገድ መሪዬ ከተስፋዬ እሸቴ ጋር በመሆን ፅህፈትቤት በሰጠን መኪና ወደ ማርዬ ሄድን፡፡ ማርዬ ደርሰን አልጋ ከያዝን በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ሄድን፡፡ ታቦታቱ ከቤተክርስቲያን መውጣት የጀመሩት ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ከሆነ በኋላ ነበር፡፡ በአካባቢው የስላሴ (ማርዬ የምትጠራበት ታሪካዊ ቤተክርስቲያን ነው)፣ የገብርኤል፣ የሚካኤል፣ የማርያም፣ የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያኖች ናቸው ያሉት፡፡ እኛም ከእነዚህ ውስጥ በአንድ አቅጣጫ የመጡትን የስላሴ፣ የገብርኤል፣ የሚካኤል፣ የማርያም፣ ታቦቶችን አጅበን ወደ ታቦት ማደሪያው ቦታ ተጓዝን፡፡ ታቦታቱን ካጀባቸው ሰው ውስጥ አዝማሪ አልነበረም፡፡ በዚሁ ይቀጥል ይሆን የሚል ስጋት ያዘኝ፡፡ በዚያ ላይ አዝማሪዎችን ፈልጎ

ሊያገናኘኝ ቃል የገባው የቀበሌ ሊቀመንበር አቶ ፈንታዬ ብቅ ሳይል መቅረቱ ሌላ ሃሳብ ሆኖብኝ አደርሁ፡፡

ጥር አስራ አንድ 2005 ዓ.ም. የጥምቀት በዓል ነው፡፡ በጠዋት ተነስቼ አለባበሴን ለበዓሉ የተስማማ በማድረግ (ቀሚስ፣ ነጠላ ትዕምርት መስቀል አለባበስ) ታቦት ወዳረፈበት ቦታ ሄድሁ፡፡ ከመንገድ መሪዬ ከተስፋዬ ጋር ነኝ፡፡ ቅዳሴ እየተቀደሰ ደረስን፡፡ ቅዳሴው ካለቀ በኋላ ከህዝቡ ጋር ወደ ወንዝ ወርደን ‹‹ተጠመቅን››፡፡ ጥምቀቱ ረጅም ስነስርዓት ነበረው፡፡

አምስት ሰዓት አካባቢ ወደአረፍንበትና ‹‹የሽመልስ ቤት›› ብለው ወደሚጠሩት ‹‹ሆቴል›› (ምግብ፣ አረቄ፣ ጠጅ፣ ቢራ ይሸጥበታል) ተመልሰን ቁርስ በላን፡፡ ከዚያ በኋላ ወጣ ብለን መዟዟር ጀመርን፡፡ ዋና ትኩረታችን አዝማሪ መፈለግ ነበር፡፡ ከአንድ ጠጅ ቤት ገባን፡፡ ወደዚህ ጠጅ ቤት የገባነው ምሳ እየበላን አንድ አዝማሪ ወደጠጅ ቤቱ አቅጣጫ ሲያልፍ አይተን ስለነበር እዚህ ገብቶ ይሆናል ብለን ነው፡፡ ነገር ግን በጠጅ ቤቱ ውስጥ ከአዝማሪው ይልቅ እመጣለሁ ብሎ የጠፋውን የቀበሌ ሊቀመንበር አገኘነው፡፡ ስለመጥፋቱ ወቀስነው፡፡ ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ ገጥሞት እንደነበርና ዛሬ እንደሚያገናኘን ነገረን፡፡ ከውጫሌ ይገኘው በመጣሁት መረጃ መሰረት በተለይ ብርሃን ትኩንና ማስረሻ ፈንታው የተባሉ ሰዎችን እንደምፈልግ ነገርሁት፡፡ ፈቃደኝነቱን ገለፀልኝ፡፡ ከዚያም ለጥቂት ጊዜ ከእሱ መረጃ እየሰበሰብሁ አብረን ቆየንና ሶስታችንም ከጠጅ ቤቱ ወጣን፡፡

ሰባት ሰዓት ላይ ታቦታቱ ካደሩበት ቦታ ወደ የቤተክርስቲያናቸው ለመሄድ ተነሱ፡፡ አካባቢያችንን በትኩረት ስንቃኝ ከአንዱ ታቦት አጠገብ ብቻ ሶስት አዝማሪዎች አሉ፡፡ በሌሎች ታቦታት አጠገብ አዝማሪ የለም፡፡ በኋላ ቆይቼ እንደተረዳሁት አዝማሪዎች ያጀቡት ታቦት የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ታቦት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህንን ታቦት ያጀቡበት ምክንያት የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን የሚገኘው የአዝማሪዎች ቤት ወዳለበት አቅጣጫ በመሆኑ በዓሉ ካበቃ በኋላ ወደቤታቸው ለመሄድ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡ ሌሎች ታቦታት ከዚህ አቅጣጫ በተቃራኒው የሚጓዙ ነበሩ፡፡ እኛም አዝማሪዎች ያሉበትን የበዓል ክዋኔ በመከተል እንቅስቃሴያቸውን ስንመለከትና አመቺ በሆነበት ሁሉ በቪዲዮ ካሜራ ስንቀርፅ ዋልን፡፡

የታቦት አጀባው ቦታ እያለሁ የቀበሌው ሊቀመንበር ጠርቶኝ ከሁለት ሰዎች ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ እነዚህ የምትፈልጊያቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ብርሃን ትኩና ማስረሻ ፈንታው ይባላሉ አለኝ፡፡ ሰዎቹ በእድሜ በሰል ያሉ ናቸው፡፡ መሰንቆ ግን አልያዙም

ነበር፡፡ ከሰዎቹ ጋር ስንገናኝ ታቦቱ ከቤተክርስቲያኑ ሊደርስ ትንሽ ቀርቶት ነበር፡፡ እኔም ከዚህ በኋላ ያለውን ጊዜ ከሰዎቹ ሳልርቅ ወደቤተክርስቲያኑ ደረስን፡፡ ታቦት ከገባ በኋላ ከዚህ እንውጣና አንድ ቦታ ተቀምጠን እናውራ ስል ባቀረብሁት ሃሳብ በመስማማታቸው ከቤተክርስቲያኑ ወጣን፡፡ ለሰዎቹ የመጣሁበትን ምክንያትና የስራዬን አላማ አስረዳሁ፡፡ ‹‹ልክ ነው ከእኛ የተሻለ ይህንን ማን ሊነግርሽ ይችላል›› ከሚል በጎ አስተያየት በኋላ መረጃ መስጠቱን ፈቀዱልኝ፡፡ ለቀሪው ጉዳይና ለሙዚቃ ክዋኔ ነገ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ የሚካኤል በዓል በሚከበርበት ቦታ ለመገናኘት ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡

በበነገታው እስከጧቱ አራት ሰዓት ድረስ ቀጠሮ የሰጡኝ ሰዎች አልመጡም፡፡ እንዳይቀሩ እየሰጋሁ ጠበቅኋቸው፡፡ አራት ሰዓት ሲሆን ትናንት ከቀጠርኋቸው ውጪ አራት ሰዎችንም ጨምረው መሰንቆ ይዘው መጡ፡፡ ከሰላምታ ልውውጥ በኋላ ከሁለት ሰዎች በስተቀር ሌሎች ወደጠጅ ቤት ገቡ፡፡ ከገቡበት ቤት መሰንቋቸው እንዲቀመጥላቸው ሲሰጡ አየሁ፡፡ ቀሪዎቹ ሁለት ሰዎች ታቦቱ ወዳረፈበት ቦታ እየሄዱ እንደሆነና እዚያ ማውራት እንደምንችል ነገሩኝ፡፡ ተከትያቸው ሄድሁ፡፡ ከጠጅ ቤት የገቡት ሰዎች እስኪወጡ ድረስ ከሁለቱ ሰዎች በቃለመጠይቅ መረጃዎችን ስሰበስብ ቆየሁ፡፡ ሰባት ሰዓት ሲሆን ታቦቱ ተነሳ፡፡ ሰዎቹም ከመጠጥ ቤቱ ውስጥ ተደብቆ እንዲቀመጥ የሰጡትን መሰንቆ ተቀብለው ተነሱ፡፡ ተከተልኋቸው፡፡ የተወሰነ መንገድ ድረስ ከታቦቱ ፊት ፊት እየተጓዙ፣ በመሰንቆ ድምፅ ብቻ መዲናና ዘለሰኛ ሲጫወቱ በቪዲዮ ካሜራ ስቀርፅ ቆየሁ፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ሁሉም ቀስ በቀስ ወደኋላ ሲመለሱ አይቼ አብሬያቸው ተመለስሁ፡፡ የመጡት ለእኔ እንደሆነና ታቦቱን ተከትለው እስከመጨረሻው ከተጓዙ ስለሚመሽ መገናኘት የማንችል መሆኑን ነገሩኝ፡፡ ለውይይት ያመቻል ብለን እኔ ወደተከራየሁት ክፍል ሄድን፡፡ ወደዚህ ቤት ስንሄድ ዘጠኝ አዝማሪዎች አብረውኝ ነበሩ፡፡ በትውውቃችን እንደተረዳሁት እነዚህ ሰዎች ወንድማማቾችና የወንድም ልጆች ናቸው፡፡ በክፍሉ ውስጥ ሁሉም ሰው የሚቀመጥበትን ቦታ ከያዘ በኋላ ትናንት ጀምሮ ጨዋታ የሚመጣው መጠጥ ሲጠጣ፣ ሰውነት ሞቅ ሲለው ነው በማለት አስረግጠው ስለነገሩኝ ሁሉም ሰው የፍላጎቱን መጠጥ እንዲያዝዝ ጋበዝሁኝ፡፡ ትልልቆቹ ነጭ አረቂ እንጠጣለን አሉ፡፡ ከወጣቶች አንድ ሁለቱ ቢራ፣ ሌሎች ደግሞ ለስላሳ አዝዘው ውይይት ተጀመረ፡፡ ከውይይቱ በኋላም በተለይ እነሱ ሊታወቅ የሚገባው የአባት አደሩ የመሰንቆ ጨዋታ ስርዓት ነው ያሉትን የመሰንቆ ጨዋታ እየተቀባበሉ ተጫወቱልኝ፡፡ የመረጃ

መሰብሰቢያ ዘዴው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ሲሆን በጣም አስደሳችና አስተማሪ እንዲሁም አጥጋቢ መረጃ የተገኘበት ነው፡፡ አያት ልጅና የልጅ ልጆች የተሳተፉበት፣ የዘር ሃረግም የተቆጠረበት ነበር፡፡ የሚካኤል በዓል ካለፈ በኋላ ደግሞ የበዓል ድባብ በሌለበት መረጃዎችን ለማግኘት በመፈለጌ የተተኳሪ ቡድን ውይይቶችን በማዘጋጀት ለሶስት ቀናት መረጃዎችን ሰብስቤ ጥር አስራ ስድስት ቀን እኔና መንገድ መሪዬ ተስፋዬ ወደውጫሌ ተመለስን፡፡

ጥር አስራ ሰባት ወደለጋምቦ ወረዳ ሄድሁ፡፡ ወደዚህ ቦታ ስሄድ መንገድ መሪዬ የነበረው ሰው አቶ ሙሐመድ ፋንታሁን የተባለ የለጋምቦ ወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት ባልደረባ ሲሆን እኔ ላገኘው የቻልሁት ለስብሰባ ደሴ በመምጣቱና ይህንንም የዞኑ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ቢሮ እንዳውቅ ስላደረገና እርዳታም እንዲያደርግልኝ ስላመቻቸ ነው፡፡ ወደ አቀስታ (የለጋምቦ ወረዳ ዋና ከተማ) የሄድነው በሚኒ ባስ ነው፡፡ ጉዞው አራት ሰዓታትን የፈጀ ነበር፡፡

በሚቀጥለው ቀን ከአቶ ሙሐመድ ጋር ብዙ ጠብቀን በተገኘች ሚኒባስ እኔ ‹‹ጋቢና›› ውስጥ ከሹፌሩ ጋር ሶስተኛ ሰው ሆኜ ተሳፍሬ (ከኋላ የተሳፈረውን የሰው ብዛት መገመት በጣም አስቸጋሪ ነው) ‹‹ኢላዳ›› ተብሎ ወደሚጠራው የአዝማሪዎች መንደር የሚገኝበት ቀበሌ ሄድን፡፡ ኢላዳ ከአቀስታ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ይርቃል፡፡ እዚያ ደርሰን የኢላዳ ቀበሌ ሊቀመንበር የሆነውን አቶ ከበደ ፋንታሁንን አነጋገርን፡፡ ከብዙ ሰዎች ጋር ቆሞ እያወራ ነበር፡፡ አዝማሪዎች የሚኖሩበት መንደር በረከት እንደሚባል፣ ነገ ካልሆነ ዛሬ አዝማሪዎች ወደ ገበያ ስለሚሄዱ እንደማናገኛቸውና ሌሎች አዝማሪዎች የተመለከቱ መረጃዎችን ከሊቀመንበሩና አብረውት ካሉት ሰዎች አገኘን፡፡ እኔም ወደኋላ ከመመለስ ወደገበያው ቦታ መሄድ ስለፈለግሁ እንደገና ከረጅም ሰዓት ጥበቃ በኋላ በመጣች ሚኒባስ እንደተለመደው ጋቢና ሶስተኛ ሰው ሆኜ ‹‹እምባጮ በር›› ወደሚባል የአካባቢው ገበያ ሄድን፡፡ በአካባቢው በርካታ ጠላ ቤቶች አሉ፡፡ ከብዙዎቹ ውስጥ ወጣ ገባ እያልን ብናይም መሰንቆ የያዘ ሰው ማየት አልቻልንም፡፡ ስለዚህ ከአንድ ጠላ ቤት አረፍ ብለን መጠየቅን ስለመረጥን ገብተን ተቀመጥን፡፡ ሁለት ጠላ የሚጠጡ ሰዎች ተቀምጠው ነበር፡፡ እኛም ጠላ እንዲመጣልን ጠይቀን ሴትዮዋ ጠላውን ይዛ አጠገባችን ስትደርስ ‹‹አዝማሪ አይመጣም ወይ?›› የሚል ጥያቄ አቀረብን፡፡ ይመጣሉ አለች፡፡ ንግግራችን ምናልባት እንግድነታችን ስቧቸው ሳይሆን አይቀርም ትኩር ብለው ሲያዩን ከነበሩት ሰዎች ጆሮ አላመለጠም፡፡ አንደኛው ‹‹ለምን ተፈልገው ነው?›› የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡ የመጣንበትን ምክንያት ነገርነው፡፡ ‹‹ልፈልጋቸው፣ ችግር የለም ይመጣሉ››

ብሎ ወጣ፡፡ የቤቱ ባለቤት እሱም አዝማሪ ነው አለችን፡፡ ሶስት ሰዎች ከፈላጊው ጋር አራት ሆነው መጡ፡፡ ነገር ግን በጣም አስቸጋሪ ሰዎች ሆነው ተገኙ፡፡ ምንም ነገር ካፋቸው ሳይወጣ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ጠየቁ፡፡ ተረጋግተው እንዲቀመጡ ካደረግኋቸው በኋላ ጠላ እንዲጠጡ ጋበዝኋቸው፡፡ የጠላ ግብዣው እንኳን ይሉኝታ ሊያሲይዛቸው አልቻለም፡፡ በጣም አስቸጋሪ ሆነው ነበር፡፡ በተለይ ከመካከላቸው በዕድሜ ገፋ ያሉና የተሻለ ንቃት አለኝ የሚል ስሜት የሚያንፀባርቁ ሰው ወደውጭ ወጥተው ከቆሙ በኋላ ሌሎችን በየተራ እየጠሩ ይመክሩ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእኛን መምጣት የሰሙ ሌሎች አዝማሪዎች በተለይ ሴቶች እየመጡ በመጨመራቸው የስብስቡን ቁጥር አብዝተውት ነበር፡፡ እነዚህም ሰዎች ያለምንም አገልግሎት ግብዣና ስጦታን ይጠብቁ ነበር፡፡ ሁሉንም ሰዎች ጠላ ጠጡ አልኋቸው ያለምንም ማቅማማት ግብዣውን ይቀበላሉ፡፡ እኔ የውስጡንም ሆነ የውጩን ትርኢት በአንክሮ እከታተላለሁ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ ምክክር በኋላ ከውጭ የነበሩት ሰዎች ገብተው ተቀመጡ፡፡ በመረጃ ስብሰባ ውስጥ ትዕግስት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ከተረዳሁ ቆይቻለሁ፡፡ ለእነዚህ ሰዎች ያለመሰልቸት እንደ አዲስ አላማዬን አስረዳሁ፡፡ አሁንም ቢሆን መረጃ ለመስጠት ያላቸው ፍላጎት ብዙ መሻሻል አልታየበትም፡፡ እኔ ደግሞ በብዙ ቦታዎች ዞሬ መረጃ የሰበሰብሁ መሆኑንና እንቢ ካሉ ትቼ ልሄድ እንደምችል፤ በዚህ ከቀጠሉ ደግሞ የእነሱን ዕውቀት ራሳቸው ብቻ ይዘውት እንደሚኖሩ እንጅ ሌላ ማንም ሳያውቅላቸው ተዳፍኖ እንደሚቀር፣ ይህ ደግሞ ሁላችንንም እንደሚጎዳ ለማስረዳት ጥረት አደረግሁ፡፡ በዚህ መሃል ሙሐመድ ለምን መረጃ መስጠት እንደማይፈልጉ ጠየቃቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠልም እሱ ከአቀስታ እንደመጣ፣ የሙዚቃ ባለሙያ እንደሆነና የእሱ ቢሮ ከአካባቢው ነዋሪዎች የወረዳውን የኪነት ቡድን ለመመስረት እቅድ ላይ መሆኑን ነገራቸው፡፡[21] ታዲያ እነሱ እውቀታቸውን ለሌላው ሰው ማካፈል ካልፈለጉ ወረዳው እንዴት ሊረዳቸው እንደሚችልም ጠየቃቸው፡፡ ይህ ሃሳብ የሁለት ሰዎችን ስሜት ቀሰቀሰ፡፡ አንደኛው ‹‹ባለፈው ጊዜም እንዲህ ተብሎ ነበር፤ የት ደረሰ?›› አለ፡፡ ሌላኛው ሰውዬ ደግሞ ‹‹ኧረ እኔ በጣም ጎበዝ፣ አራቱንም ቅኝቶች ጠንቅቆ የሚያውቅ ልጅ አለኝ፡፡ እሱ የኪነት ቡድን ውስጥ እንዲገባ እፈልጋለሁ›› አለ፡፡ ወዲያውኑ ለልጁ ስልክ ደውለውለት ሲሰራበት ከነበረበት ቤት ከነመሰንቆው እንዲመጣ አደረጉ፡፡

[21]ሙሐመድ ይህንን ያለው እውነቱን ነበር፡፡ እኔና እሱም ለመገናኘት የቻልነው በዚሁ ሃሳብ ላይ ለመወያየት በተጠራ ስብሰባ ደሴ በመምጣቱ ምክንያት ነው፡፡

ከእኔ ዓላማ ይልቅ የሙሐመድን ተስፋ በመናፈቅ ለማቀርብላቸው ጥያቄ መልስ መስጠት ጀመሩ፡፡ የቡድን ውይይት አካሄዱ፡፡ ከዚያ አልፎም በየተራ እየተቀባበሉ መሰንቆ ተጫወቱ፡፡ በክፍያ መልኩ ሳይሆን ለዘፈናቸው ሽልማት በመስጠትና በመጋበዝ የፈለጉትን ያህል ባይሆንም የምችለውን ያህል ገንዘብ አወጣሁ፡፡ በዚህ መልኩ በብዙ ማባበል መረጃውን ካገኘን በኋላ ነገ ወደ በረከት ለመመለስ አቅጄ ወደ አቀስታ ተመለስሁ፡፡

ጥር አስራ ዘጠኝ 2005 ዓ.ም. በጠዋቱ ተነስቼ ራሴን ለጉዞ አዘጋጀሁ፡፡ ሙሐመድ መጥቶ ነበር፡፡ ትናንት በትራንስፖርት ሰበብ ያገኘን ድካም አሳስቦን ስለነበር ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ወሰንና ወደ ወረዳው አስተዳደር በመሄድ መኪና እንዲሰጡን ጠየቅን፡፡ አልከለከሉንም፡፡ በተለይ ‹‹ደብዳቤ ይዛለች›› የሚለው የሙሐመድ ማሳሰቢያ መኪና ለማግኘት ትልቅ ቁልፍ ነበር፡፡ ቢሮዎች ደብዳቤ ይዞ የመጣን ሰው በፍጥነት ያስተናግዳሉ፡፡ ይህንን በተለያዩ ቦታዎች አይቻለሁ፡፡

ትንሽ ከጠበቅን በኋላ የተፋሰስ ስራ ለማሰራት እኛ በምንሄድበት አቅጣጫ ከሚሄዱ አራት የተለያዩ ቢሮ ባለሙያዎች ጋር አብረን እንድንሄድ ተነግሮን መኪናው ላይ ተሳፈርን፡፡ ሰዎች በየመንገዱ እየወረዱ ጉዞው ቀጠለ፡፡ እኛም ትናንት ባገኘነው መረጃ መሰረት ኢላዳ ከመድረሳችን በፊት አስቀድመን ብንወርድ የተሻለ መንገድ እንደምናገኝ ስላወቅን ኢላዳ ከመድረሳችን በፊት ‹‹ጥቅሲ›› የሚባል ቦታ ላይ ወረድን፡፡ ከዚያም በዳገታማ መንገድ ሁለት ሰዓት ተጉዘን በረከት ደረስን፡፡ ብዙ ሰዎች ‹‹ከልማቱ ሄደዋል›› (በአካባቢው በገበሬው የተፋሰስ ስራ እየተሰራ ነው) ተባለ፡፡ እስኪመጡ ድረስ እቤት ካሉ ህፃናትና አንዳንድ ሰዎች መረጃ ስንሰበስብ፣ አካባቢውንና ቤቶቻቸውን ስንመለከት፣ ቆዩን፡፡ እንዲሁም ልማት ሳይሄዱ በመቅረታቸው ከቤት ካገኘናቸው ተመስገን ፈንታና የሮም አያሌው ከተባሉ ባልና ሚስት አዝማሪዎች እንዲሁም በቤቱ ውስጥ እኛን አይተው ከተሰበሰቡ ሰዎች በውይይት እንዲሁም በቃለ መጠይቅ መረጃ ስንሰበስብ ቆዩን፡፡ ከሰዓት በኋላ ሲሆን ልማት የሄዱ የመንደሩ ሰዎች ሰዎች ተመለሱ፡፡ በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ቡድኖችን በማደራጀት መረጃ ስንሰበስብ ውለን ስለመሸ እዚያው አደርን፡፡ በሚቀጥለው ቀን ሲረፋፍድ ወደ አቀስታ ተመለስን፡፡

ጥር ሃያ 2005 ዓ.ም. አቀስታ ከተማ ሰርግ ቤት ውስጥ መረጃ ሰበሰብሁ፡፡ ሙሐመድ በሰጠው መረጃ መሰረት ወደሰርግ ቤቱ የሄድን ሰባት ሰዓት ላይ ነው፡፡ ሰርግ ቤቱ እኛ ካለንበት በግምት አራት ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል፡፡ መንገዱ የመኪና መንገድ ቢሆንም በእግር ጉዞ ሄድን፡፡ ቁልቁለት ስለሆነ ፍጥነትን መቆጣጠር በጣም አስቸጋሪ

ነበር፡፡ መንገድ ላይ እንደ እኛ ወደ ሰርጉ የሚሄዱ ሰዎች ይታያሉ፡፡ ከቦታው ከደረስን በኋላ ሙሐመድ ‹‹እንግባ›› አለ፡፡ እኔ ግን መጀመሪያ ከሰርጉ ባለቤቶች ፈቃድ እንዲጠይቅ ገፋፋሁት፡፡ ለባለቤቶችም ሆነ ለታዳሚው አዲስ ሰው በመሆን ግራ ማጋባት አልፈለግሁም፡፡ ሙሐመድ ወደሰርጉ ባለቤቶች በመሄድ መግባትና ማየት እንዲሁም መቅረፅ እንደምንፈልግ ነገራቸው፡፡ ባለቤቶቹ በደስታ እንድንገባና የምንፈልገውን እንድንቀርፅ ፈቀዱልን፡፡ ‹‹ይህማ የእኛን ስራ ማገዝ አይደለም እንዴ?›› በሚል ጥያቄያዊ መልስ ፈቃዳቸውን ሰጡን(በነገራችን ላይ በየትኛውም የመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃ ሰጪዎች ፎቶ መነሳት በጣም የሚወዱ መሆኑን አይቻለሁ፡፡ መረጃ አልሰጥም ብለው ያስቸገሩ ሰዎች እንኳን የፎቶ ካሜራ ሲያዩ ፎቶ እንዳነሳቸው ይጠይቃሉ)፡፡

ከሰርጉ ቤት ታዳሚ ሆነን እየበላን እየጠጣንና ግጥም እያዳመጥን ከአራት ሰዓት በላይ ቆየን፡፡ መጠጡ፣ ጠላ፤ ምግቡ የገብስ እንጀራ በክክ ወጥ ነው፡፡ ሰርጉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ነው(ከመረጃ ሰጪዎች እንደተረዳሁት በአካባቢው ብዙዎቹ ነዋሪዎች የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው)፡፡ አዝማሪዎቹን ሌላውን ሰው ሲያጫውቱ እየቀረፅን፣ እኛን ሲያጫውቱ ደግሞ እየሸለምን ቆየን፡፡ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ከሰርግ ቤቱ ወጥተን የመልስ ጉዞ ጀመርን፡፡ ስንመጣ እየተንደረደርን የወረድነው መንገድ አሁን አቀበት ሆኗል፡፡ ስለዚህ ቶሎ ቶሎ መጓዝ አስቸጋሪ ሆነ፡፡ ጊዜው ደግሞ በዚያው መጠን እየመሸ መንገዱ ጥቅጥቅ ወዳለ ጨለማ እየተለወጠ መጣ፡፡ መንገዱ አስፈሪ ገፅታ ያዘ፡፡ በተለይ መንገድ መሪዬ ሙሐመድ በአካባቢው ጅብ እንዳለና ልናገኝ እንደምንችል ስለነገረኝ በመፍራቴ ላበቴ እየተንጠፈጠፈ፣ ልቤ ልትከዳኝ እስከምትደርስ ድረስ እየተጣደፍን ለአንድ ሰዓት ያህል ተጉዘን አቀስታ ገባን፡፡ ቀጣይ ሰባት ቀናትን በአቀስታ ‹‹ከተማ›› ቡድኖችን በማደራጀት በተጠኝ ቡድን ውይይትና በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ስሰበስብና የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በ ‹‹ሲዲ›› ስገለብጥና ሳደራጅ ሰነበትሁ፡፡

አቀስታ ሆኜ ባገኘሁት መረጃ ወደ ወረኢሉ[22] መሄድ እንዳለብኝ ስላመንሁ ጥር ሃያ ስድስት ወደ ወረኢሉ ከተማ ሄድሁ፡፡ በወረኢሉ ከተማ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለሶስት

[22]ወረኢሉ ከደቡብ ወሎ ወረዳዎች ውስጥ አንዷ ስትሆን ከአዲስ አበባ በ492፣ ከባህር ዳር በ571፣ ከደሴ ደግሞ 91 ኪሎ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

ቀናት ቆይቼ ጥር ሃያ ዘጠኝ 2005 ዓ.ም. ወደ ደሴ ተመለስሁ፡፡ ከሰዓት በኋላ፣በማግስቱ ወደ ከድጆ[23] ለመሄድ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ሳመቻች ዋልሁ፡፡

በሚቀጥለው ቀን ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ አቶ አሰፋ ለገሰና አቶ ሙሐመድ ሁሴን ከተባሉ መንገድ መሪዎቼ ጋር አውቶብስ ተራ ተገናኘን፡፡ መኪና ማግኘት ከአንድ ሰዓት በላይ ወሰደብን፡፡ ያም ሆኖ አውቶብስ ተራ ውስጥ መኪና ማግኘት አልቻልንም፡፡ ስለዚህ ከዚያው አካባቢ የሚሰሩ ሰዎች በሰጡን መረጃ መሰረት ሰኞ ገበያ ወደሚባል አካባቢ ሄደን፤ ገራዶ፣ ዳባ መግለቢያ እያለ የሚጠራ በጣም ያረጀ ተሸከርካሪ አገኘን፡፡ እዛ ገብተን ተሳፈርን፡፡ ከመኪናው ማርጀት የሹፌሩ ስርዓት አልበኝነት (መኪና ውስጥ ሲጋራ ያጨሳል፤ መኪናውን እየነዳ ዞሮ ያወራል፣ ያለማቋረጥ ጮክ ብሎ ያወራል) ከአሁን አሁን ተገለበጥን በሚል ፍርሃት ውስጥ እንደተዘፈቅሁ ዳባ መግለቢያ የሚባለው ቦታ ደርሰን ወረድን፡፡ ከዚያ በኋላ በእግር የተያያዝነው መንገድ ሁለት ሰዓት ፈጀ፡፡ አንደኛው መንገድ መሪዬ አቶ አሰፋ ለገሰ ይዞን የሄደው የአባታችን ርስት ነው ወዳለው ቤተሰቦቹ ወደሚኖሩበት መንደር ነው፡፡ ሄደን የገባንበት ቤትም የትልቅ ወንድሙ አቶ ፈንታው ለገሰ ቤት ነው፡፡ በቤቱ ውስጥ ከፍተኛ መስተንግዶና አቀባበል ተደረገልን፡፡ መንገድ መሪዎቼ እኔን ካደረሱ በኋላ ለመልሱ ጉዞ ሊመጡልኝ ተነጋግረን በሚቀጥለው ቀን ወደ ደሴ ተመለሱ፡፡ እኔ ማረፊያ ቦታዬን የአቶ ፈንታውን ቤት በማድረግ ለአስራ አምስት ቀናት ከድጆ ውስጥ መረጃዎችን በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተጠኝ ቡድን ውይይት ከአቶ ፈንታው፣ ከባለቤታቸውና ከሌሎች በአካባቢው ከሚኖሩ ሰዎች ሰብስቤ ወደ ደሴ ተመለስኩ፡፡

የመልስ ጉዞው ግን የመሄዱን ያህል ቀላል አልነበረም፡፡ ወደ ደሴ ለመሄድ የተነሳነው ከሰዓት በኋላ ነበር፡፡ መንገዱ እየመሸ ሲመጣ አስጊ ነው በመባሉ መንገድ ቀይረን መጓዝ ጀመርን፡፡ መንገዱ በመንደሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን በጣም ረጅም ነው፡፡ በዚያ ላይ እየመሸ መምጣቱ መንገዱን አሰልቺና አስፈሪ አደረገብን፡፡ በተለይ መኪና መንገድ ከገባን በኋላ መኪና ልናገኝ አለመቻላችን ስቃያችን አበዛው፡፡ በአጋጣሚ ሰው ሳይጭን ባዶውን ሲሄድ አግኝተነው ወደ መንደር እንዲያስጠጋን የጠየቅነው ባለታክሲ 300 ሜ. ለማይሆን መንገድ አንድ መቶ ሃምሳ ብር አስከፈለን፡፡ ያም ቢሆን በተለይ አቶ አሰፋ እግሩ ማነከስ ጀምሮት ስለነበር የሚናቅ እገዛ አልነበረም፡፡ በዚህ ሁኔታ በአጠቃላይ አምስት ሰዓት በእግር ተጉዘን ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ደሴ ገባን፡፡ ደሴ ስንገባ ግን ለእኔና ለመሃመድ አስቸጋሪ ጉዳይ ገጠመን፡፡ ይኸውም የማደሪያ ችግር ነበር፡፡

[23]ከድጆ ደሴ ዙሪያ የሚገኝ ቀበሌ ነው፡፡

ደሴ እንደገባን የመጀመሪያ ተግባራችን አልጋ ፍለጋ ቢሆንም ደሴ ከሌላ ቦታ በመጡ ተሰብሳቢዎች፣ በርቀት ትምህርትና በብቃት ፈተና ተፈታኞች ተጨናንቃ ኖሮ አልጋ የሚባል ነገር ማግኘት አስቸጋሪ ሆነ። በመጨረሻ ከአንድ ሰዓት በላይ በወሰደ ፍለጋ በኋላ ከአንድ ‹‹ጭፈራ ቤት›› ውስጥ አልጋ ተገኘ። እያንዳንዳችን በአርባ ብር ክፍሎችን ተከራየን። ስለአልጋው መቆሸሽ፣ ስለሙዚቃው ረብሻ ምንም ማውራት አይቻልም። ሁሉም ነገር አስቸጋሪ ነበር። ብቻ መንገድ ላይ ከማደር የማይሻል ነገር የለም በሚል ክፍሎችን ተከራየናቸው። የጭፈራ ቤቱ ሙዚቃ እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ይጮህ ነበር። እኔ ያለሁበት ክፍል ወለል ለጭፈራ ቤቱ ጣሪያ ነው። ይህ ወለል መሃሉ ክፍተት ስላለው (በስብራት) ሙዚቃው እዚያው ያለሁ ያህል ይሰማኛል። በዚህ ሁኔታ ያለምንም እንቅልፍ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆኖ ሙዚቃው ተዘጋ።  እኔም ለመተኛት እንቅልፌን ማባበል ጀመርሁ። ይሁን እንጅ ከያዝሁት አልጋ ጎን ካለ ክፍል ‹‹አልጋውን የያዝሁ፣ እኔ ነኝ›› የሚል የሁለት ሰዎች የጠብ ድምፅ የሙዚቃውን ጩኸት ተክቶ በጩኸት ታጅቤ ሌሊቱ ነጋ።

በጠዋት ተነስቼ የተሻለ ፀጥታ ወዳለበት ቦታ ሄጄ ክፍል ተከራየሁ። የተሰማኝ ድካም ስራ ሊያሰራኝ ስላልቻለ ረፋዱን በሙሉ ተኝቼ አሳለፍሁና ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ እቅዴን መከለስ ጀመርሁ። በደቡብ ወሎ ዞን አያቸዋለሁ ያልኳቸው መንደሮች አይቼ ጨርሻለሁ። በተጓዝሁባቸው መስኮች የሰራኋቸውን ስራዎች ገመገምሁ። ጠንካራና ደካማ ያልኳቸውን ጎኖቼን መረመርሁ። የዕለት ውሎ ማስታወሻዬን አሟላሁ። ከዚህ በኋላ ደቡብ ወሎ ውስጥ ያለኝን ጉዳይ የጨረስሁ ስለሆነ የካቲት አስራ ስምንት 2005 ዓ.ም. ከሰሜን ወሎ ወረዳዎች አንዷ ወደ ሆነችው መቄት/ፍላቂት ወረዳ መጣሁ። ፍላቂት ከባህር ዳር 125 ኪሎ ሜትር ርቃ ትገኛለች። መቄትን በጥናቴ ለማካተት የመረጥሁበት ምክንያት አዝማሪዎች ብቻ የሚኖሩበትን መንደር የያዘች በመሆንዋ ነው። በመቄት ወረዳ አዝማሪዎች የሚኖሩበት ቀበሌ ‹‹ቀለባስ››፣ ልዩ መንደሩ «ክትክታ ለበስ» ይባላል። በዚህ ቦታ ከሚኖሩ አዝማሪዎች ጋር የአንድ ዓመት ቀጠሮ አለኝ። በሚቀጥለው ጊዜ እመጣለሁ ስል ለመንደሯ ሊቀመንበርና ለአንዳንድ ሰዎች ነግሬ ቀጠሮ አስይዣለሁ። እንግዲህ ዛሬ መቄት ስመጣ መድረሻ ቦታዬ ክትክታ መንደር ናት ማለት ነው። ነገር ግን  ወደ ክትክታ መንደር ለመሄድ መንገድ መሪ አስፈላጊ ነውና ለዚሁ ስል ባለፈው ዓመት ተዋውቂያቸው ጥሩ ጓደኛ ወዳደረግኋቸው የመቄት ወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት የባህላዊ የሙዚቃ ቡድን አባላት ሄድሁ። በቡድኑ ውስጥ ካሉት አባላት ውስጥ በተለይ ወንዶቹ መንገድ በማሳየት

እንዲያግዙኝ ነግሬያቸው አሸናፊ መኮንን የተባለ ወጣት ችግር የለውም በማለቱ በነጋታው ወደ ቀለባስ ለመሄድ ቀጠሮ ያዝን፡፡

የካቲት አስራ ዘጠኝ 2005 ዓ.ም. በጠዋት ተነስተን የተያያዝነው መንገድ ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ ተጠናቅቆ ቀለባስ ክትክታ ለበስ መንደር ደረስን፡፡ ባለፈው አመት የተዋወቅሁትን የቀበሌ ሊቀመንበር አገኘሁትና ከአካባቢው ሰዎች ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ በተለይ አንድ ቤተሰብ በቤት ውስጥ የፈለግሁትን ያህል ጊዜ እንድቀመጥ ፈቀደልኝ፡፡ የቤቱ ባለቤት አቶ መላክ ታረቀና ወይዘሮ ትርንጎ መለሰ የተባሉ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ ሁለት ሴትና አንድ ወንድ ልጆቻቸው አብረዋቸው ይኖራሉ፡፡ ሴቶቹ በለጥና ፀሃይ ወንዱ ደግሞ በሪሁን ይባላሉ፡፡ ይህንን ቤተሰብ ማረፊያዬ አድርጌ ለአንድ ሳምንት ክትክታ መንደር ውስጥ መረጃዎችን ስሰበስብ ቆየሁ፡፡

ቀጥሎ ያለው እቅዴ ወደ ሌሎች መንደሮች መሄድ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ  በሰሜን ወሎ የሚገኙ መንደሮችን ለማግኘት የሚያስሄደው የእግር መንገድ በጣም ፈታኝ እንደሆነ ይልቅስ የመጋቢት መድሃኒዓለም ለዚህ መንደር ዓመት በዓሉ በመሆኑ ያን ጊዜ እዚህ ብመጣ የሁሉንም አገር አዝማሪዎች እዚህ እንደማገኝና ካለአስፈላጊ ድካም እንደምድን፤ እግረ መንገዳቸውንም ለመድሃኒዓለም በዓል የጠሩኝ መሆኑን ነገሩኝ፡፡ እኔም ለመድሃኒያለም  ልመጣ ቃል ገብቼ ስለተደረገልኝ መስተንግዶና ግብዣ አመስግኜ የካቲት ሃያ ሰባት ወደ መቄት ተመለስሁ፡፡

ከክትክታ ለበስ መንደር ከተመለስሁ በኋላ ከፍተኛ ህመም ይሰማኝ ጀምሯል፡፡ በአፍንጫዬ ደም የሚፈስስ ከመሆኑ ሌላ በጣም ያስለኝ ጀመር፡፡ ከእለት እለት አቅሜ እየደከመ ሲመጣ ይታወቀኛል፡፡ በመረጃ በኩልም ቢሆን ከዚህ የበለጠ እዚህ መቆየት የሚያመጣው ለውጥ ያለ አልመሰለኝም፡፡ የማገኘው መረጃም ተደጋጋሚ እየሆነ መጥቷል፡፡ ስለዚህ አሁን ወደቤት ብመለስና ህክምና ባገኝ መረጃዬንም ብመረምር ይሻላል ብዬ በማሰብ ወደ ባህር ዳር ተመለስሁ፡፡ ከዚያም እስከ መጋቢት ሃያ አራት ድረስ ባህር ዳር ቆየሁ፡፡

መጋቢት ሃያ አምስት 2005 ዓ.ም. ለሶስተኛ ዙር የመስክ ስራ ከባህር ዳር ከተማ ተነስቼ ወደ መቄት/ፍላቂት መጣሁ፡፡ ዛሬ ወደዚህች ከተማ የመጣሁት ከአንድ ወር በፊት በክትክታ ለበስ መንደር የሚኖሩ ሰዎች ለመጋቢት መድሃኒያለም እንድመጣ በጠሩኝ መሰረት ነው፡፡ ወደዚህ ቦታ መምጣቴ ሁለት ጥቅም አለው፡፡ አንደኛው ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ አዝማሪዎች በአንድ ቦታ ተሰብስበው የማገኝ መሆኔ ሲሆን

ሁለተኛው ደግሞ በጥሪያቸው መሰረት ተገኝቼ ከሰዎች ጋር የምፈጥረው የመግባባት ስሜት ነው፡፡

በዚህ መሰረት በዚሁ ቀን ፍላቂት ከደረስሁ በኋላ ለነገ ወደ ክትክታ ለበስ መንደር ለመሄድ መንገድ መሪዬን በማግኘትና ለጋባዦቼ ስጦታ በማዘጋጀት ራሴን ለጉዞ አሰናዳሁ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ከሰዓት በኋላ ከአሸናፊ ጋር ወደ ክትክታ ሄድን፡፡ ዛሬም ልክ እንዳለፈው ቀን መንገዱ ሁለት ሰዓት ፈጀብን፡፡ ባለፈው ወደተስተናገድሁበት ቤት ሄድን፡፡ የቤቱ ባለቤት በደስታ ተቀበሉን፡፡ ወዲያውኑ ከቤት እንደገባን ‹‹ቶሎ በሉ የእግር ውሃ አምጡ›› ሲሉ አዘዙ፡፡ አንዲት ልጅ ውሃና ገበቴ ይዛ ቀረበች፡፡ እኛ ነን የምንታጠብ ብንል እንኳን እንቢ ብላ አሸንፋን እግራችን አጠበች፡፡ ቀጥላ ደግሞ ዛሬ እግርሽ በቅባት ካልታሸልሽ የወረድሽው ቁልቁለት ነገ አያንቀሳቅስሽም ብላ እግሬን በቅባት ታሽልኝ ጀመር፡፡ እኛ እግራችንን እስክንታጠብ እማማ ትርንጎ ወጥ ሰርተው ጨረሱና እግራችንን ታጥበን እንደጨረስን ምግብ ቀረበልን፡፡ ምግቡ እንደቀረበ ልብስ አጠባ የሄደችው ፀሃይ፤ ውሃ መቅዳት የሄደችው እህቷ በለጡ መጡና አንድ ላይ ሆነን መብላት ጀመርን፡፡ በለጡና ፀሃይ ባለፈው ጊዜ ሳያቸው ፀጉራቸው ረጃጅም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ተላጭቶ ገና መብቀል የጀመረ ፀጉር ከጭንቅላታቸው ላይ ይታያል፡፡

ፀጉራችሁን ለምን ተላጫችሁት? አልኳቸው፡፡

‹‹የወንድማችን ልጅ ሙታ›› አሉ፡፡ ሃዘኔን ገለፅሁ፡፡ በዚህ መሃል እማማ ትርንጎ ‹‹ይኸውልሽ ወንዶች ታስረውብን ሁላችንም በሃሳብ እየተወዘወዝን አንዳችንም እስካሁን እህል አልቀመስንም›› አሉኝ፡፡

‹‹ምን ሆነው ታሰሩ?››ስል ጠየቅሁ

‹‹ከዚህ መንደር የጣለውን እንጃ  ቦንብ ፈንድቶ የመንደሩን ወንድ ሁሉ ሰብስበው አስረውታል›› አሉኝ፡፡ አይዟችሁ ጠያይቀው ይፈቷቸዋል አያልሁ በማፅናናት ላይ እንዳለሁ አንድ ልጅ ከውጭ ወደ ቤት ገባና ‹‹በሪሁን ተፈትተን እየመጣን ነው ብሏል›› አለ፡፡ ከዚህ በኋላ በደስታ ብዛት መጯጯህ ሆነና የአንዱን ንግግር ሌላው አልሰማው አለ፡፡ የጎረቤት ልጆችም እየመጡ ደስታቸውን ሲገልፁ ቆዩ፡፡ ወዲያውም ፀሃይ የወንድሟን ስልክ ቁጥር ነገረችኝና ደውይለት የት እንደ ደረሱ ልጠይቀው አለች፡፡ ደወልሁላት፡፡ በሪሁን ‹‹እየመጣሁ ነው እያያ እንዳይወድቅብኝ ስለማዘግም ቀስ ብለን ነው የምንገባ›› አለ፡፡ ከዚህ ቤት ከበሪሁን ሌላ አባታቸው አቶ መላክ ታረቀኝም ታስረው ኑሯል፡፡ እሳቸው ከሰባ በላይ የሆናቸው ሽማግሌ ናቸው፡፡ ይህ ደስታ አንቺን ተከትሎ

የመጣ ነው ተባልሁ፡፡ እማማ ትርንጎ ደጋግመው ‹‹እርጥቧ ልጄ›› ሲሉኝ አመሹ፡፡ እነ በሪሁን ዘግይተው ቢገቡም ደስታው እንደገና አገርሽቶ ሁሉም ሲስቅና ‹‹እንኳን ደስ አለን›› ሲባል አመሸ፡፡ አቶ መላክ ከዚህ በፊት መጥቼ እያለ አይተውኝ ስለነበር የጠበቀ ሰላምታ ሰጡኝ፡፡ ጥሪያችን አክብረሽ መጣሽ ብለው ‹‹ምን አይነት ቁም ነገረኛ ልጅ ናት›› አሉ፡፡ ወዲያው እግሯ እንደገባ ደወላችሁ ሲባሉ ጊዜ ደግሞ ‹‹ግንባራሟ›› ልጄ አሉ፡፡ እኔ ያስፈታኋቸው እስኪመስል ድረስ ደጋግመው ይመርቁኝ ነበር፡፡ በዚህ መልኩ ስንጫወት አምሽተን ተኛን፡፡

መጋቢት ሀያ ሰባት 2005 ዓ.ም በጠዋት ተነስተን በቤቱ ውስጥ ያለን ሴቶች ሁሉ ወደቤተክርስቲያን ሄድን፡፡ ቤተክርስቲያኑ ከመንደሩ አጠገብ ነው፡፡ ገና ከጅምሩ ለእንግዳ መቀበያ የሚሆነው ወጥ ያልተሰራ በመሆኑ ቤተክርስቲያን ብዙ አንቆይም ስለተባለ ሁላችንም በተሎ ወደ ቤት ተመለስን፡፡ የስራ ክፍፍል ተደረገና እማማ ትርንጎ ክክ ጥደው እሱን ለማብሰል እንጨት መቆስቆስ፣ ቤት ማሰናዳት ጀመሩ፡፡ ፀሃይና በለጥ ውሃ ሊያመጡ ሄዱ፡፡ እኔ ሽንኩርትና ድንች መላጥ ጀመርሁ፡፡ እንዲህ እየተጋገዝን ወጥ ሰርተን ጨረስንና ቁርስ በላን፡፡ ቡናም እንዲሁም በመተጋገዝ ተፈልቶ ጠጣን፡፡ እኔና እማማ ትርንጎ ወጡን እየሰራን የተለያዩ ነገሮች ይነግሩኝ ነበር፡፡ ለምሳሌ ዛሬ መድሃኒያለም ዓመት በዓል ብቻ አይደለም፣ ማህበርም አለብኝ አሉ፡፡ ከነማን ጋር የሚጠጡት አልኋቸው፡፡

> *መድሃኒያለም የዚህ የአዝማሪው መንደር ታቦት ነው፡፡ ከዚህ ተራራውን አለፍ ብለሽ ትናንት ስትመጪ ከመኪና ከወረድሽበት ‹‹አርቢት›› የሚባል አገር አለ፡፡ ተዚያ ምን ምን የመሰሉ ሃብታም ወዳጆች አሉኝ፡፡ እነ መላክንም ዋስ ሁኖ ያስፈታልኝ ተዚያ የሚኖር ወዳጃችን ነው፡፡ ዛዲያ እነዚህ ሰዎች መዳኒያለም ማህበር አላቸው፡፡ ማህበርም ሲሆን፣ ሰርግም ሲሆን ዓመት ባልም ሲሆን እኛ ነን እየሄድን የምንዘፍንላቸው፡፡ አምና በሪሁን ይህችን ቆርቆሮ ቤት ይሰራልናል (ቤታቸውን እየጠቆሙ)፡፡ ቤታችን እናስመርቅ አልንና እኔ እናትሽ ሃብት ለሽ ነው፡፡ ምን የመሰለ ድግስ ደግሼ የማህበሩን ሰው ሁሉ ለጥቄ ጠራሁ፡፡ አክበሩኝ፡፡ መጡልኝ፡፡ መቼም ተይኝ ሲዘፈን፣ ሲደለቅ አደረ፡፡ መቼም ይህቺ ፀሃይ ገዳዬ ገዳዬ ያለች እንደሁ ድምጥዋ፣ የተደለቀች እንደሁ አንገቷ ሌላ ነው፡፡ የበሪሁንን መሰንቆ የሰማሽው እንደሁ ብረሪ ብረሪ ነው የሚልሽ መቼም ጉባይ ሲሆን ሰነበተ፡፡ ቤቱን መርቀውልኝ ሄዱ፡፡ እነሱም ደግሞ ኧረግ እነዚህ ሰዎች ብለው*

*አከበሩን፡፡ ከዚያ ወዲያም ደግሞ እንዲሁ መድሃኒያለም ሲሆን እንሄዳለን፡፡ ከመላክ ጋር ተነጋገርንና እንግዲህ ለእኛም መድሃኒለምን ስጡን አልን፡፡ አይሆንም አሉ፡፡ ‹‹እናንተ ከእንግዲህ ደክማችኋል ማህበር ግቡ ብለን አናስቸግራችሁም ይልቅ እየመጣችሁ መርቁን›› አሉን፡፡ እኛ ምንም የሚቸግረን ነገር የለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እናንተ እየመጣችሁ ካላገዛችሁን ሁልጊዜ እኛ ብቻ ይህንን ዳገት እየወጣን ሰልችቶናልና ከእንግዲህ እንቀራለን አልናቸው፡፡ እንደሱ ከሆነማ በሉ ግቡ ሰጥተናችኋል አሉ፡፡ እንግዲያው የመጋቢት መድሃኒያለምን ስጡን አልን፡፡ አሁን እሱን ስለተቀበልን ዛሬ ማህበርተኞቻችን ይመጣሉ፡፡ ዛሬ የገባው ማህበርተኛ ገና ሰኞ ነው የሚወጣ አለችኝ፡፡ ዛዲያ ዓመት ባሉን ሊያከብር የሚመጣው እንግዳም ስላለ እንግዳው ብዙ ነው አሉ፡፡*

እነዚህንና ሌሎችን ለጥናቴና ለዕውቀቴ የሚረዱ ጉዳዮችን እየነገሩኝ እንዲሁም በሌሎች የእለት ከእለት የህይወት ክንውኖች ውስጥ እየተሳተፉኩ ረፋዱ አለቀ፡፡ ከዚህ በኋላ ከተለያዩ ቦታዎች፣ ከግዳን፣ ዳውንት፣ ቡግና፣ ከወልድያ፤ ከሰቆጣ የሚመጡ እንግዶች፣ እንዲሁም በተለያየ ቦታ ለስራ ተበትነው የቆዩና ዛሬ ለመድሃኒያለም በዓል ቤተሰቦቻቸውን ሊጠይቁ የሚመጡ የዚያው የክትክታ ለበስ መንደር ጎልማሶች፣ ወጣቶች፣ ጥቂት ሴቶችም፤ እንደ የመጡበት ቅደም ተከተል ከእነሱ ጋር እየተዋወቅሁ ዋልሁ፡፡ እማማ ትርንጎ ‹‹ይኸው የእኛ ስራ ይስፋፋ እያለች ያንን አጥኝ ተብላ ነው የመጣች›› እያለች ታስተዋውቀኛለች፡፡ አባ መላክ ደግሞ ‹‹ልጄ ናት የዛሬ ወር መጥታ የመድሃኒያለም ነይ ብለን ብንጠራት ይኸው እሺ ብላ መጣች፡፡ እንዴት ያለች የተባረከች ልጅ መሰለቻችሁ? በዛሬ ጊዜ እንዲህ አይነት ሰው የት ይገኛል እንደ እኛ ቤት ሰው ቃሏን አክባሪ›› ይላሉ ለሄደ ለመጣው፡፡

ስድስት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ከበለጥ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ሄድን፡፡ ፀሃይ ቀድማን ሄዳ ስለነበር ስንደርስ እዚያው አገኘናት፡፡ ታቦት ወጥቶ ቁሟል፡፡ ቀሳውስት ዝማሬ እያቀረቡ ናቸው፡፡ ህዝቡ በሁለት አቅጣጫ ተከፍሎ ቆሟል፡፡ አንዱ ክፋይ እኛ የቆምንበት፣ ሌላው ክፋይ እነፀሃይ የቆሙበት ነው፡፡ በለጥ አንድ ነገር ተናገረች፡፡ ምን አልሽኝ አልኳት፡፡ ደንግጥ አለችና ‹‹አይ እድሌ እኔ እኮ አንቺ እንደእኛ እንዛታ መስለሽኝ በቋንቋ ማውራቴ ነው፡፡ እረስቼሽ›› አለች፡፡ ‹‹እኮ ምንድን ነው ያልሽ?›› አልኳት፡፡ አልነግርሽም አለች፡፡ እንድትነግረኝ አግባባኋት፡፡ ‹‹ከዚህ ከባላገሮች ጋር አንቁም ነይ ወደ ዘመዶቻችን እንሂድ›› ነው ያልሁሽ አለች፡፡ ወደ የት ነው እንድንሄድ

የፈለግሽው አልኳት ወደዚያ አለች፡፡ እነፀሃይ ወደቆሙበት እየጠቆመች፡፡ እኛ የቆምን ከባላገሩ ጋር ነው አለች፡፡ ታዲያ እንሂድ? አልኋት፡፡ አወ! ተያይዘን ሄድን፡፡ የመዘምራኑ ዝማሪ አብቅቶ ታቦቱ ወደ ማደሪያው ለመግባት ሲንቀሳቀስ ዘፈን ተጀመረ፡፡ መሰንቆ ይዘው የቆሙ አዝማሪዎችም በዘለሰኛ ታቦቱን እየመሩ አየኋቸው፡፡

ታቦቱ ወደ ማደሪው ከገባ በኋላ ህዝቡ ወደ አንድ ቦታ ተጉዞ ከዛፍ ስር ሲያርፍ እኔም ከበለጥ ጋር ወደዚያው ሄድሁ፡፡ ጠላና እንጀራ መታደል ጀመረ፡፡ የምግቡ ስርዓት ካለቀ በኋላ ግማሹ ሰው ወደቤቱ ሲሄድ ቀሪው ዘፈን ጀመረ፡፡ ከዚያ በኋላም አንዱ ሲሄድ ሌላው እየመጣ ዘፈኑ ቀጠለ፡፡ በዚህ መሃል በድምፅና በትክሻ እንጅ መሰንቆ ይዞ የሚዘፍን ሰው አላየሁም፡፡ መሰንቆ አይመታም ወይ ብዬ በለጥን ጠየቅኋት፡፡ አይ አይመታም፡፡ ባላገሩም እንዛታውም በአንድ አይነት ነው የሚያከብር አለች፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ነገሮች ተደጋጋሚ እንጅ አዲስ ነገር የሌላቸው መሆኑን ስላየሁ ወደ ቤት ሄድሁ፡፡

እቤት ስደርስ ቤቱ በእንግዳ ተሞልቷል፡፡ ቅድም የተዋወቅኋቸውና አዳዲስ ሰዎችም አሉበት፡፡ እማማ ትርንጎ በይ ስላንቺ ስነግራቸው ነው የመጣሽ እነዚህ ሰዎች ናቸው እንግዲህ ታሪክ የሚነግሩሽ እነሱን ጠይቂ ፡፡ ‹‹ይህንን ሁሉ ተራራ ያላበሳዋ የመጣች ለዚህ ብላ ነው፣ አደራ የምትላችሁን ንገሯት›› አሉ፡፡ ከመሀላቸው ተቀምጬ በእንግዳ ክብር የሚበሉትን እየበላሁ፤ የሚጠጡትን እየጠጣሁ መረጃዎችን ሰበሰብሁ፡፡ መረጃውን የሚሰጡኝ ሰዎች በእድሜ ገፋ ያሉና በቁጥር ሶስት ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች እየተጋገዙ የሚያውቁትን ሲነግሩኝ ከቆዩ በኋላ ንግግራችን ሌሎችን ሰዎች እየሳበ ውይይቱና ጨዋታው ሙሉ ቤቱን ተቆጣጠረው፡፡ በቤቱ ውስጥ አዝማሪ ያልሆኑት የእማማ ትርንጎ ማህበርተኞች ከተለያዩ ቦታዎች የመጡና የሰፈሩ ነዋሪ የሆኑ አዝማሪዎች ነበሩ፡፡ በየመሃሉ አዲስ ጠላ ሲቀርብ ከሚያቋርጠው ምርቃት በስተቀር ውይይቱ ምሽቱን ሁሉ የቀጠለ ነበር፡፡

መጋቢት ሃያ ስምንት በተለይ ከእንግዳነቴ ይልቅ ቤተኛነቴ ጎልቶ ነበር፡፡ ለእንግዳ ማስተናገጃ የሚሆነውን ወጥ የመስራት ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ በእኔ ላይ ተጣለ፡፡ የበለጥና የፀሃይ ዋና ስራ ውሃ መቅዳት ነው፡፡ እማማ ትርንጎ ጠላ ታዘጋጃለች፡፡ ወጥ ሰርቼ ከጨረስሁና እንግዳው ምግብ ከበላ በኋላ ‹‹ነይ አረፍ በይና አውጊ›› በሚለው የእማማ ትርንጎ ግብዣ መሰረት ወደቤት እየገባሁ ጥያቄዎቼን እጠይቃለሁ፤ የህይወት ክንውኖችን አስተውላለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለወጣት ሴትና ወንድ አዝማሪዎችም የቡድን ውይይት አዘጋጅቼ መረጃዎችን ሰበሰብሁ፡፡

የመጋቢት ሃያ ዘጠኝ ውሎዬም እንደ ሃያ ስምንቱ ነው፡፡ ቡድኖችን በማደራጀት መረጃዎችን በመሰብሰብና፣ የየእለት ክንውኖችን በመከታተል ዋልሁ፡፡ በዚህ ቀን የተፈጠረው የተለዩ ነገር አባ መላክ ‹‹ይህች ልጅ እኛን አክብራ ከሩቅ ሃገር ድረስ መጥታለች፡፡ ከመጣች በኋላ ደግሞ ከልጆቼ ከነትርንጎ ሳትለይ ወጥ እየሰራች እየታዘዘች መዳህኒያለምን አክብራልኛለችና መርቁልኝ›› በሚለው ጥያቄያቸው መሰረት በቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ትልልቅ ሰዎች ሁሉ የተሰጠኝ ምርቃት ነው፡፡ በዕድሜ ተዋረድ ከታች ወደ ላይ ብዙ ሰዎች መረቁኝ፡፡ ምርቃቱን ከሁሉም ሰው ፊት ለፊት ጎንበስ ብዬ ሁለት እጆቼን ወደፊት ዘርግቼ አሜን እያልሁ ተቀበልሁ፡፡ ይህንን አባ መላክ ምግብ በቀረበ ቁጥር ‹‹ተነስ ተመረቅ›› እየተባሉ ሲያደርጉ በተደጋጋሚ አይቼ ነበር፡፡

መጋቢት ሰላሳ በቤቱ ውስጥ ከነበሩት እንግዶች ውስጥ አብዛኞቹ ቁርሳቸውን እየበሉና ቡና እየጠጡ ወደ የቤታቸው ለመሄድ ተሰናበቱ፡፡ የሚሄዱት ሰዎች አስተናጋጆቻቸውን ሲሰናበቱ እኔንም አይረሱም ነበር፡፡ ሁሉም ቤተኞቹን በሚሰናበቱበት ሁኔታ ‹‹ደህና ሁኚ፣ ቸር ይግጠመን›› ይሉኝ ነበር፡፡ በተለይ ማህበርተኞቹ ስለሄዱ በቤቱ ውስጥ የቀረነው ሰዎች ጥቂቶች ነበርን፡፡ በመጀመሪያ ጉብኝቴ ያላየኋቸው ከዳውንት፣ ከግዳንና ቡግና የመጡት የእማማ ትርንጎና የአባ መላክ ሶስት ሴት ልጆቻቸውና የልጅ ባሎቻቸው ከሶስት ህፃናት ልጆች ጋር ከሩቅ የመጡ እንግዶች ሲሆኑ ሌሎች የቤቱ ልጆችና የጎረቤት ልጆች ብቻ በቤቱ ውስጥ ቀረን፡፡ ስለዚህ ዛሬ እንግዳ ስለሌለ ረጅሙን ጊዜ በስራ ሳይሆን እኔ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እነሱ ደግሞ መልስ በመስጠት አሳለፍነው፡፡ በተጨማሪም ከጎረቤት ቤቶች በተደረገልኝ የቡና ጠጪ ግብዣ ከጎረቤት ቤቶች እየሄድሁ፤ ቡና ስጠጣና አኗኗራቸውን ስመለከት ዋልሁ፡፡

ክትክታ ለበስ አካባቢ በቆየሁባቸው ቀናት ቤተክርስቲያን ውስጥ ከነበረው በስተቀር በመኖሪያ ቤቶች ዘፈን አልነበረም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እኔ ወደዚህ ከመምጣቴ ከሁለት ሳምንት በፊት የእነማማ ትርንጎ የልጅ ልጅ በመሞትዋ የተነሳ ሃዘን ስለሆነ ነው፡፡ ‹‹አምና ይህንን ጊዜ የነበረ ዘፈን ብታይ ጉድ ነበር፡፡ ለመሰንቆ ቁንጥ እየወጣለት፣ ለድለቃ ቁንጥ እየወጣለት ነበር፡፡ ዘንድሮ አልሆነም፡፡ በሰላም ካደረሰን ከርሞ ታየዋለሽ›› ብለውኛል፡፡ ስለዚህ ከዘፈን ውጪ ያለውን ህይወት እያየሁ ሰንብቼ ነገ ወደ ቤቴ ለመመለስ መወሰኔን አሳውቄያለሁ፡፡ በዚህ የተነሳም ወደዚህ ስመጣ አብሮኝ የመጣውንና በበነገታው ተመልሶ ሄዶ የነበረውን አሸናፊን ስልክ ደውዬ ስለነገርሁት ዛሬ መጥቷል፡፡ ቀኑ መሽቶ ሁላችንም በምንተኛበት መደብና መሬት ላይ ተጋድመን እየተቀባለድን እንሳሳቃለን፡፡ እኔ ነገ ልሄድ ስለሆነ መተኛታችንን ትተን እየተጫወትን

ነው፡፡ አራት ሰዓት አካባቢ ሲሆን የእማማ ትርንጎ ልጅ በሪሁን ‹‹አስቴርዬ መሰንቆ አይሰማሽም›› አለኝ፡፡ ሁላችንም ፀጥ አልን፡፡ ራቅ ካለ ቦታ የመሰንቆ ድምፅ መጣ፡፡ ‹‹አዎ ይሰማኛል ከየት መጣ?›› አልሁት፡፡ እስቲ ቆይ አለና በጨለማው ውስጥ የስልክ ባትሪውን አብርቶ ተነሳ፡፡ ከዚያም ድምፁ በሚመጣበት አቅጣጫ ያለውን መስኮት ከፈተ፡፡ አሁን የመሰንቆው ድምፅ ጎልቶ ተሰማ፡፡ ‹‹ከነተስፋ መንደር ነው›› አለ በሪሁን፡፡ ‹‹ምንድን ናቸው›› አልሁት፡፡ ‹‹ጎረቤት ናቸው፡፡ አናጠብቀውም እንጅ ዘመድም ነን›› አለ፡፡

‹‹ታዲያ ምን ሆነው ነው አሁን የሚዘፍኑ›› አልሁት

‹‹ሰርግ ሳይሆን አይቀርም››

‹‹እንሂድ›› አልሁት፡፡

‹‹እውነትሽን ነው?›› አለኝ፡፡

‹‹አዎ! በሪሁን የመሰንቆ ጨዋታ ሳላይ ልሄድ ነው ብዬ ነበር፡፡ አሁን ግን ካጋጠመኝ ልይ›› አልሁት፡፡

‹‹ተነሽ እንሂድ›› አለኝ፡፡ አሸናፊም ከተኛበት ተነሳና መሰንቆ የሰማንበትን አቅጣጫ ተከትለን ሄድን ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው፡፡ በሪሁን ባትሪ፣ አሸናፊ ደግሞ ስልኩን አብርቶ ወዳልተጠራንበት ሰርግ ሄድን፡፡ እውነትም ዳስ ተጥሎ፣ እድምተኛ ተሰብስቦ፣ ጠላ እየተጠጣ መሰንቆ እየተመታ፣ ሰው ግጥም እየሰጠ አየን፡፡ በሪሁን የቤቱን ባለቤት አስጠራና ይህች ልጅ ሰርግ ልይ ብላ ነው፡፡ እንግዳችን ናት አለው፡፡ ችግር የለም ግቡ ተባልንና ሙሽሮች ወደ ተቀመጡበት ቦታ ተወስደን ቦታ ተሰጠን፡፡ ሙሽራዋ ሽፍንፍን ብላ ተቀምጣለች፡፡ ከጎኗ መሰንቆ የሚመታ ልጅ አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ወጣቶች ጋቢ ለብሰው ተቀምጠዋል፡፡ ሙሽሮች የተቀመጡበት ቦታ ከፍ ያለ ነው፡፡ ወረድ ብሎ ወደታች እድምተኛው አለ፡፡ እኛ ሙሽሮች ካሉበት ከፍ ያለ ቦታ ተቀምጠናል፡፡ ከገባን በኋላ እዛ ቤት ካየኋቸው ሰዎች ውስጥ ብዙዎችን የሙሽራዋን እናት የሆነችውን ባለሰርግ ሳይቀር ከእነማማ ትርንጎ ቤት ተዋውቄያቸዋለሁ፡፡ እንግዳ አልሆኑብኝም፡፡ በዚህ መሃል ግን ሙሽራውን መለየት አልቻልሁም፡፡ ከጎኔ የተቀመጠውን በሪሁንን፣ ‹‹ሙሽራው የት አለ?›› ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ስቆ ከጨረሰ በኋላ ‹‹መሰንቆ የሚመታው ነው›› አለኝ፡፡ ለራሱ ሰርግ መሰንቆ የሚጫወት ሙሽራ በማየቴ በጣም ተገረምሁ፡፡ ከዚህ ሌላ የገረመኝ ነገር ደግሞ በሰርግ ቤቱ የሚገጠሙት ግጥሞች ናቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የሚሰጧቸው ግጥሞች ከዘፈንነት ይልቅ ምሾነት ባህርይ

አላቸው፡፡ ግጥሞች የተለያዩ ቢሆኑም አንድ ይዘት አላቸው፡፡ በቤቱ ውስጥ የሞተውን የቤቱን አባ ወራ እየጠሩ ዛሬን እንኳን ብቅ ብለህ ልጅህን ዳር ይላሉ፡፡ በእኛም በስማችን ግጥም እየተገጠመልን፣ እየጨፈርንና፣ እያጨበጨብን እስከሌሊቱ ሰባት ሰዓት በሰርግ ቤቱ ቆዬን፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ምንም እንኳን ጨዋታው ባይቀዘቅዝ እኔን በጣም ስለደከመኝ መተኛት በመፈለጌ ወደቤት ተመለስን፡፡

ሚያዚያ አንድ ከአሸናፊ ጋር በጠዋት ተነስተን ለጉዞ ራሳችን አዘጋጀን፡፡ ትንሽ ከቆየን የሚቀትረውን ፀሃይ በማሰብ በጠዋት ነው ከቤት ለመውጣት ያሰብነው፡፡ ይሁን እንጅ ‹‹ዛሬ ሁሉም ሰው ስለሚሄድ አንቺና እኔ ብቻ ነን የምንሆን፣ እንጼያው ስትደክሚ ሰንብተሽ ሳታርፊ አትሂጅ፣ ያ ካልሆነ ደግሞ ትንሽ አርፍጂ ከጓሮ ነጭ ሽንኩርትና ቃሪያ ይቆረጥልሽ ይዘሽ ሂጅ›› የሚለው የእማማ ትርንጎ ልመናና እኔ ደግሞ መሄድ ያለብኝ መሆኑን ለማስረዳት እናደርገው የነበረው ውይይት ጠዋቱን ትንሽ አስረፈደው፡፡ ያም ሆኖ ለመምጣት የወሰንን በመሆኑ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ወጥተው ደህና ሁኑ ብለው ሸኙን፡፡ እማማ ትርንጎ ብዙ መረቁኝ፡፡ ‹‹እግር መንገደኛ ነውና አምላክ ያለ ቀን እንገናኛለን፡፡ ደግመን ካልተገናኘን ግን ባላወቅሁሽ ጥሩ ነበር›› ብላ እንባዋን እየጠረጉ ወደ ቤት ተመለሱ፡፡ ፀሃይ ከሁሉም ቤተሰብ ተለይታ ረጅም መንገድ ድረስ ተከትላ ሸኘችን፡፡ ፀሃዩ እየቀተረ ስለመጣ ሳይሆን አይቀርም መንገዱ በጣም አስቸጋሪ ሆነብኝ፡፡ ባለፈው በሶስት ሰዓት የተጓዝሁት መንገድ አሁን ከአራት ሰዓት በላይ ጨርሶ እንደምንም አርቢት ደረስን፡፡ ከዚያም ከአርቢት ቀለባስ፤ ሚያዚያ ሁለት ባህር ዳር፣ ሚያዚያ ሶስት ደግሞ አዲስ አበባ ገባሁ፡፡

የመስክ ስራውን ከታህሳስ እስከ መጋቢት በአጠቃላይ ለአራት ወራት ያከናወንሁ ሲሆን በቀረበው መንገድ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ተጠንተውና ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡ ትንታኔው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6. የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ይህ ምዕራፍ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ ያለውን ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር ይቻል ዘንድ የቀረቡ ለወሎ አዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች ምንድን ናቸው? በዘፈን ክዋኔው ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ልምዶች ምን መልክ አላቸው? በአዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች ምንድን ናቸው? በአዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ ለተከሰቱ ለውጦች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው? የአዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ከመስክ የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች በተገኙ ፅንሰ ሃሳቦችና እና በክዋኔያዊና ማርክሳዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች እየተገናዘቡ የተተነተኑበትና የተብራሩበት ነው፡፡ በምዕራፉ የቡድኑ ተከታታይ ልምዶችና ለውጥ ለየብቻ የታዩ ሲሆን የአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸውን ለመጠበቅ ሲባል ተከታታይ ልምዶች በፊት ለውጦች ደግሞ ተከትለው ቀርበዋል፡፡

### 6.1. ተከታታይ የኑሮና የዘፈን ልምዶች በወሎ አዝማሪዎች ህይወት

Sims and Stephens (2005) እንዳሉት ተከታታይነት በቡድኖች ውስጥ ያሉ ልምዶች መቀባበልን የሚመለከት የፎክሎር ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ልምድ ደግሞ የአንድን ቡድን ዕውቀትና የዕውቀቱ መተላለፊያ መንገዶችን የሚገልፅ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ልምድ የአንድ ቡድን ዕውቀትና የዕውቀቱ መተላለፊያ መንገድ ሲሆን የሚችለውና የቡድኑን ማንነት ሊፈጥርና ሊያጠነክር የሚችለው ተከታታይነት ሲኖረው ነው፡፡ ይህም ተከታታይነትን የልምድ ዋና ባህርይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ርዕስ ስር የሚነሱት ነጥቦች የወሎ አዝማሪዎች ‹‹አዝማሪነት በኢትዮጵያ የተከሰተበት ነው›› ከሚሉት ታቦተ ፅዮንን ከእስራኤል አጅቦ መምጣት አፈ ታሪካዊ ዘመን ጀምሮ አሁን ድረስ ያሉ የቡድኑን ማንነት የፈጠሩና አጠናክረው የኖሩ ተከታታይ ልምዶች ናቸው፡፡ ልምዶቹ በአዝማሪዎች ኑሮ እንዲሁም በዘፈን ስራቸው ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ በዚህ ስራ አስቀድሞ ‹‹በኑሮ ቀጥሎ በዘፈን ውስጥ ያሉ›› ተከታታይ ልምዶች በሚል ቅደም ተከተል ሁለቱን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 6.1.1. ለአዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች

በዚህ ጥናት ውስጥ ኑሮ የሚለው ቃል የሚገልፀው በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች እንደማህበረሰብ ተሰባስበው ሲኖሩ ህይወታቸውን የሚመሩበትን አኳኋን ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ርዕስ ስር የተተነተኑትና የተብራሩት መረጃዎች አዝማሪዎች ለዘመናት እየኖሩት ባለው ህይወት ውስጥ ለቡድኑ መለያ ሆነው የኖሩ ተከታታይ ልምዶችን የሚገልፁ ናቸው፡፡

በፎክሎር እሳቤ ውስጥ ተከታታይነት የአንድን ልምድ በጊዜ ሂደት ውስጥ ሳይቋረጥ መጓዝ የሚገልፅ ፅንሰ ሃሳብ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ Tolken(1996)፡፡ ይህ ጥናትም ‹‹ለወሎ አዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች›› በሚለው በዚህ ርዕስ ስር የሚያብራራው ‹‹ለወሎዬ አዝማሪዎች›› መገለጫ ሆነው ለዘመናት የዘለቁ የቡድኑ ልምዶችን ነው፡፡ እነዚህ ልምዶች ቡድኑን ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል እንዲሁም በሌላ አካባቢ ከሚኖሩ አዝማሪዎች የሚለዩ ናቸው፡፡ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

#### 6.1.1.1. አሰፋፈር

በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች ‹‹ዘፋኝነትን›› ምክንያት አድርገው ‹‹ፎክ ቡድን›› የመሰረቱ የወሎ ማህበረሰብ አካል ናቸው፡፡ ይህ የማህበረሰብ ክፍል ከሌላው ማህበረሰብ የሚለዩ በርካታ ባህርያት አሉ፡፡ ከእነዚህ ባህርያት ውስጥ ከሌላው በተነጠሉ መንደሮች ውስጥ መኖር አንደኛው ነው፡፡ የአዝማሪዎች በተነጠሉ መንደሮች የመኖር ልማድ ምክንያቱ የአገር አስተዳደር ስርዓት እንደሆነ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ የፅሁፍና የቃል መረጃዎች እንደሚሉት ኢትዮጵያ ትተዳደርበት በነበረው የፊውዳል ስርዓት እያንዳንዱ መንደር፣ ጭቃ ሹም[24]፣ ምስለኔ[25]፣የሚባሉ አገር የሚያስተዳድሩ ሹሞች ነበሩት፡፡ በዚህ ሁኔታ እያንዳንዱ ምስለኔና ጭቃ ሹም ወደተሾመበት አካባቢ ሲሄድ በየሙያቸው አገልግሎት የሚሰጡ አጃቢዎች ይኖሩታል፡፡

---

[24]በባላባቱ ስርዓት በየአካባቢው በህዝብ ተመርጦ ከአጥቢያ ዳኛና ከመልከኛ በታች የሚያለግል የመንግስት ሹም (የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት 1993፣ 568)፡፡

[25]በባላባቱ የመሬት ስሪት ወቅት መንግስት ወይም መልከኛ የሚወክለው ስልጣኑ ከጭቃ ሹም በላይ የነበረ ሹምን ነው፡፡ የሹሙ ስልጣን በመሬት ላይ ሲሆን ለአንድ መንደር አስተዳዳሪነት የሚወከል ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት 1993፣ 78) ፡፡

በወሎ መንደር ለማስተዳደር ተሾሞ የሚሄደውን ምስለኔ ከሚያጅቡ ባለሙያዎች ውስጥ አዝማሪ አንዱ ነው፡፡ የአዝማሪ አጃቢነት የሚፈለገው ሹሙን በዘፈን እንዲያገለግል ነው፡፡ የሚመረጠው በጥሩ ተጫዋችነቱ (በድምፁ ማማር፣ በመሰንቆ ጨዋታና በግጥም ችሎታው) ነው፡፡ ሹሙ አዝማሪውን ከመረጠው በኂላ ወደ ሹመት አገሩ አስከትሎት ይሄዳል፡፡ ከዚያም የሚያስተዳድረው ‹‹አገር›› ይሰጠዋል፡፡ በተሰጠው አገር ከሌሎች ገንጠል ብሎ የራሱን ቤተሰብ የሚያኖርበት መንደር ይመሰርታል፡፡ በመንደሩም ዘመዶቹንና በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ሌሎች አዝማሪዎች ያሰፍራል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከድጆ ውስጥ ቆላ ገራዶ የተባለው ቦታ እንዴት የአባታቸው ርስት ሊሆን እንደቻለ የገለፁት አቶ አሰፋ ለገሰ[26] የተባሉ አዝማሪ ‹‹አባቴ ታዋቂ አዝማሪ ነበር፡፡ . . . ቆላ ገራዶ የእኛ ሃገር ነው፡፡ ተሰጥቶን››፡፡ ሲሉ መንደሩ እንዴት የቤተሰቡ ርስት ሊሆን እንደቻለ ይገልፃሉ (11/04/2005 ዓ.ም ከተደረገ ቃለ ምልልስ፣ ከድጆ)፡፡ ይህንን ሃሳብ ማርዬ የሚኖሩ አዝማሪዎችም ይጋሩታል፡፡ ጉዳዩን የሚከተለውን በማለት ይገልፁታል፡፡

> እንትን ላምጣልሽ ዋሂሎን ሂጅና ጊጣን ፤ በጊጣ ሰገራትን ትተሽ ውረጅ፡፡ ጥርጊያ ግቢ እንትና ማነው ገቢ ዚሃ፣ ዚሃ ግቢና ሂጅ፣ ደላንታን ክፈይ፣ ከዚያ ግራ ካሱን ተቃኝ፤ ዙሪና የተቀረውን ትተሽ ሂጅ፡፡ እንትና ሚባል አለ ከውርጌሳ በላይ ግብሻት፤ ግብሻት ትመጪና ወዲያ እንትና የሚባል አለ፡፡ ቁንጥሮ አለ፡፡ ቁንጥሮን ውረጅና ሊሙ ወደእኛ ነይ፡፡ ሊሞ ውረጅና ሚሌ ግቢ ከዚያ ወዲህ ያለው የእኛ ግዛት ነው (ብርሃን ትኩና ማስረሻ ፈንታው፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

ጥቅሱ እያንዳንዱ የአዝማሪ ቤተሰብ የራሱ የቦታ ክልል እንዳለው ይገልፃል፡፡ ለየክልሉም በመሪነት የሚያስተዳድር አለቃ ነበረው፡፡ በዚህ የተነሳ የየተሾሙበት አካባቢ አለቅነታቸው እስካሁን ድረስ የሚዘከር አዝማሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡

---

[26] አቶ አሰፋ ለገሰ መረጃ የሰጡባቸው የተለያዩ ቦታዎች በድርሳኑ ውስጥ ተጠቅሰዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እሳቸው መረጃ ሰጪ ብቻ ሳይሆኑ መንገድ መሪዬ ሆነው በተለያዩ ቦታዎች አብረን ስለተጓዝንና መረጃዎች በተገኙባቸው ቦታዎች ስለተገለፁ ነው፡፡

በተሁለደሬ፣ አሊ ሙሳ፤ በቃሉ፣ ይርጋ ሚኒሊክ (ባለቃው ነው ምኒሊክ የተባለ እንጅ፣ ይርጋ ግዛው ነው) ፤ ከድጆ፣ ለገሰ እንዳለው (የእነማሪቱ አባት)፣ በየጁ፣ ይርጋ ጧፉ፤ በጊራራ/ወልድያ፣ ተሾመ ክብረት (የአሰፋ አባተ አጎቱ) [27]እንዲያውም የሁሉ አለቃ ሆኖ ነበር። ወልድያ ይሁን እንጅ ሁሉንም ይገዛዋል። እስተኛም ተሹሞ ነበር። ተሹሞ ደሴን መገናኛ አድርጎት ነበር። ለየብቻችን የነበርነውን አንድ ላይ አድርጎን ነበር፤ ደረቅ ወይራ መኩሪያ ድጋፌ፤ ወገሳ፣ ሹመት ሺበሺ፣ ገራዶ፣ አበበ ሙሔ ይባሉ ነበር (ብርሃን ትኩና ሌሎች፣ በ10/05/2005 ዓ.ም፣ ጠጠር አምባ ላይ በተካሄደ የተተኳሪ ቡድን ውይይትና፤ ሰኢድ ኢብራሂም፣ 14/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ፣ ከተደረገ ቃለምልልስ )።

መረጃው ወሎ ውስጥ የሚኖሩ አዝማሪዎች የራሳቸውን መንደር መስርተው የሚኖሩና የመንደሩ ሃላፊ እንደነበረው፣ ሁሉን መንደሮች ደግሞ ጠቅልሎ የሚያስተዳድር አለቃ እንደነበረ ይገልፃል። ከዚህ ሁኔታ በአዝማሪዎች አኗኗር ውስጥ የስልጣን ተዋረድ የነበረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የመንደሩ አለቃ የሆነው አዝማሪ በተሾመበት ቦታ ዋና ስራው ጌታውን ማጫወትና የምስለኔው ወኪል በመሆን ምስለኔው ከሚያስተዳድረው የአካባቢው ማህበረሰብ ግብር ሰብስቦ ለአለቃው መላክ ነው። ግብሩን ከስሩ ባሉ ሌሎች አዝማሪዎች አማካኝነት (እነሱን በመላክ) ይሰበስባል። ለአገልግሎቱ ከሰበሰበው ግብር የድርሻውን ይወስዳል። በዚህ መንገድ የአንድ መንደር አለቃ ለአንድ አካባቢ ገዥ ሲሆን በዚህ መንደር መዝፈንና ገቢ ማግኘት የሚችሉት በእሱ ስር የሚተዳደሩ ቤተሰቦቹ ብቻ ናቸው።

---

[27]አሰፋ አባተ በድሮው አጠራር ወሎ ክፍለ ሃገር፣ የጁ አውራጃ፣ ጉባ ላፍቶ ወረዳ ውስጥ የተወለደ በወሎ ታዋቂ አዝማሪ ነው። አሰፋ በተወለደ በ28 ዓመቱ በ1955 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለየ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ዝናው በወሎና በሌላውም የኢትዮጵያ አካባቢዎች እንደገነነ ነው። በተለይም ‹‹የማትበላ ወፍ ተይዛ በጭራ›› በሚል ዘፈኑ ይታወቃል። በወሎ የሚገኙ አዝማሪዎች የአሰፋ አባተን ጨዋታዎች ‹‹እኔ የአሰፋ አባተን ጨዋታ ሳይቀር እጫወተዋለሁ ‹‹በሚል ገለፃ እንደችሎታ መለኪያ ይጠቀሙባቸዋል። ተሾመ ክብረት የአሰፋ አባተ አጎት ናቸው። አሰፋን ያሳደጉት እሳቸው ነው። እኒህ ሰው በጠቅላላው የወሎ አዝማሪ ሁሉ አለቃ እስከመሆን ያደረሳቸው የአዝማሪነት ችሎታ የነበራቸው ሲሆን አሰፋ የመሰንቆን ቃናና የድምፅን ለዛ ለይቶ ለማወቅና ዝነኛ የመሰንቆ ተጫዋች ለመሆን የበቃው ከአጎቱ በወረሰው ልምድ እንደሆነ ይነገራል። በየመኳንንቱና መሳፍንቱ ቤት አጎቱን ተከትሎ ይዞር ስለነበር በአዘፋፈን ረገድ ጥሩውን ከመጥፎው ለይቶ የማወቅ ችሎታን አዳብሯል ይላሉ መረጃ ሰጪዎች።

ከዚህ ቤተሰብ ውጭ የሆነ ማንም ሰው ከዚህ ክልል ገብቶ ሲዘፍን ቢገኝ ይቀጣል፡፡ ይህንን ጉዳይ አዝማሪ መረጃ ሰጪዎች ‹‹ማንም አዝማሪ አይገባም ከእኛ በስተቀር›› (አሰፋ ለገሰ፣ 11/04/2005 ዓ.ም፣ ከድጆ)፣ ‹‹ከኩራማሶ ጀምሮ ወንዙን ይዞ የእኛ ግዛት ነው፡፡ አያታችን በዘመቻ ሙተዋል፡፡ በውጫሌ፡፡ መሬት አድርገነው ኖርን፡፡ መሬት አድርገነው ስንኖር አባቶቻችን ሞቱ፡፡ ደርግ ሲመጣ ነው እንጅ ሌሎችን አናስገባቸውም ነበር፡፡ በሃይለስላሴ ጊዜ እኛ ነበርን ሃላፊዎች፡፡ ያለቦታው የመጣውን እናስገለብጠው ነበር (ብርሃን ትኩና ሌሎች፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ በ12/05/2005ዓ.ም፣ ማርዬ) በማለት ሲገልፁት ሌላ አዝማሪ ያልሆኑ መረጃ ሰጪ የሚከተለውን በማለት ሃሳቡን ይደግፉታል፡፡

> የግብር አገር ክልል ይከልላሉ፡፡ በቃ የእሱ ዘመዶች ናቸው በዚያ አገር የሚሰሩ፡፡ አገሩን ተከፋፍለውታል፡፡ አሁን ሊቀመንበር ከልሎ በሊቀመንበር ተይዞ የለም እንዴ? እንደዚያ አንዱ ያስከለለውን ሌላው አይገባበትም፡፡ ጨው ነው የሚገብሩት፣ ጋንፋር ጨው፣ ይገብራሉ፡፡ የግብር አገሬ ነው፡፡ እኔ ተጫዋች ከሆንሁ ከዚያች አገር አያስረግጠኝም፡፡ በጭቃ ሹም ያስይዘኛል፡፡ በምስለኔ ህግ መታሰር ነው፡፡ የሰው አገር ነኛ፡፡ እና ያቺን ያወጣኋትን አገሬን ማንንም አላስደርስ እለምናለሁ (ሰኢድ ኢብራሂም፣ ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

መረጃዎች አንድ የአዝማሪ ቤተሰብ የእሱ ተብሎ በተሰጠው የቦታ ክልል ሌላ እንዳይገባ እንዴት እንደሚጠብቅ ይገልፃሉ፡፡ ከመረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው አንድ የአዝማሪ ቤተሰብ ተከልሎ የተሰጠው ቦታ ራሱን የሚያስተዳድርበትን ገቢ የሚያገኝበት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከአካባቢው የሚያገኘው ገቢ በሌሎች ተወስዶ በቤተሰቡ ላይ ችግር እንዳይመጣ ከዚያ ቤተሰብ ውጪ የሆነ ሌላ አዝማሪ ወደ ክልሉ እንዳይገባ ይጠብቃል፡፡ ይህም ከመኖርና ከህልውና ጋር የተያያዘ ጉዳይ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ መልኩ ተከልለው ዛሬ ድረስ በአዝማሪ ‹‹አገርነታቸው›› የሚታወቁ በርካታ መንደሮች ያሉ መሆኑን መረጃዎች ያሳዩ ሲሆን ዝርዝራቸው የሚከተለው ነው፡፡

ሰንጠረዥ 1. የወሎ አዝማሪዎች ሰፍረው የሚገኙባቸው መንደሮች

| ወረዳ | ልዩ መንደር |
|---|---|
| ለጋምቦ | ጎንሴ፣ ኢላዳ(በረከት)፣ ሆጤ፣ ቀይ መብራት፣ ቀደ ዱር፣ ጎልቦ |
| ወግዲ | ዘሞድ፣ ለሚ፣ ሰኮሩ ስላሴ |
| ለገሂዳ | ልጓማ፣ ሽክፍ |
| ወረኢሉ | ካቤ፣ ሰኞ ገበያ |
| ቦረና | ሶዬ |
| መርሳ | ዶሮ ግብር፣ ፍዬል ድንጋይ፣ ጊራና፣ ዋይቶ |
| አምባሰል | ማርዬ፣ ጠጠር አምባ፣ ቦሎ፣ ዋታባ እየሱስ |
| ዋድላ ደላንታ | አየጂት |
| ተሁለደሬ | ኮረብቲት፣ ዋሄሎ |
| ደሴ ዙሪያ | ደረቅ ወይራ፣ ከድጆ፣ ኮሬብ |
| ወረሂመኑ | የርማ፣ አልብኮ፣ ገደራ፣ ሽሽግ ብዬ |
| አንቻሮ | አንቻሮ |
| መቄት/ፍላቂት | ቀለባስ/ክትክታ |
| ቡግና | አይደፈር |
| ግዳን | እንባጤን |
| ዳውንት | ጠጠሪያት |
| ወልድያ | አላውሃ |
| ጎብዬ | ጊራና/ዋይቶ |

*ምንጭ፡- አስቴር ሙሉ (ከአቶ ተፈራ አያሌው፣ ከአቶ ብርሃን ትኩ፣ ከአቶ ማስረሻ ፈንታው፣ ከአቶ አበባው ሙሉጌታ፣ አቶ ተስፋዬ በላይ፣ ወይዘሮ አለምፀሃይ የማና ጋር በተለያዩ ቀናት በተኪያሄዱት ቃለምልልሶችና የቡድን ውይይት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ)፡፡*

በሰንጠረዡ ከአርባ በላይ መንደሮች ስም ተዘርዝሯል፡፡ ዝርዝሩ ወሎ ውስጥ በርካታ አዝማሪዎች ለመኖራቸው ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እንዲሆን መሰረቱ የአካባቢው ፖለቲካዊ ሁኔታ ነው፡፡ ምክንያቱም በጥናት አካባቢ ገለፃ ውስጥ ‹‹የወሎ ማህበረሰብ የአስተዳደር መልክ›› በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር እንደተገለፀው ወሎ እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በተለያዩ የግዛት ክልሎች ተከፋፍላ በመሳፍንት፣ በመኳንንትና በባላባት ስትገዛ የኖረች ክፍለ ሃገር ነበረች፡፡ ወረሒመኑ፣ የጁ፣ ላስታና ደንከል ወይም አፋር ዋና ዋና ግዛቶች ሲሆኑ በስራቸው በርካታ ንዑሳን ግዛቶች ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ ግዛት ከነገስታት እስከ ባላባት ድረስ የሚያስተዳድራቸው ነበሩ፡፡ የተለያዩ አጥኚዎች ለምሳሌ (Kawase 2005; 2008 & 2010; Leslau, 1952; Ashenafi, 1969; 1971 & 1975; Teclehaimanot 1986) እንደገለፁትና የቃል መረጃ አቀባዮች

እንደተናገሩት የአዝማሪዎች ቀደምት የስራ ቦታ ከንጉስ ነገስት እስከ አካባቢ አስተዳዳሪ ድረስ የአገር ገዥዎች ቤተ መንግስትና መኖሪያ ቤት ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ከሆነ ወሎ ውስጥ የገዥዎች ቁጥር መብዛቱ ለበርካታ የአዝማሪ መንደሮች መገኘት ዋና ምክንያት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቃለመጠይቅ፣ በተጠኝ ቡድን ውይይትና በምልከታ ከተገኙ መረጃዎች እንደተረጋገጠው የአዝማሪ መንደሮች ከዋና መንገድና በአካባቢያቸው ከሚገኙ ሌሎች አዝማሪ ያልሆኑ ማህበረሰቦች ከሚኖሩባቸው መንደሮች በጣም የራቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለዚህ ጥናት ወሰን የሆኑት መንደሮች ርቀት ከአጥኝዋ አንፃር ሲታይ ኢላዳ /በረከት ከለጋምቦ ዋና ከተማ አቀስታ አምስት ሰዓት፣ ደረቅ ወይራ ከደሴ ከተማ ሶስት ሰዓት፣ ከድጆ ከደሴ ከተማ አምስት ሰዓት፣ ቀለባስ/ክትክታ ለበስ ከወረዳው ዋና ከተማ መቄት ሁለት ሰዓት፣ ማርዬ ከአምባሰል ወረዳ ዋና ከተማ ከውጫሌ ሶስት ሰዓት መንገድ ከተደረጉ ጉዞዎች በኋላ የተገኙ ናቸው፡፡ ከእያንዳንዱ መንደር ለመድረስ በርካታ ዳገትና ቁልቁለቶችን ማለፍ ይጠይቃል፡፡ ይህ ሁኔታ በበኩሉ ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር የነበራቸውን የማህበራዊ ግንኙነት ርቀት የሚጠቁም ነው ለማለት ያስችላል፡፡ ለርቀቱ መፈጠር ምክንያቱ አዝማሪዎች ‹‹የሚተዳደሩበት ስራ››/ዘፈን ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ለመተዳደሪያ እንዲሆነው የማይሰራው መሆኑ ወይም ዘፋኝነት ለአዝማሪ የተሰጠ ስራ በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ደግሞ ማርክሲሳውያን ‹‹በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ቡድኖች የታሪክ አጋጣሚ በሰጣቸው የገቢ ምንጭ ውስጥ በታሪክ አጋጣሚ በያዙት ስፍራ፣ በምርት ሂደት ውስጥ ባላቸው ግንኙነት፣ በማህበራዊ የምርት ተቋማት ውስጥ ባላቸው ሚናና ከማህበረሰቡ ሃብት ባላቸው ድርሻና ድርሻቸውን የማግኛ መንገድ አንዳቸው ከሌላቸው የተለዩ ናቸው›› Afanasyev (1987,239) ሲሉ በአንድ ትልቅ ማህበረሰብ ውስጥ በስራ ፀባያቸው ምክንያት ቡድኖች እንደሚፈጠሩ ከሰጡት ገለፃ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ምክንያቱም አዝማሪዎችን የራሳቸውን መንደር መስርተው እስኪኖሩ ድረስ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል የተለዩ ቡድኖች ያደረጋቸው ሌላው ቡድን ባላደረገው መንገድ ዘፈንን መተዳደሪያቸው አድርገው መያዛቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ከቀረበው ሃሳብ በወሎ በበርካታ ቦታዎች አዝማሪዎች ሰፍረው እንደሚገኙ መረዳት ተችሏል፡፡ መንደሮቹ የተመሰረቱት አዝማሪዎች መተዳደሪያቸውን የሚሰጧቸውን ሹማምንትን እግር ተከትሎ በመሆኑ የመንደሮቹ አመሰራረት የአዝማሪዎችን የኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲሁም የወቅቱ ማህበረፖለቲካዊ ስርዓት ነፀብራቅ


ነው ማለት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የመንደሮች አቀማመጥ አዝማሪዎች ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ጋር የነበራቸውን የአኗኗር ርቀት ሲያሳይ በአንፃሩ አዝማሪዎች በተወሰኑ መንደሮች ለብቻቸው መኖራቸው ሊመሰርት የሚችለውን ጥብቅ የእርስ በእርስ ትስስር ሊጠቁም የሚችል ነው፡፡ ቀጥሎ ስለዚሁ የእርስ በእርስ የዝምድና መልክ ቀርቧል፡፡

## 6.1.1.2. የእርስ በእርስ ዝምድና

ዝምድና ማለት በሰዎች መካከል በደም፣ በጋብቻና በሌሎች የሰዎችን ግንኙነት ሊፈጥሩ በሚችሉ ሁኔታዎች አማካኝነት የሚፈጠር ማህበራዊ ትስስር መሆኑን ፀሃፍት ይገልፃሉ Smith with Davies(2008, 61)፡፡ የወሎ አዝማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ተለይተው እንዲታወቁ ያደረጓቸው ጥብቅ የዝምድና ትስስሮች በመካከላቸው አሉ፡፡ ከእነዚህ የዝምድና አይነቶች ውስጥ መወለድ (የስጋ ዝምድና) እና ጋብቻ ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡ በአንድ መንደር የሚኖሩ የወሎ አዝማሪዎች በአመዛኙ በስጋ ዝምድና የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የመንደሮቹ ቀደምት አመሰራረት በአንድ አባወራና በቤተሰቦቹ በመሆኑ በመንደሩ የሚኖሩት አዝማሪዎች በሙሉ በመጀመሪያ ለመንደሩ አጫዋችነት ሹሙን ተከትሎ የመጣው ሰፋሪ አዝማሪ የልጅ ልጆች ናቸው፡፡ የዘር ሃረጋቸውም አሁን ካሉት ተነስቶ ወደኋላ ሲቆጠር ይህንኑ ቀዳሚ ሰፋሪ አባ ወራ የሚጠራ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ የሚያሳየው አቶ ብርሃን ትኩና ቤተሰባቸው ያደረጉት የዘር ቆጠራ ቀጣዩን ይላል፡፡


- ጤፉ ትንገር
- ጣፋጭ ጤፉ
- ሱሬ ጣፋጭ
- አቢወት ሱሬ
- ስንዴ አቢወት
- ቱቻ ስንዴ
- ነጋሽ ቱቻ
- ጉበና ነጋሽ
- ትኩ ጉበና
- ብርሃን ትኩ

ይህ የቤተሰብ ዘር ቆጠራ በብርሃን ትኩ አማካኝነት የተደረገ ነው፡፡ መረጃ ሰጪው የቤተሰባቸውን የዘር ሃረግ ከራሳቸው ጀምረው ወደ ላይ አስር ቤት ድረስ በመቁጠር አሳይተዋል፡፡ እንዳሉት በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ከአዝማሪነት በስተቀር በሌላ ስራ የተዳደረ አንድም ሰው የለም፡፡ መረጃ ሰጪው ወደላይ ያለውን የቤተሰብ ሃረግ ብቻ ሳይሆን ወደ ጎን ያለውንም በሚከተለው መንገድ ከሌሎች መረጃ ሰጪዎች ጋር በመወያየት አስቀምጠውታል፡፡





*ምንጭ አስቴር ሙሉ (ከአቶ ብርሃን ትኩ፣ ከማስረሻ ፈንታው፣ ከተፈራ አበበ፣ ከተስፋዬ በላይ፣ ከመኮንን በላይ፣ ከሻምበል በላይ፣ በ12/05/2005ዓ.ም ከተጠኝ ቡድን ውይይት የተገኘውን መረጃ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ)፡፡*

ከላይ የተዘረዘረው የሰዎች ስም የሚያሳየው ማርዬ ስላሴ ውስጥ የሚኖሩ ‹‹ባላባት›› አዝማሪዎችን የቤተሰብ የዘር ሃረግ ነው፡፡ በስዕሉ ወደ ሰላሳ አራት የሚደርሱ ሰዎች የስም ዝርዝር ሰፍሯል፡፡ እነዚህ ሰዎች የስጋ ዝምድና ያላቸው ሲሆን ማርዬ ስላሴ ተብሎ የሚጠራውን አካባቢ በአያቶቻቸው አማካኝነት በርስትነት ይዘው የኖሩ ናቸው፡፡ ከጥንት ጀምሮ የአምባሰል አዝማሪዎች ተብለው የሚጠሩ እነሱ እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ እንደዚሁ ሁሉ በሌሎች ለጥናት በተመረጡት መንደሮችም የአንድ ቤተሰብ አባላት የሚኖሩ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ መንደሩ የተመሰረተበት ዘመን ‹‹ሩቅ›› አለመሆኑን የገለፁት የቀለባስ አዝማሪዎች ያደረጉት ቀጣዩ የዘር ቆጠራ እንዲሁ በመንደሯ ነዋሪዎች ውስጥ ያለውን ዝምድና የሚያሳይ ነው፡፡




በቀለባስ ክትክታ መንደር የሚኖሩ አዝማሪዎች ቦታዋ አዝማሪ መንደር ከሆነች ሩቅ ጊዜ አለመሆኗን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መሰረት ዛሬ በመንደሯ የሚኖሩት በዕድሜ አዛውንት የሚባሉ ሰዎች ለመንደሯ መስራች አራተኛ ትውልድ ናቸው፡፡ የእነሱ ልጆች ደግሞ አምስተኛ ትውልድ ናቸው ማለት ነው፡፡ በመንደሯ ከሚኖሩ አባ ወራዎች ውስጥ የአንዱ የቤተሰብ ሃረግ (መንደሯ ከተመሰረተች ጀምሮ አራተኛና አምስተኛ ትውልድ) ቀጥሎ በምሳሌነት ቀርቧል፡፡




*ምንጭ፡ አስቴር ሙሉ፣27/07/2005 ዓ.ም ከመላክ ታረቀና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከተደረገ የተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኘውን መረጃ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ)*

በክትክታ መንደር ለሚኖሩ አዝማሪዎች የመንደሩ መስራች ወንድይራድ ካሳ ሲሆኑ አሁን በስፍራው የሚገኙትና የዚህ መረጃ አቀባይ የሆኑት ሰዎች አራተኛ ትውልድ ናቸው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንዳሉት ሁሉም ከአንድ ቤተሰብ የወጡ ናቸው፡፡ ‹‹ከዚህ የምንኖረው ሁላችንም የአንድ ሰው ልጆች ነን›› በሚል ከአንድ የዘር ሃረግ የወጡ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ሁለቱ የዘር ሃረግ ቆጠራዎችም ይህንን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ይሁንና በቡድኑ ውስጥ በደም ከተፈጠረ ትስስር በተጨማሪ የጋብቻ ዝምድናም አለ፡፡ ቡድኑ ማንኛውም ማህበረሰብ ረጅም ዘመን ለመኖሩ ምክንያቱ ዘሩን መተካቱ መሆኑ

መሰረታዊ የሰው ልጅ ባህርይ ነው፡፡ አዝማሪዎችም ይህንን ባህርይ ይጋራሉ፡፡ ለዚህ ሲሉም ጋብቻን ይፈፅማሉ፡፡ ይሁንና ምንም እንኳን ጋብቻቸው እርስ በእርስ ቢሆንም የስጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል ጋብቻን መፈፀም ነውር በመሆኑ ይህንን ላለማድረግ ሲሉ ከሚኖሩበት መንደር ወጥተው በሌሎች መንደሮች ከሚኖሩ አዝማሪዎች ጋር ጋብቻቸውን ይፈፅማሉ፡፡ በዚህ የተነሳ በመንደሮች መካከል የጋብቻ ዝምድና ይመሰረታል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ፀሃይነሽ በላይ በአምባሰል ወረዳ ማርዬ ቀበሌ ተወልዳ ያደገች የአፍራሳ ነጋሽ የልጅ ልጅ ልጅ፣ የንጋቱ አፍራሳ የልጅ ልጅ፣ የበላይ ንጋቱ ልጅ ናት፡፡ ጋብቻዋ ግን ደረቅ ወይራ ተወልዶ ካደገው መላኩ መድፉ ጋር ነው፡፡ ብርሃን ትኩ ጋብቻውን ያደረገው አንቻሮ ነው፡፡መረጃዎች እንደሚሉት አዝማሪዎች የቡድኑን ቅርፅ ለመጠበቅ ሲሉ አዝማሪ ካልሆነ ቤተሰብ ጋር የጋብቻ ቅልቅል እንዳይደረግ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ የአዝማሪዎች ቡድን በደም የተሳሰሩ ሰዎች የተሰበሰቡበት ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ቡድኑን በአንድ ትልቅ ማህበረሰብ ውስጥ የራሱን ቅርፅ እንዲይዝ ከማድረጉ ባሻገር ‹‹ የአዝማሪ ዘሩ አንድ ነው›› የሚል ግንዛቤ የፈጠረ ሆኗል፡፡

ይሁንና አልፎ አልፎ አዝማሪ፣ ከአዝማሪ ባላገር ከባላገር ይጋባ የሚለው ደንብ የሚሰበርበት አጋጣሚ እንደነበር የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ አቶ አሰፋ ለገሰ የተባሉ አዝማሪ ስለቤተሰቦቻቸው የጋብቻ ሁኔታ ሲገልፁ ‹‹የእኔ አያት አዝማሪ አልነበረም፡፡ በእኛ ጥሪ ባላገር ነው እንለዋለን፡፡ አንዲት አዝማሪ ወድዶ እስዋን አገባና አዝማሪነት ተማረ . . . አዝማሪና ባላገር መጋባት ክልክል ነበረ፡፡ ግን ፍቅር ስለሆነ ምንም ማድረግ አልቻለም ሰብሮ ገባ፡፡ ፍቅር ጋራ አይጋርደውም›› (14/04/2005 ዓ.ም፣ በተደረገ ቃለ መጠይቅ ከድጆ) ብለዋል፡፡ አቶ አሰፋም ሆኑ ሌሎች መረጃ ሰጪዎች የገለፁት የዚህ አይነት ሁኔታ አልፎ አልፎ ብቻ የሚያጋጥም እንደሆነ ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ባለው መደበኛ ሁኔታ ግን አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች አዝማሪዎችን ‹‹አጥንተ ጎደሎ›› በሚል ለማግባት የማይፈልጉትን ያህል አዝማሪዎችም በበኩላቸው ሌላውን ሰው ‹‹ባላገር/ቡጋ›[28] በሚል ስያሜ እየጠሩት ከእነሱ ጋር እንዳይጋባ ይጠነቀቁ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ሁለቱም ቡድኖች ከሌላ ቡድን ጋር ሊፈጠር የሚችልን መቀላቀል ለመከላከል ሲሉ ሲያደርጉት የኖሩ ቢሆንም ከዚህ ባለፈ ግን የሁለቱ ቡድን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ይህ እንዲሆን ሲያስገድድ የኖረ መሆኑን መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ አንፃር መኮንን በላይና ብርሃን ትኩ የተባሉ መረጃ ሰጪዎች የሚከተለውን ብለዋል፡

[28] የማያውቅ ጥበብ የሌለው የሚል ትርጉም ይይዛል፡፡

‹‹በመሰረቱ አሁን እኔ እንዲቱን የረጋ[29] ልጅ ባገባት እኔ እየዘፈንሁ እስዋ ዝም ብላ ቁጭ ልትል ነው፡፡ እንደዚያ ደግሞ መሆን የለበትም፡፡ መዝፈን አለባት፡፡ ስለዚህ የአዝማሪ ልጅ አገባለሁ፡፡ ግድ ነው፡፡ ገብቶሻል? አንደኛው ተቀማጭ አንደኛው ሰሪ መሆን የለበትም›› (መኮንን በላይ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ) ፡፡ ይህንን ሃሳብ የሚደግፍ ሌላ መረጃ የሰጡ መረጃ አቀባይም ቀጣዩን ብለዋል፡፡

‹‹የእኔ አያት እኮ አንድ ነገር ብሏል፤‹‹ተጫዋች ሆኖ የማትጫወት ሴት ማግባት፣ አንድ ጎተራ ነቀዝ እቤት አኑሮ ልመና መግባት›› ብሏል (ደምሴ አበበ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ቃለመጠይቅ፣ ጢሳ አባ ሊማ) ፡፡

መረጃዎች አንድ አዝማሪ የገበሬ ልጅ የሆነች ሴት ቢያገባ የስራ ሸክም እሱ ላይ ብቻ ይወድቅበታል ይላል፡፡ ምክንያቱም አንድ የገበሬ ልጅ አስቀድሞ ከነበረው ለዘመናት የኖረ የስራ ድልድል ልምድና ልምዱ ከሰጣት ችሎታ የተነሳ በግብርና ስራ እንጅ በዘፋኝነት ባሏን ልታግዝ አትችልም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከወንዱ እኩል አደባባይ ወጥታ ገንዘብ የምታመጣ አትሆንም፡፡ ይህም በቤተሰቡ ገቢ ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን በቀረቡት ትንታኔዎች የታየው የአዝማሪዎች የቡድን መልክ የማርክሳዊት ትውር አራማጆች ‹‹ጥንታዊ የማህበረሰብ አይነት›› ሲሉ ከሚጠሩት ‹‹ጀንስ /Gens›› ከተባለው በደምና በኢኮኖሚ ምክንያት ከተሳሰረ የቡድን አይነት ጋር የሚመሳሰል እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ Afanasyev (1978,264) ‹‹ጀንስ›› በሰው ልጆች ቡድን ምስረታ ውስጥ ታሪካዊ (ጥንታዊ) የቡድን አይነት ነው፡፡ ቡድኑ በደምና በኢኮኖሚ በተሳሰሩ ሰዎች አማካኝነት ይገነባል፡፡ በቡድኑ ውስጥ ሃብት የጋራ ነው፡፡ አባላቱ በጋራ ይሰራሉ፡፡ በጋራ ይመገባሉ፡፡ የጋራ ሃብታቸውን በጋራ ይጠብቃሉ›› ይላሉ፡፡ ከቀረቡት ትንታኔዎች የወሎ አዝማሪዎች እነዚህ ባህርያት የሚጋሩ መሆናቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አዝማሪዎች ለዘመናት አዝማሪ ካልሆነው ወገን ጋር እንዳይጋቡ ሲጠነቀቁ የኖሩ በመሆናቸው ቡድኑ በደም የተሳሰረ ሆኖ ኖሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌላው ቡድን እነሱ የሚሰሩትን ሰርቶ የማያድር በመሆኑ ለጋብቻ የሚመርጡት ተመሳሳይ ሙያ ያለውን ሰው ብቻ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታም ቡድኑ ከደም በተጨማሪ በኢኮኖሚ የተሳሰረ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህ ሁኔታ አዝማሪነት በወሎ እጅግ ጥንታዊ ሙያ መሆኑን የሚጠቁም ሲሆን ከዚህ ሌላ በጋብቻ አከዋወን ሂደት ውስጥ ሙያ ዋና ጉዳይ መሆኑ ‹‹ከእያንዳንዱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና

[29]አዝማሪ ያልሆነ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ከአዝማሪ ውጪ የሆነን ሰው አልፎ አልፎ በዚህ ስም ይጠሩታል፡፡

ባህላዊ ሁኔታ በስተጀርባ ኢኮኖሚ አለ›› ሲሉ ማርክሲሳውያን ከሚሰጡት ሃሳብ በተመሳሳይ የገቢ ሁኔታ በትዳር ውስጥ ያሳረፈውን ተፅዕኖ ለማየት ያስችላል፡፡

ይህ እርስ በእርስ ሲደረግ የኖረ የጋብቻ ስርዓት የራሱ የሆነ የአከዋወን በዓል አለው ሲሉ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጉዳይ የወሎ አዝማሪዎች መገለጫችን ነው ሲሉ የሚያቀርቡት ሌላ ገፅታቸው ነው፡፡ ‹‹የአዝማሪ ሰርግ የተለየ ነው›› ሲሉ ያብራሩታል፡፡ ይህም ‹‹የሰርግ ስርዓት›› በሚል ርዕስ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6.1.1.3. የሰርግ ስርዓት

እንደሚሉት ሰርግ ከተለያዩ የህይወት ዑደት ፌስቲቫሎች ውስጥ አንዱ ነው Green (1997, 270) ፡፡ ይህ ፌስቲቫል ሰዎች ከብቸኝነት ወደ ጥንድነት መምጣታቸውንና ቤተሰብ መመስረታቸውን ምክንያት አድርጎ ይከወናል፡፡ አዝማሪ ያልሆኑ መረጃ ሰጪዎች አዝማሪዎች የራሳቸውን ሰርግ የላቸውም፡፡ በሌላ ሰው ሰርግ ይጋባሉ እንጂ የሚል መረጃ ይሰጣሉ፡፡ አቶ ጫኔ ወርቅነህ የተባሉ መረጃ ሰጪ ይህንን ሃሳብ ሲገልፁ ‹‹አዝማሪዎች እኮ እንደሌላው ሰው ደግሰው አይጋቡም፡፡ እነሱ እንዲያውም ሲሰሩ በሄዱበት ቦታ፣ በሰው ሰርግ፣ በሰው ድግስ የሚጋቡ ናቸው፣ መቼ ከቤታቸው ተቀምጠው፣ ምን የራሳቸው እርሻ ኑሯቸው ይደግሳሉ›› ይላሉ (ቃለመጠይቅ፣13/04/2005 ዓ.ም፣ ደሴ) ፡፡

ይሁንና አዝማሪ መረጃ ሰጪዎች በዚህ ሃሳብ አይስማሙም፡፡ እነሱ እንደሚሉት አዝማሪ ያልሆኑት ሰዎች ይህንን ሃሳብ የሚሰጡት ለአዝማሪ ያላቸውን ዝቅተኛ ስሜት ለማሳየት በመፈለጋቸውና የአዝማሪን ህይወት ጠንቅቀ ካለማወቅ ነው፡፡ አዝማሪዎች ሁልጊዜ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስና ከሌሎች በሚያገኙት ችሮታ ብቻ የሚተዳደሩ ስለሚመስላቸው የራሳቸው ሰርግ እንዳላቸው አያስቡም፡፡ ለዚህ ሃሳባቸው መነሻ የሆናቸው ዋና ምክንያት ደግሞ ብዙው ሰው አዝማሪዎችን የሚያውቃቸው በመኖሪያ ሰፈራቸው ሳይሆን ለስራ በሄዱበት አካባቢ መሆኑ ነው፡፡ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ አዝማሪዎች ከትውልድ ቦታቸው ሲርቁ ማንም ከአካባቢው የራቀ ሰው በአካባቢ ተፅዕኖ ምክንያት ሊያጋጥመው እንደሚችለው የትውልድ አካባቢ ‹‹ባህልን መጣስ›› ሁኔታ ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ ይህን ጊዜ ተመልካች ያንን የግለሰብ ባህርይ በመውሰድ እንደ ቡድን መገለጫ ሊገነዘበው ይችላል፡፡ አዝማሪዎች ሰርግ አይደግሱም የሚለውም በዚህ የተነሳ የተባለ ይሆናል፡፡

ይልቁንስ አዝማሪዎች የጋብቻ ስርዓታቸውን የሚያከናውኑበት የራሳቸው ስርዓት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ ስርዓት በቤተሰብ አማካኝነት ሽማግሌ ተልኮ በሚደረግ ‹‹ልጅህን ለልጄ›› ጥያቄ ይጀመራል፡፡ ጥያቄው የሚቀርበው ከወንዱ ቤተሰብ ሲሆን ሴቷ ለሚስትነት እንድትመረጥ የሚያደርጋት ጥሩ ድምፅ ያላትና ዘፍና ለማደር ፍላጎት ያላት መሆኗ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ የሴቷ ቤተሰብ የጋብቻ ጠያቂውን ቤተሰብ ማንነት ለማወቅ እንዲረዳው ‹‹እንምከርበት ጊዜ ስጡን›› በሚል ሰበብ የጠያቂውን ቤተሰብ የዘር ሃረግና ለባልነት የመጣውን ወንድ ‹‹ጥሩ አዝማሪ›› መሆን አለመሆን አጣርቶ አቻዬ ነው ብሎ ካሰበ የጋብቻ ቀን ይወሰናል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት የሰርጉ ቀን ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ በሴቷ ቤተሰብ በኩል ከፍተኛ የሆነ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም ድግሱና ሙሽራ መሞሸሩ በሴቷ ቤተሰብ አማካኝነት የሚካሄድ ነውና፡፡ አቶ አሰፋ ለገሰ ይህንን ሲገልፁ፡-

> አወ! የአዝማሪ ሰርግ ልንገርሽ ድግሱ እንኳን ሶስት ቀን ነው፡፡ ደግሞ ሙሽራው የሚሞሽረው የት መሰለሽ? እሷ ቤት ነው፡፡ እሴቷ ቤት፡፡ ሙሽራ አሁን አሁን እየቀረ ሄዶ ነው እንጂ አስራ አምስት ቀን ይደገሳል፡፡ እንደዛሬ አዋጡ የለም፡፡ ራሱ ነው ደጋሹ የሚያቀርብ አስራ አምስት፣ ሃያ ቀን ድረስ ጠላ እንጂ ቅራሬ አይጠጣም፡፡ ቅራሬ ከቀረበላቸው ይደፉታል፡፡ ሶስት ቀን ዘመድ ይበላል፡፡ በሶስተኛው ቀን ይወጣል፡፡ ሙሽራ አስራ አምስት ቀን ድረስ ይቆያል፡፡ ጠላ አለ፤ ሙጌራ ይመጣል፤ ጨጨብሳ ይመጣል፤ ደሮ ይመጣል፡፡ ዘመዱ ሁሉ ያመጣል (ቃለመጠይቅ፣14/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ) ይላሉ፡፡

መረጃው እንደሚለው አንድ ሰርግ ደጋሽ ቤተሰብ የሰርግ ታዳሚዎቹን ለሶስት ቀን ያህል በተትረፈረፈ ድግስ ያስተናግዳል፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ ደግሞ ሙሽራውና ሚዜዎቹን ለአስራ አምስት ቀናት በማብላትና በማጠጣት ሲንከባከብ ይሰነብታል፡፡ ይህ ደግሞ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ከሌላውና አዝማሪ ካልሆነው ማህበረሰብ የተለየ ልምድ ነው፡፡ ምክንያቱም በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ ድግሱ በሁለቱም ቤተሰብ ይደገሳል፣ የድግስ ቀኑም የአዝማሪዎችን ያህል አይረዝምም፡፡

በአዝማሪዎች ቤት ድግሱ ይህንን ያህል ቀን ለመርዘሙ ራሱን የቻለ ምክንያት አለ፡፡ ይህም አስቀድሞ እንደተገለፀው አዝማሪዎች ጋብቻን የሚፈፅሙ ከመሰላቸው ጋር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ካሉበት ቦታ ርቀው እንዲሄዱ ያስገድዳቸዋል፡፡ የቦታው ርቀት እስከ ሶስት ቀንና ከዚያ በላይ ሊያስሄድ የሚችል ከሆነ ያንን ያህል ተጉዞ የመጣ ሰርገኛ የግድ ማረፍ ያስፈልገዋል፡፡ እረፍቱም በጥሩ መብልና መጠጥ የታጀበ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህንን ጉዳይ በማርዬ ጠጠር አምባ ነዋሪ የሆኑት አቶ ማስረሻ ፈንታው ሲገልፁ፡-‹‹ሰርገኛ የሚመጣ ተኮምቦልሻ ነው፡፡ ተከድጆ ነው፤ ተወልድያ ነው፡፡ ተወረኢሉ ተማንም ተቦረናም ይመጣል፡፡ ተፈላልጎ ነው የሚጋባው ብዬሽ የለም? ሰራተኛ ተሰራተኛ፤ ተጫዋች ተተጫዋች፡፡ ከሩቅ ሃገር ነው የሚመጣው፡፡ ተሩቅ ሃገር በሚመጣበት ወቅት ይደክመዋል፡፡ አድሮ ሂያጅ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሶስት ቀን የተደረገው በዚያ ምክንያት ነው›› (ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ፤) ይላሉ፡፡ በድግሱ ሙሽራ ከሚያጅበው ሰርገኛ ውጪ ጎረቤትና ዘመድ የሰርግ ስርዓቱ ታዳሚ ይሆናል፡፡ ሰርገኛው ለሁለትና ለሶስት ሳምንታት፣ ጎረቤትና ዘመዱ ደግሞ ለሶስት ቀናት ይስተናገዳሉ፡፡ አቶ አሰፋ ለገሰ ይህንን ሲገልፁት፡- ‹‹አይ አዝማሪ እኮ ብቻውን አይኖርም፡፡ አዝማሪ ያልሆኑ ጎረቤቶች አሉት፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ከስጋ ዝምድና ሌላ የፍቅር ዝምድና አለ፡፡ ስለዚህ እንግዳው ከሁሉም አይነት ነው፡፡ በግብዣው ከሩቅ ሃገር የመጡት ይቆያሉ፡፡ የቅርቡ ቀስ በቀስ ይወጣል፡፡ የቸኮለ ሁለት ቀን ሶስት ቀን አድሮ ይሄዳል፡፡ ድግሱ ቀላል አይደለም፡፡ አሁን ኑሮ እየከበደ ቀረ እንጂ ሌላ ነበር›› (ቃለመጠይቅ፣11/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ) ይላሉ፡፡

አዝማሪዎች ከድግሱ ባሻገር የዘፈን ስርዓቱም ራሱን የቻለ መልክ እንዳለው ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን አዝማሪዎች አዝማሪ ካልሆኑ ሰዎች ጋር ጉርብትና የመሰረተው ወዳጅነት ቢኖራቸውና በሰርጋቸው ታዳሚ ቢያደርጓቸውም የሰርጉ ባለቤቶች አዝማሪዎች በመሆናቸው የተነሳ የዘፈን ስርዓቱ የራሱ መልክ አለው፡፡ ይህ መልኩ ምን እንደሚመስል አቶ ማስረሻ ፈንታው የተባሉ መረጃ ሰጪ በሚቀጥለው መልክ ገልጠውታል፡፡

> ደግሞ ሰርጋችን የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌ ዛሬ እሁድ ነው፡፡ እሁድ ማታ ሰርገኛው ይገባል፡፡ ይቀርባል፤ ይቀርባል፡፡ ግን ድሮ ሞሻሪ ነበረ ከሙሽራዋ ቤት፡፡ እንሞሽራለን፤ ይገባል ሙሽራ፣ ሰርገኛ ይገባል፡፡ ቤተዘመድ ይገባል፡፡ ሚዜ ይገባል፡፡ ይቆማሉ፡፡ ምነው ቆማችሁ፡፡ አባት ትሆኑንን ብለን ቁመናል፡፡ ልጅ ከሆናችሁን አባት እንሆናችኋለን፡፡ ምን ቅርብ ቢሆን

ሽንታችን ሲመጣ የሚያሳየን አንድ ሰው ይሰጠን ይላሉ። ይሰጣቸዋል። አሳዳሪ ነው ያ። ይቀመጣል፤ ግብር ይመጣል። ይበላል። ሙሽራዋ ከጫጉላ ትገባና ትጠብቀዋለች። ይሄዳል። ደንብ አለ። ወጣ ገባ ወጣ ገባ እያለ ይገርፋታል። በኋላ መሲንቆ ከሴት ወገን አንዱ ተነስቶ መዲና/ዘለሰኛ ነካ ነካ አድርጎ ለሰርገኛ ይሰጣል። በሴት ወገን ነው የሚጀመር። ከዚያ ይዘፈናል። ሶስት ቀን ነው የሚሞሸሩ ይኸ ለምንድን ነው ቢባል። ሰርገኛ የሚመጣ ከኮምቦልቻ ነው። ከከድጆ ነው፤ ከወልድያ ነው። ተወረኢሉ ተማንም ተቦረናም ይመጣል። ተፈላልጎ ነው የሚጋባው ብዬሽ የለም? ሰራተኛ ከሰራተኛ፤ ተጫዋች ተጫዋች። ከሩቅ ሃገር ነው የሚመጣው። ተሩቅ ሃገር በሚመጣበት ወቅት ይደክመዋል። አድሮ ሂያጅ አይደለም። ስለዚህ በሶስት ቀን የተደረገው በዚያ ምክንያት ነው። ግን አሁንም ደንቡ አለ። እንግዲያ እስከጨፌ[30] በመኪና ነው የሚመጣ ግን ደንቡ አለ። ሶስት ቀን ነው ድግሱ። ከዚህ በኋላ ሌላው ቤተዘመድ ወደ ቤቱ ይሄዳል። ሰርገኛው ብቻ ይቀራል። ሰርገኛው እስከ ሁለት ሳምንት በሴቷ ቤት ሲቀለብ ይሰነብትና ሙሽራዋን ይዞ ወደ ወንዱ ቤት ይሄዳል (ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)።

መረጃው የአዝማሪ ሰርግ ራሱን የቻለ ስርዓት እንዳለው የሚያሳይ ነው። ይህ ስርዓት የሰርጉ ጅማሬ፤ መሃልና መጨረሻ እንዳለው ይገልፃል። ሰርጉ የሚጀምረው ሰርገኛው (የወንድ ሙሽራና ሚዜዎቹ) ወደ ሴቷ ቤት ሲመጣ ነው። ሰርገኛው የሚመጣው በማታ ነው። የሰርገኛውን መምጣት ተከትሎ የሴቷ ቤተዘመድ ወደ ዳሱ[31] ይገባል፣ሰርገኛው የሴቷን ቤተሰቦች ጠይቆ ለሚያስፈልገው ጉዳይ ሁሉ የሴቷን ቤተሰብ ወክሎ መልስ የሚሰጥ አንድ ሰው ይመደብለታል። ቀጥሞ ምግብና መጠጥ ይቀርባል፣ ይበላል፣ ይጠጣል። ዘፈን ይቀጥላል፣ ሁኔታው በዚህ መልኩ ለሶስት ቀናት ይቀጥላል። እነዚህ ሁሉ በሰርጉ መሃል የሚከወኑ ተግባራት ወይም የሰርጉ መሃከለኛ ክዋኔዎች

[30]ከባህር ዳር ደሴ በሚወስደው የአስፖልት መንገድ በውጫሌና ደሴ መካከል የምገኝ ትንሽ ከተማ ናት። ይህች ትንሽ ከተማ ከውጫሌ ወይም ደሴ ተነስቶ ማርዬ ስላሴ ተብሎ ወደሚጠራው አካባቢ ሲኬድ የአስፖልት መንገድ ማለቂያ ናት። ከጨፌ ማርዬ የተመደበ መኪና ባለመኖሩ፣ ጨፌ ከተደረሰ በኋላ ወደ ማርዬ የሚኬደው በእግር ነው። መንገዱም ኮረኮንች ነው። ሲሄዱ ዳገት፣ ሲመለሱ ደግሞ ቁልቁለት ነው።

[31]ብዙውን ጊዜ ድግስ ያለባቸው የገጠር ሰዎች እንግዶቻቸውን በአንድነት ለመጋዝ ያስችላቸው ዘንድ እንደ አጣና፣ ጨፈቃና ቅጠላ ቅጠል ባሉ ነገሮች የሚሰሩት ጊዜያዊ መጠለያ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት (1993 ዓ.ም ፣478)።

ናቸው፡፡ በመጨረሻ ሰርጉ የሚጠናቀቀው በአስራ አምስተኛው ሙሽሮችን ከነአጃቢያቸው ወደ ወንድ ሙሽራ ቤት በመላክ ነው፡፡ መረጃው የአዝማሪ ሰርግ ክዋኔ የሚከተላቸው ደረጃዎች እንዳሉ ይጠቁማል፡፡ ይህም በፎክሎር እሳቤ ውስጥ እያንዳንዱ ክዋኔ የሚከተለው ቅደም ተከተል አለ (Hymes,1975) የሚለውን የክዋኔያዊ ትውር ሃሳብ የሚደግፍ ነው፡፡

የዘፈን ስርዓቱ ሌላም ጥብቅ የሆነ ልማዳዊ ህግ እንዳለው መላኩ ካሳው የተባሉ መረጃ ሰጪ ይገልፃሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት አንድ ሰው ሴት ልጅ ሲድር ሚዜውና ሰርገኛው መሰንቆ ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከዚያም ከሴት ወገን በዕድሜ ገፋ ያለው ተነስቶ በመዲናና ዘለሰኛ ጨዋታ ይጀምራል፡፡ ከዚያ ወዲያ በዕድሜ ተዋረድ መሰንቆ የያዘው ሰው ሁሉ እየተነሳ ታዳሚውን ያጫውታል፡፡ በዚህ ጊዜ ታዳሚው የተሻለውን ሰው መርጦ እከሌ ያጫውተን ይላል፡፡ ያ ሰው ይቀጥላል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን አንድ ሰው ጎበዝ ተጫዋች ስለሆነ ብቻ ከትልልቆች ቀድሞ ጨዋታ አይጀምርም፡፡ ሃሳቡ በእነሱ አባባል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ‹‹ አስቀድሞ ግን መላኩ ያውቃል ተብሎ ትልልቅ ሰዎች እያሉ መላኩ ይጀምር አይባልም፡፡ ለምን ክብር አለው፡፡ ትልቁ ሰው ተነስቶ የሚጀመርበት አለ መዲና የሚባል፡፡ ያን ይጀምራል፡፡ እሱን ይላል ዘለሰኛ ይጫወታል፡፡ ከዚያ በኋላ ያቆማል፡፡ መጨረሻ ላይ እሱ ያውቃል የሚባለው ሰው ያጫውተን ተብሎ ይመረጣል›› (ቃለ መጠይቅ፣14/04/2005 ዓ.ም፣ማርዬ)፡፡

መረጃው የሚያሳየው በሰርጉ ውስጥ በርካታ አዝማሪዎች ቢኖሩም የዘፈን አከዋወን ቅደም ተከተሉ ዕድሜን መሰረት አድርጎ የሚከናወን መሆኑን ነው፡፡ ይህም በቡድኑ ውስጥ ለትልልቅ ሰዎች የሚሰጠውን ክብር የሚሳይ ነው፡፡ መረጃው ከዕድሜ ቀጥሎ ለችሎታ ክብር የሚሰጥ መሆኑንም ይገልፃል፡፡ ምክንያቱም ከሁሉም በዕድሜ ሚበልጠው ሰው ክዋኔውን ካስጀመረ በኋላ ጥሩ ችሎታ ያለው ሰው እንዲጫወት ይደረጋል፡፡

ከዚህ የተነሳ ክትክታ ለበስ መንደር ውስጥ ሲከወን በነበረ የአዝማሪ ሰርግ በትልቅ ሰው ቡራኬ ከተከፈተ በኋላ (ይህ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው) በጥሩ መሰንቆ ተጫዋቺነቱ የተነሳ በራሱ ሰርግ መሰንቆ እንዲመታ የተደረገ አዝማሪ ለማየት ችያለሁ፡፡ ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ጊዜው ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ ያረፍሁበት ቤት[32] የቤተሰብ አባል በሆነው በሪሁን በተባለው ወጣት አማካኝነት

[32]. ሃረጉ የሚገልፀው ስለ ጥናቱ አድረጊ ነው፡፡ ለመረጃ ስብሰባ በሄድሁባቸው መንደሮች ሁሉ ለማረፊያነት የተጠቀምሁት በአካባቢው ነዋሪ ከሆኑ የተጠኘ ቡድን አባላት ቤቶች ውስጥ ነው፡፡ ይህ

ሰርግ መኖሩን ስላወቅሁ መንገድ መሪየንና በአካባቢው ሰርግ መኖሩን የነገረኝን በሪሁንን አስከትዬ ወደ ሰርግ ቤቱ ሄድሁ፡፡ ሰርገኞች በደስታ ተቀበሉንና ሙሽሮች ወደ ተቀመጡበት ከፍ ያለ ቦታ ተወስደን የምንቀመጥበት ቦታ ተሰጠን፡፡ ቀጥሎም ጠላ ቀረበልን፡፡ ሙሽራዋ ጋቢያቸውን አጣጥለው ለብሰው በተቀመጡ ሶስት ወጣት ወንዶችና መሰንቆ በሚመታ ሌላ ወጣት መሃል ፊቷን ሳይቀር በነጠላ ተሸፍና ተቀምጣለች፡፡ ሙሽራውን ግን ላየው አልቻልሁም፡፡ ከጎኔ የተቀመጠውን በሪሁንን፣ ‹‹ሙሽራው የት አለ?›› ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ስቆ ከጨረሰ በኋላ ‹‹መሰንቆ የሚመታው ነው›› አለኝ፡፡ ለራሱ ሰርግ መሰንቆ የሚጫወት ሙሽራ በማየቴ በጣም ተገረምሁ፡፡ ለምን እንዲህ እንደሆነ ስጠይቅ ደግሞ ‹‹እሱ ጎበዝ አዝማሪ ስለሆነ ነው›› የሚል ምላሽ ተሰጠኝ፡፡

ከዚህ ሌላ በዚህ ሰርግ ያጋጠመኝ አዲስ ነገር በሰርግ ቤቱ የሚገጠሙት ግጥሞች ናቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የሚሰጧቸው ግጥሞች ከዘፈንነት ይልቅ ምሾነት ባህርይ አላቸው፡፡ የአንድን ሰው ስም በተደጋጋሚ እያነሱ ዛሬን እንኳን ብቅ ብለህ ልጅህን ዳር ይላሉ፡፡ ስሙ ስለሚነሳው ሰው ማንነት ጠየቅሁ፡፡ የሙሽራዋ አባት ነው፡፡ ‹‹ከሞተ ቆይቷል›› የሚል መልስ አገኘሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግጥሞቹ የሰርግ አድራጊውን ቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ በሰርግ ቤቱ ውስጥ ሃዘን፣ ደስታ፣ ውዳሴ ወዘተ የሚገልፁ ግጥሞች ይከወኑ ነበር፡፡

በዚህ መረጃ በአንድ የአዝማሪ ሰርግ ላይ የነበሩ ክዋኔዎች ቀርበዋል፡፡ ከመረጃው በሰርጉ ውስጥ ይከወኑ የነበሩ ጉዳዮች ውስጥ አብዛኞቹ ሰርጉ የአዝማሪ ሰርግ በመሆኑ ምክንያት የተደረጉ መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ ለምሳሌ በክዋኔው ወቅት መሰንቆ የሚጫወት ሙሽራው መሆኑ፣ በርካታ ሰዎች ግጥም በማቀበል ተሳታፊ የነበሩ መሆናቸውና በሚነሱ ግጥሞች ውስጥ ቤተሰባዊ ጉዳዮች መነሳታቸው በጣም በሚቀራረቡና አንድ አይነት በሆኑ ሰዎች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ይህም በራሱ አዝማሪዎች የራሱ የሆነ መልክ ያለው ሰርግ ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ከቀረቡ መረጃዎች የወሎ አዝማሪዎች ለረጅም ዘመን የኖረና ስር የሰደደ የሰርግ አከዋወን ስርዓት ያላቸው ሲሆን ይህ ስርዓት አዝማሪዎችን በመኖሪያ መንደራቸው ለሚያውቃቸው ሁሉ መለያ ሆኖ የኖረ እንደሆነና ዛሬም ድረስ በዕድሜ

---

በመሆኑ በተለይ በምልከታ ያገኘኋቸውን መረጃዎች በፅሁፉ ውስጥ ሳስገባ ልክ እንደዚህ ሃረግ በአንደኛ መደብ በመጠቀም ሁኔታውን ገልጫለሁ፡፡

ገፋ ባሉና በገጠራማው አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ የሚተገበር ባህል እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በተረፈ ይህ ጥንታዊ ልማድ በዛሬው ለውጥ በዳሰሰው የአዝማሪዎች የሰርግ ስርዓት ውስጥ እንኳን የተለያዩ አሻራዎችን እንዳሳረፈ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ሰርግ እስከተደረገ ድረስ የድግሱን ቀን ሶስት ቀን ድረስ ማራዘም አሁንም ድረስ ያለ ሲሆን ጅማሬው ከቀደመው የቦታ ርቀት የተነሳ የተፈጠረ ነው፡፡



ስዕል 4.የአዝማሪ ሰርግ፣ክትክታ መንደር

ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪዎች ጋብቻን ከአዝማሪ ጋር ብቻ እንደሚፈፅሙ አስቀድሞ ተገልጧል፡፡ ይህም የቡድኑን ህልውና ለማስቀጠልና የገቢ ሁኔታን ለማጎልበት ሲባል ሲደረግ እንደኖረ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከገቢ ሁኔታ አንፃር የተፈጠረው ሌላው የቡድኑ ቅርፅ የባልና ሚስት አዝማሪዎች የስራ ክፍፍል ነው፡፡ ይህ የስራ ክፍፍል ምን እንደሚመስል ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6.1.1.4. *ፆታዊ የስራ ክፍፍል*

በአዝማሪ ቡድን ውስጥ ‹‹አዝማሪ›› የሚለው ቃል ለሴትም ለወንድም ፆታ የሚያገለግል የሙያ መጠሪያ ነው፡፡ ሁለቱም ፆታዎች ዘፈንን በቅንጅት በመስራት ይኖሩበታል፡፡ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች በዚህ ልማዳዊ ስርዓት መሰረት ኖረዋል፡፡ በኑሮም ሆነ በዘፈን ክዋኔው ሂደት ውስጥ በሁለቱ ፆታዎች መካከል የስራ ክፍፍል

አለ። በኑሮ ሂደት ውስጥ የቤት ውስጥ ስራዎችን መስራት የሴት አዝማሪዎች ድርሻ ሆኖ ኑሯል። ቀደም ሲል አዝማሪዎች በዘፈን ስራ ብቻ በሚተዳደሩበት ጊዜም ሆነ አዝማሪዎች የመሬት ባለቤት ከሆኑበት ከደርግ ጊዜ ወዲህ ምግብ ማብሰልን የመሰሉ ስራዎች በሴቶች የሚከወኑ ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ሴቶች በቤት ውስጥ የነበራቸውን ሚና የገለፁልኝ መረጃ ሰጪ ቀጣዩን ብለዋል፡-

> ማታ በስድስት የመጣን ከሆነ በኋላ ሴቶች አንነሳለን። እንተጣጠባለን፡ ወደማበሳሰል እንሄዳለን። ወንዶች ወጥተው ተናፍሰው ይመጣሉ። ያንን በልተን ወደ መጀን ጠጅ ቤታችን። ያቺን አበሳስለን ለማታም አዘጋጅተን ነው የምንሄድ። ከጠጅ ቤቱ እንዲሁ የምትመጣ ባለጠጅ ቤት ትወስደናለች። ደንበኛም ሆነሽ ከቆየሽ እኔ ደንበኛዬን ነው የምወስድ ትላለች። ማታ እርጥብ ስጋም ከሆነ በፌስታላችን ይዘን እንመጣለን። ብርንዶ በልተን እንተኛለን። ለማልዳ የተጣደ ስጋ ይበስላል። ያንን ፈታ ይላል። ያንን ሲንፈቀፈቅ የዋለ አጥንት ወለቅ ወለቅ ይላል ካጥንቱ፣ ያንን በቅቤው በምኑ በልተን ወደ ጠጅ ቤታችን። እንጀራ መጋገር የለም ተገዝቶ ነው። ደሞ ራቅ ብለሽ ተሄድሽ እንዲያው ምናልባት፣ ቅል እንይዛለን ማቡኪያ። ያቺን ጥቅልል አርገሽ በሚህቻይቱ አርገን ምጣድ ካገኘን ጋግረን አገልግል አለች። ያቺን እጥፍ እጥፍ አድርገን በዚያች እንከታለን (ቃለመጠይቅ፣ አለምፀሃይ የማና፣ 9/05/2005፣ ውጫሌ) ።

መረጃው፣ ቀደም ባለው ጊዜ ሴት አዝማሪዎች ለስራ በሚሄዱባቸው አካባቢዎች በምን አይነት መንገድ እንደኖሩ ይገልፃል። ዛሬም ቢሆን ባልና ሚስት አዝማሪዎች በአንድ ላይ ሲኖሩ የቤት ውስጥ ስራ በአመዛኙ በሴቶች ብቻ የሚሰራ ነው። ከቤት ውስጥ ስራ ባሻገር የግብርና ስራ ግን በክፍፍል እንደሚሰራ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ። ወንዶቹ ያርሳሉ። ሴቶቹ ደግሞ ያርማሉ፣ ይጎለጉላሉ። ወደ ዘፈን ስራ ሲመጣም እንደ እርሻው ሁሉ የስራ ክፍፍል አለ። ሴቶች ያዜማሉ እንዲሁም ‹‹ይደልቃሉ››[33]፤ ወንዶች ደግሞ መሰንቆ ተብሎ የሚጠራ የሙዚቃ መሳሪያቸውን ይጫወታሉ፤ እንዲሁም ያዜማሉ። ይህ የስራ ክፍፍል ልማዳዊና ረጅም ዘመን የኖረ ሲሆን በታዳሚውም ሆነ

[33]በአካባቢው ቋንቋ ይደንሳሉ የሚል ትርጉም አለው።

በራሳቸው በአዝማሪዎች እንዲሆን የሚጠበቅ ነው፡፡ በአንድ ክዋኔ ጊዜ አንድ ላይ የሚቆሙት ሴትና ወንድ አዝማሪዎች አንድም በጋብቻ አለዚያ ደግሞ ለስራ ሲባል ብቻ የተጣመሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት በተለይ ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪዎች ለስራ የሚንቀሳቀሱት ሴትና ወንድ ሆነው በህብረት ነበር፡፡ በጉዞው ህጎች አሉ፡፡ ከህጎቹ ውስጥ ዋናዎቹ ‹‹ማንም አዝማሪ ያገኘውን ገንዘብ አብረውት ለተጓዙት ሌሎች አዝማሪዎች ሁሉ ማካፈል አለበት››፣‹‹አንድ አዝማሪ የእርሱ ያልሆነችን ሴት ለግብረ ስጋ ግንኙነት መመኘት የለበትም›› የሚሉ ናቸው፡፡ ህጎቹ ለቡድኑ የግጭት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን የኢኮኖሚና የትዳር ደህንነትን አደጋ ላይ መውደቅ የሚከላከሉ ናቸው፡፡ ማንኛውም የቡድኑ አባል ለእነዚህ ህጎች ተገዢ ሲሆን ይህ እንዲሆን መሃላ ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡ መሃላው የመሰንቆ ጭራ መበጠስ ነው፡፡ ትርጓሜውም እነዚህን ህጎች ብጥስ ‹‹የዕዝራ አምላክ እንደዚህ እድሜዬን ይቁረጥ›› ማለት ነው ይላሉ፡፡ መሃላው ለሴቷ ያለፍርሃት እንድትጓዝ ዋስትናዋ በመሆኑ ባለቤቷ ባይሆን እንኳን ከማንም ወንድ አዝማሪ ጋር ሄዳ ትሰራለች፡፡

መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ቀደም ባለው ጊዜ ወንድና ሴት አዝማሪዎች ለየብቻ ከመስራት ይልቅ በአንድ ላይ መሆንን ይመርጣሉ፡፡ ምክንያቱም ብቻውን ከሚዘፍን አዝማሪ ይልቅ ሴት ይዞ የሚዘፍን አዝማሪ የተሻለ ገቢ አለው፡፡ ይህም የሚሆነው በሙዚቃ ክዋኔ ውስጥ ሴቶች ካላቸው ሚና የተነሳ ነው፡፡ አንዲት ሴት ለወንዱ አዝማሪ፣ የድምፅም ይሁን የመሰንቆ መምታት፣ ወይም የግጥም ማስታወስና መግጠም ችግር ቢኖርበት ጉድለቱን ትሸፍንለታለች፡፡ ለምሳሌ ድምፁ አያምር እንደሁ እርሱ መሰንቆ ብቻ እየመታ እስዋ በድምፅዋ ትዘፍናለች፣ መሰንቆ አመታቱ ጥሩ ባይሆን በውዝዋዜዋና በአጀብዋ የመሰንቆውን ድምፅ በመዋጥ ክፍተቱን ትሞላለች፡፡ የጀመረው ግጥም ቢጠፋበት ታስታውሰዋለች፡፡ የታዳሚውን ስሜት በመቆጣጠር የሙዚቃ ቅኝቱን እንዲለዋውጥ ትመራዋለች፡፡ እነዚህን ማድረጓ ደግሞ እንከን አልባ ክዋኔን ስለሚፈጥር ታዳሚ ይደሰታል፤ ታዳሚ ሲደሰት ደግሞ ጥሩ ሽልማት ይገኛል፡፡ የአዝማሪም የመዝፈን ዓላማ ይኸው ገንዘብ ማግኘት ስለሆነ ሴቶችን ይዞ ለስራ መውጣት ሁልጊዜም የሚፈልጉት ነገር ነው፡፡

ወንድ አዝማሪዎች ከሴት አዝማሪዎች ጋር እንዲሰሩ የሚያስመርጣቸው ሌላም ምክንያት አለ፡፡ ይኸውም ሴቶች የጥሩ ገድ ምልክት ተደርገው የሚቆጠሩ መሆናቸው

ነው። ወንድ አዝማሪዎች ‹‹ሴት የጥሩ ገድ ምልክት ናት›› ብለው ያምናሉ። ሴት ካለች ሽልማት አለ ስለሚሉ በተቻለ መንገድ ሴቶች አብረዋቸው እንዲሰሩ ይፈልጋሉ።

በአጠቃላይ ሴት አዝማሪዎች በሙዚቃ ክዋኔ ወቅት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ይህ ሚናቸውም ጥሩ ገቢ እንዲገኝ ምክንያት ነው። ጥሩ ገቢ ማግኘት ደግሞ የግለሰብ እንዲሁም የቡድኑ ፍላጎት ነው። ስለዚህ ቡድኑ የኢኮኖሚ አቅሙ እንዲጠበቅ የሴቷን ደህንነት ይጠብቃል።

ሴትና ወንድ መረጃ ሰጪዎች እንደገለፁት ሁለቱም በእኩል ደረጃ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው የሚሰሩ በመሆናቸው ከአካባቢያቸው ውጭ ላለው ዓለም ያላቸው ተጋላጭነት እኩል ነው። በመሆኑም የአዝማሪ ሴቶች ገቢ በማምጣትም ሆነ በስልጣኔ ረገድ ከባሎቻቸው ጋር ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ይህ እኩልነት ሴቶችን በባሎቻቸው ዘንድ የተከበሩ አድርጓቸዋል። ይህ ሁኔታ በማርክሳውያን እይታ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ቡድኖች ለሚይዙት ቦታ ኢኮኖሚ ቀዳሚው ምክንያት ነው። በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ወንዶች የበላይ እንዲሆኑና ሴቶች ደግሞ የወንዶች ድጋፍ ሰጪ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምክንያት የማህበረሰቡ የምጣኔ ሃብት ሁኔታ በወንዶች እጅ በመሆኑ ነው Johnson (2005, 126) ሲሉ ከሚሰጡት እይታቸው ጋር የሚመሳሰል ነው። ምክንያቱም ሴት አዝማሪዎች በባሎቻቸውም ሆነ በቡድናቸው ውስጥ የእኩልነት ቦታ እንዲኖራቸው ያደረገ ከወንዱ እኩል ሰርተው ገቢ ማስገኘት ስለቻሉ ነው።ይሁን እንጅ ይህ የደረጃ መመጣጠን ፍፁም እኩል ነው ማለት አይቻልም። የአዝማሪነት ልምዱ ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የሚያደላበት ጊዜያት እንዳሉ መረጃዎች ይገልፃሉ።

እነዚህ አጋጣሚዎች ‹‹ዘፈንን የሚጀምር ወንድ በመሆኑና›› ‹‹በሴቶች መሰንቆ ያለመጫወት ልማድ የሚፈጠሩ ናቸው። ለምሳሌ በየትኛውም የዘፈን መከወኛ አጋጣሚ ሴትና ወንድ አዝማሪዎች አብረው ቢኖሩ ዘፈንን የሚጀምረው ወንዱ ነው። ለዚህ የሚቀርበው ምክንያት ምግብን ወንድ እንደሚባርከው ሁሉ ዘፈንንም ወንድ መባረክ አለበት የሚል ልማድ ነው። ስለዚህም ወንዱ መዲናና ዘለሰኛ በሚባሉ ለአምላክ ምስጋና ለማቅረብ በሚያገለግሉ ዜማዎች ክዋኔውን ይጀምራል። እሱ ዜማዎችን ሲጫወት ሴቷ አረፍ ብላ ትጠብቃለች። ይበቃል የሚለውን ያህልና ከታዳሚዎች ፍላጎት አንፃር አምላኩን አመስግኖ ሲያበቃ ዜማ ወይም ቅኝት[34]

[34] ምንነታቸውና በመካከላቸው ያለው ልዩነት *የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን መልክ* በሚለው ክፍል ቀርቧል።

ይቀይራል፡፡ የሴቷ ተሳትፎ የሚጀምረው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ የዘፈን ክዋኔ ለወንዶች የሚያደላበት ሌላም አጋጣሚ አለ፡፡ ወንዶች ሴቶች ባይኖሩም መዝፈን የሚችሉ ሲሆን ሴቶች ግን ወንዶች በሌሉበት መዝፈን አይችሉም፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመመልከት የተቻለበትን አንድ አጋጣሚ ቀርቧል፡፡ ጥር 22/2005 ዓ.ም ወረኢሉ ከተማ ውስጥ ወ/ሮ አፀደ ለገሰ የተባለች ሴት አዝማሪ ወደ ሰርግ ቤት ለመሄድና ለመዝፈን አንድ ወንድ አዝማሪ ቀጥራ እየተጠባበቀች ነው፡፡ ከሰውዬው ጋር በስድስት ሰዓት ለመገናኘት የተቀጣጠሩ ቢሆንም እስከ ስምንት ሰዓት ድረስ አልመጣም፡፡ ወ/ሮ አፀደ ከዚህ በኋላ ሰውዬው አይመጣም ብላ ተስፋ ቆረጠች፡፡ በዚህ ጊዜ

‹‹እሱ ቢቀር ለምን አንቺ አትሄጅም?›› አልኳት፡፡

ወ/ሮ አፀደ ‹‹ያለ መሰንቆ ምን እሰራለሁ›› አለች፡፡

‹‹እንዲሁ እንደተጠራ ሰው ለምን አትሄጅም?፡፡ ሌላ መሰንቆ የያዘ ሰው ካገኘሽ ከእርሱ ጋር ትሰሪያለሽ፡፡ ካላገኘሽ ደግሞ ምሳሽን በልተሽ ገንዘብ ሰጥተሽ ትመለሻለሽ›፡፡[35]

‹‹አይ ያማ አይሆንም የሃገሩ ሰው አዝማሪ መሆኔን ያውቃል፡፡ መሰንቆ የያዘ ሰው ጋር ተከትዬ ካልሄድሁ ‹ለቅልውጥ› መጣች ብሎ ይሰድበኛል፡፡ አንዲት ሴት ምን ጎበዝ ዘፋኝ ብትሆን መሰንቆ የያዘ ሰው ተከትላ ነው የምትሄድ፡፡ ወላ መሰንቆው ጅል ይሁን፡፡ ብቻዬን ሄጀ ልዝፈን ብትል የሚሰማት የለም›› የሚል መልስ ሰጠች፡፡

እንግዲህ ከዚህ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ሴቶች በየትኛውም የችሎታ ደረጃ ላይ ቢሆኑ ከወንዶች ጋር አብሮ መስራት ግዴታቸው መሆኑን ነው፡፡ እዚህ ግዴታ ውስጥ የከተታቸው ደግሞ ወንዶች እንጅ ሴቶች መሰንቆ የማይጫወቱ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ግን የሚቆጫቸው እንደሆነ የተለያዩ ሴት አዝማሪዎች ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ወ/ሮ አለምፀሃይ የማና ‹‹ሳስበው በጣም ይበሽቀኛል፡፡ ይህንን የመሰለ ድምፅ ይዤ መሰንቆ ስለማልጫወት ብቻ የለፋሁበትን ለማንም ጅል ሳካፍል ኖርሁ እላለሁ›› ብለዋል፡፡ ከመረጃዎች ማየት የሚቻለው አዝማሪነት የሁለቱም ፆታዎች ስራ ቢሆንም በመካከል የስራ ክፍፍል መኖሩን ነው፡፡ በስራ ክፍፍሉ የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይሁንና ለአዝማሪነት ዋናው ጉዳይ የመሰንቆ ጨዋታ በመሆኑ በዘፈን ክዋኔ ውስጥ

[35]. መረጃዎች እንደሚሉት በአካባቢው ሠርግ ተጠርቶ የሄደ ሰው ለባለሰርጎች አቅሙ የሚፈቅደውን ያህል ገንዘብ ሰጥቶ ይመጣል፡፡ ለወ/ሮ አፀደ ይህንን ምክር የሰጠኋት ከዚህ ዕውቀት በመነሳት ነው ፡፡

ሁልጊዜ መኖር ያለበት ወንዱ ነው። ማለትም ወንዱ ሴቷ በሌለችበት የዘፈን ክዋኔውን መስራት የሚችል ሲሆን ሴቷ ግን ያለ ወንዱ ዘፈንን በሰዎች ፊት መከወን አትችልም። ለወሎ አዝማሪዎች መለያ ከሚሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ሌላው ሃይማኖታቸው ነው።

### 6.1.1.5. ሃይማኖት

መረጃዎች እንደሚሉት በወሎ በአመዛኙ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሕዝብ ይኖራል። በአካባቢው የእስልምናም ሆነ የክርስትና እምነት ስር የሰደደ መሰረት ያላቸው እንደሆነ በአካባቢው የሚገኙ እንደ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት(ላሊበላ)ና ተድባብ ማርያም(ተንታ) እንዲሁም የባቂላ መስጅድ (ወረኢሉ)፣ የደሴ መስጅድ (ደሴ) ያሉ ዕድሜ ጠገብ የክርስትና እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖቶች የአምልኮ ስፍራዎች ዋቢዎች ናቸው። አካባቢው በአያሌው ጎልቶ ከሚታይባቸው እሴቶቹ ውስጥ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታይ ህዝቦች በከፍተኛ የማህበራዊ ህይወት ትስስር ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውም አንዱ ነው።

በአካባቢው የሚኖሩ አዝማሪዎችም ወሎዬነታቸው ከሚገለፅባቸው መልኮች ውስጥ ከላይ የተገለፀውን የአካባቢውን ማህበረሰብ የሃይማኖት አከታተል ስርዓት የሚጋሩ መሆናቸው አንዱ ነው። በዚህ የተነሳ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች ውስጥ የተወሰኑት የእስልምና የቀሩት ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች ከመኖሪያ ቦታ አንፃር ሲታዩ የተለያየ እምነት ተከታይ ሰዎች አንድ ላይ ተቀላቅለው የሚኖሩ የመሆናቸውን ያህል የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች ደግሞ ለየብቻ የሚኖሩባቸው አካባቢዎች አሉ። ከዚህ አንፃር በደሴ ከተማ የሁለቱም እምነት ተከታይ አዝማሪዎች ይኖራሉ። የሚከተሉት ሃይማኖት ግን በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ ጣልቃ በመግባት የሚለያያቸው አይደለም። ግንኙነታቸው በጋብቻ እስከመተሳሰር የሚደርስ ነው። በዚህ መልኩ እንደሚኖሩ መረጃ ከሰጡ ሰዎች ውስጥ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ሁለት መረጃ አቀባዮች ሁለቱም የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደሆኑና የትዳር አጋሮቻቸው ግን የክርስትና እምነት ተከታዮች መሆናቸውን ገልጠዋል። ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች ውስጥ አንደኛው በትዳሩ ምክንያት የክርስትና እምነት ተከታይ እንደሆነ ሌላኛው ግን ከባለቤቱ ጋር ለብዙ ዓመታት የኖረ ቢሆንም በዚያው በእስልምና እምነት ተከታይነቱ እንዳለ ገልፀዋል።

ከደሴ ውጪ በሆኑ የጥናቱ ትኩረት በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ አዝማሪዎች ግን ከሚኖሩበት ቦታ አንፃር የእምነታቸው ምንነት ተለይቶ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በለጋምቦ ወረዳ፣ ኢላዳ/ በረከት፣ በደሴ ዙሪያ፤ ደረቅ ወይራ፣ የሚኖሩ አዝማሪዎች የእስልምና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፣ በአምባሰል/ማርዬና በመቄት ቀለባስ መንደር የሚኖሩ አዝማሪዎች ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

አዝማሪዎቹ የሚከተሉት እምነት በሚኖሩበት አካባቢ እንዲገለፅ ምክንያት የሆነው ዘፋኝነታቸው  ነው፡፡ ምክንያቱም ከጅምሩም ሆነ ዛሬ ዘፈንን በተለይ ለኑሯቸው መግፊያ ብለው የሚከውኑት በመሆኑ ገቢ የማግኘት ሁኔታቸው ዘፈኑንን በሚያቀርቡለት ወገን ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ስለዚህም በተለይም ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ የአሰፋፈራቸው ሁኔታ የአካባቢውን ገዥዎች (ሹመኞች) አሰፋፈር ተከትሎ በመሆኑ የገዥው አገልጋይ እስከሆኑ ድረስ የእሱን የአኗኗር ፈሊጥ መከተል ግዴታ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሁኔታው ሲታይ Hussein (2001) እንዳሉት ለጋምቦና ደሴ ዙሪያ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነ ህዝብና አስተዳደር የነበረበት ሲሆን አምባሰልና መቄት ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታይ አስተዳዳሪና ህዝብ የሚኖሩባቸው ነበሩ፡፡

ይሁን እንጅ ይህ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች የሚደባለቅበት ጊዜ ብዙ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ ጋብቻ ዋናው ምክንያት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አዝማሪዎች ጋብቻን የሚፈፅሙት እርስ በእርስ ብቻ በመሆኑ ደረቅ ወይራ የሚኖር አዝማሪ አምባሰል ከምትኖር አዝማሪ ጋር ጋብቻ ሊፈፅም ይችላል፡፡ እንግዲህ በዚህ ጊዜ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ ሰዎች ሊጋቡ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ታዲያ በእንደዚህ አይነቱ ወቅት አንዱ የሌላው እምነት በመቀበል ኑሮ ይቀጥላል፡፡ ቀጣዩ ጥቅስ ይህንን የሚያሳይ ነው፡፡‹‹ በሃይማኖት ብቻ እኔ እስላም ተሆንሁ ልጆቼ እስላም፣ ተፈለገም ክርስቲያን ይሆናል፡፡ አሁን የደረቅ ወይራ ሰው እስላም ነው፡፡ የከድጆ ሰው እስላም ነው፡፡ የአምባሰል ሰው ክርስቲያን ነው፡፡ እዚህም የዞረ አለ፡፡ ግን ጋብቻ አይከለከልም፡፡ እኛ የምንፈልገው ትዳሩን ነው፡፡ ኒካ ይታሰራል፡፡ እኛ ደግሞ አምጥተን ክርስትና እናስነሳለን፤ እንደ ሙጫ ልጅ›› (ብርሃን ትኩ፣ቃለ መጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም.፣ ማርዬ)፡፡

ይህ ጥቅስ በአገር ደረጃ ሲታይ ወሎ ውስጥ የእስላምና የክርስቲያን ተብለው የተከፈሉ አካባቢዎች መኖራቸው አመልክቷል፡፡ ዳሩ ግን በትዳር ደረጃ እስላም ከክርስቲያን መጋባት የሚችል መሆኑንና ከሃይማኖቱ ይልቅ ለትዳሩ ከፍ ያለ ቦታ እንደሚሰጥ፣

ይህ ነፃነት ደግሞ እስከ ቤተሰብ ደረጃ የሚደርስና ልጅ ከአባቱ የተለዬ ሃይማኖት ሊከተል የሚችልበት ዕድል እንዳለ ያስረዳል፡፡ ይህ ሁኔታ በቡድኑ ውስጥ ከአዝማሪነት የሚቀድም ምንም ነገር እንደሌለና አዝማሪነት ቡድኑን ምን ያህል ከሌላው ሰው ጋር እንደለያየው፣ እርስ በእርሱ ደግሞ ጥብቅ የሆነ ቁርኝት እንዲመሰርት ማድረጉን የሚያመላክት ነው፡፡

### 6.1.1.6. የሚስጥር ቋንቋ

ለዚህ ጥናት በተመረጡ ደረቅ ወይራ፣ ለጋምቦ፣ አምባሰልና መቄት ወረዳዎች የሚኖሩ አዝማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ነው፡፡ ይሁን እንጅ አዝማሪ ካልሆኑ ሰዎች ሚስጥርን የሚጠብቁበት የራሳቸው ቋንቋ አላቸው፡፡ የስነ ልሳን ምሁራን ይህን አይነት ባህርይ ያለውን የአንድ ቡድን ቋንቋ Argot /‹‹አርጎት›› ብለው ይጠሩታል፡፡ ይህ ንዑስ ርዕስ የዚህ ቋንቋ ምንነት ባህርያትና ቡድኑ እንዴት ‹‹ቋንቋው››ን እንደሚገለገልበት የቀረበበት ነው፡፡

አዝማሪዎች እርስ በእርሳቸው የሚግባቡበትን ‹‹ቋንቋ›› ‹‹እንዛትኛ›› ብለው ይጠሩታል፡፡ አዝማሪዎች እንዛትኛ መቼ እንደተጀመረ አያውቁም፡፡ ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ በዚኸው ‹‹ቋንቋ›› አባቶቻቸው ሲጠቀሙበት እንደኖሩ ይገልፃሉ፡፡ በስራ ላይ ሲሆኑ ሚስጥር ለመጠበቅ፣በቤት ውስጥ ደግሞ ለመግባባት ይገለገሉበታል፡፡ ስራን በሚሰሩበት ጊዜ ሊጠብቁት የሚገባ ሚስጥር ይኖራል፡፡ ለምሳሌ እነሱ በመጠጥ ቤትም ሆነ በሰርግ አለዚያ በሌሎች ቦታዎች ዘፈንን የሚከውኑ ታዳሚን አስደስተው ገንዘብ ለማግኘት መሆኑ እየታወቀ አንዳንድ ምንም ገንዘብ ሳይሰጥ እነሱን እንደልቡ አዝዞ ማስዘፈንና መዝናናት የሚፈልግ አለዚያ ደግሞ በሚያቀብለው ግጥም ሌላን ታዳሚ በነገር እየጎሸመ የስራ ድባቡን ሊያደፈርስ የተነሳ ታዳሚ ያጋጥማቸዋል፡፡ ይህንን ጊዜ ወንዱ አዝማሪ ‹‹ቃኸው›› ይላል፡፡ ተይው ማለቱ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሚሸልም የሚመስላቸው ሰው ሲመጣ ‹‹የቹ›› ይላል ያኸው ነው፡፡ በእንዲህ አይነት መልኩ ሽልማት ሊሰጡ የሚችሉና የማይችሉ ሰዎችን በመለየትና በሚስጥር በመነጋገር ስራቸውን ይሰራሉ፡፡

አንዳንዴ ደግሞ ስራ በሚሰሩበት ጊዜ (ዘፈንን በመጠጥ ቤት፣ በሰርግ ቤትና በተለያዩ ቦታዎች በሚጫወቱ ጊዜ) በሌሎች ጊዜ ጠብ ሊጋጥማቸውና ጠቅላላ ሁኔታው ለደህንነታቸው አስጊ የሚሆንበት አጋጣሚ ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ በእንደዚህ ያሉ

አጋጣሚዎች ሁኔታውን ቀድሞ የተገነዘበ አዝማሪ ለሌላው አዝማሪ እንዛትኛውን ተጠቅሞ በሚስጥር ጉዳዩን በማስረዳት መወሰድ የሚገባውን የመፍትሄ እርምጃ በመውሰድ ራሳቸውን ከአደጋ ይጠብቃሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ መረጃ ሰጪ ‹‹ቋንቋው›› ምን ያህል ህይወታቸውን ከአደጋ የሚጠብቁበት መሳሪያቸው እንደሆነ ሲያስረዳ የሚከተለውን ማስረጃ አቅርቧል፡-

> አንድ ቀን እኔና ጓደኛዬ ወልድያ ሰርግ ሄደናል፡፡ እኛ እንዘፍናለን፡፡ ሙሽራይቱ የመጀመሪያ ጓደኛዋን ትታ ሌላ ሰው የምታገባ ኑራለች፡፡ በዚህ የበሸቀው የቀድሞ ጓደኛዋ በአካባቢው ቁሞ ሙሽሮች ወደ ዳሱ እስኪወጡለት እየጠበቀ ነው፡፡ ይህንን አንድ ሰው ለሌላ ሰው ሲያወራ ሰማሁት፡፡ ልክ ሙሽሮች ወደ ዳሱ ሲወጡ ለጓደኛዬ በእንዛትኛ ተሎ በል ከዚህ ዳስ እንውጣ ጠብ ሊነሳ ነው አልሁት፡፡ ተያይዘን ወጣን፡፡ ወዲያውኑ በዳሱ ውስጥ ተኩስ ተሰማ፡፡ አካባቢው ተበጠበጠ፡፡ በመጨረሻም ከሙሽራዋ ጋር አራት ሰው ሞተ፡፡ እኛ በቋንቋችን የተነሳ ሁለታችንም ተረፍን፡፡ ይህ ቋንቋ ባይኖር በአማርኛ ነበር የምናወራ፡፡ ይህንን ጊዜ ምን ሚስጥር ታውቃላችሁ ተብለን በራሳችን ላይ ችግር እንፈጥር ነበር፡፡ ግን ቋንቋችን አዳነን (በሪሁን መላክ፣ ቃለመጠይቅ፣ 27/07/2005 ዓ.ም.፣ ቀለባስ)፡፡

መረጃ ሰጪው በዚህ መረጃ እሱና ጓደኛው በእንዛትኛቸው የተነሳ ራሳቸውን እንዴት ከአደጋ እንደጠበቁ፣ ‹‹ቋንቋው›› ለህልውናቸው ከፍተኛ አለኝታ እንደሆናቸው ይገልፃል፡፡ በሌላ የህይወት አጋጣሚም ‹‹ቋንቋውን›› ሚስጥርን ለመጠበቅ ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ያጋጠመኝን (የዚህ ጥናት አድራጊ) ጉዳይ ብገልፅ ጉዳዩን አጉልቶ ለማሳየት ይረዳል፡፡

> ቦታው ቀለባስ መድሃኒዓለም ነው፡፡ ክትክታ መንደር የመድሃኒያለምን በዓል ለማክበር ካረፍሁበት ቤት ባለቤቶች ልጅ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ሄጃለሁ፡፡ በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ታቦት ወጥቷል፡፡ ህዝቡ በሁለት አቅጣጫ ተከፍሎ

ቆሚል፡፡ በአንዱ ክፋይ አብሬያት ከሄድጊት ልጅ ጋር (በለጥ ትባላለች) ቆመናል፣ ሌላው ክፋይ ከፊት ለፊት ይታያል፡፡ በለጥ በእንዛትኛ አንድ ነገር ተናገረች፡፡ ምን አልሽኝ አለቻት አልጊት፡፡ ድንግጥ አለችና አይ እድሌ እኔ እኮ አንቺ እንደእኛ መስለሽኝ በቋንቋ ማውራቴ እኮ ነው፡፡ እረስቼሽ አለች፡፡ እኮ ምንድን ነው ያልሽው፡፡ አልነግርሽም አለች፡፡ ልትነግሪኝ የፈለግሽውን ንገሪኝ እንዛታ ባልሆን ጓደኛሽ ሆኜ አይደል አብሬሽ የቆምሁ አልሁ፡፡ ‹‹ከዚህ ከባላገሮች ጋር አንቁም ነይ ወደ ዘመዶቻችን እንሂድ›› ነው ያልሁሽ አለች፡፡ ወደየት ነው እንድንሄድ የፈለግሽው? ወደዚያ አለች፡፡ ፊት ለፊታችን ወደ ሚታየው ቡድን እየጠቆመች፡፡ እኛ የቆምን ከባላገሩ ጋር ነው አለች፡፡ እሽ አሁን ያልሽውን በእንዛትኛ እንዴት እንደሚባል ንገሪኝ አልሁ፡፡ አልነግርሽም፡፡ እኔ ቋንቋዬን ለሌላ ሰው ላላስተምር መሃላ አለብኝ አለች፡፡ ለምን ማልሽ? ሁሉም ሰው ምሏል እንዴ? አወ ባይምልም የመሐላ ያህል ነው፡፡ ቋንቋችንን ለሌላ ሰው አናስተምርም ክልክል ነው (ምልከታ፣ 27/07/2005 ፣ ክትክታ ለበስ) ፡፡

መረጃው የሚሳየው በአዝማሪዎቹ በኩል የቋንቋውን ሚስጥራዊነት መጠበቅ ግዴታ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት እነሱ ቡድናቸውን እንደ ቡድን ጠብቀው ከሚያኖሩበት መንገዶች አንዱ ይኸ የራስን ሚስጥር መጠበቂያ የሆነ ቋንቋ በመፍጠርና የቋንቋውንም ዕውቀት እንደ እነሱ ካልሆነ ሌላ ቡድን በመጠበቅ ነው፡፡

መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ‹‹ቋንቋው›› በተለይ በስራ ወቅት ለሚደረግ የእርስ በእርስ መግባባት የሚያገለግል ቢሆንም በቤት ውስጥም ቢሆን ይጠቀሙበታል፡፡ ለምሳሌ በቤት ውስጥ አዝማሪ ያልሆነ ሰው እንግዳ ሆኖ ቢመጣና ከእርሱ የሚሸሽግ ነገር ቢኖር ‹‹ቋንቋ››ው አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡

ከዚህ በተረፈ ቋንቋው ሚስጥር ከመጠበቅ ውጪም በቤት ውስጥ ለመግባቢያ እንደሚያገለግል መረጃ ሰጪዎች ገልፀዋል፡፡ Leslau (1952,9) ‹‹አዝማሪዎች ሙዚቃን በሚከውኑበት ወቅት ከሌሎች ሰዎች ሚስጥር ለመደበቅ ሲሉ ቋንቋውን ይጠቀማሉ›› በማለት እንደገለፁት የአዝማሪ ‹‹ቋንቋ›› በወሎ ለሚስጥር መደበቂያ ብቻ

ሳይሆን በምልከታና ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በቤት ውስጥ እንደ አንድ አማራጪ መግባቢያ ያገለግላል፡፡ ስራ ሲሰራም ሆነ በእረፍት ጊዜ በቋንቋው የማውራት አጋጣሚ አለ፡፡ ይህንን ጉዳይ የገለፁት መረጃ ሰጪዎች፡- ‹‹አይ ከቤት ያለነውም እናውቀዋለን፡፡ እንደ እናንተ በትምህርት ባንይዘውም፤ ዘፈን ብንዘፍንም ባንዘፍንም ይነግሩናል›› (ፈንታዬ ሞላና ዘሪቱ ከበደ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 17/04/2005 ዓ.ም.፣ ደረቅ ወይራ) በማለት ቋንቋው በስራ ቦታ ብቻ ሳይሆን በቤት ውስጥም አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡ ይህንን ጉዳይ ከመጋቢት ሃያ ስድስት እስከ መጋቢት ሰላሳ 2005 ዓ.ም. ድረስ ቀለባስ በነበርሁበት ጊዜ ተመልክቻለሁ፡፡ የመድሃኒዓለምን በዓል ለማክበር የተሰበሰቡ አዝማሪዎች በየንግግራቸው ጣልቃ በማስገባት በ‹‹ቋንቋው›› ይገለገሉበት ነበር፡፡

ከነዚህ መረጃዎች ለዘፈን ስራ የሚወጣም ሆነ የዘፈን ችሎታ የሌለው አዝማሪ ‹‹ቋንቋውን›› የማወቅ እድሉ ሰፊ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ቋንቋው በቤት ውስጥም አገልግሎት ይሰጣልና፡፡ ይህ ከቤት ውስጥ በቋንቋው የሚደረግ መግባባት ሆን ብሎም ባይሆን በቤት ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ ቋንቋውን የሚማሩበት አንድ መንገድ ነው፡፡

አዝማሪ መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልፁት እንዛትኛ በራሱ ሙሉ ቋንቋ ነው፡፡ በቋንቋው ምንም አይነት ነገሮችን መግለፅ ይቻላል፡፡ በህይወታቸው ውስጥ ያሉ እንቅስቃሴዎች በሙሉ በቋንቋው ይገለፃሉ፡፡ በዚህ አቅሙ እነሱና ሌላው የአካባቢ ነዋሪ ከሚነጋገርበት የአማርኛ ቋንቋ  አቅም ጋር ይተካከላል ይላሉ፡፡ እንዲያውም ይህንን ለማስረዳት ‹‹አይደለም እኛ ወሎዬዎች ከጎጃም፣ ከትግሬ፣ ከጎንደር አዝማሪዎች ጋርም ቋንቋችን ይግባባል፡፡ አሁን እኛ አለመጠየቃችን ነው እንጅ በብሄር ብንለይ ቋንቋችን አንድ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንድ አዝማሪዎች ከዶክተሩም ዶክተር አለን፤ ከመምህሩም መምህር አለን፤ ለምን በብሔር አንለይም ይሉ ነበር፡፡ ግን ሃሳቡ ምንም ጥቅም የሌለው ስለሆነ አልቀጠለም››(ማስረሻ ፈንታው፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

አዝማሪዎች ‹‹ቋንቋቸው›› ራሱን የቻለና በራሱ ሙሉ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ አንዳንድ ምሁራን ደግሞ መነሻው አማርኛ ቋንቋ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ Leslau(1952) መደበኛውን አማርኛ ቋንቋ ሆን ብሎ በማጣመም እንደሚፈጥሩትና የአዝማሪ ቋንቋ ቃላት ‹‹ስር›› ከተሰኘው የአማርኛ የቃል ክፍል የሚመሰረቱ ናቸው፡፡ አመሰራረታቸው መደበኛውን የአማርኛ ቋንቋ በማጣመም ሲሆን ቃላቱ የሚከተሏቸው የአመሰራረት

ሂደቶች መቁረጥ (metathesis)፣ ፊደል/ድምፅ መጨመር (augementation) ማባዛት፣ reduplication፣ ማሳጠር (Substitution of a radical and shortening) ናቸው ይላሉ።

ይሁንና ይህ ከላይ የቀረበው የ Leslau ሃሳብ በተወሰነ መልኩ ሊያስስኬድ ቢችልም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል አይደለም። ምክንያቱም ቀጥሎ በሚቀርቡ ምሳሌዎች ለማሳየት እንደተሞከረው በእንዛታ ቋንቋ ውስጥ ከተባለው መንገድ ውጭ የሆኑና ራሳቸውን ችለው የቆሙ ቃላት አሉ። እነዚህ ቃላት እንደተባለው የአማርኛውን ቋንቋ ቃላት በመቁረጥ፣ ፊደል/ድምፅ በመጨመር በማባዛትና፣ በማሳጠር የተፈጠሩ አይደሉም። እንዲያውም የቃላቱን መገኛ በእርግጠኝነት መናገር ይከብዳል። ይህንንም ሆነ አጠቃላዩን የቋንቋውን ባህርይ ለማስረዳት ቀጥሎ ጥቂት የእንዛትኛ ቃላቶችና ሃረጋት ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 2. የአዝማሪ ‹‹ቋንቋ››/እንዛትኛ ቃላት ጥቂት ምሳሌዎች

| **እንዛትኛ** | **አማርኛ** | **እንዛትኛ** | **አማርኛ** |
|---|---|---|---|
| ቲንካብ | መሰንቆ | ዛፍቷል | የለም |
| ወፋኝ | ዘፋኝ | ኩሮ | አህያ |
| እንዛታ | አዝማሪ | ዝሞ | ከብት |
| ቅሬ | አዝማሪ | እስበስካው | እርስ በእርሱ |
| እቲህ | እዚህ | ይደካካ | ይጋባ |
| ድስንድስ | ደሴ | ተበርግተን | ተነስተን |
| ባበታቴ | ቃሉ | እንደይም | እንሂድ |
| ሩስ | መንግስት | ሰነጠ | መታ |
| ዚሎ | የወንድ ብልት | መሊልኩ | ታላቅ |
| እንጤ | የሴት ብልት | ላልንጀራ | ባልንጀራ |
| ቱሉ | ሁሉ | ዛፌች | አለች |
| ትልሚድ | ልምድ | ሰምክተናል | ሰምተናል |
| ቡጋ | ጅል/አዝማሪ ያልሆነ | ስንኬ | እኔ |
| ሻሜ | ወንድ | እምህና | እናት |
| አቱን | ትናንት | የአብህና | አባት |

ሰንጠረዥ 3. የአዝማሪ ‹‹ቋንቋ››/እንዛትኛ ሃረጋት ጥቂት ምሳሌዎች

| እንዛትኛ | አማርኛ |
|---|---|
| አቱን ለታ ክንቻ ታትዳዋልን ደየመች | ትናንትና ጠጅ ሳትገዛልን ሄደች ፡፡ |
| ሽጌው ነው የወሰገደብን | ሰውዬው ነው የወሰደብን |
| ከመሊልኩ እትሞ ጋራ ላልእንጀራ ነን | ከትልቅ እህቱ ጋር ባልንጀራ ነን፡፡ |
| ዛፈች እንዛታ ማለትን ሰምክተናል | አዝማሪ አለች ማለትን ሰምተናል፡፡ |
| የእምህናና የአብናዬ ላልንጀራ ቶነች | የእናቴና የአባቴ ባልንጀራ ትሆናለች፡፡ |
| ስንካችን አንክማትም | እኛ አናውቃትም፡፡ |
| የስንኬ አድባር ባበታቴ ነው | የእኔ አገር ቃሉ ነው፡፡ |
| የምንደካካው ዘረማ ለዘረማ ነው | የምንጋባው አዝማሪ ለአዝማሪ ነው፡፡ |
| ቡኖና እንዛታ ጋር አይደካካም | አዝማሪ ከባሪያ  ጋር  አይጋባም፡፡ |
| ታቴ ውርምሽ  ሁሉም ይዳካል | በዛሬ ዘመን ሁሉም ይጋባል፡፡ |
| ዘረማ ለዘረማ አሎጠረም | ዘር ለዘር አልቆጠረም፡፡ |
| ባብህኖቻችን በእምህኖቻችን በዘረማ እናጨነጭናለን | በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ጊዜ ዘር መርጠን እንተጫጫለን፡፡ |
| ሰንካችን ከቲያ እነቲያ ወደቲህ እንደካካለን | እኛ ወደዚያ እነዚያ ወደ እኛ መጥተው እንጋባለን፡፡ |
| እምናና አብና ይሚጫሉ | እናትና አባት ደስ ይላቸዋል |
| ሽላይቱ ሌልሞ ለክ ታጠዋለች | ልጅቱ ሌላ መልክ ታወጣለች |
| ስንኬ የጎፎዬን አብህናና እምህና እዳዋቸዋለሁ | እኔ የሚስቴን አባትና እናት እወዳቸዋለሁ፡፡ |
| ኮንቲ ሽላ ሞቀሱኝ | ቆንጆ ልጅ ሰጡኝ |
| እንዛታዎችን እዳዋቸዋለሁ | አዝማሪዎችን እወዳቸዋለሁ፡፡ |
| ጉፎዬን እዳዋለሁ | ሚስቴን እወዳለሁ፡፡ |
| ይቲ የሚያቶኑት ክራሪቲ ጢንጠብ ቶኑ | ክራር የሚጫወቱት ትግሬዎች ናቸው፡፡ |

*ምንጭ፡- አስቴር ሙሉ (ከአቶ መላኩ መድፉ፣ ከአቶ አሰፋ ለገሰ፣ አቶ በሪሁን መላክ፣ ከአቶ ካሳው መላኩ ፣ ከወ/ሮ ትርንጎ መላክ፣ ወይዘሮ አለምፀሃይ የማና ጋር በተለያዩ ቀናት በተኪያሄዱ ቃለምልልሶች ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ)፡፡*

እነዚህ ቃላትና ሃረጋት በጣም ጥቂቶቹ አዝማሪዎች ሲያወሩ በተፈጥሯዊ መቼት፣ ብዙዎቹ ደግሞ አዝማሪዎች ሆን ብለው ቃላቱን ከነትርጉማቸው እንዲናገሩ አርቲፊሻል መቼት በማዘጋጀት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ቃላቱ እንደሚታዩት የተለያዩ የቃላት ክፍሎችንና ሃሳቦችን ወክለው የቆሙ ናቸው፡፡ ደረጃቸውም ከቃላት እስከ ዓረፍተ ነገር የሚደርስ ነው፡፡ የቃላቱ የፆታ፣ የቁጥርና የመደብ አረባብ የአማርኛ ቋንቋን መንገድ የተከተለ ነው፡፡ ለምሳሌ ‹‹ቋንቋ አያውቅም›› የሚለው የአማርኛ ዓረፍተ ነገር በእንዛትኛ‹‹ላንቋ አይለክምም›› በሚል ይገለፃል፡፡ ይህ ዓ.ነገር ለሴት ሲሆን ‹‹ላንቋ አትለክምም››፣ ለብዙ ሲሆን ‹‹ላንቋ አይለክሙም›› በሚል የሚገለፅ ይሆናል፡፡ በዚህ መንገድ ማንኛውንም እንቅስቃሴያቸውን በቋንቋው አማካኝነት መግለፅ እንደሚችሉ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ስለ አዝማሪዎች ቋንቋ ከተሰጡ ትንታኔዎች ቋንቋው እንዛትኛ የሚባል መሆኑን፤ የተጀመረበት ጊዜ በውል የማይታወቅ መሆኑን፣ አዝማሪዎች ምስጢር ለመጠበቅ ሲሉ እንደሚገለገሉበትና ቋንቋው በራሱ ምልዑ ነው ብለው የሚያምኑ መሆናቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት እንዛትኛ ከመጀመሪያውም ቢሆን ምስጢር ለመደበቅ ሲባል የተፈጠረ ቋንቋ እንደመሆኑ ዛሬ አዝማሪነት እየቀረ አዝማሪዎች ሌላው ሰው በተሰማራበት ማንኛውም ስራ ላይ ሲሰማሩ የሙያውን ደህንነት መጠበቅ ያን ያህል አሳሳቢ ስላልሆነ የቋንቋው አገልግሎት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ቋንቋውን ሌሎች አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች እንዳያውቁ ይደረግ የነበረው ጥረትም ቀስ በቀስ እየቀነሰ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ሳይሆን አይቀርም አልፎ አልፎ አዝማሪ ያልሆኑ ነገር ግን በአዝማሪዎች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በተለይ በአምባሰል እንዛትኛ ቋንቋ መናገርና ማዳመጥ የሚችሉ ሆነዋል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የቋንቋው ሚስጥራዊነት እየቀረ መምጣቱን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ስለአዝማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነትና ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ ቀጥሎ ይኸው ቀርቧል፡፡

## 6.1.1.7. ማህበራዊ ደረጃ

በዚህ ጥናት ውስጥ አዝማሪ የሚለው ቃል ወይም ፅንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ ብያኔ እንደሌለውና ቢያንስ ከሶስት አቅጣጫዎች አንፃር ሊበየን እንደቻለ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እነዚህ አቅጣጫዎች የየራሳቸውን አካሄድ የተከተሉ ቢሆንም ከሁሉም

ብያኔዎች አንድ የጋራ የሆነ ነጥብ ማውጣት ተችሏል፡፡ ይኸውም አዝማሪ የሚለው ቃል ዘፈንን በመጫወት ህይወታቸውን የሚመሩና ዘፋኝ በመሆናቸው ምክንያት ከሌላው ማህበረሰብ ተለይተው፣ የራሳቸውን ማንነት መስርተው የሚኖሩ ቡድኖች መጠሪያ መሆኑን ነው፡፡ የዚህ ንዑስ ርዕስ ትኩረት እነዚህን በዘፋኝነታቸው የተለዩ ቡድኖች በሌላው ማህበረሰብ መካከል ያላቸውን ደረጃ ማሳየት ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ አዝማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት፣ ለሌላው ሰው ያላቸው አመለካከት፣ሌላው ሰው ለአዝማሪዎች ያለው አመለካከት የሚሉ ርዕሶች ቀርበዋል፡፡

## 6.1.1.7.1.አዝማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት

በወሎ አዝማሪዎች የሚኖሩባቸው መንደሮች የአዝማሪዎች ብቻ የነበሩ ቢሆንም ዛሬ ግን በተከናወኑ ለውጦች የተነሳ ሁለት መልክ ያላቸው ሆነዋል፡፡ አንዳንዶቹ መንደሮች አዝማሪዎች ብቻ የሚኖሩባቸው ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ አዝማሪና አዝማሪ ያልሆኑ ቤተሰቦች በአንድነት የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት የወሰን ትኩረት ከሆኑት ውስጥ በለጋምቦ ወረዳ በኢላዳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው ‹‹በረከት››፣ በደሴ ዙሪያ የሚገኘው ‹‹ከድጆ››፣ በመቄት ወረዳ በቀለባስ ቀበሌ የሚገኘው ‹‹ክትክታ›› መንደሮች አዝማሪዎች ከሌሎች ሰዎች ሳይቀላቀሉ የሚኖሩባቸው መንደሮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በደሴ ዙሪያ የሚገኘው ደረቅወይራ፣ በውጫሌ ወረዳ በሚገኘው ማርዬ ቀበሌ የሚገኙት፣ ‹‹ዋታባ እየሱስ››፣ ‹‹ጠጠር/ጢጠር አምባ››፣ ‹‹ቦሎ››፣ ‹‹ገገባ›› የተሰኙት መንደሮች ቀደም ሲል የአዝማሪዎች ብቻ የነበሩ ቢሆንም ቀስ በቀስ መቀላቀሉ ስለመጣ ዛሬ ላይ አዝማሪዎችና አዝማሪ ያልሆኑ ቤተሰቦች በአንድነት የሚኖሩባቸው መንደሮች ሆነዋል፡፡

ለብቻቸው የሚኖሩትም ሆኑ ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩት አዝማሪዎች ከሌላውና አዝማሪ ካልሆነው ማህበረሰብ ጋር ሊያነካኩዋቸው የሚችሉ አያሌ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ለብቻቸው የሚኖሩት አዝማሪዎች፣ በገበያ፣ ከመንግስት በሚገኙ ፍትህን በመሳሰሉ የተለያዩ ግልጋሎቶች የተነሳ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር የሚገናኙ ሲሆን በአንድ ላይ ተቀላቅለው የሚኖሩት ደግሞ ከማናቸውም የዕለት ከዕለት ግንኙነት አንስቶ በደስታም ሆነ በሃዘን አብሮ በመተጋገዝና በመተባበር የሚኖሩ ናቸው፡፡

የአዝማሪዎችና አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች የዕለት ከዕለት ግንኙነት ሲታይ በተለይ አዝማሪና አዝማሪ ያልሆኑ ቤተሰቦች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ በዕለት ከዕለት ግንኙነቶች ውስጥ የታመመን መጠየቅ፣ ሃዘን መድረስ፣ ቡና መጠራራትና ስራ መተጋገዝ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ውጫሌ ውስጥ የሚኖሩ ወ/ሮ አለምፀሃይ የማና የተባሉ አዝማሪ እንደገለፁት ቡና የሚጠጡት፣ በዓላትን የሚያከብሩትና የመሳሰሉ ትብብር የሚጠይቁ ተግባራትን የሚፈፅሙ አዝማሪ ካልሆኑ ጎረቤቶቻቸው ጋር ነው፡፡ በሃዘናቸውም ሆነ በደስታቸው የሚደርሱላቸውም እነዚሁ ጎረቤቶቻቸው ናቸው (ምልከታና ቃለመጠይቅ 17/04/2005 ዓ.ም፣ውጫሌ)፡፡

አዝማሪና  አዝማሪ ያልሆኑ ቡድኖች ሃይማኖታዊ ስርዓቶችን በጋራ ይተገብራሉ፡፡ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች እንደአጠቃላዩ ማህበረሰብ ሁሉ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ በተለይ ከቦታ አንፃር ሲታዩ ግን በበረከት/ለጋምቦ፣ በከድጆ፣ በደረቅ ወይራ ያሉ አዝማሪዎች የእስልምና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ በማርዬና ቀለባስ ያሉ አዝማሪዎች የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ ታዲያ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ አዝማሪዎች ከሚከተሉት ሃይማኖት እንዲያደርጉ የሚጠበቁባቸውን ተግባራት ከሌላው ማህበረሰብ እኩል ያከናውናሉ፡፡ ለምሳሌ አቶ መላኩ መድፉ የተባለ የእስልምና እምነት ተከታይ አዝማሪ  እንደገለፀው አዝማሪዎች እስከፈለጉ ድረስ መስጊድ ይሄዳሉ፣ ስግደት ይሰግዳሉ፤ ረመዳንን ይፆማሉ (ቃለ መጠይቅ፣ 16/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

ወደ ክርስትና እምነት ተከታይ አዝማሪዎችም ሲመጣ ጉዳዩ ተመሳሳይ ነው፡፡ አዝማሪዎች እንደሌላው ማህበረሰብ ሁሉ ክርስትና የሚጠይቃቸውን ተግባራት እኩል ከሌላው ሰው ጋር ይከውናሉ፡፡ ፆም ይፆማሉ፣ በዓላትን ያከብራሉ፣ በቤተክርስቲያን በመገኘት ቅዳሴ ያስቀድሳሉ፡፡ ከዚህ ውጭም ቢሆን ሌላው ማህበረሰብ እንደሚያደርገው ለቤተክርስቲያን በቅስናና በድቁና የሚያገለግሉ የአዝማሪ ልጆች አሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አዝማሪዎች የድቁናና የቅስና ትምህርት ይማሩ እንደሆነ ጥያቄ የቀረበላቸው በቀለባስ ነዋሪ የሆኑ አዝማሪዎች የሰጡት መልስ በግርምት የተሞላ ነበር፡፡ ‹‹እህ ምን ማለትሽ ነው!? የእኛ የእህታችን ባል እኮ ቄስ ነው፡፡ ቅድም ከቤተክርስቲያኑ ያየሽው መስቀል ያሳለመን ቄስም አጎታችን ነው›› (በለጡ መላክ፣ ቃለመጠይቅ፣ 27/06/2005 ዓ.ም፣ ክትክታ ለበስ)፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሃይማኖታዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች እንደሌሎች አዝማሪዎች ዘፈንን የማይዘፍኑ ናቸው፡፡

ከዚህ በተረፈ ግን በሃይማኖታዊ ግልጋሎቶች አዝማሪዎች ሌላው ማህበረሰብ ከሚያደርገው ውጪ የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ ይኸውም ታቦታት በሚወጡባቸው በዓላት ከታቦቱ ቀድመው በመቆም ‹‹መዲና››ና ‹‹ዘለሰኛ›› ዜማዎችን በመሰንቆ ብቻ (እነሱ ሳይዘፍኑ) በመጫወት በዓላቱን ያከብራሉ፡፡

በስራ ረገድ ያለው ግንኙነት ሲመረመር ደግሞ አዝማሪዎች ስራቸው መዝፈንና ግብርና፣ ለሌሎች ደግሞ ግብርናና ከዘፈን ውጪ የሆኑ ሌሎች ገቢ የሚያስገኙ ተግባራት ናቸው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ከዘፈን በስተቀር በሚከወኑ ሌሎች ተግባራት አቻ የሆነ ግንኙነት ያከናውናሉ፡፡ ዘፈን ላይ ሲመጣ ግን ጉዳዩ የተለየ መልክ ይይዛል፡፡ ምክንያቱም ዘፈን አዝማሪዎች ብቻ የሚያከናውኑት ተግባር በመሆኑ ይህንን ተግባራቸውን ለማይዘፍኑት በማቅረብ ገንዘብ ያገኙበታል፡፡ የማይዘፍኑት ደግሞ በፈንታቸው ገንዘብ በመክፈል (በሽልማት) ይዝናናሉ፡፡ ግንኙነቱ የአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ መልክ ይይዛል ማለት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ አቶ ብርሃን ትኩ የተባሉ መረጃ ሰጪ ሲገልፁት፣ ‹‹አዝማሪ ከባላገር ይለያል፡፡ እግዚአብሔር እኮ ሲፈጥር አንዱን ደህና አንዱን ሰንካላ ያደርገዋል፡፡ እኛ ስንፈጠር ከእሳቸው ጋር አንድነት የለንም፡፡ እኛ ከሳቢ ነን፣ እነሱ ተከሳቢ ናቸው፡፡ ትናሞግሳቸው እኛን እያኮሩን ነው ያሉ፡፡ በዚያ ላይ በላናቸው (በለጥናቸው ማለት ነው) ይላሉ›› (ብርሃን ትኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/5/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

ይህ ሁኔታም በስራ ረገድ ምንም እንኳን ግንኙነቱ ቢኖር ይህ ግንኙነት ግን እያንዳንዱ ቡድን ያለውን የስራ ክፍፍል የሚያሳይ ነው፡፡ Merriam (1964, 123) እንደሚሉትም አዝማሪዎች በትልቁ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉት የስራ ክፍፍሎች ውስጥ (የስራ ክፍፍል የሌለው ማህበረሰብ የለም) የሙዚቃ ባለሙያነት ድርሻቸውን ወስደው እሱን በማከናወን ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች ናቸው ማለት ነው፡፡

አዝማሪዎች ከሌላው ሰው ጋር የሚገናኙበት ሌላው አጋጣሚ ድግስ ነው፡፡ ለድግሶች ምክንያት ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ በዓላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አለዚያ ሰርግ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱ ምንም ይሁን አዝማሪዎች ሌላው በሚደገስበት ጊዜ መሰንቋቸውን ይዘው በአዝማሪነታቸው፣ አለዚያ ደግሞ መሰንቋቸውን ትተው በጎረቤትነታቸው አዝማሪ ካልሆኑ ሰዎች ቤት የድግስ ታዳሚ ይሆናሉ፡፡ በግልባጩ ደግሞ አዝማሪዎች የአካባቢያቸውን ታቦት ምክንያት አድርገው በሚደግሱት ድግስ ወይም በሚያዘጋጁት ሰርግ ሌላው ሰው ታዳሚ ይሆናል፡፡ ይህንን ሁኔታ የገለፁት መረጃ ሰጪ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ ‹‹አይ አዝማሪ እኮ ብቻውን አይኖርም አዝማሪ ያልሆኑ ጎረቤቶችም አሉት፡፡

በዚያ ላይ ደግሞ ከስጋ ዝምድና ሌላ የፍቅር ዝምድና አለ፡፡ ስለዚህ እንግዳው ከሁሉም አይነት ነው›› (አሰፋ ለገሰ፣ ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

ይህንን ሁኔታ የሚያረጋግጥ አጋጣሚም ቀለባስ/ክትክታ መንደር ውስጥ በመገኘት ለማየት ተችሏል፡፡ በቀለባስ/ክትክታ መንደር የሚኖሩ አዝማሪዎችና የመጋቢት መድሃኒያለምን ዓመታዊ ክብረ በዓልን ድግስ ደግሰው ጎረቤት ዘመድ ጠርተው ያከብራሉ፡፡ የዚህ ጥናት አድራጊም በጥር ወር በአካባቢው ለመረጃ ስብሰባ ተገኝታ በነበረ ጊዜ ነዋሪዎች ባደረጉላት ጥሪ መሰረት የክብረ በዓሉ እንግዳ ሆና በአንድ ቤተሰብቤት ተገኝታ ነበር፡፡ ይህ ቤተሰብ ብዙ እንግዶች ነበሩት፡፡ ከእንግዶች ውስጥ ግማሽ ያህሉ አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች ሲሆኑ ከሁለትና ሶስት ሰዓት በላይ ተጉዘው የመጡ ነበሩ፡፡ ከሩቅ የመጡት እንግዶች ሶስት ቀናትና ከዚያ በላይ ተስተናግደዋል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች የሆኑ አዝማሪዎች ደግሞ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የድግሱ ተሳታፊ ሆነው ሰንብተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ እንግዲህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት አይነት የሚያሳይ ምሳሌ ሲሆን አዝማሪዎች በትልቁ ማህበረሰብ ውስጥ ለራሳቸው የሰጡት ቦታ ምንድን ነው የሚለውን ለማየት ደግሞ ቀጣዩ ርዕስ ቀርቧል፡፡

## 6.1.1.7.2. አዝማሪዎች ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት

Merriam (1964, 123) ‹‹ሙዚቀኞች ከሌላው የማህበረሰብ አባል ባልተናነሰ ሁኔታ የማህበረሰቡ አባል ናቸው›› እንደሚሉት በወሎ የሚኖሩት አዝማሪዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ከሌላው ሰው የሚለያቸው ዘፋኝነታቸው ብቻ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ቀጣዩ ጥቅስ ይህንን ያሳያል፡- ‹‹ . . . ሁሉም ሰው ዘመድ ነው፡፡ የአዳምና ሔዋን ልጅ እኮ ነው፡፡ ቆይ አንቺ የእኛ ዘመድ መሆንሽን ታውቂያለሽ አታውቂም? ሙያ ነው፡፡ ሁሉም የተለያየ ሙያ ይያዝ እንጅ የተለየ ነገር የለውም›› (ማስረሻ ፈንታው፣ቃለ መጠይቅ፣ 11/05/2005ዓ.ም ፣ማርዬ)፡፡

መረጃው አዝማሪዎች ከሌላው ሰው የሚለያቸው ነገር አለ እንደሆነ ለቀረበ ጥያቄ የተገኘ መልስ ነው፡፡ ጥቅሱ ‹‹ሰዎች ሁሉ በሚሰሩት ስራ የተለያዩ ይሁን እንጅ በአፈጣጠራቸውና በሰውነታቸው እኩል ናቸው›› የሚለውን የአዝማሪዎችን አመለካከት ይገልፃል፡፡ በርካታ አዝማሪዎች በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ዕውቀት የተገኘው ከክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች በመሆኑና እያንዳንዱ አዝማሪ ደግሞ ከሁለቱ እምነቶች አንዱን የሚከተል በመሆኑ ብዙ አዝማሪዎች በሃሳቡ ሊስማሙ

ችለዋል፡፡ ነገር ግን አዝማሪዎች በሰውነታቸው ከሌላው ሰው ጋር እኩል ቢሆኑም በሙያቸው የተነሳ ከሌላው የተሻሉ እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ የተሻልን ነን የሚሉትም ክፍል *2.1.9. ስር ‹‹የአዝማሪዎች አመጣጥ››* በሚለው ርዕስ ውስጥ የቀረበው ሃተታ እንደሚለው እነሱ የሚጫወቱት መሰንቆ የተባለ የሙዚቃ መሳሪያ ለድንግል ማርያም ማመስገኛነት ተመርጧል ስለሚሉ ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ደግሞ አዝማሪነታቸው በአንድ ሼህ የተመረቀ መሆኑን ያምናሉ፡፡ እምነታቸውን በቀጣዩ ሃተታ በቡድናቸው ውስጥ ተክለውታል፡-

> አዝማሪ በነብያችን ተመርቋል፡፡ የተመረቀበት ምክንያት አንድ ሸህ ከሸማኔ ዘንድ ጨርቅ ያሰራሉ፡፡ ሸሁ አንዲት የጣት ወርቅ ነበረቻቸው፡፡ ሸማኔው ለሰራው ጨርቅ ያቺን የጣት ወርቅ ይስጡኝ ይላል፡፡ አይ ገንዘብ ልስጥህ ቢሉት አምቢ ይላል፡፡ ለምነውት እሺ ሊል ስላልቻለ እያዘኑ ቀለበታቸውን ይሰጡታል፡፡ ቀለበታቸውን ሰጥተው ጨርቁን ተቀብለው ይሄዱና ከአንዲት ደደሆ[36] ጥላ ስር አዝነው ይቀመጣሉ፡፡ ያን ጊዜተጫዋች/አዝማሪ እየገሰገሰ ቲሄድ ያገኛቸዋል፡፡ ነብያችን ምን ሆነዋል? አቦ እዚህ ላይ ያለ ሸማኔ ጨርቅ አስቋጥሬ ነበር ጨርቁን ስወስድ ቀለበትህን ካልሰጠኸኝ ብሎ እምቢ አለ፡፡ እዚሁ ቁጭ ብለው ይጠብቁኝ ይዤለወት እመጣለሁ ብሎ ወደ ሸማኔው ቤት ሄደና በመሰንቆ እያጫወተ ቀለበቱን እንዲሰጠው ማስገደድ ያዘ፡፡ ገንዘብ ልስጥህ ቢለው እምቢ ቀለበትህን ነው የምፈልግ ብሎ አስጨነቀው፡፡ ሸማኔውም አልለቅም ማለቱን ሲያይ ቀለበቷን ይሰጠዋል፡፡ አዝማሪው ቀለበቷን ይዞ ሸሁ ወደሚጠብቁት ቦታ ሄዶ የያዙት ሸማ ላይ ይጥላታል፡፡ ሸሁም ይህን አይተው በሸማ ብላ፣ መጣልን እንጅ መጣብን አትባል፡፡ እስተልጅ ልጅህ ተመረቅ፡፡ መጋረጃ ገልጠህ ዙፋን ረግጠህ ኑር፣ የመረቅኸው የተመረቀ፣ የረገምኸው የተረገመ ይሁን አሉት፡፡ ምርቃቱ መስራቱን ለማረጋገጥ ደግሞ ይህቺን ደደሆ እርገማት አሉት፣ ረገማት ደረቀች፡፡ መርቃት አሉት መረቃት ለመለመች፡፡ ከዚያም ደደሆዋ ለእሳቸውም መጠለያ ሆና ስለቆየች ከአዝማሪውጋር አብረው መረቋት፡፡

[36]በቆላና በወይና አደጋ አካባቢ የሚበቅል፣ ትናንሽ ፍሬዎችን የሚያፈራ ዛፍ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት (1993፣ 171)፡፡

በዚህ የተነሳ ዛሬ ድረስ አዝማሪ መጣ ሲባል ኸረ እሰይ ግባ በሉት ይባላል የሚል ነው፡፡ (በተለያዩ ቀናት የተደረጉ ቃለመጠይቆችና የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች)

ይህ አፈታሪክ አዝማሪነት የተመረቀ ሙያ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ሙያው ብቻ ሳይሆን አዝማሪው ራሱ ‹‹የመረቀው የተመረቀ፤ የረገመው ደግሞ የተረገመ እንዲሆን›› ስልጣን የተሰጠው እንደሆነም ይገልፃል፡፡ ይህ አዝማሪዎች ስለራሳቸው ያላቸው እምነት ነው፡፡ ይህንን እምነታቸውን በአፈታኮች አማካኝነት ለልጆቻቸው ሲያስተላልፉ ኖረዋል፡፡ አፈታሪኮች ሲጫወቱት በኖሩት ማንነትን የመትከልና የማጠንከር ሚና የተነሳ ሙያው ዘመናትን ሲሻገር ኖሯል፡፡ ይሁንና ሌላው ሰው ይህንን ታሪክ ባለማወቁ ዝቅ አድርጎ ሲመለከታቸው እንደኖረ ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ምናልባት እንኳን ከተናቁ ሊናቁ የሚችሉ ባላቸው የሃብት ደረጃ እንጅ በማንነታቸው ሊሆን እንደማይችል በሃተታም ሆነ ቀጥሎ በቀረበው አይነት ቃልግጥም ይገልፃሉ፡፡

በሰው ልጅነቴ አልጠረጠርም
ግን በድህነቴ ሳልናቅ አልቀርም

(የሮም አያሌው፣ ምልከታ እና ቃለመጠይቅ፣ 19/05/2005 ዓ.ም.፣ በረከት)፡፡

የዚህ ግጥም ከዋኝ ይህንን ቃልግጥም ለመከወን የበቃችው ሌላው ሰውና አዝማሪዎች ያላችሁ ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ሂደት ውስጥ ነው፡፡ ቃል ግጥሙ በአካባቢው (ወሎ) በሌላው ሰውና በአዝማሪዎች እንዲሁም በእጅ ስራ ሰራተኞች መካከል ያለውን የደረጃ ልዩነት ለመግለፅ የሚጠቅም ‹‹የሰው ልጅ ነው›› ‹‹አይደለም›› አባባል መሰረት አድርጎ የተገጠመ ነው፡፡ ማህበረሰቡ የእጅ ስራ ሰራተኞችንና አዝማሪዎችን ‹‹አጥንተ ጎደሎ›› ናቸው/ ‹‹የሰው ልጅ አይደሉም›› ይልና ራሱን ደግሞ ‹‹የሰው ልጅ ነኝ› በማለት ይገልፃል፡፡ ነገር ግን አዝማሪዎች በግጥማቸው ይህ ስህተት ነው፡፡ እኛ ደሃ በመሆናችን እንናቅ ይሆናል እንጅ ዘራችን ምንም እንከን የሌለበት የሰው ልጆች ነን ይላሉ፡፡

አዝማሪዎች የተመረጠ ሙያ ባለቤት ብቻ ሳይሆን ‹‹ከባላገሩ›› የተሻለ ስልጣኔ እንዳላቸውም ይናገራሉ፡፡ ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ምክንያቱ ደግሞ በአዝማሪነታቸው የተነሳ ከቦታ ቦታ መዘዋወራቸው በአካባቢያቸው ከሚኖሩት ገበሬዎች የተሻለ የአካባቢና የአለምን ግንዛቤ ስለፈጠረላቸው እንደሆነ ይናገራሉ ‹‹እኔ ብዙ አገር ዙሪያለሁ፡፡ አዲስ አበባን፣ ጂማን፣ አጋሮን አይቻለሁ፡፡ ከባላገሩ ይቅርና መንደር ለመንደር ከሚከሰበው[37] አዝማሪ የተሻለ ብዙ ነገር አውቃለሁ፤ የሰው ድካም ይገባኛል፤ የገንዘብን ምንነት ተገንዝቤያለሁ፡፡ (ብርሃን ትኩ፣ ቃለምልልስ፣ 12/05/2005ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡ መረጃው አዝማሪዎች ከቦታ ቦታ፣ ከአገር አገር የሚጓዙ ሰዎች መሆናቸው ትልቅ ንቃተ ህሊና የፈጠረላቸው መሆኑን ይገልጻል፡፡ በአጠቃላይ አዝማሪዎች በሙያቸው የተነሳ የተመረጡና የተሻሉ ሆነው እንደተፈጠሩና እንደሚኖሩ ያምናሉ፡፡ ታዲያ ስለራሳቸው እንዲህ የሚያስቡት አዝማሪዎች ስለሌላው ሰውም የሚሉት አለ፡፡

## 6.1.1.7.3. አዝማሪዎች ለሌላው ሰው ያላቸው አመለካከት

አዝማሪዎች በዙሪያቸው ያለው ሌላው ማህበረሰብ ከእኛ በዕውቀት ያነሰ ነው የሚል አመለካከት አላቸው፡፡ በዕውቀት እንበልጠዋለን የሚሉትን ማህበረሰብ አላዋቂነት ለመግለፅ ‹‹ባላገር/‹‹ቡጋ›› ብለው ይጠሩታል፡፡ የባላገሩ አላዋቂነት መጠን አልባ ነው የሚሉት አዝማሪዎች እነሱን ሲንቅና ሲሰድብ የኖረው ስለ ጥበብ ካለው ዝቅተኛ ዕውቀት የተነሳ እንደሆነ ማመናቸውን ቀጣዩ ጥቅስ ይገልፃል፡-

> ድሮ እንደ አነስተኛ ነው የሚያደርጉት፡፡ ጥበቡን ስለማያውቁት እንደ አነስተኛ ያዩታል፡፡ አንዲት ሴት፣ አዝማሪ ወደደች የተባለ እንደሆን ከባላባትነት ስሜቱ ዝቅ ያደረገው ስለሚመስል ልጁን አዝማሪ እንዳይደፍራት አብሉ አጠጡና ሸኑልኝ የሚባል ጊዜ ነበረ፡፡ ግን አዝማሪ በዕውቀትም፣ በመልክም ከባላባቱ ስለሚበልጥ ነው ይሽ ፍርሃት የመጣ፡፡ እንዲያውም ምን የሚባል ነገር አለ መሰለሽ አዝማሪ ሴቶች ቆንጆዎች ናቸው፡፡ እና ሌላው ሰው ይመኛቸዋል፡፡ <u>ስለዚህ አዝማሪ ሚስቱ እንዳትወሰድበት የአዝማሪ ሴት የነካ ይመለጣል የሚል አባባል አለ፡፡</u>

[37]በአዝማሪዎች ቋንቋ፣ በእንዛትኛ ‹‹መከሰብ›› ማለት መዝፈን ማለት ነው፡፡

ስለዚህ አዝማሪ ሴት የትም ብቻዋን ብታድር የሚነካ የለም፡፡ አዝማሪው በጨዋታ መሃል ሆን ብሎ ይህንን ህዝብ እንዲሰማው አድርጎ ይናገራል (አሰፋ ለገሰ፣ ቃለመጠይቅ፣ 15/04/2005፣ ደሴ)፡፡

መረጃው አዝማሪ ያልሆነው ማህበረሰብ ከአዝማሪው ጋር በጋብቻም ሆነ በሌላው ማህበራዊ ግኙነት እንዳይቀላቀል ሲጠነቀቅ ኖሯል፡፡ ይህ የሆነው ግን አዝማሪ ያልሆነው ማህበረሰብ ለጥበብ ያለው ዕውቀት በጣም ደካማ በመሆኑ ነው፡፡ በአንፃሩ አዝማሪው ጥበብን ከመረዳት አልፎ ጥበበኛ በመሆኑ ሴቶቹ በሌላው እንዳይወሰዱበት ጥበባዊ በሆነ መንገድ ይከላከላል ይላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃው ሌሎች ሰዎች ሴት ልጆቻቸው በአዝማሪ እንዳይደፈሩ ይፈሩ እንደነበር ይገልፃል፡፡ እንደመረጃው አባባል ሰዎች አዝማሪዎችን የሚፈሩበት ምክንያት አዝማሪዎች በዕውቀት፣ በውበትና አርቆ በማሰብ ከሌሎች ሰዎች የተሻሉ በመሆናቸው ሴቶችን አግባብተው የፈለጉትን ማድረግ እንደሚችሉ ስለሚያውቁ ነው፡፡

አዝማሪዎች ባላገር ብለው የሚጠሩት አባወራ ለትዳር አጋሩ የማይመች ነው ይላሉ፡፡ ይህ በመሆኑ የተነሳም ሴቷ ከባሏ ያጣችውን ፍቅር ፍለጋ ወደ አዝማሪ የምትመጣበት ጊዜ ብዙ ነው ሲሉ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ቀደም ባለው ጊዜ የባላገር ሴት የአዝማሪን ወንድ በይፋና በህጋዊ መንገድ አታገባም፡፡ አዝማሪውም ቢሆን የባላገር ሴት ማግባት አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም አዝማሪው እሱ ሲዘፍን አብራው ስለማትዘፍን አይፈልጋትም፡፡ እሷ ደግሞ አዝማሪ አላገባም ትላለች፡፡ አቶ መላኩ መድፉ፣ «አይ አናገባትም፡፡ አትዘፍንልንም፡፡ እስዋም አዝማሪ ኣላገባም ትላለች፡፡ ንቀት አለ» ሲል ጉዳዩን ይገልፃል፡፡ ግን ይላል አቶ መላኩ፣ በጨዋታው በባህሪው ትወደዋለች፡፡ በመሰንቆው፣ በአነጋገሩ፣ በቅልጥፍናው ይሰብካታል፡፡ ተሰጦው በሰው ይወደዳል፡፡ ማጫወቱ፤ ሌላ ደግሞ አዝማሪ መልከኛ ነው፡፡ ማንኛውም ነገር ዝግጅተኛ ነው፣ ጥዳት አለው፣ ተጫዋች ነው፣ በተለያየ ነገር ይሄዳል፡፡ ስልጡን ነው፡፡ ባላገር ባሏ ያ ሁሉ የለውም፡፡ ይተኛል ይነሳል፡፡ ስራ ይሄዳል፡፡ ይሄ ነው፡፡ ይህ ይሰለቻታል፡፡ ስለዚህ የአዝማሪ ወዳጅ ታበጃለች›› (መላኩ መድፉ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 14/04/2005፤ ደረቅ ወይራ) ፡፡ ሲል አዝማሪ ቀልጣፋ፣ መልከ መልካም፣ ንፁህ፣ ስልጡን መሆኑን ሲገልፅ በአንፃሩ ሌላው ሰው ግን እነዚህ ባህርያት የጎደሉት መሆኑን ይገልፃል፡፡ ቀጣዩ በተፈጥሯዊ አውድ የተገኘ መረጃም ይህንን የሚያጠናክር ነው፡፡

መረጃው የተገኘው ቀለባስ መድሃኒዓለም ክትክታ መንደር ነው፡፡ በአንድ የአዝማሪ ቤት ውስጥ የሰርግ ስርዓት እየተከናወነ ነው፡፡ የሰርጉ ታዳሚዎች በመንደሯ ውስጥ የሚኖሩ አዝማሪዎችና ከሌሎች መንደሮች የመጡ ገበሬዎች ናቸው፡፡ ሁሉም በአንድ ቤት ውስጥ ቢሆኑም አቀማመጣቸው ግን ለየብቻ ነበር፡፡ እኔ (የዚህ ጥናት አድራጊ) በዚህ ሰርግ ቤት የዚያችው ቀበሌ ነዋሪ ከሆነ ወጣት አዝማሪ ጋር ተገኝቻለሁ፡፡ አዝማሪው በሰርጉ ቤት ያለውን ስርዓትና ሌላውንም ባህል እየገለፀልኝ ስለአጠቃላይ ሁኔታው እንዳውቅ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ስለሰርጉ ባለቤቶች፣ ስለታዳሚዎች ማንነት ስለሰርጉ ደንብ ወዘተ፡፡ በመሃል አንድ መግለጫ ሰጠ፡፡

‹‹ዝም ብለሽ እኮ በማየት እንዛታውንና ቡጋውን ትለይዋለሽ›› እንዴት?

እስቲ እይና አንቺ ንገሪኝ፤

እኔ ልዩነቱ አይታየኝም፤

ኸረ ልብሱን እይው፣ መልኩን እይው ምንም አይገናኝም፡፡ ባላገሩን እይው የመልኩን ክፋት፣

የልብሱን ዘልዛላነት፡፡

አዝማሪው ይህንን የሚናገረው እዚያው የተቀመጡ አዝማሪዎችንና ባላገሩን እያነፃፀረ ነው፡፡ በንፅፅሩ የአዝማሪዎችን በልብስና በመልክ ማማር ይናገራል፡፡ በእለቱ ሁለቱም ወገኖች በቦታው የተገኙት ሰርግ ለመታደም ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ሁሉም በተሻለ አለባበስ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን መረጃ ሰጪው አዝማሪ ለዘመናት ይዞት በኖረው ግንዛቤ የተነሳ ‹‹ከባላገሩ›› ይልቅ አዝማሪው የተሻለ ውበትና አለባበስ እንዳለው ለማስረዳት ሲጥር ይታያል፡፡ እዚህ ላይ ግን የሁለቱን ወገኖች የውበት አጠባበቅና አለባበስ አስመልክቶ ተፅዕኖ ስለሚያደርገው ጉዳይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የሁለቱ ሰዎች የስራ ፀባይ ነው፡፡ አዝማሪዎች ምንም እንኳን የግብርና ስራ ቢሰሩም የእርሻ ስራ ወቅት ሲያልፍ ደግሞ ወደተለያዩ ከተሞች በመንዝ ይዘፍናሉ፡፡ ይኸ ወደ ከተሞች የሚደረግ ጉዞ ደግሞ የንፅህና ንቃተ ህሊና እንደሚሰጣቸው መገመት አይከብድም፡፡ በዚያ ላይ ዘፈኑን የሚዘፍኑት ለሰዎች በመሆኑ ‹‹ከሰው ፊት›› ሲቆሙ ንፁህ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቀለል ያሉ ልብሶችን በመልበስ ረገድም ቢሆን የከተማ ኑሮ ተፅዕኖ እንደምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ‹‹ገበሬው ግን በስራ ፀባዩ የተነሳ የአዝማሪዎችን ያህል ንፁህ ያልሆነ ልብስ ሊለብስ ይችላል፡፡ በውበት አጠባበቅ ረገድም የእነሱን ያህል ላይጨነቅ ይችላል፡፡

አዝማሪዎች ሌላውን ሰው ‹‹ሆዳም›› ነው፡፡ ይላሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ መረጃ የሰጡ አዝማሪዎች እንዳሉት ‹‹የእኛ ሰው ከመጠጡ ይደፍራል እንጅ ለምግብ ግድ የለውም፡፡ ትንሽ ጣፋጭ ነገር ካገኘ በቃው፡፡ ባላገሩ ግን ምግብ በቃኝ አይልም፡፡ ማጓፊፍ ነው ስራው›› ይላሉ ማስረሻ ፈንታው፣ (ብርሃን ትኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም፣ማርዬ) ፡፡ ይህ መረጃ አዝማሪዎች ምግብን መጥነው ብቻ ሳይሆን መርጠው ይመገባሉ ይላል፡፡ ከምግብ ደግሞ ለመጠጥ እንደሚያደሉ፤ ሌላው ሰው ግን ለምግብ እንደሚያደላ ይገልፃል፡፡ አዝማሪዎች በዚህ መረጃ እነሱ የተሻሉ መሆናቸውን ለመናገር ይሞክራሉ፡፡ መረጃው ግን ከዚህ ባሻገር ስለሁለቱ ወገኖች የሚናገረው አለ፡፡ ይኸውም ሌላው ሰው ጉልበትን በሚያደክም ስራ የተሰማራ በመሆኑ ያወጣውን ጉልበት ለመተካት ብዙ ምግብ እንደሚበላ፣ አዝማሪዎች ደግሞ በዘፈን ምክንያት ጉረሮሯቸው የሚደርቅ በመሆኑ ወደ መጠጡ ማድላታቸውን ያሳያል፡፡ ይህም የሁለቱ የስራ ፀባይ በአመጋገብ ልምዳቸው ላይ ያሳረፈውን ተፅዕኖ የሚያመላክት ነው፡፡

ከዚህ በተረፈ አዝማሪዎች ከሰው ፊት ቆመው በማግባባት፣ በማስፈራራትና በሌሎችም መንገዶች ገንዘብን ከታዳሚ የሚጠይቁ በመሆናቸው እነዚህን ጉዳዮች ሲተገብሩ በታዳሚያቸው ፊት ነቃ ብለው ለመታየትና ድፍረትን ለማግኘት እንደሚጠጡ መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ መገለጫቸው ሲሆን እንደቻለ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መልክ አዝማሪዎች አዝማሪ ላልሆነው ማህበረሰብ ዝቅተኛ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በአንፃሩ ሌላው ሰውም ለአዝማሪዎች የሚሰጣቸው ደረጃ አለ፡፡ ይህም በአመለካከቱ ይገለፃል፡፡

## 6.1.1.7.4. ሌላው ማህበረሰብ ስለአዝማሪዎች ያለው አመለካከት

አዝማሪ ያልሆነው ማህበረሰብ ለአዝማሪዎች ያለው አመለካከት በሁለት ተቃርኗዊ ስሜቶች መካከል የሚገኝ ነው፡፡ አንደኛው ስሜት የአዝማሪዎችን ስራ በእጅጉ መፈለግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከአዝማሪዎች ጋር ምንም አይነት ማህበራዊ ትስስር ላለመፍጠር መጠንቀቅ ናቸው፡፡

አዝማሪ ያልሆነው ማህበረሰብ አዝማሪዎችን የግድ የሚፈልግበት ጊዜ አለ፡፡ በተለይ ሰርግ አዝማሪዎች በሌላው ሰው እጅግ የሚፈለጉበት ጊዜ ነው፡፡ አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች አዝማሪ የሌለበት ሰርግ ሃዘን ቤት ነው ይላሉ፡፡ ‹‹ድሮ አዝማሪ ከዳስ ካልገባ

የሞት ቤት እንኳ ያንን ያህል አይከብድም፡፡ ሰርጉ ሃዘን ቤት ይመስላል ይላሉ (አቶ ሽመልስ፣ ቃለ ምልልስ፣ 16/04/2005ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡ ይህ በመሆኑ የተነሳም አንድ አዝማሪ ወደ ሰርግ ቤት በሚመጣበት ጊዜ በተለየ ክብር ይስተናገዳል፡፡ የሚበላውና የሚጠጣው ነገር በተለይ ለእርሱ ተብሎ ይዘጋጅለታል፡፡ አቶ አሰፋ ለገሰ የተባሉ መረጃ ሰጪ እንደሚገልፁት ‹‹የድሮ አዝማሪዎች የሚበሉ የሰርገኛ ወጥ ነው፡፡ የሰርገኛ ወጥ ማለት ለሙሽራ ለሚዜ የሚሰራ ወጥ ነው፡፡ የተለየ ክፍል ይዘጋጅና፤ እንጀራው፤ ወጡ፣ ዳቦም( ሙጌራ) እዚያ እንደ እንግዳ ይበላሉ፡፡ ጨዋታቸውን ይቀጥላሉ›› (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 16/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

መረጃው አዝማሪዎች በሰርግ ቤት የሚደረግላቸውን እንክብካቤ የሚያሳይ ሲሆን እንክብካቤው ከሙሽራ እኩል ነው ይላል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በሰርግ ቤት ውስጥ ካላቸው ተፈላጊነት የተነሳ ነው፡፡ መስተንግዶው ከመብልና ከመጠጥ በተረፈ ‹‹የዳስ ደንብ›› የሚል ስም በወጣለት ደንብ መሰረት ክፍያ ይጨመርበታል፡፡ አዝማሪ ባይኖር ኖሮ ሰርጉ ሰርግ አይሆንም ነበር ስለሚባል አዝማሪውን እንዳይከፋው ጥንቃቄ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይም ሌላው ሰው ሰርግን የሚያደምቀው ድግስ ሳይሆን አዝማሪ ነው የሚል አመለካከት አለው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የወሎ ማህበረሰብ አዝማሪዎች እርጥብ (የመልካም ገድ ምልክት) ናቸው የሚል አመለካከት አለው፡፡ ይህ በመሆኑም አዝማሪዎች ለዘፈን ወደ አንድ አካባቢ በሚሄዱበት ጊዜ መልካም አቀባበል ይደረግላቸዋል፡፡ ቀጣዩ መረጃ ያንን ይላል፡-

> አዝማሪዎች ቢሳደቡም የሚነካቸው የለም፡፡ ድሮ እኔ ህፃን ሁኜ አዝማሪ ተሳደበ ብሎ የሚሳደብ የሚማታ የለም ነውር ነው፡፡ ውሻዎች እንኳን በአዝማሪና በሌላው ሰው ላይ አንድ አይደሉም፡፡ ውሻ በአዝማሪ ላይ አይጮህም ቢጮህ እንኳ አዝማሪው ተው እያለ መሰንቆ እየመታ ያበርደዋል፡፡ እና እነዚህ እንስሳ ሳይቀር የሚወዳቸው ሰው እንዴት ይጠላቸዋል? ለዚህ ነው ሁሉም ጠበቃቸው ነው ያልሁሽ (አቶ ሞላ ተገኝ፤ ቃለመጠይቅ፣ 09/05/2005 ዓ.ም፣ ውጫሌ) ፡፡

በዚህ የተነሳ አዝማሪዎች ያላቸው ችሎታ ሌላው ሰው የሌለው በመሆኑና፣ ሌላው ሰው ለአዝማሪዎች ባለው ‹‹የተመረቁ ናቸው››፣ ‹‹የመልካም ገድ ምልክት ናቸው››

የሚል አመለካከት የተነሳ የትም ቦታ ተወድደው እንዲኖሩ ዕድል ፈጥሮላቸው ኖሯል፡፡ ሌላውም ሰው በነፃነት እንዲኖሩ የችሎታውን ሁሉ ሲያደርግ ኖሯል፡፡

> በአባቶቻችን አመለካከት አዝማሪ ቤትሽ ገብቶ ጓዳ እንኳን ቢሆን ወተት ካለ፣ ቅቤ ካለ ለአዝማሪ አይደበቅም፡፡ ከብት ካለበት ቦታ አዝማሪ የግድ ወተት ሳይጠጣ፣ እርጎ ሳይደፋ[38] አይሄድም ነውር ነው፡፡ እለቱን ባይቻል እንኳን ቀጠሮ ይሰጣቸዋል፡፡ እንዲያውም አዝማሪ ሲመሽበት የሚያድረው ካገኘው ቤት አይደደለም፡፡ በራሳቸው አመለካከት ጥሩ ነው ካሉት ቤት ነው፡፡ አዝማሪ የሚያድርበት ወደፊት ጥሩ ነገር አለው ተብሎ ይታሰባል (ሞላ ተገኘ፣ ቃለመጠይቅ፣ 09/05/2005 ዓ.ም፣ ውጫሌ)፡፡

በዚህ መልኩ አዝማሪዎች ከቦታ ቦታ በነፃነት ሲንቀሳቀሱ እንደኖሩና በማንም ሰው ቤት ሳይከለከሉ እየዘፈኑ በምላሹ ምግብና መጠጣቸውን እንዲሁም ልብሳቸውን ሲያገኙ እንደኖሩ መረጃው ይገልፃል፡፡ ይሁንና ሌላው ሰው ለአዝማሪ ያለው አመለካከት መልካም ብቻ አለመሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከሚሰጡት አገልግሎት የተነሳ እስከመሳደብ የሚደርስ መብት ቢሰጣቸውም ጋብቻን በመሳሰሉ የዝምድና መፍጠሪያ ግንኙነቶች ከአዝማሪ ጋር መቀላቀልን እንደውርደት ቆጥሮ ላለመቀላቀል ሲጠነቀቅ ኖሯል፡፡ ከአዝማሪ  የተጋባንም ሲንቅና ሲያገልል ኖሯል፡፡ ይህ ሃሳብም አዝማሪን እንደዝቅተኛ ‹‹ዘር›› ከመቁጠር የመነጨ ሲሆን አዝማሪ ለምኖ እንጅ ሰርቶ አይበላም፣ አዝማሪ ተሳዳቢ ነው የሚሉት አመለካከቶች አዝማሪውን አዝማሪ ባልሆነው ወገን የተናቀ እንዲሆን አድርገውት ኖረዋል፡፡ ይህንን ሁኔታ ሲገነዘቡት መኖራቸውን በግጥሞች ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

> ይህን በሰው አገር መኖር
> ሆዱ ይወደው ነበር
> ስጋና እንጀራ ያጠግባሉ
> አጥንት ያሳንሳሉ (ማስረሻ ፈንታው፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

---

[38]በእርጎ ሳይበላ ለማለት ነው፡፡

ግጥሙ በሰምና ወርቅ ቅኔ የቀረበ ነው፡፡ የዚህ ግጥም ከዋኝ አቶ ማስረሻ ፈንታው ግጥሙን ሲከውኑ ከአጠገባቸው ከአምስት በላይ አዝማሪዎች የእሳቸውን ክዋኔ በማድመጥ፣ የእነሱን ግጥም በመስጠትና ተራቸው ደርሶ ዘፈንን ለመከወን ግጥም በመስጠት፣ አብረው ነበሩ፡፡ በሁሉም አዝማሪዎች ፊት ሳቅና ደስታ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ግጥም በሚከወንበት ጊዜ ሁሉም አዝማሪዎች ሁለተኛውን ስንኝ በሃዘንና በአሳዛኝ ድምፅ በመቀበል አብረው ከወኑት፡፡ ግጥሙ በሰሙ ገጣሚው በሚኖርበት የሰው ሃገር እንጀራና ስጋ ጠግቦ እንደሚበላ አጥንት ግን በበቂ ሁኔታ እንደማያገኝ ይገልፃል፡፡ በወርቁ ደግሞ አብሮት የሚኖረው ማህበረሰብ አጥንትህ ትንሽ ነው፣ ከእኔ ታንሳለህ እንደሚለው ይገልፃል፡፡ ግጥሙ በሚከወንበት ጊዜ የነበረው የግጥሙ የአከዋወን ድምፀት ሌላው ሰው ለአዝማሪዎች ያለው ንቀት በስሜታቸው ላይ ከባድ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው የሚያሳይ ነበር፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ከቀረበው ትንታኔ አዝማሪ ያልሆነው ማህበረሰብ የአዝማሪዎች ሙያ በእጅጉ በመፈለግ፣ ነገር ግን ሰዎችን ደግሞ በመናቅ ተቃራኒ ስሜቶች መካከል የኖረ ነው፡፡ የአዝማሪዎችን ማህበራዊ ደረጃ በሌላው ማህበረሰብ መካከል ብቻ ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ካለ ግንኙነት አንፃር ሊዳሰስ ይችላል፡፡

## 6.1.1.7.5. ማህበራዊ ደረጃ በአዝማሪዎች መካከል

በአዝማሪውና አዝማሪ ባልሆነው ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በአዝማሪዎች መካከልም ማህበራዊ ደረጃዎች እንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ ደረጃም ከአሁን ይልቅ በተለይ ቀደም ባለው ጊዜ ትልቅ ግምት የነበረው ሲሆን የሚመነጨው ከመሰንቆ ጨዋታ ችሎታና ከመደብ ነው፡፡

ከመሰንቆ ችሎታ አንፃር ያለው ምድብ ጥሩ ችሎታ ላለው አዝማሪ በሌሎች አዝማሪዎች ዘንድ ‹‹ኀበዝ አዝማሪ›› የሚል ስም የሚያሰጠው ከመሆኑ ባሻገር የሰውዬውን የዘፈን መከወኛ ቦታም ይወስነዋል፡፡ በወሎ አንድ አዝማሪ ኀበዝ አዝማሪ የሚባለው ከተፈጥሯዊ ድምፁ መልካምነት ባሻገር ቅኝት[39] ለይቶ ሲያውቅና በቂ የግጥም ክምችት ወይም ፈጣን የመግጠም ችሎታ ሲኖረው ነው፡፡

[39]የቅኝት ምንነትና አይነቶች የዘፈን መልክ በሚለው ንዑስ ርዕስ ውስጥ ተገልጿል፡፡

ቅኝቶችንና ዜማዎች ለይቶ የሚጫወት አዝማሪ በታላላቅ ሰዎች ሰርግ ቤቶችና በተከበሩ ሰዎች ቤት ተጠርቶ ይጫወታል፡፡ እነዚህ ችሎታዎች የሌሉት ሰው ግን የሚጫወተው በመጠጥ ቤቶች ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ የተገኙት መረጃዎች ቀጣዩን ይላሉ ፡‹‹ሁሉም አሁን ደበላልቆ ይችላል፡፡ መዲና ሌይሌይ (ዘለሰኛ) ያልቻለ ሰው ሰርግ ቤት ሄዶ አይዘፍንም፡፡ ከዚያ ከመጠጥ ቤት[40] ሄዶ ይጫወታል እንጅ›› (ብርሃን ትኩ ፣ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

መረጃው አንድ አዝማሪ የመሰንቆ ጨዋታ ችሎታው የዘፈን መከወኛ ቦታውን እንደሚወስንለት ይገልፃል፡፡ በዚህ የተነሳ መዲናና ዘለሰኛን ዜማዎች በደንብ መጫወት የሚችል አዝማሪ በሰርግ ቤት ሲጫወት፣ እነዚህን ዜማዎች ያልቻለ አዝማሪ ደግሞ ቦታው መጠጥ ቤት ነው፡፡ ከመረጃው መረዳት የሚቻለው ሁለቱ አውዶች የተለያየ ደረጃ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ሰርግ ቤት ማህበራዊ ክብር ያለው ቦታ ነው፡፡ መጠጥ ቤት ደግሞ ሰካራሞች የሚገኙበትና ዝቅ ያለ ደረጃ ያለው አውድ ነው፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ቦታዎች የሚከውነው አዝማሪ ክብሩን ከአውዶቹ ይጋራል፡፡

የአንድ አዝማሪ የመሰንቆ ጨዋታ ችሎታ ደረጃ ከመጠጥ ቤት አንስቶ በቤተመንግስት እስከ መዝፈን የሚደርስ ሲሆን ለቤተመንግስት፣ ለምስለኔና ጭቃ ሹም አዝማሪ መሆን ከተራ አዝማሪነት አውጥቶ ክብር ያሰጣል፡፡ ስለዚህም አዝማሪው በወቅቱ አንድ ባላባት ያለውን ክብርና ጥቅም ሁሉ የሚያገኝ ሰው ነው ማለት ነው፡፡ በአመጋገቡ፣ በአለባበሱና በጠቅላላ አኗኗሩ ከተራው አዝማሪ የተለየ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ አዝማሪው የተለየ መሆኑን የሚገልፅ ሹመት ከዚያው ከባላባቱ ይሰጠዋል:: ይህ ሹመት ‹‹እከሌ ቀሚስ ለበሰ›› በሚል የሚገለፅ ነው፡፡ ለእንደዚህ አይነቱ ማዕረግ የሚሰጠው ቀሚስ የራሱ የሆነ መልክ አለው ይላሉ መረጃ ሰጪዎች ‹‹ቀሚስ ቢሉሽ እንደዚህ እንደታቦቱ ጌጥ ያለው፣ እንደ እጀጠባብ ያለ ነው፡፡ እጅና እጁ፣ እንዲሁም ታቹ በብልጭልጭ ነገር የተቀመቀመ ነው፡፡ እንደዚያ ያለ ይቀበላል፡፡ ይኸ የእከሌ አባ መልኩን ቀሚስ የለበሰ አዝማሪ ነው ይባላል፡፡ ያ የዛን ጊዜ ነበር›› (ብርሃን ትኩ፣ ቃለምልልስ፣ 12/05/2005ዓ.ም፣ ማርዬ:)፡

አዝማሪው ለክብሩ መገለጫ የሆነውን ቀሚስ ለብሶ በበዓላት ቀን ከጌታው ፊት በመቆም የሚዘፍን ሲሆን በሚያሳየው ብቃትና ለጌታው በሚፈጥረው ደስታ የተነሳ የቀሚስ

---

[40] መረጃ ሰጪው ይህንን ቃል አልተጠቀሙም እሳቸው ይህንን ቃል ለመግለፅ ከሸርሙጣ ቤት ነው ያሉ፡፡ ቃሉን እንዳለ መጠቀሙ ከስነምግባር ውጪ እንዳያደርግ ስለተፈራ ተቀይሯል፡፡ በግርጌ ማስታወሻ ማስቀመጥ የተፈለገበት ምክንያት ደግሞ ገለፃቸው የሁለቱን አውዶች ልዩነት የሚያሳይ ሲሆን ከዚያ በላይ የአዝማሪውን የችሎታ ደረጃ ለመግለፅ የሚጠቅም ነው ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡

ሽልማቱ እየጨመረ ይመጣል፡፡ በዚህም የተነሳ ‹‹እከሌ ይህንን ያህል ቀሚስ ለበሰ›› የሚለው አባባል ደረጃን የሚገልፅ ነው፡፡

አቶ አሰፋ ለገሰ የሰጡት ቀጣዩ መረጃ ይህንን የሚያሳይ ነው፡፡ ‹‹አባቴ ታዋቂ አዝማሪ ነበር፡፡ ቀሚሱን እንኳን እራሴ ነኝ ለብሼ የጨረስሁት፡፡ እንደ ታቦት ልብስ አለ አይደለም? ካባ ነበር፡፡ አምስት ቀሚስ ነበረው፡፡ ያንን ከባላባት ፊት ብቻ የሚለብሰው ነው፡፡ ደንበኛ ተጫዋች ስለሆነ በሽልማት የተሰጠው ነው፡፡›› (ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005 ዓ.ም.፣ ደሴ) ሌላ አቶ ተፈራ አያሌው የተባሉ መረጃ ሰጪም ባላባት አዝማሪ የሚባለው ምን እንደሆን ደረጃውም እንዴት እንደሚገለፅ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> ቀሚስ ነው ሚለብስ፡፡ ማዕረጉ ቀሚስ ነው፡፡ እክሌ የእከሌ አባ በሉ አዝማሪ ነው፡፡ ቀሚስ ለበሰ ነው የሚባለው፡፡ ያን ለብሶ መታየት ነው፡፡ ወደ መንግስትም ሲሄድ ቀሚስ ነው የሚለብሰው ስሙ ገነነ፣ መንግስት አወቀው፤ ቲገባም ደግሞ ከመንግስቱ ቤት ከልካይ የለውም፡፡ አሽከር ገረዱ ሁሉ ዝም ነው የሚለው አጋፋሪ የለውም፡፡ ወይዘሮይቱን ያጫውታል፡፡ እሱን ያጫውታል፡፡ ጥሩት ነው የሚባለው፤ ዘመቻ ቲሄድ አብሮ ይሄዳል፡፡ ዘመቻ ቲሄድ ነጋሪቱ ሲያገሳ ይባላል፡፡ በቅሎው ቀሚስ ይለብሳል፣ ፈረሱ ቀሚስ ይለብሳል፡፡ ጡሩንባ ነፊ አለ፣ ተጫዋች አለ፡፡ ይኸ ሁሉ ታዲያ እንዳሁኑ ታይሆን ነው (ቃለመጠይቅ፣11/05/2005 ዓ.ም፣ደሴ)

በዚህ መልኩ የቤተመንግስትና፣ የመጠጥ ቤት፣ ቀሚስ የለበሰና ያልለበሰ በሚል የወጣው ደረጃ በአዝማሪዎች መካከል ለሚደረገው ጋብቻ የራሱ የሆነ መልክ ሰጥቶታል፡፡ ይኸውም የአንድ አዝማሪ ቤተሰብ አዝማሪ ስለሆነ ብቻ ከሌላው የአዝማሪ ቤተሰብ ጋር በጋብቻ አይቀላቀልም፡፡ የእነማን ዘር ነው፣ አባታቸው የማን አዝማሪ ነበር የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ በዚህ ሁኔታ አቻ የሆኑ እንደሁ ብቻ ነው ጋብቻው የሚከናወነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ በቃለ ምልልስ የተገኘው መረጃ ቀጣዩን ይላል፡፡

ለምሳሌ ዝቅተኛ ዘር የሚባል አለ፡፡ ይኸ እኮ ባህሉ ነው፤ አይደለም እንዴ? ባላባት የሚባል አለ፡፡ በስመ አዝማሪ ሁሉም ተፈላልጎ አይጋባም፡፡ አሁን መንገሻ አልክ (መንገድ መሪዬን እየተመለከተ)፤ መንገሻ የእኛ ዘር አይደለም፡፡ ቀድሞ ባሪያ ነው እየተባለ፤ ዝም ብሎ በአባይ ገነን [41]የተማረ ነው እንጅ፡፡ በደርግ በአይወማ ኪነት ነው የተማረ፡፡ መለያው ዘር ነው፡፡ በእናንተስ አለ አይደለም፡፡ እከሌ ባላባት ነው፡፡ እከሌ የጭሰኛ ዘር ነው የሚባል፡፡ እንደዚያ ነው (ተስፋዬ በላይ፣ ማርዬ፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም) ፡፡

መረጃው በአዝማሪዎች መካከል የደረጃ ልዩነት ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ የደረጃ ልዩነት ምንም እንኳን ከመሰንቆ ችሎታ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ቢሆንም በቡድኑ መካከል የተከበረና ያልተከበረ የሚያስብል መደብ ፈጥሯል፡፡ የተከበረ የሚባለው ቡድን ዘፈኑን በተሻለ ቦታ ይከውናል፣ ኑሮውን በተደላደለ ሁኔታ ይመራል፡፡ ጥሩ የኢኮኖሚ አቅም አለው፡፡ ሌላው ቡድን ደግሞ ከመጀመሪያው ቡድን በተቃራኒ ሁኔታ የሚኖር ነው፡፡ ይህ አዝማሪዎች ከሌላው ሰው ጋር ያላቸው ደረጃ፣ ‹‹በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ቡድኖች፣ ከምጣኔ ሃብታቸው ምንጪ የተነሳ ይለያያሉ›› ከሚለው የማርክሳውያን አመለካከት ጋር የሚስማማ ሲሆን የአዝማሪዎች ቡድን በመካከሉ የፈጠረው ቡድን ደግሞ ቡድኖች የማህበረሰቡን ምጣኔ ሃብት በመካፈል ድርሻቸው የተለያዩ ናቸው›› ከሚለው ሌላኛው ትውር ጋር የሚስማማ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ የወሎ አዝማሪዎችን ባህላዊ መለያ ገፅታዎች ለመረዳት አሰፋፈራቸው፣ የእርስ በእርስ ዝምድናቸው፣ የሰርግ ስርዓታቸው፣ የቡድኑ የፆታ ተራክቦ፣ ቡድኑ የሚከተለው ሃይማኖት፣ የቡድኑ ቋንቋ፣ ማህበራዊ ደረጃ የሚሉ ርዕሶች ታይተዋል፡፡ በእነዚህ ርዕሶች አማካኝነትም የወሎ አዝማሪዎች ወሎ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በበርካታ ቦታዎች የራሳቸውን መንደር መስርተው እንደኖሩ፣ ከጋብቻ አንፃር ሲታዩ ቀደም ባለው ጊዜ እርስ በእርስ ብቻ ይጋቡ እንደነበሩ፣ የራሳቸው የሰርግ ስርዓት እንዳላቸው፣ በመካከል ያለው የፆታ ግንኙነት በመከባበርና በመተባበር ላይ የተመሰረተ እንደሆነ፤ በቀለባስና በአምባሰል የሚኖሩ አዝማሪዎች የክርስትና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ በደረቅ ወይራ፣ በከድጆና በለጋምቦ የሚኖሩት ደግሞ የእስልምና እምነት

[41] ሙያውን ከቤተሰብ የወረሰው ሳይሆን ራሱ በልምምድ የገባበትነው ማለት እንደሆነ መረጃ ሰጪው ይገልፃሉ፡፡

ተከታዮች መሆናቸውን፣ እንዛትኛ የሚባል የቡድን መግባቢያ ቋንቋ እንዳላቸው፣ ዛሬ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ከጥንቱ የተሻለ ቢሆንም እኩል አለመሆኑን በአዝማሪዎች መካከል ጎበዝ አዝማሪና ጎበዝ ያልሆነ አዝማሪ እንዲሁም ባላባትና ጭሰኛ የሚባሉ ደረጃዎች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት ንዑሳን ርዕሶች የወሎ አዝማሪዎችን ከሌላው ማህበረሰብ የሚለዩ የአዝማሪዎች ማንነት መገለጫ መልኮች ናቸው፡፡ ይሁንና አዝማሪዎችን ከምንም በላይ ከሌላው ቡድን የለያቸው ዘፋኝነታቸው ነውና ይህ መልካቸው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6.1.2. በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ልምዶች

ዘፈን ለወሎ አዝማሪዎች ፎክሎር ነው፡፡ ፎክሎር ደግሞ (Ben-Amos, 1971) እንደሚሉት የአንድ ቡድን ዕውቀት፣ የተግባቦት ስልትና የአስተሳሰብ መንገድ ነው፡፡ ወሎዬ አዝማሪዎች ስለሚከውኑት ዘፈን የጋራ ዕውቀት አላቸው፡፡ በፎክሎሩ ይግባቡበታል፤ አለምን የሚገነዘቡበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ለዘመናት በትውልድ መካከል ሲተላለፍ ኖሮ በቡድኑ ውስጥ ተከታታይ ባህርያትን ፈጥሯል፡፡ ተከታታይ ባህርያቱ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

### 6.1.2.1. የዘፈን ግንዛቤ

የወሎ አዝማሪዎች ዘፈንን በሁሉም የህይወት ክስተት ውስጥ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ አድርገው ይገነዘቡታል፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ከመንፈሳዊው አንስቶ እስከ አለማዊው አውድ ድረስ በአዝማሪ ዘፈን ሃሳብ ሲገለፅ፣ በዕድሜ ከገፉ ሰዎች ጀምሮ እስከ ወጣቶች ድረስ በአዝማሪ ዘፈን ሃሳባቸውን ሲገልፁ መኖራቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ በአፈ-ታሪካቸው መነሻችን ሲሉ ከሚጠቅሱት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ አዝማሪ ለመኖሩ ምክንያት ዘፈን ለሰው ልጅ አስፈላጊ ጉዳይ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ እንደ እምነታቸው ዘፈንንና የመሰንቆን ድምፅ አይደለም የሰው ልጅ እንስሳት እንኳን ይወዱታል፡፡ ቀጥሎ ያለው ጥቅስ ይህንን እምነት ያሳያል፡፡

> መሰንቆ ማይገባበት ምን ነገር አለ? በሰላም ጊዜ መደሰቻ ነው፡፡ በጦርነት ጊዜ ማዋጊያነው፣ ሰርግ ያለአዝማሪ ዘፈን አይደምቅም፤ ንጉሶች ሲቀመጡ

የሚያጫውታቸው፣ በግብር የሚዘፍን አዝማሪ ነበራቸው፡፡ ድሮ እኮ በደስታ ይቅርና ታዋቂ ሰው ሲሞት አዝማሪ በለቅሶው ይኖራል፡፡ ደሞ ሰው ይቅርና ወደ መንደር ሲሄድ ውሻ አላስገባም እንዳይል መሰንቆ ይመታል፡፡ አባቶቻችን ወንዝ ሲሻገሩ መጀመሪያ መሰንቆ መትተው ነው፡፡ ዘፈን የማይወድ ማን አለ? ከሰው እስከ እንስሳው፣ ፍጥረቱ ሁላ ዘፈንና ምስጋና ይወዳል፡፡ (መላክ ታረቀ፣ ቃለመጠይቅ፣ 28/07/2005 ዓ.ም፣ ቀለባስ) ፡፡

ይህንን ሃሳብ በተለያዩ የጥናቱ ቦታዎች ያሉ አዝማሪዎች የሚጋሩት ሲሆን መረጃው አዝማሪዎች ዘፈን ለፍጥረት ሁሉ አስፈላጊ ነው ብለው የሚገነዘቡ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለዚህ ግንዛቤያቸው ምክንያቱ በተለያዩ አውዶችና ሁኔታዎች የሚከውኑት መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ አዝማሪዎች ዘፈን ለሰው ልጅ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን የሚረዱበት መንገድ እነሱ ዘፋኝ በመሆናቸው የተነሳ ሲያገኙ የኖሩትን ጥቅም ከመግለፅ አንፃር ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ከሹማምንት በስተቀር ለሌላ ሰው ክልክል በሆነው ቤተመንግስት ገብተው ግብር እስከመብላት፣ በሰርግ ውስጥ የተለየ ምግብ ይዘጋጅላቸው እስከመባል፣ ከተከበሩ ሰዎች ጋር እስከመዋል ያደረሳቸውን ክብር ያስገኘላቸው ዘፈን ለሰው ልጅ አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

የሃገር ባህል ጨዋታ ጥሩ ነው፤ ሳወቀበት፡፡ የእኛ ጨዋታ ጥሩ ነው፡፡ በጣም ጥቅም አለው፡፡ ከደህና ሰው ጋር እውላለሁ፡፡ ከሴት ወይዘሮ ጋር እውላለሁ፤ ጥሩ እበላለሁ፤ ምን ይበሉ ይሆን ተብለን፣ ቁርጥ ተቆርጦልን፣ ቅቤው ተፈትፍቶ ነው፤ ምሳቸሁን ብሉ፣ ራታችሁን ብሉ ተብሎ ነው፡፡ እንዳልባሌ አያደርጉንም፣ ምክንያቱም ዳሱ ያለእኛ አይሞቅም፣ ወታደሩ ያለእኛ አይዘምትም፣ የንጉስ ግብር እንኳን በዛ ሁሉ ድግስ መሃል አዝማሪ ይፈልጋል፡፡ በደንብ ሆኜ ኖሪያለሁ፤ እግዚአብሔር ይመስገን (አለምፀሃይ የማና፣ ቃለመጠይቅ፣17/04/2005 ዓ.ም፣ ውጫሌ)፡፡

ይህ መረጃ ከላይ የተባለውን ሃሳብ የሚደግፍ ነው፡፡ መረጃው እንደሚለው አዝማሪዎች አዝማሪ በመሆናቸው የተነሳ የተከበረ ማህበራዊ ደረጃ ካላቸው ሰዎች ጋር ይውላሉ፤ ምግባቸው ለእነሱ ተብሎ በስርዓት የሚዘጋጅ ነው፡፡ ከፍ ያለ ክብር አላቸው፡፡ ይህም

ሲሆን የቻለው ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር ነው፡፡ አገልግሎታቸው ደግሞ ዘፈን ሲሆን ዘፈኑ የተከበሩ ከሚባሉ ሰዎች አንስቶ እስከ ‹‹ተራው›› የማህበረሰብ ክፍል ድረስ አስፈላጊ በመሆኑ ተቀባይነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ዘፈንን በዚህ መልኩ የሚረዱት በመሆኑ በተለይ ቀደም ባለው ጊዜ ስራዬ ብለው ሲለማመዱትና ለትውልድ ሲያስተላልፉት ኖረዋል፡፡ ለመዳው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

### 6.1.2.2. የዘፈን ለመዳና ተስተላልፎ

ዘፈን ለወሎ አዝማሪዎች የማንነት መገለጫቸውና የኑሯቸው መሰረት ሆኖ ኖሯል፡፡ ማንኛውም ሰው ከአምላክ በተሰጠው ‹‹ፈን››/ዕድል ይኖራል ብለው የሚያምኑ በመሆኑ ለእነሱም አዝማሪነት ከአምላክ የተሰጣቸው ስራ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ደረቅ ወይራ ላይ የተገኘው ቀጣዩ መረጃ ይህንኑ ሃሳብ የሚያሳይ ነው፡-

> ሁሉም ከጠዋት ነው፡፡ ለአንቺም እንጀራሽ ይኸ ነው፣ ለአንተም እርስትህ ይኸ ነው፣ለአንተም ጠበንጃ ነው እርስትህ እያለ ሲታደል፤ አዝማሪ ሁሉም ታለቀ ወዲያ መጣች አሉ፡፡ እኼሳ? ልመና! ሂጅና ለምነሽ ብይ አላት አሉ፡፡ ሄደች፤ ወለደች፣ ልጅዋ መሰንቆ ተስተማረ አሉ፤ ለሁሉም አንቺ ሽክላ ስሪ አንቺ ይህንን ስሪ እየተባለ እርዚቅ[42] ሲታደል እስዋ ወጥታ ሄዳ ሁሉም ሲያልቅ መጣች ልመና [43]ተሰጣት፡፡ ለገበሬውም፤ ለሁሉም ተጠዋት ነው እድሉ (ወ/ሮ አሰጉ፣ ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

ጥቅሱ አዝማሪዎች እንዴት ዘፋኝ ሊሆኑ እንደቻሉ የሚገልፅ የየት መጣ ትረካ ነው፡፡ የዘርፉ ሙሁራን እንደሚገልፁት የየትመጣ ትረካ የተራኪው ቡድን እምነት የሚገለፅበት የፎክሎር ዘርፍ ነው፡፡ ተራኪው ቡድንም በትረካው ሊያስተላልፈው የሚፈልገውን እሴት በትረካው ውስጥ የሚያስቀምጥባቸው ዘይቤዎች (Metaphor) አሉ (Leeming, 2002,15)፡፡ እንደዚህ ሁሉ ይህ የአዝማሪነትን የት መጣ የሚገልፀው

[42]እጣ ፈንታ፣ ሃብት

[43]ልመና አዝማሪዎች በቀጥታ ገንዘብ ከማግኘት ጋር አስበው ሲዘፍኑ ዘፈንን የሚጠሩበት ስያሜ ነው (ከተጠኝ ቡድን ውይይቶች የተገኘ)፡፡


ትረካ አዝማሪነትን ጨምሮ ሁሉም የመተዳደሪያ ሙያዎች ከፈጣሪ ዘንድ ለሰዎች እንደተሰጡ ይገልፃል፡፡ ከትረካው አዝማሪዎች ሙያቸውን ከሌሎች ሙያዎች ጋር እኩል የሚያዩት እንደሆነ ተገልጧል፡፡ ለዚህም ማስረጃው ትረካው ሁሉም ሙያዎች ምንጫቸው አንድ ነው የሚል መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በትረካው ‹‹ . . . *ሄደች፤ ወለደች፣ ልጅዋ መሰንቆ ተስተማረ››* በሚል ስለ ሙያው ከእናት ወደ ልጅ ተስተላልፎ ተጠቁሟል፡፡ ይህ ትረካ ለዘመናት የኖረውን የአዝማሪዎች የሙያ ተስተላልፎ ይገልፃል፡፡ ምክንያቱም መረጃዎች የሚያሳዩት አዝማሪነት ለዘመናት ከአባት ወደ ልጅ ሲተላለፍ የኖረ ሙያ መሆኑን ነው፡፡

ዘፈን ለወሎ አዝማሪዎች የፈጣሪ ስጦታና የአባት ሙያ ከመሆኑም ሌላ መተዳደሪያ ነው፡፡ በተለይም እንደዛሬው ሌሎች አማራጭ መተዳደሪያዎች ከመገኘታቸው በፊት አዝማሪው ዘፍኖ በሚያገኘው ገቢ ወላጆቹን ይረዳል፤ የራሱን ቤተሰብ ይመሰርታል፡፡ ይህም በመሆኑ በተቻለ መጠን ማንኛውም አዝማሪ ቤተሰብ ልጁ አዝማሪነትን እንዲማርለትና ገቢ እንዲያስገባለት ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ሲል ልጆችን ወደ ሙያው የሚገፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ልምምዶችን ያበረታታል፡፡ ይሁን እንጅ ማንም ልጅ አዝማሪ ለመሆን የሚወስደው መደበኛ ትምህርት የለም፡፡ ልምምዱ ሌሎች የሚሉትን መስማትና ደግሞ ማለትና ማድረግ ነው፡፡ ወጣቶች ትልቆች የሚያደርጉትን በመኮረጅ ራሳቸውን ዘፈን ያስተምራሉ፡፡

ማንኛውም አዝማሪ በአዝማሪነት ሙያ ውስጥ እንዲለምድ የሚጠበቅበት መሰንቆ ጨዋታና ግጥም መግጠም ነው፡፡ መሰንቆ ወንዶች የሚጫወቱት የአዝማሪዎች የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡ በምልከታ እንደታየውና Timkehet (2009) እንደሚገልፁት መሰንቆ ከእንጨት፣ ከቆዳና ከፈረስ ጭራ የሚሰራ የክር የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ የሙዚቃ መሳሪያ ምሰሶ፣ ገበታ(የድምፅ ሳጥን)፣ በርኩማ፣ ጭራ(ልሳን)፣ መግረፊያ (መምቻ) የሚባሉ ክፍሎች አሉት፡፡ ምሰሶ ሁሉንም ክፍሎች ይሸከማል፡፡ ምሰሶ ቀጥ ያለ እንጨት ሲሆን አንደኛው ጫፉ ይቦረቦርና አግድም አንድ እንጨት ይገባበታል፡፡ አግድም የገባው እንጨት መቃኛ ይባላል፡፡ የምሰሶው ሌላኛው ጫፍ ትንሽ ትርፍ እንጨት ተትቶለት የድምፅ ሳጥኑ ወይንም ገበታው ይቀመጥበታል፡፡ ገበታ የሬክታንግል ቅርፅ አለው፡፡ አራት ጣውላዎች እርስ በእርስ ተገጣጥመው የ‹‹ዲያመንድ›› ቅርፅ ይይዙና ከታች በጣውላ ከላይ ደግሞ በቆዳ ተሸፍኖ ይሰራል፡፡ ገበታ መሰንቆው በሚመታበት ጊዜ የሚወጣው ድምፅ እንዲያስተጋባ የሚያገለግል ክፍል በመሆኑ ለዚሁ እንዲረዳ ሲባል በጣውላው በኩል ትንሽ ክብ ቀዳዳ

ይደረግለታል፡፡ ከመቃኛው ጫፍ የፈረስ ጭራ ይታሰርበታል፡፡ የጭራው ጫፍ ወደ ታች ይወርድና በቆዳ የተሸፈነውን የድምፅ ሳጥን አልፎ በሚገኘውና የምሰሶው አካል በሆነው እንጨት ጫፍ ይታሰራል፡፡ ከጫፍ እስከጫፍ የታሰረው ጭራ ከእንጨት ጋር ከተነካካ ለዘፈን የሚሆን ተመጣጣኝ ድምፅ ስለማይሰጥ እንዳይነካካ ወደላይ ከፍ አድርጋ የምትይዘው በርኩማ የምትባል ከድምፅ ሳጥኑ ላይ ቀዳዳው በተደረገበት ተቃራኒ የምትቀመጥ ትንሽ እንጨት አለች፡፡

መሰንቆ ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም መምቻ፣ መግረፊያ ወይም ደጋን የሚባል ክፍል አለው፡፡ ይህ ክፍል ከዋናው አካል የተለየ ሆኖ የደጋን ቅርፅ ባለው እንጨት የሚዘጋጅ ነው፡፡ ከጫፍ እስከጫፍ የፈረስ ጭራ ተወጥሮ ይታሰርበታል፡፡ ከዚያም ሁለቱን ጭራዎች በማጋጨት ሙዚቃን መጫወት ይቻላል፡፡




ስዕል 5. የመሰንቆ ክፍሎች

መረጃ ሰጪዎች መሰንቆ የራሱ የሆነ መጠን እንዳለው ይናገራሉ፡፡ ለሙዚቃ ቅኝቱ ማማር የመሰንቆው መጠን ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህንን በተመለከተ መረጃ የሰጠው አበባው ሙሉጌታ ‹‹ጥሩ መሰንቆ ማለት፤ እንደዚህ ልሳኑን ስትለኪው (ጭራውን እየለካ) አንድ ክንድ የሚሆን ነው፣ እንደዚህ ካልሆነ ቅኝቱን አይመልስልሽም፡፡ እንደዚያ ሲሆን ግን አራቱንም[44] ቅኝቶች ለመጫወት ያስችላል›› (አበባው ሙሉጌታ፣ ቃለመጠይቅ፣ 10/05/2005፣ ውጫሌ) ብሏል፡፡

መረጃው መሰንቆ የራሱ የሆነ ልኬት ያለው መሆኑን ይናገራል፡፡ ይህ ልኬቱም በአዋቂ ሰው አንድ ክንድ ያህል ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ልኬት በታችም ሆነ በላይ የሆነ መሰንቆ ተጫዋቹ እንደልቡ ሊያዝዘው የማይችል ይሆንና የዘፈኑን ቃና እሱ እንደሚፈልገው አይመጣለትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በየራሳቸው መልክ መቅረብ የሚገባቸውን ቅኝቶች ለይቶ ለመጫወት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ተጫዋቹ መግረፊያውን እንደፈለገው የማያዝዘው በመሆኑ የየቅኝቶችን መነሻና መድረሻ ድምፅ ለይቶ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡ ለዚህ ሲባል የመሰንቆው ልኬት ተጠብቆ ይሰራል፡፡


አዝማሪዎች ለሙዚቃ ጨዋታ የሚገለገሉበትን መሰንቆ ራሳቸው ይሰሩታል፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ መረጃሰጪ ‹‹መሰንቆውን የምንሰራው እራሳችን ነን፡፡ ለምሳሌ እኔ ራሴ ነኝ የምሰራው፡፡ የትም አይገዛ፣ የትም አይመጣ፡፡ ሰው እዚሁ ራሱ እየሰራ ነው የሚጫወት፡፡ በእኛው ነው የሚሰራ›› (መላኩ ካሳው፣ ቃለመጠይቅ 12/05/2005 ዓ.ም.፣ ማርዬ) ብለዋል፡፡ እንደዚህ ሁሉ ሌሎች መረጃ ሰጪ አዝማሪዎች መሰንቋቸውን ራሳቸው የሚሰሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ለመሰንቆ መስሪያ የሚያገለግሉት ቁሶችም በዚያው በአካባቢው የሚገኙ ናቸው፡፡ የእቃዎችን ዝርዝር አስመልክቶ የተገኘው መረጃ መሰንቆ፤ ከእንጨት፣ ከቆዳና፣ ከጭራ ይሰራል ይላል፡፡

> ዕቃው እንደ ጣውላ ያለ አለ፡፡ እቃው እንደ ማግኘት ማጣትሽ ይወሰናል፡፡ ከዋንዛ ይሰራል፤ ከቁልቋል ይሰራል፤ ከሾላ ይሰራል፡፡ ከዚያ ወዲያ በፍዬል ቆዳ ይሰራል፡፡ ቆዳው ግዴታ የፍዬል መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ስስ ሁና እንድትጮህ፤ በእርግጥ ከበሮ የከብት ቆዳ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከበድ እንዲል ይህኛው ግን ሲው ብላ እንድትጮህ ስለ ስስነቷ የፍዬል ቆዳ ትደረጋለች፡፡

[44]የአራቱ ቅኝቶች ምንነትና ባህርይ ወደኂላ የዘፈን መልክ በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ተገልጧል፡፡

እንጨቱ፣ ዋንዛ ገበታ ጥሩ ነው። መምቻዋ፣ ከወይራ፤ ከታሉም ትሰራለች። ታሎ የሚባል እንጨት አለ። ጭራው የፈረስ ጭራ ነው (መላኩ ካሳው፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/04/2005፣ ማርዬ)”።

መሰንቆ ለአዝማሪው ዋና ንብረቱ እንደመሆኑ በከፍተኛ እንክብካቤ የሚያዝ ዕቃ ነው። ይህ በመሆኑ አንድ አዝማሪ በየትኛውም ቦታ በሚጓዝበት ወቅት መሰንቆው ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንዳደርስ ይጠነቀቃል። በቤት ውስጥም ቢሆን ከመሬት በመቀመጡ የተነሳ ጭራ እንዳይበጠስ ወይንም እንጨቱ እንዳይሰበር ሲባል የቤት ግድግዳ ላይ ይሰቀላል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ጭራው ቢበጠስ ወይንም እንጨቱ ቢሰበር ግን ስራ ተስተጓጎለ ማለት ነው። ከዚህ በተረፈ ደግሞ ጭራውን ምንም አይነት ርጥበት ወይንም ቅባት ነገር ቢነካው የሙዚቃ ድምፅ የማያወጣ በመሆኑና ቢያወጣ እንኳን የተፈለገውን ቅኝት የማያጫውት በመሆኑ እነዚህ ሁኔታዎች እንዳይደርሱ ሲባል ለመሰንቆው አቀማመጥ ጥንቃቄ ይደረጋል። ከዚህ ጥንቃቄ አልፎ ቢቆሽሽ ግን በውሃና በሳሙና በደንብ ይታጠባል።



ስዕል 6. የመሰንቆ አቀማመጥ፣ኢላዳ

ቆሻሻን ከማስለቀቅ ዓላማ ባሻገር መሰንቆ በቋሚነት የሚታጠብበት ወቅት አለ፡፡ ይህም መስከረም አንድ ቀን የሚከበረው የዘመን መለወጫ በዓል ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ይህ ጊዜ አሮጌው ዓመት አልቆ አዲሱ ዘመን የሚተካበት እንደመሆኑ አዲሱ ዘመን መልካም የስራ ጊዜ እንዲሆን በመመኘት በንፅህና ለመቀበል ሲባል መሰንቆ ይታጠባል፡፡ መሰንቆው ከታጠበ በኋላ በፀሃይ ይደርቃል፡፡ ከዚያም ጭራው ለስላሳ ድምፅ እንዲያወጣ በፅድ ሙጫ ይለሰልሳል (ትርንጎ መለሰ፣ መላክ ታረቀኝ፣ አገኘሁ ደሴ፣ ሲሳይ አጥናፌ፣ በለጡ መላክ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 14/04/2005 ዓ.ም. ደረቅ ወይራ)፡፡

የፅድ ሙጫ አዝማሪው መሰንቆ እስከያዘ ድረስ ምንጊዜም በኪሱ ይዞት የሚዞር የመሰንቆው ጭራ ማለስለሻ ነው፡፡ ከፅድ ዛፍ ተለቀቅሞ ይዘጋጃል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደገለፁትና በምልከታ እንደተረጋገጠው በመጀመሪያ ከፅድ ዛፍ ላይ ሙጫ ይለቀማል፡፡ ንፁህ ብረት ምጣድ ውሃ ተደርጎበት እሳት ላይ ይጣዳል፡፡ የተጣደው ውሃ ሲፈላ ሙጫው ይደረጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ሙጫው አንድ ላይ እስኪያያዝ ድረስ በንፁህ እንጨት እየተማሰለ ይቆያል፡፡ ብረት ምጣዱ ላይ ያለው ሙጫ ተያይዞ ሲያበቃ ብረት ምጣዱ ከእሳቱ ላይ ይወርዳል፡፡ ሙጫው ሲበርድ በትንንሹ የኳስ ቅርፅ እንዲኖራቸው ተደርገው እንክብሎች ይዘጋጁና በፀሃይ ይደርቃሉ፡፡ ከዚያ መሰንቆው ለዘፈን በተፈለገ ጊዜ በተዘጋጀው ሙጫ ጭራው እየለሰለሰ ጨዋታው ይጀመራል፡፡

አንድ ልጅ መሰንቆ ጨዋታ ይችላል የሚባለው ቅኝት ለይቶ ሲጫወት ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ቅኝቶችን ለማወቅ የሚቻለው ሌሎች ሲጫወቷቸው በደንብ በመስማትና በልብ በመያዝ ከዚያም ያንን የመሰለ ቅኝት እስኪመጣ ድረስ በክሩ ላይ የጣቶችን ቦታ እየቀያየሩ በመፈለግ ነው፡፡ ዜማው መምጣት አለመምጣቱ በጆሮ በማድመጥ ብቻ የሚታወቅ ሲሆን ሌላ ተጫዋች ሲጫወት በማየት የእሱን የጣት አቀማመጥ በቀጥታ በመኮረጅ ለመጫወት መሞከር ብዙም አዋጪ ዘዴ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የየሰው የጣት መጠን የሚለያይ በመሆኑ በትክክል መኮረጅና ያንን መሆን አይቻልም፡፡ ይሁንና በደንብ መጫወት የሚችልን ሰው አጠቃላይ የጣት አቀማመጥ በማየት በዚያው አካባቢ መፈለግና ቅኝቶችን ለይቶ መምታት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በዚህና በሌላ መንገድ ማንም ወንድ ልጅ መሰንቆ መጫወት እንዲችል ወላጆቹም ሆኑ የአካባቢው ሰው ያበረታታዋል፡፡ አባቶች እነሱ ከሚጫወቱበት መጠኑ አንድ ክንድ ያነሰ መሰንቆ ሰርተው ለልጆቻቸው ይሰጣሉ፡፡ አለዚያ ደግሞ የራሳቸውን መሰንቆ ልጁ እንዲለማመድበት ይሰጣሉ፡፡ የልጁን የሙዚቃ ልምምድ ችሎታ

መሻሻልና አለመሻሻል እየተመለከቱ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መሰንቆ ጨዋታ እንዴት እንደለመደ መረጃ የሰጠ አንድ አዝማሪ ሲናገር ‹‹እኔ መሰንቆ ጨዋታን የለመድሁ ከሰፈር የሚጫወቱትን ጓደኞቼንና አባቴን እያየሁ ነው፡፡ ቅኝት ለይቼ እንድመታ ያስተማረኝ አባቴ ነው፡፡ እጣቴን እንዴት ሳደርግ ትዝታ፣ እንዴት ሳደርግ ደግሞ አንቺ ሆዬ ቅኝት እንደሚመጣልኝ አሳይቶኛል›› ብሏል (ፍቅሩ ታደሰ፣ ቃለምልልስ፣ 27/07/2005 ዓ.ም፣ ክትክታ ለበስ)፡፡

ሌሎች መረጃ ሰጪዎችም መሰንቆን የተማሩ በራሳቸው ጥረት እንደሆነና አጀማመራቸውና ዜማ ለይቶ የመጫወት ችሎታቸውን ለማዳበር ከአባቶቻቸው እንዲሁም ቀደም ብለው ችሎታውን ካዳበሩ ጓደኞቻቸው በመኮረጅ እንደተማሩ ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥሩ የመሰንቆ ተጫዋች ለመሆን ዋናው ጉዳይ ተደጋጋሚ ልምምድና በመሰንቆ ጨዋታ ውስጥ ሃሳብን ‹‹ወደሌላ ሳይበትኑ›› መሰንቆው የሚያወጣውን ድምፅ ልብ ብሎ በማዳመጥ ድምፁን (ዜማውን) ወደሚፈለገውና ተለማማጁ ሊጫወተው ወደ መረጠው ዜማ ለማምጣት የሚደረግ ጥረት እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡

አዝማሪዎች መሰንቆ ጨዋታን ለማወቅ የሚያደርጉት ትግል በአንዳንድ ልማዳዊ ድርጊቶችም የታጀበ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ ‹‹ከወፍጮ ላይ ሆኖ ከመቱ መሰንቆ ተሎ ይገባል›› የሚለው አባባል ብዙ የአዝማሪ ልጆችን ወፍጮ ላይ ተቀምጠው እንዲያድሩ ያደርጋቸው እንደነበር ደምሴ አበበ የተባሉ መረጃ ሰጪ ገልፀዋል፡፡ መረጃ ሰጪው እንዳሉት ለልምምድ አመቺው ጊዜ ማታ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ነገር ጭር ስለሚል ሃሳብ ወደሌላ ሳይበተን የመሰንቆውን ድምፅ ብቻ እየተከተሉ ለማስተካከል ይመቻል፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ተሎ የመልመድ ጉጉቱ ስላለ ‹‹እንዲህ ብታደርግ ተሎ ትለምዳለህ›› የሚባለውን ሁሉ በማድረግ የማያቋርጥ ልምምድ ይደረጋል፡፡ ይሁንና ከሁሉም በላይ ተደጋጋሚ ልምምድ የችሎታው ባለቤት እንደሚያደርግ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ገልፀዋል፡፡

> በአንድ ጊዜ አይለመድም፡፡ እለት እለት በልምምድ ነው፡፡ ድሮ ‹እወፍጮ ላይ ሆነው ቲመቱ መሰንቆ ተሎ ይገባል› ይባል ስለነበር እኛም ልጆች ሆነን ወፍጮ ላይ ተቀምጠን እንመታ ነበር፡፡ ግን ያ ተረት ነው፡፡ ልምምድ ነው የሚያስችለን፡፡ እኛ ልጆች ሆነን ያም ያም ያዝማሪ ቤት ነው፡፡ ሁላችንም መሰንቆ ይዘን ጢው ጢው ነው፡፡ ድምጡን በመሰንቆው እያወጣን በአንድ እጣት ነካ፣ ነካ እያደረግን ቃል እንዲሆን እናደርገዋለን፡፡

እንዲያ እንዲያ እያለ እንለምደዋለን (ደምሴ አበበ፣ ቃለመጠይቅ፣ 17/04/2005 ዓ.ም፣ ጢሳ አባ ሊማ)

መረጃው እንደሚለው መሰንቆን ተሎ ያስችላሉ ተብሎ የሚነገሩ አባባሎች ቢኖሩም ዋናው ነገር ልምምድ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ አዝማሪዎች መሰንቆ መጫወት እስኪችሉ ድረስ ያለመሰልቸት ይለማመዳሉ፡፡

መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት በተለይ ቀደም ባለው ጊዜ ማንኛውም የአዝማሪ ቤተሰብ መተዳደሪያው የመሰንቆ ጨዋታ ስለሆነ የቤተሰቡ አባል የሆነ ልጅ ሁሉ የመሰንቆ ጨዋታ ችሎታ እንዲኖረው ይፈለጋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ውጪ ለመሆን የሚፈልግ ልጅ በጎረቤቶቹና ዘመድ አዝማዶቹ ዘንድ በቃ ‹‹ተበላሸ›› የሚል ስጋት ይፈጥራል፡፡ (ፈንታው ለገሰ፤ ቃለመጠይቅ፣ 25/05/2005 ዓ.ም.፣ ከድጃ)

አንድ የአዝማሪ ልጅ ከመሰንቆ ጨዋታ ሌላ እንዲኖረው የሚጠበቅበት ግጥምና የአገጣጠም ዕውቀት ነው፡፡ ግጥም ለአዝማሪ ከመሰንቆ ችሎታ በላይ እንዲኖረው የሚፈለግ ችሎታ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንጊዜም ቢሆን አዝማሪዎች ዘፈናቸውን ለሌላው ሰው የሚያቀርቡት በመሆኑ ዘፈኑ የሚቀርብለት ሰው ለአዝማሪው ጨዋታ ጆሮ ሊሰጥ የሚችለው የግጥሙን ይዘት መሰረት አድርጎ ነው፡፡

ዘፈን ለአዝማሪው የገቢ ምንጩ መሰረት እንደመሆኑ ለአውዱ የሚስማሙ፣ የታዳሚውን ስሜት የሚነኩ ግጥሞችን ማወቅ አለበት፡፡ ያ ሲሆን አላማው ግቡን ይመታል፤ ከታዳሚው የሚፈልገውን ጥቅምም ያገኛል፡፡ ከዚህ ለአውድ የተስማማ ግጥም የመግጠም ችሎታ የገንዘብ ጥቅም ብቻ ሳይሆን በታዳሚውና በሌሎች አዝማሪዎች ዘንድ ጥሩ አዝማሪ የሚያስብል ስምም ያሰጣል፡፡

ብርሃን ትኩ፣ ማስረሻ ፈንታውና ሌሎችም እንደገለፁት ለአውድ ተስማሚ የሆኑ ግጥሞች በመፍጠር ወይም በማስታወስ የሚገጠሙ ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ ለአውዱ የሚመችን ግጥም ፈጥሮ ማለቱ አዝማሪውን አስታውሶ ከማለቱ የበለጠ የሚያስወድሰው ሲሆን ለአውዱ የሚሆንን ግጥም አስታውሶ ማለቱም ቢሆን የጎበዝ አዝማሪ ችሎታ ነው፡፡ ታዲያ አዝማሪው ይህንን ችሎታውን በልምምድ የሚያገኘው ነው፡፡ ልምምዱ ሁለት መልክ አለው፡፡

አንደኛው በአካባቢ ከሚገኙ ሌሎች አዝማሪዎችና ከታዳሚዎች ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጋብቻ አማካኝነት ከሚቀላቀሏቸው ሰዎች ነው፡፡ አንድ አዝማሪ በመጀመሪያ

የመሰንቆውንም ሆነ የግጥሙን ችሎታ በአካባቢው ካሉ ሰዎች በመስማትና በማየት ይማረዋል፡፡ ከዚህ በኋላም ችሎታውን አሻሽሎ በጠላ ቤቶችና ጠጅ ቤቶች ውስጥ ስራ በሚጀምርበት ጊዜ ታዳሚዎች ‹‹ተቀበል›› እያሉ የሚያቀብሉትን ግጥሞች በመሰብሰብና በማስታወስ ለራሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ እንግዲህ አንደኛው የግጥም መማሪያ ዘዴው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጋብቻ አማካኝነት ከሚቀላቀላቸው ሰዎች የሚያገኘው ነው፡፡ የዘር ሃረግ ቃለመጠይቁ እንደሚያስረዳው አዝማሪዎች በጋብቻ የሚተሳሰሩት ከአዝማሪ ቤተሰብ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ አዝማሪ እሱ ከኖረበት አውድ ውጪ በማምራቱ ለእሱ አዳዲስ የሆኑ ግጥሞች ወደሚከወኑበት ሌላ መንደር ሄዶ ይቀላቀላል፡፡ በዚህ ጊዜ አዳዲስ ግጥሞቹን የሚሰማ በመሆኑ በውስጡ ያለውን የግጥም ክምችት ያሳድጋል፡፡ ይህም ሌላው የመማሪያ መንገድ ነው፡፡

በአጠቃላይ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች ዘፈን ለእነሱ ጥሩ የመተዳደሪያ መንገድ ሆኗቸው የኖረ፣ በሁሉም የህይወት ክስተት ውስጥ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ እንደሆነ የሚገነዘቡት ሲሆን ከዚህ ግንዛቤ የተነሳ እያንዳንዱ የአዝማሪ ቤተሰብ ልጁ የመሰንቆ ጨዋታ እንዲለምድ ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ ልጁም የጥሩ ድምፅ ባለቤት ሆኖ፣ የመሰንቆ ጨዋታንና ግጥም የመግጠም ልምድን በማሳደግ ጥሩ አዝማሪ የሚያስብለውን ችሎታ ያዳብራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ዳብሮ ለትውልድ ሲተላለፍ የኖረው የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን መልክም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

### 6.1.2.3. የዘፈን መልክ

ዘፈንን በተለዋጭነት ጨዋታ ብለው የሚጠሩት አዝማሪዎች ግጥምን ከዜማ አዋህደው ራሳቸውን መሰንቆ በተባለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ አጅበው ይጫወቱታል፡፡ ይህም በመሆኑ የአዝማሪ ዘፈን ሲታሰብ መሰንቆን በተስተካከሉ ቅኝቶች መጫወት፣ የቅኝቶችን ቅደም ተከተል ማወቅ፣ ቅኝቶች የሚጠሯቸውን ግጥሞች መለየትና ሁነትን የሚገልፁ ግጥሞችን መፍጠር አለዚያ ማስታወስ፣ የተለያየ የጥልቀት ደረጃ ያላቸውን ግጥሞች ማወቅ ታዳሚውም ሆነ ራሳቸው አዝማሪዎች ከአዝማሪ ዘፈን የሚጠብቋቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይህንን የገለፀው መረጃ ቀጣዩን ይላል፡- ‹‹ጎበዝ አዝማሪ የሚባለው ጭራው ጥሩ የሆነ፣ ድምጡ ጥሩ የሆነ፣ ቅኝቶችን ለይቶ የሚጫወት፣ ጥሩ ጥሩ ግጥሞችን የሚያውቅ፣ ባየው ነገር ተሎ የሚገጥም፣ ቅኔ የሚያውቅ ነው፡፡ ግን ድምጥ

በተፈጥሮ ነው የሚገኝ፡፡ ዋናው ነገር ጥሩ ጥሩ ግጥም ማወቅና ቅኝት ለይቶ መጫወቱ ነው (ደምሴ አበበ፣ ቃለመጠይቅ፣ 9/04/2005 ዓ.ም፣ ጢሳ አባ ሊማ)፡፡

መረጃው ከአንድ አዝማሪ የሚጠበቁ ዕውቀቶች ምን እንደሆኑ ይዘረዝራል፡፡ የአካባቢው አዝማሪዎች የእነዚህን ችሎታዎች ባለቤት እስከሆኑ ድረስ የአካባቢው ዘፈንም በእነዚህ ባህርያት የሚገለፅ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ዝርዝራቸው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6.1.2.3.1. ቅኝቶች

የወሎ አዝማሪዎች ዘፈንን ትዝታ፣ አምባሰል፣ አንቺ ሆዬና ባቲ በሚባሉ አራት ቅኝቶች ይጫወታሉ፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት አንድ አዝማሪ አዝማሪ ለመባል አራቱን ቅኝቶች በደንብ ማወቅና ለይቶ መጫወት (በመሰንቆው) አለበት፡፡ ምክንያቱም ቅኝቶቹ ዛሬ ላይ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሃብት ቢሆኑ መነሻቸው ወሎ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ የተነሳ ‹‹ማንም አዝማሪ የአገሩን ቅርስ ጠንቅቆ ማወቅ ግዴታው ነው›› በሚል እምነት አዝማሪ ሁሉ ለዚህ ዕውቀት ትኩረት እንዲሰጥ በዕድሜ የገፉ አዝማሪዎች ያበረታታሉ፡፡

እንደመረጃ ሰጪዎች ገለፃ ቅኝት ማለት በመሰንቆው ጭራ ላይ የጣትን አቀማመጥ ርቀት በማስፋትና በማጥበብ የሚፈጠር የድምፅ ቃና ነው፡፡ በዚህ መሰረት ትዝታ፣ አምባሰል፣ አንቺሆዬና ባቲ ቀደም ሲል ተፈጥረው ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገሩ ዛሬ ላይ የደረሱ የአካባቢው የአዝማሪ ዘፈን ቃና አይነቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት እያንዳንዱ የዘፈን ቃና የጣቶችን አቀማመጥ መሰረት አድርጎ የሚፈጠር ስለሆነ እነዚህ ከላይ ስማቸው የተዘረዘረ ቅኝቶች የየራሳቸው የጣት አቀማመጥና የተለየ ዜማ አላቸው፡፡ ይህንኑ ጉዳይ ለመረዳት በመሰንቆ ጭራ ላይ የጣቶችን አቀማመጥ የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡



በትዝታ ቅኝት የጣት አቀማመጥ

የትዝታን ቅኝት ከመሰንቆው ለማግኘት ከመቃኛው ስር የሁለት ጣት ርቀት ዝቅ ብሎ አውራ ጣትይቀመጣል፡፡ በየጣቶች መሐል ደግሞ የሁለት ጣት ያህል ርቀት ክፍተት እየተወ አመልካች፣ መሐልና ቀለበት ወይም ትንሽዋ ጣት[45] ተዘርግተው ይቀመጣሉ፡፡



በአምባሰል ቅኝት የጣት አቀማመጥ


[45]ሁለቱ ጣቶች ተቀያያሪ ናቸው፡፡

የአምባሰልን ቅኝት ለማግኘት  አውራ ጣት ከመቃኛው በአንድ ጣት ወይም የንፋስ ያህል ርቀት ይቀመጣል፡፡ አመልካች ጣት ባለበት ሁኔታ ተዘርግቶ ይቀመጣል፡፡ መሐል ጣት ከአመልካች ጣት በአንድ ጣት ርቀት ትቀመጣለች፡፡ ቀለበት (ትንሽዋ) ጣት ደግሞ መሐል ጣትን ተጠግተው ይቀመጣሉ፡፡



በአንቺ ሆዬ ቅኝት የጣት አቀማመጥ

የአንቺሆዬን ቅኝት ለማግኘት እንደአምባሰል ቅኝት አውራ ጣት ከመቃኛው የአንድ ጣት ወይም የንፋስ ክፍተት ያህል ርቆ ይቀመጣል፡፡ አመልካች ጣት ከአውራ ጣት ሰፊ ርቀት እንዲፈጠር እስከመጨረሻው ተዘርግታ ትቀመጣለች፡፡ መካከለኛ ጣት አመልካች ጣትን ተጠግታ ትቀመጣለች፡፡ ቀለበት (ትንሽዋ) ጣት ደግሞ ከቀለበት ጣት በአንድ ጣት ርቀት ይቀመጣሉ፡፡



**በባቲ ቅኝት የጣት አቀማመጥ**

ስዕል 7. በመሰንቆ ጭራ ላይ ለአራቱ ቅኝቶች የጣቶች አቀማመጥ

ባቲ ቅኝትን ለማግኘት አውራ ጣት ከመቃኛው የአራት ጣት ርቀት ይቀመጣል፡፡ አመልካችና መካከለኛ ጣት ከአውራ ጣት ተጠጋግተው ይቀመጣሉ፡፡ ቀለበት (ትንሽዋ) ጣት ከመሐል ጣት የአንድ ጣት ያህል ክፍተት በመተው ይቀመጣሉ፡፡

ከላይ በመሰንቆ ጭራ ላይ የጣቶችን አቀማመጥ የሚያሳዩ ስዕሎች ቀርበዋል፡፡ በልማዳዊው ደንብ የአንድ መሰንቆ ቁመት አንድ ክንድ ነው፡፡ ስለዚህ  የተገለፀው የቅኝቶች አፈላለግ ይህንኑ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ እንደታየው እያንዳንዱ ቅኝት የየራሳቸው የጣት አቀማመጥ ይፈልጋሉ፡፡ የጣቶቹ አቀማመጥና የሚቀመጡበትና የሚነሱበት የድምፅና የእረፍት ጊዜ መጠን የተለያዩ ቅኝቶችን ይፈጥራል፡፡

በዚህ መልኩ አራቱን ቅኝቶች ከመሰንቆው ላይ በመፈለግ ይጫወቷቸዋል፡፡ ይሁንና መሰንቆ ጨዋታ አዝማሪዎች በልምድ የሚያገኙት ችሎታ እንደመሆኑ ይህ ህግ ለሁሉም ሰው የሚሰራ አይደለም፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ የሚጫወቱ ሰዎች እንዳሉም መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡

አዝማሪዎች አራቱን ቅኝቶች ለመጫወት አምስት ድምፆችን ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ ድምፆች  አራት ጣቶችን የመሰንቆው ጭራ ላይ በማስቀመጥ፣ በማንሳትና አንድ ጊዜ ደግሞ ባዶውን ጭራ ከመሰንቆው መምቻ (በመግረፊያው) ላይ ባለው ጭራ በማጋጨት

የሚፈጥሩት ነው። መሰንቆውን ለመጫወት አውራ ጣት፣ ሌባ ጣት፣ መሐል ጣትና ቀለበት ጣት የሚያገለግሉ ሲሆን አንዳንድ አዝማሪዎች የቀለበት ጣታቸውን ትተው በትንሽ ጣት ይጫወታሉ።

ከላይ የተገለፀው አጨዋወት መደበኛ በሆነ ሁኔታ ብዙ አዝማሪዎች መሰንቆ የሚጫወቱበት ሁኔታ ነው። ከዚህ አለፍ ሲልና የመጠቀ የመሰንቆ ጨዋታ ችሎታ ያላቸው አዝማሪዎች ግን በሁለት ጣት ብቻ አራቱንም ቅኝቶች እስከመጫወት እንደሚደርሱ ‹‹ሁሉም አዝማሪ በአራት እጣቱ ነው የሚጫወት። አንዳንድ ግን በዚህችና በዚች (አውራና ሌባ ጣታቸውን እያሳዩ)ብቻ የሚጫወቱ አሉ። እነዚህ ጎበዝ ተጫዋቾች ናቸው። ንቀውት ነው በሁለት ጣት ብቻ የሚጫወቱ›› ሲሉ አለምፀሃይ የማና የተባሉ መረጃ ሰጪ ይናገራሉ (ቃለመጠይቅ፣ 20/04/2006ዓ.ም፣ ውጫሌ)። ነገር ግን በየትኛውም ጣት ይጫወቱ ቅኝቶቹ አምስት ድምፆችን ይፈልጋሉ። በዚህ መሰረት አራቱም ቅኝቶች በእነዚህ አምስት ድምፆች የሚፈጠሩ ሲሆን ቅኝቶች የየራሳቸውን ቃና የሚይዙ ግን ጣቶች በጭራው ላይ ባላቸው አቀማመጥ እንዲሁም ጭራው ላይ በሚቆዩበት ፍጥነት ነው።

*ምንጭ፡- አስቴር ሙሉ (ከ አቶ ተፈራ አያሌው፣ ከ አቶ ብርሃን ትኩ፣ ከአቶ ማስረሻ ፈንታው፣ ከአቶ አበባው ሙሉጌታ፣ አቶ አሰፋ ለገሰ፣ከአቶ አራጌ ይማም፣ ከአቶ ጫኔ ወርቅነህ ከወይዘሮ አለምፀሃይ የማና ጋር በተለያዩ ቀናት በተካያሄዱ ቃለመጠይቆችና የተተኳሪ ቡድን ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ)።*

ቅኝቶች የየራሳቸው ቃና ብቻ ሳይሆን አፈጣጠራቸውን በተመለከተም የየራሳቸው ታሪካዊ ዳራ እንዳላቸው መረጃዎች ያመለክታሉ። ስማቸው የተዘረዘረ መረጃ ሰጪዎች ቅኝቶችን በተመለከተ ቀጣዩን ብለዋል።

**ትዝታ ቅኝት፡-** ይህ ቅኝት በሌላ ስሙ ወሎ ቅኝት ይባላል። ቅኝቱ ስያሜውን ያገኘው ከሚያነሳው ጉዳይ አንፃር ነው። በትዝታ ቅኝት የትናንትን ህይወት (ያለፈን ጉዳይ) የሚያነሱ ግጥሞች ይቀርቡበታል። ያለፈው ህይወት ምን ይመስል እንደነበር፣ ትናንት ከዛሬ የተሻለ ጥሩ የነበረ መሆኑን፣ ትናንት በማለፉ የተሰማን ፀፀት የሚገልፁ ግጥሞች ይቀርቡበታል።

ትዝታ ቅኝት በወሎ አዝማሪዎች ተለይተው የሚታወቁና አንድ አዝማሪ ሊያውቃቸው ይገባል የሚባሉ ሌሎች ተጨማሪ ዜማዎችንም በስሩ ይይዛል፡፡ እነሱም መዲና፣ ዘለሰኛና ሙኄ ይባላሉ፡፡ መዲናና ዘለሰኛ (ዘለሰኛን ሌይሌይ ብለውም ይጠሩታል)፡፡ እነዚህ ዜማዎች በአንድነት ደግሞ ሰለሞን ጨዋታ ይባላሉ፡፡ ለአምላክ ምስጋና የሚቀርብባቸው፣ የክርስትና ሃይማኖትና ስነምግባር የሚሰበክባቸው ግጥሞች የሚከወንባቸው ዜማዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ዜማዎች መጀመሪያ የሚቀርቡበት ዋናው ምክንያት አዝማሪዎች ምንም እንኳን ዛሬ ቢቀየር የመሰንቆ ጥንት አፈጣጠር አምላክን ለማመስገን ነበርና ያንን ለማዘከር ዘፈንን በምስጋና መጀመር ይገባል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

**ሙኄ**፣ በትዝታ ቅኝት ውስጥ ቢሆንም እንኳን ፈጣንና ለውዝዋዜ የሚጋብዝ ዜማ ነው፡፡ በዚህ ዜማ የፍቅር ዘፈን ይቀርባል፡፡ ገጣሚው ለወደዳት ልጅ ፍቅሩን ይገልፅበታል፡፡ የዜማው አይነት ሰቆጣ ተብሎ በሚጠራው የወሎ አካባቢ የሚዘፈኑ ዘፈኖችን ምት የያዘ ነው፡፡

**አምባሰል፡-** በወሎ ከሚገኙ ግዛቶች ውስጥ አምባሰል በሚባለው በአንዱ ግዛት ስም የተሰየመ ቅኝት ነው፡፡ የአምባሰል ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት ያዘጋጀው በራሪ ወረቀትና በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቅሱት አምባሰል ‹‹አምባ›› እና ‹‹ሰል›› ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ቃል ሲሆን አምባ ማለት ተራራ፣ ሰል ማለት ደግሞ ማር ማለት ነው፡፡ ስለዚህም አምባሰል ማለት የማር ተራራ ማለት ነው፡፡ አካባቢው ይህንን ስም ያገኘው በአካባቢው በርካታ የማር ምርት የሚመረትበት ስለሆነ ነው፡፡ በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ ‹‹ማርዬ›› የተባለችው ቦታ ለአምባሰል የማር ሃገርነት ማስረጃ ልትቀርብ የምትችል ቦታ ናት ይላሉ መረጃ ሰጪዎች፡፡ ምክንያቱም የቦታዋ ስያሜ ከዚሁ ከማር ሃገርነቷ የተሰጠ ነውና፡፡ የአምባሰል መልክዓ ምድር ተራራና ገደል የበዛበት፣ ለጉዞ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁንና አምባሰል በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ግማሽ አካል (ግማደ መስቀሉ) አለበት የሚባለው ግሸን ደብረ ከርቤ ቤተክርስቲያን የሚገኝበት ነው፡፡ የአፄሃይለስላሴ ሚስት እቴጌ መነንም በዚሁ ወረዳ ውስጥ በምትገኝ ‹‹እን ተክለሃይማኖት›› በምትባል ቦታ እንደተወለዱ ይገለፃል፡፡

**አንቺ ሆዬ (ለእኔ)** ፦ አፈታሪኩ እንደሚለው አንቺ ሆዬ ዜማ የተፈጠረው በአንድ ወታደር አማካኝነት ነው፡፡ በአንድ ወቅት በተደረገ ዘመቻ ከሚሴ ውስጥ ርቄ በምትባል ቦታ ወታደር ሰፍሮ ነበር፡፡ በዚህ ቦታ ከሰፈሩ ወታደሮች አንዱ ከአካባቢው ነዋሪ ከሆነች ሴት ጋር ፍቅር ይይዘዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለ ጦሩ እንዲነሳ ይታዘዛል፡፡ ይህንን ጊዜ ወታደሩ በጣም ተጨንቆ ፍቅሩን ለመግለፅ ይሆነው ዘንድ ‹‹መገን አንቺ ሆዬ›› የሚለውን ዜማ አንጎራጎረላት፡፡ ከዚያ በኋላም ዜማውን ፍቅር የያዘው ሰው ሁሉ፣ የፍቅሩን መጠንና የፍቅረኛውን ውበት ለመግለፅ እየተቀባበለ የሚያንጎራጉረው ሆነ፡፡ በድግግሞሹ የተነሳ አንድ ቅኝት ለመሆን በቃ፡፡ አንቺ ሆዬ ቅኝት ከሌሎች ቅኝቶች ለየት ያለ ፀባይ አለው ይላሉ መረጃ ሰጪዎች፤ በጀመረበት የማይጨርስ በጨረሰበት የማይጀምር ‹‹አወናባጅ›› ቅኝት ነው ይሉታል፡፡ ሌሎች ቅኝቶች ግን በጀመሩበት ድምፅ የሚጨርሱ፣ በጨረሱበት የሚጀምሩ ናቸው፡፡

**ባቴ(ቲ)፦** ባቲ ቅኝት ስያሜውን ያገኘው ወሎ ውስጥ ከሚገኙ የአካባቢ ስያሜዎች በአንዱ ነው፡፡ ይህ ቅኝት ራሱን ባቲንና ሌሎችን የወሎን አካባቢዎች የሚጠቃቅሱ ግጥሞች የሚቀርቡበት ነው፡፡ ባቲ የሚባለው በወሎ ውስጥ የሚገኝ ቦታ ጎድጓዳ ነው፡፡ በዚህ ዜማ የሚገጠሙ ግጥሞችም ይህንኑ መልክዓ ምድር በተደጋጋሚ ይገልፃሉ፡፡

## 6.1.2.3.2. የቅኝቶች ቅደም ተከተል

Bauman (1976, 295) ‹‹የማንኛውም ማህበረሰብ ባህላዊ ክዋኔዎች ማህበራዊ ስምምነት የተደረገበት ቅርፅና የመክፈቻና የመዝጊያ ደንቦች አሏቸው›› ይላሉ፡፡ የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ቅኝቶችም ይህ ነው የተባለ ቅርፅ፣ እንዲሁም የአጀማመርና አጨራረስ ደንቦች አሏቸው፡፡ አንድ አዝማሪም ቅኝቶችን ጠንቅቆ ካወቀ በኋላ በአንድ ክዋኔ ውስጥ የቅኝቶችን ቅደም ተከተል ማወቅ አለበት፡፡ በዚህ መሰረት አንድ አዝማሪ ዘፈንን መጀመር ያለበት በመዲና ነው፡፡ ከዚያ ዘለሰኛ ይቀጥላል፡፡ ከዘለሰኛ በኋላ ትዝታ፣ ከትዝታ ቀጥሎ ሙኔ፣ ከሙኔ አምባሰል፣ አንቺ ሆዬና በመጨረሻ ባቲ ቅኝት ይቀርባል፡፡

ዜማዎች በዚህ ቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ምክንያት አለ፡፡ ይህም የአድማጭን ስሜት በጥንቃቄ ከቅዝቃዜ ወደ ሞቅታ ለመውሰድ ሲባል ነው፡፡ የዜማ መጀመሪያ የሆነው መዲናና ተከታዩ ዘለሰኛ ዜማዎች አምላክን የሚያመሰግኑ፣ የክርስትናን እምነትንና ስነምግባር የሚሰብኩ፣ መንፈሳዊ ስሜት ያላቸውና አድማጪ መንፈሳዊ ህይወቱን እንዲፈትሽ፣ ስለፅድቅና ኩነኔ እንዲያስብ የሚስገድዱ ዜማዎች ናቸው፡፡ አዝማሪው በእነዚህ ዜማዎች የታዳሚውን ስሜት ተጭኖ ከቆየ በኋላ ወደ ትዝታ ዜማ ይሄዳል፡፡ በሁለቱ ዜማዎች መካከል ያለው ቃና የተለያየ በመሆኑ ታዳሚው ዜማ መቀየሩን ለመረዳት አይቸግረውም፡፡ ያ ባይሆን ግን አዝማሪው ዜማውን ሲጀምር በሚለው ‹‹የሃዘን አይሉሽ ወይንም የደስታ/ አባካኝ ጨዋታ እንዴት ነሽ ትዝታ›› የሚል ግጥም ዜማ መቀየሩ የግድ ግልፅ ይሆናል፡፡ የትዝታ ዜማ ቃና፣ ከመዲናና ዘለሰኛ ይልቅ ለስሜት ቀለል ይላል፡፡ ይሁን እንጅ ዜማው ናፍቆትን እሽሩሩ የሚል በመሆኑ የሰው ስሜት በመዲናና ዘለሰኛ ከገባበት ጫና በጥቂቱ የሚወጣ ቢሆንም ብዙ ርቆ መሄድ አይችልም፡፡ በዜማው የተለያዩ የትዝታ ስሜትን የሚነግሩ ግጥሞች እየተከወኑ የታዳሚን ስሜት ይዘው ይቆያሉ፡፡ ቀጥሎ ጫና ያረፈበትን የታዳሚ ስሜትቀስ በቀስ ከጫናው ለማውጣት ሲባል ሙኄ የተሰኘው ዜማ ይቀጥላል፡፡ ሙኄ ከትዝታ ዜማዎች ሁሉ ፈጠን ይላል፡፡ ከሙኄ በኋላ አምባሰል፣ ከአምባሰል፣ አንቺ ሆዬ በመጨረሻ ባቲ ቅኝት መደምደሚያ ይሆናል፡፡ ቅኝቶቹ በተደረደሩበት ቅደም ተከተል ፍጥነታቸው እየጨመረ የሚሄድ ነው፡፡ በጨዋታ ቅደም ተከተላቸው ሲታዩ መዲናና ዘለሰኛ በትዝታ ቅኝት ስር ‹‹መቃኛ›› ሲሆኑ ባቲ ‹‹መውረጃ›› ነው ይባላል፡፡ በዚህ የተነሳ አዝማሪዎች፡-

ከሃገሩ ሁሉ ባቲን አልወደውም/ መዳፊያ ነው እንጅ መቃኛ የለውም (ደምሴ አበበ፣ ቃለመጠይቅ፣ 21/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡ ሲሉ የሚቀኙት ቅኔያዊ ግጥም በአንድ በኩል ባቲ የሚባለውን ሃገር ጎድንዳማ መልክዓ ምድር ሲገልፅ በሌላ በኩል የዜማውን በመጨረሻ ተከዋኝነት የሚያሳይ ነው ይላሉ መረጃ ሰጪዎች፡፡

ከላይ የተገለፀው የዘፈን ስርዓት በክርስትናም ሆነ በእስልምና እምነት ተከታይ አዝማሪዎች አከዋወን ደንብ ዘንድ ተመሳሳይ ነው፡፡ መዲናና ዘለሰኛ ዜማዎች የክርስትና እምነት የሚሰበክባቸው ግጥሞችን የሚይዙ ቢሆንም የእስልምና እምነት ተከታይ አዝማሪዎችም ለዘፈን ስርዓቱ በመገዛት ይከውኗቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አምባሰል ውስጥ ጢሳ አባ ሊማ በሚባል ቦታ የተገኙ ደምሴ አበበ የተባሉ የ72 ዓመት የእስልምና እምነት ተከታይ አዝማሪ መረጃ ሰጪ በመዲናና ዘለሰኛ ዜማዎችና የታወቁ

የክርስትና እምነት እውቀቶችን በሚዘክሩ ግጥሞች ዘፈናቸውን ሲጀምሩ ለማየት ተችሏል፡፡ ይከውኗቸው ከነበሩ ግጥሞች ውስጥ፡-

ሀ. ክበር ተመስገን ጌታችን
 ለዚህ ያደረስከን

ለ. ዳዊት እደግማለሁ የኢሳያስን
 እምባቆም ብዬ ብል አቃተው አይኔን

ሐ. ፈርኦን የሚባል ንጉስ
 ህዝቡን ሲያባርር በፈረስ
 ቅዱስ ሚካኤል ቢደርስበት
 ሆዱን ባር ባር አለበት

የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡ በ‹‹ሀ›› የቀረበው ግጥም በጥቅሉ አምላክን የሚያመሰግን ሲሆን በ‹‹ለ››ና በ‹‹ሐ›› የቀረቡት ደግሞ ለክርስትና እምነት መመሪያ ሆኖ ከሚያገለግለው መፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ ይህንን አይነቱን ልማድ ለጋምቦ ወረዳ ላይ የተገኙ አዝማሪዎችም ሲከውኑት ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሁለቱም እምነት ተከታይ አዝማሪዎች በክርስትና እምነት እውቀት ላይ ተመስርተው የሙዚቃ ክዋኔያቸውን የሚያከናውኑ ሲሆን በሁለቱ ሃይማኖቶች ዘንድ እንዴት ተመሳሳይ አጀማመር ኖረ ለሚለው ጥያቄ አዝማሪዎቹ ‹‹ሁሉም ስሙ ይቀያየር እንጅ የሚመሰገነው አንድ ጌታ ነው›› ይላሉ፡፡ ይሁንና ከዚህ ራቅ ተደርጎ ሲታሰብ አዝማሪዎቹ እኛ ከዕዝራ ዘር የወጣን ነን ሲሉ በሚሰጡት የየት መጣ ታሪካቸው የአይሁድን እምነት የወረሰው የክርስትናው እምነት በመሆኑ የተነሳ ለልምዱ ቀዳሚ መስራች ክርስትናው መሆኑንና (በእስልምናው ይህንን የሚገልፅ አፈ-ታሪክም ሆነ ሌላ መረጃ አልተገኘምና) እስልምናው የክርስትናውን ልምድ እንዳለ ወርሶት ሊሆን እንደሚችልም መገመት ይቻላል፡፡ ከቅኝቶች ቅደም ተከተል ጋር አብሮ የሚታሰበው ጉዳይ የግጥሞች ሁኔታ ነው፡፡

## 6.1.2.3.3. ግጥሞች

የወሎ ዘፈን መልክ ከግጥሞች አንፃርም የሚታይ ነው፡፡ ይኸውም የቅኝት ስርዓቶችን የተከተሉና አውድን ግምት ውስጥ ያስገቡ ግጥሞችን መግጠም ለአንድ አዝማሪ ወሎዬና ለወሎ ዘፈን መገለጫዎች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ባህላዊው ደንብ እስከተጠበቀ ድረስ ግጥሞች የሚከወኑበት ቅጥ አለ፡፡ ይህ ቅጥም ግጥሞች ቅኝቶችን የሚገልፁ መሆናቸው ነው፡፡ ለትዝታ ፣በትዝታ ስር ለሚባሉት መዲናና ዘለሰኛ፣ ለአምባሰል፣ ለአንቺሆዬና ለባቲ የየራሳቸው ግጥሞች አሏቸው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ከተገኙ መረጃዎች ውስጥ ‹‹የጨዋታዎቹ ልጆች የተለየ መልክ ነበራቸው፡፡ ባቲ የሚባል አለ፡፡ አንቺሆዬ የሚባሉ አሉ፣ የባቲ ጨዋታ የብቻ ነው፡፡ የየጁ ጨዋታ የብቻ ነው፡፡ ልዩ ነው፡፡ ቀለሙ፣ ተረቱ ማለት ነው (ብርሃን ትኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ) የሚለው ይህንኑ የሚገልፅ ነው፡፡ ቀጥሎ በየዜማው ስር ጥቂት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡

### በመዲናና ዘለሰኛ ዜማዎች የሚቀርቡ ግጥሞች

እነዚህ ግጥሞች ሃይማኖትና ስነምግባርን የሚሰብኩ ናቸው፡፡ ሁለቱም ዜማዎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ግጥሞችን የሚይዙ ሲሆን በሁለቱ ዜማዎች በሚቀርቡ ግጥሞች መካከል ያለው ልዩነት በዘለሰኛ ዜማ የሚቀርቡ ግጥሞችን ለመጫወት ‹‹ና ምነው ወዳጄ›› የሚል አዝማች መግባቱ ነው፡፡

ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
አመስጋኝማ ሰው ቢኖር

ክበር ተመስገን ጌታችን
ለዚህ ያደረስኸን

ወልድ በራስህ ኮርተህ
ከሰማያት ወርደህ
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
አብ አይበልጥም ወይ አባትህ
ተለማኝ እናትህ

## ዘለሰኛ

እህ ና ምነው ና ምነው (ይደጋገማል) (ከግጥሞቹ መሃል ይመጣል)
አምላክ ግብር አርጎ ያበላል ይላሉ

አንድ ቀሪ የለም ሁሉም ይጠራሉ

አምላኬ ግብርህን እንዳታሳንሰው

እንቢ ብሎ አይቀርም አንተ የጠራኸው ሰው

እመቤቴ ማርያም ኧረ ተይ ኧረ ተይ

ኧረ ተይ ኧረ ተይ ልጅሽን ተቆጭው

አንቺ እንደምን አዘንሽ አንድ ቀን ብታጭው

መፆሙን ይፆማል ሁሉም ያምላክ ልጅ

የጊዜውን መድረስ የሚያውቅ የለም እንጅ

## በትዝታ ቅኝት የሚባሉ ግጥሞች

የሃዘን አይሉሽ ወይንም የደስታ

አባካኝ ጨዋታ እንዴት ነሽ ትዝታ

ትዝ ብላኝ አልቅሼ እላለሁ ቢርበኝ

ከሆዴ ሰው ቢኖር እንዴት በታዘበኝ

ትዝታሽ ዘወትር ወደ እኔ እየመጣ

እፎይ የምልበት ህይወቴ ጊዜ አጣ

ተይኝ ትቼሻለሁ ረሳሁሽ እርሽኝ

እንደደረቀ ጠጅ እየጣልሽ አታንሽኚ

## በአምባሰል ቅኝት የሚባሉ ግጥሞች

እኒህ አምባሰሎች አበላል ያውቃሉ
ከገብስ እንጀራ ላይ ሳማ አርጉ ይላሉ

እንዴት ነሽ አምባሰል እንደምን ነሽ ጢሳ
የተቋደስንብሽ ፍቅር ራት ምሳ

የአምባሰል ማር ቆራጪ ይወርዳል በገመድ
አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ

አምባሰል ለገደል ምን ያሽሟጥጡታል
ፈረስ ባያስጋልብ ሰው ይወጣበታል
ግማደ መስቀሉ ተቀምጦበታል
ንጉስና ጳጳስ ይወለድበታል

ላሊበላን ሳምሁት ካመት ሁለት ጊዜ
ላስታም እመጣለሁ ሁልጊዜ ሁልጊዜ

## በአንቺሆዬ ቅኝት የሚባሉ ግጥሞች

ሰዎች ተሰብስቡ ፍቅርን እንክሰሰው
ባንከሰው እንኳን ትንሽ እንውቀሰው
እንዲህ ማታ ማታ ከሰው ደጃፍ ወስዶ መጎለቱን ይተው

እኔ ጠላ ወዳጅ እስዋ ጠላ ወዳጅ
የዚህ ጠላ ነገር እኔስ ጠፋኝ ቅጡ
እናቲቱ ገብተው እየበጠበጡ

ወድጄሽ ብቆጣ ፍቅርሽ ቢጠናብኝ
ቀናተኛ ብለሽ ምነው የላክሽብኝ

በሰቆጣ መንገድ በመንበረ ጣይ
ሽጌ ጥላ ይገፍ ልከተለሽ ወይ

## በባቴ(ቲ) ቅኝት የሚባሉ ግጥሞች

ኧረ ባቲ ባቲ ባቲ ገንደላዩ
ሃድራው የሚገባው ደራርበው ሲተኙ

እምቢ ብላ ነበር እየኮበለለች
ባቲ ላይ ታትደርስ ተገርፋ ተያዘች
ባቲ ባቲ ገንደላዩ
ሌላ አይወዱም አንቺን ያዩ

የሰው ሁሉ ህመም ራስ ወገቡን ነው
የእኔ በሽታዬ ባቴ ነው ባቴን ነው።

እንደባቴ ያለ ሃገር ካገኘህ
ሂድና ሞክረው ቀልጠህ ካልቀረህ

ይሄ ባቴ ማለት ድንበሩ ጨረቃ
እደርሳለሁ ብሄድ ብገሰግስ ደርቃ

በዚህ መሰረት የግጥሞች ይዘት የቅኝቶችን ስልት ተከትሎ የሚፈስ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ። ይሁንና ይህ ጉዳይ ሁልጊዜ የማይጠበቅ ሊሆን ይችላል። ዛሬ በጥንታዊዎቹና ጎበዝ በሚባሉት ሰዎች ሳይቀር ሁልጊዜ ተጠብቀው የሚሄዱ ላይሆኑ ይችላሉ። በአንድ ጨዋታ እንኳን በአንዱ ቅኝት የተባለው ግጥም ለሌላው ቅኝት ሲዞር (ሲሆን) ይታያል። ምሳሌዎች የቀረቡ መሰረታዊው ልምድ ምን እንደሆነ ለማሳየት ያህል ነው። በዚህ ዕውቀትና ቅደም ተከተል አዝማሪዎች ዘፈንን በተለያዩ አውዶች ሲከውኑ ኖረዋል። ሌላው በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን መልክ ውስጥ የሚታየው ጉዳይ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ግጥሞች ማወቅ ነው።

### 6.1.2.3.4. የግጥሞች ደረጃ

ገጣሚነት አንድ አዝማሪ ከመሰንቆ ጨዋታ በላይ የሚጠበቅበት ችሎታ ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት አዝማሪዎች የሚከውኗቸው ግጥሞች ደረጃ አላቸው፡፡ግጥሞቹ ደረጃቸውን የሚገኙት ከሚከወኑበት አውድ ነው፡፡ ዘፈን ለአዝማሪው የገቢ ምንጩ መሰረት እንደመሆኑ በርካታ ግጥሞችን ማወቅ አለበት፡፡ አዝማሪው ግጥሞችን በሚከውንበት ጊዜ ለአውዱ ተስማሚና በተለይ የታዳሚውን ደረጃ የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ያ ሲሆን አላማው ግቡን ይመታል፤ ከታዳሚው የሚፈልገውን ጥቅም ያገኛል፡፡ ከዚህ ለአውድ የተስማማ ግጥም የመግጠም ችሎታ የገንዘብ ጥቅም ብቻ ሳይሆን በታዳሚውና በሌሎች አዝማሪዎች ዘንድ ጥሩ አዝማሪ የሚያስብል ስም ያሰጣል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ‹‹የተከበሩ›› ለሚሏቸው ሰዎች የሚገጥሟቸውን ግጥሞች በመጠጥ ቤት ውስጥ አያቀርቧቸውም፡፡ ይህንን ሃሳብ አለምፀሃይ የማና እንዲህ ይገልፁታል፡፡

> *አይ ጠጅ ቤት እንኳን አመጣው ወሰደው ነው፡፡ የእነ ገሬ ጌታ፣ የነጫላ ጌታ ነው የምንላቸው፡፡ ይኸ እንኳን እንዲያው ዝም ብሎ ነው፡፡ ዝም ብለን ደስ እንዲላቸው፡፡*

በሬው ቲፈታበት ወጥቶ ማያስር ሰው
ኧረ እንደምን አርጎ ደረትሽን ዳሰሰው
እመስሪያ ቤት ሄዶ ውል እማይመልሰው
የጎመን ወጥ በልቶ እጁን የሚልሰው
ኧረ እንዴት ብሎ ነው አንቺን የጠቀሰው

*እንላለን እጠጅ ቤት፡፡ አይ የጠጅ ቤቱስ እንዲያው ዝም ብሎ አጨዳ ሽምጠጣ ነው፡፡ እንደገባልን ነው የምንጫወተው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣* 17/04/2005 ዓ.ም፣ ውጫሌ)

መረጃው፣ የጠጅ ቤት ዘፈን ብዙ ጥንቃቄ የማይጠይቅ እንደሆነ፣ ለጠጪው ጊዜያዊ (ቅፅበታዊ) ደስታ ከመፍጠር ያልዘለለ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

በአንፃሩ የተከበረ ማህበራዊ ደረጃ አላቸው ለሚባሉ ሰዎች የሚቀርቡ ግጥሞች ደረጃቸው ከፍ ያለ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይህንን ሲገልፁም ‹‹ግጥም እኮ ብዙ አይነት

ነው፡፡ አንድ አዝማሪ ብስል ተጥሬ ግጥም ነው የሚያውቅ፡፡ ተግብር ላይ የሚገጠመው፣ ለሴት ወይዘሮ የሚገጠመው ግጥም የባለዬ ታይሆን ክብራቸውን የጠበቀ ነው፡፡ መጠጥ ቤት ሲሆን ደግሞ ለሳቅ የሚሆን፣ ለጊዜው የሚያጫውት ነው››፡፡ ተጫዋች ሲባል፡፡ ጨዋታ ከማን ያመጣል ከቀሳውስት፣ ከሙህሮች፣ በታቦቱ፣ በአንቺ ስራ በአባትሽ ስራ፣ሴት ወይዘሮ እንደሆነች በሴት ወይዘሮ ስራ፣ በአባቷ ገብቼ ነው የሚገጠም፡፡ በተከበረ ቦታ የሆነ እንደሁ ምን ተብሏል፡፡

እንዴት ዳዊት ይሙት ቆሜ ሳልጠይቀው
የሚመጣውን ቀን በገና የሚያውቀው
እትጌ መነን ምን ተብላለይ?
ሰድባ ሰደደችው ሽማግሌውን
እስቲ ተመልከቷት ባልጋለች መነን፡፡
(ብርሃን ትኩ፣ ማስረሻ ፈንታው፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት 12/05/2005 ዓ.ም. ፣ ማርዬ)

መረጃዎቹ፣ አዝማሪዎች በየአውዱ የሚከውኗቸው ግጥሞች ቅርፅና ይዘት የተለያየ እንደሆነና የግጥሞቹ የይዘት ጥልቀትና የቅርፅ ምጣኔ ብቃት ልዩነት አውድን መሰረት ያደረገ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ዕውቀትና ቅደም ተከተል አዝማሪዎች ዘፈንን በተለያዩ አውዶች ሲከውኑ የኖሩ ሲሆን የመከወኛ አውዶች ምንነትና ባህርይም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 6.1.2.4. የዘፈን መከወኛ አውዶች

(Finnegan, 1992, 88) አውድ፣ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ከክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ክዋኔ ሲመረመር አውድን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ይህም በሰዎች መካከል ያለ ግንኙነትና ባህላዊ ስምምነቶችን ለመረዳት ያስችላል፡፡ በማለት የአውድን ምንነትና አስፈላጊነት ሲገልፁ (Dundes,1986,4) ደግሞ አውድ የአንድን ክዋኔ አካላዊ መቼት፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና፣ የድርጊት ቅደም ተከተል፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋትና በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት አጠቃሎ እንደሚይዝ ይገልጻሉ፡፡ ይህ በመሆኑም የአውድ ጥናት ሲደረግ ለእነዚህ ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥ

እንደሚገባ ይጠቁማሉ። ከዚህ በመነሳትም ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት የአዝማሪ ዘፈን ይከወንባቸው የነበሩና ዛሬም የሚከወንባቸውን ነጥቦች ለመመርመር ተሞክሯል።

የወሎ አዝማሪዎች ከጥንት አንስቶ እስካሁን ድረስ ዘፈናቸውን የሚከውኑባቸው የተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ አውዶች አሏቸው። እነዚህ አውዶች መንደሮች፣ ገበያ፣ ግብር፣የተለያዩ ድግሶች፣መጠጥ ቤቶች፣ ጦርነት፣ የታቦት ንግስ ናቸው። የተዘረዘሩት አውዶች የየራሳቸው ባህርይ ያላቸው መሆኑን የሚገልፁት አዝማሪዎች በእያንዳንዱ አውድ የሚከውኑት ዘፈን የተለያየ መልክ አለው ይላሉ። እያንዳንዱ አውድ ሲመረመር የሚከተለውን ይመስላል።

## 6.1.2.4.1. ግብር

ግብር ቀደም ባለው የኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ንጉሱ ወይም አስተዳዳሪው ለቤተመንግስት ባለሟሎች የሚያደርገው ግብዣ መሆኑ በግርጌ ማስታወሻ ተራ ቁጥር ሃያላይ ተጠቅሷል፡፡ ግብር የሚከናወነው በአስተዳዳሪው ቅጥር ግቢ ወይም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡

መረጃዎች ደሴ ከተማ የሚገኘውና አይጠየፍ የሚባለው አዳራሽ ንጉስ ሚካኤል ለግብር ማብያ ያሰሩት እንደሆነ ይገልፃሉ (ገብረኪዳን፣ 1981፣15)፡፡ ንጉስ ሚካኤል አዳራሹን ያሰሩት ነባሩን በአዳራሽ ውስጥ ግብር የማብላትን ልማድ ተከትለው እንደሆነና ለውጡ ትልቅና ዘመናዊ አገነባብ የተከተለ አዳራሽ ማዘጋጀታቸው እንደሆነ ለማየት ይቻላል፡፡

መረጃዎች እንደሚሉት ግብር ዋና ታዳሚዎቹ ሹማምንት ናቸው፡፡ እነዚህ ሹማምንት ወደ አዳራሹ ከገቡ በኋላ በስልጣን ተዋረድ ይቀመጣሉ፡፡ የምግብ አቀማመጡ መስተንግዶው የራሱ ስርዓት አለው፡፡ የአዝማሪ የዘፈን ክወና የስርዓቱ አካል ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት በግብር ስርዓት ውስጥ ተራ ከሚባለው ማህበረሰብ ውስጥ ያለምንም ከልካይ መግባት የሚችለው አዝማሪ ብቻ ነው፡፡ አዝማሪዎች ይህ ሊሆን የቻለው ‹‹ከጥንት ጀምሮ መጋረጃ ገልጠህ፣ ዙፋን ረግጠህ ግባ›› የሚል ምርቃን ስላለን ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ቁጥራቸው ምንም ያህል ቢሆን ወደ ግብር ቦታ በመሄድ ዘፈንን ከውነው፣ ግብሩን በልተው፣ ሽልማት ተቀብለው ይወጣሉ፡፡ በግብር ውስጥ ያለው ስርዓት ምን እንደሚመስል የገለፁት ብርሃን ትኩ የተባሉ መረጃ ሰጪ፡-

> ከዚያ ከታች ጀምሮ ነጭ ለባሹ ይቆማል፡፡ እኛ ሰተት ብለን እንገባለን፡፡ መኳንንቱ መሳፍንቱ ተቀምጧል፡፡ ከእሱ ፊት ለፊት ሆነሽ የግብር ግጥም እየገጠምሽ ትቆያለሽ፡፡ ግብሩ አንድ ጊዜ ነው፡፡ ግብር ሊቀርብ ሲል ቦታ ይሰጥሻል፡፡ እረፉ ተቀመጡ ይባላል፡፡ ከዚያ ቢላዋውም ምኑም ይቀርብልሻል፡፡ ብርንዶ፣ አልጫ፣ ቀይ ወጥ የፈለገው ይመጣልሻል፡፡ ኋላ ልትወጭ ስትይ እጅ ስትነሽ ጌታው ለአስተናጋጁ አስተናግዳቸው ብሎ ገንዘቡን ይሰጠዋል፡፡ አላፊ አላችሁ ብሎ ይጠይቃል፡፡ ካለው አንዱ ትልቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያ ከዙፋን ችሎት ይህንን ያህል አግኝተናል ተብሎ መከፋፈል ነው፡፡ ለእያንዳንድሽ አትሰጭም፡፡ ያውቃል፣ አያውቅም የለም፡፡ አይምታምም፣ ከሞከረ ይካፈላል፡፡ አዝማሪ ነው፡፡ የዕዝራ ልጅ ይባላል ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም)፡፡

መረጃው አዝማሪዎች በግብር ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባርና የሚያገኙትን መስተንግዶ የሚገልፅ ነው፡፡ መረጃው እንደሚለው በግብር ወቅት አዝማሪዎች የሚጫወቷቸው ዜማዎች መዲናና ዘለሰኛ ናቸው፡፡ አንድ አዝማሪ በግብር ቦታ ተገኝቶ ለመዝፈን እነዚህን ዜማዎች መጫወት መቻል የመጀመሪያ መስፈርት ነው፡፡ እነዚህ ዜማዎች ለስላሳና አዝማሪዎች ብቻቸውን የሚጫወቷቸው ናቸው፡፡ ዜማዎች የታዳሚን እዝነ ልቦና እንጅ ጭብጨባና ግጥም መቀበል ስለማይጠይቁ ታዳሚዎች ምግብን እየበሉ ግጥሞችን ያዳምጣሉ፡፡ ከዚህ በተረፈ ደግሞ በቤተ መንግስት ውስጥ በሚደረግ ግብር ዋና ታዳሚዎች ሹማምንት ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ደግሞ ‹‹የተከበሩ›› ሰዎች እንደመሆናቸው በፊታቸው የሚቀርበው ማንኛውም ነገር ስርዓት ያለው እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ እንግዲህ ከስርዓቶቹ ውስጥ በግብር ወቅት መዲናና ዘለሰኛን እያዳመጡ መመገብ አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንኑ ስርዓት ለመጠበቅ ሲባል መዲናና ዘለሰኛ ዜማዎችንና ግጥሞችን የመጫወት ችሎታ ያላቸው አዝማሪዎች በግብሩ ላይ ተገኝተው ዜማዎቹን ይጫወታሉ፡፡ ሌላው የአዝማሪ ዘፈን የመከወኛ አውድ መንደር ነው፡፡

## 6.1.2.4.2. መንደሮች

መንደር የሚለው ቃል በዚህ ጥናት ውስጥ የሚገልፀው የተለያዩ ቤተሰቦች በአንድነት ተሰብስበው የሚኖሩበትን አካባቢ ነው፡፡ መንደር አዝማሪዎች ዘፈንን ከሚከውኑባቸው አውዶች መካከል አንዱ ነው፡፡ አዝማሪዎች ወደ መንደሮች በሚሄዱበት ጊዜ በሰፈሩ ውስጥ ድግስ ሊኖር ወይም ላይኖር የመንደሩ ነዋሪዎችም የተለመደ የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን እየከወኑ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰዎች በየትኛውም ሁኔታ ይኑሩ አዝማሪዎች ወደሰፈሩ በመጠጋትና ሰው ወዳዩበት ቤት በመሄድ መምጣታቸውን የሚገልፁ ዜማዎችን ያሰማሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ወደሰፈሩ ሲገቡ አስቀድመው መረጃዎችን ሰብስበው ስለሆነ የተሻለ ሃብት ወዳለው ቤት ይሄዳሉ፡፡ በዚህ መንደር የሚገኙት በሰዓቱ የተሰማቸውን ረሃብ ለማስታገስ፣ ቡና እንዲፈላላቸው ለመጠየቅ አለዚያ ደግሞ በመምሽቱ የተነሳ እንዲያሳድሯቸው ለመጠየቅ ይሆናል፡፡ ምንም ጉዳይ ይሁን አይሰጡንም የሚል ስጋት ሳያድርባቸው ወደ ሰፈሩ ይጠጉና የሚፈልጉትን ነገር በዜማና በቀልድ በማዋዛት ይጠይቃሉ፡፡ በተለይ ሴት አዝማሪዎች የድግስ ቀንም ይሁን አይሁን በየመንደሩ በመዞር የሚያስፈልጋቸውን ነገር (እህል፣ ቅቤ፤ እርጎ፣ወዘተ)

የቤት እመቤቶች እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ፡፡ ጥያቄው፣ በዘፈን፣ በምርቃት አለዚያ ደግሞ እኔ አዝማሪ ስለሆንሁ ስጡኝ በሚል ደረቅ ልመናም የሚካሄድ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ  ወ/ሮ አሰጉ ሰኢድ የተባሉ መረጃ ሰጪ ፡-

> እንዲያው በገባንበት ቤት ሁላ እንዘፍናለን፡፡ የጎበዝ ቤት፣ የደህና ቆንጆ ቤት ታገኝን እንዘፍናለን፡፡ መጣን አዝማሪዎች እነ ታጥቆ ሜዳ እነ ወለል ቀዳ፣ እነ አሳብ የለሽ እነ በሰል ብላ እንላለን፡፡ ይኸው ነው፡፡ አወ እንግዲህ ታጥቀን እንሄድ የለ? ሚያዘፍን ያዘፍነናል፤ ማያዘፍን ምርቃት ለከጀለ፣ በይ እንግዲህ እቴ የጠራራው ሸህ መጣ፣ ወንድና ጀበና ሲቆም ነው የሚወደደው፤ ቡና አፍይልን እንላታለን፡፡ አልወለደች እንደሁ፣ እንድትወልጅ ብለን ዱኣ[46] እናደርጋለን እንላለን (ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

መረጃው አዝማሪዎች ከማንም ሰው ቤት የመግባት መብት እንዳላቸው እነሱ ግን መርጠው ሃብታም ነው ካሉት ቤት እንደሚገቡ ይናገራል፡፡ ወደመንደሩ ሲሄዱ የሚያሰሙት ዜማም እነሱ ትጥቃቸውን አሳምረው ለብሰው በየቤቱ እየዞሩ ከመለመን በቀር የራሳቸው የሆነ ቤትና ሃብት የሌላቸው መሆኑን ይገልፃል፡፡

በዚህ ጊዜ ማህበረሰቡ የለኝም አይልም፡፡ በትክክል ባይኖር እንኳን ለሌላ ቀን ተቀጥረው ይሄዳሉ እንጅ ፈፅሞ አልሰጥም አይባልም፡፡ ይህ ሁኔታ በማህበረሰቡና በአዝማሪዎች ካሉ ‹‹አዝማሪዎች የመረቁት የተመረቀ፤ የረገሙት ደግሞ የተረገመ ይሆናል›› እና ‹‹አዝማሪነት የአባት ስራ በመሆኑ ማንም አዝማሪ ‹ለምኖ› መብላት ግዴታው ነው›› ከሚሉ እምነቶች የተነሳ በማህበረሰቡም ሆነ በሹሞቹ ዘንድ ስራው ፈቃድ የተሰጠው በመሆኑ ነው፡፡  ስለዚህ ማንም ለአዝማሪ አልሰጥም የሚል ሰው በሹም ይከሰሳል፡፡ ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ አቶ ማስረሻ ፈንታው የተባሉ መረጃ ሰጪ በተተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት ‹‹እንደ አባታቸው ይሰሩ ከተባለ ገበሬው ሁሉ ይታዘዝልኛል፡፡ በጭቃ እኮ ታስገድጅዋለሽ፡፡ አንቺ ገበሬ ሁነሽ አልሰፍርም ታልሽ ጭቃው፣ ምስለኔው ምን ይብላ? ይለዋል›› (11/05/2005 ዓ.ም.፣ ማርዬ) ብለዋል፡፡

---

[46]ፀሎት፡- ከአረብኛ  ቋንቋ የተገኘ ሲሆን በአካባቢው በስፋት አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡

ጥቅሱ አዝማሪዎች የገቢ ምንጫቸው ከሌላው ሰው የሚያገኙት ሽልማት እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡ ሽልማቱም ሲፈለግ ወይም ደስ ሲል የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ለአዝማሪው እንደደሞዝ ታስቦ የሚሰጥ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለአዝማሪው የሚበላውን የመስፈር፣ የሚለብሰውን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ሌላ መረጃ ሰጪ እንደገለፁት አዝማሪዎች ሲዞሩ በዋሉበት ሃገር ቢመሽባቸው ያለምንም ስጋት ወደ አንድ መንደር በመሄድ መስተንግዶ ያገኛሉ፡፡ ጉዳዩን እንደሚከተለው ነው የገለፁት፡-

> አዝማሪ በንጉሱ ጊዜ በመሲንቆ ይተዳደር ነበር፡፡ የትም ቢገባ አትግባ ብሎ የሚከለክለው የለም፡፡ ስዞር በዋልሁበት አገር ሲመሽ ወደ አንዱ ቤት እሄድና ከደጃፍ እቀመጣለሁ፡፡ ባለቤቱ አምሽቶ ሲመጣ እነማን ናቸው ይላል፣ አዝማሪዎች ይባላል ኸረ ግቡ በሏቸው ይባላል እንገባለን፣ ይነጠፋል ፣ ይጎዝጎዛል፣ መብል ይመጣል፣ መጠጥ ይመጣል፣ ከዚያ ወዲያ መሲንቆ አነሳለሁ፡፡ ሰው ያለውን ይሰጣል ኩታም ሆነ፣ ልብስም ሆነ እሱን ተቀብዬ አድሬ እሄዳለሁ (ብርሃን ትኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ 09/04/2005፣ ማርዬ)::

ስለዚህም አዝማሪዎች በየመንደሩና በየአገሩ እየዞሩ ለማህበረሰቡ የሚያስፈልገውን የዘፈን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በመልሱም ከእለት ሽልማት አንስቶ እስከ ዓመት ቀለብ የሚሆናቸውን ነገር ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይ የድሮ አዝማሪዎች ባህርይ ቢሆንም ዛሬም ቢሆን እንዳልቀረ ወጣት አዝማሪ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡ ወደ የትኛውም መንገድ ጉዞ እያደረጉ በመንገድ ላይ ቢራቡ ወይም ቢጠሙ ወደ መንደር ጎራ ብለው እህል ውሃ የሚጠይቁ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይህንን ሲያደርጉም የቤት ባለቤቶች እነሱ አዝማሪ መሆናቸውን እንዲያውቁ መሰንቆ እየመቱ፣ የሙገሳ ግጥሞችን እየተጫወቱ ወደ ቤት በመጠጋት ነው፡፡ ባለቤቶች አዝማሪ መምጣቱን እስካወቁ ድረስ ወደቤት እንዲገባ በማድረግ ቤት ያፈራውን ነገር ይሰጣሉ፡፡ ይህንን ልምዱን የገለፀው የሃያ አንድ ዓመት ወጣት አበባው ሙሉጌታ ቀጣዩን ብሏል፡-

> እዚህ ላይ አንድ ገጠመኝ አለኝ፡፡ ወደ ላሊበላ ስሄድ፡፡ ዘመድ ለመጠየቅ ማለት ነው፡፡ ከድሮ ጀምሮ ዱላ መያዝ አልወድም፡፡ ይህችን መሰንቆዬን

ብቻ ይዣለሁ፡፡ እርቦኛል በጣም፡፡ አሁን የሆነ ቤት ነው፡፡ ስሄድ ውሻው ተኝቷል፡፡ በጣም ሃይለኛ ውሻ ነው፡፡ ክላሽ ሁሉ ይቀማል አሉ፡፡ አሁን ያንን ማስንቆ ይዤ ከበር ጀምሮ እየመታሁ ገባሁ፡፡ ስለራበኝ ልበላ ነው ወደዚያ ቤት የገባሁ፡፡ ያ ውሻ ቀና ብሎ አይቶ ዝም አለ፡፡ ባለቤቶቹ እንዴት ዝም አለህ ብለው ተገረሙ፡፡ ወደቤት አስገቡኝና የምበላውን ሰጥተው ሸኙኝ፤ (አበባው ሙሉጌታ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/5/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ )፡፡

መረጃው አዝማሪው ከውጫሌ ወደ ላሊበላ ዘመድ ለመጠየቅ ሲሄድ በመንገድ ላይ ረሃብ ስላጋጠመው ረሃቡን ለማስታገስ ወደ አንድ መንደር መጠጋቱንና በአንድ ቤት ውስጥ ምሳ መብላቱን የሚገልፅ ነው፡፡ መረጃው እንደሚለው አዝማሪው ይህ ቤት የማን ስለመሆኑ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ ይህ በመሆኑም አደጋ ሊያደርስበት ይችል የነበረ ሃይለኛ ውሻ በቤቱ መኖሩን አላወቀም፡፡ ያም ሆኖ ግን ውሻው ምንም አደጋ ሳያደርስበት ወደቤቱ ገብቶ ለመስተናገድ ችሏል፡፡ መረጃ ሰጪው ለምን ውሻው እንዳልበላው ሲናገር ‹‹ውሻኮ የመሰንቆ ድምፅ ከሰማ ይለሰልሳል ብሏል፡፡ ሰዎች ያስተናገዱት ደግሞ አዝማሪ ከማንኛውም ሰው ቤት ገብቶ የመስተናገድ የጥንት ልማድ ስላለ ነው ሲል ገልጧል፡፡ በአጠቃላይ መረጃ ሰጪው አዝማሪነቱ ያስገኘለትን መብት ተጠቅሞ መልካም መስተንግዶ ማግኘቱን መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡

አዝማሪዎች ይህንን ከመንደር መንደር እየተዘዋወሩ በዘፈንና በውዳሴ ገቢ ማግኘት ‹‹ልመና›› ሲሉ ይጠሩታል፡፡ ይህንንም የሚሉበት ዋና ምክንያትም በዚህ አውድ የሚደረግ ማንኛውም ክዋኔ እንደሌሎች አውዶች ሁሉ ተዝናንቶ በማዝናናት ገቢ ለማግኘት ሲባል ሳይሆን ግልፅ በሆነ መንገድ ስጦታን (ጥቅምን) ለማግኘት ሲሉ ብቻ የሚከውኑት በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ክዋኔው በዚሁ መንገድ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ብቻ ዘፈን የሚከወንበት አውድ ገበያ ነው፡፡ የገበያ የክዋኔ መንገድና ሁኔታም የሚከተለው መልክ አለው፡፡

### 6.1.2.4.3. ገበያ

ገበያ ለአዝማሪዎችም ሆነ ለሌላው ሰው ዋና የመገናኛ ቦታ ነው፡፡ ሰዎች በገበያ ውስጥ የተለያዩ ሸቀጦችን ለሽያጪ ያቀርባሉ፡፡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ‹‹ገበያ የሚሰጠውን የእናት ልጅ አይሰጥም›› እንደሚባለው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለመሸመት ወደገበያ ይወጣሉ፡፡ ሽያጪና ግዥውም ‹‹ሰጥቶ በመቀበል››መርህ መሰረት ይተገበራል፡፡ ማለትም ሰዎች ለሚፈልጉት ሸቀጥ ተገቢ የተባለውንና የተስማሙበትን ዋጋ በመክፈል ሸቀጡን ይወስዳሉ፡፡

ሌላው የማህበረሰብ ክፍል በዚህ መንገድ የሽያጪና ግዥ ስርዓት ሲያከናውን አዝማሪዎች ደግሞ መሰንቋቸውን ብቻ ይዘው ወደ ገበያ ይወጡ እንደነበር መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ከዚያም በገበያው ውስጥ በመዘዋወር ሰዎች ከያዙት ነገር እንዲሰጧቸው በውዳሴ ይጠይቃሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ወንዶች መሰንቆ በመጫወት የሚጠይቁ ሲሆን ሴቶች ግን በመሰንቆ ሳይታጀቡ፣ ዘፈንም ሳይጫወቱ አዝማሪ መሆናቸውን በመግለፅ ብቻ የፈለጉትን ነገር ጠይቀው ይወስዳሉ፡፡ ይህንን ጉዳይ አቶ ተስፋዬ በላይ ‹‹በተለይ ገበያ ሂደው የሚለምኑ ሴቶች ናቸው፡፡ የፈለጉትን ነገር ሁሉ ስጡኝ ይላሉ፡፡ አይከለከሉም፡፡ ምክንያቱም ገበያው ለእነሱ አገር ሆኖ የተሰጠ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር የሚያገኙ ከዚያው ነው፡፡ እነሱም ወደሌላ አይሄዱም፡፡ ሌላውም አይመጣባቸው፡፡ የአገሬው ሰው አዝማሪ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ይሰጣቸዋል›› ሲል ይገልፀዋል (ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ማርዬ)፡፡

በገበያ ውስጥ የሚደረገው ‹‹ልመና›› የማስገደድ ባህርይ ያለው ነው፡፡ አዝማሪዎች የፈለጉትን ነገር ስጡኝ የሚሉ ሲሆን ሌላው ሰው ደግሞ እንቢ ለማለት ምንም መብት የሌለው ይመስላል፡፡ በተለይም በዘውድ አገዛዝ ዘመን አዝማሪዎች መተዳደሪያቸው ይኸው የመሰንቆ ጨዋታ ብቻ በመሆኑ ሌላው ሰው የሚበሉት ካልሰጣቸው ችግር ስለሚሆንባቸው በመንግስት አስተዳደር በኩል ከሌላው ሰው የሚፈልጉትን እንዲያገኙ የመጫን ሁኔታ ነበር፡፡

በዚህ መሰረት ስርዓቱ የሰጣቸውን ዕድል በመጠቀም የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከማህበረሰቡ ዘንድ ለማግኘት ሲሉ ዘፈንን በገበያ ውስጥ ሲከውኑ ኖረዋል፡፡ ሌላው የአዝማሪዎች የዘፈን መከወኛ አውድ የነበር ቦታ ጦርነት ነው፡፡ የአውዱ ገፅታ የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

### 6.1.2.4.4. ጦርነት

ጦርነት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ ዘመን የኖረ ክስተት ነው፡፡ ወሎም ከኢትዮጵያ ክፍላተ ሃገራት አንዱ እንደመሆኑ የዚህ ክስተት ሰለባ ሆኖ ኖሯል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ በስልጣን ሽኩቻ የተነሳ እርስ በእርሳቸው ሲዋጉ ከነበሩት ባላባቶች አንስቶ የውጪ ወራሪ ጠላት ድረስ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ጦርነቶችን አስተናግዷል፡፡ መረጃዎች እንደሚሉት በእነዚህ የጦርነት ጊዜያቶች ሁሉ አዝማሪዎችን ይዞ ወደ ጦርነት መጓዝ የውጊያ አንድ ገፅታ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ለውጊያ የሚወጣው እያንዳንዱ ባላባት ሊቀመኳስ በሚል ማዕረግ ወይም በአዲስ ቀሚስ ሽልማት አዝማሪውን ሾሞ ወደ ውጊያው ቦታ ይሄዳል፡፡

ዝክረ ነገር (1942) ሊቀ መኳስን በኢትዮጵያ መንግስት የስልጣን አደረጃጀት መሰረት አለማዊ የሆነ (መንፈሳዊ ያልሆነ)፣ የስቪል (ወታደራዊ ያልሆነ) ማዕረግ ነው በማለት ሲበይን፣ የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር መዝገበ ቃላት (1993) ደግሞ ሊቀ መኳስን ፣ እንደንጉስ  የሚለብስና በንጉስ አጠገብ የሚቆም የንጉስ ባለሟል በማለት ይፈታዋል፡፡ ዝክረ ነገር (1942፣ 647) ይህንን ማዕረግ የሚቀበለውን ሰው ተግባር ሲገልፅ ‹‹ይህ ስም ከንጉሰ ነገስቱ ለሁለት ሰው ከንጉሱ ደግሞ ለአንድ ሰው ብቻ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ሻለቃ በዚህ ስም ሊሾም አይችልም፡፡ ስራውም ንጉሰ ነገስት በነገሰና ጉባኤ ባደረገ ጊዜ ታላቅ ማዕረግና ግርማ ያለውን ልብስ ለብሶ ግራና ቀኝ መቆም ነው፡፡ የአቃቤ ሰዓቱንም ስነ ስርዐት የሚያስከብረው እሱው ነው፡፡ በተሻረም ጊዜ ከፍ ብሎ ሲሾም ደጃዝማች ይባላል  ይላል፡፡ Kefyalew (1998)ም “Minstrels in Addis Ababa: a Study in the Social Life of Gonderian Inzatas.” በሚል ርዕስ ባደረጉት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው ‹‹ሊቀ መኳስ›› አዝማሪዎች ከሚጠሩባቸው አዝማሪ፣ አጫዋች፣ እንዛታ ከሚሉ ስሞች ውስጥ አንዱ ሲሆን የአዝማሪዎችን ክብር የሚገልፅ ስም ነው ብለዋል፡፡

በወሎ የሚገኙ መረጃ ሰጪዎችም ዛሬ ዛሬ ይቅር እንጅ ‹‹ሊቀ መኳስ›› ለአዝማሪዎች ይሰጥ የነበረ ሹመት ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሹመት በጦርነት ለተካፈለ፣ ‹‹በለው እያለ ላዋጋ›› አዝማሪ የሚሰጥ ሹመት ነው፡፡ የዚህ ሹመት ባለቤት የሆነ አዝማሪም ከባላባቱ ልጅ እስከመጋባት የሚያደርስ ክብር አለው በማለት ይናገራሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ አንድ መረጃ ሰጪ ሲገልፁ፡-

አንድ ፊታውራሪ ወይም ደጃዝማች በሚዘምትበት ጊዜ የራሱ አዝማሪ አለው፡፡ የራሱ የሆነ ሞራል ሰጪ አለው ይባላል፡፡ ያን ጊዜ አዝማሪው ሊቀመኳስ የሚባል ማዕረግ ይዞ ነው አብሮ የሚዘምተው፡፡ ይህ ማዕረግ ትልቅ ነው፡፡ የመሬት ባለቤት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ብዙ ሽልማት አለ፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ልጁን ሊድርለት ይችላል፡፡ አሁን አዝማሪ ተንቆ አዝማሪ አግብተህ እንደሚባለው ሳይሆን ከዚያ ውጪ ነው፡፡ የአዝማሪው ሹመት ከደጅ አዝማች፣ ከቀኝ አዝማች ጋር የሚስተካከል ነው (ጫኔ ወርቅነህ፣ ቃለመጠይቅ፣ 13/04/2005፣ ደሴ) ብለዋል፡፡

መረጃው እንደሚለው አዝማሪዎች በጦርነት በመሳተፋቸውና ወታደሩን እየመሩ በማዋጋታቸው የተነሳ ሊቀመኳስ የሚባል ማዕረግ ያገኛሉ ነው፡፡ ይህ ማዕረግ ትልቅ በመሆኑ የተነሳ አዝማሪውን የመሬትና የበርካታ ሽልማቶች ባለቤት እስከማድረግና ከባላባቱ ጋር በጋብቻ እስከመተሳሰር የሚያደርስ ነው፡፡

አዝማሪ በጦር ሜዳ መሳተፉ ግዴታና ከጦር ደንቦች አንዱ ጉዳይ ነው፡፡ አዝማሪው በጦር ሜዳ በመገኘት የሚከውነው ተግባር ለወታደሩ የወኔውና የጀግንነቱ ምንጪ ስለሆነ በፍፁም ሊቀር አይችልም፡፡ ይህንን ጉዳይ መረጃ ሰጪዎች ሲገልፁት ‹‹ነገስታት በመሲንቆ ያመልኩ ነበር፡፡ ወደ ጦርነት ሲወጡ አዝማሪ ሳይዙ አይወጡም፡፡ የመሲንቆ ድምፅ የጠላትን ልብ ያሸብራል፡፡ የወገንን ጦር ደግሞ ያበረታል፡፡ በዚህ የተነሳ ጥሊያን እንኳን ተሸንፏል፡፡ አሁን መሲንቆ ተናቀ፡፡ አዝማሪ ተረሳ›› (ተፈራ አበበ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005፣ ማርዬ)፡፡

እንደመረጃው አባባል አዝማሪ በጦርነት ቦታ መገኘቱ ትልቅ ትርጉም አለው ፡፡ የወገን ጦር በሚያውቀው ዜማና የሙዚቃ መሳሪያ ታጅቦ ወኔው እየጠነከረ ሞትን እየናቀ ከጠላቱ ጋር ፊት ለፊት ሲፋጠጥ ይህንን የሚያየው የጠላት ጦር ማፈግፈግና መሸሽት ይቀጥላል፡፡ ስዚህም የአዝማሪው የመሰንቆ ጨዋታ ለወገን ወታደር ስንቁ ነው፡፡ እንዲህ ለወገን ጦር ብርታት፣ ለጠላት ጦር ደግሞ ሽብር የሆነው አዝማሪው በጦር ሜዳ የሚከውነው ዜማ በሌላ ቦታ ከሚከወኑ ዜማዎች የተለየ ነው፡፡ ስሙም ‹‹ሰንጌ›› ይባላል፡፡

ይህ ግጥምም በስነግጥም ሙያዊ ቃል ‹‹ሰንጎ መገን›› የሚባለው ነው፡፡ ዜማው ከትዝታ፣ አምባሰል፣ አንቺ ሆዬና ባቲ ዜማዎች የተለየና የሚገጠሙት ግጥሞች

ምጣኔም በሃረግ አምስት ቀለም የሆነ፣ ለሌሎች ዜማዎች ከሚገጠሙ ግጥሞች ያነሰ ነው። ለምሳሌ ከግጥሞቹ ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

በለው በለኝና ላሳጣው መድረሻ
የሰው ልክ አያውቅም ባለጌና ውሻ

አባረርሃቸው በቃ ተመለስ
ማንን ይተኳል አንት ብትጨረስ

አንሄድም ወይ ጥለንላቸው
መንገዱ የእኛ ቀየው የእሳቸው

በለው በለው ሲል ነው የወንድ ልጅ ሞቱ
ሴትም ትገላለች ከረጋ መሬቱ

ከጓደኞቹ ጠዋት የተለየ
እንደአጥቢያ ኮከብ ሲነጋ ታዬ

የሚሉት ይገኙበታል። ስለዚህ አዝማሪው እነዚህንና መሰል ወኔ ቀስቃሽ ግጥሞችን ከጦሩ ፊት ሆኖ ራሱን በመሰንቆ አጅቦ ይጫወታል። ይህንን ጊዜ ፍርሃት ቦታውን እየለቀቀ ጀግንነትና ወኔ እየተተኩ ይመጣሉ። በዚህ ተግባሩ አዝማሪው ድልን ከማምጣት አንፃር ትልቅ ሚና ያለው በመሆኑ በተለይም በሁለት የሃገር ቤት ተዋጊዎች መካከል በሚደረግ ጦርነት አዝማሪውን መማረክ ለማራኪው ጦር ትልቅ ጉልበት ሲሆን ለተማረከበት ወገን ደግሞ ትልቅ ኪሳራ ነው። ይህንን የሚገልፀው መረጃ ቀጣዩን ይላል፤

አዝማሪዎች ውጊያ ሲሆን ያዘምታሉ። እንደዛሬው ኦኬስትራ የለም። እነሱ ነበሩ ሰራዊቱን የሚያበረታቱ። ሊቀመኩዋስ የሚባል ማዕረግ ነበራቸው። ራሶችና ሌሎች አለቆች ወደጦርነት ሲሄዱ አዝማሪ ይዘው ነበር። አዲያ ሁለት ወገኖች ጦርነት ሲገጥሙ አዝማሪው እንዳይማረክ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልግ ነበር። የአዝማሪ መማረክ ውርደት ነው። ምክንያቱም አዝማሪ

ብዙ ነገር ነው። የሚዲያ ሰው ስለሆነ። እሱን መማረክ ብዙ መረጃ ያስገኛል›› (መላኩ መድፉ፣ ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005፣ ደሴ) ።

መረጃው እንደሚገልፀው አዝማሪው ለወገኑ ብዙ ነገር ነው። በሙዚቃ ወኔ ከመቀስቀስ ተግባሩ የበለጠ የብዙ እውቀት ባለቤት ነው። የጌታውን አጠቃላይ አስተዳደር ሁኔታና ህዝቡ ለአስተዳዳሪው ያለውን ስሜት ሁሉ ያውቃል። አንድ ቡድን የተቃራኒውን ቡድን አዝማሪ ሲማርክ የጠላቱን የወኔና የጥንካሬ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የጦር ሚስጥር ሁሉ በእጁ አስገባ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ድልን የሚያጎናፅፈው ጉዳይ ነው። በአንፃሩ አዝማሪ ለተማረከበት ቡድን ደግሞ ኪሳራን ያመጣል። ከኪሳራው በላይ ግን አዝማሪውን አለማስማረክ የክብርም ጉዳይ ነው። አዝማሪ የተማረከበት ወገን ድል ከእጁ ከመውጣቱ በላይ በመሰንቆ ብቻ የሚዋጋውንና በእሱ ጥበቃ ስር ያለውን አዝማሪ (የጦር መሳሪያ ሳይዝ) መጠበቅ ባለመቻሉ ውርደት ይሆንበታል።

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ አዝማሪዎች ጌቶቻቸውን ተከትለው በመሄድ በጦርነት የሚሳተፉ ሲሆን በጦርነት መሳተፉ ማዕረግንና ሽልማትን ያስገኝላቸዋል። በአንፃሩ ግን አዝማሪዎች እንደማንኛውም ወታደር ሁሉ በጦርነቱ ወቅት የመቁሰልና የመሞት አጋጣሚ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ለምሳሌ የማርዬ ስላሴ አዝማሪ የነበሩት አፍራሳ ነጋሽ በሰገሌ ጦርነት ሲያዋጉ እንደሞቱ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ‹‹የእኔና የማስረሻ አባት አንድ ናቸው። በሰገሌ ጦርነት ዘምተው ነው የሞቱ ›› (ብርሃን ትኩ፣ ማስረሻ ትኩ፣ ተስፋዬ በላይ፣ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ) ሲሉ በተጠኝ ውይይት ወቅት ገልፀዋል።

የታሪክ መረጃዎች እንደሚገልፁት ሰገሌ በአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪና (አፄ ሃይለ ስላሴ ንጉስ ከመባላቸው በፊት) በንጉስ ሚካኤል መካከል ጥቅምት 16፣ በ1909ዓ.ም የተካሄደ ጦርነት ነው። በዚህ ጦርነት ከሁለቱም ወገን ብዙ ጦር ያለቀ ሲሆን የድሉ ባለቤት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ነበሩ (አለቃ ተክለ እየሱስ፣ 2002) ። በዚህ ጦርነት ሲሳተፉ አባታችን አልፈዋል ሲሉ መረጃ የሰጡት በማርዬ ስላሴ የሚኖሩ መረጃ ሰጪዎች አዝማሪዎች በጦርነት ላይ መሳተፍ ዋና ስራቸው እንደነበር የቤተሰባቸውን ታሪክ በመግለፅ አስረግጠዋል።

አዝማሪዎች በጦርነት ወቅት አብሮ ከመዝመት ሌላም በማህበረሰቡ ውስጥ ሆነው የቅስቀሳ ስራም የማከናወን ተግባርን ሲያከናውኑ የኖሩበት ጊዜ እንዳለ መረጃዎች

ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልፁት በሃይለስላሴ ዘመን በነበረው የጣሊያኖችን ወረራ አዝማሪዎች የማህበረሰቡን ወኔ በመቀስቀስ ሰው አርፎ እንዳይገዛ ይቀሰቅሱ ነበር በዚህም ጊዜ፡-

ፈረንጅ መጣ ቢሏት ደሮ ደነገጠች
መባረኪ ቀርቶ በጥምዝ አለቀች (አለምፀሃይ የማና፣ ውጫሌ)

የበቅሎ ዕቃ ጌጡ ሙካሽና ጥልፍ
ለጥቁሩ ይሆናል የነጩ መርገፍ (አለምፀሃይ የማና፣ ውጫሌ)

አንበሳው ሲሸሽ ዘራፍ ያለ ማነው
ዘወር ያለለታ አህያ መሆን ነው (ተፈራ አያሌው፣ ደሴ)

አየ ፈረንጅ ሞኙ አየ ጣሊያን ሞኙ
መድፉን መትረየሱን አንተ ብትሰራው
እንጨት እንኳ ሚያልቀው በገዛ እጀታው(ወ/ሮ አሰገ ሰኢድ፣ ደረቅ ወይራ)

የሚሉ ግጥሞችን በመግጠም ፈረንጆች ባህልና ሃይማኖትን ሊያጠፉ የመጡ እንደሆነ በመስበክ፣ አፄ ሃይለ ስላሴ ተመልሰው እንደሚመጡና አሁን ለጣሊያን መታዘዝ እንደማይፈልግ በመንገር፣ የኢትዮጵያን ወታደር ጀግንነትና አሸናፊነት በመግለፅ የህዝቡን ወኔ በማነሳሳት ህዝቡ አልገዛም ባይነት ስሜት እንዲኖረው ስነልቦናዊ ጦርነት አከናውነዋል፡፡

ይህንን የአዝማሪዎችን ሚና የተረዱ የወራሪው ጦር መሪዎችም ብዙ አዝማሪዎችን እንደገደሉ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ተስፋዬ በላይ፣ 12/05/2005 ማርዬ የዚህን ሁኔታ አስመልክቶ በቃለመጠይቅ እንደገለፁት በጣሊያን ጊዜ አርበኛ የነበሩት አያቱ ጣሊያኖች ስራዬ ብለው በያዙት ባላባትንና አዝማሪን የማጥፋት ስራ የተነሳ ተደብቀው ከሞት እንደተረፉ ‹‹እንግዲህ ጣሊያን መጥቶ እያንዳንዱን ባላባት እየያዘ እየገደለ ነበር፡፡ አዝማሪንም ባላባትንም፡፡ እያንዳንዱን አጥፋ ተብሎ ነበር፡፡ መሳሪያም እየቀማ እየገደለ ሲል የአባቴ አባት ብዙ ጊዜ ተደብቆ ነው አሉ የዳነ›› ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የጣሊያንን መምጣት የሚቃወሙና የሚታገሉ አርበኞች የመኖራቸውን ያህል ለጣሊያን ያደሩና የወሎ ህዝብ የጣሊያንን መንግስት እንዲቀበል የሚሰብኩ ግጥሞችን የሚገጥሙ ባንዳ አዝማሪዎች እንደነበሩ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ እንደዚህ አይነት አዝማሪዎች ከሚገጥሟቸው ግጥሞች ውስጥ፡-

እንዲህ ያለ መንግስት የነቃ የበቃ
አስኬደን ባስካርባ (በጫማ) እንዳይነካን ጭቃ፤

የሚለው አንዱ ነው (ወ/ሮ አለምፀሃይ የማና፣ ውጫሌ፡ ደምሴ አበበ ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005 ዓ.ም፣ጢሳ አባ ሊማ) ፡፡

እነዚህ አይነት አዝማሪዎች የጣሊያንን መንግስት ስልጣኔ በመግለፅ ህዝቡ ትግሉን እንዲያቆምና ቅኝ ግዛቱን እንዲቀበል ይሰብኩ ነበር፡፡ ይሁንና መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት በጣሊያን ጊዜ የዘፈን ስራቸውን የሚሰሩት አዝማሪዎች አንድም ከአርበኞች ጋር የወገኑት አለዚያ ደግሞ ከጣሊያን የወገኑ ባንዳዎች ናቸው እንጅ በጥቅሉ በመጠጥ ቤቶችና በተለያዩ ቦታዎች ይደረግ የነበረው የአዝማሪ ዘፈን ቆሞ ነበር፡፡ ምክንያቱም ጣሊያንም ቢሆን በአርበኞች ትግል የተነሳ ተረጋግቶ መቀመጥ ስላልቻለ ማህበረሰቡን በተረጋጋ ሁኔታ መግዛትና ማረጋጋት አልተቻለውም፡፡ ስለዚህ በዚሁ ሁኔታ ለአምስት ዓመታት ያህል በአርበኛና ባንዳ አዝማሪዎች መካከል የሚካሄደው ጦርነት እንደቀጠለ አፄ ሃይለስላሴ ወደ ሃገራቸውና ስልጣናቸው ተመለሱ፡፡ ህይወት በወሎ እንደገና የቀድሞ መልኳን መያዝ ጀመረች፡፡ ይህንን ሁኔም ለመግለፅ አዝማሪዎች ፡-

ዕድሜ ለአባ ጠቅል ለሃይለ ስላሴ

ታስራ የነበር ተፈታይ ምላሴ

(አሰጉ ሰኢድ፣ቃለመጠይቅ 16/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)

እያሉ መጫወት ጀመሩ፡፡ ይህ ግጥም ሃይለስላሴን የሚያወድስ ሲሆን እሳቸው በሃገር ባልነበሩበት ዘመን ማንም አዝማሪ ዘፈን የሚባል ሳይጫወት መቆየቱን፤ አሁን ግን እሳቸው በህይወት በመመለሳቸው የተነሳ ዘፈን መጀመራቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

አዝማሪዎቹ በዚህ ግጥም ከምስጋና ውጪም ለአፄ ሃይለስላሴ ተጨማሪ ዕድሜ ይለምናሉ፡፡ ሌላው አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑበት አውድ መጠጥ ቤት ነው፡፡

### 6.1.2.4.5. መጠጥ ቤቶች

የወሎ አዝማሪዎች ዘፈንን በጠላ፣ በአረቄና በጠጅ ቤቶች ሲከውኑ ኖረዋል፡፡ ባለመጠጥ ቤቶች የአዝማሪን ዘፈን ለመጠጥ ማሻሻጫነት ይጠቀሙበታል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ይህ ጉዳይ ጥንታዊ ልማድ ሲሆን አሁንም ቢሆን በአንዳንድ ቦታዎች አለ፡፡ አዝማሪዎች በመጠጥ ቤቶች ለሚከውኑት ክዋኔ ከመጠጥ ቤቱ ባለቤት ጋር የሚያደርጉት የክፍያ ስምምነት አለ፡፡ ይህ ስምምነት ቀደም ሲል ከሃምሳ ሳንቲም የሚጀምር ሲሆን ዛሬ እስከ አስርና አስራ አምስት ብር ድረስ ደርሷል፡፡ ይህ የመጠጥ ቤቱ ባለቤት ለአዝማሪው በቀን የምትከፍለው ክፍያ ሲሆን አዝማሪው ከጠጪዎች የሚያገኘው ሽልማት የራሱ ነው፡፡ የመጠጥ ግብዣ ከጠጪዎች ካላገኘም የመጠጥ ፍጆታው በመጠጥ ቤቱ ባለቤት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

መጠጥ ቤቶች የአዝማሪዎች ዋና የስራ ቦታ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለእለት ከመቀጠር አንስቶ ‹‹ኩንትራት›› እስከ መዋዋል በደረሰ ስምምነት ዘፈን በመጠጥ ቤት ይከውናሉ፡፡ ለምሳሌ በአንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲሰራ መኖሩን የገለፀ አንድ አዝማሪ ሃሳቡን በዚህ መልኩ ነው ያብራራው፡፡

> ድሮ ገና ከጠላ ጀምሮ ኩንትራት ይዘውኝ የነበሩ የነአባይ ቤተሰቦች ነበሩ፡፡ እዚህ ማለት ነው፡፡ ድሮ ጠላ በስልሳ ሳንቲም ይሸጡ በነበረ ጊዜ፤ የዛን ጊዜ አምስት ብር ትልቅ ብር ናት፡፡ በአምስት ብር ያዙኝ፡፡ ስል አስራ አምስት፣ስል ሃያ ብር ገባሁ፤ ጠጁም እያደገ ሄደ፡፡ እስከ ሃያ አምስት ብር እየከፈሉኝ ስጫወት እንደፈለግሁኝ እየጠጣሁ፤ አቅሙ በፈቀደው መጠን እንደዛ እያልን ኑረናል እስታሁን (መላኩ ካሳው፣ ቃለመጠይቅ፣ 20/04/2005፣ ማርዬ)፡፡

አዝማሪዎች በመጠጥ ቤት የሚያደርጉትን ክዋኔ ከወሎ ውጪ ወደሌሎች አካባቢዎች በመንዝ ጭምር ይከውኑታል፡፡ ለምሳሌ በነገሌ ቦረና፣ በጨንቻ፣ አርሲ ወዘተ

የሚዘዋወሩ ሲሆን በተለይ ግን በዋናነት አዝማሪዎቹ ለስራ ከሚሄዱባቸው ቦታዎች ውስጥ አዲስ አበባ አንዱ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም በጠላና በጠጅ ቤቶች በመዘዋወር የዘፈን ስራቸውን ይሰራሉ፡፡ ከዚያም ሲኖሩ አንዳንድ አዝማሪዎች በቋሚ ደንበኝነት የሚሰሩባቸው ጠጅና ጠላ ቤቶች ሲኖሯቸው ሌሎች ደግሞ ፈላጊ መጥቶ እስኪጠራቸው ድረስ አንድ ቦታ ተቀምጠው ይጠብቃሉ፡፡

በቋሚ ደንበኛነት ይሰሩ ከነበሩ አዝማሪዎች ውስጥ የህይወት ልምዳቸውን የገለፁ አራጌ ይማም የተባሉ አዝማሪ ‹‹ቅዳሜና እሁድ ሶስት ብር፣ በአዘቦት ሁለት ብር፡፡ ሽልማት የራሴ ነው፣ መጠጥ ሰው ከጋበዘኝ ጋበዘኝ ካልጋበዘኝ በእስዋ ነው›› (ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005 ዓ.ም፣ ደሴ) ሲሉ በ1954 ዓ.ም አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ በአዝማሪነት በሚሰሩበት ጊዜ ቋሚ ባለጠጅ ቤት አሰሪ ደንበኛ እንደነበረቻቸውና በዚያ ቦታም ከሽልማት ውጭ በስራ ቀናት ሁለት ብር ቅዳሜና እሁድ ደግሞ ሶስት ብር እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጠጪው ከጋበዛቸው ጋበዛቸው ያ ካልሆነ ደግሞ አዝማሪው የፈለገውን ያህል መጠጥ በባለቤቷ ወጪ የሚጠጣ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህም አዝማሪው በመጠጥ ቤት መገኘቱ ለመጠጥ ማሻሻጫ እስከሆነ ድረስ ጠጪ በሚዛባቸው የእረፍት ቀናት የአዝማሪው ክፍያ ከፍ እንደሚል በሌሎች ቀናት ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

አዝማሪዎች መጠጥ ቤት ውስጥ ለመስራት ወደ ተለያዩ ቦታዎች የሚሄዱት በቡድን እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ ቡድን አስቀድሞ የተደራጀ ወይም ደግሞ በድንገት የሚፈጠር ሊሆን ይችላል፡፡ ቡድኑ በድንገት የሚፈጠረው ከተለያየ ቦታ የመጡ አዝማሪዎች በስራ ቦታው ሲገናኙ ሲሆን አስቀድሞ የሚደራጀው ቡድን ደግሞ የአንድ አካባቢ አዝማሪዎች ገና ከቀያቸው ሲነሱ የሚመሰርቱት ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ከተገኙ መረጃዎች ውስጥ ቀጣዩ ጉዳዩን በሚገባ ይገልፃል፡-

> አዲስ አበባ ትንቀመጥ መጀን ጠጅ ቤት የሚባል ነበር፡፡ እዚያ እንሰበሰብና ዙሪያውን መሰንቆ ይሰቀላል፡፡ የምትወስድሽ ሴትዮ ትመጣለች፡፡ አንዱ መሰንቆ ያነሳል፡፡ እስቲ አንቺ ሞክሪ ትልሻለች፡፡ የዚያን ጊዜ ነጭ ሽልንግ ነው በሰሃን እየተሰፈረ ነው፡፡ እሱን ይዛ ትመጣና ተራውን ሴቶች ይቀመጣሉ፡፡ እንዘፍናለን፡፡ እስቲ አንቺ ሞክሪ ትላለይ፡፡ ጭራውን ይመታል፡፡ እስዋ ትመለከታለች፡፡ ሚስትህ የታለች ትላለይ፡፡ ዝፈኝ ትላታለይ፡፡ የእስዋ ድምጥ ካላማረ አትቀጠርም፡፡ የእስዋ ድምጥ እያማረ

> የእሱ ጭራ ታላማረ አይቀጠርም፡፡ ያም ይህም ይፈተናሉ፡፡ ከዚያ የሚያምር ጭራ ያለውንና የሚያምር ድምጥ ያላትን እፈልጋለሁ ትላለይ፡፡ ሞኝ ተደግ አይሄድም እንዴ ወንድዬው ሞኝ ቢሆን ሴቲቱ ጥሩ ናት ውሰጅ ቲሿት፣ እንቢ ትላለይ፡፡ በሉ አይቅርብን ሂዱ ይባላል፡፡ ያንን ሽልንጎን ከፍላ ይዛ ትሄዳለይ፡፡ ሞኙም እንዳቅሙ ሂዶ ይውላል፡፡ ዙሮ ዙሮ ሁላችንም የሰራነው ከአንድ ላይ ተሰብስቦ እኩል ነው ምንካፈለው፡፡ እኔ ሺ ብር ባገኝ ሌላው አንድ ብር ቢያገኝ አላካፍልም የለም፡፡ እኩል ነው የምንካፈል፡፡ መጀመሪያውኑ መሃላ ስላለ አንካካድም፡፡ ጭራ በጥሱ ይባላል፡፡ (አለም ፀሃይ የማና፣ ቃለመጠይቅ፣ 18/04/2005 ዓ.ም፣ ውጫሌ)

መረጃው እንደሚለው በዘመኑ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ቦታዎች እየተዘዋወሩ የሚሰሩ አዝማሪዎች በቡድን ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ይህ የቡድን እንቅስቃሴም ከአንድ ቦታ ተሰብስቦ ከመኖር አንስቶ በስራ የሚያገኙትን ገቢ እስከመከፋፈል የሚደርስ ነው፡፡ ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው የአኗኗር ሁኔታቸው ማህበራዊ ነው፡፡ ይህ ማህበራዊነት አብሮ በመስራት፣ አብሮ በመብላት፣ ደካማውን ጠንካራው የሚደግፈው በመሆኑ የሚገለፅ ነው፡፡ ቡድኑ በትልቁ ማህበረሰብ ውስጥ እዚህ ግባ የማይባል ቁጥር ባላቸው አባላት የተገነባ እንደመሆኑ ትልቁ ማህበረሰብ በሚያደርሰው ተፅዕኖ የተነሳ ላለመጥፋት በቡድኑ መካከል ያለው ማህበራዊ ትስስር ዋስትና ነው፡፡ ይህ ዋስትና ዘላቂ እንዲሆንም መሐላው ትልቅ ማሰሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ አዝማሪዎች ዛሬም ቢሆን ዘፈንን በመጠጥ ቤት የሚከውኑ ሲሆን የአከዋወን መልኩ ግን ቀደም ከነበረው ሁኔታ የተለወጠ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ ለውጥ በሚለው ክፍል የሚነሳ በመሆኑ እዚህ ማንሳት አስፈላጊ አልሆነምና ቀጥሎ ሌሎች አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑባቸው አውዶች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ አውዶች ውስጥ አንዱ የታቦት ንግስ ነው፡፡



ስዕል 8. አዝማሪዎች በመጠጥ ቤት፣ ኢላዳ



ስዕል 9.  አዝማሪዎች በመጠጥ ቤት፣ ማርዬ

## 6.1.2.4.6. የታቦት ንግስ

‹‹ታቦት ሙሴ ከፈጣሪ የተቀበላቸውን አስርቱ ትዕዛዛት የተፃፉበት፣ የክርስትና እምነት ተከታዮች ለእምነታቸው የማዕዘን ድንጋይና የእግዚአብሔር ሃይልና ክብር መገለጫ አድርገው የሚቆጥሩት ክቡር ንዋየ ቅዱስ ነው›› (Hancock: 1992, 125) ፡፡ የክርስትና

እምነት ተከታዮች በዓመታዊ ክብረ በዓላትና በጥምቀት በዓል ታቦትን ከቤተክርስቲያን ውስጥ አውጥተው፣ በታላቅ ክብርና ምስጋና አጅበው የቤተክርስቲያን ቅፅርን በመዞር አለዚያ ደግሞ በተዘጋጀ ንፁህ ቦታ በማስቀመጥ አምልኮ ይፈፅማሉ፡፡

ታቦት ከቦታው ተነስቶ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ማንም ምዕመን በአቅሙና በችሎታው ደረጃ አምላክን ማመስገን የሚጠበቅበት በመሆኑ በእነዚህ አውዶች ብዙ አይነት ዝማሬዎች ይከናወናሉ፡፡ ከሚከናወኑ ዝማሬዎች ውስጥ የአዝማሪ ዝማሬ እጅግ የተለመደው ነው፡፡ ለዚህ ዝማሬ መነሻ ምክንያቱ ምናልባት በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የተጠቀሱ የእስራኤላውያን በቃልኪዳኑ ታቦት ፊት ያደርጓቸው የነበሩ የአምልኮ ስርኣቶች ናቸው (2ኛ ሳሙ፡ 6፣5፤ 2ኛ ሳሙ፡ 6፣14፤ 2ኛ ዜና መዋ.35፣25)፡፡ በጥቅሶች እንደተገለፀው እስራኤላውያን የዜማ ባለሙያዎች ታቦቱ ከቦታ ቦታ በተንቀሳቀሰ ጊዜ ሁሉ ከታቦቱ ፊት በመቆም በዜማ አምላክን ያመሰግናሉ፡፡ አዝማሪዎችም በየት መጣ ትረካቸው ከዚህ ልምድ ጋር ትስስር አለን ሲሉ የሚገልፁ እንደመሆናቸው በታቦት ፊት ቆመው ለአምላክ ምስጋናን ያቀርባሉ፡፡

ይህ ቦታ መንፈሳዊ ቦታ በመሆኑ የተነሳ አዝማሪዎች ታቦቱን የሚያጅቡት በመንፈሳዊ ዜማ ነው፡፡ ዜማዎችን ያለ ሰው ድምፅ በመሰንቆ ብቻ እየተጫወቱ ታቦቱን ከተሸከመው ቄስፊት ፊት ይጓዛሉ፡፡ ይህንን መረጃ ሰጪው ‹‹ከታቦቱ ቀጥለን የምንቆም እኛ ነን፡፡ እንኳን ሌላ ቀርቶ ቅጭል ቅጭል የሚያደርጉት እንኳን ከእኛ ኋላ ናቸው›› ሲሉ ገልፀውታል (ብርሃን ትኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም.፣ ውጫሌ) ፡፡ ሁኔታው በምልከታም ተረጋግጧል፡፡

አዝማሪዎች በቀጥታ ከታቦቱ አጠገብ የመቆማቸው ምክንያት ከዜማዎቹ ባህርይ ጋር የተያያዘ ይመስላል፡፡ ማለትም ከላይ እንደተገለፀው ዜማዎቹ ለአምላክ ምስጋና ማቅረቢያ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ዜማዎችን በቀጥታ ከታቦት አጠገብ ሆኖ መጫወት በትክክለኛ ቦታ ላይ መገኘት ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ይህም ልማድ ጥንታዊነት ያለው መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ ቀዳማዊ ሚኒሊክ ታቦተ ፅዮንን ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ይዞ ሲገባ ዜማ ተጫዋቾቹ ከታቦቷ ቀድመው ይጓዙ እንደነበር ኤልያስ (2005፣ 72) ‹‹ቀዳማዊ ምኒሊክ ታቦተ ፅዮንን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ከእርሱ ጋር የመጡት . . . ገሚሶች የታቦተ ፅዮን ባለወጎች ማለትም ጅራፍን እያስጮሁ፣ መለከት፣ እምቢልታን፣ ቱልቱላንና ዋሽንትን እየነፉ መሰንቆ እየመቱና በገናን እየደረደሩ ታቦተ ፅዮን ስትንቀሳቀስ በፊት ለፊት የሚሄዱ ነበሩባቸው›› ሲሉ ፅፈዋል፡፡ በዚህ መሰረት አዝማሪዎች ቀደምት ልምዳችን የሚሉትን እምነታቸውን

መሰረት አድርገው ጥምቀትን ጨምሮ ታቦት በሚወጣባቸው ዓመታዊ ክብረ በዓላት ሁሉ ከታቦቱ ፊት ለፊት በመንዝ መዲናና ዘለሰኛን እየከወኑ ታቦት ያጅባሉ፡፡ መዲናና ዘለሰኛ የሚከወኑበት ሌላው አውድ ደግሞ ተዝካር ነው፡፡



ስዕል 10. አዝማሪዎች ታቦት ሲመሩ፣ ማርዬ

## 6.1.2.4.7. ተዝካር

ተዝካር አንድ ሰው በሞት ሲለይ ለሞተው ሰው መታሰቢያ የሚዘጋጅ ድግስ ነው፡፡ ድግሱ ለሞተ ሰው መታሰቢያ የሚዘጋጅ እንደመሆኑ ስርዓቱ የምግብ ግብዣ ቢኖረውም ዘፈንን የመሰለ ደስታና ፈንጠዝያ አይደረግበትም፡፡ ያም ሆኖ አዝማሪዎች መሰንቋቸውን ይዘው በተዝካር ላይ ይገኛሉ፡፡ እንዲህ ያለው ልምድ በተለይ ሰሜን ወሎ ውስጥ በሚገኙ ቦታዎች የሚገኝ ሲሆን አዝማሪዎች በተዝካር ቤት በመገኘት መዲናና ዘለሰኛ ዜማዎችን ይጫወታሉ፡፡ በተለይም ዘለሰኛ በተባለው ዜማ የሚቀርቡ ግጥሞች የሰውን ከንቱነት፣ የሞትን አይቀሬነት የመሳሰሉ ምግባራዊ ይዘቶች ያሏቸው ናቸው፡፡ ግጥሞቹ የሚቀርቡባቸው ዜማዎች ሃዘንን የመጥራት አቅም ያላቸው በመሆኑ በተዝካር ላይ ለመከወን ችለዋል፡፡ ምክንያም ተዝካር ለሞተ ሰው መታሰቢያ የሚዘጋጅ ድግስ በመሆኑ የሃዘን ስሜት ያለበት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ አቶ መኮንን ፀጋዬ የተባሉ መረጃ ሰጪ ሲገልፁ፡- ‹‹በዚህ በእኛ አዝማሪዎች በተዝካር ይዘፍናሉ፡፡

ዘፈኑ መዲና ዘለሰኛ ነው፡፡ ወንዱ መሰንቆውን እየመታ ስለአምላክ፣ ስለሚቱ፣ በመንደሩ ስለሞቱ ሌሎች ሰዎች ይተርታል፡፡ መዲናና ዘለሰኛ የወንዱ ዘፈን ስለሆነ ሴቷ ዝም ብላ ነው የምትበላ የምትጠጣ፡፡ አትዘፍንም፡፡ ግን በተዝካር አዝማሪ ማምጣት ደንብ ነው ›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ 01/08/2005፣መቂት)፡፡

መረጃው ተዝካር የአዝማሪዎች የዘፈን መከወኛ አውድ እንደሆነና ዘፈኑን የሚከውኑት ግን ወንዶች እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ይህም ዘለሰኛ በአንድ ሰው ለዚያውም በወንዶች ብቻ የሚከወን የሙዚቃ አይነት ስለሆነ ነው፡፡ መዲናና ዘለሰኛን መነሻ በማድረግ ሌሎች ዘፈኖችም የሚከወኑበት ሌላው የአዝማሪዎች የዘፈን መከወኛ አውድ ሰርግ ነው፡፡ የሰርግ አውድ ገፅታ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

## 6.1.2.4.8. ሰርግ

ሰርግ የወሎ ማህበረሰብ ከሚከውናቸው ታላላቅ ማህበራዊ በዓላት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በምግብ ድግስና በዘፈን ታጅቦ ይከወናል፡፡ አዝማሪዎች በሰርግ ላይ ለሚደረግ የዘፈን ክዋኔ ዋና ዘፈን ከዋኞች ናቸው፡፡ አዝማሪዎች ከባለሰርገኞች ጋር ‹‹ይህንን ያህል እከፍልሃለሁ ወይም እከፍላችኋለሁ›› በሚል የቅድሚያ ውል አለዚያ ደግሞ ራሳቸው ሰርጉ ያለበትን ቦታ ፈልጎ በማግኘት በሰርግ ቤት ይገኛሉ፡፡ አስቀድመው በተደረገ ውል መሰረት ወደ ሰርግ በሚሄዱበት ጊዜ የሚከፈላቸው ክፍያ እንደ የዘመኑ የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ መረጃ ሰጪዎች ድሮ ሲሉ በሚጠሩት በሃይለስላሴ ዘመን አንድ ብርም ሁለት ብርም የሚሰጣቸው ሲሆን ቀስ በቀስ ግን ይህ ክፍያ መጠኑን እየጨመረ ዛሬ በገጠሩ አካባቢ እስከሙቶ ብር በከተማ ደግሞ ስምንት መቶ ብር ደርሷል፡፡ ይህ ክፍያ ማንኛውም የሰርግ ታዳሚ በጨዋታው ተደስቶ የሚሰጠውን ሽልማት አይጨምርም፡፡ መጀመሪያ ውል ሳይኖራቸው ሰርግ መኖሩን ብቻ ተመልክተው ወደ ሰርግ ቤት የሚሄዱ አዝማሪዎች ደግሞ ከሰርጉ የሚያገኙት ገቢ ሽልማት ብቻ ነው፡፡

ሰርግ በውል ለሚሄዱትም ሆነ በራሳቸው ጊዜ ለሚሄዱት አዝማሪዎች ጥሩ ገቢ ማግኛ ቦታ ነው፡፡ ያም ሆኖ በራሳቸው ፈቃድ ሰርግ ፈልገው ከሚሄዱት ይልቅ ተጠርተው የሚሄዱ ሰዎች የተሻለ ክብር አላቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ይመስላል መረጃ የሰጡ ብዙ አዝማሪዎች ስለሰርግ ክዋኔ ሲጠየቁ ‹‹እኔ ተጠርቼ ካልሆነ በስተቀር ራሴ ሰርግ ፈልጌ ሄጄ አላውቅም›› የሚል መልስ ይሰጣሉ፡፡ ይህንን የሚሉበት ምክንያት ሙያቸው ተፈላጊ እነሱም ክብር ያላቸው መሆኑን ለመግለፅ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ይህንን አባባል

የሚቀጥለው መረጃ ያጠናክረዋል፡- ‹‹ ስታስቢው ተጠርቶ የሄደ ነው ወይስ በራሱ ጊዜ የሄደ ሰው የሚከበር? በራሱ እግር የሄደ ሰው እኮ ልመና የሄደ ማለት ነው፡፡ ተጠርቶ የሄደ ሰው ሁሉ ነገር ተሰናድቶ ይጠብቀዋል፡፡ በራሱ እግር የሄደ ግን ብዙ አዝማሪ ቀድሞት ሄዶ ቦታ ይጠብና ከዳሱ ሳይገባ ሊመለስ ይችላል›› (አበባው ሙሉጌታ፣ ቃለመጠይቅ፣ 09/05/2005፣ ውጫሌ)፡፡ ከመረጃው ማየት እንደሚቻለው ተጠርቶ በመሄድና ሳይጠሩ በመሄድ መካከል ያለው ልዩነት የክብር ጉዳይ ነው፡፡ ተጠርቶ የሄደው በራሱ ጊዜ ከሄደው አዝማሪ የተሻለ ክብር አለው፡፡ ያም ሆኖ በውል የሄዱትም ሆኑ በራሳቸው ጊዜ የሄዱት አዝማሪዎች በሰርግ ቤቱ ውስጥ እስከተገኙ ድረስ አትግባ አይባሉም፡፡ ቁጥራቸው ምንም ያህል ይሁን ወደ ሰርግ ቤቱ ገብተው የየራሳቸውን ጨዋታ ይጫወታሉ፡፡ አንዳንዴ ተራ እየጠበቁ አንዱ ከተጫወተ በኋላ ሌላው በመቀጠል ሰርገኛውን የሚያጫውቱ ሲሆን ሌላ ጊዜ ግን ሁሉም በተለያየ አቅጣጫ በመቆም ይዘፍናሉ፡፡ ለምሳሌ ጥር አስራ ዘጠኝ 2005 ዓ.ም. ለጋምቦ ወረዳ፣ አቀስታ ከተማ በሰርግ ቤት ውስጥ በተደረገ ምልከታ ሁለት ወንድና አንድ ሴት በአጠቃላይ ሶስት አዝማሪዎች ዘፈንን ይከውኑ ነበር፡፡ ሴቷና ወንዱ አዝማሪ የዳሱን አንድ አቅጣጫ ይዘው አንድ ላይ ሆነው እየተቀባበሉ ይዘፍናሉ፡፡ አንዱ አዝማሪ ደግሞ በዳሱ ሌላኛው አቅጣጫ በመሆን ለብቻው ይዘፍናል፡፡ በዳሱ ውስጥ በርካታ ሰዎች ቢኖሩም ሁሉም ሰዎች ተደርድረው ተቀምጠው የተወሰኑት ምግብ ይበላሉ፤ ሌሎች ደግሞ ጠላ ይጠጣሉ፡፡ ዘፈን የሚዘፍኑ አዝማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ሰው ፊት እየዞሩ ስም እየጠሩ ያወድሳሉ፡፡ ስሙ ተጠርቶ የሚወደሰው ሰው ለአዝማሪዎች ብር ይሰጣል፡፡ ግጥም የሚያቀብሉም አሉ፡፡ በክዋኔው መሃልና በኋላ ከአዝማሪዎቹ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ አዝማሪዎቹ እዚሁ ወረዳ ውስጥ ከሚገኘው በረከት የተባለ የአዝማሪ መንደር እንደመጡና በዚህ አካባቢ በሚደገሱ ድግሶች ምንጊዜም ቢሆን በውልም ሆነ በሽልማት የዚያ መንደር ነዋሪ የሆኑ አዝማሪዎች እንደሚዘፍኑ፣ እነሱ ግን ያለ ውል ሰርግ መኖሩን በማወቃቸው ብቻ እዚህ መጥተው እየዘፈኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ከሽልማት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ቀደም ባለው ጊዜ ታዳሚ ለአዝማሪዎች የሚሰጠውን ሽልማት የሚያስቀምጥበት ሰሃን በየሰው ፊት ይዞር ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በአዝማሪው ወይም በአዝማሪዋ ግንባር ላይ ይለጠፋል፡፡ አለዚያ ደግሞ በእጅ ይሰጣል፡፡ አዝማሪዎችም የዘፈን ክዋኔያቸውን ከጨረሱ በኋላ የተገኘውን ገቢ እኩል ተካፍለው ወደየአቅጣጫቸው ይበታተናሉ፡፡

አዝማሪዎች ‹‹የዳስ ደንብ›› ተብሎ በሚጠራ ስርዓት ከሰርግ የሚያገኙት ገቢም አለ፡፡ የዳስ ደንብ አንድ ሰርግ ሰራጊ ሰው አዝማሪዎች በሰርጉ ስለተገኙ ብቻ የሚሰጠው ክፍያ ነው፡፡ የክፍያው መጠን እንደሰጪው ፍላጎት የሚወሰን ሲሆን አዝማሪው በደንብ ሰራም አልሰራ ደንብ ስለሆነ ብቻ የሚደረግ ነው፡፡ ዛሬ ላይ ሰርጋቸውን በመንፈሳዊ ዜማ ብቻ በሚከውኑ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ እንኳ አዝማሪ የጥንቱ ደንብ እንዳይቀር በሚል ‹‹የዳስ ደንብ›› ገንዘብ ይሰጣሉ፡፡

አዝማሪዎች በሰርግ ቤት ሲገኙ ዘፈንን የሚጀምሩ በዘለሰኛ ነው፡፡ እነዚህ ዜማዎች ምግብ ተበልቶ እስኪያበቃ ሲከወኑ ይቆያሉ፡፡ ሌሎች ዘፈኖች የሚዘፈኑት የምግብ ስርዓቱ ካለቀ በኋላ ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት እነዚህን ዜማዎች የማያውቅ አዝማሪ ሰርግ ቤት አይሄድም፡፡ ይህንን ሃሳብ ብርሃን ትኩ ሲገልፁት፡-

> የሚባለው መዲና ሌይሌይ (ዘለሰኛ) ነው ብዬሻለሁ፡፡ ግብር ቀርቦ ሲበላ እሱ ነው የሚባል፡፡ አንቺ ሴት ወይዘሮ ሁነሽ ቤተ መንግስት ገብተሽ ግብር ስትበይ ከፊትሽ የምንቆም እኛ ነን፡፡ ቡድንነት የለብን፡፡ ስትትጎርሽ ዝም ብሎ ግጥም መግጠም ነው፡፡ ግብር የምታበይበትን ግጥም ይገጠማል፡፡ አንቺ ሴት ወይዘሮ ሁነሽ ድግስ ትደግሻለሽ፤ ድግስሽ ይወደሳል፡፡ የተጠሩት ከገቡ በላይ እኛ እንገባለን፡፡ እስኪበላ መዲና ዘለሰኛ እንጫወታለን፡፡ ሞሰብ ሲነሳ ቡናና እርጥብ ስጋ ይቀርባል፡፡ እያመሰገንን በልተን እንወጣለን፡፡ ታዲያ ይኸ ድሮ ክብር በነበረው ጊዜ ነው (ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም) ይላሉ፡፡

መረጃው እንደሚለው አዝማሪዎች ምግብ እስኪቀርብና ምግብ በሚበላበት ጊዜ እነዚህን ጩኸትና ጭብጨባ የማይፈልጉ ዜማዎች ይጫወታሉ፡፡ ታዳሚውም ዜማዎችን እያደመጠ ምግብ ይመገባል፡፡ ታዳሚው ምግብ በልቶ ካበቃ በኋላ ደግሞ ለእነሱ የተዘጋጀላቸው ምግብ ይቀርብላቸውና ይመገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ከመዲናና ዘለሰኛ ውጪ የሆኑ ሞቅ ያለ ዜማ ያላቸውን ዘፈኖች በመጫወት ሰርጉን ያደምቃሉ፡፡

አዝማሪ ያልሆኑ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ሰርግ ከምንም በላይ አዝማሪዎች የሚፈለጉበት ቦታ ነው፡፡ በአንድ ሰርግ ላይ አዝማሪ ከሌለ ‹‹ሰርግ ቤቱ ሰርግ ቤት መሆኑ ቀርቶ ሃዘን ቤት ይመስላል›› ምክንያቱም ሰርግ ቤት በባህርይው ዘፈንና ሞቅ ሞቅ ያለ ድባብ ይፈልጋል፡፡ ይህን ድባብ ለመፍጠር የአዝማሪዎች አስተዋፅኦ ከፍተኛ

ነው፡፡ በአንፃሩ የአዝማሪ አለመኖር የሰርጉን ድባብ ያቀዘቅዘዋል፡፡ በተለያዩ የጥናት ቦታዎች በምልከታ የተረጋገጠውም ይኸው ነው፡፡

> ለምሳሌ ቀለባስ ክትክታ መንደር በአንድ ቤት ውስጥ ሰርግ እየተካሄደ ነው፡፡ ከዚህ ቤት በሞትና ህይወት መካከል የሆነ በሽተኛ ተኝቷል፡፡ በሽተኛው የሙሽራዋ ወንድም ነው፡፡ ነገር ግን ሰርጉ አስቀድሞ ቀጠሮ ተይዞለት ስለነበር ለመተው አልተቻለም፡፡ ሰርገኞች በሃዘንና ደስታ በሁለት ስሜት ውስጥ ሆነው ሰርጉን ያካሂዳሉ፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን ስሜታቸው ወደሃዘን ቢያደላም ሰርግ ያለአዝማሪ የማይታሰብ በመሆኑ ሌሊቱን በሙሉ እየተፈራረቁ የሚዘፍኑ አዝማሪዎች ነበሩ (ምልከታ፣ 28/07/2005 ቀለባስ ክትክታ መንደር) ፡፡

ዛሬም ቢሆን ዘመን ተለውጦና የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሳሪያዎች የአዝማሪን ስራ እየተኩ ባሉበት ወቅት እንኳን በሰርግ ቤት አዝማሪ የግድ ይፈለጋል፡፡ ደሴን በመሰሉ ከተማዎች ውስጥ በሚደረጉ ሰርጎች ሌላውን ሰዓት በሙሉ ዳሱን ሲያደምቁ የነበሩ ቴፕሪከርደርና የሙዚቃ ባንድ ‹‹ሙሽራ ከቤት ሲወጣ›› በሚባለው ሰዓት በአዝማሪ ዘፈን ይተካሉ፡፡ በዚህ ሰዓት አዝማሪ መዝፈኑ እንደባህል የሚታይ በመሆኑ ዛሬም ቢሆን የአዝማሪዎች በሰርግ ቤት መዝፈን እንደተፈለገ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ አዝማሪዎች በሰርግ ቤት ሲገኙ የተለየ ክብርና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ ሌሎች ከሰርግ ጋር ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑባቸው አውዶች ዓመታዊ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የሚደገሱ ድግሶች ናቸው፡፡



ስዕል 11. ሴትና ወንድ አዝማሪዎች፣ኢላዳ



ስዕል 12. አዝማሪው በሰርግ ቤት፣ ኢላዳ

## 6.1.2.4.9.ድግሶች

ወሎ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነ ማህበረሰብ የሚኖርበት አካባቢ መሆኑ በአካባቢ ገለፃ ወቅት ተነግሯል፡፡ ይህ በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ እንደሚከተለው የእምነት አይነት እምነቱ የሚያዝዛቸውንና እምነቱን ጠገግ አድርገው የተመሰረቱ ልማዳዊ ድርጊቶችን ሲከውን ኖሯል፡፡ በመከወን ላይም ነው፡፡ በዚህ

መሰረትም በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ የክርስትና እምነት ተከታዮች ‹‹የፃድቃንንና ፣ ሰማዕታትን ስም ለማክበር ሲሉ›› በፃድቃንና ሰማዕታት ስም ዓመታዊ ድግሶችን ይደግሳሉ፡፡ እነዚህን ድግሶች ከሩቅ ሃገር ዘመዶችን፤ ከቅርብ ደግሞ ጎረቤቶችን በመጥራት፤ ምግብና መጠጥ አዘጋጅተው በመጋበዝ ያከብራሉ፡፡ በእነዚህ አይነት ድግሶች አዝማሪዎች መሳተፋቸው የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲመጡ ተጋብዘው አለዚያ ደግሞ ራሳቸው ድግስ መኖሩን በማወቃቸው ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በምንም አይነት ምክንያት ይምጡ አትግቡ ተብለው አይከለከሉም፡፡ በቤቱ ውስጥ ለእንግዳ ከተዘጋጀው መብል መጠጥ እየተካፈሉ፣ ባለድግስ ቤቶችንና የድግሱን ተሳታፊዎች እያወደሱ በዓሉን በማድመቅ ይሰነብታሉ፡፡ በዚህ ድግስም ከመብልና መጠጥ አንስቶ የሽልማት ገንዘብ እስከ ማግኘት ይደርሳሉ፡፡ በድግስ ቤቶች የሚደረግ የዘፈን ክዋኔ አይነትም በመዲናና ዘለሰኛ ተጀምሮ ሞቅ ያሉና የሚያስጨፍሩ ዜማዎችን እስከመጫወት የሚደርስ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀጣዩ ልምድ ታይቷል፡፡

> በማርዬ ስላሴ የጥምቀትን በዓል ምክንያት አድርጎ በአንድ ቤት በተዘጋጀ ድግስ አቶ ሙሉጌታ አበበ የተባሉ አዝማሪ ድግስ መኖሩን በመስማት ብቻ ወደ ድግስ ቤቱ ገብተው እየተጋበዙ ደጋሾችንና ታዳሚውን በማወደስ ድግሱን ሲያደምቁ ለማየት ተችሏል፡፡ በተደረገላቸው ቃለመጠይቅ ይህ የቆዬ ልማድ እንደሆነና ሌሎችም እንደዚህ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል (ምልከታ፣ 11/05/2005ዓ.ም.፣ ማርዬ) ፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን Batt-Rawden (2007) በብዙ ሃገሮች ሙዚቃ በህይወት ውስጥ ዋና ነገር ነው፡፡ የተለያዩ ጠቃሚ የሆኑ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ሚናዎችን ይጫወታል ሲሉ እንደሚገልፁት እስካሁን የቀረቡ መረጃዎች፣ የወሎ አዝማሪዎች ዘፈንን ከቤተ መንግስት ግብር እስከተራው ህዝብ መኖሪያ መንደር፣ ከቤተክህነት የታቦት ንግስ እስከ አለማዊው ሰርግ፣ ከድግስ እስከ አዘቦት ቀን፣ ከጦርነት እስከ ሰላማዊ ቀን ለምሳሌ መጠጥ ቤቶች ውስጥ ሲከውኑ መኖራቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህም የአዝማሪዎች ዘፈን በማህበረሰቡ ሁለንተናዊ የህይወት ክንውን ውስጥ አንድ አካል ሆኖ የራሱን ሚና በመጫወት በግብር ሃይማኖትና ስነምግባር የመስበክ፣ ሂስ የመስጠት፣ በታቦት ንግስ ሃይማኖትን የመስበክ፣ በሰርግ በጎ እሴትን በመትከል፣ በመንደሮች የአኗኗር ብልሃትን የመጠቆም፣ በጦርነት ወታደሩን የማበረታታት፣

ተግባር ሲያከናውን መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ክዋኔን አስመልክቶ Kapchan (1995, 479) ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህሪ፣ በአካል የሚከወን፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈፀም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ ነው ሲሉ የሰጡትን ሃሳብ የሚያረጋግጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 6.2. በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ባህል ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች

ለውጥ የሚለው ቃል በነበረው ተጨባጭ ሁነት ላይ ጊዜ የፈጠራቸው ማሻሻያዎች፣ መተኪያዎችና ሁነቶች መፈጠራቸውን የሚያሳይ ፅንሰ ሃሳብ እንደሆነ ፀሃፍት ይገልፃሉ፡፡ ይህ የለውጥ ትርጓሜ በፎክሎር እሳቤ ውስጥ ቦታ አለው፡፡ Toelken (1996) ተከታታይነትና ተለዋጭነት የፎክሎር ሂደት መንታ ህጎች ናቸው ሲሉ እንደሚገልፁት የወሎ አዝማሪዎች የአዝማሪነት ልማድ በተከታታይነት (አይለወጤ) ባህርይው ቡድኑ በርካታ ጉዳዮችን ሲጋራበት ቢኖርም በጊዜ ሂደት ውስጥ በርካታ ለውጦችን አስተናግዶ ዛሬ ያለውን መልክ ይዟል፡፡ በዚህ ክፍልም በቡድኑ የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች፣ የለውጥ ምክንያቶች የለውጡ ውጤት ቀርቧል፡፡

### 6.2.1. በአዝማሪዎች ኑሮ ውስጥ የተከናወኑ ለውጦች

ባህል በጊዜ ሂደት ውስጥ እየተለወጠ የሚመጣ ጉዳይ ነው Bohlman (1988) ፡፡ የወሎ አዝማሪዎች የኑሮ ልምድም የባህል አካል እንደመሆኑ በጊዜ ሂደት ውስጥ በመለወጥ ላይ ነው፡፡ ከለውጦቹ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

#### 6.2.1.1. ከህዝብ ጋር መቀላቀል

አዝማሪዎች አዝማሪነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ታቦተ ፅዮንን አጅቦ ወደ ኢትዮጵያ ከገባው እስራኤላዊ ቡድን ጋር ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው መሰንቆ ቅዱስ የዜማ ዕቃ በመሆኑ በታቦቱ ፊት ለዝማሬ ስለሚያገለግል ነው፡፡ ከዚህ አፈ-ታሪካዊ እምነት የተነሳ መሰንቆ ንጉሳዊ በሆነው የኢትዮጵያ አስተዳደር ስርዓት

ውስጥ በሰሎሞናዊው የዘር ሃረግ የመጨረሻው ንጉሰነገስት እስከሆኑት የአፄ ሃይለስላሴ የንግስና ዘመን ድረስ በቤተክህነትና ቤተመንግስት ውስጥ ሲያገለግል እንደኖረ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ የሃይለ ስላሴ የንግስና ዘመን አብቅቶ ደርግ ወደ ስልጣን ሲመጣ የአዝማሪዎች የአኗኗር ፈሊጥ ተቀይሯል፡፡ ይሁንና የባህል ለውጥ ድንገት በአንድ ሌሊት በቅሎ የሚያድር ጉዳይ ባለመሆኑ በደርግ ዘመን የታየው የአዝማሪዎች የአኗኗር ልምድ ለውጥ በሃይለ ስላሴ ዘመን ብቅ ማለት ጀምሯል፡፡ በዘመኑ ምንም እንኳን የተወሰኑት አዝማሪዎች በቤተመንግስትና በባላባቶች ቤት የሚያገለግሉ ቢሆንም ብዙዎች ‹‹ኖግብር አገራቸው›› በሚል ተከልለው ከቆዩት ልማድ በመውጣት የትውልድ አካባቢያቸውን ለቅቀው ከተሞች ወዳሉበት በመጓዝ የከተማውን ሰው የሚያጫውቱና በመልሱ በሚያገኙት ሽልማትና ክፍያ የሚተዳደሩ ሆነዋል፡፡

በዘመኑ ንጉሱ (አፄ ሃይለስላሴ) ግዛታቸውን ወደ መሃል አገር እያጠናከሩ መምጣታቸውና ከተሞች መመስረታቸው አዝማሪዎች የነበረውን ለአንድ ጌታ የመገዛት ልማድ እየተው ቀስ በቀስወደ ከተማ እንዲገቡ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በነገሌ ቦረና፣ በጨንቻ፣ አርሲ ወዘተ ሲዘዋወሩ የኖሩ ሲሆን አዲስ አበባ ግን በዋናነት ለስራ የሚሄዱበት ቦታ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም በጠላና በጠጅ ቤቶች በመዘዋወር የዘፈን ስራቸውን ይሰራሉ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ አዝማሪዎች በቋሚ ደንበኝነት የሚሰሩባቸው ጠላና ጠጅ ቤቶች ሲኖሯቸው ሌሎች ደግሞ ፈላጊ መጥቶ እስኪጠራቸው ድረስ አንድ ቦታ ተቀምጠው ይጠብቃሉ፡፡

በቋሚ ደንበኛነት ይሰሩ ከነበሩ አዝማሪዎች ውስጥ የህይወት ልምዳቸውን የገለፁ አንድ መረጃ ሰጪ እንደገለፁት ‹‹ቅዳሜና እሁድ ሶስት ብር፣ በአዘቦት ሁለት ብር፡፡ ሽልማት የራሴ ነው፣ መጠጥ ሰው ከጋበዘኝ ጋበዘኝ ካልጋበዘኝ በእስዋ ነው››፡፡ (አራጌ ይማም፣ ቃለመጠይቅ 14/04/2005 ዓ.ም፣ ደሴ) ሲሉ በ1954 ዓ.ም አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ በአዝማሪነት በሚሰሩበት ጊዜ ቋሚ ባለጠጅ ቤት አሰሪ ደንበኛ እንደነበረቻቸውና በዚያ ቦታም ከሽልማት ውጭ በስራ ቀናት ሁለት ብር ቅዳሜና እሁድ ደግሞ ሶስት ብር እየተከፈላቸው ይሰሩ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጠጪው ከጋበዛቸው ጋበዛቸው ካልጋበዛቸው ግን አዝማሪው የፈለገውን ያህል መጠጥ በባለቤቷ ወጪ የሚጠጣ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የቀረቡት መረጃዎች አዝማሪነት የቤተ መንግስት ሙያ መሆኑ ቀርቶ የህዝብ መገልገያና መዝናኛ እየሆነ መምጣቱን ያሳያሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አዝማሪዎች መተዳደሪያ የሚሆናቸውን ነገር ለማግኘት አገር ለአገር የሚዞሩ ሰዎች ሆነዋል፡፡ አቶ አራጌ ይማም

(ደሴ)፣ ወ/ሮ አለምፀሃይ የማናና (ውጫሌ)፣ አቶ ብርሃን ትኩ (ማርዬ) በየፊናቸው ዞርንባቸው ከሚሏቸው ሃገሮች ውስጥ ዲላ፣ ሲዳሞ፣ አናጎ፣ ጅማ፣ ወለጋ፣ ጊምቢ፣ ነቀምት፣ ድሬዳዋ፣ ሚዛን ተፈሪ፣ ሲዳሞ፣ ይርጋ ጨፌ፣ አጋሮ፣ ጥቂቶች ናቸው፡፡ የሚዘዋወሩባቸውን ቦታዎች የሚመርጡት ነዋሪው ማህበረሰብ ጥሩ ገቢ አለው ብለው ሲያስቡ ሲሆን በቦታው ደርሰው ግምታቸው ልክ ካልሆነ የተሻለ ፍለጋ ወደ ሌላው ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሃገር አገር ሲዞሩ ወደ ትውልድ መንደራቸው ሳይመለሱ በዚያው ሞተው የሚቀሩ አዝማሪዎች ብዙ እንደነበሩ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ፡-

ከሃገራችን ከወጣን ዓመታችን
አልተጠመዱም በሮቻችን
ለገመሳ እንኳን ባንደርስ
ለዘር እንመለስ (ማስረሻ ፈንታው፣ ምልከታ፣12/05/2005 ዓ.ም. ማርዬ)

በሚለው ቃል ግጥም ይገልፁታል፡፡ ቃል ግጥሙ ከአንድ ዓመት በፊት ቀዬውን ለቅቀው የወጡ ሰዎች የእርሻ ስራ ሳያከናውኑ ጊዜ ማለፉን በሰሙ የሚገልፅ ሲሆን በወርቁ ደግሞ በተሰደድንበት ሃገር ሁላችንም ሞተን አንለቅ፣ የዘር ሃረጋችን ለመቀጠል እንድንችል ጥቂቶቻችን እንኳን ወደ ቤት እንመለስ ይላል፡፡ ከቃል ግጥሙ መረዳት የሚቻለው በርካታ ሰዎች መሞታቸውን ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ገጣሚው ‹‹ለዘር እንኳን እንትረፍ›› በማለት ጥቂቶችን ሲለምን ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ የአዝማሪዎች ህይወት ከጉዞ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የተፈጠረ ነው፡፡

በዚህ ዘመን በአዝማሪዎች የሙዚቃ ልምድ ውስጥ አዲስ ነገር መከሰቱን መረጃ ሰጪው ይገልፃሉ፡፡ ይህ አዲስ ነገርም አንዳንድ አዝማሪዎች መሰንቋቸውን ትተው አኮርዲወን በተባለ የሙዚቃ መሳሪያ መዝፈን መጀመራቸው ነው፡፡

አኮርዲዎን በበርካታ የአለም አገራት የሚታወቅ ሳጥን መሰል ቅርፅ ያለው የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ መሳሪያው ወናፍ የመሰለ የሚዘረጋና የሚታጠፍ እንዲሁም ድምፅን የሚፈጥሩ ቁልፎች አሉት፡፡ አኮርዲወን ተጫዋቹ ሙዚቃን በሚጫወትበት ጊዜ ወናፍ መሰሉን ክፍል ከእሱ በስተግራ፣ ቁልፎቹን ደግሞ በቀኝ እጁ አቅጣጫ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በኋላም ቁልፎቹን በጣቶቹ በመነካካት ድምፅ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ የሚወጣው ድምፅ ተጫዋቹ በግራ እጁ ይዞ አጠፍ ዘርጋ ከሚያደርገው የመሳሪያው አካል ጋር

ሲጋጭ ዜማ ይይዛል። ዜማው የተለያየ ቃና እንዲኖረው ወናፍ መሰሉን አካል በተለያየ የጊዜ ርዝመት ያጥፈዋል ይዘረጋዋል (አሰፋ ለገሰ፣ ቃለምልልስ 08/04/2005፣ ደሴ)።



ስዕል 13. አኮርዲወን

አኮርዲወንን በሙዚቃ መሳሪያነት መጫወት የጀመሩ የተሻለ የከተሜነት ፀባይ ያዳበሩና ለውጥን ለመቀበል ፈጣን የሆኑ ወሎን ትተው በአዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ አዝማሪዎች ናቸው። መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት አኮርዲወን በአዝማሪዎች እጅ የገባው በ1954 ዓ.ም አካባቢ ነው። ይህንን ሁኔታ አንድ መረጃ ሰጪ ሲገልፁ፡-

> እቴጌ እንደሞቱ ጊዜ አዲስ ሙዚቃ፤ አኮርዲወን ነበር። በቀኝ ነው የሚመታው። የዛን ጊዜ ትምህርት ያለው ማሲንቆውን እየተወ እሱን ለመደ። በቃ እነአሰፋ ለገሰም አሁን ደሴ ያለው የኤም ትልቅ ወንድሜ በዚያ ነበር የሚጫወቱት። በቃ ይኸ ነው። በዚህም በዚያም ያፋጫጫ ጊዜ ሌላ ነበር። ያን ጊዜ ቴፕ አልመጣም ነበር። ቴፕ በኋላ ነው የመጣ። አኮርዲወን ነው የመጣ። ታች ፒያሳ ነው የሚሸጥ አንተ (መንገድ መሪዬን እያዩ) እና እኔ ሄደን እንመርጣለን። አምጣ እንለዋለን ቀይ አለ ጥቁር አለ። መቀየሪያ ያለው አለ። አንድ ብቻ የሆነ አለ። ያን መርጠህ (እንደላይኛው) መግዛት (ብርሃን ትኩ፣ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)።

ሲሉ መቼና እንዴት የአኮርዲወን ጨዋታ በኢትዮጵያውያን አዝማሪዎች እንደተጀመረ ገልፀዋል፡፡ ይህንን ሁኔታ ካደረጉ ሰዎች ውስጥ አንዱ የሆኑት አቶ አራጌ ይማምም ቀጣዩን ገለፃ በመስጠት ለጉዳዩ ምስክርነት ይሰጣሉ፡፡

> ሃምሳ አራት አካባቢ እቴጌ ሞቱ ተባለ፡፡ ሃዘን ሆነ፡፡ እቴጌ ሞተው ሃዘን በመሆኑ በሬዴዮ የሚተላለፈው ሃዘን ነው እንጅ ዘፈን የለም፡፡ አዝማሪ የሚባል ወዴት መጥቶ? የሚሰራ ነገር የለም፡፡ ወዲያው ደግሞ ልጃቸው ሳህለ ስላሴ ሞተ፡፡ የእሳቸው ሃዘን ለቀቅ ሲል ደግሞ እሱ የሞተ ጊዜ አይ ሃዘናችንን አንስተናል፡፡ ቀጥሉ በየስራችሁ ፈቅደናል ተብሎ በሬዴዮ ተነገረ፡፡ ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ ሄድሁ፡፡ ወዲያው ከወታደሮች በመቶ ሰባ ብር አኮርዲወን ገዛሁ፡፡ ያን ጊዜ መቶ ሰባ ብር ማለት በጣም ብዙ ብር ነው፡፡ ገዛሁዋት፡፡ ማንም ሰው አላስለመደኝም፡፡ እራሴ እዛ ማሞ ካቻ ግቢ አካባቢ ትልቅ ባህርዛፍ ግቢ ቦታ አለ፡፡ እዚያ ተማሪዎች የሚያጠኑበት ነው፡፡ ተወዲያ ወህኒ ቤቱ አለ፡፡ ተወዲህ ማሞ ካቻ ጋራዥ አለ፡፡ ባህር ዛፍ ምሪት ነው (አራጌ ይማም፣ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005 ዓ.ም፤ደሴ)፡፡

ይህ መረጃ፣ መረጃ ሰጪው አኮርዲወንን መቼና እንዴት እንደለመዱ ይገልፃል፡፡ ይህና ሌሎች መረጃዎች እንደሚሉት ከተጠቀሰው ጊዜ ወዲህ በርካታ አዝማሪዎች መሰንቋቸውን እየተው የአኮርዲወን ጨዋታ ጀምረዋል፡፡ ይህ መሆኑ ቀደም ሲል የነበረው ለአዝማሪ ይደረግ የነበረ ክፍያ መጠን አሳድጎታል፡፡ በአኮርዲወን የሚዘፍኑ አዝማሪዎች ክፍያ በመሰንቆ ከሚከፍሉት አደገ፡፡ አራጌ ይማም ይህንን ሲገልፁ፡ ‹‹. . . ከዚያ መሰንቆውን ትቼ አኮርዲወን መጫወት ጀመርሁ፡፡ ከዚያ ደንበኛን ገንዘብ ጨምሪልኝ ስላት በዚያው በመሰንቆ ዋጋ እንጅ አዲስ አልከፍልህም አለችኝ፡፡ ትቺያት ወለጋ›› (አራጌ ይማም፣ ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005 ዓ.ም፤ ደሴ) ይላሉ፡፡ መረጃው የሚያሳየው አዝማሪው መሰንቆ ጨዋታን ትተው ወደ አኮርዲወን ጨዋታ በመምጣት ገቢያቸውን ለማሳደግ ያደረጉትን ጥረት ነው፡፡ አዝማሪው መሰንቆን ትተው አኮርዲወንን ለመለማመድም ሆነ ከደንበኞቻው ተለያይተው ወደ ሌላ ቦታ ለመሄዳቸው ምክንያቱ የተሻለ ገቢ የማግኘት ፍላጎት ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በዚህ ዘመን ሰዎች የሚዝናኑበት ሙዚቃ የአዝማሪ ዘፈን ብቻ

ነው፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ በአዝማሪዎች መካከል የተሻሉ ሆኖ በመገኘት የተሻለ ገቢ ማግኘት ግዴታ ነው፡፡ ለዚህ ሲሉ ቁጥራቸው ትንሽ የማይባል አዝማሪዎች ወደ አኮርዲወን ተጫዋቺነት መጥተዋል፡፡ ይሁንና አዝማሪ በባህሉ ውስጥ ይዞት የቆየው ሚና ጠንካራ በመሆን የተነሳ የአኮርዲወን ጨዋታ መጀመር በመሰንቆ ጨዋታ ላይ ልምድ ለውጥ መፍጠሩ ባይቀርም መሰንቆን ከክዋኔ ሊያስወጣው አልቻለም፡፡ ስለዚህም ጥቂት አዝማሪዎች አኮርዲወን፣ በርካቶች ደግሞ መሰንቆን ይዘው ወደ ደርግ ዘመን ተሸጋግረዋል፡፡

የደርግ ዘመን አዝማሪዎች ሙሉ በሙሉ ከቤተ መንግስት የወጡበት ጊዜ ነው፡፡ ስርዓቱ ከንጉሳዊ አስተዳደር ፍፁም የተለየ ስርዓት በመሆኑ የአዝማሪዎችን በቤተመንግስት መዝፈን የሚፈልግ አልነበረም፡፡ ይህ መሆኑም አዝማሪዎችን የተከበሩና የቤተመንግስት ሰው ከመሆን አውጥቶ የመካከለኛው ማህበረሰብ አባል አድርጓቸዋል፡፡ እንዲያውም በዚህ ዘመን መሬት ላራሹ በመታወጁ አዝማሪዎች ራሳቸው የመሬት ባለቤት ለመሆን የበቁበት ጊዜ ነው፡፡ ይህም ከሌላው አርሶ አደር ጋር የሚመሳስላቸው ነገር ሆኗል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ዘመኑ የእኩልነት ዘመን ነው፡፡

በዘመኑ አዝማሪዎች ራሳቸው ህዝባዊ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን መሰንቋቸውን የዘመኑን ህዝባዊነት (የደርግ መንግስትን ፖሊሲ) ለሌላው ለማስረዳት ተጠቅመውበታል፡፡ ይህንንም መረጃዎች ‹‹አሁን እንደገና ተይው በክበብ እኛው ሆነ፡፡ በመሰንቆ እያጀብን ልማት የምናሰራ እኛ ሆነ፡፡ በደርግ ጥሩ ነበር ማለቴ ነው›› (ተስፋዬ በላይ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005ዓ.ም.፣ ማርዬ) ሲሉ ይገልፁታል፡፡ መረጃው የአዝማሪዎችን ህዝባዊ ሆኖ በህዝባዊ ዘመን መኖር የሚገልፅ ሲሆን ለዚህ መገለጫ ከሆኑ ነጥቦች ውስጥ እንደ የወሎ ላሊበላ ኪነት ቡድን ባሉ የተለያዩ የኪነት ቡድን ውስጥ መሳተፋቸው አንዱ ነው፡፡ ከእንደዚህ አይነት ተሳትፎዎች ውጪ ግን መዝፈን እስከፈለጉ ድረስ ገንዘብ ‹‹አገኝበታለሁ›› ብለው ባሰቡት ቦታ ሁሉ ተንቀሳቅሰው የሚሰሩ ሆነዋል፡፡ ይህ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ደግሞ ቡድኑ ለዘመናት ‹‹የእኔ›› ብሎ የኖረበትን የአሰፋፈር ልምድ ቀይሮታል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

### 6.2.1.2. የቡድኑ አሰፋፈር

የወሎ አዝማሪዎች በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተለይተው ከሚታወቁባቸው ባህርያት ውስጥ የራሳቸውን መንደር መስርተው ይኖሩ የነበረ መሆኑ አንዱ ነው፡፡ አዝማሪዎች ምንም እንኳን የስራቸው ባህርይ ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ የሚያደርጋቸው ቢሆንም የትም ዞረው የሚያርፉባቸው በቋሚነት የእኔ የሚሏቸው መንደሮች አሏቸው፡፡ በእነዚህ መንደሮች ከአዝማሪ ያልተወለደ ሰው የማይኖርባቸው ሲሆን አዝማሪዎችም ቢሆኑ የእናት አባቶቻችን ርስት ብለው የያዟቸው ነበሩ፡፡

ይሁንና ይህ ልምድ ከደርግ ወደ ስልጣን መምጣት በኋላ የቀረ መሆኑና አሁን የማይተገበር መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ፡፡ አዝማሪዎች ለመኖሪያም ሆነ ለስራ በጥቂት መንደሮች ተወስኖ የመኖር ልምዳቸውን እየተው እንደ ማንኛውም ሰው ለመኖር አመቺ ሆነው ባገኟቸው ቦታዎች ሁሉ እየኖሩ ነው፡፡ ጥንት የአዝማሪ ብቻ የነበሩ መንደሮችም ዛሬ አዝማሪ ያልሆኑ ሰዎች ተቀላቅለው የሚኖሩባቸው ሆነዋል፡፡

ቀደም ሲል ይደረግ የነበረው መንደርን ከልሎ የእገሌ ርስት ነውና ከእሱ ቤተሰብ ውጪ ማንም አዝማሪ ገብቶ እንዳይዘፍን የሚለው ‹‹የግብር አገር›› የሚባለው ስርዓት ቀርቷል፡፡ በዚህ የተነሳ ማንም ፍላጎቱ ያለው አዝማሪ የትም ቦታ ሄዶ መስራት እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹አዲያ የድሮዎች አልቀዋል፡ ልጅ ልጆች ናቸው ያሉ፡፡ ግን ልጆችም የአባታችን አገር ብለው አይሄዱም፡፡ ቀድሞ ደርግ የገባ ጊዜ ሁሉንም ከርክሞታል፡፡ ሰርተህ ብላ ነው›› (ሰኢድ ኢብራሂም፣ ቃለመጠይቅ፣ 14/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

መረጃው ጥንታዊዎቹ ህጎች እንዲጠበቁ የሚፈልጉት የጥንት ሰዎች በሞት የተወሰዱ እንደሆነና ባህሉን የተቀበሉት ልጆች ደግሞ ስለቤተሰቦቻቸው ርስት ጥበቃ የማይጨነቁ መሆኑን ይገልፃል፡፡ ለዚህ ጉዳይ ዋናው ምክንያት ከደርግ ስርዓት በኋላ አዝማሪዎች በተከለሉ መንደሮች ተወስኖ ከመኖር ይልቅ በተለያዩ ቦታዎች ተጉዘው የመስራት ልምድ በመፍጠራቸው፣ እንዲሁም በግብርናና በመሳሰሉ ሌሎች ስራዎች ውስጥ በመሰማራታቸው ነው፡፡ እንዲያውም በዚህ ዘመን ‹‹ዘፍነን በምናገኘው ገንዘብ እንኖራለን›› የሚለውን አስተሳሰባቸው እየተቀየረ የገቢ ምንጫቸውን በሌሎች ስራዎች ላይ ማድረጋቸው በኑሮ ልምዳቸው ላይ የመጣ ለውጥ ሆኗል፡፡ ይህ በአሰፋፈር ደንብ ላይ የመጣ ለውጥ ግን በአዝማሪዎች ማህበራዊ አኗኗር ላይ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ይህም በአንድ ላይ ተሰብስቦ ከመኖር ይልቅ ከሌሎች አዝማሪ ካልሆኑ ሰዎች ጋር

የመቀላቀል ህይወት ፈጥሮላቸዋል፡፡ ይህም ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ፎክሎሩ የሚሰጠው የአገልግሎት መጠን በማህበረሰቡ ማህበራዊ ህይወትና ማህበራዊ ግንኙነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ አለ Finnegan (1992,32) ከሚሉት ጋር የሚገጥም ነው፡፡

በአዝማሪዎች የአሰፋፈር ልማድ ላይ ትልቁን ለውጥ የፈጠረው በአዝማሪነት ላይ ብቻ ተወስኖ የኖረው የገቢ ምንጫቸው አማራጪ በማግኘቱ እንደሆነ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህም በአዝማሪዎች ውስጥ ከተከሰቱት ለውጦች ውስጥ አንዱ ወደሆነው የገቢ ምንጪ ለውጥ ወደ ሚል ሃሳብ ይመራል፡፡

## 6.2.1.3. የገቢ ምንጭ ለውጥ

የወሎ አዝማሪዎች ኢትዮጵያ ትተዳደርበት ከነበረው የፊውዳል ስርዓት ጀምሮ እስከ ደርግ ወደ ስልጣን መምጣት ድረስ ራሳቸውን ከዘፈን በሚያገኙት ገቢ ብቻ ሲያስተዳድሩ ኖረዋል፡፡ ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ እያንዳንዱ የአዝማሪ ቤተሰብ የመሬት ባለቤት በመሆኑ የተነሳ ፍላጎት ከሌላቸው ጥቂት አዝማሪዎች በስተቀር የብዙ አዝማሪዎች መተዳደሪያ ዘፈንና እርሻ ሆነው ኖረዋል፡፡ ባለሁለት የገቢ ምንጪ መሆናቸው በተለይ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በመዝፈን ብቻ ህይወታቸውን ይገፉ ለነበሩ አዝማሪዎች በየጊዜው ወደ ተወለዱበት መንደር እንዲመለሱ፣ በሃብት ደረጃም ከቀድሞው የተሻለ አኗኗር እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል፡፡ ይሁንና መረጃዎች እንደሚገልፁት ዛሬ አዝማሪነትም ሆነ ግብርና የሚያስገኙት ገቢ ኑሮን ለማሸነፍ የሚበቃ አይደለም፡፡ በተለይም አዝማሪነት የሚያስገባው ገቢ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ አዝማሪዎች እንደ በፊቱ ልጆቻቸው በዘፈን ብቻ የሚተዳደሩ እንዲሆኑ አይፈልጉም፡፡ ልጆችም ቢሆኑ ማህበረሰቡ ለአዝማሪነትና በአዝማሪነት አማካኝነት ለሚገኘው ገቢ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት አንገታቸውን የሚያስደፋቸው እየሆነ በመምጣቱ ሌሎች የስራ አማራጮችን መፈለግ እንደሚገባቸው ወስነዋል፡፡ በመሆኑም ዛሬ ላይ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች ከመሰንቆ ይልቅ ዘመናዊ ትምህርት መማር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡ ስለዚህ ገበሬና ተጫዋች ከሚለው የስራ ምድብ በተጨማሪ የመንግስት ስራ በአዝማሪዎች መንደር ሌላው የገቢ ማግኛ መንገድ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ይህንን ጉዳይ ሲያስረዱ፡-

አሁን የእኛ ልጆች የመንግስት ሰራተኞች ናቸው፡፡ የአባት ስራ እየቀየረ መጣ፡፡ ለምንድን ነው? አልጠቀመውም፡፡ አሁን እኔም ትቼዋለሁ፡፡ አሁን ጊዜው ገደለው፡፡ እኛም እንደጊዜው ሆነን መኖር ፈለግን፡፡ ለምን? ካላበላሽ፣ ስድብ ተሆነ ስምሽ ምንድን ነው ጥቅሙ? እንደሰው ሰርተሽ መኖር አትችይም እንዴ? ብር ለምነን መቶ ብር ቢያገኝ በመቶ ብር ልጅ? ሚስት ማስተዳደር ይቻላል? ሺ ብር እንኳን ያስተዳድራል? ማስረሻ ፈንታዉ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣12/05/2005 ማርዬ)

መረጃው እንደሚገልፀው የአዝማሪነት ሙያ የሚያስገኘው ጥቅም እያነሰ በመሄዱና በዘፈን የሚገኘው ገቢም ቤተሰብን ለማስተዳደር የማይበቃ በመሆኑ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን በሌላ ስራ እንዲሰማሩ እየገፋፉ ነው፡፡ ራሳቸው ወላጆችም ቢሆኑ አዝማሪነትን እየተው በሌላ የተሻለ ገቢ ሊያስገኝ በሚችል ሙያ እየተሰማሩ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀጣዩ መረጃ አዝማሪዎች ቀደም ሲል አዝማሪነትን ይዘውት የኖሩ የገቢ ምንጫቸው ስለነበረ እንደሆነና ዛሬ ግን የሚያስገባው ገቢ በማነሱ የስራ ለውጥ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡

አዝማሪነት እኮ እንደሌላው ስራ ነው፡፡ እሱን ሰርተን ገንዘብ ስለምናገኝ ነው የምንሰራው እንጅ ብንተወውም ይተዋል፡፡ ግዴታ አይደለም፡፡ አንዳንዶች አዝማሪዎች ‹ዘፈን ቢያቆሙ እንቆመጣለን ብለው ይፈራሉ› ይላሉ፡፡ ግን አይደለም፡፡ ይኽ የእኛ ሳይሆን የአባ ውዴዎች ተረት ነው፡፡ የእኛ ሰው እንዲህ አይልም፡፡ አሁንም ቢሆን ብዙ ሰው መሰንቆውን እየተወ እየተማረ በሌላ ስራ እየተሰማራ ነው፡፡ አስተማሪ ብትይ፣ ግብርና ብትይ፣ ፖሊስ ብትይ ብዙ የእኛ ሰው አለ፡፡ ዛዲያ እኒህ ሁሉ አዝማሪነቱን ትተውታል፡፡ ምክንያቱም ጥቅም የሌለው ሆነ›› (ዘሪቱ ከበደ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 14/04/2005፣ ደረቅ ወይራ)፡፡

መረጃው የሚያገኙት ገቢ ለመኖር የማይበቃ ስለሆነባቸው የተሻለ ገቢ በሚያስገኙ ሌሎች ስራዎች ላይ እየተሰማሩ ነው ይላል፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው አዝማሪዎች በአዝማሪነት ስራ ሊቀጥሉ የሚችሉት ከስራው የሚገኘው ገቢ ለኑሮ የሚበቃቸው እስከሆነ ድረስ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ያ ካልሆነ ግን ራሳቸውን በአግባቡ ማስተዳደር ይችሉ ዘንድ ሌላ ስራ ፍለጋ ይሄዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ የማርክሲሳዊ እሳቤ አራማጆች ከቀላሉ የአደንና ፍራፍሬ መሰብሰብ ውስብስብ እስከሆነው የኢንዱስትሪ ስራ ድረስ ሰው ከተፈጥሮና ከሰው ጋር የሚያደርገው ግንኙነት፣ ለመኖር የሚያደርገው ጥረት ነው ilitskaya (1978) ሲሉ ከሚሰጡት ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ስለዚህም ከመረጃዎች በመነሳት አዝማሪነት እያስገኘ ያለው ገቢ ማነስ የቡድኑን የገቢ ምንጮች እየለወጡ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ይህ የስራ ለውጥ ደግሞ የቡድኑ የጋብቻ ልምድ እንዲቀየር ምክንያት ሆኗል፡፡

## 6.2.1.4. የጋብቻ ልምድ

የወሎ አዝማሪዎች የጋብቻ ግንኙነት ሲመረመር ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪን የሚያገባ አዝማሪ ብቻ ነበር፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የነበረው የገቢ ምንጪ ምክንያት ነው፡፡ አዝማሪ ዘፋኝ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ገበሬ ነው፡፡ አንዱ የሌላውን ስራ እየናቁ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ ያሉ ወንዶች በስራ የምታግዛቸውን ሴት እንጂ ሌላዋን ማግባት ሳይፈልጉ ኖረዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ አዝማሪ ከገበሬ ቤተሰብ ሚስት ቢያገባ ዘፍና ልታግዘው አትችልም፡፡ አንድ ገበሬም አንድን የአዝማሪ ልጅ ቢያገባ የእርሻ ስራውን የገበሬን ልጅ ያህል ልትከውንለት አትችልም፡፡ ይህ ደግሞ በሁለቱም ላይ ድህነትን የሚያመጣ ነው፡፡ ስለዚህ ኢኮኖሚ የጋብቻውን መልክ ወስኖት እንደኖረ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡

ይሁንና የደርግ ስርዓተ ማህበር ሁሉንም አዝማሪዎች እንደማንኛውም የገጠር ነዋሪ የመሬት ባለቤት ማድረጉ አንድ የአዝማሪ ልጅ መዝፈን እንኳን ባይችል ባለሃብት ያደረገ በመሆኑ የኢኮኖሚን ችግር የለምና ከየትኛው ወገን እንዲጋባ ዕድል ፈጠረ፡፡ ይህ ደግሞ አዝማሪ ከገበሬ ጋር ለመጋባት በትንሹ መንገድ ከፈተ፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በደርግ ስርዓት የተጀመረው በጋብቻ መቀላቀል በስፋት ቀጥሏል፡፡ ምክንያቱም አዝማሪዎች ከዘፋኝነት ውጭ የሌሎች ሙያዎች ባለቤት እየሆኑ በመምጣታቸው ከአብዛኛው ሰው የአኗኗር ፈሊጥ ጋር ተመሳሳይ ኑሮን እየኖሩ ነውና ከሌላው ሰው ጋር ያላቸው ልዩነት በመጥበቡ ነው፡፡ ጉዳዩን መረጃ ሰጪዎች ‹‹አሁን ግን ሁሉም

እየሰለጠነ፣ እየተማረ ሲመጣ ሁላችንም በመማርም በምንም አንድ አይነት ሙያ እየኖረን ሲመጣ፣ በመምህርም መምህር ሆነናል፣ በዶክተርም ዶክተር ሆነናልና መጋባት ችለናል፡፡ ምንም ችግር የለም፡፡ ድሮ ግን እንዳይጋቡ ያግዳቸው የነበረ የሙያ ልዩነት ነው፡፡ (መኮንን በላይ፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

መረጃው አዝማሪዎች ዘፈንን በመዝፈን ብቻ ይተዳደሩ በነበረበት ጊዜ ሌላው ሰው ዘፋኝነትን አሳንሶ በማየቱ በሁለቱ ቡድን መካከል የጋብቻ ግንኙነት አልነበረም፡፡ ዛሬ ግን አዝማሪዎች እንደሌላው ሰው ዘመናዊ ትምህርት በመማራቸውና ሌላው ሰው በተሰማራበት ሙያ በመሰማራታቸው በመካከል የነበረው የሙያ ልዩነት ጠፍቶ በቡድኖች መካከል የጋብቻ ግንኙነት ተመስርቷል ይላል፡፡ ከዚህ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ጉዳይ ለሁለቱ ቡድኖች በጋብቻ መለያየት ዋና ምክንያት ሆኖ የኖረው የገቢ ምንጫቸው ልዩነት ነው፡፡ ዛሬ አዝማሪዎች ራሳቸውን በሌላ ስራ የማሰማራት ዕድል ስላላቸውና አዝማሪነቱንም ቢሆን መርጠው የሚሰሩት ስራ በመሆኑ በቡድኖቹ መካከል ያለው የስራ ምንነት ላለመጋባት ምክንያት አይደለም፡፡ በሁለቱ መካከል ለመጋባት መስፈርቱ በመካከላቸው ያለው ስሜት ብቻ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ የሚገልፁት ጥቅሶች የሚከተለውን ይላሉ፡-

> እህ ያማ ፍቅራቸው ነው ያገናኛቸው፡፡ ድሮ ቀረ እናትና አባት ጠይቆ መጋባት፡፡ ከወደደችው መሰንቆም ይዞ ብታየው መሰንቆ ቢመታ እረጋይቱ ከወደደች ትጠጋዋለች፡፡ ያገባታል ማለት ነው፡፡ ድሮ አባቶቻችን ለክፉም ለደግም ፈልገው ነበር የሚያጋቡ፡፡ ማለት የቅሬ ጎሳ አለ ማለት ነው፡፡ ከባላባት ጎሳ ይጋባል፣ ግን እሳ ከሰራተኛ ጎሳ አይጋባም፡፡ የቅሬ ጎሳ የሚሉሽ የአዝማሪ ጎሳ ነው፡፡ ድሮ፣ ከአምባሰል፣ ከክድጆ ተፈልጎ ነበር መጋባት፤ ዛሬ የቅሬው ልጅ ከረጋዋ ጋር ይጋባል፡፡ . . . ዛሬ ሁሉም ይጋባል፡፡ . . . ዛሬ በከተማም በይው በገጠርም በይው አዝማሪና ቅሬ እየተጋባ ተዋልዷል፡፡ ምንም አጥንተ ሰባራነት የለውም ማለቴ ነው ሲሉ ይገልፁታል፡፡ (ወ/ሮ ዘሪቱ ከበደ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 14/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)

ይህንን ሃሳብ የራሳቸውን ተጨባጪ ልምድ በመግለፅና ዛሬ ልጆቻቸው ያሉበትን የአኗኗር መልክ ዋቢ በማድረግ መረጃ የሰጡ ሌላው መረጃ አቀባይ ደግሞ፡- ‹‹ዛሬ አዝማሪ፣ ባሪያ የሚባል ነገር የለም፡፡ አሁን የኔ ልጆች ምሁር ነው ያገቡት ለጥቆ፣ እነሱም ምሁር ናቸው፡፡ የእኔም ልጅ እጮኛ አለችው የእናንተ ወገን ናት (እይ እንግዲህ የእናንተ ወገን አልሁሽ በቃ እንግዲህ እንደዚህ ነው) አሁን ነው የተቀየረው እንጅ በፊት አዝማሪ ባሪያ ልዩ ነው›› ብለዋል፡፡ (ማስረሻ ፈንታው፣ 11/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

እነዚህ መረጃዎች የአዝማሪዎችን የጋብቻ ስርዓት ቀደምትና የአሁን መልክ የሚገልፁ ሲሆን ዛሬ የድሮው ስርዓትና ደንብ እየተቀየረ መምጣቱን ይናገራሉ፡፡ ለውጡ ከአዝማሪዎች የስራ ጠባይ መቀየር ጋር የተያያዘ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪዎች ከሌላው የሚለዩበት የጋብቻ ስርዓት ቢኖራቸው ዛሬ ከመሰንቆ ጨዋታ ውጪ በሌሎች ስራዎች እየተሰማሩ ስለመጡ የጋብቻ መልኩ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ በአጠቃላይ እስካሁን በቀረበው ትንታኔ በወሎ አዝማሪዎች ተከታታይ ልምዶች ላይ ለውጦች መከሰታቸውን ለማየት የተቻለ ሲሆን ለውጦቹ አዝማሪዎች ከቤተክህነትና ቤተመንግስት ወጥተው ወደ ህዝብ መቀላቀላቸው፣ በተወሰኑ መንደሮች ከመኖር ወጥተው ሌሎች ሰዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች መኖር መቻላቸው፣ በዘፈን ብቻ መተዳደራቸውን ትተው በግብርናና ሌሎች ሙያዎች መሰማራታቸው፣ እርስ በእርስ ብቻ ይደረግ ከነበረ የጋብቻ ልማድ ወጥተው ከማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል ጋር ጋብቻን እየፈፀሙ መሆናቸው ናቸው፡፡ እስካሁን የቀረቡት የማህበረሰቡ ለውጦች ከኑሮ አንፃር የታዩ ሲሆን ከዘፈን ልምድ አንፃርም ለውጦች መኖራቸውን ለማስተዋል ተችሏል፤ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

### 6.2.2. በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች

የወሎ አዝማሪዎች የቡድናቸውን ማንነት ለዘመናት ሲገልፁበት የኖሩት የአኗኗር ባህርያቸው በመቀየር ላይ መሆኑን ከዚህ ቀድሞ በቀረቡ ርዕሶችና ንዑሳን ርዕሶች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በርዕሶቹ አዝማሪነትን እስከመተው የደረሱበት ሁኔታ እንዳለ ታይቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን የዘፈንን ስራ በቋሚነት ወይም በተጨማሪነት በመያዝ ከዚያ በሚገኘው ገቢ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን በማስተዳደር ላይ የሚገኙ ሰዎች

እንዳሉ መረጃዎች ይገልፃሉ። ይሁንና የእነዚህ ሰዎች የዘፈን አከዋወን በዘፈን ክዋኔ ደንቡ ላይ ለውጥ መኖሩን የሚያሳይ ነው። የለውጡ አይነት ቀጥሎ ቀርቧል።

### 6.2.2.1. የዘፈን አከዋወን ደንብ

በወሎ የአዝማሪ ዘፈን የራሱ የአከዋወን ስርዓት እንዳለው ቀደም ሲል ተገልጧል። ከደንቦቹ ውስጥ በአንድ የክዋኔ ቦታ ሴትና ወንድ አዝማሪዎች በአንድነት መከወን የሚለው ይነሳል። ይሁንና ይህ ልምድ አሁን በመቅረት ላይ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ይህንን ሃሳብ ካንፀባረቁ በርካታ ሃሳቦች ውስጥ አቶ መላኩ ካሳው የተባሉ መረጃ ሰጪ የሰጡት መረጃ ‹‹በድሮ በአባቶቻችን ጊዜ እንጅ ዛሬ ሴት ዘፋኝ የለችም። በዚህ በአምባሰልም ተከትላ የምትሰራ ሴት የለችም›› ይላል። (ቃለመጠይቅ፣ 19/04/2005ዓ.ም፣ ማርዬ) ።

ለዚህ ጥናት አላማ ተብሎ በተለያዩ የወሎ አካባቢዎች በተደረገ ምልከታ መረጃ ሰጪው የሰጡትን መረጃ የሚደግፉ እውነቶች ታይተዋል። በየትኛውም አውድ የወንዶችን ያህል የሴት አዝማሪዎች አልታዩም። ይሁን እንጅ ይህ ሁኔታ ከምዕራቡ ይልቅ በምስራቁ አካባቢ ጎልቶ የሚታይ ይመስላል። ምክንያቱም በምዕራብ ወሎ አካባቢ በሚገኙ እንደ ለጋምቦና ወረኢሉ ባሉ አካባቢዎች ብዙ ሴት አዝማሪዎች ከባሎቻቸውና ከስራ አጋሮቻቸው ጋር እንደሚሰሩ መረጃ ሰጥተዋል። በምልከታም ለማረጋገጥ ተችሏል። እንዲሁም በሰሜን ወሎ በቀለባስ ቀበሌ ቁጥራቸው ቢያንስም የሴት አዝማሪዎች አሉ። በጥቅሉ ሲታይ ግን የሴቶች ተሳትፎ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መምጣቱን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከዚህ ያታዊ የዘፈን ልማድ ባሻገር ከወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ደንቦች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ደንብ ቅኝት መለየትና፣ የቅኝቶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ መጫወት እንደሆነም ተብራርቷል። ‹‹የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን መልክ›› በሚለው ርዕስ ውስጥ እንደተገለፀው ወሎዬ አዝማሪዎች መነሻቸው ወሎ ውስጥ ነው ሲሉ የሚናገሩላቸው ትዝታ፣ አምባሰል፣ አንቺሆዬና ባቲ የሚባሉ የዘፈን ቅኝቶች አሉ። አንድ አዝማሪ ዘፈንን በሚጫወትበት ጊዜ እነዚህን ቅኝቶች አንዱን ከሌላው በአግባቡ እንዲለይና ቅኝቶችንም በልማዳዊው ቅደም ተከተል መሰረት እንዲጫወት ይገደድ ነበር። በዚህ መሰረት አንድ አዝማሪ ዘፈንን ሲዘፍን በመጀመሪያ መዲናና ዘለሰኛ የተባሉ ዜማዎችን (በትዝታ ቅኝት)፣ ከዚያም ትዝታ ዜማን፣ በመቀጠል አምባሰልን ከአምባሰል አንቺ

ሆዬን፣ በመጨረሻም ባቲን ይጫወታል፡፡ በቅኝቶቹ ስር የቅኝቶችን ማንነትና ምንነት የሚገልፁ ግጥሞችን ይገጥም ነበር፡፡ ይህ ልማዳዊ ህግ ለዘመናት የአዝማሪው ችሎታ መለኪያና የአዝማሪ ዘፈን መለያ ሆኖ ኖሯል፡፡ አሁን ግን ይህ ሁኔታ እየተለወጠ መሆኑን መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡

ዛሬ በተለይ ወጣት አዝማሪዎች ዘፈንን በሚከውኑበት ጊዜ ለነበረው ደንብ ሲገዙ አይታዩም፡፡ ቅኝቶችን ለይቶ ከመጫወት አንፃር ብዙዎቹ አራቱን ቅኝቶች በትክክል የማይለዩአቸው ሲሆን የሚለዩአቸው እንኳን ቢሆን ቅደም ተከተላቸው እንዲጠበቅ ለሚያዝዘው ህግ ቦታ አይሰጡም፡፡ እንዲያውም በአንዳንዶቹ ዘንድ ደንቡ እስከመኖሩ እንኳን አይታወቅም፡፡ ይልቁንም የሚሰሟቸውን ዘመናዊ ዘፈኖች በመሰንቆ ለመጫወት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ለአንድ ወጣት አዝማሪ ጎበዝነት መለኪያው ዘመናዊ ዘፈንን በመሰንቆ መጫወት መቻሉ ሆኗል፡፡ በምልከታ ማረጋገጥ የተቻለውም ይህንኑ ወጣቶች ስሜታቸውን በሳበው በማንኛውም አይነት ዘፈን ክዋኔያቸውን እንደሚጀምሩና እንደሚጫወቱ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ዛሬ የአዝማሪ ዘፈን የአከዋወን ደንብ እየተለወጠ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ከዘፈን አከዋወን ደንብ ለውጥ አንፃር የግጥሞች አይነትና ደረጃም እየወረደ መምጣቱን ይገልፃሉ፡፡ የድሮዎች አስደሳች በቅኔ የሚጫወቱ ነበሩ፡፡

እንዴት ዳዊት ይሙት፣ ቆሜ ሳልጠይቀው፤
የሚመጣውን ቀን፣ በገና የሚያውቀው ይሉ ነበር፡፡

> ተጫዋች ሲባል ከማን ይመጣል? ከቀሳውስት፣ ከሙህሮች፣ ተነዛ ቅኔ ፈልፍሎ ይሰጠዋል፡፡ ያንን ይዞ ይሰራ ነበር፡፡ በአሁኑ እኔም የሳይንስ ተማሪ፣ አንቺም የሳይንስ ተማሪ፣ ስለቅኔ ማን ነው የሚያውቀው? አየሽው፡፡ ለምንድን ነው ያልቻልነው? ጊዜው አፈነን! (ማስረሻ ፈንታው፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005 ማርዬ)

መረጃው ቀደም ብለው በአዝማሪዎች የሚከወኑ ግጥሞች ጥሩ የይዘትና ቅርፅ ደረጃ የነበራቸው መሆኑን ይገልፃል፡፡ ግጥሞቹ ይዘታቸውን ከባህላዊው ትምህርት ቤት

ከሃይማኖት ቤቶች ያገኙ እንደነበርና አቀራረባቸው ደግሞ ቅኔያዊ እንደነበረ ተገልፆአል፡፡ ይሁን እንጅ መረጃው ከዚህ በተጨማሪ አሁን ላይ አዝማሪዎች ዘመናዊ ትምህርት እየተማሩ በመሆኑ የቅኔ ባህል እየጠፋ መምጣቱን የሚገጥሟቸው ግጥሞችም ቅኔያዊነት የሌላቸው እየሆኑ መምጣታቸውን አብራርቷል፡፡ ሌሎች መረጃ ሰጪዎችም ቢሆኑ ዛሬ የሚከወኑ ግጥሞች በይዘትም ሆነ በቅርፅ ደረጃ ከጥንቶቹ በጣም ያነሰ ደረጃ ያላቸው መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ወ/ሮ አለምፀሃይ የማና የተባሉ መረጃ ሰጪ ይህንን ሲያስረዱ ቀጣዩን ይላሉ፡፡

> የድሮ ግጥም አርእስት ያለው ነው፡፡ ታሪክ ያለው ነው፡፡ እንግዲያ ዛሬማ ምን እንጨቱን ድንጋዩን አገጣጥመው ነው የሚዘፍኑ፡፡ ይህች ልጅ አሁን አዲስ የዘፈነች ናት፡፡ ‹‹አንተዬ ነይ በለኝ ዝም አትበለኝ›› ምትለው ይህቺ ናት፡፡ አዲያ ግጥሙ አመጣው፣ ወሰደው፣ ነው አርእስት የለውም፡፡ የሚፈለገው ሰምና ወርቅ ጨዋታ፣ የመሰረት ጨዋታ ነበረ፡፡ አልሆነም፡፡ አሁን መሰንቆ ይዘው የሚጫወቱት ሁሉ ግጥማቸው ፍጪው ቁይው ነው (አለምፀሃይ የማና፣ ቃለመጠይቅ፣ 19/04//2005፣ ውጫሌ) ፡፡

መረጃው የግጥሞች ደረጃ ከድሮው ይልቅ አሁን እየቀነሰ መምጣቱን ይገልፃል፡፡ ቀደም ሲል ይገጠሙ የነበሩ ግጥሞች ስለምን (የሚባሉበት ምክንያት) ያላቸውና በሰምና ወርቅ ቅኔ የሚቀርቡ ነበሩ፡፡ የአሁኖቹ ግጥሞች በአንፃሩ የዚያን ያህል ጥልቀት የሌላቸው መሆኑን ይገልፃል፡፡ በአዝማሪዎች የዘፈን ልምድ ውስጥ የታየው ሌላው ለውጥ የዘፈን መከወኛ አውዶች ናቸው፡፡

### 6.2.2.2. የዘፈን መከወኛ አውዶች

በወሎ አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑባቸው የታወቁ ልማዳዊ ቦታዎች እንደነበሯቸው አስቀድሞ ተገልጧል፡፡ እነዚህ ቦታዎች ግብር፣ መንደሮች፣ ገበያ፣ ጦርነት፣ መጠጥ ቤቶች፣ የታቦት ንግስ፣ ተዝካር፣ ሰርግ፣ ድግስ ቤቶች፣ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አውዶች ውስጥ አንዳንዶቹ ከቀላል እስከ ከባድ ለውጥ ቢከሰትባቸውም ከጥንት አንስቶ አሁንም ድረስ አሉ፡፡ ጥቂቶቹ ግን በሰበበ ክዋኔያቸው መጥፋት የተነሳ ጠፍተዋል፡፡

ከዚህ አንፃር የታቦት ንግስ፣ ተዝካር፣ ድግስ ቤቶች በነበሩበት መልክ አሁንም ዘፈን የሚከወንባቸው አውዶች ናቸው፡፡ ግብር፣ ገበያና ጦርነት ዛሬ ዘፈን የማይከወንባቸው አውዶች ናቸው፡፡ ግብር በመንግስት ስርዓት ለውጥ የተነሳ፣ ገበያ አዝማሪዎች ሌላ መተዳደሪያ በማግኘታቸው፣ ጦርነት ደግሞ በጦር ሜዳ የነበረው የአዝማሪዎች ሚና ሙሉ በሙሉ በዘመናዊ ባንዶች በመተካቱ ከዘፈን መከወኛነት ወጥተዋል፡፡

ከተወሰኑ ለውጦች ጋር ዘፈን እየተከወነባቸው ከሚገኙ አውዶች ውስጥ ሰርግና መጠጥ ቤቶች ይጠቀሳሉ፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንዳሉት ቀደም ባለው ጊዜ ‹‹አዝማሪ የሌለው ሰርግ የሃዘን ቤት ይመስላል›› ይባል ነበር፡፡ ይህ በመሆኑም ሰርግ ቤት አዝማሪ የሚፈለግበት ዋና ቦታ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ እየተቀየረ ነው፡፡ ምክንያቱም ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የአዝማሪዎችን ሚና እየተኩት በመሆኑ አዝማሪዎች ሙሽራ ‹‹ከቤት እስኪወጣ›› ድረስ ባሉ የተወሰኑ ሰዓታት እንዲከውኑ ከመፈለግ ባሻገር ‹‹ባይመጡም ምንም አይደለም›› እስከመባል እየደረሱ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በርካታ አዝማሪዎች ሰርግ ቤት ፍለጋ መዞርን በመተው ላይ ናቸው፡፡ ይሁንና ምንም ቢሆን በደገሱት ሰርግ ላይ አዝማሪ እንዲገኝ የሚፈልጉ ሰዎች በመኖራቸው በሰርግ ቤት የሚዘፍኑ አዝማሪዎች አሉ፡፡ እነዚህ አዝማሪዎች ግን ራሳቸው ሰርግ ቤት የት አለ? በማለት ፈልገው የሚዘፍኑ ሳይሆኑ ባለ ሰርግ ቤቶች ፈልገዋቸው መጥተው አስቀድሞ በሚደረግ የገንዘብ ስምምነት ወደሰርግ ቤቱ ሄደው የሚዘፍኑ ናቸው፡፡

ወደመጠጥ ቤቶች ሲመጣ የሚታየው ለውጥ ሰፊ ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪዎች መጠጦችን ለማሻሻጥ ሲባል ‹‹በኮንትራት›› አለዚያ ደግሞ በዕለት ስምምነት በአረቄ፣ በጠላና በጠጅ ቤቶች ውስጥ ይዘፍኑ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ እየተቀየረ ነው፡፡ ምክንያቱም የመጠጥ ቤት ባለቤቶች ለመጠጥ ማሻሻጫ እንዲሆናቸው ቴፕና ቴሌቭዥንን እየተጠቀሙ በመሆኑ አዝማሪዎችን መቅጠር ትተዋል፡፡ በአንፃሩ ግን እንደ ደሴ ባሉ ከተማዎች በአዝማሪ ሙዚቃ ብቻ የሚሰሩ ‹‹የባህል ምሽት›› ቤቶች በመከፈታቸው  አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑበት አዲስ አውድ ተመስርቷል፡

የባህል ምሽት ቤቶች መጠጥ የሚሸጥባቸው ቦታዎች በመሆናቸው ቀደምት አዝማሪዎች ይከውኑባቸው ከነበሩት መጠጥ ቤቶች ጋር ተመሳሳይ ቢሆኑም ከቀደምቶች የሚለዩባቸው ባህርያት አሉ፡፡ የስራ ሰዓታቸው ሌሊት ነው፤ ወጣቶችን፣ ከሌላ ቦታ የመጡ እንግዶችን፣ ውጪ አገር የኖሩ ኢትዮጵያውያንን አስበው የሚሰሩ ናቸው፡፡ በእነዚህ ቤቶች የማንኛውም መጠጥ ዋጋ ሌሎች መጠጥ ቤቶች ከሚሸጡበት

በአጥፍና ከዚያ በላይ ነው፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንዳሉት በምሽት ቤቶቹ የሚታደሙ ሰዎች ደህና የመክፈል አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ አዝማሪዎች በእነዚህ ቤቶች ሲከውኑ በርካታ ሽልማቶችን ያገኛሉ፡፡ ያ ሊሆን የሚችለው ግን ታዳሚውን ማስደሰት የቻሉ እንደሁ ነው፡፡

እንዳልካቸው የተባለ መረጃ ሰጪዬ እንዳለው የባህል ምሽት ቤት ደንበኞች «ለየት ያለ ነገር» ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ ክዋኔው የግድ የታዳሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት አዝማሪው ለራሱም ሆነ ለምሽት ቤቱ ገቢ ለማስገኘት የታዳሚውን ፍላጎት መጠበቅ አለበት፡፡ ከታዳሚ የሚመጣው ሽልማት ካልታከለበት በስተቀር ከምሽት ቤቱ የሚገኘው ደሞዝ ለኑሮ በቂ አይደለም፡፡ ስለዚህ የደንበኛን ፍላጎት መሰረት ያደረገ «ለየት ያለ ነገር» ማቅረብ ጥሩ ገቢ ማግኘት ነውና እሱ ሁኔታ እየተከወነ ነው፡፡ ከእነዚህ ለየት ያሉ ከሚባሉ ነገሮች ውስጥ አብዛኛው ማህበረሰብ ፀያፍ የሚላቸውን ቃላት መጠቀም የሚለው ዋናው ነው፡፡

የሚከወኑ ግጥሞች ሳቅን ለመፍጠር ሲባል የሚቀርቡ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ማህበረሰቡ ‹‹ነውር ናቸው›› የሚላቸውን ቃላትና ሐሳብ የያዙ ናቸው፡፡ ይህንን የግጥም አከዋወን ከአዝማሪዎች ይልቅ ታዳሚው የሚፈልገው ይመስላል፡፡ ለምሳሌ ደሴ ከተማ ‹‹ቃተኛ›› ተብሎ በሚጠራ ባህላዊ ምሽት ቤት አዝማሪው ክዋኔውን በዘለሰኛ ጀምሮ ዜማውን በመቀየር የተለያዩ ግጥሞችን ሲከውን አብዛኛው ታዳሚ በራሱ ወሬ ተጠምዶ የሚያዳምጠው አይመስልም፡፡ ይህንን የተገነዘበው አዝማሪ ታዳሚው ትኩረቱን ወደ እሱ እንዲያዞር ሲል፡-*የዘሬ ነው ብሎ ይፋጃል በርበሬ/ መች ተስማምቶ ያውቃል ማሲንቆና ወሬ* ፣ የሚል ግጥም ቢገጥም እንኳን ታዳሚውን ወደራሱ መመለስ ተቸግሮ ቆዬ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን የግጥሞችን ይዘት በመቀየር በአብዛኛው ሰው ዘንድ አይነኬ የሚባል ይዘት ያላቸው ግጥሞችን መከወን ሲጀምር ወዲያውኑ የቤቱ ድባብ ተቀየረ፡፡ የየራሱን ወሬ ይዞ የነበረው ታዳሚ ሁሉ ትኩረቱን ወደ አዝማሪው በማድረግ ግጥሞችን በሳቅ እያጀበ፣ በእጁ እያጨበጨበ ያዳምጥ ነበር፡፡ በሰዓቱ በአዝማሪው ሲከወኑ ከነበሩ ግጥሞች ውስጥ፡-

ሳሚዬ ሳሚካ(የአንድ ታዳሚ ስም)
ትወዳለህ አሉ ማታ ነካ ነካ

አዝማሪው አንድን ታዳሚ ፊት ለፊት እየተመለከተ ነው ይህንን ግጥም የተጫወተው፡፡ በአዝማሪውና ስሙ «ሳሚዬ» ተብሎ በተጠራው ታዳሚ መካከል ምናልባት የቀደመ ዕውቀት ሳይኖር አይቀርም፡፡

የጦሳን አቀበት አትወጣውም ዶሮ
ክላሽ የማይበሳው ቂጥ አየሁ ዘንድሮ

ለአዝማሪው ይህንን ግጥም መግጠም ምክንያቱ ከውጪ ወደ ውስጥ የሚገቡ ሴቶች ናቸው፡፡ ይህ ግጥም በሚገጠምበት ጊዜ የአብዛኛው ታዳሚ ትኩረት ወደሴቶች ዞሮ ነበር፡፡ ብዙው ሰው አዝማሪውን በሳቅ ያጅበው ነበር፡፡

ጠጪለት ጠጪለት አንድ ካሳ ቢራ
ከፍ በይ ዝቅ በይ ማታ አለብሽ ስራ

አንድ ላይ ተቀምጠው ቢራ እየጠጡ በመዝናናት ላይ የነበሩ ሴትና ወንድ ታዳሚዎችን እያየ የገጠመው ግጥም ነው፡፡ አዝማሪው በዚህ ግጥሙ የሚጠቁመው በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለው ግንኙት የፆታዊ ተራክቦ መሆኑን፣ ወንዱ ሴቷን እየጋበዘ እንደሆነ ሴቷ ደግሞ ለተደረገላት ግብዣ መመለስ የሚገባት ግዴታ እንዳለ ነው፡፡

መረጃ ሰጪው የቃላት አጠቃቀሙን አስመልክቶ ላቀረብሁለት ጥያቄ የሰጠኝ ምላሽ ‹‹ያንን ካላልሽ ገቢያ አይኖርም፡፡ እኔ ማንኛውንም ግጥም የምገጥም ገንዘብ ለማግኘት ነው፡፡ ጥያቄው ምን ብል እሸለማለሁ ነው›› መረጃው ከታዳሚዎች የሚገኘው ገቢ በዘፈን መከወኛ ቦታዎችና በአከዋወን ልምዱ ላይ ተፅዕኖ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

የዘፈን መከወኛ አውዶችን አስመልክቶ ጥንት በነበሩት ላይ ከታዩ መጠነኛ ለውጦች ባሻገር አዲስ የአዝማሪ ዘፈን መከወኛ አውድ ተፈጥሯል፡፡ ይህ አውድ የስብሰባ አዳራሽ ነው፡፡ በስብሰባ አዳራሽ ዘፈናቸውን የሚከውኑ አዝማሪዎች በራሳቸውና ልማዳዊ በሆነው መንገድ ዘፈንን እየከወኑ የሚኖሩ አይደሉም፡፡ ይልቁንስ የየወረዳዎች ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅ/ቤቶች ባቋቋሟቸው የባህላዊ የሙዚቃ ቡድኖች ውስጥ በመሰንቆ

ተጫዋቺነት የተቀጠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ አዝማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ብቻቸውን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሌሎች የባህል ቡድን አባላት ጋር በመሆን በፖለቲካ ምክንያት በሚደረጉ ስብሰባዎችና በአንዳንድ ከሌላ ቦታ ለሚመጡ እንግዶች በሚደረጉ የአቀባበል ስርዓቶች ላይ በመገኘት የዘፈን ክዋኔያቸውን ያቀርባሉ፡፡ የግጥሞቹ ይዘት አልፎ አልፎ ቢቀላቀልበትም የስብሰባውን አጀንዳ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ለምሳሌ በእንደዚህ አይነት አላማ በተዘጋጀ ‹‹የ2005 ዓ.ም የአምባሰል ወረዳ ወረዳና ቀበሌ የምርጫ ዕቅድ ትውውቅ›› ለመድረኩ መክፈቻ እንዲሆን የተዘጋጀ የአዝማሪ ዘፈን ነበር፡፡ በቦታውም አበባው ሙሉጌታ የተባለ አዝማሪ፣ ሞላ ተገኝ የተባለ ባልንጀራውን በመሰንቆ አጅቦ የዘፈን ክዋኔ አቅርበዋል፡፡ የግጥሞቹ ይዘት ‹‹ልማት አስፈላጊ እንደሆነ ››፣ ‹‹አባይን መገደብ የመንግስት ዋና አላማ እንደሆነና ይህንን ለማድረግ ሃገሪቱ ትልቅ አቅም ያላት እንደሆነ›› የሚገልፁ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ግብር፣ መንደሮች፣ ገበያ፣ መጠጥ ቤቶች፣ የታቦት ንግስ፣ ተዝካር፣ ሰርግ፣ ድግስ ቤቶች፣ ጦርነት የወሎ አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑባቸው የታወቁ ልማዳዊ አውዶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ቦታዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ከጥንት አንስቶ አሁንም ድረስ ያሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ሰበበ ክዋኔያቸው በመጥፋቱ የተነሳ ጠፍተዋል፡፡ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ካሉ አውዶች ውስጥ መጠጥና ድግስ ቤቶች፣ ታቦት ንግስ፣ ተዝካርና ሰርግ የሚሉት የሚጠቀሱ ሲሆን በሰበበ ክዋኔያቸው መጥፋት የተነሳ የጠፉት ደግሞ ገበያ፣ ግብርና ጦርነት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ቤት ለቤት የሚደረግ ክዋኔ ዛሬም ድረስ አልፎ አልፎ በመከወን ላይ የሚገኝ ሲሆን የስብሰባ ቦታ ደግሞ አዲስ የተፈጠረ አውድ ሆኗል፡፡ ሌላ በወሎ አዝማሪዎች ዘፈን ልምድ ውስጥ የተከሰተ ለውጥ የግጥሞች ይዘትና ቅርፅ ለውጥ ነው፡፡

### 6.2.2.3. የግጥሞች ይዘትና ቅርፅ

ይዘት በአንድ የኪነጥበብ ስራ ውስጥ የሚተላለፍ መልዕክት ሲሆን ቅርፅ ደግሞ በኪነጥበብ ውጤቱ ውስጥ ያለው መልዕክት የሚተላለፍበት መንገድ ነው፡፡ ከያኒያን በኪነት ስራቸው ውስጥ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በማንሳት መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ፡፡ የኪነጥበቡን ባህርይና የግል ፈጠራቸውን መሰረት አድርገው ለመልዕክቱ ማስተላለፊያ የሚሆናቸውን መንገድ ይጠቀማሉ፡፡ የአዝማሪ ግጥም ኪነጥበብ እንደመሆኑ የራሱ የሆነ ይዘትና ቅርፅ አለው፡፡ ይህ ይዘትና ቅርፅ ደግሞ አብዛኛው ማህበረሰብ የሚያውቀውና ምንነቱን የሚገልፀው

ነው። ይሁንና መረጃዎች የሚያሳዩት ዛሬ በሚከወኑ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘትና ቅርፅ ላይ የይዘትና ቅርፅ ለውጥ መኖሩን ነው። የለውጡ ሁኔታ ቀጥሎ ቀርቧል።

## 6.2.2.3.1. የግጥሞች ይዘት ለውጦች

ግጥም የአዝማሪ ማንነት ከሚገለፅባቸው ዋናዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው። አንድ አዝማሪ ጥሩ አዝማሪ ነው ተብሎ ሊገለፅ የሚችለው ከጥሩ ድምፃዊነቱና ከቅኝት አዋቂነቱ በተጨማሪ ጥሩ ግጥም የመግጠም ችሎታ ሲኖረው ነው። የመግጠም ችሎታ ለአውዱ የሚስማማን ግጥም ወዲያው ከመፍጠር አለዚያ አስታውሶ ከማለት ጋር ይያያዛል። ብዙ አዝማሪዎች ይህንን ለመሆን ጥረት ያደርጉ ነበር። ምክንያቱም አውድን መሰረት አድርገው የሚገጠሙ ግጥሞች የአዝማሪውን ጉብዝና ከመግለፃቸው በተጨማሪ ዘመን ተሻጋሪ ይሆናሉ። ዛሬ ላይ የወሎን ታሪክ መዝግበው የሚገኙ የአዝማሪ ግጥሞች የመልዕክታቸው ምንጩ አውዳዊነታቸው ነው። ለምሳሌ በተፈሪ መኮንንና በራስ ጉግሳ ወሌ መካከል የነበረውን የግጭት ሂደት፡-

ከኛይቱ ወረቀት ያልፈረመ የለም
መላው ታጥቆ ገባ ግዴለም ግዴለም
ትግሬም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት
ጎጃምም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት
የወሌውን ጉግሳ ሞኙን የኔ ጌታ መፈተኛ አርጎት

ሲሉ የራስ ጉግሳ ወሌ አዝማሪ የነበሩት ምስጋናው አዱኛ እንደገለፁት (ባህሩ፣ 1999-147) ፅፈዋል። ነገሩ እንዲህ ነው፡- ራስ ጉግሳ ወሌ ( የዘውዲቱ ባል) ከሃይለ ስላሴ ጋር በገጠሙት ጦርነት (ጉግሳን ለአመፅ በመጎትጎቱ ላይ የጣሊያኖቹና የጎረቤቶቹ የጎጃሙ በራስ ሃይሉና የትግሬው ራስ ስዩም ሚና ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም። የጉግሳ ዕጣ የሚያዝነው ግን ኃይሉና ስዩም መጎትጎቱ ላይ እንጅ አብሮ መሰለፉ ላይ አለመኖራቸው ነው። ቆቅ ስለሆኑ ሃይ ሃይ ብለው አስነስተው ጦርነት አፍጥጦ ሲመጣ ገሸሽ አሉ። ይህንን ሁኔታ ነው አዝማሪው የተናገሩት። እኚሁ አዝማሪ ራስ ጉግሳ የወደቁበትን ቦታም እንዲህ ገልፀውታል።

በሴት ስም ቢጠሩሽ ምን ያስኮርፍሻል
አንቺም ክፉ ሰው ነሽ ሃያል ሰው ገለሻል (መላክ ታረቀ፣ ቃለመጠይቅ፣ 27/05/2005 ዓ.ም፣ ክትክታ ለበስ)፡፡

‹‹አንችም›› ራስ ጉግሳ የሞቱባት ቦታ ናት፡፡ ሰሜን ወሎ ውስጥ ቀለባስ በተባለው ቀበሌ ክትክታ መንደር አካባቢ ትገኛለች፡፡ በዚህ መልኩ በርካታ ታሪክን የተሸከሙ አውዳዊ ግጥሞች በቀደምት አዝማሪዎች ይገጠሙ ነበር፡፡ ግጥሞቹ ታሪክ ብቻ ሳይሆን እንደ ታዳሚዎቻቸውና እንደ አውዱ ሁኔታ ሌሎች የህይወት ገፆችንም ይመለከታሉ፡፡ ከዚህ ረገድ ቀደም ባለው ጊዜ ይገጠሙ የነበሩ ግጥሞች ናቸው ተብለው በመረጃ ሰጪዎች የተመሰከረላቸው ቃልግጥም በአግባቡ ተጠንተው ከይዘታቸው አንፃር ሲመደቡ ሃይማኖትና ስነምግባር፣ የአካባቢ ገለፃ፣ የሴት ልጅ ውበት፣ የሃገር ፍቅር፣ የስራ ክቡርነት በአጠቃላይ የጊዜውን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት በሙሉ የሚዳስሱ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ የተገለፀው ሃሳብ በጥቂት ምሳሌዎች ተደግፎ ቀርቧል፡፡

## ሃይማኖትና ስነምግባርን የሚገልፁ ቃልግጥም

ሃይማኖትና ስነምግባር የአንድ ማህበረሰብ መለያ እሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች ማህበረሰቡ በአዎንታ ጎናቸው የተቀበላቸው ስለሆኑ እርሱ ይዟቸው እንደቆየ ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲሸጋገሩለት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል፡፡ የወሎ ማህበረሰብም ሃይማኖቱና ስነምግባሩ በአዝማሪ ግጥሞች አማካኝነት ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገሩለት መቆየቱን ቀጥሎ ከቀረቡ ቃልግጥም መረዳት ተችሏል፡፡

ሀ.ወልድ በራስህ ኮርተህ
ከሰማይ ሰማያት ወርደህ
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
አብ አይበልጥም ወይ አባትህ
ተለማኝ እናትህ

ለ. ወላዲት አምላክ በእርጉዟ
አዝና ነበረ ተክዛ
እግዚአብሔር ያጥናሽ አልናት ወይ
ወልዳ አልሞታትም ወይ

እነዚህ ቃልግጥም ሲከወኑ የተገኙት በአምባሰል ወረዳ ማርዬ ቀበሌ ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ ከዋኝ ብርሃን ትኩ የተባሉ የሰማንያ ሁለት ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡ ከዋኙ ቃልግጥምን ያቀረቧቸው የዘፈን ክዋኔዎች ሁሉ መጀመሪያ አድርገው ነው፡፡ ይህንንም አምላክን የሚያመሰግኑና ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ግጥሞች መጀመሪያ መከወን በአዝማሪ ዘፈን ክዋኔ ውስጥ ደንብ ነው በማለት ምክንያቱን አስረድተዋል፡፡ ከዋኙ ግጥሞችን በሚከውኑበት ጊዜ ወንበር ላይ ተቀምጠው፣ አብዛኛውን ጊዜ አይኖቻቸውን እየጨፈኑና ከአፋቸው ለሚወጡ ቃላት ክብር የሚሰጥ በሚመስል ሁኔታ እየተመሰጡ ነበር፡፡ በክዋኔው ውስጥ አዝማሪ የሆኑና ያልሆኑ ታዳሚዎች ነበሩ፡፡ ከሁሉም ወገን ያሉ ብዙ ታዳሚዎች ክዋኔው በሚካሄድበት ጊዜ በፀጥታ ግጥሞችን ያደምጡ ነበር፡፡ ግጥሞች በመዲናና ዘለሰኛ ዜማዎች የተባሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ዜማዎች ደግሞ አስቀድሞ የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን መልክ በሚለው ክፍል እንደተገለፀው ሃይማኖትና ስነምግባር የሚሰብኩ ግጥሞች የሚቀርቡባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በእነዚህ ከላይ በቀረቡ ቅኔያዊ ግጥሞች ሃይማኖት ሲሰበክ ይታያል፡፡ ቃል ግጥም ‹‹ሀ›› እግዚአብሔር ወልድ በራሱ ስልጣን ከሰማይ ወርዶ፣ ከድንግል ማርያም እንደተወለደ ይገልፃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ገጣሚው እግዚአብሔር ወልድን በሰማይ ካለው ባለስልጣን አባትህ ይልቅ እንዴት ደሃ እናትህን መረጥህ ሲል ይጠይቃል፡፡ ቃል ግጥም ‹‹ለ› ደግሞ ድንግል ማርያም ልጅ ወልዳ ስለሞተባት እንዳዘነች ይገልፃል፡፡

እነዚህ ቃልግጥም ቅኔያዊ ግጥሞች ናቸው፡፡ ገጣሚው ከላይ የተገለፁትን የግጥሞችን የላይ ትርጉም ተገን አድርጎ በቃል ግጥም ‹‹ሀ›› የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆንና እሱን የወለደችው ድንግል ማርያም ደግሞ አምላክን በመውለዷ የተነሳ ‹‹የምትለመን››/ ባለፀጋ መሆኗን፣በቃል ግጥም ‹‹ለ›› ደግሞ እግዚአብሔር ወልድ መሞቱ ተሰብኳል፡፡ ይህ ዕውቀትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ‹‹ሚስጥረ ስላሴ›› ከተሰኘው‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች /የሰው ልጆችን ለማዳን ሲል ከሰማይ ወርዶ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍፁም ሰው ሆነ::

በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን ተቀበለ፡፡ ሞተ ተቀበረ . . .›› ውዳሴ ማርያም፣1993 ዓ.ም ) ከሚለው አስተምህሮ የተቀዳ ነው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ በበገናና ዘለሰኛ ዜማዎች ስነምግባር የሚሰበክባቸው ግጥሞች ይገጠማሉ፡፡ ቀጥለው ያሉት ግጥሞች ለዚህ አባባል ማስረጃዎች ናቸው፡፡

ሐ. እናት አባቴ ማለት
እት ወንድሜ ማለት
ሳይታመም ነው ሳይሞት
ከሞተ ወዲያ ዋይ ዋይ
ላፈር ለዲንጋዩ ነው ወይ፡፡

መ. ሁለት ኮረቻ ተሰቅሎ የፈረስና የበቅሎ
ያንን ኮረቻ ስታነሱ መርገፍ አለና እንዳትረሱ፡፡

ቃል ግጥሞቹ በአቀስታ ወረዳ፣ ኢላዳ ቀበሌ፣ በረከት መንደር ሲከወኑ የተገኙ ናቸው፡፡ የግጥሞቹ ከዋኝ ግጥሞቹን የከወኗቸው በዘለሰኛ ዜማ ነው፡፡ ግጥሞቹ ሲከወኑ የከዋኙ ቤተሰቦች፣ እንዲሁም ጎረቤቶች በዙሪያው ተሰብስበው ያዳምጡ ነበር፡፡ ከዋኙ ዜማዎችን በማስተማር ድምፀት ያቀርቧቸው የነበረ ሲሆን ታዳሚዎች ደግሞ አፀፌታውን መመሰጣቸውን በሚገልፅ መልኩ መላ ትኩረታቸውን ወደ ከዋኙ በማድረግና አንገታቸውን በመነቅነቅ ይገልፁ ነበር፡፡

እነዚህ ቃልግጥም ሰዎች በምድር ላይ ሲኖሩ በምን ሁኔታ ሊኖሩ እንደሚገባቸው ያስተምራሉ፡፡ ለምሳሌ በመጀመሪው ቃል ግጥም የሰው ልጅ ከሞተ በኂላ ልክ እንደ አፈርና ድንጋይ ግዑዝ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች ሊረዳዱ የሚገባቸው በህይወት እያሉ ነው፡፡ ከሞቱ በኂላ እነሱን እያነሱ ማልቀስ ለአፈርና ለድንጋይ እንደማልቀስ ነው ይላል፡፡ በቀጣዩ ቃል ግጥም የቀረበው ስነምግባራዊ ትምህርት ደግሞ ሰዎች በህይወት ሲኖሩ አንድ ቀን መሞት እንደማይቀር እያሰባችሁ ኑሩ የሚል ነው፡፡ ገጣሚውን ይህንን ሃሳብ ለማስተላለፍ ‹‹መርገፍ›› የሚል ቃል ተጠቅሟል፡፡ በግጥሙ አውድ ውስጥ ‹‹መርገፍ›› ለሚጋለቡ ፈረስና በቅሎዎች የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ እናም ገጣሚው በዚህ ቅኔያዊ ግጥሙ ሰዎች ሞትን አስበው ጥሩ እንዲሆኑ ይሰብካል፡፡ ሃይማኖትና

ስነምግባርን የሚሰብኩ ግጥሞች በመዲናና ዘለሰኛ ብቻ ሳይሆን በትዝታ፣ አምባሰል፣ ባቲና አንቺ ሆዬ ቅኝቶችም ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

ሀ. ያልሁሽን ብትሰሚ ያልሽኝን ብሰማ
መቼ ያገኘን ነበር የትዳር ጠማማ

ለ. ያሳለፍኳት ጊዜ ቀልድ እየመሰለች
እንደቀለድሁባት ቀልዳብኝ ሄደች

እነዚህ ሁለት ቃልግጥም ጢሳ አባ ሊማ ውስጥ አባ ደምሴ አበበ የተባሉ አዛውንት መረጃ አቀባይ በአንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ሲከውኗቸው የተገኙ ናቸው፡፡ መረጃ ሰጪው ቃልግጥምን ይከውኗቸው የነበሩ በትዝታ ዜማ ነው፡፡ በቦታው ሰባት ያህል ታዳሚዎች ነበሩ፡፡ ሁሉም ታዳሚዎች አዝማሪ ካልሆነ ቤተሰብ የመጡ ናቸው፡፡ ገጣሚው እነዚህንና ሌሎችን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ህይወት የሚዳስሱ ግጥሞችን በማስታወስና ከታዳሚዎች በመቀበል በተዘበራረቀ ቅደም ተከተል ያቀርባሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምናልባት የታዳሚዎች ልዩነት ሊሆን እንደሚችል መገመት የሚያስችሉ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ምክንያቱም በቦታው አጥኝዋን ጨምሮ ከዋኙ የማያውቋቸው ሶስት ታዳሚዎች የነበሩ ሲሆን የእነዚህን ታዳሚዎች ማንነት አለማወቃቸው የግጥሞቻቸውን ፍሰት አንድ መልክ እንዳይዝና አዝማሪው የሚያውቋቸውን ግጥሞች ሁሉ እንዲያሳዩ ተፅዕኖ የፈጠረባቸው ይመስላል፡፡ ከተከወኑት ግጥሞች ውስጥ በርካታ ስነምግባርን የሚገልፁ ግጥሞች የነበሩ ሲሆን ለእነዚህ ምሳሌ ይሆናሉ ተብለው ከላይ የቀረቡት ግጥሞቹ ይዘት ሲታይ በግጥም ‹‹ሀ›› በባልና ሚስት መካከል መደማመጥ ሊኖር የሚገባ መሆኑን በግጥም ‹‹ለ›› ደግሞ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ ያ ሳይሆን ሲቀር ግን ህይወት በከንቱ እንደሚቀር ተገልፆአል፡፡

## አካባቢን የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. ባቲ ጎድጓዳ ነው አይታይም ጪሱ
በሽንጣም አውቶብስ እዛው ካልደረሱ

ለ. አንቻሮ ቀረና ገርቢ ተገበየ
ቀረ ወዳጅ ዘመድ እንደተለያየ

ሐ. አንባሰል ለገደል ምን ያሸሚጥጡታል
ፈረስ ባያስጋልብ ሰው ይወጣበታል
ግማደ መስቀሉ ተቀምጦበታል፡፡

እነዚህ ቃልግጥም ደሴ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አዝማሪዎች ሲከውኗቸው የተገኙ ናቸው፡፡ ግጥሞቹ ብዙ የተለመዱ በሚመስል ሁኔታ በርካታ ቁጥር ያላቸው አዝማሪዎች እነዚህን ግጥሞች ይከውኗቸዋል፡፡ እነዚህ ግጥሞች በሚከወኑበት ጊዜ የሚኖሩ ታዳሚዎችም ግጥሞችን አብረው ሲከውኑ ይታያል፡፡ ለምሳሌ እነዚህ ግጥሞች ወሎ ውስጥ ስለሚገኙ ሶስት ቦታዎች መልክዓምድራዊና ማህበራዊ ሁኔታ ይገልፃሉ፡፡ የመጀመሪያው ቃል ግጥም ባቲ ተብሎ ስለሚጠራው የወሎ አንድ ክፍል መልክዓ ምድር ይገልፃል፡፡ ባቲ ደቡብ ወሎ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ አካባቢ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ጎድጓዳ መሆኑን ስለ አካባቢውን የተፃፉ የተለያዩ ፅሁፎች ገልፀዋል፡፡ በዚህ ግጥምም ይኸው የአካባቢው ባህርይ ተገልፆአል፡፡ ወረዳው ጎድጓዳ ቦታ በመሆኑ በውስጡ የሚገኙ መንደሮች/ሰፈሮች እዛው ካልተገባ በስተቀር በሩቅ አይታዩም፡፡ ስለዚህ ባቲ ውስጥ የሚገኙ መንደሮችን ለማየት የግድ እዛው መሄድ ያስፈልጋል፣ መሄድ የሚቻለውም በአውቶብስ ነው ይላል፡፡ ይህ ግጥም ወደ ቦታው መሄድ ያለበት በአውቶብስ ነው ብሎ ሲናገር ሌሎች መጓጓዣዎች የሉም ማለቱ አይደለም፡፡ ነገር ግን ገጣሚው ለማስተላለፍ የፈለገው ዋና ጉዳይ አካባቢው የመኪና መንገድ የተሰራለት መሆኑን ነው፡፡

ቀጣዩ ግጥም ደግሞ በአንድ ወቅት የተደረገን የገበያ ቦታ ዝውውር ይገልፃል፡፡ ይኸውም አንቻሮ ውስጥ የነበረው ገበያ ገርቢ ወደተባለው አካባቢ መዞሩን ያሳያል፡፡ ገርቢ አንቻሮ ውስጥ የሚገኝ አካባቢ ነው፡፡ መረጃዎች እንዳሉት አንድ ወቅት አንቻሮ ይባል የነበረ ገበያ ነበረ፡፡ በኋላ ላይ በአስተዳደራዊ ምክንያት ገበያው ወደ ገርቢ ዞረ፡፡ ይህን ጊዜ ታዲያ የቦታ ለውጡ በአካባቢው ነዋሪዎች ማህበራዊ ህይወት ላይ ተፅዕኖ ፈጠረ፡፡ በገበያ ሰበብ (ምክንያት) አንቻሮ ውስጥ ይገናኙ የነበሩ ሰዎች ገበያው ወደ ሌላ ቦታ (ገርቢ) በመሄዱ ምክንያት መለያየታቸውን በዚህ የተነሳ ነባር ወዳጅነት መቅረቱን ግጥሙ ያሳያል፡፡

ሶስተኛውና ስለአምባሰል ወረዳ የሚገልፀው ግጥም ደግሞ የአምባሰል ወረዳ በገደላማነቱ የተነሳ ፈረስ የማያስጋልብ መሆኑን ይገልፅና ነገር ግን በዚህ ዝቅ ተደርጎ ሊታይ እንደማይገባው ይናገራል፡፡ ምክንያቱም መረጃው እንደሚለው አምባሰል ፈረስ ከማስጋለብ የተሻሉ ገፅታዎች እንዳሉት ያሳያል፡፡ መልካም ሰዎችን ያፈራ (ይኸም የእቴጌ መነን የትውልድ ስፍራ በመሆኑ የተባለ ነው) እንደሆነና ክርስቶስ የተሰቀለበት አንደኛው ክንፍ ነው ተብሎ የሚታመንበት መስቀል በስፍራው የሚገኝ መሆኑን ይገልፃል፡፡ እነዚህ ጉዳዮችም ቦታውን የተከበረና ቅዱስ ያደረጉት በመሆኑ ከእነዚህ ጉዳዮች አንፃር ፈረስ አለማስጋለብ ያንን ያህል ቦታ ሊሰጠው የማይገባ መሆኑን ማስረዳት የግጥሙ ፍሬ ነገር ነው፡፡

## የሴትን ልጅ ውበት የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. ከተረከዞቿ ውሃ ጠብ ሚለው
እልፍ ብሎ ባቷ ቡችል ቡችል ያለው
ሽንጥና ዳሌዋ የቴደላደለው
አንገቷ እንደ ጠርሙስ አፈፍ ለቀቅ ያለው
ግንባሯ መስታይት የሚያጥበረብረው
ጠጉሯ ሃር ነዶ ግንፍል ግንፍል ያለው
ዋ በግድ ይለዩ ጥያት መሄዶ ነው

ለ. እግር ባቷ ገብርኤል ወገቧ ሰንበት
ይላል ቅዱስ ቅዱስ አይኗ ቲከፈት
ከእስዋ ጋር የኖረ ይገባል ገነት
ሰላም እመቤቴ የእከሌ (የሰው ስም)ሚስት

ሐ. አለፍ ብሎ  ባቷ ደብለል ደብለል ያለው
ወገቧ እንደሸቦ አፈፍ ለቀቅ ያለው
ግንባሯ መስታይት የሚያጥበረብረው
ወይ ሸዋ አፍዋ ቅመም የጥርሷ ክትር
ይበላታል አፈር አይቀርም ግብር

ቃልግጥም ሲከወኑ የተገኙት በአምባሰል ወረዳ ማርዬ ቀበሌ ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ ከዋኝ ግጥሞቹን ይከውኑ የነበረው በርካታ ታዳሚዎች በነበሩበት ነው፡፡ ከታዳሚዎቹ ውስጥ አብዛኞቹ አዝማሪዎች ሲሆኑ ከዋኑ ግጥሞችን ይከውኑ የነበረው ከሌሎች አዝማሪዎች እየተቀበሉ ነበር፡፡

በእነዚህ ቃልግጥም የሴት ልጅ ውበት ተገልጧል፡፡  በመጀመሪያው ቃል ግጥም ገጣሚው ውዳሴውን ከሴቲቱ ተረከዝ ጀምሮ ወደ ላይ በመጓዝ ባቷን፣ ሽንጥና ዳሌዋን፣ አንገቷን፣ ግንባሯንና ፀጉሯን ያደንቃል፡፡ እነዚህን አከላቶቿን ሲያወድስ ለሁሉም አቻ ምሳሌ አቅርቦላቸዋል፡፡ ይህ በመሆኑ የሴትዮዋ ውበት ለታዳሚ ጎልቶ የመታየት አቅም አለው፡፡ በሁለተኛው ግጥም ደግሞ መንፈሳዊ ማነፃፀሪያ በመስጠት የሴትዮዋ ውበት ተገልጧል፡፡ ባቷ ገብርኤል ነው ይላል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንዳሉት ገብርኤል ቁጡ ነው ይላሉ፡፡ የሴትዮዋ ባት በገብርኤል መመሰሉ ደግሞ ጠንካራነቱንና ፈርጣማነቱን ለመግለፅ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ሰንበት ደግሞ ክቡር ነው፡፡ የወገቧ ከሰንበት ጋር መመሳሰል የወገቧ ቅርፅ መጠበቅ ለውበቷ የሰጠውን መደላደላ ያሳያል፡፡ ‹‹ይላል ቅዱስ ቅዱስ አይኗ ሲከፈት›› የሚለው ሃረግ የሴትዮዋ የአይን አከፋፈት ቀስ ያለና እርጋታ ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ግጥሙ የሴትዮዋን ውበት ከቅድስና ጋር አያይዞ ይገልፃል፡፡ ይህም ሴትዮዋ እጅግ ውብ መሆኗን ለመግለፅ ሲባል የተደረገ ነው፡፡ በሶስተኛው ቃል ግጥምም ቢሆን የሚገለፅ የአንዲት ሴት እጅግ ውብ መሆን ነው፡፡ ግጥሙ ሴትዮዋ ሰው በመሆኗ ምክንያት ከሞት የማታመልጥ መሆኗን ቢጠቁምም ውበቷ እጅግ የተጋነና እርሷም እንደሌላው እምትሞት መሆኑ የሚያስቆጪ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

## የተቃራኒ ፆታ ፍቅር የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. ሃይቅና ውጫሌ መገናኛው ደቦት
ምን ትጠቀሚያለሽ አንቺን ብዬ ብሞት

ለ. ትዝ ብላኝ አልቅሼ እላለሁ ቢርበኝ
ከሆዴ ሰው ቢኖር እንዴት በታዘበኝ

ሐ. አርዳኝ ጥላኝ ሄደች ዘልዝላ ዘልዝላ
ከእንግዲህ ተነስቶ ሰው አይሆንም ብላ

ሶስቱም ቃልግጥም በታቃራኒ ፆታ መካከል ያለን ፍቅር ይገልፃሉ፡፡ በተራ ቁጥር ‹‹ሀ›› የቀረበው ግጥም አፍቃሪው ፍቅሩን አጥቶ በናፍቆት ሊሞት መድረሱን በመግለፅ ከእሱ ሞት ምንም ጥቅም የማታገኝ በመሆኑ እንድትመጣለት ይማፀናል፡፡ በሁለተኛው ግጥምም አፍቃሪው በናፍቆት ብዛት የሚያለቅስ መሆኑን ይህንን ደግሞ ሌላ ሰው እንዳያውቅበት በረሃብ እንደሚያመካኝ ይናገራል፡፡ ገጣሚው ፍቅሩ የድብቅ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በተራ ቁጥር ‹‹ሐ›› የቀረበው ግጥም እንዲሁ አፍቃሪው ከፍተኛ ፍቅር ውስጥ መውደቁን ፍቅረኛው ግን ከእርሱ እርቃ መሄዷን ይናገራል፡፡ በአጠቃላይ በእነዚህ ለዋቢነት በቀረቡ ቃልግጥም አፍቃሪዎች ለተፈቃሪዎቻቸው ፍቅርን በምን አኳኋን እንደሚገልፁ ለማየት ይቻላል፡፡

## የስራን ክቡርነት የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. በስራ ላይ ሆኖ ስራን ካከበሩ
ይመጣ የለም ወይ ገንዘብ በገዛ እግሩ
ለ. ስንፍና የሚባል የሆድ ውስጥ በሽታ
ጎልቶ ይውላል ከጠዋት እስከ ማታ
ሐ. ኧረ ስሩ ስሩ ኧረ ስሩ በጣም
ለፍቶ ያደረ ሰው ዋጋውን አያጣም
መ. ተምሮ ነው እንጂ ጥበብን መስራት
በስራ ላይ ሆኖ የለም ማቧለት

ግጥሞቹ የተገኙት ጢሳ አባ ሊማ ውስጥ ነው፡፡ ከዋኙ ለእነዚህ ግጥም መከወን ምክንያት የሆናቸው ጉዳይ ከእሳቸው ጋር የሚደረገው ውይይት ከስራ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ማወቃቸው ነው ተብሎ ይገመታል፡፡ ከዋኙ ቃል ግጥሞቹን በተለያዩ ዜማዎች እያስገቡ በተደጋጋሚ ይከውኗቸው ነበር፡፡ቃል ግጥሞቹ ስራን ማክበር ይገባል የሚል ሃሳብ የያዙ ናቸው፡፡ በመጀመሪያው ግጥም ስራን አክብረው ከሰሩ ሃብታም መሆን እንደሚቻል፣ በሁለተኛው ግጥም ደግሞ ስንፍና ከሰዎች አእምሮ ጋር የተያያዘ መጥፎ ስሜት እንደሆነ (የሆድ ውስጥ በሽታ በሚል ተገልጧል) መገለጫውም ያለስራ ተቀምጦ መዋል እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ በሶስተኛው ቃል ግጥም የሰራ ሰው ዋጋውን እንደማያጣ ተጠቁሟል፡፡ በአራተኛው ደግሞ ስራን እያሳደጉ እያበለፀጉ መስራት እንጅ ቀልድ እንደማያስፈልግ ተገልጧል፡፡

## የሃገርን ፍቅር የሚገልፁ ግጥሞች

ሀ. ኢትዮጵያ ሃገሬ ውዲቱ ውዲቱ
በሶስቱ ቀለማት የተሸለምሽቱ
አንቺን የማይረዳ ካለ በህይወቱ
በረከቱን ይንሳው እስተለተ ሞቱ

ይህ ግጥም ማርዬ ውስጥ የተገኘ ነው፡፡ አዝማሪው ግጥሞችን በሚከውንበት ጊዜ ከተለያዩ ታዳሚዎች ግጥሞች እየተሰጡት ነበር፡፡ ግጥም አቀባዮች ለአዝማሪው ግጥሞችን የሚሰጡት የውድድር መንፈስ በሚታይበት ሁኔታ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ አንድ ግጥም አቀባይ፣

የአምባሰል ጃንጥራር የደሴ ንግስት
ሰቆጣን ለዋግሹም የጁን መሳፍንት
አምላክ የፈጠራት ሁሉን አስተካክሎ
የሁላችን ሃገር ለምለሚቱ ወሎ

የሚል ግጥም ለአዝማሪ ሰጡ፡፡ ይህንን ጊዜ በቦታው ከነበሩ ታዳሚዎች ውስጥ ከሁሉም በዕድሜ የሚበልጡ ግጥም አቀባይ ከላይ የቀረበውን ስለኢትዮጵያና ሰንደቅ አላማ የሚገልፀውን  ግጥም ለአዝማሪው ሰጡ፡፡ ይህም የተወሰኑ ታዳሚዎችን የመብቀያ አካባቢ ከማወደስ ይልቅ ሁላችንም ታዳሚዎችን የሚያጠቃልል ርዕሰ ጉዳይ ለማንሳት ሲሉ ያደረጉት የሚመስል ስሜት ነበረው፡፡ ግጥሙ ገጣሚው ለሃገሩ ያለውን ፍቅር ይገልፃል፡፡ ገጣሚ የሃገሩ መገለጫ የሆነውን ባንዲራ ጠቅሶ ማንኛውም ዜጋ እንድታድጊ ሊረዳሽ፣ እንድትኖሪ ሊጠብቅሽ ይገባል፡፡ ይህንን ማድረግ ባይወድድ ግን ‹‹ብኩን ይሁን፣ሃብት አይኑረው›› ሲል ይራገማል፡፡ በአጠቃላይ ቀደም ባለው ጊዜ

በአዝማሪዎች ይገጠሙ የነበሩ ግጥሞች ይዘቶቻቸው ሲዳሰሱ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጨባጭ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ ሁኔታ የሚገልፁ ነበሩ፡፡

አሁን በሚከወኑ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘት ከቀደመው ልማድ የተለየ ባህርይ እየታየ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይም አዝማሪዎችን ለማግኘት ታስቦ በሚኬድባቸው የምሽት ቤቶች የሚከወኑ ግጥሞች ይዘት ሲመረመር አልፎ አልፎ ሰዎችን የማወደስ ይዘት ያላቸው ጥንታዊና ጥቂት ወቅታዊ የፓለቲካ ሁኔታውን የሚገልፁ ቃልግጥም የሚከወኑ ቢሆንም በዋናነት ሁለት አይነት መልክ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የመጀመሪያው ፆታዊ የፍቅር ግንኙነት የሚገለፅባቸው ሲሆኑ የእነዚህ ግጥሞች ምንጫቸው የታተሙ ካሴቶች ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ከታየባቸው ቦታዎች ውስጥ ደሴ ከተማ የሚገኝ ቃተኛ የተባለ የባህል ምሽት ቤት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ባህላዊ ምሽት ቤት ሁለት አዝማሪዎች ዘፈንን ይከውናሉ፡፡ አዝማሪዎቹ ታዳሚዎቻቸውን ለማዝናናት ከሚከውኗቸው ግጥሞች ውስጥ ግማሾቹ በካሴት የታተሙ ግጥሞች ናቸው፡፡ ታህሳስ ሰባት 2005 ዓ.ም ሲከወኑ ከነበሩ ግጥሞች ውስጥ፡-

ሀ. አይሽ አይሽና ይመጣል እንባዬ
አንቺም ወይ እድልሽ እኔም ወይ እዳዬ
የቸገረ ነገር የጠፋበት መላ
እንዴት ይለያያል ሰው ሳይጠላላ
ከአውላላው ሜዳ ላይ ፍሪዳ ተጥሎ
እንቢ አለ ቢላዋው ልብ አልቆርጥ ብሎ
ያንቺስ ቆረጠልሽ ስለት ነው መሰለኝ
እየገዘገዘ የእኔውስ እንቢ አለኝ
(ይርዳው ጤናው በ1987 ዓ.ም ካሳተመው ካሴት፡ መረጃ ሰጪው እንዳለው፣)

ለ. ስሚ ውባለም አለሜ

ገብታለች ከደሜ

አበቅ የለሽ ጎንደር ፋርጣ የኔ ገላ

ማርና ወለላ

ገዳሙ ገዳሙአገር ማለት ጎንደር ከነፋስ መውጫው

ሰው ማለት ጎንደሬ ቁም ነገረኛው (ፋሲል ደሞዝ፣2004 ያሳተመው ነጠላ ዜማ)

እነዚህ ግጥሞች ይዘታቸው ፆታዊ ፍቅር እንዲሁም የሃገር ውዳሴ ነው፡፡ ይሁንና ከካሴት የተወሰዱ በመሆናቸው የአዝማሪ ግጥሞች ብሎ ለመጥራት ይቸግራል፡፡ ይሁንና በራሳቸው በአዝማሪዎች የሚገጠሙ ግጥሞችም በምሽት ቤቶች ይከወናሉ፡፡ እነዚህ ግጥሞች ሲታዩ ትኩረታቸው የታዳሚውን አካላዊ ገፅታ በማየት የሚባሉ ትረባዎችና ወሲብ ነው፡፡ ቀጥለው ምሳሌዎች ቀርበዋል፡-

ለሁለት አይቻል እንኳንስ ለብቻ

ሃይለኛ ነው አሉ የእንዳልክዬ መምቻ

አጋጣሚ ሆኖ እዚህ ከመጣህ

የደላላ ክፊል እኔ ላጣብስህ

ብቻህን ቁጭ ብለህ ከሚደብርህ

የእኔይቱን ሽፋፋ እኔ ላጣብስህ

እንዳያልቅ አድርገህ ትመልሳለህ

አሁን ገና ገባኝ የወንድሜ ሙድ

አስተኝቶ መጥቶ ቀማቅሞ ሊሄድ

የእኛማ ብራዘር ትርፍ ጭነሃል
ትራፊክ ካገኘህ በጣም ይቀጣሃል

ጀኔፈር
ቀለምና ከንፈር
በነ መቶ አለቃ መታሰር ባልነበር
አንቺን ነበር ዛሬ አስገድዶ መድፈር

የእኛማ ወንድም ክፉ አመል አለህ
እኛ እያጫወትንህ ኮል ታበዛለህ

እንዲህም እንዲህም አይቀላውጥ አይንህ
ወይ ከመጀመሪያ ይዘህ በመጣህ

አጭር ነው ይሉታል እድሜያቸው ይጠር
ከወገቡ በታች አለው መዘውር
እንኳን አንቺንና ያስነሳል ባቡር

አጭር ነው ይላሉ ይሁን ያምርበታል
የቁመቱን ፈንታ ወደ ታች ሰጥቶታል

ምነው ባደረገኝ የሹፌር ጎረቤት
እሱ መስመር ሲሄድ እኔ ወደእሱ ቤት

በአጠቃላይ አሁን የሚከወኑ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘት ቀደም ካለው ጊዜ አንፃር ሲታይ ፍፁም የተለየ ነው ለማለት ባይቻልም በመጠን ግን ውስንነት እየተንፀባረቀበት ነው፡፡ ማለትም ቀደም ባለው ጊዜ አዝማሪዎች በተለያዩ የህይወት ክስተቶች ላይ ግጥሞችን የሚገጥሙ ሲሆን አሁን ግን አንድና ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ግጥሞችን የሚያቀርቡ ሆነዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ አዝማሪ ያልሆኑ መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልፁት ዛሬ ላይ በአዝማሪ ቤት የሚከወኑ ቃልግጥም በአመዛኙ ሲታዩ ማህበረሰቡ ለዘመናት

ከገነባው ግብረ ገባዊነት ያፈነገጠ አካሄድ በመከተል ላይ ናቸው፡፡ ይህም ከይዘት አንፃር በግጥሞች ላይ እየተካሄደ ያለውን ለውጥ የሚጠቁም ነው፡፡ ግጥሞች በይዘት ብቻ ሳይሆን በቅርፃቸውም ለውጥ እየመጣ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ቀጥሎ በቅርፅ ላይ የተከሰተው ለውጥ ቀርቧል፡-

### 6.2.2.3.2. የግጥሞች ቅርፅ ለውጦች

ምጣኔ፣ ምት፣ ዜማና ቁጥብነት የግጥም ዋና መገለጫ ቅርፆቹ መሆናቸውን የመስኩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ ምጣኔ በግጥሙ ውስጥ ባሉ ሃረጋት ውስጥ ያሉ ቀለማት እኩል መሆንን ይመለከታል፡፡ ምት ደግሞ በግጥሙ ውስጥ ያለው የቀለማት እኩል መሆን ድግግሞሽ ነው፡፡ ዜማ ድግግሞሹን ተከትሎ የሚፈጠረው ሙዚቃዊ ቃና ነው፡፡ ቁጥብነት ደግሞ በጥቂት ቃላት ብዙ ሃሳብ መያዝን ይመለከታል፡፡ ይህ ሁኔታም የተመረጡ ቃላትን ከመጠቀም ይመጣል (ተሾመ፣1997፣39) ፡፡

የአዝማሪ ግጥሞችም ግጥሞች እንደመሆናቸው እነዚህ ባህርያት አሏቸው፡፡

ይሁንና ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ በግጥሞቹ ውስጥ የተወሰኑ የቅርፅ ለውጦች እየመጡ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ መረጃ ሰጪዎች ይህንን ሲገልፁ፡-

> ማርዬ፣ ከማርዬም ውስጥ ጠጠር አምባ የምትባለው ጎጥ አለች፡፡ አዝማሪዎች በብዛት የሚገኙባት፣ ከዚህ ክልል ውስጥ ይህ የታወቀ መንደር ነው፡፡ ታላላቅ የታወቁ የቅኔ ተጫዋቾች ነበሩ፡፡ እኔም ብዙ ያልደረስሁባቸው የማስረሻ ፈንታው አባት፣ ፈንታው ጎበና ታላቅ የታወቁ ተጫዋች ነበሩ፡፡ ቅኔ ነበር የሚጫወቱ በእነሱ በዓላችን በጣም ይደምቅ ነበር፡፡ እነሱ ከሌሉ በቃ ችግር ነበር፡፡ ሰርግ በሚደረግ ጊዜ፣ ቤተክርስቲያን ታቦት በሚወጣበት ጊዜ እነዚህ እነዚህ ነገሮች ያለእነሱ በጭራሽ አይደምቁም ነበር፡፡ ያሁን ልጅ ግን መዝፈኑን ብዙም አይፈልገውም ቢዘፍንም ግጥሙ አይጥምም፡፡ ቅኔ ሚባል የለው፡፡ ልብን አይነካ (ፈንታዬ አበራ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ) ይላሉ፡፡

መረጃው ቀደምትና ወቅታዊ አዝማሪዎች የሚከውኗቸውን ቃልግጥም ያነፃፅራል፡፡ በንፅፅሩም የአሁን አዝማሪዎች የሚከውኗቸው ቃልግጥም ከበፊቶች በቅርፅ ያነሱ እንደሆነ ለዚህም መገለጫው የአሁን ግጥሞች እንደበፊቶቹ ቅኔያዊ ባህርይ የሌላቸው መሆኑን ይናገራል፡፡ ከዚህም ተነስቶ በሁለቱ በጥንታዊና በወቅታዊ አዝማሪዎች የሚከወኑ ቃልግጥም ከቃላት መረጣ አንፃር ልዩነት የተፈጠረ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቃተኛ ባህላዊ ምሽት ቤት ውስጥ እየተከወኑ የተሰበሰቡ ግጥሞች ቅርፅ  መረጃ ሰጪዎች የጥንት የአባቶቻችን ናቸው ሲሉ ከሚገልፅዋቸው ግጥሞች ጋር በንፅፅር ሲታዩ በግጥሞች ቅርፅ ላይ ለውጦች መታየታቸውን እነዚህ ለውጦችም የግጥሞች ኪነጥበባዊ ደረጃ ዝቅ እያለ መሆኑን የሚጠቁሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ ቀጥለው የቀረቡት ግጥሞች ይህንን ያሳያሉ፡፡ ግጥሞቹ በመስክ ከተሰበሰቡ በርካታ ቃልግጥም ውስጥ በነፃ ብድግ ብድጎሽ የንሞና ዘዴ የተመረጡ ናቸው፡፡

ሀ.   ወድጄሽ ብቆጣ ፍቅርሽ ቢፀናብኝ
      ቀናተኛ ብለሽ ምነው የላክሽብኝ

ለ.  አልነገርሽኝም ወይ ባላባት ነኝ ብለሽ
      እንግዲያ ዘንድሮ እዚህ አገር የለሽ

ሐ. እንደምን እንደምን ያልቅ ይሆን መንገዱ
      ልብን ወደኋላ አርገውት ሲሄዱ

መ. ሰጋሪቱ በቅሎ መስገሩን ተወችው
      ልብ ወደኋላ ሲሄድ እያየችው፡፡

እነዚህ አራት ቃልግጥም መረጃ ሰጪዎች ‹‹የአባቶቻችንን ጨዋታዎች እንጫዎትልሽ›› በሚል ገለፃ የከወኗቸው ናቸው፡፡ ቃልግጥም የግጥም ቅርፅ መገለጫ

ከሆኑ ባህርያት አንፃር ሲታዩ የሁሉም ምጣኔ በሃረግ ስድስት ቀለማትን የያዙ፣ በዚህ የተነሳም ምታቸው የተስተካከለ (ድግግሞሽ ያላቸው) ድግግሞሹ ደግሞ በተራው ሙዚቃዊ ቃና የፈጠረላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ግጥሞች እጅግ ቁጥቦች ናቸው፡፡ አብዛኞቹ በሁለት መስመር በላይ አልያዙም፡፡ እነዚህ ሁለት መስመሮች ግን ጥልቅ ሃሳብ የያዙ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የተፈጠረው ግጥሞቹ የተመሰረቱባቸው ቃላት የተመረጡ እንጅ ተራዎች ባለመሆናቸው ነው፡፡ የቃላቱ ምርጥነት ለግጥሞቹ የሰውን ስሜት የመያዝና ያለመረሳት አቅም

የአሁን ግጥሞች እንደ ይዘት ሁሉ በቅርፅ ረገድም ከቀድሞዎቹ የተለየ ባህርይ እያሳዩ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ለማሳየት ግጥሞቹ ደሴ ከተማ ቃተኛ የባህል ምሽት ቤት ውስጥ ሲከወኑ የተገኙ ግጥሞች በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ግጥሞች እንደ መጀመሪያዎቹ ከመስክ ከተሰበሰቡ በርካታ ቃልግጥም ውስጥ በነፃ ብድግ ብድጎሽ የተመረጡ ናቸው፡፡

ሀ. እግዜር ከሰራው ከሞላ አካልህ
   እስዋን የማረካት የአንገት እስካርፍህ

ለ. አፍንጫ ጎራዳ ተወደደልሽ
   እኔም ካፍንጫዬ ልጎረድልሽ
    አንቺ የኢትዮጵያ ልጅ በጣም ቆንጆ ነሽ

ሐ. ለምን ትይዋለሽ አፍንጫ ጎራዳ
      ቀምሰሽ አታውቂም ወይ የሸንኮራ አገዳ

መ. ተምሬ ነበረ እስከ አምስተኛ
     ደብተሬን ባይቀማኝ ያ ወደል ዘበኛ

ግጥሞቹ በምጣኔ በኩል ሲታዩ ከሞላ ጎደል በሃረግ ተመጣጣኝ ቀለም የያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ግጥም አምስትና ሰባት በሃረጋት ስድስት ቀለማትን የያዙና የተስተካከለ ምጣኔ

ያላቸው ናቸው፡፡ በአንፃሩ ግጥም ስድስትና ስምንት የምጣኔ መፋለስ ይታይባቸዋል፡፡ የምጣኔው መፋለስ ደግሞ በተራው የምትንና የዜማን አለመጣጣም ይፈጥራል፡፡ (በእርግጥ አዝማሪው ዜማውን ለማመጣጠን ድምፆችን በማርዘምና በማሳጠር ዘፈኑን ይጫወታል) ይህ ሁኔታ ደግሞ በቃላት መረጣ ላይ ችግር ያለ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በግጥሞቹ ውስጥ ከቀረቡ ቃላት ውስጥ የተወሰኑት ሲታዩ ግጥሙ ቤት እንዲመታ ከማድረግ በላይ ምንም ጥቅም የሌላቸው እንዲያውም የግጥሙን ሃሳብ የሚያጣጥሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አድማጪ፣ ‹‹እግዜር ከሰራው ከመላ አካልህ›› የሚለውን ስንኝ ሲሰማ ቀጥሎ በሚመጣው ስንኝ አንድ የሰውነት አካል ይጠራል ብሎ ይጠብቃል፡፡ ነገር ግን በዚህ ግጥም ውስጥ መድፊያ ሆኖ የሚመጣው ስንኝ ‹‹የአንገት እስካርፍህ›› የሚል ይሆናል፡፡ ‹‹እስካርፍ›› ደግሞ ልብስ እንጅ የሰውነት ክፍል አይደለም፡፡ ስለአፍንጫ ጎራዳነት የሚያወሩት በተራ ቁጥር ስድስትና ሰባት የቀረቡት ግጥሞችም ቢሆኑ በሙያ ተመሳሳይ ባልሆኑና አቻነት በሌላቸው ቃላት የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በተራ ቁጥር ሰባት የቀረበው፡-

ለምን ትይዋለሽ አፍንጫ ጎራዳ
ቀምሰሽ አታውቂም ወይ የሸንኮራ አገዳ

የሚል ግጥም ሲታይ አፍንጫ ጎራዳነትንና ሸንኮራ አገዳን ያነፃፅራል፡፡ በመሰረቱ ሁለት ነገሮች ለማነፃፀር በሚነፃፀሩት ነገሮች ውስጥ የባህሪ መመሳሰል ሊኖር ይገባል፡፡ በዚህ ግጥም ግን ለንፅፅር የቀረቡት ነገሮች የሚያመሳስላቸው ባህርይ የለም፡፡ ‹‹የሸንኮራ አገዳ›› የሚለው ቃል ‹‹ዳ›› የሚል ድምፅ ስላለው ብቻ ጎራዳ ከሚለው ቃል ጋር ቤት እንዲመታ ሲባል የገባ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የገጣሚውን በቃላት ምርጫ ላይ ያለመጨነቅ የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል የነበረውን የአዝማሪዎችን የዘፈን ልምድ መሰረት በማድረግ በጊዜና ቦታ አማካኝነት የተፈጠሩ ለውጦች ሲመረመሩ የዘፈን አከዋወን ደንብ (ጥንታዊና ጥብቅ ህጎችን በመተው ዘመናዊ ዘፈኖችን በመሰንቆ መጫወት) የዘፈን መከወኛ አውዶች (አዳዲስ የዘፈን መከወኛ አውዶች መፈጠር፣ የግጥሞች ይዘትና ቅርፅ ለውጥ፣ በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ልምድ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች ናቸው፡፡

## 6.3. ለወሎ አዝማሪዎች ኑሮና ዘፈን ልምድ መለወጥ ዋና ዋና ምክንያቶች

እስካሁን ድረስ በዚህ ወረቀት በተነሱ ርዕሶች ስር ስለወሎ አዝማሪዎች የስራና የህይወት ታሪክ ተከታታይነትና ለውጥ ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች በዘፈንም ሆነ በአጠቃላይ ባህላቸው በርካታ ለውጦች እየተከናወኑ እንደሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል። እነዚህ ለውጦች ደግሞ በጥቅሉ ሲታዩ የአዝማሪዎችን የዘፈን ባህል ሊያጠፉ እስከሚችሉ ድረስ ጠንካራዎች ናቸው።

በመሰረቱ ጥናቶች እንደሚያሳዩትና Sims and Stephens (2005) ም እንደሚሉት ልምድ እንዲያበቃ ወይም እንዲጠፋ የሚያደርጉ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ የድንበር ጦርነቶች፣ ሆን ተብለው የሚደረጉ የዘር ማጥፋት ተግባራት፣ በሽታ፣ ቅኝ ገዥዎች ወዘተ ልምድን በፍጥነትና በአደገኛ ሁኔታ የሚያጠፉ አስቸጋሪ ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ አንፃር ለወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ መቀየር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ። ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ የመንግስት ርዕዮተ ዓለም ለውጥ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከት፣ የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሳሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት የሚሉት ዋና ዋናዎች ናቸው። የእያንዳንዳቸው ተፅዕኖ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 6.3.1. የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከት

አዝማሪዎች የሚኖሩበት ትልቁ ማህበረሰብ አዝማሪነትን እንደ ትንሽ ሙያ ቡድኑንም እንደዝቅተኛ ሲያይ መኖሩን መረጃዎች ያሳያሉ። መረጃዎች ለዚህ አመለካከት የአዝማሪዎች የቆዬ የአኗኗር ልማድ ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ይገልፃሉ። ከላይ የአዝማሪዎች የገቢ ምንጩ ሲገለፅ እንደታየው ከጥንት ጀምሮ ለማደሪያ የሚሆናቸውን ማንኛውንም ገቢ የሚያገኙት ከሌላው ማህበረሰብ ነው። ይህም በመሆኑ ገቢ ሊያስገኟቸው በሚችሉ ቦታዎች ሁሉ ሲዞሩ ኖረዋል።

ማንኛውም ሰው ለአዝማሪ ሽልማት የሚሰጠው ላገኘው የዘፈን ግልጋሎት ቢሆንም የአኗኗር ፈሊጣቸው እነሱን ተቀባይ ሌላውን ሰው ደግሞ ሰጪ አድርጎ ማሳየቱ ስላልቀረ በሌላው አዝማሪ ባልሆነው ማህበረሰብ ዘንድ አዝማሪን «ዘዋሪ ለማኝ ተሳዳቢና ከሌላው ማህበረሰብ ጋር እኩል ያልሆነ የሚል መደብ አሰጠው»። ስለዚህም

አዝማሪ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በጋብቻና በማህበራዊ ኑሮ የማይገናኝ የተገለለ ቡድን ሆነ፡፡

ይህ ሁኔታ ምንም እንኳን ክብደቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም አሁንም ድረስ ያለ በመሆኑ ብዙ ወጣት አዝማሪዎች ‹‹አዝማሪ ነው/ናት›› መባልን የሚጠሉት ነገር እንዲሆን አድርጓል፡፡ መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ዛሬም ድረስ አዝማሪነት የመሰደቢያ ስም ነው፡፡ የአዝማሪ ልጆች የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ‹‹ ‹አዝማሪ› ብለው ይሰድቧቸዋል›› (አበባው ሙሉጌታ፣ ቃለመጠይቅ፣ 09/05/2005 ዓ.ም ውጫሌ፤ ተፈራ አበበ፣ 12/05/2005 ዓ.ም ፣ ማርዬ)፡፡

ስለዚህም በተቻለ መጠን አዝማሪነታቸውን የሚገልፁ አሻራዎችን ለማጥፋት የሚጥሩ አድርጓቸዋል፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች ውስጥም የመሰንቆ ጨዋታ አለመልመድ አንድ ጉዳይ ሆኖ ወላጆቻቸው መሰንቆ እንዳይጫወቱ መከልከልም ሌላው መገለጫ ጥረት ነው፡፡ ለምሳሌ ልጆቹ መሰንቆ መጫወቱን የማይወዱለት አንድ አዝማሪ ‹‹እንዲያውም እኛ የድሮ ሰው ሆነን ነው እንጅ የአሁን ልጆች እኮ አዝማሪነቱን አይፈልጉትም፡፡ አሁን የእኔ ልጆች ተማሪዎች ናቸው፡፡ መሰንቆ የሚያውቅ የለም፡፡ እኔም መሰንቆውን ወደ ቤት ሳስገባ በኸረጢት ሸፍኘ ሰቅዬ ነው፡፡ ቋንቋ አያውቁ፡፡ የእኛን ቋንቋ፡፡ የአዝማሪ ቋንቋ አያውቁ፡፡ እኔና ባለቤቴ ስናወጋ ምንድን ነው የምትሉት ይላሉ›› (መላኩ መድኑ፣ ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005 ዓ.ም፣ ደረቅ ወይራ)

መረጃው የሚለው ዛሬ የአዝማሪ ልጆች መሰንቆ ጨዋታ አይችሉም ነው፡፡ አለመቻል ብቻ ሳይሆን አይፈልጉም፡፡ ይህ አለመፈለጋቸው ደግሞ በእነሱ ብቻ ሳይሆን በወላጆቻቸው ችሎታ ላይም እየመጣ ነው፡፡ ከልጆቻቸው ፍላጎት ውጪ መሰንቆ የመጫወት ፍላጎት ያላቸው ወላጆችም ቢሆኑ የልጆችን ስሜት ላለመጉዳት ሲሉ መሰንቆ እንደሚጫወቱ ልጆቻቸው እንዳያውቁ ይጠነቀቃሉ፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተገኘ ሌላ መረጃ እንደሚለው ልጆች ወላጆቻቸው ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ በሚሰሩት ስራ ብቻ ሳይሆን አዝማሪዎች ዋና ስራችን በሚሉት የታቦት አጀባ ላይም ሳይቀር እንዳይገኙ ይከላከላሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት በጓደኞቻቸው ዘንድ የአዝማሪ ልጆች መሆናቸው እንዳይታወቅና እንዳይሰደቡ ሲሉ ነው፡፡ ቀጣዩ መረጃ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚለው አለ፡፡

አሁን አንቺ የእሱ ልጅ ነሽ (ካጠገቡ የተቀመጠን አዝማሪ እየጠቆመ)፡፡ አንዱ አባትሽን መሰንቆ የለህም እንዴ ሲለው ብትሰሚ ቅር አይልሽም እንዴ? ይልሻል! አይ የእኛ አባት እኮ መሰንቆ ይዞ እየለመነ ትያለሽ፡፡ እንግዲያ ያደግንበት ሙያችንን ነው፡፡ ቅድም እዚያ መሰንቆ ሲመታ ያየሽው ሰውዬ ልጅ ትናንትና አበደ፡፡ ጋሽ ሊያዋርደኝ እኮ ነው ይኸ ሰውዬ መሰንቆውን ይዞት ሄደ፡፡ ትምህርት ቤት አንተ የአዝማሪ ልጅ ሊያስብለኝ ነው አለ፡፡ እኛ እኮ ዘራችን የታወቀ ነው፡፡ አሁን ዛሬ ታቦት ማጀብ ነበረብን፡፡ ግን`ሳ እዩት ይህንን ሽማግሌ ሆነ ነገሩ፡፡ ሰርቶ አይበላም እንዴ የሚባል አማርኛ መጣ (ማስረሻ ፈንታው፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም) ፡፡

የዚህ ታሪክ ባለቤት የሆኑት አዝማሪ የጥምቀት እለት መሰንቆ ይዘው መዲናና ዘለሰኛ በመጫወት ታቦት ሲያጅቡ ውለዋል፡፡ ነገር ግን በመረጃው እንደተገለፀው አባት ታቦት ለማጀብ ብለው መሰንቆ ይዘው ሲወጡ ልጃቸው ደስ አላለውም፡፡ ልጁ የአባቱን መሰንቆ መያዝ የጠላበት ዋና ምክንያት ትምህርት ቤት ውስጥ ከጓደኞቹ የሚገጥመውን ስድብ በመፍራቱ ነው፡፡ ይህ ስሜት የአንድ ወጣት ስሜት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር መረጃ የሰጡ ብዙ ወላጆችና ወጣቶችም ሃሳቡን ይጋሩታል፡፡ አዝማሪ ተብለው መታወቅን አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም አዝማሪ ነው የሚለው ቃል ትርጓሜው እነሱን የሚያሳንስ ነው፡፡ ስለዚህም በርካታ ወጣቶች ወላጆቻቸው መሰንቆ እንዳይጫወቱ ይከለክላሉ፡፡ እነሱም ቢሆኑ በተቻለ ፍጥነት አዝማሪነታቸውን ለመቀየር በሚያስችሉ ስራዎች ላይ ለመሰማራት ከፍተኛ ትግል ላይ ናቸው፡፡ ይህም እንግዲህ የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ሙያ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት በሙያው ህልውና ላይ የፈጠረውን ተፅዕኖ የሚያሳይ ነው፡፡ ሌላው ለቡድኑ ልምድ ለውጥ ምክንያት የመንግስታት ርዕዮተ ዓለም ለውጥ ነው፡፡

### 6.3.2.የመንግስታት ርዕዮተ ዓለም ለውጥ

ጠቅለል ባለ መንገድ ሲታይ የኢትዮጵያ አዝማሪዎች ሶስት ርዕዮተ ዓለሞችን በሚከተሉ መንግስታት ስር እንደኖሩና እየኖሩ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ርዕዮተ ዓለሞች፣ ‹‹ዘውዳዊ››፣ ‹‹ሶሻሊዝም››እና አብዮታዊ ‹‹ዴሞክራሲያዊ›› ናቸው፡፡

Ashenafi (1976) «በሙዚቃ ውስጥ ያለ ለውጥ ሁልጊዜም ቢሆን በሃገሪቱ ያለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታ የሚያመጣው ነው›› ሲሉ እንደሚገልፁት ርዕዮተ ዓለሞች የየራሳቸው የሆነ አስተዳደራዊና የኢኮኖሚ ስርዓት ያላቸው በመሆኑ በአዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ህይወት ቀጥተኛ ተፅዕኖ ፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ በዘውዳዊው ስርዓተ ማህበር የአፄዎቹ ዘመን ተብሎ በሚጠራው የኢትዮጵያ የፖለቲካ አስተዳደር ወቅት አዝማሪዎቹ በቤተክህነት፣ ቤተመንግስትና በባላባቶች ቤት ውስጥ የሚዘፍኑ የሹማምንት አጫዎቾች ነበሩ፡፡ በዚህ ወቅት ማንም አዝማሪ መተዳደሪያውን የሚያገኘው በዘፋኝነቱ ብቻ ነበር፡፡ አዝማሪውም ራሱ ታላቁ የህይወት ግቡ የሹም አዝማሪ መሆን ነው፡፡ ምክንያቱም የሹም አዝማሪ ምግቡንም ሆነ ማንኛውንም ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር የሚያገኘው ከሚያገለግው ሹምና ሹሙ ከሚያስተዳድረው ማህበረሰብ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ድካም የለበትም:: በአዝማሪነቱም ተከብሮ ለመኖር ይችላል፡፡ ይህንን ለመሆን ያልቻሉት ደግሞ በተለያዩ ከተሞች በመንዝ በመጠጥ ቤቶች ውስጥ በመዝፈን ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ ኖረዋል፡፡

በዚህ ሁኔታ የቆዬው የአዝማሪዎች የዘፈንና የህይወት ልምድ ደርግ ሲመጣ ሌላ መልክ እንደያዘ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የፅሁፍ መረጃዎች እንደሚሉት ደርግ በ1966 ዓ.ም ስልጣን ይዞ 1967 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መሬት ላራሹ የታወጀበት ጊዜ ነው Bahru (2002, 240)፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ሰው የመሬት ባለቤት የመሆን እድል አጋጥሞታል፡፡ የባላባትና ጭሰኛ አኗኗር ዘይቤ ተቀይሯል፡፡ ይህ የለውጥ ሂደት እንደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ የአዝማሪዎችን ህይወትም ነክቷል፡፡ ጉዳዩን ከግምት ሳያስገቡና የተለመደውን አኗኗራቸውን ለመቀየር ባለመፈለጋቸው የተነሳ ከቀሩ በስተቀር በወቅቱ በአካባቢው የነበሩም ሆነ ለስራ በየቦታው ተበትነው የነበሩ አዝማሪዎች ሁሉ ወደ የትውልድ ሰፈራቸው በመምጣት የመሬት ባለቤት ሆኑ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በዘፈን ብቻ የመተዳደር ባህል አዳብረው የነበሩ አዝማሪዎች በእርሻና በዘፈን የሚተዳደሩበት ባህል ተጀመረ፡፡ ‹‹በደርግ ተጫዋቹ ሁሉ መሬት አገኘ፡፡ ከዚያ እነሱ ባለሁለት ገቢ ሆኑ የሚል ተቃውሞ ቢነሳም ወድዳችሁ የምትሰጧቸው በመሆኑ አይከለከሉም ስለተባለ፤ የግብርና ስራችን እንሰራለን በትርፉ ደግሞ መሰንቋችን ይዘን እንወጣለን›› በሚል በመረጃ ሰጪዎች ተገልጧል (ማስረሻ ፈንታው፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005 ዓ.ም. ማርዬ)፡፡

መረጃው አዝማሪዎች መሬት በማግኘታቸው በአንድ ገቢ ብቻ የሚተዳደረውን ገበሬ የኢኮኖሚ የበታችነት ስሜት በመፍጠሩ መሬት ማግኘታቸው ተቃውሞ ገጥሞት የነበረ

ቢሆንም እነሱግን ባለሁለት ገቢ መሆን መቻላቸውን ያሳያል፡፡ በዚህ ሁኔታ በአዝማሪና አዝማሪነት ላይ አንዳንድ ጉልህ ለውጦች ታይተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ማህበረሰቡ ለአዝማሪው ገንዘብም ሆነ ሌላ ክፍያ መስጠት ግዴታው መሆኑ ቀረ፡፡ ስለዚህም ‹‹አዝማሪ የሚዘፍነው ለራሱ ተጨማሪ ጥቅም ለማግኘት ሲል ነው›› በሚል ሃሳብ መነሻ አዝማሪው በአንዳንድ የግድ አስፈላጊ በሆኑ እንደሰርግ ባሉ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የሚሰጠው አገልግሎት እየቀረ፣ የሚያገኘው ክብርና ማህበረሰቡ ለእርሱ ያለው ፍላጎት እየቀነሰ መጣ፡፡

አዝማሪውም በበኩሉ ረጅም ጊዜውን በእርሻ ስራ የሚያጠፋ በመሆኑና ብዙ ገቢውንም ከእርሻ የሚያገኝ በመሆኑ የዘፈን ስራውን ችላ እያለ እስከመተው ደረሰ፡፡ ስራው ‹‹የአባት ነው›› ልንተወው አይገባም ያሉና ከእርሻው በተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆናቸው እንደሚችል ያመኑ አዝማሪዎች ደግሞ ከሰኔ እስከ ታህሳስ ወርየእርሻ ስራቸውን ሲያከናውኑ ይኖሩና የሰርግና የበዓላት ጊዜ ከሚጀመርበት ከታህሳስ ወር ጀምሮ እስከ ዐቢይ ፆም መግቢያ ድረስ ከአካባቢያቸው ርቀው በመጓዝ የዘፈን ስራን ይሰራሉ፡፡ ከዚያም የሚያገኙትን ገንዘብ ይዘው ወደ መኖሪያ ቀያቸው ይመለሳሉ፡፡ ይህንን የገለፁት መረጃ ሰጪዎች ‹‹የእርሻ ጊዜ እንግዲህ በሚያዝያ ያው ወደ ገመሻ እንገባለን፡፡ ግንቦት አያማ የሚባል አለ፡፡ ሰኔ ሐምሌ ዘር አለ፡፡ ከዚያ ወዲያ መስከረምን ነሐሴን እናርማለን፡፡ ህዳርና ጥቅምትን እናስገባለን፡፡ ታህሳስን ማሲንቋችንን ይዘን ስራ እንሄዳለን›› ብለዋል (ተመስገን ፈጠነና የሮም አያሌው፣ የተጠኝ ቡድን ውይይት፣ 19/05/2005 ዓ.ም. ኢላዳ/በረከት)፡፡

እነዚህ ወደ ተለያዩ ቦታዎች የሚጓዙ አዝማሪዎች ብዙዎቹ የገጠር ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ከመኖሪያ መንደራቸው አንስቶ ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች በመጓዝ ዘፈንን ይከውናሉ፡፡ ለክዋኔያቸውም ሰርግ ቤቶችን፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሚደረጉ ድግሶችንና በዓላትን ምክንያት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በዘውድ አገዛዝ ዘመን ይደረግ የነበረው አንድ አካባቢ ለአንድ ቤተሰብ የተወሰነ መሆኑ፣ በአዘቦት ቀን በየሰው ቤት እየተዞረ የሚደረገው ‹‹ልመና›› ቀረ፡፡ አዝማሪዎች በአዘቦት ቀን በመዝፈን ገንዘብ እናገኛለን ብለው አያስቡም፡፡ ማህበረሰቡም በአዘቦት ቀን አዝማሪዎችን አያስተናግድም፡፡ ይህ አይነቱ ልማድ ከዘውዳዊው ስርዓት ጋር አብሮ የቀረ ሆነ፡፡

ከዚህ ሌላ ደግሞ በደርግ ስርዓት ምክንያት በአዝማሪዎች የስራ ልምድ ላይ ከመጡ ለውጦች ውስጥ አንዱ አዝማሪዎች ቀድሞ ያደርጉት ከነበረው ግላዊ የስራ እንቅስቃሴ ወጥተው ለአብዮቱ ማገልገል መጀመራቸው ነው፡፡ ‹‹አሁን እንደገና ተይው በክበብ

እኛው ሆንን፡፡ በመሰንቆ እያጀብን ልማት የምናሰራ እኛ ሆንን፡፡ በደርግ ጥሩ ነበር ማለቴ ነው›› (ተስፋዬ በላይ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም.፣ ማርዬ) ሲሉ ይገልፁታል፡፡ መረጃው የአዝማሪዎችን ህዝባዊ ሆኖ በህዝባዊ ዘመን መኖር የሚገልፅ ሲሆን ከዚህ ህዝባዊነት መገለጫቸው ውስጥ በተለያዩ የኪነት ቡድን ውስጥ መሳተፋቸው አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዘመን አዝማሪዎች ይሳተፉባቸው ከነበሩ የኪነት ቡድኖች ውስጥ የወሎ ላሊበላ ኪነት ቡድን አንዱ ነው፡፡

‹‹የወሎ ላሊበላ ኪነት›› ከገጠር ወጥተው ከተማ ይኖሩ የነበሩ አዝማሪዎች ኑሮን ከማቅለል አንፃር ህብረት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማመን የመሰረቱት ማህበር ነው፡፡ ይህ ማህበር ይህንን ስም ከማግኘቱ በፊት ‹‹የወሎ ተጫዋቾች ማህበር በሚል ስም ነበር የተመሰረተው፡፡ ‹‹የወሎ ላሊበላ ኪነት ቡድን›› የሚለውን ስም ያገኘው ‹‹ኪነት ለልማት›› በሚለው የደርግ ሃሳብ መሰረት ሲሆን በርካታ አብዮታዊ የኪነጥበብ ስራዎችን ሲሰራ ኖሯል፡፡ ይህ ማህበር በስፋት የተንቀሳቀሰና በመላ ሃገሪቱ ስሙ ናኝቶ የነበረ ሲሆን አቶ አራጌ ይማም የተባሉ መረጃ ሰጪ እንደገለፁት ከጅምሩ ዘጠና ሁለት ያህል አባላት ይዞ ነበር፡፡ ማህበሩ ሴትና ወንድ አባላትን የነበሩት ሲሆን ሁሉም በትውልድ ከአዝማሪ ቤተሰብ የመጡ ናቸው፡፡

በዚህ መልኩ የቆየው የአዝማሪዎች የዘፈንና የኑሮናህይወት በኢህአዴግ ዘመን ደግሞ ሌላ መልክ እየያዘ መምጣቱን መረጃ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡ እንደሚሉትም በኢህአዴግ ዘመን አዝማሪዎች አዲስ የአኗኗር ብልሃትን እየፈጠሩ መጥተዋል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ጊዜው ለአዝማሪነት የተመቸ አይደለም ይላሉ፡፡ ማንኛውም የአዝማሪ ቤተሰብ ልጆቹን መሰንቆ እንዲማሩ ከመገፋፋት ይልቅ ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩለት የሚያስገድድ ሆኗል፡፡ ከአዝማሪነት ይልቅ መማር የተሻለ መሆኑን ለማሳመንም፡-

ትምርት ነው ቆንጆ ታላቅ ሹመት ማለት
መንግስት የማይሽረው ወራሽ የሌለበት

ተምሬ በነበር በጣም ተጠንቅቄ
እኔም እንደሳቸው እሾም ነበር ዛሬ

ትምርቷ ነው እንጅ አንቱ ያስባላት
እስኪ ተመልከቷት ገና ሙጫ[47] ናት

---

[47]በዕድሜ ልጅ ናት የሚል ትርጉም አለው፡፡ ግጥሙ በቀረበበት አውድ በተለይ ለመረጃ ሰብሳቢዋ የተባለ ነው፡፡

> እኔስ የተማረ ሲደኽይ አላውቅም
> ራሱን ይችላል ሌላውን ባይጠቅም
>
> (የሮም አያሌው፣ ምልከታ፣ 19/05/2005 ዓ.ም፣ በረከት)

የሚሉ ዘመናዊ ትምህርትን የሚያወድሱ ግጥሞች በየአውዱ ይከወናሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በአዝማሪነት የሚገኘው ገቢ ከዕለት ዕለት እያነሰ መምጣቱ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መንግስት በየትኛው መመሪያው አዝማሪነትን የሚከለክል ሃሳብ አላቀረበም፡፡ ነገር ግን ጊዜው ራሱ ከአዝማሪነት ጋር የማይጣጣም እየሆነ መጣ፡፡ ይህንን አቶ ማስረሻ ሲገልጡ ‹‹አሁን ግን ተይው ጊዜው እየሰለጠነ መጣ፡፡ በኢህአዴግ፡፡ ህጉ ሳይከለክል በራሳችን ጊዜ እያስከለከልነው መጣን፡፡ ህጉ አይደለም፡፡ በራሳችን ጊዜ የመከልከል ነገር መጣ›› (ቃለመጠይቅ፣ 10/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ) ብለዋል፡፡

መረጃው እንደሚለው ሰዎች ከአዝማሪ ዘፈን ይልቅ በቴፕሪከርደር የሚከፈት ሙዚቃን እያዳመጡ መዝናናትን እየመረጡ መጡ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ አዝማሪዎች ምንጊዜም የሚዘፍኑት ገንዘብ ለማግኘት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሌላው ሰው ገንዘብ የማያስወጣውን መዝናኛ ፍለጋ መሄድ ጀመረ፡፡ ይሁንና ምንም እንኳን የአብዛኛው ሰው ስሜት እንዲህ አይነቱን ሁኔታ እየመረጠ ቢሄድም ሁሉም ሰው በቴፕ መዝናናትን የሚመርጥ ባለመሆኑ የአዝማሪዎች ህልውና ጨርሶ የሚጠፋ አልሆነም፡፡ በአዝማሪዎች መዝናናትን የሚመርጡ ሰዎችም አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በተለይ በአዝማሪ መዝናናትን የሚመርጡት በቴፕ የሚዳምጡት ሙዚቃ አንድ አቅጣጫ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች ግጥሙን ከአዝማሪ መስማት ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ግጥም መስጠት የሚፈልጉ አይነትም ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ መረጃ ሰጪ ይህንን አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል፡-

> የእነሱ ትልቁ የሚለይበት፣ሙዚቃ ማዳመጥ ብቻ ነው፡፡ አንቺ የምትይውን መልሶ አያንፀባርቅልሽም፡፡ የእነሱ ግን የልብ ትርታሽን፣ ቅኔ ማስገጠም ከፈለግሽ፣ ይገጥሙልሻል ከዚያ የምትወጅውን ሰው የህይወት ታሪክ፣ የሞተውን ይሆናል ለማስታወስ፣ ያለውንም ክብሩን ለመግለፅ በእነሱ አሁን የነበረው እንትን በጣም ስሜትሽን የሚነካ ነበረ፡፡ ሙዚቃ ይኸ ሁሉ

የሉትም፡፡ እንዲያው በጣም እኔ አሁን ሳስበው መደገፍ እንደገና መታደስ ነው ያለበት ምክንያቱም የእኔን የልብ ትርታ መግለጫ ነው (ፈንታዬ አበራ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም.፣ ማርዩ)

መረጃው በቴፕሪከርደር የሚሰማው ሙዚቃ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚመጣ መሆኑንና ታዳሚው አዳማጭ ብቻ በመሆን የሚሳተፍ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የአዝማሪ ዘፈን ግን የአዝማሪው ሃሳብ ብቻ ሳይሆን የታዳሚውም ሃሳብ የሚገለፅበት ነው፡፡ በዚህና በሌሎች ባህርይው የተነሳ የአዝማሪን ጨዋታ የሚወዱ ሰዎች በመኖራቸው አዝማሪነት ጨርሶ እንዳይጠፋ ዋስትና ሆነውታል፡፡ ይሁን እንጅ የዚህ አይነት ባህርይ ያላቸው ሰዎች ቁጥር ብዙ አለመሆኑ አዝማሪው በዘፈን በቂ ገንዘብ እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡ ይህ መሆኑም አዝማሪዎች ከዘፋኝነት ወጥተው ወደሌላ ሙያ እንዲገቡ፣ ልጆቻቸውንም የተሻለ ገቢ ያመጣል ወደሚሏቸው ስራዎች እንዲሄዱ እንዲገፋፏቸው አድርጓቸዋል፡፡ ቀጣዩ ጥቅስ ይህንን ያሳያል፡፡

አሁን እኮ ስትጮሂ ብትውይ ገንዘብ የሚሰጥ የለም፡፡ አንዳንዱ መጠጥ ጠጪ ይልሻል፡፡ መጠጥ ደግሞ የእለቱን እንጅ ለልጅ ማሳደጊያ አይሆንም፡፡ ለዚያውስ ብቻውን መጠጥ ምን ሊያደርግ? አሁን የእሱ ልጅ አንዱ ሃይቅ ይማራል፡፡ አንዱ ደሴ በመንግስት ይሰራል፡፡ አንዲቱ ወታደር ሁና ትሰራለች፣ አንዲቱ ደግሞ ሃብታም አግብታ ሃይቅ ትኖራለች፡፡ እኒያን ያሳደጋቸው በጨዋታ ነው፡፡ አሁን ቢሆን እንዲህ ጨዋታ ቲቀር በምን ያስተምራቸው ኖሯል? እና በኋላ እየከፋን፣ ልጆቻችንም ደስ አልላቸው እያለ . . . አሁን ይኸ ሰውዬ እየተጫወተ ልጁ ቢመጣሳ፣ ልጅቱስ ብትመጣ እዚህ ቁጭ ብለን አንዱ ብድግ አርጎ አንተ አትዘፍንም እንዴ ቢለው ማን ይቀየማል? (ብርሃን ትኩ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዩ)፡፡

በዚህ ሁኔታ ሃገሪቱን የሚያስተዳድሩ መንግስታት ርዕዮተዓለም የተለያየ መሆኑ በአዝማሪዎች የገቢ ምንጪ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሚያሣድር ሆነ፡፡ እስከ ሃይለ ስላሴ ዘመን ለቤተክህነትና ቤተ መንግስት ግልጋሎት እንዲሰጥ ይፈለግ የነበረው

አዝማሪነት፣ በደርግ ጊዜ በምርጫ የሚከወን ተግባር ሆነ፣ አሁን ደግሞ ከመኖሩ ይልቅ አለመኖሩን የሚያበረታቱ ሁኔታዎች በዙ፡፡ በመሆኑ አዝማሪዎች መተዳደሪያ የሚሆናቸውን ገቢ ከማግኘት አንፃር ሙያቸውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚው በሚያዝዘው መንገድ ለማመቻቸት ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል፡፡ ይህንን ሁኔታ አዝማሪዎች በቀጣዩ ግጥም ይገልፁታል፡፡

እዚያ ላይ አቃንቶ እታች ሲመልሰው
እንዴት ባኗኗሩ አላውቅም ይላል ሰው
(ማስረሻ ፈንታው፣ ምልከታ፣ 12/05/2005 ዓ.ም ፣ ማርዬ)

ግጥሙ አዝማሪዎች ከፍተኛ ከተባለ የኑሮ ደረጃ ተነስተው ወደ ዝቅተኛው እንደወረዱ ይገልፃል፡፡ ይህ በመሆኑም በምቹም ሆነ ምቹ ባልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ስለኖሩ የህይወትን ገፅታዎች በደንብ ማወቃቸውን ይናገራሉ፡፡ ስለዚህም አንድም ራሳቸውን ከሁኔታዎች ጋር አመቻችተው እየኖሩ እንደሆነ አምድም ደግሞ ኑሮ ምን ማለት እንደሆነ ለሌላው ማስረዳት የሚችሉ መሆናቸው በግጥሙ ተገልጧል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ንዑስ ክፍል የመንግስታት ርዕዮተ ዓለም ልዩነት በአዝማሪዎች ህይወት ውስጥ ያመጣው ለውጥ ተብራርቷል፡፡ ከመንግስታት ርዕዮት ባሻገር ሌላው ለቡድኑ ልምድ ለውጥ ምክንያት እየሆነ ያለው ጉዳይ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ወደ አካባቢው መግባት ነው፡፡

## 6.3.3. የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት

ዛሬ የወሎ አዝማሪዎች በዋናነት የዘፈን ስራቸውን ከሚከውኑባቸውና ጥሩ ገቢ ከሚያገኙባቸው ቦታዎች ውስጥ ሰርግ፣ መጠጥ ቤቶች (ጠጅ ቤቶችና፣ አረቄ ቤቶች) ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ልማድ መሰረት ዘፈን በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ አዝማሪዎች ከእነዚህ ቦታዎች አይጠፉም፡፡ በማንኛውም የሰርግ ቦታ የአዝማሪ ጨዋታ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ መጠጥ ቤቶችም ቢሆኑ ጠጪዎችን የሚስቡትና የሚይዙት በሙዚቃ በመሆኑ ለዚሁ ለመጠጥ ማሻሻጫ ይሆናቸው ዘንድ አዝማሪዎችን መቅጠራቸው የተለመደ ተግባር ነበር፡፡

አብዛኛውን በሰርግ፣ ሁለተኛ ደግሞ እንደዚሁም በመጠጥ ቤት ኩንትራት እያዛለሁ። ድሮ ገና ከጠላ ጀምሮ ኩንትራት ይዘውኝ የነበሩ የነአባይ ቤተሰቦች ነበሩ። እዚህ ማለት ነው። ድሮ ጠላ በስልሳ ሳንቲም ይሸጡ በነበረ ጊዜ፤ የዛን ጊዜ አምስት ብር ትልቅ ብር ናት። በአምስት ብር ያዙኝ። ስል አስራ አምስት፣ ስል ሃያ ብር ገባሁ፤ ጠጁም እያደገ ሄደ። እስከ ሃያ አምስት ብር እየከፈሉኝ ስጫወት እንደፈለግሁኝ እየጠጣሁ አቅሙ በፈቀደው መጠን እንደዛ እያልን ኑረናል እስካሁን። አሁን ግን ወደ እርሻ ስራ እያዘነበልሁ ስለሆነ እየተውሁት ነው (መላኩ ካሳው፣ ቃለመጠይቅ 19/04/2005 ዓ.ም ፣ ማርዬ)

መረጃው አዝማሪዎች ከሰርግ ቤት በተጨማሪ በጠላና በጠጅ ቤት የሚሰሩ መሆኑን የገለፀ ሲሆን በአንድ ቀን ለስራ በሚውልበት ጊዜም ከስልሳ ሳንቲም ጀምሮ ቀስ በቀስ እያደገ እስከ አምስት ብር ድረስ ደርሶ የነበረ መሆኑንና አሁን ስራውን በመተው ላይ መሆኑን ገልጧል። አቶ መላኩ ብቻ ሳይሆን በርካታ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች የዚህ አይነት ልምድ አላቸው። ይሁንና ዛሬ ከሰርግ በላይ በመጠጥ ቤቶች የአዝማሪዎች ተፈላጊነት እየቀረ መምጣቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዚህም ምክንያቱ በየገጠሩ ኤሌክትሪክ መግባቱና መጠጥ ቤቶችም ከአዝማሪ ዘፈን ይልቅ የቴፕና የቴሌቭዥን ሙዚቃን በመምረጣቸው ነው። በተለያዩ የወሎ አካባቢዎች በተደረገ ምልከታም በባህላዊ መጠጥ ቤቶች አዝማሪዎች ሲዘፍኑ የማይታዩ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ መረጃ የሰጡት ባለመጠጥ ቤቶች ‹‹ቴፕና ቴሌቭዥን አንድ ጊዜ ይገዙና ሁል ጊዜ የእኛ ሆነው ይኖራሉ፤ ለአዝማሪ ግን በየቀኑ መክፈል አለብን። በዚያ ላይ መጠጥ የምንችል እኛ ነን። ስለዚህ ከወጪ አንፃር ሲታይ ያኛው አዋጪ ስለሆነ አዝማሪ ማዘፈን ትተናል። በዚያ ላይ ደግሞ ብዙ ጠጪ ከአዝማሪ ይልቅ የቪዲዮ ዘፈን ስለሚመርጥ እዚህ ከሌለ ወደ አለበት ይሄዳል። ስለዚህ ለገበያችን ስንል እሱን እንጠቀማለን ብለዋል›› (ወ/ሮ አባይ ሽመልስ፤ ቃለመጠይቅ፣ 19/05/2005 ዓ.ም፣ማርዬ)።

የቀረበው መረጃ አዝማሪዎች በመጠጥ ቤቶች ውስጥ መዝፈን ማቆማቸውን ይገልፃል። ይህም ሊሆን የቻለው ቴፕና ቴሌቭዥን በየገጠሩ በመግባታቸው ምክንያት እንደሆነ ተጠቁሟል። እነዚህ መሳሪያዎች አዲስ መሆናቸው የጠጪውን ትኩረት መሳቡ አንድ ነገር ሲሆን መጠጥ ሻጮችም ቢሆን ከወጪ አንፃር ከአዝማሪ ይልቅ ቴፕና ቴሌቭዥን

የተሻለ ነው ብለው ስለሚያስቡ የአዝማሪ ዘፈን በኤሌክትሮኒክስ እየተቀየረ ነው ብለዋል፡፡ ‹‹ሙዚቃውን ተመልከቼው፡፡ የእኔ ማሲንቆ ምንድን ነው? ቢጫወት ይሰማል? ህዝቡ ሰለጠነ፡፡ እኛ የምንጫወተው ለገንዘብ ነው፡፡ ይኽ ገንዘብ አይከፈልበትም (ቴፕ እየዘፈነ ነበር) ያን ያዳምጥ?›› ይህ ንግግር አቶ ማስረሻ ፈንታው በቴክኖሎጅ መምጣት የተነሳ አዝማሪነት ጥያቄ ውስጥ የወደቀ መሆኑን የገለፁበት ነው (ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)፡፡

ቴፕና ቴሌቭዥን ብቻ ሳይሆኑ የሞባይል ቴክኖሎጅም የአዝማሪን ዘፈን ተፈላጊነት እያቀዘቀዘው መምጣቱን መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መመልከት እንደተቻለው ጥናቱ በተደረገባቸው የገጠርም ሆነ የከተማ አካባቢዎች ብዙ ሰዎች የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ በአካባቢውም ባህል እስኪመስል ድረስ ወጣቶች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በሞባይል ስልካቸው ሙዚቃን ያዳምጣሉ፡፡ ታዲያ ይህ ሁኔታ ከሙዚቃ ክዋኔ እያስወጣቸው እንደሆነ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ አቶ ደምሴ አበበ የተባሉ መረጃ ሰጪ ከሁኔታው ጋር አያይዘው ጉዳዩን ሲያስረዱ ‹‹ዛሬማ ይኸው ቴብ መጣ፣ በየሰርጉ ቴብ ሆነ፡፡ እኛ በየት እንግባ፤ ቴብን ደግሞ ሞባይል አሸነፈችው፡፡ ልጁ ሁሉ በየመንገዱ አብሮ ይዘፈን ያዘ . . . ቀድቶ፣ ቀድቶ ይዞታል፡፡ ያንን በጆሮው ሰክቶ በቃ . . . ›› ሲሉ በየጊዜው እየተሻሻለ የመጣው ቴክኖሎጅ በአዝማሪና አዝማሪነት ላይ የፈጠረውን ተፅዕኖ ይጠቁማሉ (ቃለመጠይቅ፣ 17/04/2005ዓ.ም፣ ጢሳ አባ ሊማ/አምባሰል)፡፡

በአጠቃላይ የመንግስት ርዕዮተዓለም ለውጥ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከት፣ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት የሚሉ ነጥቦች ለወሎ አዝማሪዎችና አዝማሪነት ልምዶች መለወጥ ዋና ዋና ምክንያቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ ዛሬ ላይ ያለው የወሎ አዝማሪዎች አኗኗርና የዘፈን አከዋወን ልምድ የራሱን መልክ እንዲይዝ አድርገውታል፡፡

## 6.4. የወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር

እስከአሁን በተነሱ ርዕሶች የወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ታሪካዊ ሂደቱ ቀርቧል፡፡ በዚህ ርዕስ ደግሞ ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎች በሚሰበሰቡበትና ይህ ጥናት በሚደረግበት ወቅት አዝማሪዎች እንዴት እየኖሩ እንደሆነ የሚገልፁ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ቀደምት ርዕሶች እንዳሳዩት የወሎ አዝማሪዎች በአፄዎቹ ዘመን

በዘፋኝነት፣ ከደርግ ስልጣን መያዝ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በዘፋኝነትና በገበሬነት ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ ኖረዋል፡፡ በሁለቱም ዘመናት ማንነታቸውን በመግለፅና ለገቢ ምንጫቸው ምክንያት በመሆን ጎልቶ የሚታወቀው ዘፋኝነታቸው ነበር፡፡ ወደ ወቅታዊው የኑሮ ሁኔታቸው ሲመጣ ግን ቡድኑ ሁለት አይነት መልክ ባለው መንገድ እየኖረ ነው፡፡ የመጀመሪያው የአኗኗር መልክ ዘፋኝነት፣ ሁለተኛው ደግሞ ገበሬነትና የመንግስት ሰራተኛነት ነው፡፡

## 6.4.1. በዘፋኝነት የሚተዳደሩ

በወሎ አሁንም ድረስ ከዘፈን በሚገኝ ገቢ ብቻ የሚተዳደሩና እንደተጨማሪ ስራ ገቢያቸውን እየደጎሙ የሚኖሩ አዝማሪዎች አሉ፡፡ እነዚህ አዝማሪዎች በገጠርም ሆነ በከተማ ይገኛሉ፡፡ መረጃዎች እንደሚሉት በገጠር የሚኖሩ አዝማሪዎች ለነባሩ የዘፈን አከዋወን ልምድ ተገዥዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሰርግ ቤት ፈልጎ በማግኘት፣ በጠጅ ቤቶች በመዘዋወር ዘፈናቸውን የሚከውኑ ሲሆን የአከዋወን ስርዓታቸውም ለቅኝቶች ቅደም ተከተል ተገዥ ነው፡፡

በከተማ የሚኖሩ አዝማሪዎች ደግሞ አዝማሪነትን ወደዘመናዊው አለም በማምጣት የሙያውን ዕውቅናና የራሳቸውን የኑሮ ደረጃ በማሳደግ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አዝማሪዎች የወሎን ባህላዊ ዘፈን ለሌላው ያስተዋወቁ ጥቂት ሰዎችን ፈለግ በመከተል የሚሰሩና እነሱ ደግሞ በተራቸው ባህሉን ‹‹ለማሳደግ›› የሚሰሩ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የዚህ አይነት ዓላማ ያላቸው አዝማሪዎች ዘፈንን የሚከውኑ በሁለት ቦታዎች ነው፡፡ አንደኛው በወሎ በሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ ያሉ የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅ/ቤቶች በመሰረቷቸው የባህል ቡድኖች ውስጥ በመቀጠር የወር ደሞዝተኛ በመሆን ሲሆን ሌሎች ደግሞ በባህል ምሽት ቤቶች በመቀጠር ነው፡፡

በባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ፅህፈትቤት የሚሰሩ አዝማሪዎች ፅ/ቤቶች ካሏቸው ባህላዊ እሴቶችን የመንከባከብ አላማ አንፃር በባህል ቡድኑ ውስጥ አባል የሆኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም የአካባቢውን የዘፈን ባህል ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ ይሰራሉ፡፡

> እኔ እዚህ መስሪያ ቤት የተቀጠርሁት ባህልን ለማስተዋወቅ ነው፡፡
> የሙዚቃ ቡድኑ በተለያዩ መኪና በሚገባባቸው ገጠሮች እየዞረ

> ስለተለያዩ ጉዳዮች በሙዚቃ ያስተምራል፡፡ እኔም የቡድኑ አባል ስለሆንሁ ይህንን እየሰራሁ ነው፡፡ በግሌ ብሰራ አሁን ያለኝን ያህል ክብር አላገኝም፡፡ ምክንያቱም በግል ስሰራ የግድ ገቢዬን ለማግኘት ባልተጠራሁባቸው ቦታዎች ስለምሄድ ንቀት አለ፡፡ አሁን ግን የመንግስት ሰራተኛ ነኝ (አበባው ሙሉጌታ፣ ቃመጠይቅ፣ 14/04/2005 ውጫሌ)፡፡

መረጃው አዝማሪነት እየተከተለያለውን አንድ መንገድ ያሳያል፡፡ መረጃ ሰጪው ከኪነት ቡድን ውስጥ በመቀላቀሉ ቀደም ከነበረበት ሁኔታ በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሆነ ይናገራል፡፡ አሁን የመንግስት ሰራተኛ በመሆኑ በፊት ‹‹አዝማሪ›› ተብሎ በሚታይበት ስሜት የማይታይ መሆኑንም ይገልፃል፡፡ በዚህ ሁኔታ በሰሜንም ሆነ ደቡብ ወሎ ውስጥ ያሉ የባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤቶች በያሉበት ወረዳ የሚገኙ ወጣት አዝማሪዎችን አወዳድረው በመቅጠር በመሰረቷቸው የኪነት ቡድኖች ውስጥ እያሰሯቸው ነው፡፡ በእነዚህ የኪነት ቡድን ውስጥ የተሰማሩ አዝማሪዎች ራሳቸውን ‹‹አርቲስት›› በማለት ሲጠሩ የኪነት ቡድኑ አባላት ደግሞ ‹‹የመሰንቆ ተጫዋቾች›› ሲሉ ይጠሯቸዋል፡፡ ቡድኖችም ሆኑ በየቡድኖቹ ውስጥ ያሉ አዝማሪዎች ልምዶችን ከመጠበቅ አንፃር በጣም እንደሚተጉ ይናገራሉ፡፡ የሙዚቃ ስራቸውን የተለያዩ ዞኖች በሚያዘጋጇቸው የባህል ክዋኔዎች ውድድርና በተለያዩ ፌስቲቫሎች ይከውናሉ፡፡ የአካባቢውን ባህል ለሌላው አካባቢ ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ አዝማሪዎች መደበኛ ስራቸው ለባህል ቡድኑ መስራት ቢሆንም በግላቸው ደግሞ ካሴቶችን በማሳተም የራሳቸውን እውቅና ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ ቀጣዩ መረጃ ይህንን ያሳያል፡፡

> በፊት እሰራ የነበረ ግዳን ነው፡፡ ከዛ እንደማንኛውም ተጫዋቺ በየሰርጉ እየዞርሁ መሰንቆ እጫወት ነበር፡፡ የግዳን ባህል ቡድን ሲመሰረት በመሰንቆ ተጫዋቺነት ተቀጠርሁ፡፡ ቀጥሎ በውድድሩ ጊዜ ችሎታዬን ስላዩኝ የወልድያ ባህል ቡድን ሃላፊዎች እዚህ እንቅጠርህ አሉኝ፡፡ እሺ ብዬ ተቀጠርሁ፡፡ እኔ በዚሁ ስራዬ ማደግ ስለምፈልግ ከተማ ይሻለኛል ብዬ ነው እሺ ያልኳቸው፡፡ አሁን ወልድያ ደሞዝተኛ አርቲስት ነኝ፡፡ በግሌ ደግሞ ካሴት ለማሳተም እየሰራሁ ነው፡፡ አሁን አንድ ‹‹ማሬዋ›› የሚል ነጠላ ዜማ ለቅቂያለሁ፡፡ . . . እኔ ብቻ አይደለሁም፡፡ አሁን በየወረዳው ያለው መሰንቆ ተጫዋቺ አርቲስት

> አንዳንዱ በባህል ብቻ አንዳንዱ ደግሞ ኪቦርድና ሌሎች፣ ክራር ከሚጫወቱ አርቲስቶች ጋር በመሆንካሴት እየሰራ ነው፡፡ እንደዚያ ካልሆነ በባህል ቡድን ብቻ እየሰራን ልናድግም ሆነ ልንታወቅ አንችልም (መላክ ጫኔ፣ ቃለመጠይቅ፣ 10/04/2005 ዓ.ም፣ ቀለባስ)፡፡

መረጃው የመረጃ ሰጪውንና በእርሱ ዕድሜ የሚገኙ አዝማሪዎችን የስራ ሁኔታ ያሳያል፡፡ እንደሚለውም ወጣት አዝማሪዎች ከገጠር ወደ ከተማ በመምጣት በክበባት ውስጥ ተቀጥረው እየሰሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ ዘፈናቸውን በካሴት በማሳተም ለገበያ በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡ ይህም የአዝማሪነት ሙያው በህትመት ላይ መሆኑን ከማሳየቱ ባሻገር ባህላዊ መልኩ ‹‹ዘመናዊነት›› እየተቀላቀለበት እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

ሌሎች የወሎን ዘፈን ‹‹ወደዘመናዊው ዓለም›› በማስገባት ለመኖር የሚታገሉ ወጣቶች ደግሞ ዘፈናቸውን የሚሰሩ በባህላዊ ምሽት ቤቶች ነው፡፡ ወሎ ውስጥ በርካታ ባይሆኑም መጠጥና ምግብ የሚሸጥባቸው የተለያዩ ባህላዊ ምሽት ቤቶች አሉ፡፡ ባህላዊ ምሽት ቤቶች ባህላዊነታቸውን የሚገልፅ የራሳቸው መልክ ያላቸው ናቸው፡፡ ለደንበኛ መቀመጫ የተሰናዱ ወንበሮች፣ ለቤቶቹ ማስጌጫ የዋሉ ጌጦች፣ ደንበኛን ለማስተናገድ ወዲህ ወዲያ የሚሉ አስተናጋጆች የሚለብሷቸው ልብሶች የአካባቢውን ቀደምት ባህል የተከተሉ ናቸው፡፡ በእነዚህ ቤቶች በተለይ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ የሚቀርበው ሙዚቃ የአዝማሪ ዘፈን ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ባህላዊ የምሽት ቤቶች የጥቂት ወጣት አዝማሪዎች ወቅታዊ የስራ ቦታዎች ሆነዋል፡፡

> ድሮ ምሽት ቤት የሚባል የለም ነበር፡፡ አሁን በዚህ መንግስት የመጣ ነው፡፡ እዚህ መስራት ጥሩም መጥፎም ነገር አለው፡፡ መጥፎው ነገር በማታ ነው የምንሰራ፣ የምንኖረው ከሰው በተቃራኒ ነው፡፡ ቀን እንተኛለን፤ ሌሊት ሰው ሲተኛ ደግሞ እኛ ለስራ እንነሳለን፡፡ ከሌላው ሰው ጋር ያለሽ ግንኙነት ደካማ ነው ማለት ነው፡፡ ሌላው ችግር ደግሞ ብዙ ሰው ምሽት ቤት የሚመጣ ሰክሮ ስለሆነ አንዳንዱ ይሳደባል፡፡ ግጥሜን አልተቀበልህም፣ ወይ እኔ በአንድ አቅጣጫ ስሰራ ለምን እኔን አታጫውትም ብሎ ልማታ ይላል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ጠብ አይጠፋም፡፡ በዛ ጊዜ ወይ ልንደበደብ

እንችላለን። ጥሩው ነገር ግን ገንዘብ ታገኛለሽ። ደሞዝ አለ፤ ሽልማት አለ። አሁን እኔ ሌላ ቦታ ከምሰራው ይልቅ ምሽት ቤት ሽልማት በደንብ አገኛለሁ። ለዚህ ስል ችግሩን ከምንም ሳልቆጥር ምሽት ቤት ውስጥ እሰራለሁ (እንዳልካቸው መኮንን፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/04/2005፣ ደሴ)።

ከመረጃው ምሽት ቤቶች ወቅታዊ የዘፈን መከወኛ አውዶች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። የእነዚህ ቦታዎች ታዳሚዎች ጥሩ ሸላሚዎች መሆናቸውንም መረጃው ይገልፃል። ይህ በመሆኑ ዛሬ ላይ በከተማ የሚኖሩ አዝማሪዎች ምሽት ቤቶችን እንደ አንድ የስራ ቦታ በመቁጠር የገቢ ማግኛ ቦታዎቻቸው አድርገዋቸዋል።

መረጃዎች እንደሚሉት በክበባትም ሆነ በባህላዊ ምሽት ቤቶች በመቀጠር የሚዘፍኑ አዝማሪዎች ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ከመሆኑ በስተቀር ስራቸውን በሚሰሩበት አካባቢ ቤት ተከራይተው ኑሯቸውን ይገፋሉ። ኑሯቸውን ከዘፈን ጋር ያስተሳሰሩ በመሆኑ የወደፊት ህይወታቸውን በዚሁ በዘፈን ዙሪያ በማድረግ ዘፈኖችን በካሴት በማስቀረፅና ለሽያጪ በማቅረብ ለመኖር የወሰኑ ናቸው።

ስለወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ሲነሳ ከወሎ ውጪ ባሉ ከተሞች የሚኖሩ አዝማሪዎችም ይጠቀሳሉ። እነዚህ አዝማሪዎች የተሻለ ኑሮ ፍለጋ አካባቢያቸውን ለቅቀው በሃገር ውስጥ በአዲስ አበባ፣ ከሃገር ውጪ ደግሞ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ናቸው። እነዚህኛዎችም በክበባትና በባህላዊ ምሽት ቤቶች እንደሚሰሩት አዝማሪዎች ህይወታቸውን ከዘፈን ጋር ያስተሳሰሩ ናቸው። በሚኖሩባቸው ከተሞች ባህላዊ ምሽት ቤቶችን በመክፈት፣ በባህላዊ ምሽት ቤቶች በመቀጠር የሙዚቃ ስራቸውን ለታዳሚያቸው በማቅረብ ከዚያ በሚገኘው ገቢ ራሳቸውን ያስተዳድራሉ ይህንን ሃሳብ ለማስረገጥ የቀረበው መረጃ ቀጣዩን ይላል። ‹‹የእኛ ሰው እኮ እግረኛ ነው። የትም ሂዶ ነው የሚሰራ። ከዚህ ሂዶ አዲስ አበባ እየዘፈነ የሚኖር ብዙ ተጫዋቺ አለ። እኔ ራሴ በኋላ ተውሁት እንጂ ማሪቱ (ለገሰ) አዲስ አበባ ካሳንቺስ የከፈተች ጊዜ አዲስ አበባ ነበርሁ። ታዲያ እስዋ ትልቅ ናት በአምስት ዓመት አካባቢ ትበልጠኛች። ግን እኔ ነኝ ያረጀሁ። ‹አባትሽ ናቸው ይሏታል›። እንስቃለን። እሷ ባለቤት ሆና እንሰራ ነበር›› (አሰፋ ለገሰ፣ ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005 ዓ.ም)።

መረጃው አዝማሪዎች ከወሎ ውጪ በሌሎች ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ እንዴት እንደሚኖሩ ያሳያል። በመረጃው እንደተገለፀው በዘፈን ስራ የሚኖሩ የወሎ አዝማሪዎች

በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች የመዝናኛ ቦታዎች ውስጥ በቀጣሪነት እንዲሁም በተቀጣሪነት እየኖሩ ነው፡፡ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አዝማሪዎች በመዝናኛ ቦታዎች እየዞሩ ከመስራት ባሻገር የመሰንቆ አጀብ የሚፈልጉ ዜማዎችን የሚያዜሙ ዘፋኞችን የካሴት ስራዎችን በማጀብ፣ በአንዳንድ በውጪ ሃገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሚዘጋጁ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ ተጋብዘው በመገኘት የዘፈን ስራቸውን በመከወን እየኖሩ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ የገለፁት መረጃ ሰጪ ቀጣዩን ብለዋል፡፡

> ወሎ እኮ ከጥንት ጀምሮ ብዙ ባለሙያ አዝማሪ አላት፡፡ ባህሩ ቀኜን ታውቂያለሽ፣ መቼም ስለ አሰፋ አባተ ሰምተሻል፡፡ አሁን ደግሞ ታዋቂው ማሲንቆ መቺ እንድሪስ ሃሰን ወሎዬ ነው፡፡ እንድሪስ የአልብኮ ሰው ነው፡፡ አሁን እሱ ስንቱን ዘፋኝ እያጀበ እሰራ ነው፡፡ እስከ ውጪ ሃገር እየዞረ ለራሱ ተጠቅሞ ባህሉን እያስተዋወቀ ነው፡፡ እሱን ምሳሌ ልጥራልሽ እንጅ ብዙ ሰው አለ፡፡ እነ ብርሃን ሞላ ሁሉ ወሎዬ ናቸው፡፡ አሁን እሱ የዘለሰኛ ሲዲ ሰርቷል፣ የባህል ዘፈን አሳትሟል፡፡ ሌሎች ዘፋኞችን በመሰንቆው እያጀበ ነው (ጫኔ ወርቅነህ፣ ቃለመጠይቅ፣ 16/04/2005 ዓ.ም. ደሴ)፡፡

መረጃው የወሎ አዝማሪዎች ከወሎ ውጪ ከአዲስ አበባ እስከ ውጪ ሃገር ድረስ ዘፈን በመከወን እየኖሩ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህ ሁኔታ ዛሬ፣ የአዝማሪ ዘፈን ከአካባቢ መገለጫነት አልፎ ሃገርን እስከመግለፅ የደረሰበት ጊዜ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ምክንያቱም አዝማሪዎች በአዲስ አበባ ዘፈንን ሲከውኑ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በመሆኗ ከተለያዩ የሃገሪቱ፣ የአህጉሪቱና የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ታዳሚዎችን የሚፈጥር በመሆኑ ባህሉ በሌሎች ዘንድ እየታወቀ ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ደግሞ አዝማሪዎች ራሳቸው ከኢትዮጵያ ውጪ ወደ ሌሎች ቦታዎች ሂደው ሲሰሩ ዘፈኑን በሌላውና መብቀያው ባልሆነ ቦታና ማህበረሰብ መካከል የሚከውኑት በመሆኑ የአዝማሪ ባህል በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ እንዲታወቅ የማድረግ ዕድላቸው ሰፊ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን አዝማሪነትን የተውና በሌሎች ስራዎች የሚኖሩ ወገኖችም አሉ፡፡ ስለእነሱ ቀጥሎ ተገልጧል፡፡

### 6.4.2. በገበሬነትና የመንግስት ሰራተኛነት የሚተዳደሩ

የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ በሆኑት ከድጆ፣ ደረቅ ወይራ፣ በረከት፣ ማርዬና ቀለባስ በተባሉ የአዝማሪ መንደሮች በተደረጉ ምልከታዎችና ቃለ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች የሚያሳዩት ጥንት በአዝማሪነት ይተዳደሩ የነበሩ በርካታ ሰዎች ዛሬ አዝማሪነትን በመተው ላይ መሆናቸውን ነው። ይህ በመሆኑ ዛሬ አዝማሪነትን የሚሰሩ ሰዎች በቁጥር በጣም ጥቂቶች ሲሆኑ በገጠር የሚኖሩት በግብርና፣ በከተማ የሚኖሩት ደግሞ በመንግስት ስራ የተሰማሩና ከአዝማሪነታቸው ይልቅ ገበሬነታቸው ወይም የመንግስት ሰራተኛነታቸው እንዲታወቅላቸው የሚፈልጉ ናቸው። ለምሳሌ የዚህ ጥናት አድራጊ ደረቅ ወይራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኝ አንድ የአዝማሪዎች መንደር ለመረጃ ስብሰባ በሄድሁ ጊዜ ሴቶችን ብቻ አገኘሁ። ለእነዚህ ሴቶች አላማዬን አስረድቸ ጥቂዎችን እንዲመልሱልኝና ከመንደሩ ወንዶች ጋርም ውይይት ማድረግ እንደምፈልግ ገለፅሁ። እነሱ ግን አዝማሪነትን ከረጅም ጊዜ በፊት እንደተውት፣ በሰፈሩ ውስጥ ሁሉም ሰው በእርሻ ስራ እንደሚተዳደር ወንዶችም ለተፋሰስ ስራ ሰፈሩን ለቅቀው መሄዳቸውን በመግለፅ ስለአዝማሪነት መወያየት ስለቀረ ነገር ማውራት መሆኑን በመግለፅ መረጃ ለመስጠት አለመፈለጋቸውን በአንክሮ ይገልፁ ነበር።

የልጆቻቸውን ሙያ አስመልክቶ ባደረጉት ገለፃ ‹‹ኧረ እንደዚያስ ባለስራ ሁሉ አሉ የአዝማሪ ልጆች። አስተማሪ ብትይ፣ ግብርና ሚኒስትር የሚሰሩ የእኛ ዘሮች አሉ . . . መሰንቆውን እየተው ትምህርት እየተማሩ ነው ዛሬ ሹፌሩ ብትይ የእኛ ነው። ባለሱቁ ብትይ የቅሬ[48] ጎሳ ነው›› ዘሪቱ ከበደና ፈንታዬ ሞላ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ 14/04/2005፣ደረቅ ወይራ) ሲሉ ዛሬ ላይ አዝማሪዎች ዘፈንን በመተው ራሳቸውን በምን ሙያ ላይ እንዳሰማሩ ይገልፃሉ። መረጃ ሰጪዎች ይህንን መረጃ ሲሰጡ ልጆቻቸው ከአዝማሪነት ይልቅ በሌሎች ስራዎች መሰማራታቸው የተሻለ ህይወት እንደሰጣቸው እንዲታወቅላቸው የመፈለግ አዝማሚያ ይታይባቸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በአምባሰል ማርዬ ነዋሪ የሆነ አቶ ተስፋዬ በላይ የተባለ ከአዝማሪ ቤተሰብ የተወለደ አንድ ሰው የእኔ ድካምና ማግባባት መረጃ እንዲሰጥ ስላደረገው እንጂ ከሃገሩ ሰው ውስጥ አንድም ሰው ‹‹አዝማሪ›› ብሎ ቢጠራው ክስ የሚሄድ መሆኑን ገልጧል። ለምን ለሚለው ጥያቄ ሲመልስም ‹‹እኔ ዛሬ ጥሩ አምራች ገበሬ ነኝ። መንግስት የሚያውቀኝ በገበሬነቴ ነው። መሰንቆ መጫወት የተውሁ ድሮ ነው።

[48] በእንዛትኛ (በአዝማሪ አርጎት) ቅሬ ማለት አዝማሪ ማለት ነው።

ታዲያ እኔ በግብርና ስራ እየተዳደርሁ ከአዝማሪ ቤተሰብ ስለተወለድሁ ብቻ አዝማሪ ነው ማለት ስድብ ነው››ሲል የመተዳደሪያ ስራው ከአዝማሪነት ወደግብርና የመጣ መሆኑን ገልጧል፡፡

እነዚህ መረጃዎች የጥቂት አዝማሪዎችን ህይወት የሚያሳዩ ቢሆኑም ለጥናት በተመረጡት በአራቱም ቦታዎች የሚኖሩ አባወራ አዝማሪዎች ሁሉ የሚያርሱት መሬት አላቸው፡፡ ጥቂት መሰንቆን በመጫወት ገንዘብ የሚያገኙ ሰዎች ቢኖሩም ለእነዚህ ሰዎች አዝማሪነት ተጨማሪ እንጅ ቋሚ ስራቸው አይደለም፡፡ የግብርናውን ያህል ትኩረት አይሰጡትም፡፡ በዚህ የተነሳ ጥቂቶቹ ብቻ ጊዜያቸውን ለዘፈንና ለግብርና ከፋፍለው ሲሰሩ ብዙዎቹ ለእርሻ ስራቸው ብቻ ትኩረት ሰጥተው በመስራት ላይ ናቸው፡፡

ለግብርና ስራ አቅማቸው የደከመ አዛውንት አዝማሪዎችም ቢሆኑ ዘፈን መዝፈን ቢችሉ እንኳን ልጆቻቸው ያንን እንዲያደርጉ የማይፈልጉ በመሆኑ ልጆቻቸው በሚሰጧቸው ወርሃዊ ተቆራጪ ራሳቸውን እንደሚያስተዳድሩ ይናገራሉ፡፡ ‹‹እቤቴ ለራሴ እጫወታለሁ፡፡ ወደ ውጪ ወደ ከስብ[49] ቦታ መሄዱን ትቼዋለሁ፡፡ እየደከመኝ ላዩን ነበር ምሄድ፡፡ ትልቅ ሰው ስለሆንኩ፣ ልጄም ደግሞ ይህ ነገር መቅረት ይገባሃል፣ ትልቅ ሰው ነህ፣ ከአንዱ ሰርግ ላይ ውለህ ማታ ትትሄድ ብትወድቅ ችግር አለበት፡፡ እኔ እያለሁኝ ችግር የለም ብሎ አስቀርቶኛል›› (ብርሃን ትኩ፣ ቃለመጠይቅ፣ 11/05/2005 ዓ.ም.ማርዬ) የሚለው ጥቅስ ይህንን ያሳያል፡፡ ይህ ሁኔታም ዕድሜያቸው ከአርባ በላይ በሆነ አዝማሪዎች ዘንድ እየሆነ ያለ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን አዝማሪነትን ፍፁም በመሸሽ ላይ ያሉ ቡድኖችም እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይ የወጣቶች መገለጫ ነው ማለት ይቻላል፡፡

መረጃ ሰጪዎች እንደሚሉት ዛሬ አዝማሪነት በሰዎች ዘንድ ከሚፈጥረው የዝቅተኛነት ስሜት ባሻገር የሚያስገኘው ገቢም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አዝማሪዎች ልጆቻቸው እንደ ድሮ በዘፈን የሚተዳደሩ እንዲሆኑ አይፈልጉም፡፡ ልጆችም ቢሆኑ ማህበረሰቡ ለአዝማሪና አዝማሪነት ያለው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑና በአዝማሪነት የሚያገኙት ገቢም የዕለት ፍላጎትን እንኳን ማሟላት የማያስችል መሆኑን ከወላጆቻቸው ህይወት ሲያዩ ሌሎች የስራ አማራጮችን መፈለግ እንደሚገባቸው ወስነዋል፡፡ በዚህ የተነሳ ዛሬ ላይ በወሎ የሚኖሩ አዝማሪዎች ከመሰንቆ ይልቅ ዘመናዊ

---

[49]በእንዛትኛ ዘፈን የሚከወንበት ቦታ (ዘፈን መዝፈን) ማለት ነው፡፡

ትምህርት መማር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡ ስለዚህም ገበሬና ተጫዋች ከሚለው የስራ ምድብ ውጪ የመንግስት ሰራተኛ የሚባል ምድብ በአዝማሪዎች መንደር ተፈጥሯል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ይህንን ጉዳይ ሲያስረዱ፡-

> አሁን የእኛ ልጆች የመንግስት ሰራተኞች ናቸው፡፡ የአባት ስራ እየቀረ መጣ፡፡ ለምንድን ነው? አልጠቀመውም፡፡ አሁን እኔም ትቼዋለሁ፡፡ አሁን ጊዜው ገደለው፡፡ እኛም እንደጊዜው ሆነን መኖር ፈለግን፡፡ ለምን? ካላበላሽ፣ ስድብ ተሆነ ስምሽ ምንድን ነው ጥቅሙ? እንደሰው ሰርተሽ መኖር አትችይም እንዴ? ብር ለምነን መቶ ብር ቢያገኝ በመቶ ብር ልጅ፣ ሚስት ማስተዳደር ይቻላል? ሺ ብር እንኳን ያስተዳድራል? ማስረሻ ፈንታዉ፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/05/2005 ዓ.ም፣ ማርዬ)

መረጃው እንደሚገልፀው የአዝማሪነት ሙያ የሚያስገኘው ጥቅም እያነሰ በመሄዱና በዘፈን የሚገኘው ገቢም ቤተሰብን ለማስተዳደር የማይበቃ በመሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን በሌላ ስራ እንዲሰማሩ እየገፋፉ ነው፡፡ ራሳቸው ወላጆችም ቢሆኑ አዝማሪነትን እየተው በሌላ የተሻለ ገቢ ሊያስገኝ በሚችል ሙያ እየተሰማሩ አዝማሪነትን በመሸሽት ላይ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ሲመረመር ምንም እንኳን ጥቂቶቹ በተለያዩ አውዶች ዘፈንን በመከወን ላይ ያሉ ቢሆን አብዛኞቹ ግን ቀስ በቀስ ራሳቸውን ከዘፈን ስራ እያላቀቁ ሌላው የአካባቢው ነዋሪ በተሰማራባቸው ግብርናና ሌሎች ተግባራት ላይ በመሰማራት ላይ ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ቡድኑ በአካባቢው ከሚኖረው ሌላው ማህበረሰብ ጋር የነበረውን ድንበር እያፈረሰና ተመሳሳይ የሆነ ኑሮ እየገፋ ይገኛል፡፡

# 7. ማጠቃለያና ይሁንታ

## 7.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ለአዝማሪ ባህል ባለኝ ፍላጎትና አስቀድሞ የተጠኑ ጥናቶች ያለባቸው ክፍተት በጥናት ሊሞላ ይገባል በሚለው እምነቴ ምክንያት የተደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ ‹‹የወሎ አዝማሪዎችን የዘፈንና የኑሮ ልምድ ተከታታይነትና ለውጥ መመርመር የሚል ሲሆን ዋና አላማው ከግብ እንዲደርስ ለወሎ አዝማሪዎች ኑሮ መገለጫ የሆኑ ተከታታይ ልምዶች ምንድን ናቸው?፣ በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ልምዶች ምን መልክ አላቸው?፣ የወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ የለውጥ ሂደት ምን መልክ አለው?፣ በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ የተከሰቱ ለውጦች ምንድን ናቸው?፣ በወሎ አዝማሪዎች ኑሮና የዘፈን ክዋኔ ልምድ ውስጥ ለተከሰቱ ለውጦች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?፣ የወሎ አዝማሪዎች ወቅታዊ አኗኗር ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረዱ መረጃዎች ከቤተመፃህፍት በንባብና ወሎን ይወክላሉ ከተባሉ ለጋምቦ፣ ደሴ ዙሪያ፣አምባሰልና መቄት ከተባሉ ወረዳዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተጠኝ ቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአግባቡ ተጠንተው በጥናቱ ዓላማ የተነሱ ጥያቄዎችን ከመመለስ አንፃር ያመጡትን ተፈጥሯዊ ቅጥ (Pattern) በመከተል በአግባቡ ተደራጅተው በክዋኔያዊና (Performing theory) ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳቦች (Marxist theory) ተተንትነዋል፡፡ ከትንታኔውም ቀጥለው የቀረቡ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ወሎ ውስጥ በማህበረ ፖለቲካዊ ስርዓት ምክንያት የተፈጠሩ አዝማሪዎች ብቻ የሚኖሩባቸው በርካታ መንደሮች ያሉ መሆኑ፣ (በዚህ ጥናት እንደምሳሌ ከአርባ በላይ መንደሮች ቀርበዋል፡፡ የወሎ አዝማሪዎች ቀደምት የጋብቻ ልማድ እርስ በእርስ ብቻ የሚከወን መሆኑ ሴትና ወንድ አዝማሪዎች አብሮ በመስራትና በመከባበር የሚገለፅ ግንኙነት አላቸው፣ የራሱ መለያ ባህርያት ያሉት የየሥርግ ልማድ ያላቸው መሆኑ፣ የዘፈን ስራን ለመስራት ሄደው የሰፈሩበት ቦታ ማህበረሰብ በሚያደርስባቸው ተፅዕኖ ምክንያት ሙስሊሞች ወይም ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ ይህም በሚኖሩበት አካባቢ ይገለፃል፡፡ በስራ ቦታና በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ‹‹እንዛትኛ›› የሚባል የሚስጥር ቋንቋ/‹‹አርጎት›› ያላቸው መሆኑ፣ በአዝማሪዎች መካከል አሁንም ድረስ የሚዘከር

የበላይና የበታችነት ደረጃ አለ የሚሉት ለወሎ አዝማሪዎች ኑሮ ተከታታይ መገለጫዎች ሆነው የኖሩ ባህርያት ናቸው፡፡

የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ለመዳ ሂደት ኢመደበኛ የልምምድ ሂደት መከተሉ፣ በአዝማሪዎች ዘንድ ዘፈንን በሁሉም የህይወት ክስተት ውስጥ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ተደርጎ መታየቱ፣ በወሎ አዝማሪዎች አንድ አዝማሪ ጥሩ አዝማሪ ለመባል ትዝታ፣ አምባሰል፣ አንቺ ሆዬና ባቲ በሚባሉ አራት ቅኝቶች ዘፈንን መጫወትና የቅኝቶችን የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ እንዲሁም ቅኝቶች የሚጠሯቸውን ግጥሞች ለይቶ ማወቅ ያለበት መሆኑ፣ የወሎ አዝማሪዎች ከጥንት አንስቶ እስካሁን ድረስ ዘፈናቸውን በመንደሮች፣ በገበያ፣ በግብር፣ በድግሶች፣ በመጠጥ ቤቶች፣ በጦርነት፣ በታቦት ንግስ መከወናቸው በወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ህይወት ውስጥ ያሉ ተከታታይ ልምዶች ናቸው፡፡

በወሎ አዝማሪዎች የዘፈንና ኑሮ ተከታታይ ልምዶች ላይ ለውጦች ተከስተዋል፡፡ ከኑሮ አንፃር የታዩት ለውጦች በቡድኑ አሰፋፈር፣ በጋብቻ ልማድ፣ በገቢ ማግኛ መንገድ፣ በሰርግ አከዋወን ደንብ ላይ የታዩ ሲሆን ከዘፈን ልምድ አንፃር ደግሞ በዘፈን አከዋወን ደንብ፣ በግጥሞች ቅርፅና ይዘት፣ በዘፈን መከወኛ አውዶች፣ በአዝማሪው ብቃት መለኪያ መስፈርቶች፣ ላይ ለውጦች ተከስተዋል፡፡

ለወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ መቀየር የመንግስት ርዕዮተዓለም ለውጥ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ ለአዝማሪነት ያለው አመለካከትና የኤሌክትሮኒክስ የሙዚቃ መሳሪያዎች ወደ አካባቢው መግባት በቡድኑ ገቢና የገቢ ሁኔታ ላይ የፈጠሩት ተፅዕኖ ነው፡፡

አብዛኞቹ የወሎ አዝማሪዎች ከአዝማሪነት የሚያገኙት ገቢ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር በቂ አልሆን በማለቱ ራሳቸውን ቀስ በቀስ ከዘፈን ስራ እያላቀቁ ሌላው የአካባቢው ነዋሪ በተሰማራባቸው ግብርናና ሌሎች ተግባራት ላይ በመሰማራት ላይ ናቸው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ከእነዚህ ውጤቶች በመነሳት ለወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ባህላዊነቱን ጠብቆ ለመዝለቅም ሆነ ለመለወጥ ዋና ምክንያቱ ቡድኑ በየዘመኑ ከዘፈን ስራው ያገኘው

የነበረውና የሚያገኘው የገቢ መጠን ሁኔታ ነው ከሚል መደምደሚያ ተደርሷል፡፡ ከመደምደሚያው በመነሳት ቀጥለው የሚገኙ ይሁንታዎች ቀርበዋል፡፡

ከእነዚህ ውጤቶች በመነሳት ለወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ባህላዊነቱን ጠብቆ ለመጓዙም ሆነ ለመለወጥ ዋና ምክንያቱ ቡድኑ በየዘመኑ ከዘፈን ስራው ያገኘው የነበረውና የሚያገኘው የገቢ መጠን ሁኔታ ነው ከሚል መደምደሚያ ተደርሷል፡፡ ከመደምደሚያው በመነሳት ቀጥለው የሚገኙ ይሁንታዎች ተሰጥተዋል፡፡

## 7.2. ይሁንታ

የወሎ አዝማሪዎች አዝማሪነትን ለረጅም ዘመን ጠብቀውት ኖረዋል፡፡ ሙያውም ለአዝማሪዎች መተዳደሪያ ለኢትዮጵያ ደግሞ መገለጫ ሆኖ ለብዙ ዘመናት ኖሯል፡፡ አሁን ግን ይህ ሙያ በፍጥነት በመለወጥ ላይ መሆኑን የዚህ ጥናት ውጤት አመልክቷል፡፡ ይህ ባህል ሲለወጥ ብዙ ነገሮች ከመመዝገባቸው በፊት አብረው ይለወጣሉ፡፡ ለምሳሌ ልማዳዊው የአዝማሪ ባህል ሲለወጥ በርካታ ቃላዊ ታሪኮች ይጠፋሉ፣ ሃገር በቀል የግጥም አገጣጠም ስልቶች ይጠፋሉ፤ የነገስታትና የቦታ ታሪኮች ይረሳሉ፣ ወዘተ እነዚህ የሃገር እሴቶች እንዳይጠፉ መታደግ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሊደረጉ ይገባቸዋል የተባሉ ጥረቶች እንደሚከተለው ተጠቁመዋል፡፡

1. የባህሉ ባለቤት የሆኑት አዝማሪዎች ኑሮን ለማሸነፍ ሲሉ የአዝማሪነትን ሙያ ከሚተውት ይልቅ በራሱ በሙያው የተሻለ ገቢ የሚያገኙባቸውን አማራጭ መንገዶች ቢፈልጉ ለምሳሌ ጎብኝዎችን ሊስቡ የሚችሉ የመከወኛ አውዶችን ቢፈጥሩ፤
2. የፌዴራልና የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎችና ፅ/ቤቶች አዝማሪዎች በተደራጀ መልኩ ቡድን መስርተው ዘፈኖቻቸውን ከውነው ገቢ የሚያገኙባቸው ፌስቲቫሎችንና ክብረ በዓሎችን ቢያዘጋጁ፤
3. የየወረዳ የባህል፣ ቱሪዝምና ልማት ፅ/ቤቶች ለወጣት አዝማሪዎች የመለማመጃ መድረኮችን ቢያዘጋጁ፣ ስራ የማግኛ መንገዶችንም ቢፈጥሩ፤

4. የየወረዳ የባህል፣ ቱሪዝምና ልማት ፅ/ቤቶች የአዝማሪነትን ሙያ ጥቅምና አስፈላጊነት የሚያስገነዝቡ ውይይቶችን በየጊዜው ቢያዘጋጁ፤
5. ባህሉን በትውልድ አእምሮ መቅረፅ ይቻል ዘንድ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ አዝማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቶች መጥተው ሙዚቃን የሚከውኑበት ፕሮግራም ቢያመቻቹ፤
6. ጥናቱ በተደረገበት ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች (በተለይ) መምህራንና ተማሪዎቻቸው በአዝማሪ ባህል ዙሪያ ጥናቶችን እንዲያደርጉ ቢያበረታቱና ድጋፍ ቢያደርጉ፤
7. በወሎ አካባቢ እንዲሁም በሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች የሚሰሩ የሙዚቃ ባለሙያዎች ትኩረታቸውን የአዝማሪ ዘፈንን ከነሙሉ ተፈጥሯዊ ምንነቱ እንደአንድ የሙዚቃ ዘርፍ ወደ ህዝብ የሚደርስበትን እድል ቢፈጥሩ
8. ቀጣይ አጥኝዎች የወሎ አዝማሪዎች የዘፈን ባህል ጥንታዊ መልኩን ጠብቆ ይኖር ዘንድ ድጋፍ የሚያደርጉ የተግባራዊ ፎክሎር ጥናቶችን ቢያደርጉ።

## ዋቢዎች


ሐረገወይን ሽዋረጋ፡፡ ‹‹በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ››፡፡ ያልታተመ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣2004 ዓ. ም፡፡

ሐሰን ታጁ፡፡ ሐላልና ሃራም በኢስላም፡፡ (ቅፅ 3) ዶር.ዩሱፍ አልቅርዳዊ፡ ነጃሽ ኢስላማዊ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ 1998 ዓ.ም.፡፡

መንገሻ አማረ፡፡ «የወገል ጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃልግጥሞች»፡፡ ያልታተመ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቢኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ዝክረ ነገር፡፡ አዲስ አበባ፣ማተሚያ ቤት አልተገለፀም፣1942 ዓ.ም፡፡

ሣህሉ ጥላሁን፡፡ ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናትን? ከሲና እስከ አክሱም፡፡ አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት አልተገለፀም፣ 1999ዓ.ም፡፡

ስፖርት ሚኒስቴር፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊስ፡፡ አዲስ አበባ፣1996 ዓ.ም፡፡

ቤተልሔም አለምሰገድ፡፡ ‹‹የቃል ግጥም ክዋኔ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ አዝማሪ ቤቶች››፡፡ ያልታተመ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም፡፡

ባዬ ይማም፡፡ የአማርኛ ሰዋስው (የተሻሻለ ሁለተኛ የአማርኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ ኦፍ ኢትዮጵያ (ኬዝ)፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ተስፉ ገብረ ስላሴ፡፡ የዘወትር ፀሎት፣ውዳሴ ማርያም፡፡ አንቀጸ፣ ብርሃን፣ ይዌድስዋ መላእክት ዋሽራ ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፣1987 ዓ.ም፡፡

ተሾመ ይመር፡፡ ‹‹የአማርኛ ግጥም አይነቶች›› የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት፡፡ቅፅ XXX, ቁጥር1፣ ገፅ 89- 134፡፡ አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም፡፡ 1997ዓ.ም፡፡

ተክለፃድቅ መኩሪያ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1981 ዓ.ም፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ በይነ ዲስፕሊናዊ የስነፅሁፍ ንባብ፡ስነፅሁፍ እና ሚቶሎጅ፣ ፍልስፍና፣ ስነልቡና፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፣ 2001ዓ.ም፡፡

ትምህርትና ስነጥበብ ሚኒስቴር፡፡ ታሪክና ምሳሌ (3ኛመፅሃፍ)፡፡ አዲስ አበባ፣ቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1961ዓ.ም፡፡

አለማየሁ ወ/ዮሐንስ፡፡ የመሰንቆ፣ የክራርና የዋሸንት መማሪያ ያለአስተማሪ፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.፡፡

አለቃ ተክለ እየሱስ፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ (ሐተታ) በስርግው ገላው፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፤ 2002 ዓ.ም፡፡

አለቃ ታዬ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፤ባጭር ቃል የወጣ፡፡ አስመራ፣ በሚሲዮን ስዌዴስ ማህተም ታተመች፣1920 ዓ.ም፡፡

አልማዝ አበበ፡፡«አዝማሪና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ»:: ያልታተመ፣ በኢትዮጵያቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቢኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣1974 ዓ.ም፡፡

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፡፡ የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር አትላስ.፡፡ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣1999. ዓ.ም፡፡

አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የኮምኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ዓመታዊ መፅሃፍ፣ባህር ዳር፣ ማተሚያ ቤት አልተገለፀም፣ 2002 ዓ.ም፡፡

አስቴር ሙሉ፡፡ ‹‹የቡርቧክስ አዝማሪዎች ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መልክ››፡፡ Seminar in Oral History (Folk 803) ለሚል ኮርስ ማሟያ የተሰራ ‹‹ተርም›› ወረቀት፣ 2003 ዓ.ም.፡፡

__________:: ‹‹የሴት አዝማሪዎች ድርብ ሚና፡ በባህርዳር ከተማ በሚኖሩ አዝማሪዎች ተተኳሪነት›› ባህር ዳር፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ባህል ለልማት ያለው ጠቀሜታ በሚል ርዕስ በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ የቀረበ፣ 2005 ዓ.ም.::

አበበ ማለደ:: «በጎንደር ዙሪያ ወረዳ በብርቧክስ ቀበሌ የአዝማሪነት ሙያና የዘፈን ግጥሞች»:: ያልታተመ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የኤም.ኤ.ዲግሪ ቴሲስ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም.::

አንለይ ሙሉ:: «የአዝማሪ ታደለ የህይወት ታሪክና ቃላዊ ግጥሞቹ»:: ያልታተመ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣ 1995 ዓ.ም::

ኤልያስ አብርሃ:: ታቦተ ፅዮን በኢትዮጵያ:: አዲስ አበባ፤ ማተሚያ ቤት አልተገለፀም፣ 2005 ዓ.ም::

ገ/ኪዳን ወ/ሐዋርያት:: ‹‹በታሪክ ዘርፍ የተሰሩ ስራዎች ከ1977-1981ዓ.ም››:: ያልታተመ፣ በወሎ ክፍለሃገር ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ቅ/መ/ቤት፣ ደሴ፣ 1981 ዓ.ም::

ጌታቸው መኮንን ሃሰን:: ወሎ-የአገር ድባብ:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም.::

ደስታ ተክለ ወልድ:: ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም. ::

ኑርሁሴን ሙሐመድ:: «በፎገራ አካባቢ የሚሰሙ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘት ትንተና››:: ያልታተመ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ፣ 1986 ዓ.ም::

የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት:: የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስ ማህበር፣ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.::

የሰሜን ወሎ ዞን የ2003 ዓ.ም የመረጃ መፅሃፍ:: ያልታተመ፣ በሚዲያ ልማትና ጥናት ምርምር የስራ ሂደት ታህሳስ 2003 ዓ.ም::

የአማራ ክልል ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፡፡ የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሃብቶች (አጭር ቅኝት)፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር፡፡‹‹ቃለ ምልልስ››፡፡ አዲስ አበባ፣ 2007 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ ክብረነገስት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1994ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ፣ ቤት፣ 1993 ዓ.ም፡፡

የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ፣ 1996 ዓ.ም፡፡

ያለው እንዳወቀ ሙሉ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ማተሚያ ቤቱ አልተገለፀም፤ ባህር ዳር፤ 1998 ዓ.ም፡፡

ያሬድ ገ/ስላሴ፡፡ ‹‹የወሎ ባህል አምባ የላሊበላ ኪነት ቡድን››፡፡ ያልታተመ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቲያትር ጥበባት ክፍል፤ የቢኤ.፣ዲግሪ ማሚያ ፅሁፍ፣አዲስ አበባ፣ 1974 ዓ.ም፡፡

ፀጋዬ ደባልቄ፡፡ ‹‹አዝማሪ ምን አለ?›› አዲስ ዘመን ጋዜጣ፡፡ ገፅ2፣ 1968 ዓ.ም.፡፡

ፈቃደ አዘዘ (አዘጋጅ) ፡፡ ‹‹ስለ ስነፅሁፍ 13 መጣጥፎች መድብል››፡፡ ያልታተመ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣1975 ዓ.ም፡፡

___________፡፡ የስነቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመፅሃፍት ማዕከል፣ 1993 ዓ.ም፡፡

Afanasyev, G.V. Marxist Philosophy: A Popular Outline. Soviet Socialist Republics, Progress Publishers, 1980.

Allen, Barbara. "The Personal Point of View in Orally Communicated History".Western Folklore. Vol. 38, No. 2, pp. 110-118.Western States Folklore Society, 1979.

Ashenafi, Kebede "The Music of Ethiopia: its Development and Cultural Settings. PhD Dissertation, Wesleyan University, 1971.

____________"The '*Azmari*', Poet-Musician of Ethiopia": IntheMusical Quarterly. Vol. 61, No. 1 (Jan., 1975), pp. 47-57, Oxford: Oxford University, Press Badge Wallis (2007[1st ed., 1932]). 1971.

____________."Zemenawi Muzika: Modern Trends in Traditional Secular Music of Ethiopia". The Black Perspectivein Music, Vol. 4, No3, pp. 289-301, 1976, http:// www.jstor.org/stable/1214537.Accessed: 02/02/2013 10:00

Aster, Mulu. "The Responsibility of Female Azmariewoch: The case of Bahir Dar Town". Presented on the first international conference in Ethiopian Azmari, World music center, Germany, Hildishim University, 2012.

Bahru, Zewede. A History of Modern Ethiopia 1855 – 1991. Addis Ababa, Addis Ababa University Press, 2002.

Ball, Philip.et.althe Music Instinct: How Music Works andWhy We Can't Do Without It. Oxford University Press, Inc. 2010.

Barnard, Alan. History and Theory in Anthropology. United Kingdom, Cambridge University Press, 2004.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore". The Journal of American Folklore, Vol.67, No.266 pp 333-349, American Folklore Society, (Oct.-Dec., 1954).

Batt-Rawden, Kari Bjerke. "Music as a transfer of faith: Towards recovery and Healing". Journal of Research in Nursing, 2007.

Bauman, Richard. “Verbal art as performance”. American Anthropologist. New Series Vol.77.N$^{o}$ 2.Jun, pp290 – 311. 1976.

Ben - Amos, Dan. “Towards a new perspective in Folklore”. The Journal of American Folklore, Vol.84, No.331, pp 3-15, American Folklore Society, (Jan.-Mar., 1971)

____________. “Folklore in African Society”.Research in African LiteratureVol.6, No.2, pp 165 – 198, 1975.

____________ .Story, Performance and Event: Contextual Studies of Oral Narratives. London, Cambridge University Press, 1986.

____________.“Folklore in Context”, New Delhi: South Asian publisher.1993.

____________“Context in Context” Theorizing Folklore: Toward new Perspectives on the Politics of Culture. Western Folklore Society. Vol. 52, No. 2/4, pp. 209-226, 1993.

Blacking, John. Music, Culture and Experience. The University of Chicago Press, 1995.

Bohlman, Philip V. The Study of Folk Music in the Moder World.Folkloristic.Indiana University press, Bloomington and Indiana Press, 1988.

Bolay, Anne. “The Azmari: Voice of Ethiopian Memory.” Ethiopian Studies at the End of the Second Millennium - Proceedings of the 14th International Conference of IES, Vol. I. Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa, Addis Ababa University, Pp.75-83.2002.

Bryman, Alan. Ethnography. (Ed) Vol.1.Saga Publication. Great Britain at Cambridge University press, Cambridge, England. 2001.

Burton, Richard F, the Jew, the Gypsy and El Islam. Chicago and New York, Herbert S. Stone and Company, 2000.

Bronner, Simon J. "Art, performance and praxis: The Rhetoric ofContemporary Folklore Studies", Western folklore.vol 47, no.2, Pp.75 -10, 1988.

Cohn, Werner. The Gypsies. London, Addison – Wesley publishing Company.1973

Clements, William, M. "Personal Narrative, the Interview Context, and the Question Of Tradition," Western Folklore. Vol. 39, No. 2, pp. 106-112. Western States, 1980. Folklore Society. Www.jstor.Accessed: 07/04/2013 10:0

Davison, Archibald T., et al. "Report of the committee on graduate Studies".Journal Of the American Musicological Society. Pp153-54, 2006.

Dawson, Catherine. A Practical Guide to RESEARCH METHODSA friend Manual for Mastering research techniques and projects. British Library Cataloguing in Publication, Oxford United Kingdom, 2007.

Dorson, Richard M.Folklore and folk life: An introduction.Chicago, London, The University of Chicago press, 1972.

Dundes, Alan. "Who are the folk?"In Interpreting Folklore. Pp.1–19. Bloomington: Indiana University Press, 1980.

--------------------«The Anthropologist and the Comparative Method in Folklore. » Journal of Folklore Research 23:125 – 146. Rpt. in Folklore Matters. 57–82. Knoxville, University of Tennessee, 1986.

Ege, Svein and Yigremew, Adal. Farming Asests in North wolo: Stastistics, maps and Impression from a travel to north wolo. Norwegian University of Science and Technology, Department of Social Anthroplogy, Trondheim, 2000.

Ezra Abate." Ethiopian Kiñit (scales): Analysis of the formation and structure of the Ethiopian scale system. In: Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies. pp 1213 – 1224, 2009.

___________. Oral Poetry: it's Nature, Significance and Social context. Bloomington and Indiana, Indiana University press, 1977.

Finnegan, Ruth. Oral Traditions and The verbal Art. Routledage, Inc. NewYork, 1992.

Fife, Wayne. Doing fieldwork: ethnographic methods for research in Developing Countries and beyond. Macmillan Division of St. Martin's Press, LLC and of Palgrave Macmillan Ltd, New York, 2005.

Gaunt, Simon and Kay, Sarah. The Troubadours: An Introduction. Britain, Cambridge University press, 1999.

Glassie, Henry. « Tradition».The Journal of American Folklore, Vol. 108, No. 430, Common Ground: Keywords for the Study of Expressive Culture.pp. 395- 412, 1995 American Folklore Society. http://www.jstor.org/stable/541653.15/10/201407:34

Green, Thomas. A. an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, music and Art. California, Denver, ABC- CLIO, Inc, Santa Barbara, 1997.

Goldstein, Kenneth S. A Guide for Field Workers in Folklore. Detroite: Gale Research Company, 1974.

Grhome boy. "Sparta vs Athens: The Battle for the Ancient World". Culture History Mythology, 2006.

Hancock, Graham. THE SIGN AND THE SEAL: A Quest for the lost ark of Covenant. Britain Cox & Wyman Ltd, Reading.Berkshire, 1992.

Henze, .Paul. BLayers of time: a History of Ethiopia.Palgrave.Newyork.2000.

Hield,Fay. English Folk Singing andthe Construction of Community. The University Of Sheffield.2007.

Horner, Alice E. ‹‹The Assumption of Tradition: Creating, Collecting, and Conserving Cultural Artifacts in the Cameroon Grassfields (West Africa) ››. Ph.D. Dissertation in Anthropology, University of California, Berkeley. 1990.

Hussein, Ahmed.Islam in nineteenth –Century Wallo, Ethiopia .Revival, Reform and Reaction, Brill, Leiden, Boston, Koln, 2001.

Hymes, Dell. ‹‹Breakthrough in to performance»: *In APPROACHES TO SEMIOTICS. Netherlands. Library of congress.* 1975.

Ilitskaya, linina.ABC of Dialectical and Historical Materialism.Union of Soviet Socialist Republics, Progress Publishers, 1978.

Johnson, Allan G. *The Gender Knot: Unravelling Our Patriarchal Legacy*. Revised And Updated Ed. USA: Temple University Press. (2005). Retrieved on 12 March 2010 from gigapedia.

Kapchan, Deborah A. “Performance”.The Journal of American Folklore.University of Llinois press, Vol. 108, No. 430, pp 479- 508.Autumn, 1995.

Kawase, Itsushi. “Musical Performance and Self-Designation of Ethiopian Minstrels: *Azmari*”. Graduate School of Asian and African Area Studies, Kyoto University, Sakyo-Ku, Kyoto, 606-8501, Japan.2005.

___________ “The Transformation of Musical Activities and Self-imposed Group Markers of *Azmari* in Ethiopia”. In Cultures Sonoresd’Afrique IV.publie’sous ladirection de Junzo KAWADA, *Institut de Rechrches sur les Cultures Populaires du Japan.* University’ Kanagawa: Yokohama, Japan. 2008

___________ “Intercultural Dialogue on the Visualization of Local Knowledge: Films on Hereditary Singersin Ethiopia”.In African study Monographs, supp l.41:101-109, 2010.

Kefyalew Azeze. “Minstrels in Addis Ababa: a Study in the Social Life of Gonderian Inzatas”. Unpublished MA Thesis, Addis Ababa University, 1998.

Kimberlin. Cynthia T. “The Music of Ethiopia”. In Musics of many cultures: an introduction USA, Paperback Printing, 1983.

Kolesowe, Nicolay.political Economy of Socialism.Mosco, Novostyprinting Service, 1976.

Leeming, David. Myth a Biography o f Belief. Newyork.Oxford University Press, 2002

Leslau, Wolf. “An Ethiopian Minstrels' Argot” In Journal of the American Oriental Society. Vol. 72, No. 3 (Jul. - Sep., 1952), pp. 102-109, American Oriental Society, 1952.

Leslau, Wolf and Ken L. Thomas.Amharic cultural reader. Harrassowitz. Verlago. Wiesbaden. 2001.

Lortat-Jacob, Bernard (1984). “Music and Complex Societies: Control and Management of Musical Production”.In Yearbook for Traditional Music, Vol. 16, pp. 19-33, 1984.

Merriam, Alan P.THE ANTHROPOLOGY OF MUSIC Evanston, Illinois North-Western University Press. 1964.

Mesganaw Andualem. “Change and Continuity in the Lives of Birbuax Azmaris”. Unpublished MA Thesis, Addis Ababa University, School of Graduate Studies, Department of Social Anthropology, 2010.

Maykut, Pamela *and* Morehouse, Richard. Beginning Qualitative ResearchA Philosophic and Practical Guide. The Falmer Press, London, Washington, D.C, 1994.

Munslow, Alun. Deconstructing History: (2nd ed), simultaneously published in the USA and Canada by Routledge, New York, 1997.

Oakley, Judith. The Traveller-Gypsies. Britain, Cambridge University Press, 1983.

Okpewho, Isdore.African Oral literature. Bloomington and Indiana, Indiana University Press, 1992.

Oxford Advanced Learner’s Dictionary of Current English, England, Oxford University Press, 1974, p.185.

Patric, Julian, N. et al. Music and Emotion: Theory and Research. New York, Oxford University Press, 2008.

Powen, Micheal. Ethiopian Music: An introduction. London, Oxford University Press, 1968.

Reck, David B. “The Minstrels”. In Music Educators Journal, Vol. 63, No. 2 Oct. 1976. pp. 28-37. MENC: The National Association for Music Education, 1976.

Ritchie, Donald. An“An oral history of our time”. Doing Oral History.1997.

Sage, Bethany. “West African story tellers: Griotes and Griottes. Journal.oral tradition.org. files/articles/12il/2Hale.Pdf. Acceded. October 2/1914.

Schomeker, George. (ed) Introduction basic Concepts of Folkloristics. In the Emergence of Folklore In everyday life: A field guide and Sourcebook .Trickster press, Bloomington, 1990.

Shelemay, Kaufman. K. Sound scapes: Exploring Music in a Changing World. (2nd Ed), W.W. Norton & and Company, Inc. 2006.

Shelemay, KaufmanK. And Peter, Jeffery, “Ethiopian Chant and Notation in Western Scholarship.” Ethiopian Christian Liturgical Chant: An Anthology. Madison, WI: A- R Editions, pp. 131-48, 1997.

Sheppard, Tim, “Traditional story telling”.www.co.uk/story/dir/traditions/australia. Htm/.2004.Accessed: 07/07/2014, 8:00

Sims, Martha.C. And Stephens, Martine. Living Folklore: An Introduction to Study of People and their traditions.Utah state university press, USA, 2005.

Smith, Cameron M. with Davies, Evan. T. Anthropology for Dummies. Canada, Wiley Publishing, Inc. Indianapolis, Indiana, 2008. .

Stahl, Sandra, K. D. “The Personal Narrative as Folklore”.Journal of the Folklore Institute. Vol. 14, No. 1/2, Special Double Issue: Stories of Personal Experiences, pp. 9-30, Indiana University Press, 1977.

Teclehaimanot Gebere Selase. “A brief Survey Study of the Azmareis in Addis Abeba”. Proceedings of the international Symposium on the Centerary of Addis Ababa. Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa, November 24 -25, Pp.161 -172, 1986.

Ter, Ellingson, et al. “Toward the Remodelling of Ethnomusicology”.In Ethnomusicology: Journal of the Society for Ethnomusicology. (3rd Ed), Ann Arbor, Michigan, 1987.

Timkehet, Teffera. “One-Stringed Fiddle *Masinqo*: Its Function and Role in the Contemporary Ethiopian Music and its Future”.Accessed: 01/07/2013 11:00 http://addisconnexion.com/index.php/ Music/The Masinqo.html. 2009.

Titon, ToddJeff. “The Life Story”. The Journal of American Folklore, Vol. 93, No. 369, pp, 276-292, 1980 American FolkloreSociety. http://www.jstor.org/stable/540572.

Toelken, Barre. Dynamics of folklore. Logan: Utah State Univeristy Press, 1996.

Tyson, Lois. Critical theory today: A user friend’s guide (2nd ed.), New York, 2006.

## ካሴቶች

ማሪቱ ለገሰ፣ ወሎ 2003 ዓ.ም.፡፡

ፋሲል ደሞዝ፣ የደህና ሰው ዘሩ፣ 2004 ዓ.ም. (ነጠላ ዜማ)፡፡

ይርዳው ጤናው፣ ያገሬ ልጅ 1987 ዓ.ም.፡፡

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- የመረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ

### በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሰዎች አጠቃላይ መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የመኖሪያ ስፍራ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከድር ሙሐመድ | 52 | ወንድ | ደሴ | ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች፣ የመንግስት |
| 2 | ሰመረ ከበደ | 45 | ወንድ | ደሴ | የግል (ሙዚቀኛ) |
| 3 | ፀጋው መኮንን | 30 | ወንድ | ደሴ | የመንግስት (ባህልና ቱሪዝም) |
| 4 | ጫኔ ወርቅነህ*[50] | 65 | ወንድ | ደሴ | አዝማሪና የመንግስት |
| 5 | እንዳልካቸው ዘሪሁን* | 29 | ወንድ | ደሴ | አዝማሪ |
| 6 | አራጌ ይማም * | 72 | ወንድ | ደሴ | አዝማሪ |
| 7 | ተፈራ አያሌው* | 74 | ወንድ | ደሴ | ዘበኛ/ አዝማሪ የነበሩ |
| 8 | አሰፋ ለገሰ* | 67 | ወንድ | ደሴ | አዝማሪ |
| 9 | መላኩ መድፉ* | 69 | ወንድ | ደሴ/ደረቅ ወይራ | አዝማሪ |
| 10 | ዘሪቱ ከበደ* | 37 | ሴት | ደረቅ ወይራ | ገበሬ/አዝማሪነት የተው |
| 11 | ፈንታዬ ሞላ* | 32 | ሴት | ደረቅ ወይራ | ገበሬ/አዝማሪነት የተው |
| 12 | አሰጉ ሰኢድ* | 82 | ሴት | ደረቅ ወይራ | አዝማሪ |
| 12 | ትርንጎ መለሰ | 55 | ሴት | ቀለባስ | አዝማሪና ገበሬ |
| 13 | አለም ፀሃይ የማና* | 72 | ሴት | ውጫሌ | አዝማሪ |
| 14 | ደምሴ አበበ* | 72 | ወንድ | ጢሳ አባ ሊማ | አዝማሪ |
| 15 | አበባው ሙሉጌታ* | 26 | ወንድ | ውጫሌ | አዝማሪ/የባህ.ቱ.ፓርኮች |
| 16 | ሞላ ተገኘ* | 56 | ወንድ | ውጫሌ | ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች |
| 17 | አባይ ሽመልስ | 38 | ሴት | ማርዬ ስላሴ | ሆቴል |
| 18 | መላኩ ካሳው* | 40 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ገበሬና አዝማሪ |

[50]ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 19 | ፈንታዬ አበራ* | 61 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | የቀበሌ ሊቀመንበር |
| 20 | ማስረሻ ፈንታው* | 47 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ገበሬ/አዝማሪ የነበረ |
| 21 | ብርሃን ትኩ* | 74 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | አዝማሪና ገበሬ |
| 22 | መኮንን በላይ* | 29 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ተማሪ |
| 23 | ተስፋዬ በላይ * | 33 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ገበሬ/አዝማሪየነበረ |
| 24 | ሙሉጌታ አበበ | 69 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | አዝማሪ |
| 25 | አሰፋ ታደሰ | 58 | ወንድ | ኢላዳ (በረከት) | ገበሬ |
| 26 | ጫኔ ሃብት ይመር | 70 | ወንድ | ኢላዳ (በረከት) | ገበሬ |
| 27 | ጥላሁን ሰይድ | 47 | ወንድ | ኢላዳ (በረከት) | ነጋዴ |
| 28 | ሰለሞን አሰፋ | 27 | ወንድ | ኢላዳ (በረከት) | አዝማሪ |
| 29 | ተመስገን ፈንታ * | 40 | ወንድ | ኢላዳ (በረከት) | አዝማሪና ገበሬ |
| 30 | የሮም አያሌው* | 35 | ሴት | ኢላዳ (በረከት) | አዝማሪና ገበሬ |
| 31 | አባ ነጋ ካሴ | 70 | ወንድ | ወረኢሉ | አዝማሪ |
| 32 | አልማዝ ለገሰ* | 40 | ሴት | ወረኢሉ | አዝማሪ |
| 33 | ፈንታው ለገሰ* | 75 | ወንድ | ከድጆ | ገበሬ |
| 34 | ሐዋ ሰኢድ | 78 | ሴት | ከድጆ | ገበሬ |
| 35 | ሙሐመድ ፈንታው | 25 | ወንድ | ከድጆ | ገበሬ |
| 36 | አባ መርቆሪዎስ ሞላ | 81 | ወንድ | ማርዬ | የሃይማኖት መሪ |
| 37 | ጥበብ አለሙ | 65 | ሴት | ቀለባስ | አዝማሪና ገበሬ |
| 38 | ተስፋዬ ፀጋው | 71 | ወንድ | ቀለባስ | አዝማሪ |
| 39 | አገኘሁ ደሴ | 63 | ወንድ | ቀለባስ | አዝማሪና ገበሬ |
| 40 | ሽጋው አገኘሁ | 45 | ወንድ | ቀለባስ | አዝማሪ |
| 41 | መላክ ታረቀ* | 71 | ወንድ | ቀለባስ | አዝማሪና ገበሬ |
| 42 | በሪሁን መላክ* | 24 | ወንድ | ቀለባስ | አዝማሪ |
| 43 | በለጡ መላክ* | 22 | ሴት | ቀለባስ | የቤት እመቤት |
| 44 | ፀሃይ መላክ | 20 | ሴት | ቀለባስ | ተማሪ |
| 45 | ሲሳይ አጥናፌ | 54 | ወንድ | ቀለባስ | ገበሬ/ሊቀ መንበር |
| 46 | መንግስት ብርሃን | 38 | ወንድ | ቀለባስ | ገበሬ |
| 47 | መኮንን ፀጋ* | 56 | ወንድ | መቄት | ገበሬ |
| 48 | ፍቅሩ ታደሰ* | 21 | ወንድ | ቀለባስ | አዝማሪ |
| 49 | ሰኢድ አወል | 59 | ወንድ | ደረቅ ወይራ | ገበሬ |
| 50 | ሃይሉ ታደሰ | 42 | ወንድ | ደሴ | ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች |
| 51 | እንዳልካቸው በቀለ | 30 | ወንድ | ደሴ | አዝማሪ |
| 52 | መላክ ጫኔ* | 37 | ወንድ | ግዳን | አዝማሪ |
| 53 | አማረ አንገቶ | 39 | ወንድ | ደሴ | አዝማሪ |

በተተኪሪ  ቡድን ውይይት የተሳተፉ ሰዎች አጠቃላይ መረጃ

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | ፆታ | መረጃ የተሰ. ቦታ | ሙያ | መረጃ የተሰ. ቀን (ዓ.ም) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰኢድ አወል | 59 | ወንድ | ደረቅ ወይራ | ገበሬ | 14/04/2005 |
| 2 | ፀጋው መኮንን | 30 | ወንድ | ደረቅ ወይራ | የመንግስት | 14/04/2005 |
| 3 | መላኩ መድፉ* | 69 | ወንድ | ደረቅ ወይራ | አዝማሪ | 14/04/2005 |
| 4 | ሽመልስ ላቀ | 70 | ወንድ | ደረቅ ወይራ | የእጅ ስራ ባለሙያ | 14/04/2005 |
| 5 | ደምሴ ቀማው | 42 | ወንድ | ደረቅ ወይራ | ገበሬ | 14/04/2005 |
| 6 | ዘሪቱ ከበደ* | 37 | ሴት | ደረቅ ወይራ | ገበሬ/አዝማሪነ ትየተው | 14/04/2005 |
| 7 | ፈንታዬ ሞላ* | 32 | ሴት | ደረቅ ወይራ | ገበሬ/አዝማሪ የነበሩ | 14/04/2005 |
| 8 | አበባው ሙሉጌታ* | 26 | ወንድ | ማርዬ | አዝማሪ | 12/05/2005 |
| 9 | ማስረሻ ፈንታው* | 47 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ገበሬ/አዝማሪ የነበሩ | 12/05/2005 |
| 10 | ብርሃን ትኩ* | 74 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | አዝማሪና ገበሬ | 12/05/2005 |
| 11 | ሙሉጌታ አበበ | 69 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | አዝማሪ | 12/05/2005 |
| 12 | ተፈራ አበበ | 68 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | አዝማሪ | 12/05/2005 |
| 13 | መኮንን በላይ* | 29 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ተማሪ | 12/05/2005 |
| 14 | ተስፋዬ በላይ * | 33 | ወንድ | ማርዬ ስላሴ | ገበሬ/አዝማሪ የነበሩ | 12/05/2005 |
| 15 | ሰለሞን አሰፋ | 27 | ወንድ | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |
| 16 | ሙሐመድ ፋንታሁን | 24 | ወንድ | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |
| 17 | ሙሐመድ ጌታሁን | 26 | ወንድ | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |
| 18 | ሰለሞን ፈንታ | 22 | ወንድ | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |
| 19 | አንቺነሽ ጌታዋ | 27 | ሴት | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |
| 20 | መንግስት በሽር | 21 | ወንድ | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |
| 21 | ሲሳይ ከድር | 33 | ወንድ | ኢላዳ | አዝማሪ | 19/05/2005 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | ፈንታው ለገሰ* | 75 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 23 | ሰኢድ ሃኪም | 78 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 24 | ሙሐመድ ፈንታው | 25 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 25 | አሰፋ ለገሰ | 67 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 26 | ሙሐመድ ሁሴን | 40 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 27 | ሰኢድ ፋንታው | 44 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 28 | ፈንታሁን አመዴ | 66 | ወንድ | ከድጆ | አዝማሪ | 25/05/2005 |
| 29 | በለጡ መላክ* | 22 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪ | 27/07/2005 |
| 30 | ፀሃይ መላክ | 20 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪና ተማሪ | 27/07/2005 |
| 31 | ልዕልት አገኘሁ | 25 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪና ተማሪ | 27/07/2005 |
| 32 | ትርንጎ መለሰ | 55 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪና ገበሬ | 27/07/2005 |
| 33 | ጥበብ አለሙ | 65 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪና ገበሬ | 27/07/2005 |
| 34 | ፀጋነሽ አለም | 35 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪ | 27/07/2005 |
| 35 | አስናቁ በላይ | 36 | ሴት | ክትክታ | አዝማሪ | 27/07/2005 |

## አባሪ ሁለት፡- የምርምር ጥያቄዎች

### ሀ.‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ›› በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከአዝማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**ጠቅላላ መመሪያ፡-**

ውድ መረጃ ሰጪዎች በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ቀረቡ ጥያቄዎች ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ›› በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ‹‹ነገርን ነገር ያነሳዋል›› እንዲሉ በቃለምልልሳችን ውስጥ ሁኔታው እንዲነሱ ዕድል የሚሰጣቸው ሌሎች ጥያቄዎች ይካተታሉ፡፡ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ ሲሆን የሚገኙት መረጃዎች በምንም መንገድ ከዚህ ዓላማ ውጪ እንደማይውሉ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ ለምታደርጉልኝ ትብብር እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

የመረጃ ሰጪ ስም ፡ ____________________

ዕድሜ ፡ ____________________

ስራ፡ ____________________

ፆታ፡ ____________________

መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ፡____________________

መረጃው የተሰበሰበበት ቀን፡ ____________________

ሃይማኖት፡ ____________________

የጋብቻ ሁኔታ፡ ____________________

የትምህርት ሁኔታ፡ ____________________

በአካባቢው የኖሩት ዓመት፡ ____________________

1. አዝማሪ ምንድን ነው?
2. አዝማሪነት የሚባል ስራ እንዴት ኖረ?
3. አዝማሪዎች ዛሬ በሰፈሩባቸው ቦታዎች ለመስፈራቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

4. የወሎ አዝማሪ ከሌላው አካባቢ አዝማሪ የዘር ሃረግ ግንኙነት የለውም ወይ?
5. የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታይ አዝማሪዎች በመካከላቸው ያለው ልዩነትና ተመሳስሎ ምንድን ነው?
6. አዝማሪዎች አዝማሪ ካልሆነው ሰው የሚለዩባቸው ልማዶቹ ምን ምን ናቸው?
7. ከወሎ አዝማሪዎች ውስጥ ስመ ጥር የነበሩ አዝማሪዎች አሉ ወይ?
8. በአዝማሪነት ህይወት ውስጥ የተሻለ የሚባል ዘመን አለ ወይ?
9. በአዝማሪነት ህይወት ውስጥ መጥፎ የሚባል ዘመን ነበረ?
10. የአዝማሪነት ሙያ የወደፊት እጣ ምን መልክ ይኖረዋል ብለው ያስባሉ?
11. በድሮውና በአሁኑ አዝማሪ መካከል ምን ልዩነት አለ?
12. የድሮ ሴት አዝማሪዎች የስራ ድርሻ ምን ነበር? የዛሬዎችስ?

## ለ. ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ›› በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት አዝማሪዎች ካልሆኑ ሰዎች በቃለ መጠይቅ

### መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**ጠቅላላ መመሪያ፡-**

ውድ መረጃ ሰጪዎች በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ቀረቡ ጥያቄዎች ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ›› በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ‹‹ነገርን ነገር ያነሳዋል›› እንዲሉ በቃለ ምልልሳችን ውስጥ ሁኔታው እንዲነሱ ዕድል የሚሰጣቸው ሌሎች ጥያቄዎች ይካተታሉ፡፡ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ ሲሆን የሚገኙት መረጃዎች በምንም መንገድ ከዚህ ዓላማ ውጪ እንደማይውሉ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ ለምታደርጉልኝ ትብብር እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

የመረጃ ሰጪ ስም ፡ ____________________
ዕድሜ ፡ ____________________
ስራ፡ ____________________
ፆታ፡ ____________________
መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ፡____________________
መረጃው የተሰበሰበበት ቀን፡ ____________________
ሃይማኖት፡ ____________________
የጋብቻ ሁኔታ፡ ____________________
የትምህርት ሁኔታ፡ ____________________
በአካባቢው የኖሩበት ዓመት፡ ____________________

1. አዝማሪ ምንድን ነው?
2. ወሎ ውስጥ የአዝማሪ መንደሮች የት የት እንዳሉ ያውቃሉ?
3. አዝማሪዎች ለምን በተለየ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ይመስለዎታል?
4. አንተና ቤተሰቦችህ ከአዝማሪ ቤተሰቦች ጋር በምን በምን ሁኔታዎች ትገናኛላችሁ?
5. እዚህ አካባቢ የሚኖሩ አዝማሪዎች ወሎዬ የሚያስብላቸው ባህርይ ምንድን ነው?
6. አዝማሪዎች ከሌላው ሰው የተለየ ባህል አላቸው ብለው ያስባሉ?
7. አዝማሪዎች ዘፋኞች የሆኑት በምን ምክንያት ነው?
8. በድሮውና በአሁኑ ዘመን የአዝማሪዎች የዘፈን ክወና ልዩነት አለ? ካለ ቢገልፁልኝ?

## ሐ. ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ›› በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት አዝማሪዎች ካልሆኑ ሰዎች በተጠኝ ቡድን ውይይት መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

### ጠቅላላ መመሪያ፡-

ውድ መረጃ ሰጪዎች በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ቀረቡ ጥያቄዎች ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ›› በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ‹‹ነገርን ነገር ያነሳዋል›› እንዲሉ በውይይታችን ውስጥ ሁኔታው እንዲነሱ ዕድል የሚሰጣቸው ሌሎች ጥያቄዎች ይካተታሉ፡፡ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ ሲሆን የሚገኙት መረጃዎች በምንም መንገድ ከዚህ ዓላማ ውጪ እንደማይውሉ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ ለምታደርጉልኝ ትብብር እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

### አዝማሪ ላልሆኑ መረጃ አቀባዮች የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች

1. እናንተ ከአዝማሪዎች ጋር ምን ግንኙነት አላችሁ? መቼ መቼ ትገናኛላችሁ?
2. ድሮ ግን አዝማሪዎች እዚህ መጥተው ሲዘፍኑ ምን ይከፈላቸው ነበር?
3. ልጅ ስትድሩ ትጠሯቸዋላችሁ ወይስ ራሳቸው ይመጣሉ?
4. አሁንስ እንዴት ነው ክፍያ የሚከፈላቸው ተተምኖ ነው?
5. የድሮዎቹ ጨዋታውን መተው አይፈልጉም?
6. አዝማሪ ድሮ፣ ከመዝፈን ሌላ ምን ተግባር አለው?
7. አዝማሪ ራሱ ደግሶ ይጋባል?

### ለአዛውንት አዝማሪዎች የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች

1. አዝማሪ ዘሩ የት መጣ ይባላል?
2. አዝማሪዎች የሚኖሩባቸው መንደሮች የት የት ይገኛሉ?
3. ልጆቻችሁን መሰንቆ እያስተማራችሁ ነው?
4. ልጆቻችሁ ለሙያው ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው
5. መሰንቆ የሚጫወቱ ልጆቻችሁ ለባህሉ ምን ያህል ይገዛሉ
6. በጥንቱና በአሁኑ የመሰንቆ አጨዋወት ምን ልዩነት አለ?
7. የድሮ ሰዎች ምን እያሉ ይዘፍኑ ኑረዋል?

## ለወጣት አዝማሪዎች የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች

1. ስለ አዝማሪ አመጣጥ የሚባለው ነገር ምንድን ነው?
2. በትምህርት ቤት የምታገኟቸው ጓደኞቻችሁ ስለእናንተ ምን አመለካከት አላቸው?
3. በድሮውና በአሁን የመሰንቆ ጨዋታ ልዩነት አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. የቀደምት አባቶችን ጨዋታ መጫወት ትችላላችሁ ወይ?
5. ወላጆቻችሁ መሰንቆ ሲጫወቱ ምን ይሰማችኋል?
6. ሙያውን ለመማር ምን ያህል ፍላጎት አላችሁ?

## ለሴት አዝማሪዎች የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች

1. አዝማሪ ሴት ገድ ናት ይላል ይባላል። ይህ ነገር እንዴት ነው?
2. ሴቶች መሰንቆ የማይጫወቱ ለምንድን ነው?
3. ሴቶች ብቻቸውን ለዘፈን ስራ አይወጡም ወይ?
4. ሴት አዝማሪ ከወንድ ጋር ስራ ስትወጣ ዋና ተግባሯ ምንድን ነው?
5. ከጊዜ አንፃር ሲታሰብ ሴቶች በየትኛው ዘመን ነው በአዝማሪነታቸው የገፉበት?

## መ. ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ›› በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት የአዝማሪዎችን የዘር ሃረግ ለመጠየቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

### ጠቅላላ መመሪያ:-

ውድ መረጃ ሰጪዎች በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ቀረቡ ጥያቄዎች ‹‹ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ ውስጥ›› በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት ማሟያ የሚሆን መረጃ ለማግኘት ሲባል የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ በተለይ በየመንደሮችን የሚኖሩ አዝማሪዎች የዘር ሃረግ ቆጠራ እንዲያደርጉ ይጠይቃሉ፡፡ በመሆኑም መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ መሆኑንና በምንም መንገድ ከዚህ ዓላማ ውጪ እንደማይውሉ ተገንዝባችሁ መረጃዎችን ያለምንም ማቅማማት እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ለምታደርጉልኝ ትብብር እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

### የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች

የመረጃ ሰጪ ስም : ____________________
ዕድሜ : ____________________
ስራ: ____________________
ፆታ: ____________________
መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ:____________________
መረጃው የተሰበሰበበት ቀን: ____________________
ሃይማኖት: ____________________
የጋብቻ ሁኔታ: ____________________
የትምህርት ሁኔታ: ____________________
በአካባቢው የኖሩት ዓመት: ____________________

1. ለምን ያህል ጊዜ በአካባቢው ኖረዋል?
2. ቤተሰቦችዎ እንዴት አዝማሪ ሊሆን ቻሉ?
3. ወደፊትም ሆነ ወደ ኋላ በሚደረግ የዘር ሃረግ ቆጠራ አዝማሪ ያልሆነ ሰው በቤተሰቦችዎ ሃረግ ውስጥ አለ?
4. በእናትም ሆነ በአባት በኩል እስከ ስንት ቤት የዘር ሃረግ መቁጠር ይችላሉ?
5. በሌሎች መንደሮች ውስጥ ከሚኖሩ አዝማሪዎች ጋር ዝምድና አላችሁ? ካለ ዝምድናው ምን አይነት ነው?
6. የአዝማሪዎች የጋብቻ ልምድ ከሌላው ማህበረሰብ ይለያልን?
7. አዝማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ጋር መጋባት የጀመሩት መቼ እንደሆነ ያስታውሳሉ

## አባሪ ሶስት፡- ቃል ታሪክ (ከአንድ መረጃ አቀባይ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ)

የመረጃ ሰጪ ስም ፡ አቶ አራጌ ይማም

ዕድሜ ፡- ሰባ ሁለት

ስራ፡ አዝማሪነት

መረጃው የተሰበሰበበት፡ቦታ ደሴ ከተማ ወሎ ባህል አምባ አዳራሽ

መረጃው የተሰበሰበበት ቀን፡6/4/2005 ዓ.ም

መረጃው የተሰበሰበበት ሰዓት፡ ከረፋዱ አራት እስከ ቀኑ ሰባት ተኩል ሰዓት

መረጃ ሰብሳቢ፡ አስቴር ሙሉ

ርዕሰ ጉዳይ ፡- የህይወት ታሪክ፤የወሎ አዝማሪዎች አጠቃላይ ገፅታ

ስምዎት ማን ይባላል?

አራጌ ይማም

ዕድሜዎት ምን ያህል ነው?

ሰባ ሁለት

የመተዳደሪያ ስራዎት ምንድን ነው?

ተጫዋች ነኝ፡፡ ቀድሞ በወሎ ላሊበላ ኪነት ውስጥ መሰንቆ እጫወት ነበር፡፡ ኪነቱ ከፈረሰ በኋላ ግን አልፎ አልፎ በሚኖር ዝግጅትና ደግሞ በምሽት ቤቶች እሰራለሁ እንጅ ብዙ ጊዜ አልሰራም፡፡

መሰንቆ ጨዋታን እንዴት ለመዱት?

መነሻዬ ከጉዳት፣ከብሶት የተነሳ ነው፡፡ በዘሬ ተጫዋች የለም፡፡ እኔ ብቻ ነኝ ተጫዋች አንዳንድ አዝማሪዎች ሲመጡ ሳይ ደስ ስለሚለኝ ደግሞ ሲሰሩ ኑረው ሲመጡ፣ እንዲያው ለብሰው ሲመጡ፣ሻል ያሉ ሆነው ሲመጡ የእከሌ እረኛ ነበር፣ የእገሌ ገበሬ ነበር ይባላል፡፡ እኔ ከሰው ቤት ተቀጥሬ ከብት አግዳለሁ፡፡ ያንግዜ በቃ ማሲንቆ የቆርቆሮ ማሲንቆ ቁልቋል እንጨት ወትፈን በዚያች ነው የለመድሁት፡፡

ቆርቆሮዋ ይህች ከታች ያለችው ናት? (የመሰንቆውን የድምፅ ሳጥኑን እየጠቆምሁ)

አወ ቆዳው ያለበት ቦታ ነው ቆርቆሮ የሚሆነው፡፡ ከዚያች ላይ ችራ አድርጌ በጣም ትጣፍጣለች ጨዋታዋ፡፡ድምፅዋ በጣም ደስ ትላለች፡፡ በዚያች ለመድሁኝ ከዚያ ከሰው ቤት እንዳለሁኝ ጌታዬ በጣም ጥሩ ሰው ነበሩ፡፡ ማታ ማታ አጫውተኝ አራጌ አጫውተኝ ይላሉ፡፡ የልጅ ልጃቸውም አራጌ ይባላል እሱ እግራቸውን ያሻል፡፡ እኔ በትራሳቸው ሆኜ ያቺን መሰንቆ እመታለሁ፡፡ መሰንቆ ስመታላቸው በጣም ደስ ይላቸዋል፡፡ ለእኛ እርጎውን ምኑን ምኑን ይሰጡናል፣ያቺን ስል በቃ ለመድሁኝ በጣም፡፡ እንዴያው ደህና ከዚያ በኋላ ጎረምሶች አዋጥተው መሰንቆ ገዙልኝ፡፡ ከዚያ ከበግ ነጋዴዎች ጋር ተከትዬ በእግሬ በጅሩ በአህያ ፈጅ ወረኢሉ ጃማ ነው ሃገሬ ተከትዬ አዲስ አበባ ገባሁ፡፡ በ51 ዓ.ም. ከዚያ እንጫወታለን፡፡ ስል እንዲያው ሰው ይወደኝ ጀመር፡፡ ሰላ በይ የሚባል ዘፈን የዚያን ጊዜ ነበር የመጣ፡፡ እሱን እየዘፈንሁ . . .

ዘፈኑ እንዴት ነው?

ሰላ ሰላ በይ ሰላ በይ ሰላ አሁን ያን ዜማ በምጫወትበት ጊዜ ድምፄ ቀጭን ነው፡፡ልጅ ነኝ፡፡ ደስ እላለሁ፡፡ ሰው ሁሉ ይወደኝ ጀመር፡፡ አራጌ የሚለኝ የለም፡፡ ሰላ በይ ነይ ነው፡፡ እንዲያ እያልሁ አዲስ አዲስ አበባ መጫወት ጀመርሁ፡፡

አዲስ አበባ የት ነበር የሚጫወቱት?

መጠጥ ቤት፡፡ 53 ላይ መንግስቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግስት እንቅስቃሴ ሲያደርግ የነበርሁበት አካባቢ ለገሃር ነበር፡፡ ወታደሮቹ ተበተኑ፡፡ ሲበተኑ እኔም ተከትዬ ጅማ ሄድሁኝ፡፡ እዚያም መጣ ተባልሁ፡፡ ያጅቡኝ ጀመር፡፡ ሰፈሩ ቆጭ ይባላል፡፡ እዚያ ስንል 54 አካባቢ እቴጌ ሞቱ ተባለ፡፡ ሃዘን ሆነ፡፡ ተመልሼ ወደ ሃገሬ መጣሁ፡፡ እቴጌ ሞተው ሃዘን በመሆኑ በሬዴዬ የሚተላለፈው ሃዘን ነው እንጅ ዘፈን የለም፡፡ አዝማሪ ሚባል ወዴት መጥቶ የሚሰራ ነገር የለም፡፡ እንግዲህ አገሬ መጣሁ፡፡ የአንድ የአራት አመት አበል ተቀበልሁኝ፡፡ እሱን ይዤ ወደ ሃገሬ ደሴ መጣሁኝ፡፡ ወዲያው ደግሞ ልጃቸው ሳህለ ስላሴ ሞተ፡፡ የእሳቸው ሃዘን ለቀቅ ሲል ደግሞ እሱ የሞተ ጊዜ አይ ሃዘናችንን አንስተናል፡፡ ቀጥሉ በየስራችሁ ፈቅደናል ተብሎ በሬዴዮ ተነገረ፡፡ ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ ሄድሁ፡፡

አሁንስ በትራንስፖርት ነው?

አወ የዚያን ጊዜ 5 ብር ነው ከደሴ አዲስ አበባ በትራንስፖርት ሄድሁ፡፡ ወዲያው ከወታደሮች በመቶ ሰባ ብር አርሞሪካ ገዛሁ፡፡ ያን ጊዜ መቶ ሰባ ብር ማለት በጣም ብዙ ብር ነው፡፡ ገዛሁዋት፡፡ ማንም ሰው አላስለመደኝም፡፡ እራሴ እዛ ማሞ ካቻ ግቢ አካባቢ ትልቅ ባህርዛፍ ግቢ ቦታ አለ፡፡ እዚያ ተማሪዎች የሚያጠኑበት ነው፡፡ ተወዲያ ወህኒ ቤቱ አለ፡፡ ተወዲህ ማሞ ካቻ ጋራዥ አለ፡፡ ባህር ዛፍ ምሪት ነው፡፡
የት ነው አካባቢው?
ገነት ሆቴል አካባቢ፡፡ ማሞ ካቻ ጋራዡን አታውቂውም መሰል?
አላውቀውም፡፡
ፖፑላሬ ይባላል፡፡ ከዚያ ሁለት ቢራዬን እይዝና እሄዳለሁ፡፡ ዝም ብዬ እዘፍናለሁ፡፡ ተማሪዎች ይመጣሉ ዝፈኑልኝ እላቸዋለሁ፡፡ ይዘፍኑልኛል እኔ የእነሱን ድምፅ እየተከተልሁ እመታለሁ፡፡ እንዲህ ስል በወር ከአስራ አምስት ቀኔ ቻልሁ፡፡ ከዚያ መሰንቆውን ትቼ አኮርዲወን መጫወት ጀመርሁ፡፡ ከዚያ ደንበኛን ገንዘብ ጨምሪልኝ ስላት በዚያው በመሰንቆ ዋጋ እንጅ አዲስ አልከፍልህም አለችኝ፡፡ ትቺያት ወለጋ፡፡

ያኔ ተቀጥረው ነበር የሚሰሩ ማለት ነው?

አሃ አወ፡፡ ቅዳሜና እሁድ ሶስት ብር፣ በአዘቦት ሁለት ብር፡፡ ሽልማት የራሴ ነው፣መጠጥ ሰው ከጋበዘኝ ጋበዘኝ ካልጋበዘኝ በእስዋ ነው፡፡ ከዚያ አልከፍልም ያለች ጊዜ ትቺያት ወለጋ፡፡ ነቀምት አንድ ወር ተቀመጥሁና፣ ጊምቢ፡፡
ቋንቋውስ?
አማርኛ ነው፡፡
ይሰማሉ ማለት ነው?

አወ የእኛው ሰው አለ፡፡ እነሱም ቢሆን እንዲያውም የእኛውን አማርኛውን ጨዋታ ይፈልጋሉ፡፡ የእነሱ ኦሮምኛ ጨዋታ እያለ የእኛውን ነው የሚፈልጉት፡፡ እንደዛ ስል፡፡ ጊምቢ ጥሩ ወርቅ ዳውድ የምትባል ነበረች፡፡ አዲስ አበባ ነው የማውቃት፡፡ ትዳር የላትም፡፡ እስዋን አገባሁ፡፡ እስዋም ትዘፍናለች፡፡ ከእስዋ ጋር ስንል . . . .
እስዋ አዝማሪ ናት?

ትዘፍናለች፡፡ ዘርዋ አዝማሪ አይደለም፡፡ ዝም ብላ የገባች ናት፡፡ ከእስዋ ጋር ስንዘፍን ቆይተን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን፡፡ አልሆን አለ፡፡ ተመለስንና ወደ ጅማ አጋሮ ሄድን፡፡ ትንሽ ካሰባሰብን በኋላ በዚያን ጊዜ ኑሮ እርካሽ ነው፡፡ እራሱ መንግስት ሳይቀር ሽጉጥ መያዝ ይፈቅዳል፡፡ ሽጉጥ ሳይቀር ገዛን፡፡ ለእኔ ሽጉጥ፣ለእስዋም ወርቅ ገዛንና ወደ አዲስ አበባ መጣን፡፡ ከዚያ አዲስ አበባ መጥተን በምን እንጣላለን በባቄላ አሹቅ፡፡

እንዴት?

እኔ ያም የሆነ ጊዜ ንፍሮ እወዳለሁ፡፡ ወይም አሹቅ ባቄላ እስዋ ደግሞ እኔ የሰራሁት አልጥምህ ብሎ ነው ንቀሽኝ ነው ወይ ትላለች፡፡ በዚህ የተነሳ አልፈልግህም አለች፡፡ እኔም አልፈልግሽም አልሁና ትቺያት ደሴ፡፡ እዚያው አዲስ አበባ ትቺያት መጣሁ፡፡ ከዚያ ወደ ደሴ መጣች፡፡ እንዲያው ብትመጣም፣ ብንታረቅም አልስማማም አልን፡፡ በኋላ እስዋም መዝፈኑን ተወችና መጠጥ ቤት ከፈተች፡፡ በኋላ ደህና ስትኖር ስትኖር ሞተች፡፡ እኔ ተመስገን ይኸው አለሁ ፡፡ ልጆች ወልጀ፤ ሌላ ሚስት አግብቼ ኑሮዬን አስተካክዬ እኖራለሁ፡፡

የላሊበላው ቅጥርስ እንዴት ነው?

የላሊበላው ቅጥር መጀመሪያ መነሻው የወሎ ሃገር ባህል ተጫዋቾች ማህበር ነበር፡፡ ብዛታቸው ወደ 97 ነበር፡፡ የዛን ጊዜ እኔ እንደአባል ነበርሁ፡፡ በሙያ እረዳቸው ነበር እንጂ የማህበሩ አባል አልነበርሁም፡፡ በውጭ አስተባብራቸው ነበር እንጂ ሰርግ ሲሄዱ ሰርግ አልሄድም ነበር፡፡ በቅጥር፣ ሂሳቤን ከከፈሉኝ እሄዳለሁ፡፡ አለዚያ ከአባላቱ ጋር አልሄድም ነበር፡፡ ያቺው መጠጥ ቤት ኩንትራት አለችን ማታ ማታ በሁለት ሰዓት እገባለሁ፡፡ በአምስት ሰዓት እወጣለሁ፡፡ የሚከፈለው ይከፈለኛል ያቺን ይዤ ወደ ቤቴ እገባለሁ፡፡ እነሱ ሰርግ ቤት ሄደው እንዳይጣሉ አስተባብራለሁ፡፡ እኛ ደግሞ እዚሁ እንዳለን አሰልጣኝ ፈለግን እኔ፣ በዛብህ፣ ተፈራ አያሌው ሶስታችን አዲስ አበባ ሄድን፡፡ ጠየቅን፡፡ ይሰጣችኋል ተባልን፡፡ ያን ጊዜ የባህል ሚኒስትሩ ተወካይ ኢዩኤል ዩሃንስ ነበሩ፡፡ በመጨረሻ ምን ሆነ? እዚህ መጥተን ስንጠባበቅ ቀለም ወርቅ ተላከ፡፡ ከዚያ ቀለም ወርቅ መጥቶ ተጫዋቾች ሲገመገሙ ብዙዎቹ ወደቁ፡፡ አልቻሉም፡፡ አስራ ስምንት የምንሆን ሰዎች ስንቀር ሌሎች ተበተኑ፡፡ አሁንም መሰንቆ የምመራ እኔ ነኝ፡፡ የተቀረው መሰንቆ ከበደም አለ የማሪቱ ባል፡፡ አሰፋ ለገሰም ነበር፡፡ ማሲንቆ ይመታሉ፡፡

ስንል ከወጣቶች ከዚህ ከቀበሌው መውጣጣት ጀመሩ ፀሃይ ካሳ፣ ፀሃይ አማረ፣ዙሪያሽ አብዩ እ . . . ዘነብ ገብረ ዮሃንስ፣ ዘነበች እሸቴ፣ ጥጋብ በለጠ፣ ሙሉጌታ አድነው፣መስፍን ደምሴ፣ ሙሉነት አድነው፣ ዚነት ሙሃባው፣ እነዚህ እነዚህ ወጣቶች ከየቀበሌው መጡ፡፡ ከወጣቶች ጋር ስንል ታዋቂነት መጣ፡፡ ልጆችም ደግሞ በቃ ዜማ ከአፍ ከአፍ ሆነ የሚነጥቁ ወዲያው ለቀም ያደርጋሉ፣ሞራል ይሰጣሉ፡፡ ደሞዝ እስከዚህም አይደለ፡፡ ስንል ትንሽ ደሞዝ መሰጠት ተጀመረ፡፡ ሽልማት ይጠራቀማል፡፡ ያንን እንካፈላለን፡፡ ስንል አቶ ቀለም ወርቅ ዜማ ይደርሳል፡፡ ፈጣን ነው ባቡሩ የሚለውን ዘፈን ደረሰ፡፡ አውቶብስ ለማግኘት ቻልን፡፡ በቃ በጣም ታዋቂ ነበርን አብዮት የወለደው ነበር የምንባል፡፡ ቀድሞ ከመኪና ስንወርድ ሊሽከሙን ነው የሚደርሱ፡፡ ስንል ሰማንያ ሶስት፣ በቋሚነት አልተያዝን ፈረሰ፡፡ ከዚያ ወዲህ ምንም የለ ስራውን ትቼው ኖርሁ፡፡ አሁን ደግሞ ትንሽ ትንሽ ጭላንጭል ሲያሳዩን (ከፅህፈትቤት እንዲሁም ከሰዎች እንደተገኘው መረጃ የደሴ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈትቤት አንዳንድ ዝግጅቶች ሲኖሩ የቀድሞ የላሊበላ ኪነት አባላት በሚል አቶ አራጌ፡- በመሰንቆ፤አቶ አሰፋ ለገሰ፡- በአኮርዲወን፣ አቶ ጫኔ ወርቅነህ፣በዋሽንት ሙዚቃ እንዲያቀርቡ ማድረግ ጀምሯል፣የባህል ቡድኑም እንደገና ሊመሰረት ሂደት ላይ ነው) ማሲንቆውን አነሳሁት እንጅ ስራውን ትቼው ነው የኖርሁ፡፡

ታዲያ ምን ሲሰሩ ኖሩ?

ምንም! ብቻ አንድ ሰሞን ለአንድ ለሶስት አራት ዓመት ወደ ወረኢሉና ማጀቴ የምትባል ገጠር ሄጀ ስሰራ ቆየሁ፡፡ ከዚያ ተመልሼ ከቤቴ ቁጭ አልሁ፡፡ ትንሽ የቤት ኪራይ አገኛለሁ፡፡ በእርሷ እንተዳደራለን፡፡ አሁን ደግሞ እናንቀሳቅሳችኋለን ሲሉ ጀመርሁ፡፡ ይህንን ይመስላል፡፡

ግን የመጀመሪያውን የወሎ ተጫዋቾችን ማህበር ለማቋቋም እንዴት ሃሳቡ መጣ?

ይህንን ጉዳይ አሁን ደሴ ሙዚየም የሚሰራ ተፈራ አያሌው የሚባል ሰው አለ እሱን ብትጠይቂው በጣም ያስረዳሻል፡፡ እሱ ብዙ ውስጣዊ ታሪክ ያለው ሰው ነው፡፡ እነሱ ናቸው ይህንን መጀመሪያ ያቋቋሙት፡፡ ሲያቋቁሙ እኔም አብሬያቸው ሆንሁ፡፡ እነሱ ማህበሩን ያቋቁሙ እንጅ ሙያው ብዙም የላቸውም፡፡ ስለዚህ አሁን እነሱ ደግሞ ይህንን አቋመው የትም መበተን የለባቸውም ተብሎ ወደ ተለያዩ መስሪያ ቤቶች ወሰዷቸው፡፡ እንደዚሁ ሽንብራ ካሳ የምትባል አሁን ፍርድ ቤት የምትሰራ አለች እሷ ተወዛዥም ድምፃዊም ነበረች፡፡ አልሆነላትም፡፡ ወደ ፅዳት ወሰዷት፡፡

እሷም አዝማሪ ኖራለች?

አወ!

እዚህ የወረዳው ፍርድ ቤት ነው ያለች፡፡ ሽንብራ ትባላለች፡፡ እና እንዲህ እያደረግን ስንሰራ ቆየን፡፡ እነዚህ በሙያው አነስ ያሉት በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ተሰገሰጉ፡፡ በፅዳት፣በዘበኝነት በአስተናባሪነት፡፡ የተቀረነው ጥቂቶች እየሰራን እየሰራን ቆየን፡፡ እነዚህ ከየቀበሌው የተሰባሰቡት ወጣቶች ገነቡት፡፡ ከዚያም ላሊበላ ተብሎ ሲሰራ ቆየ፡፡ ሌላ ደግሞ ትናንት ጋሽ ጫኔ ነግሮኛል፡፡ ግን የተለዩ ነገር እንዳለው እንዲሁም ይሰፋ እንደሁ ለማየት ፈልጌ ነው፡፡ ወሎንና ቅኝቶችን ምን ያገናኛቸዋል? ቅኝቶች
የወሎ ለመሆናቸው ምን ማስረጃ አለ?

እንግዲህ ይኸ ለእኛም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው እንጅ እኛ የፈለሰፍነው አይደለም፡፡ ለምሳሌ ባቲ፣ አንቺሆዬ እንደ አንቺ አሮ አይነት ቅኝት አካሌ ውቤን የምንጫወትበት አንቺ ሆዬ ነው ቅኝቱ፣ ትዝታ ደግሞ በፊት ወሎ ነበር የሚባለው፣

ኧረ ደሴ ደሴ <u>ገራዶ ገራዶ</u> (2)
አለቀልሽ ልቤ ተንዶ ተንዶ
ተይ ምነው መቻል ምን ይከፋል
ሆድ ካገር ይሰፋል

} በዜማ ( በትዝታ ቅኝት)

የሚለው ቅኝት ዛሬ ተሻሽሎ ትዝታ ይባል እንጅ ወሎ ነበር ስሙ፡፡ ሌላ ደግሞ አምባሰል የሚባል ቅኝት አለ፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ እንጅ ማን እንደፈለሰፋቸው አይታወቅም፡፡ በሃገሩ ስለሚጠራ ግን የወሎ ቅኝቶች ናቸው የሚለው <u>የሚያስሄድ</u> ይመስለኛል፡፡

ቀጥሎ ቅኝቶች ለይቶ ለማሳየት ሙዚቃ በመሰንቆ እንዲሁም አቶ ጫኔ ወርቅነህ በዋሽንት ሙዚቃ ተጫወቱ፡፡ መሰንቆውን አስቀድሞ በፅድ ሙጫ አለሰለሱና፡፡
ጅማሬው በመዲና ነው፡፡ የመዲና ቅኝቱ ትዝታ ነው፡፡ መጀመሪያ ባቲን ተጫወቱ፡፡ ጨዋታው ሲያልቅ አመስግኜና መርቂ ልወጣ ስል የእኔ ምርቃት አንድ ታሪክ ስላስታወሳቸው እሱን ነገሩኝ (ን)

አንድ ረሺድ በላቸው የሚባሉ ትልቅ ሰው ነበሩ፡፡ እኒህ ሰውዬ አዝማሪ ናቸው፤እንዳንድ ጊዜም ይናገራሉ (ትንቢት)፡፡ እና እኒህ ሰው ልጃቸውም መሰንቆ ለመደና ልጅወት አዝማሪ ሆነ ተብሎ ሲነገራቸው ብልሹ በለው አሉ፡፡ ስማቸው ረሺድ ብልሹ ተባለ፡፡ ረሺድ በላቸው የሚለው ቀረና ስማቸው ረሺድ ብልሹ ሆነ፡፡ ታዲያ ይህ ልጃቸው ከሚስቱ ጋር ሆኖ እሳቸው በቆሙበት ሰርግ ይቆማል፡፡ የእሱ ድምፅ መቼም ድንቅ ነው፡፡ እሳቸው ግን ያው በትልቅ ሰውነት ይሸለማሉ እንጂ እስከዚህም አልነበሩም፡፡ እና ይህ ልጅ እየዘፈነ ሽልማታቸውን እየወሰደ አስቸገራቸው፡፡ እሳቸው በጣም አዘኑበት፡፡ ልጄ ዘፈንህ ይሰማልህ፤ገንዘብ አታግኝ ብለው ረገሙት፡፡ አሁን እሱ ይዘፍናል፤ ድምፁ ያምራል፡፡ ሲሰራ መቼም ድምፁ ሌላ ነው፡፡ ግን ገንዘብ አያገኝ፡፡ ሰርግ ሲሰራ ውሎ ከእኛ ነው ገንዘብ የሚለምን፡፡ እኔን ግን መርቀውኛል፡፡ ሰርግ እሰራለሁ፤ ያልተጠራሁበት ሰርግ ግን አልሄድም፡፡ ካልጠሩኝ እንደማንኛውም ሰው ሄጄ በልቼ ገንዘቤን ከፍዬ እመጣለሁ፤ ቀጥረውኝ ስሄድ ግን እሰራለሁ እግዚአብሔር ይመስገን አገኛለሁ፡፡ እና ምርቃን ጥሩ ነው፡፡ አሁን ሂጅና ተፈራን አግኘው፡፡

# አባሪ አራት፡ -  ፎቶ ግራፎች[51]




ከአንድ አዝማሪና ከአንድ የሃይማኖት መሪ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ፣ማርዬ ስላሴ




ከአንድ አዝማሪና ከአንድ ዋሽንት ተጫዋች ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ፣ደሴ(ወሎ ባህል አምባ አዳራሽ ግቢ)

ከግራ ወደ ቀኝ አጥኝዋ፣ጫኔ ወርቅ፣አራጌ ይማም

[51]ሁሉም ፎቶ ግራፎች የተነሱ በአጥኝዋ ነው፡፡




አጥኝዋ ከመንደሯ ነዋሪ ህፃናትና ወጣቶች ጋር፣ቀለባስ መድሃኒያለም



በአባቱ መሰንቆ የሚጫወት ህፃን፣ ኢላዳ(በረከት)



የተጠኝ ቡድን ውይይት፣ኢላዳ (በረከት)




ከአዛውንት አዝማሪ ጋር ቃለምልልስ ሲደረግ፣ደረቅ ወይራ

ከግራ ወደ ቀኝ አጥኝዋ፣አሰጉ ሰኢድ፣መላኩ መድፉ



የተጠኝ ቡድን ውይይት፣ደረቅ ወይራ

ከግራ ወደ ቀኝ አሰፋ ለገሰ፣መላኩ መድፉ፣ደምሴ ቀማው፣ሰኢድ ኢብራሂም፣አጥኝዋ




ከሴትና ወንድ አዝማሪዎች ጋር ውይይት ሲካሄድ፣ ደረቅ ወይራ

ከግራ ወደ ቀኝ ዘሪቱ ከበደ፣መላኩ መድፉ፣አሰፋ ለገሰ፣አጥኝዋ፣ፈንታዬ ሞላ




ደምሴ አበበ፣ጢሳ አባ ሊማ(አምባሰል)




አጥኚዋ፣ በታዋቂዋ የባህል ዘፈን ተጫዋች ማሪቱ ለገሰ ታላቅ ወንድም በአቶ ፈንታው ለገሰ ቤት ውስጥ፣ ከድጆ

ከግራ ወደ ቀኝ አሰፋ ለገሰ፣አጠኚዋ፣ፈንታው ለገሰ፣የልጅ ልጃቸውና ባለቤታቸው




አጥኝዋ ከሴት አዝማሪ ጋር፣ ውጫሌ (አምባሰል)

ከግራ ወደ ቀኝ አለም ፀሃይ ፣የማና አጠኝዋ

## አባሪ አምስት፡- ቃልግጥም

ክበር ተመስገን የእኛ ጌታ
ከጠዋት አንስቶ እስከማታ፡፡

ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
አመስጋኝማ ሰው ቢኖር፡፡

የልጃገረድ አውታታ
ካውራ መንገድ ላይ ተኝታ
ተነሽ ቢሏት ምነው
ይኸ ሁሉ አለማፈር ነው

የድሮ አባቶቻችን ዋና
ላይ በላይ ነበር በጤና
የዛሬ ልጆች ይበልጣሉ
ውስጥ ለውስጥ ይሄዳሉ፡፡

ከሰማይ ሰማያት ወርደህ
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
አንተንም አሙህ እንደሰው
ምንና ምን ብለው

ኧረ ባቲ ባቲ ባቲ ገንደልዩ
ትዝታው ይመጣል ተሸፋፍነው ሲኙ

ኧረ ደሴ ደሴ ውድመን ውድመን
እህል እየበሉ ሰው ወዶ መመንመን

አዝማሪ ቤት መጥቶ መሳቅ መጫወት ነው
ስብሰባ ከሆነ እዚያው ፓርላማ ነው

እኔ ተቀምጬ ታናሼ እያገባ
ትንሹም ትልቁም ይለኛል አባባ

እንደባቲ መንገድ እንደገንዳላዩ
ሃድራው የሚመጣው ደራርበው ሲተኙ

እናቴንማ ወላጄን
አርግዣታለሁ ፈንታዬን
እንዴያው በሆዴ ትጉላላለች
የራብ ቀን ትሆናለች፡፡

ዋድላ ደላንታ ሙክት
አልሰባም አለ ቢያርዱት
እንደኛ አገር ጠቦት

ጭቅቅት ነው ጭቀቅቅት ነው ቀሚስ ያለቤቱ
አሽከሮቹ  እያሉ ጌተቶቹ በቀቱ

አቆርቋዥ መንግስት ዳግመኛ አይነሳ፣
አድሃሪው መንግስት ዳግመኛ አይነሳ
ውጭጨ አስር ሳንቲም ግብሩ አንድ ብር ካምሳ

ፊርማና ወረቀት ቀሪ ነው ተቀዳጅ
መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ

ጠላት በጨለማ ምን ይለኝ ብለህ
አደራ ፈጣሪ ቀን እንዳይጥልህ

የሚዳቋ  ግልገል ትበላለች ለምለም
ሚስጥር አትንገሩ የሚታመን የለም፡፡

ጥርሴማ ዝም ብሎ መሳቁን ይስቃል፡
ወደጀን ጠላቴን ልቦናዬ ያውቃል፡፡

እግዚአብሔር ከሰራው ከፈጠረው አለም
ካለስምምነት ደስ የሚያሰኝ የለም
ሃብታም እንደ እግዚአብሔር ቢኖረው መብት
ደሀን ይለው ነበር በእኔ ፈንታ ሙት

የአንባሰል ልጅና የጣት ወርቅ አንድ ነው
ከእጅ ካመለጠ ፈላጊው ብዙ ነው

ውሸቴን ነው እንጂ እንዲያው ትግደረደር
እኔ ለአምባሰል ልጅ ውሃ ሽጩ ልደር

ብርህን ወሰድሁት እየጣፈጠኝ
እባክህ ወንድሜ ስምህን  አውሰኝ

ከተማ ጥሩ ነው ጣዕሙን ላወቀው ሰው
ያገር ቤት ኑሮ ነው ሳምባዬን ያጨሰው

ተዋዶ ተዋዶ ካልወለዱ ልጅ
እንደመንገደኛ ደህና ዋል ነው እንጅ

ጠላቶችህ ሁሉ ሲገፉ ሲገፉ
የብረት ምሰሶ አርገውህ አረፉ

አንቺ የቆላ ሰው የእንጨት ስም አታውቂ
ይኸ ሰው ወይራ ነው ከእንግዲህ እወቂ

ጠጅ እጠጣ ነበር ከወር አንድ ቀን
ከነጠላው ቀረ ወይ ደሃ መሆን

መሄድ መሄድ አለኝ መንኮልኮል መንኮልኮል
አፌ ባይናገር ሆዴ ይሗል ተንኮል

አንተ እና እኔ እንብላ ሁለታችንን
ሌላው ጦሙን ይደር እጎዳ እንደሆን

# አባሪ ስድስት፡- የድጋፍ መጠየቂያ ደብዳቤዎች


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮ ሚዩኒኬሽን
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት
☎ +251-11-123-98-00 Ext. 127
+251-11-123-97-02
✉ 1176

Humanities, Lang. Studies, Journalism & Com
Department of Amharic Lang. Lite. & Folklore
E-mail: dtell@ils.aau.edu.et
http://www.aau.edu.et/index.php/ethiopian-languages-and-literature


ቀን፡- ኅዳር 10 ቀን 2005 ዓ.ም.
ቁጥር፡- ቋጥፋ/አክት/052/2005

ለሰሜን ወሎ ዞን ጽ/ቤት

ወልዲያ

ጉዳዩ፡- **ወ/ሮ አስቴር ሙሉ በዞናችሁ ለሚያደርጉት የፒኤችዲ ጥናት የትብብር ጥያቄን ይመለከታል**፡፡

ወ/ሮ አስቴር ሙሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በፎክሎር (የባህል ጥናት) የፒኤችዲ ተማሪ ናቸው፤ ወ/ሮ አስቴር «የወሎ አዝማሪዎች ታሪክ፣ የዘፈናቸው ጥቅምና ማኅበራዊ አውድ» በሚል ርዕስ ጥናታቸውን ለማድረግ ያቀረቡትን ትልመ ጥናት (PROPOSAL) በአጥጋቢ አልፈዋል፡፡ ጥናቱ ሲጠናቀቅ ለክልሉም ሆነ ለሀገር የባህልንና የልማትን ቁርኝት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ስለታመነበት ዋናውን የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን በዞናችሁ እንዲያደርጉ ክፍለ ትምህርቱ ወስኗል፡፡

በመሆኑም ከኅዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ በዞናችሁ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚቆዩ አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉላቸው እየጠየቅን ለሚደረገላቸው ትብብር በቅድሚያ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ደረጀ ገብሬ (ረ/ፕ)የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት ሊቀመንበር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮ ሚዩኒኬሽን
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት
☎ +251-11-123-98-00 Ext. 127
+251-11-123-97-02
✉ 1176

Humanities, Lang. Studies, Journalism & Com
Department of Amharic Lang. Lite. & Folklore
E-mail: dtell@ils.aau.edu.et
http://www.aau.edu.et/index.php/ethiopian-languages-and-literature

ቀን፡- ኅዳር 10 ቀን 2005 ዓ.ም.
ቁጥር፡- ቋጥፋ/አክት/051/2005

ለደቡብ ወሎ ዞን ጽ/ቤት

ደሴ

ጉዳዩ፡- **ወ/ሮ አስቴር ሙሉ በዞናችሁ ለሚያደርጉት የፒኤችዲ ጥናት የትብብር ጥያቄን ይመለከታል።**

ወ/ሮ አስቴር ሙሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በፎክሎር (የባህል ጥናት) የፒኤችዲ ተማሪ ናቸው፤ ወ/ሮ አስቴር «የወሎ አዝማሪዎች ታሪክ፣ የዘፈናቸው ጥቅምና ማኅበራዊ አውድ» በሚል ርዕስ ጥናታቸውን ለማድረግ ያቀረቡትን ትልመ ጥናት (PROPOSAL) በአጥ.ጋቢ. አልፈዋል። ጥናቱ ሲጠናቀቅ ለክልሉም ሆነ ለሀገር የባህልንና የልማትን ቁርኝት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ስለታመነበት ዋናውን የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን በዞናችሁ እንዲያደርጉ ክፍለ ትምህርቱ ወስኗል።

በመሆኑም ከኅዳር 17 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ በዞናችሁ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚቆዩ አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉላቸው እየጠየቅን ለሚደረገላቸው ትብብር በቅድሚያ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ከሰላምታ ጋር

ደረጀ ገብሬ (ረ/ፕ)የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት ሊቀመንበር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርክ ልማት ቢሮ
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
CULTURE, TOURISM & PARKS DEVEL BUREAU
BAHIR DAR

ቁጥር ባቱ5/ኦ-1/57/05
No-
ቀን 09 /04/ 2005ዓ.ም
Date

**ለሰሜን ወሎ ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት መምሪያ**

ወልዲያ

ጉዳዩ፡- **ትብብር ስለመጠየቅ**

ወ/ሮ አስቴር ሙሉ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር ፕሮግራም ባልደረባ ስሆን አሁን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪዩዋን እየተማረች መሆኑን ገልፃ ‹‹የወሎ አዝማሪዎች ታሪክ የዘፈናቸው ጥቅምና ማህበራዊ አውድ ›› በሚል ርዕስ ምርምር በማድረግ ላይ ስለሆነች ቢሯችን አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን እንዲያደርግላት ጠይቃለች፡፡

ቢሮውም የጥናት ርዕሷን በመመልከት ጥናቱ ቢደረግ ሊያበረክት የሚችለውን አካዳሚያዊ፣ማህበራዊ፣ባህላዊና ታሪካዊ ጠቀሜታ አምኖበታል፡፡ ስለዚህም ተጥኝዋ ጥናቱን ለማካሄድ በዞናችሁ የምትገኝ በመሆኑ ለምታደርጉላት ትብብር ከወዲሁ እያመሰገንን ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መጓጓዣ፣ መንገድ መሪ፣የድጋፍ ደብዳቤዎችን መጻፍ የመሳሰሉ ጉዳዮችን ድጋፍ ታደርጉላት ዘንድ የተለመደ ትብብራችሁን እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር !

ዋጋው ኃይሉ
የባህል እሴቶችና ተዛማጅ ጥናት ልማትና አጠቃቀም የሥራ ሂደት መሪ

+251 058 220 11 33
222 10 50
220 22 04
220 11 32

"ቱሪዝም ባህልን ያስተሳስራል!"

P.O.box 1616
Fax +251 058 220 26 50 /22 18 34
E-mail: amhtour@telecom.net.et
WWW.amharatours.org.et/tourism

ተያቢ መ.ወ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርክ ልማት ቢሮ
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
CULTURE, TOURISM & PARKS DEVEL. BUREAU
BAHIR DAR

ቁጥር - ባቱፓ/አ-1/0143/04
Ref. No
ቀን - 25/08/2004ዓ.ም
Date

ለደቡብ ወሎ ባህልና ቱሪዝም ቅ/ጽ/ቤት

ደሴ፣

ለሰሜን ወሎ ባህልና ቱሪዝም ቅ/ጽ/ቤት

ላሊበላ፣

ጉዳዩ፡- ትብብር እንዲደረግ

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባልደረባ የሆኑት ወ/ሮ አስቴር ሙሉ በወሎ አዝማሪዎች የሙዚቃ ጥበባቸው አነሳስና እድገት ላይ ጥናት እያደረጉ መሆኑን ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ24/08/04ዓ.ም በቁጥር 48/1727/04 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆ እንቅስቃሴ በሚያደርጉባቸው አካባቢዎች አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው ተጠይቀናል።

ጥናቱ የክልላችን ባህልና የህብረተሰባችንን ነባር ትውፊቶች ለማወቅና ለመጠበቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስለአለው አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው እየጠየቅን በሚደረግላቸው ትብብር እናመሰግናለን።

" ከሠላምታ ጋር "

ዋጋው ኃይሉ መሸሻ
የባህል እሴቶችና ቱሪዝም ጥናት
ልማትና አጠቃቀም የሥራ
ሂደት መሪ

ግልባጭ

- ለወ/ሮ አስቴር ሙሉ

  በአሉበት፣

+251 058 220 11 33
222 10 50
220 22 04
220 11 32

"ቱሪዝም ባህልን ያስተሳስራል!"

P.O.box 1616
Fax +251 058 220 26 50 /22 18 34
E-mail: amhtour@telecom.net.et
WWW.amharatours.org.et/tourism

ተያቢ መ.ወ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
የደቡብ ወሎ ዞን
ባህልና ቱሪዝም መምሪያ

Amhara National Regional State
South Wollo
Culture &Tourism Department

ቁጥር፡ ባቱ-1-20/464

ቀን፡ 17/05/2005

ለ መግዲ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት

ለ ለጋምቦ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት

ለ ለገሂዳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት

ለ ወረኢሉ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት

በያሉበት፤

**ጉዳዩ ፡- ትብበርን ይመለከታል፣**

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት እጩ ዶክተር አስቴር ሙሉ ለ 3ኛ ዲግሪያቸው የማሟያ ጽሁፍ ለማዘጋጀት እንዲችሉ ለሥራ ወደ ወረዳችሁ ተንቀሳቅሠዋል፡፡

ስለሆነም ለአጥኝዋ ማንኛውንምና አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ታደርጉላቸው ዘንድ እናሳስባለን፡፡

"ከሠላምታ ጋር"

ሙሉጌታ ገብረእግዚአብሄር
የባህል እሴቶችና ተ/ጥ/ ልማትና አጠቃቀም የሥራ ሂደት ባለቤት

*ግልባጭ*

- ለ ወ/ሮ አስቴር ሙሉ

  ባሉበት

033 119 08 11
033 811 90 16
Email: swctb@ethionet.et
Fax: 033 112 51 27
1474
« ቱሪዝም ባህልን ያስተሳስራል "
" Tourism፡ connecting cultures"